

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
ድኅረ ምረቃ ፕሮግራም

የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ወሽባክ

በአገኘሁ ተስፋ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2006 ዓ.ም

ABABA UNIV
LIBRARIES
P. O. BOX
ABABA



አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ድኅረ ምረቃ ፕሮግራም

የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ወሽባክ

በአገኘሁ ተስፋ

የጥናቱ አማካሪ

ዶክተር ተሾመ ደምሴ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

‹‹የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ወሽባክ›› በሚል ርዕስ ለተግባራዊ ስነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በአገኘሁ ተስፋ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን ጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል።

የፈታኝ ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ፡- ተሾመ ደምሴ (ፒኤችዲ)

ፊርማ..... ቀን..20 June 2014

የውጭ ፈታኝ፡- ስዩም ተሾመ (ፒኤችዲ)

ፊርማ..... ቀን..13/10/2006

የውስጥ ፈታኝ፡- ታዬ ረጋሳ (ፒኤችዲ)

ፊርማ..... ቀን..20 June 2014

ማረጋገጫ (Declaration)

የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና ወሸባክ፤ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፣ በሂማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት በተግባራዊ ሥነ-ልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ጥናት ከዚህ በፊት በሌላ አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን እንዲሁም የተጠቀምኩባቸው ጽሑፎች በትክክል ዋቢ የተደረጉና አዲስ አበባ ዩንቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም አገኘሁ ተስፋ ፊርማ _____ ቀን 14/08/06

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

አህጽሮተ ጥናት (ABSTRACT)

የጥናቱ ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተናን ወሽባክ ለማጥናት ነው። ይህን ዓላማ ለማሳካት የተመረጠው የምርምር ንድፍ አይነት ደግሞ ቅይጥ (mixed) ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች በጥናቱ የተካተቱት፣ በአማራ ክልል በሚገኙ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ በእድል ሰጪ ንሞና ዘዴ የተመረጡ 303 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ በጠቅላይ የንምና ዘዴ የተመረጡ 89 የአማርኛ መምህራን፣ በዓላማ ተኮር ንምና ዘዴ የተመረጡ የፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች፣ የዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤቶችና የዞን ትምህርት መምሪያዎች ኃላፊዎች ናቸው። ከእነዚህ ተሳታፊዎች መጠናዊ መረጃዎች በተማሪዎችና በመምህራን በተሞሉ የጽሑፍ መጠይቆችና በተደራጀ የክፍል ምልከታ፣ ዓይነታዊ የሆኑት ከ25 መምህራንና ከ12 የዞን የትምህርት ኃላፊዎች በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች፣ እንዲሁም በከፊል-በተደራጁ ቃለ መጠይቆች፤ ከዘጠኝ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የአማርኛ መምህራን፣ ከአራት የፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች፤ ከሰነዶች ደግሞ ከመርሐ ትምህርቶች፣ እ.አ.አ. ከ2000-2004 ዓ.ም ከተዘጋጁት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች፣ እ.አ.አ. በ2004 እና በ2005 ዓ.ም ከተዘጋጁት የክፍል ፈተናዎችና ከፖሊሲ ሰነዶች ተሰብስበዋል። በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎችም ዓይነታዊ የሆኑት በጭብጠቻቸው መሰረት በተለያዩ ክፍሎች እየተመደቡ፣ መጠናዊ የሆኑት በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ (በቁጥር፣ በመቶኛ፣ በአማካይ፣ በተዛምዶና በህብረ-ድህረት ዘዴዎች ተተንትነዋል።

የጥናቱ ግኝቶች እንዳመለከቱት አንደኛ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና በአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች፣ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና በቋንቋው ትምህርት ዓላማዎች፣ በቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችና በክፍል ፈተናዎች መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ የለም። ሁለተኛ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን፣ በተማሪዎችና ሌሎች የትምህርት ባለድርሻ አካላት ግንዛቤና ተግባራት ላይ በአብዛኛው ጠንካራ የሚባል ተፅዕኖ እያሳደረ ነው። ይህም ተጽዕኖ የመማር-ማስተማር ሂደቶቹ ፈተና ተኮር እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። በፈተናው ጫና የሚደርስባቸው ዋና ዋና የትምህርት ምድቦችም የትምህርቱ ተግባራት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ የትምህርቱ ይዘቶችና የክፍል ምዘናዎች ናቸው። ይህም የቋንቋው ትምህርት፣ ሥርዓተ ትምህርቱ በተመሰረተበት ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት ፍልስፍናና መርሆዎች እንዳይመራና የትምህርቱ ዋነኛ ጉዳይ የሆኑት የቋንቋው ክሂሎች ችላ እንዲባሉ እያደረገ ነው። ለእንደዚህ ያሉ የወሽባክ ገፅታዎች መከሰትም በጥናቱ የተመረመሩት አብዛኞቹ የወሽባክ መከሰቻ ምክንያቶች (ለምሳሌ መምህራን ስለማስተማር ሙያና ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ፣ በፈተናው ስለሚካተቱ ይዘቶች ያላቸው ዕውቂያ፣ የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በመምህራን ላይ የሚያሳድረው ጫና፣ የጊዜው ማነስ ወዘተ.) ላቅ ያለ በአብዛኛውም አሉታዊ የሆነ አስተዋፅዖ እንዳበረከቱ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። በጥናቱ የተገኙት አሉታዊ የወሽባክ ገጽታዎች የትምህርት ሥርዓቱን በሚመሩ ወገኖች የማስተካካያ ርምጃ እየተወሰደባቸው አለመሆኑን ብቻ ሳይሆን እየተበረታቱም እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ከእነዚህ የጥናቱ ግኝቶች ላይ በመመስረትም በባለድርሻ አካላት ሊከናወኑ የሚገባቸው የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል።

ምስጋና

በመጀመሪያ ትምህርቴን እንድጀምር በጓደኛዬ አስረደው አማካኝነት ላነሳሳኝ፣ ከዚያም ሰላምን፣ ጤናንና ብርታት ሰጥቶ የተጀምረው ከዚህ እንደደርስ ለረዳኝ አምላኬ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ቀጥዬ ከሁለተኛ ዲግሪዬ ጀምረው ለአማከሩኝ ለዶክተር ተሾመ ደምሴ ላቅ ያለ ምስጋና አቀርበለሁ፡፡ ከጥናቱ መጀመሪያ ጀምረው ጠቃሚና ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በማስተካከል፡ ጥናቱ ከወቅት ጋር የተያያዘ መሆኑን በመረዳት የማህበራዊ ኑሮ ግንኙነቶች በሚበዙበት በጥር ወር ቅዳሜና ዕሁድ ሳይቀር ቅድሚያ ሰጥተው በማረም፣ በማስተካከል ጥናቱ ተገቢ አቅጣጫ እንዲይዝልኝ አግዘውኛል፤ ጠቃሚ አስተያየቶች ሰጥተውኛል፤ አበረታተውኛል፡፡ በማንኛውም ቦታ ሆነ በስልክ ለምጠይቃቸው ጥያቄዎች በቀጠሮም፣ ያለ ቀጠሮም በቢሯቸው እየተገኘሁ እንዲያማክሩኝ በማነሳቸው ጉዳዮች ላይ ሁሉ ተገቢ የማከር አገልግሎት ሰጥተውኛል፣ ልምዳቸውን አካፍለውኛል፤ ከትልመ ጥናቱ ጀምረው ዋናው ጥናት አስከሚጠናቀቅ በየደረጃው የጥናቱን እያንዳንዱን ምዕራፍ በማንበብና አማራጭ አቅጣጫዎች በማሳየት ተገቢ አቅጣጫ አሲዘውልኛል፡፡ ከዋናው ጥናት ጎን ለጎንም ለሰሚናር የሚሆኑ የጥናት ወረቀተችን እየጻፍኩ እንድለማመድም ረድተውኛል፡፡ በእሳቸው ድጋፍና ማበረታትም የዋና ጥናት ወረቀት እዚህ ደረጃ ደርሶልኛል፡፡

የካናዳው ውድ ጓደኛዬ አስረደው ዘውዱ እንድማር በማበረታታትና በጥናቱ የተጠቀምኩባቸውን አብዛኛዎቹን መጻሕፍትና አርቲክሎች ገዝቶ በመላክ፣ ደክተር ማረው ዓለሙ፣ ዶክተር አረጋ ኃ/ሚካኤል፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመገምገምና፣ የጥናቱን ረቂቅ የመጀመሪያ አራት ምዕራፎች አንብቦ ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠት፣ አቶ አምባው ደምሴና ተሻገር አማረ እንዲሁ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመገምገምና የጥናቱን የተወሰኑ ክፍሎች አንብቦ አስተያየት በመስጠት ስለተባበሩኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በጥናቱ የጽሑፍ መጠይቅ በመሙላት፣ በቡድን ውይይቶችና በቃለ መጠይቆች በመሳተፍ ለተባበሩኝ በደሴ፣ደብረ ብርሃን፣ ባህር ዳርና ጎንደር ዙን ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ 20 አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራን እንዲሁም የጽሑፍ መጠይቅ በመሙላት ለተሳተፉት በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ይማሩ ለነበሩት ተማሪዎች፣ በቡድን ተኮር ውይይቶች ለተሳተፉት የዞን የትምህርት ባለሙያዎች፣ በቃለ መጠይቆች ለተሳተፉት የፈተናዎች ኤጀንሲ ጎላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች፣ የፈተናውን ጥያቄዎች ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር በማዛመድ ለተባበሩኝ የጎንደር መምህራን ኮሌጅ የሥነ-ትምህርትና የአማርኛ መምህራንና መረጃ በመሰብሰብ ላገዙኝ ለደሴው ጋሽ ደመቀ ሙሉጌታ፤ ለደብረ ብርሀኑ ዘውዱ ናሁሰናይ፣ ለባህር ዳሩ ጋሻው በላይና ለጎንደሩ ዓለማየሁ ጸጋዬ፤ ረቂቁን በኮምፒውተር ለጻፈችልኝ ወ/ት ቅድስት የሽጥላ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በቀርቡ በትምህርት ላይ እያለሁ በሞት የተለየኝ አባቴ መላኩ መዊዕ/ ቀኝጌታ ተስፋ ተሰማ ከልጅነት እስከተለየን ቀን ድረስ ልጆቹን ለማሳደግና አስተምሮ ለቁም ነገር ለማብቃት ሲከፍልልን የኖረው መስዋዕትነት /ያደረገልን ውለታ ሲታወሰኝ የሚኖር ነው፡፡ እናቴ ወይዘሮ ትበይን በላይ በአዲስ አበባ ቆይታዬ የምኖርበት ቤት በማመቻቸት ወንድሞቼና እህቶቼ ቁሳቁሶችን በማሟላትና መ.ያዊ ድጋፍ በመስጠት ድጋፍ አደርገውልኛል፡፡ ባለቤት ወይዘሮ ሻሼ ዘውዱ፤ ልጆቼ ኤርምያስ፣ በረከትና እጹብ አገኘሁ እንዲሁ በቃላት የማይገለጽ ድጋፍ ያደረጉልኝ ባለውለታዎቼ ናቸው፡፡

አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲና ጎንደር ዩንቨርሲቲ ለምርምሩ ስራ የሚያግዘኝ የንዘብ ድጋፍ አድረገውልኛል፡፡ እህቴ ያይኔ ተሰፋ ገና ትምህርት እንደጀመርኩ (ኋላ የደረገችልኝ ድጋፊ ሳይጨመር) 80ሺ ብር ልካልኛለች፤ ስለዚህ ለእነዚህ ተቋማትና ለእህቴ ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

A Study of Washback: The Ethiopian General Secondary Education Certificate Amharic Examination in Focus

PhD Thesis

Submitted in Fulfillment of the Requirement of the Degree of Doctor of Philosophy in Applied Linguistics and Ethiopian Languages Teaching

By: Agegnehu Tesfa

Supervisor: Associate Professor Teshme Demisse (PhD)

Summary of the study

Different scholars both from the field of general education and language testing (for example Ebel 1979; Grounlund 1986, Alderson 1999, 2004, Dauglas 2010, Dejene 1990, Henning 1987, Taylor 2005, Teshome 1995) discuss that teaching and learning are so closely interrelated in educational process. They are inseparable as the two sides of a coin. Alderson (1999[2]) added that "[3]it is impossible to imagine teaching without assessing how well learners are doing."

Tests are also considered as powerful measurement of the teaching and learning practices (Douglas 2010 and Henning 1987). In many countries, they are considered as the means of controlling the standard of achievement in education. They have also been seen as a means of certification of achievement in education, and as ways to upgrade knowledge and to improve the performance of institutions (Shohamy 2001).

All the above expressions show the relationship between teaching and testing and the power of tests on the teaching and learning processes. That is why Alderson and Wall (1993□115) state that "Tests are held to be powerful determiners of what happens in the classroom." Similarly, Madaus (1988:83) states that "[3]it is testing[4] not the official stated curriculum that is increasingly determining what is taught, how it is taught, what is learned and how it is learned."

In applied linguistics, washback/the influence of test on language teaching and learning has numerous definitions. However, most of them (for example Alderson and Wall 1993, Chang and Curts 2004) agree with the definition that washback is the influence of testing on teaching and learning. Similarly Hughes (2003:1) defines it as "[3]the effect of testing on teaching and learning."

The effect of a test on teaching and learning processes can be either positive or negative (harmful), strong or weak, general or specific, intended or unintended (Watanabe 2004).

The scope of washback is also divided into two: its effect at micro/classroom level and at macro level/outside the classroom (Watanabe 2004, Bachman and Palmer 1996). Accordingly, the effect of a test on teachers and students is known as micro level. On the other hand, its effect on other stakeholders, such as on parents, school principals/administrators, educational authorities at different levels and policy makers is called macro level effect of a test(Watanabe2004).

This suggest that the influences of tests do not take place solely in the classroom, their consequences are also educational, social and political (Messick 1989).

Due to this, researchers recommend that a washback study incorporates both micro and macro levels. In line with this, Bachman and Palmer (1996:208) write: "...when exploring the broad phenomenon of washback both micro effects in the classroom and macro effect on the educational systems and society at large have to be examined." However, if we wish to know whether an examination can bring about changes in classroom teaching and learning, since that is where most teacher-student interaction occurs, we must first examine the influence of the test on teachers and students (Cheng 2005 and Wall 2005).

Based on these ideas, this study examined both the micro and macro effects of the Ethiopian General Secondary Education Certificate Amharic Examination.

To investigate the washback of Ethiopian General Secondary Education Certificate Amharic Examination, the researcher developed a washback model based on the Bailey (1996) and Green (2007) washback models. Bailey has developed a washback model by combining Alderson and Wall's (1993) 15 washback hypotheses (which are also considered as washback theory) and Hughes' (1993) framework. The model has three components: participants, processes and products. All these components might be affected by the nature of a test (Bailey 1999). Among these three components, as Bailey (1999) and Green (2007) explain the washback studies focus on the first two parts. Regarding this Green (2007:69) states that "...washback studies can broadly be divided into those focusing on perceptions and those concerned with actions."

According to this model, participants are language learners, teachers, Administrators and the like "...whose perceptions and attitudes toward their work may be affected by a test" (Green 2007:26). On the other hand, the term process refers to "any actions taken by the participants who may contribute to the process of learning" Hughes (1993:2) as cited in Bailey (1999).

When Green (2007:26) explains about participants and processes in the context of washback study, he states that "[3]washback will occur to participants, affecting their attitudes towards their work, participants' attitudes will affect processes, including both what participants do, how they do it."

This shows clearly that a test affects participants' perceptions towards their work first and then it affects their work positively or negatively.

According to Green (2007: 69), among these two main components of washback, "[3]the area of participant perceptions has long been a cornerstone of washback studies." Nevertheless, many scholars from applied linguistics like Alderson and Wall (1993), Watanabe (1997, 2004), Chen (2002) and Cheng (2005) suggest that washback studies will focus on both participants` perceptions and their actions. That is why this study gives attention for both participants` perceptions and Practices.

In the context of language teaching, a great body of research has noted that national/public examinations may influence teacher's perceptions of their teaching particularly in six domains or dimensions. These are lesson planning or syllabus design, contents of the subject, classroom activities, teaching materials, teaching methods and classroom assessment (Chen 2002).

Different teachers and context related factors or characteristics were reported by empirical studies to affect the degree of washback on teaching. Among these, teacher-related factors/characteristics are considered as the major factors. Teachers` characteristics consist of teaching experience (Alderson and Hamp-lyons 1996, Watanabe 1997), teachers` training processes or levels of professional training (Wall and Alderson 1993, Watanabe 1997), teachers' perceptions of test importance (Shohamy et al 1996), teachers' awareness of the test format and content (Alderson and Wall 1993, Chen 2002), teachers' commitment to the teaching profession (Wall and Alderson 1993). Contextual factors/ characteristics also include students learning attitudes (Alderson and Wall 1993, Chen 2002), the timing of the course that is offered (Shohany et.al 1996), and the variation of students' abilities in the class (Hawkey 2006), the size of the class (Alderson and Hamp-lyons 1996).

This study has examined all these factors in the context of Ethiopia as independent variables.

In addition to the perceptions and practices of the participants and factors that affect the perceptions and practices of the participants, the study has also investigated the relationships between the examination and the objectives of cognitive domain and the syllabi of the language.

Based on the above brief review of related literature and theoretical framework/ model, the researcher formulated the following research questions in order to facilitate the investigation of the washback of the Amharic National Examination.

1. What strategies does the National Assessment and Examination Agency use to improve the National Examinations positive washback?
2. Does the Amharic national examination overlap with the objectives of
   - The cognitive domain?
   - The secondary education Amharic syllabi?
3. How do the secondary schools Amharic teachers' perceive the impact of the Amharic national examination?

Under this broad question, the following sub-questions are formulated.

3.1 What are the teachers' perceptions of the impact of Amharic national examination on their lesson planning and instruction in relation to basic teaching domains (teaching contents, activities, materials, methods and assessment)? (Dependent variable)

3.2 What are the factors/intervening variables that influence the teachers` perceptions of the impact of the Amharic national examination on their lesson planning and instruction? (Independent variables)

3.3 What are the relationships among teacher's characteristics and teachers' perceptions on the impact of the examination /the dependent variable?

3.4 What are the relationships among the contextual variables and teachers' perceptions on the impact of the examination?

3.5 What are the intervening variables of each of the teacher characteristics that influenced the dependent variable?

4. What are the perceptions of students on the impact of the Amharic national examination?
5. What are the influences of the Amharic national examination on teaching and learning practices?
6. What are the Secondary National Examinations impacts on macro level educational parties?
7. What elements of positive washback are encouraged by the examination?
8. What elements of negative washback are encouraged by the examination?

The main objective of this study was to discover the washback of the Ethiopian General Secondary Education Certificate Amharic Examination. From this main objective, the following specific objectives are driven.

1. Identify the basic strategies the National Examination Agency uses to improve the positive washback of their examinations.
2. Assess the relationships between:
    - The objectives of cognitive domain and the Amharic national examination.
    - The objectives of secondary school Amharic syllabi and the examination.
3. Explore how the Amharic teachers perceive the impact of Amharic national examination on their planning and instruction.
4. Investigate students' perceptions about the influences of the Amharic national examination on the teaching and learning processes.
5. Explore the impact of the examination on the teaching and learning practices in the context of Amhara National Regional State.
6. Explore the impact of the secondary education national examinations on different levels of educational authorities and experts.
7. Identify the positive elements encouraged by the Amharic national examination.
8. Indicate the negative elements encouraged by the exam.

In order to answer the above research questions, the present research employed mixed method research approach. Hence, sufficient and relevant data were collected from different sources by using both quantitative and qualitative methods. Accordingly, quantitative data were collected using structured observations and questionnaires. Qualitative data were also collected by using semi-structured interviews, focus group discussions and document analysis. Their reliability and validity were checked through reviewers and pilot study.

In order to generate data, different participants were selected randomly and purposively. Accordingly, 89 teachers and 303 grade 10 students filled in the survey questionnaires. This was aimed at exploring their perceptions on the impact of the exam and the factors which may affect their perceptions. To see and explore the impact of the exam on the teaching and learning practices, structured classroom observation was conducted. 95 lessons were observed in two months and 15 days time. In addition, in order to understand the problem in-depth and examine

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA

both micro and macro levels washback of the exam, focus group discussions were made with 25 teachers who were teaching from five different schools and 12 education authorities from four different zones . Finally, in order to investigate the macro effects of the examinations and the intended washback, semi-structured interviews were made with six school principals, two authorities and two experts of the agency.

To see how the exam overlap/match with the objectives of the cognitive domain and the syllabi of the language and how it influenced the teaching and learning processes, five years Amharic national exams (2000-2004 E.C) papers and two years teacher made test (2004 and 2005 E.C) papers were also collected and analyzed.

The qualitative data were analyzed by using the following steps.

- Descriptive statistics were used to organize and summarize the data and to answer research questions 3.1 and 3.2.
- Vibrate correlation analysis was used to determine the direction , magnitude and significance levels of the relationships among each of the independent variables and the dependent variable (teachers' perceptions on the impact of the exam)
- Multiple regression analysis using a hierarchical entry and standard entry stages examined the relationships among the independent variables and the dependent variable.

Whereas the data collected through focus group discussions, semi-structured interviews and document analysis were organized thematically and then analyzed qualitatively. Discussions were made integrating the findings of both the qualitative and quantitative data analyses to answer the posed research questions.

The major findings of these analyses are the following:

1. The National Assessment and Examination Agency has been employing different strategies which are related to hiring experts (for exam preparations), selecting item writers, providing intensive training (for experts), giving motivating feedback for the heads of education bureaux of regional states .

2. There is no positive relation/overlap between:

   - Objectives of the cognitive domain and the exam.
   - Objectives of the syllabi and the exam.

Especially, the central parts of cognitive categories such as application, analysis, synthesis and evaluation and the language skills, particularly writing, speaking and listening skills were not represented in the exam in line with the policy documents and the secondary school Amharic syllabi. For instance, the higher order intellectual levels of this cognitive domain parts (application, analysis, synthesis and evaluation) were represented by less than 10% items. On the other hand, knowledge and comprehension from the cognitive domain and grammar, vocabulary, the concept of literary concepts were represented in the exam by more than 90% and 60% items consecutively. These findings show clearly that there are mismatches between the cognitive domain and the exam and the syllabi and the exam. This implies that the national Amharic exam encourages more negative washback than positive.

3. The general secondary school Amharic teachers perceived that the national exam has a strong effect on teaching contents, activities, materials and teacher made tests, and a moderate effect on planning stage and teaching methods. This shows teachers perceived that the teaching domains are affected by the national exam.
4. From the main independent variables/teachers' characteristics, teachers' attitude to the teaching profession, teaching experience, teachers' perceived importance of the national exam, and from contextual characteristics: perceived students learning attitudes, the timing of the course that is offered, the variation of students' abilities in the class were found factors which were affect teachers perceptions of the impact of the exam strongly.
5. Concerning the correlation and multiple regression analysis the major findings were the following:

   - A positive, significant ($p < 0.001$) and strong relation was found between teachers' perceptions on the impact of the national exam/dependent variable and teachers' attitude to the teaching profession.
   - A positive, significant ($p<0.001$) and moderate relation existed among the dependent variable (teachers' perceptions of the exam) and the following main independent variables: Teachers' perceived awareness of the format and content of the national exam,

teachers' perceived importance of the exam and teachers' perceived students' learning attitudes.

- A negative, insignificant ($p>0.5$) and weak relationship was seen among the dependent variables (teachers' perceptions of the impact of the national exam) and the following independent variables: teachers` educational background, teachers' participations in service training, the timing of the course that is offered.
- When the set of independent variable was added, the proportion of variance in dependent variable explained by the independent variable was 44% which was statistically significant.
- Teachers' attitude to the teaching profession, teachers' perceived awareness of the test format and content, teachers` perceived importance of the exam and teachers' perceived students' learning attitudes contributed significantly and moderately to the regression. That is the four independent variables contributed significantly to explain the variance of the teachers' perceptions of the impact of the Amharic national exam on teachers' planning and instruction.

6. The analysis of students' response for the questionnaire shows that, students perceived that the Amharic language national exam had a strong impact on the learning and teaching processes/practices of the language.
7. The analysis of the classroom observations and semi-structured interviews held with teachers after the observations indicate the following results:
   - Almost all classes spent most of the time in whole class activities with the teacher addressing the class. In other words, classes or participant organization was not student-centered as indicated in the educational policy documents.
   - In the context of the study, the common teaching methods teachers used to teach the language was lecture and student modality (preferred learning style) was listening. That is to say, though group work, pair or group discussions and individual tasks were the most preferable methods in the philosophy of constructivism and theory of communicative language learning and teaching were not encouraged. As a result classes were largely teacher-centered, and students spent more time using receptive skills than productive skills.

- The contents of the lessons were found influenced by the exam in that teachers and students focus area of teaching and learning was on form-related, not on meaning. Thus, a considerable part of the lessons were spent focusing on grammar, vocabulary, reading, technical aspects of writing, speaking and listing skills and literary concepts, When the teachers taught these lessons, they used exam related materials and the previous year's exam papers. The classroom exams were also found similar to the certificate/national exam instead of overlapping with the objectives of the education policy and the syllabi of the language.

Generally as the quantitative and qualitative data analyses show, almost all the domains of teaching were found influenced by the exam. The magnitude of the washback on teachers' and students' perceptions and practices was strong. Its direction was also negative or encourages more negative washback elements than positive.

8. The analyses of data collected from school principals, educational authorities who work at different levels of Amhara National Regional State also indicate that the Ethiopian General Secondary Education Certificate Examinations' washback did not happen only in the classroom. The influences extend to other educational parties' perceptions and practices at different levels. These influences also affect the educational parties' perceptions and practices strongly and negatively.

Based upon the findings of this study, the following recommendations are suggested for the different educational stakeholders in the context of the study.

- Make reformations in the examination that would encourage teachers and students to practice communicative activities in line with the objectives of the cognitive domain and the syllabi of the language. This includes making formats and contents of the exam unpredictable.
- Provide teachers with professional development opportunities/in- service training which enable them to teach the language skills according to the emphasis given in the syllabi.
- Change/modify teachers' monitoring and evaluation system.

- Allot periods for the subject (Amharic) based on the federal government curriculum framework guideline.
- Develop mechanism/regulation which should enforce classroom tests which will reflect the syllabi instead of the national exam.
- Integrate[5] classroom assessment results into national exam.

ማውጫ

አህጽሮተ ጥናት (ABSTRUCT)..... i

ምስጋና ii

Summary of the Study iii

የይዘት ማውጫ xiii

የሰንጠረዥ ማውጫ xix

የምስል ማውጫ..... xxii

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ (Background of the Study)..... 1

1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር (Statement of the Problem)..... 8

1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች (Basic Research Questions)..... 12

1.4 የጥናቱ ዓላማ (Objectives of the Study)..... 14

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት(significance of the Study) 15

1.6 የጥናቱ ወሰን (Scope of the Study)..... 16

1.7. የጥናቱ ውስንነት (Limitation of the Study) 18

1.8. የቁልፍ ቃላት (ጽንሰ ሀሳቦች) አጠቃቀም ብያኔ 19

ምዕራፍ ሁለት፤ የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

2.1 መግቢያ..... 23

2.2 የጥናቱ ዐውድ (Context)፤ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኢትዮጵያ 23

2.3. የቋንቋና የአማርኛ ፈተና ታሪካዊ ዕድገት 28

2.4 በትምህርትና በፈተና መካከል ያለ ተጣጥሞሽ (Overlapping) 34

2.4.1 የአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) ክፍሎች/ችሎታዎችና የፈተና ጥያቄዎች ተጣጥሞሽ (Overlapping) 35

2.4.2 በመሰረታዊ የቋንቋ ትምህርት ምድብ (Domains) ክፍሎችና በፈተና መካከል ያለ ተጣጥሞሽ/ዝምድና (Overlap)..... 48

2.5. የወሽባክ ምንነት/ ብያኔዎች እና ታሪካዊ ዳራ 55

2..6 በወሽባክ ጫና ሊደርስባቸው የሚችሉ ጉዳዮች (Areas Affected by Washback) 60

2.7 በወሽባክ ላይ ጫና የሚያሳድሩ ምክንያቶች (Factors Affecting Washback)..... 63

2.7.1 ከመምህራን ጋር የተገናኙ/ የተያያዙ ምክንያቶች (Teacher related factors/ Teachers` Characteristics)..... 64

2.7.2 ከዐውድ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች (Context Related Factors) 68
2.8 የወሸባክ መለኪያዎች (Dimensions of Washback) 71
2.8.1 የወሸባክ ወሰን (Scope) 71
2.8.2 የወሸባክ ጥቅል/ ንጥልነት (specificity) 72
2.8.3 የወሸባክ ጥንካሬ (Intensity) 73
2.8.4 የወሸባክ አቅጣጫ/ ዓይነት (Direction/Value) 74
2.8.4.1 አሉታዊ ወሸባክ 74
2.8.4.2 አዎንታዊ ወሸባክ 76
2.9 አዎንታዊ የፈተናዎች ወሸባክን እንዴት ማዳበር ይቻላል? 76
2.10 በወሸባክ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች 80
2.11 የወሸባክ መላምቶችና ምዴሎች (Models) 86

ምዕራፍ ሦስት፤ የአጠናን ዘዴ (METHODOLOGY OF THE STUDY)
3.1 መግቢያ 94
3.2 የምርምሩ ንድፍ ዓይነት(Type of Research Design/ Study Design) 94
3.3 የምርምር ቦታና የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ 95
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች (Data Collection Instruments) 105
3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አግባብነትና አስተማማኝነት (Validity and Reliability) 118
3.5.1 ከገምጋሚ ባለሙያዎች (Reviewers) የተገኙ የአግባብነት መረጃዎች (Evidences of Validity) 119
3.5.2 ከሙከራ ጥናቶቹ የተገኙ የአግባብነትና አስተማማኝነት ማስረጃዎች 121
3.5.2.1 የሙከራ ጥናት አንድ 121
3.5.2.2. የሙከራ ጥናት ሁለት 124
3.6. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት (Data Collection Procedures) 127
3.7. የመረጃ ትንተና ሂደት (Data Analysis Procedure) 130

ምዕራፍ አራት፤ የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ
4.1 መግቢያ 136
4.2. የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ታላሚ ተፈታኞችን የመመዘን ደረጃና አዎንታዊ ወሸባክ ከፍ ለማድረግ የፈተናዎች ኤጀንሲ የሚጠቀምባቸው ስትራቴጂዎች 137

4.3 የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ከአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain)፣ ከቋንቋው መርሐ ትምህርቶች ዓላማዎች እና ከክፍል ፈተናዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት የውጤት ትንተናና ማብራሪያ 157
4.3.1 የአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) ክፍሎችና የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ተዛምዶ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 157
4.3.2 በዘጠነኛና በ10ኛ ክፍል መርሐ ትምህርቶች የተካተቱ አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማዎችና የተመደበላቸው የክፍለ ጊዜ መጠን ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 160
4.3.3 የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና የመርሐ ትምህርቶቹ ዓላማዎች ተጣጥሞሽ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 165
4.3.3.1. በባለሙያዎቹ የተካሄደ የፈተናዎቹ ጥያቄዎችና የትምህርቱ ተጣጥሞሽ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 165
4.3.3.2 የማጠናቀቂያ ፈተናውንና የትምህርቱን ተጣጥሞሽ በተመለከተ ከመምህራን ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተገኘ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 178
4.3.3.3 የክፍል ፈተናዎች ከመርሐ ትምህርቶቹ ዓላማዎችና ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 187
4.3.3.4 ተጣጥሞሽን በተመለከተ በመጠናዊና ዓይነታዊ ዘዴዎች የተካሄዱ ትንተናዎች ግኝትና ማብራሪያ 190
4.4 የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ ያላቸው ግንዛቤ 194
4.4.1. መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ ያላቸው ግንዛቤ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 195
4.4.1.1 መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በሚመለከት ስላላቸው ግንዛቤ በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 195
4.4.1.2. መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በሚመለከት ስላላቸው ግንዛቤ በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ..202

4.4.1.3 የማጠናቀቂያ ፈተናውን ተጽዕኖ በተመለከተ በዓይነታዊና መጠናዊ ዘዴዎች የተካሄዱ የውጤት ትንተናዎች ውህዳዊ ግኝትና ማብራሪያ 213
4.4.2 የወሸባክ መከሰቻ (መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ላዳበሩት ግንዛቤ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ) ምክንያቶች (Factors) ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 217
4.4.2.1 የወሸባክ መከሰቻ ምክንያቶችን በሚመለከት በጽሑፍ መጠይቅ ከመምህራን የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 218
4.4.2.2 የወሸባክ መከሰቻ ምክንያቶችን በሚመለከት በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ከመምህራን የተሰበሰበ ዓይነታዊ መረጃ ውጤት ትንተና 226
4.4.2..3 በመጠናዊና ዓይነታዊ ዘዴዎች የተተነተኑ የወሸባክ መከሰቻ ምክንያቶች ውህዳዊ ውጤትና ማብራሪያ 248
4.4.4. የተዛምዶ ትንተና (Correlation Analysis) ውጤትና ማብራሪያ 256
4.4.4.1. መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጦው) እና በመምህራን ባህርያት መካከል ያለው ተዛምዶ የውጤት ትንተናና ማብራሪያ 258
4.4.4.2 መምህራን በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤና በዐውዳዊ ባህርያት መካከል ያለው ዝምድና ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 264
4.4.5. የህብረ ድኅረት ትንተና (Multiple Regressions Analysis) እና ማብራሪያ 266
4.4.5.1 በጥገኛ ተላውጦው ላይ ተፅዕኖ በሚያደርስ ዐቢይ ተላውጦ ላይ ጣልቃ የሚገቡ ተላውጦዎች 266
4.4.5.2. በእያንዳንዱ ነጻ ተላውጦ የተገለጸው የጥገኛ ተላውጦው ልዩነት ትንተናና ማብራሪያ 271
4.5 ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ትንተናና ማብራሪያ 275
4.5.1 የጥናቱ ተሳታፊዎች ዳራና የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራንና በተማሪዎች ስለሚሰጠው ትኩረት ያላቸው ግንዛቤ 276

4.5.2 ተማሪዎች ስለማስተማሪያና መማሪያ ተግባራት፣ ቋንቋውን ስለሚማሩባቸውና ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ገጽታዎች (Aspects) ያላቸው ግንዛቤ 278
4.5.2.1 ተማሪዎች ስለማስተማሪያና መማሪያ ተግባራት (Classroom Teaching & Learning Activities) ያላቸው አመለካከት 278
4.5.2.2 ተማሪዎች በመማር ገጽታዎች ላይ ያላቸው ግንዛቤ (Perceptions of Aspects of Learning) 288
4.5.2.3 ተማሪዎች ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ገጽታዎች (Aspects) ያላቸው አመለካከት 291
4.6 የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ 296
4.6.1 የመምህራን የማስተማር ባሕርያትን (Behaviours) በሚመለከት በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 296
4.6.2. በተደራጀ የክፍል ምልከታ (Structured Observation) የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 303
4.6.3 ከክፍል ምልከታዎች በኋላ ከመምህራን ጋር በተካሄዱ ቃለ መጠይቆች የተሰበሰበ መረጃ ትንተናና ማብራሪያ 330
4.6.4 በጽሑፍ መጠይቅ፣ በተደራጀ የክፍል ምልከታና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች ውህዳዊ የውጤት ትንተናና ማብራሪያ 337
4.7 በውጫዊ (macro) የትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ስለሚያሳድሩት ተፅዕኖ ከተተኳሪ የቡድን ወይይቶችና ከሰነድ የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 340
4.8 በማጠናቀቂያ ፈተናው መርሐ ግብር ምክንያት የተበረታቱ አዎንታዊና አሉታዊ የወሸባክ አላባዎች 349

ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሄ

5.1. መግቢያ 354
5.2. ማጠቃለያ 354
5.3. መደምደሚያ 365
5.4. መፍትሄ 369
ዋቢዎች 372
አባሪዎች
አባሪ አንድ፤ በሙከራ ጥናትና በመምህራን የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ 380

አባሪ ሁለት፣ በመ/ከራ ጥናት ፩ የተካሄደ የቡድን ተኮር ውይይት መምሪያ 386
አባሪ ሦስት፤ በመ/ከራ ጥናት ፪ በመምህራን የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ 387
አባሪ አራት፡ በመ/ከራ ጥናት ፪ በተማሪዎች የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ 394
አባሪ አምስት፤ ለፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎች የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ 399
አባሪ ስድስት፣ ለፈተናዎች ኤጀንሲ የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች የተዘጋጀ ቃለመጠይቅ 401
አባሪ ሰባት፤ ለመ/ከራ ጥናት ፪ እና ለዋናው ጥናት ከመምህራን ጋር ለተካሄደ ተተኳሪ የቡድን ውይይት የተዘጋጀ መምሪያ 403
አባሪ ስምንት፣ በዋናው ጥናት በመምህራን የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ 406
አባሪ ዘጠኝ፣ በዋናው ጥናት በተማሪዎች የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ 412
አባሪ 10፣ ለምክትል/ ርዕሳነ መምህራን የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ 416
አባሪ 11፤ ከዞን የትምህርት ባለሙያዎች ጋር ለተካሄደ ቡድን ተኮር ውይይት የተዘጋጀ መምሪያ 417
አባሪ 12፤ የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት መገለጫ የምልከታ ንድፍ/ ቅጽ 418
አባሪ 13፤ የፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ምላሾች ናሙና 419
አባሪ 14፤ ተተኳሪ ቡድን ተኮር ውይይቶች የተሳተፉ መምህራን ምላሾች ናሙና 425
አባሪ15፤ የዞን ትምህርት ባለሙያዎች ምላሾች ናሙና 444
አባሪ16፤ በመምህራን የተሞላው የጽሑፍ መጠይቅ ክሮቫሽ አልፋ 447
አባሪ17፤ ተማሪዎች ቋንቋውን በክፍል ውስጥ ስለሚማሯቸው ንዑሳን የትምህርቱ ክፍሎች ያላቸው ግንዛቤ በመቶኛ ስሌት ሲታይ 448
አባሪ 18 በጥናቱ የተካተቱት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ናሙና 449
አባሪ 19፤ በጥናቱ የተካተቱት የክፍል ፈተናዎች 474

የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 4.1፣ የፈተና ጥያቄዎች ስርጭት ከአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች አንፃር ጠቅላላ ድምር በቁጥርና በመቶኛ ስሌት 158

ሰንጠረዥ 4.2፣ በ9ኛና 10ኛ ክፍል መርሐ ትምህርቶች የቀረቡ ዓላማዎችና የተመደበላቸው የክፍለ ጊዜያት መጠን 161

ሰንጠረዥ 4.3፣ ባለሙያዎች /Lecturers ከ2000-2004 ዓ.ም የተዘጋጁ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎችን ከአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ዓላማዎች ጋር በግልና በተለያዩባቸው ክፍሎች ላይ በጋራ በመወያየት ያካሄዱት የጥያቄዎች ምደባ ውሳኔ ስሌት በአማካይ 166

ሰንጠረዥ 4.4 የክፍል ፈተናዎች ከመርሐ ትምህርቶቹ ዓላማዎችና ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት በቁጥርና በአማካይ ስሌት 188

ሰንጠረዥ 4.5 የማጠናቀቂያ ፈተናው በተግባራት/ ጊዜ አደላደል ላየ የሚያሳድረው ተፅዕኖ 196

ሰንጠረዥ 4.6፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው የማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ የመምህራን ግንዛቤ 197

ሰንጠረዥ 4.7፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ የመምህራን ግንዛቤ 198

ሰንጠረዥ 4.8፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በቋንቋው ትምህርት ይዘቶች ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የመምህራን ግንዛቤ 199

ሰንጠረዥ 4.9፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በክፍል ትምህርት ምዘና ምድብ ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ የመምህራ ግንዛቤ 201

ሰንጠረዥ 4.10 መጠይቅ በመሙላት የተሳተፉ መምህራን አጠቃላይ መረጃ 218

ሰንጠረዥ 4.11፣ መምህራን ለሙያቸው ያላቸው ከበሬታ ምድብ (Domain) ውጤት 219

ሰንጠረዥ 4.12፣ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው እውቂያ/ግንዛቤ ምድብ ውጤት ስሌት በአማካይ 220

ሠንጠረዥ 4.13፣ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ውጤት ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ በአማካይ 221

ሰንጠረዥ 4.14፣ የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በመምህራን ላይ የሚፈጥረው ጫና 222

ሰንጠረዥ 4.15፣ ውጫዊ ጫናዎች በመምህራን ግንዛቤ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ 223

ሰንጠረዥ 4.16፣ ቋንቋውን ለማስተማር የተመደበው ክፍለ ጊዜ የሚፈጥረው ጫና 224
ሰንጠረዥ 4.17፣ የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ በመምህራን ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ 225
ሰንጠረዥ 4.18 መምህራን በማጠናቀቂያ ፈተና ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ ባላቸው ግንዛቤና በመምህራን ባህሪያት መካከል ያለው ተዛምዶ 259
ሰንጠረዥ 4.19፣ መምህራን ስለፈተናው ተፅዕኖ ባላቸው ግንዛቤ እና በዐቢይ ነጻ ተላውጠዎች መካከል ያለው ተዛምዶ 262
ሰንጠረዥ 4.20፣ የድህረት ውጤት ተዋረዳዊ ድኅረት ((Sequential Regression) ማጠቃለያ ሞዴል (Model Summary) 268
ሰንጠረዥ 4.21፣ የድህረት ውጤት ማጠቃለያ ሞዴል መደበኛ ድህረት (Regression Output: Model Summary (Standard Regression) 271
ሰንጠረዥ4.22፣ የመደበኛ ድህረታዊ መጣኝ (standard regression coefficient_Beta) ውጤት 273
ሰንጠረዥ 4.23፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመማር-ማስተማር ሂደቶች ስለሚሰጠው ትኩረት የተማሪዎች ግንዛቤ 276
ሰንጠረዥ 4.24፣ ተማሪዎች ስለመምህሩ የክፍል ውስጥ ንግግር መጠን ያላቸው ግንዛቤ በመቶኛ ስሌት 278
ሰንጠረዥ 4.25፣ የክፍል ውስጥ የመምህሩ ተግባራትን በተመለከተ የተማሪዎች ግንዛቤ በመቶኛ ስሌት 280
ሰንጠረዥ 4.26፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለሚማሯቸው የትምህርቱ ክፍሎች/ ተግባሮች ያላቸው ግንዛቤ በመቶኛ ስሌት 281
ሰንጠረዥ 4.28፣ ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩባቸው ተግባሮች በመቶኛ ስሌት 284
ሰንጠረዥ 4.29፣ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳባር የሚያግዟቸው ከክፍል ውጭ የሚያከናውኗቸው ተግባራት 286
ሰንጠረዥ 4.30፣ ተሳታፊዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ /አተያይ 289
ሰንጠረዥ 4.31፣ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ያላቸው መነሳሳት 290
ሰንጠረዥ 4.32፣ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር የሚመርጧቸው ስልቶች/ስትራቴጂዎች 291
ሰንጠረዥ 4.33፣ ለፈተና ለመዘጋጀት የሚያደርጉት ልምምድ በመቶኛ ስሌት 292
ሰንጠረዥ 4.34፣ በፈተና ነክ ጉዳዮች ላይ የተማሪዎች ግንዛቤ 293
ሰንጠረዥ 4.35፣ የክፍል ትምህርት ይዘት አደረጃጀት በቁጥርና በመቶኛ 298
ሰንጠረዥ 4.36፣ የትምህርት አዘገጃጀት (Lesson Preparation) በሚመለከት የመምህራን ምላሽ በቁጥርና በመቶኛ ስሌት 299

ሰንጠረዥ 4.37፣ የመምህሩ ንግግር በቁጥርና በመቶኛ 300
ሰንጠረዥ 4.38፣ የመምህሩ የማስተማር ተግባራት በቁጥርና በመቶኛ ስሌት 301
ሰንጠረዥ 4.39 ፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የከተማና የከፊል ከተማ
ት/ቤቶች የ9ኛ ክፍል ትምህርቶች የተሳታ/ አደረጃጀት 304
ሰንጠረዥ 4.40፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የገጠር 9ኛ ክፍል ት/ ቤቶች
የተሳታፊዎች አደረጃጀት 304
ሰንጠረዥ 4.41፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የከተማ፣ የከፊል ከተማና
ገጠር ት/ቤቶች የ10ኛ ክፍል ትምህርቶች የተሳታፊዎች
አደረጃጀት 305
ሰንጠረዥ 4.42፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የከተማ ት/ቤቶች የዘጠነኛ
ክፍል ትምህርቶች ይዘት 310
ሰንጠረዥ 4.43 ፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የከፊል ከተማ ትምህርት
ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት 311
ሰንጠረዥ 4.44፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የገጠር ትምህርት ቤቶች
የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት 317
ሰንጠረዥ 4.45፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የከተማና የከፊል ከተማ
ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት 319
ሰንጠረዥ 4.46፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የገጠር ት/ቤቶች የ10ኛ ክፍል
ትምህርቶች ይዘት 320
ሰንጠረዠ 4.47፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ
ክፍል ትምህርቶች ይዘት ቁጥር 324
ሰንጠረዥ 4.48፣ የከተማና ከፊል ከተማ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል
ተማሪዎች የመማሪያ ዘዴ 325
ሰንጠረዥ 4.49፣ የገጠር ት/ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመማሪያ ዘዴ 326
ሰንጠረዥ 4.50፣ የከተማ፣የከፊል ከተማና የገጠር ት/ቤቶች የ10ኛ ክፍል
ተማሪዎች የመማሪያ ዘዴ 326
ሰንጠረዥ 4.51፣ የከፊል ከተማና የገጠር ት/ቤቶች የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የመማሪያ ... 327

የምስል ማውጫ

ምስል 2.1፡ በ Bailey (1996) የቀረበ የወሸባክ ሞዴል 88
ምስል 2.2፡ የGreen የወሸባክ(ትምህርት-ፈተና) ተጣጥሞሽ (Overlapping) ሞዴል 91
ምስል 2.3፡ የትምህርት ዓላማዎችና የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ተጣጥሞሽ እና ፈተናዎች በተሳታፊዎች ግንዛቤና ተግባራት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ሞዴል (ከBaily 1996 እና Green 2007 የወሸባክ ሞዴሎች ላይ ተመስርቶ የዳበረ)..... 93

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ (Background of the Study)

ፈተና በማንኛውም ማህበራዊ ሕይወት የሚገኝና ሁሉ አቀፍ (universal) ገፅታ ያለው መሆኑ ይታወቃል፡፡ የፈተናና ምዘና ሊቃውንቱ (Grounlund 1986 እና Ebel 1979) እንደሚገልፁት፣ በተለይ በመደበኛ ትምህርት የፈተና አስፈላጊነት ላቅ ያለ ነው፡፡ የማስተማርና የፈተና ትስስር በተለያዩ ባለሙያዎች በተለይም በፈተና ኤክስፐርቶች በተደጋጋሚ ሲገለፅ የኖረው ለዚሁ ነው፡፡

ለፈተናዎች እንዲህ ያለ ክብደት መሰጠቱም ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ‹‹ፈተናዎችን ሊተካ የሚችል ትምህርታዊ የግምገማ ስልት የለም›› (Ebel 1979, 28):: Ebel (1979)፣ Alderson (1999)፣ Madaus (1998) እና ሌሎች በምዘና ላይ ምርምር የሚያካሂዱ ምሁራን እንደሚገልጹት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችንና ዘዴዎችን አዋጭነት፣ የሚማሩትን አካላት የመማር ውጤት ለመገምገምና ተገቢ ግብረ-መልስ ለመስጠት፣ ስለመማር-ማስተማር ሂደቱ አስተማማኝ መረጃ ለማግኘትና በተገኘው መረጃ መሠረት ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለመወሰን፣ የትምህርቱን አሰጣጥ የጥራት ደረጃ ለመቆጣጠር (Quality Control) ፈተናዎች የተሻሉ የመመዘኛ ስልቶች ናቸው::

በእርግጥ በመደበኛ ትምህርት ሥርዓት ለተለያየ ዓላማ የተለያዩ ፈተናዎች ይዘጋጃሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ብዙ ጊዜ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን የሚጠቀሱት የችሎታ መለኪያ (Achievement) ፈተና፣ የመምረጫ /የብቃት መለኪያ (Proficiency) ፈተና፣ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ (Diagnostic) ፈተና እና የቅድመ ችሎታ መለኪያ (Aptitude) ፈተና በመባል የሚታወቁት ናቸው (ተሾመ 1995፣ Alderson 1999፣ Hughes 2003፣ Madson 1983):: እነዚህ ፈተናዎች ከተለያየ ይዘት፣ በተለያየ መንገድ የሚዘጋጁ ስለሚሆኑ እንደሚሰጡበት ዓላማ የሚያስገኙት መረጃም ሊለያይ ይችላል፡፡ ከዚህ አስተሳሰብ በመነሳት በኢትዮጵያ የፈተናዎች ኤጀንሲ በየዓመቱ የሚዘጋጁ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ዓላማ ምን እንደሆነ መለየት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በኤጀንሲው የሚታለመውን ወሸባክ ለመረዳትም ሆነ፣ ጠቅላላ

ADAMA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1888
ADAMA, ETHIOPIA

የጥናቱን አቅጣጫ ለመወሰን የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎች በየትኛው የፈተና ዓይነት ውስጥ እንደሚመደቡ የሚመለከታቸውን በኤጀንሲው በኃላፊነትና በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያነት የሰሩና እየሰሩ ያሉ ባለሙያዎችን ለማነጋገር ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ምላሽም በኢትዮጵያ በኤጀንሲው የሚዘጋጁ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ (Achievement) ፈተናዎች እንደሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፤ (ዝርዝር ማብራሪያቸው በምዕራፍ አራት ቀርቧል)፡፡ በቋንቋ ትምህርትም ከዚህ የተለየ አተያይ የለም፡፡ በተለይ ለተግባቦታዊ የቋንቋ ችሎታ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ከተጀመረበት ከ1970ዎቹ ወዲህ ስለሁለቱ (ስለ ቋንቋ ማስተማርና ፈተና) ትስስር በብዙዎቹ የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች ሥራዎች ሳይነሳ የማይታለፍ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል፡፡ እንደምሁራኑ አተያይ ቋንቋ ማሰተማርና መፈተን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፤ አንዱ ለሌላኛው በጣም ያስፈልገዋል (ደጀኔ 1990፣ Bachman 1990፣ Harison1983፣ Heaton 1988፣ Hughes 2003፣ Madson 1983፣ McNamara 2000፣ 2004፣ Richards 1996፣ ተሾመ 1995፣ Weir 1990፣ 2005)፡፡

Alderson (1999)ም እንዲሁ፣ ፈተና የመማር ማስተማር ሂደት አካል ብቻ ሳይሆን በማስተማር-መማር ሂደት ላይ በአዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አቅጣጫ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ይገልጻሉ፡፡ ይህም ፈተና የመማር-ማስተማር ሂደት አካል ብቻ ሳይሆን አቅጣጫ አመልካች የሚሆንበት ሁኔታም እንዳለ የሚያመለክት ነው፡፡ Alderson (1999) ከዚሁ ጋር አያይዘውም ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል ዐውቀዋል ወይም በተግባር መሥራት ችለዋል? ብሎ የማይገመግም ማስተማር አለ ብሎ ማሰብ እንደማይቻል ያስረዳሉ፡፡

በትምህርትና በፈተና መካከል ያለው ትስስር ጥሩ መማርን የሚያበረታታ /አዎንታዊ መሆን አለመሆኑ የሚመረመረውም፣ በሌላ ክፍል በስፋት እንደተገለጸው፣ በዋነኝነት በወሽባክ ጥናት ነው (Watanabe 2004፣ Cheng 2005፣ Green 2007)፡፡

በጥናት መስክነትም Bachman and Cohen (1998) እንደሚገልፁት፣ በእነዚህ አንድነት እየፈጠሩ በመጡት የተግባራዊ ሥነ-ልሳን ሁለት መስኮች (የቋንቋ ትምህርትና የቋንቋ ፈተና) በተለይ ከ1980ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የሚካሄዱት

ጥናቶችና የአጠናን ዘዴዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ እየጨመሩና እድገት እያሳዩ መጥተዋል። በተለይ በተግባቦታዊ ስልት ቋንቋን ማስተማርና መፈተን ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኙ ከመጡ ወዲህ የቋንቋ ፈተና ወሽባክ ከፍተኛ ትኩረት እያገኘና የተለያዩ ምርምሮች እየተካሄዱበት ነው(Alderson 2004፣ Cheng እና Curtis 2004፣ Watanabe 2004)።

የቋንቋ ፈተናዎች ትክክለኛ መረጃዎች የሚሰጡትና በተገኙት መረጃዎች መሰረት ጠቃሚ ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚያስችሉት ግን አንደኛ አግባብነት (Validity)፣ አስተማማኝነት /Reliablity) እና ተተግባሪነት (Practicality) በመባል የሚታወቁትን የጥሩ ፈተና ባህርያት መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ ነው (Harison 1983፣ Weir 1990፣ 2005.)። ሁለተኛ በመማር-ማስተማር ሂደቶች ላይ አዎንታዊ ወሽባክ /ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሲሆኑ ነው (Bailey 1996፣ Brown 2004፣ Cheng, Curtis and Watanabe 2004፣ Hughers 2003፣ Weir 2005፣)::

አግባብነት /Valdity ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ሲሆን ጥቅል በሆነ አገላለጽ የአንድን ፈተና ወይም የፈተና ክፍሎች ትክክለኛነት የሚመለከት ነው (Alderson እና ሌሎች 1995)። አስተማማኝነት ተፈታኞች በፈተና ወቅት ከሚሰጡት መልስ ወጥነት (consistency) ጋር የተያያዘ ነው። ተተግባሪነት በቀላሉ፣ ፈተናውን ለመሥራት፣ ውጤት ለመስጠትና ለመተርጎም የሚቻል ከመሆኑና ከኢኮኖሚ ጋር የተሳሳሩ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው። እነዚህ የፈተና ባሕርያት በራሳቸው በፈተናዎቹ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው_እንደወሽባክ ፈተናዎች በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ አያካትቱም።

ከፈተናዎች ጋር ተያይዞ የሚነሳውና በተለይም ከAlderson እና Wall (1993) ጥናት ወዲህ ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ የመጣው የፈተናዎች ወሽባክ ነው። ወሽባክ በተለያዩ የመስኩ ተመራማሪዎች የተለያየ ፍቺ ሲሰጠው የነበረ ቢሆንም አሁን አሁን ይበልጥ ተቀባይነት እያገኘ የመጣው "ወሽባክ ፈተና በቋንቋ ማስተማርና መማር ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ ነው" የሚለው ብያኔ ነው (Cheng 2004 iv)። ወሽባክ እንደ አግባብነትና አስተማማኝነት ዋነኛ ትኩረቱን በራሳቸው በፈተናዎቹ ባህርያት ላይ የሚያደርግ አይደለም። ‹‹ወሽባክ በተግባራዊ ሥነ-ልሳን ትልቅ ቦታ እያገኘ የመጣ፣

ፈተና በቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ላይ የሚፈጥረውን ተፅዕኖ የሚመለከት ፅንሰ ሀሳብ ነው›› (Messick 1996፣ 241) የሚለው አገላለፅም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው። ይህ ከጠባብ (Micro) ትርጉሙ አንጻር ያለው አተያይ ነው። ከሰፊ/ ውጫዊ (Macro) ትርጉሙ አንጻር ሲታይ ደግሞ ወሽባክ ፈተና በሥርዓተ ትምህርት ቀራጮች፣ በመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች፣ በተመራማሪዎችና ሌሎች የትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ሁሉ ያካትታል (Baily 1996፣ 1999፣ Cheng 2005፣ Green 2007)።

አንደኛውን የወሽባክ ገጽታ በሚመለከት Tayler (2005) ባስረዱበት ክፍል እንደገለጹት፣ ፈተናዎች በትምህርት ሂደቶች ላይ በተለያየ መንገድ ተጽዕኖ (Influence) እንደሚያሳድሩ ከረጅም ጊዜ በፊት ጀምሮ የሚታመን ጉዳይ ነው። ይህን በሚመለከት ያለው አንዱ አተያይም መምህራን ስለፈተናው ያላቸው ዕውቀት እየጨመረ በሄደ ቁጥር የማስተማሪያ ዘዴዎቻቸው፣ የሚያስተምሯቸው ይዘቶች...፣ ፈተናው ከተማሪዎቹ የሚፈልገውን ነገር/ ችሎታ እንዲያንጸባርቁላቸው እያደረጓቸው ይመጣሉ። ዕቅዳቸውም ይህንኑ የሚያንጸባርቅ እንዲሆን ያደርጉታል። ይህም የፈተና በመምህራን ላይ ተጽዕኖ የማሳደር ሀይል ውጤት ነው(Tayler 2005)። Alderson እና Wall (1993) እንዲሁ ፈተና በመምህራንና በተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚከናወኑ አዎንታዊና አሉታዊ ነገሮች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የማሳደር ሀይል እንዳለው ሲገልጹ፤ Madaus (1988፣ 83) ደግሞ "መምህራን ምን ማስተማርና እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው፤ እንዲሁም ተማሪዎች ምን መማርና እንዴት መማር እንዳለባቸው የመወሰን አቅሙ እየጎለበተ እየመጣ ያለው መደበኛ ሥርዓተ ትምህርቱ (Official Stated Curriculum) ሳይሆን ፈተና ነው፤" ይላሉ። አበበ (1990) ይህንኑ ሐሳብ ይጋራሉ። ለምሳሌ ስለሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ቀረጻ በሚገልጸው ስራቸው በሥርዓተ ትምህርት ላይ ጫና የሚፈጥሩ ዋና ዋና ምክንያቶች ብለው ከጠቀሷቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የትምህርት ቤት መልቀቂያ/ ብሔራዊ ፈተናዎች ናቸው የሚል ማጠቃላያ ላይ ደርሰዋል። በማስረጃነትም በወቅቱ በኢትዮጵያ 12ኛ ክፍል ላይ ይሰጥ የነበረው የ፪ኛ ደረጃ ትምህርት መልቀቂያ በመባል የሚታወቀው ፈተና የሀገሪቱን ሥርዓተ ትምህርት ከታቀደው ውጭ የሆነ ቅርጽ(Shape) እንዲይዝ እንዳደረገው በማስረጃነት ጠቅሰዋል።

በAlderson (1999) ሥራ አጽንኦት ተሰጥቶት እንደቀረበውም በተለይ የፈተናው ዓይነት የችሎታ መለኪያ (Achievement)፣ የዕድገት (Progress) መለኪያና ተማሪዎችን በየደረጃቸው ለመደልደል (Placement) ከሆነ፣ ፈተናዎቹ በተቻለ መጠን ከሥርዓተ ትምህርቱና ከክፍል ትምህርቱ ጋር የሚዛመዱ ወይም የሥርዓተ ትምህርቱና የክፍል ትምህርቱ ነጸብራቅ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ችሎታን ለመለኪያ፣ ለውጥን ለመለኪያና ተማሪዎችን በችሎታቸው ለመደልደል የሚዘጋጁ ፈተናዎች ዋጋ/ አዎንታዊ ትርጉም እንዲኖራቸውም ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር እንዲጣጣሙ/ ተገቢ ተዛምዶ እንዲኖራቸው ማድረግን ይጠይቃል። ሌላው ቀርቶ የብቃት መለኪያ (Proficiency) ፈተና እንኳ ቢሆን መምህራኑ ካስተማሩት/ ተማሪዎቹ ከተማሩት ትምህርት ጋር መሰረታዊ ልዩነት (Major Mismatch) እንዳይታይበት ጥንቃቄ መደረግ አለበት (Alderson 1999)። በኢትዮጵያ ብሔራዊም ሆኑ የክፍል ፈተናዎች ከአዕምሯዊ ምድብ ስድስት ዓላማዎች/ ችሎታዎችና በየትምህርቱ ዓይነት ከተነደፉት ዓላማዎች ጋር እንዲጣጣሙ እየተደረጉ ሊዘጋጁ እንደሚጋባቸው በትምህርት ፖሊሲ ሰነዶች ውስጥ (ለምሳሌ እ.ኢ.አ. በ1986 በወጣው የትምህርትና ስልጠና ፖሊስው እና በስርዓተ ትምህርት ማስፈጸሚያ 2010) በግልጽ ሰፍሯል። በፈተናዎች ኤጀንሲም ብሔራዊ ፈተናዎቹ የሚዘጋጁት በብሉምና ሌሎች ስራ በቀረበውና በትምህርት ፖሊሲ ሰነዶች ትኩረት ተሰጥቷቸው በተካተቱ የአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) ስድስት ዓላማዎችና በየትምህርት ዓይነቶች ዓላማዎች መሰረት እንደሆነ ቃለመጠይቆች ሲካሄዱ አስረድተዋል። የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች በመባል የሚታወቁትም በተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ክፍል በስፋት እንደተገለጸው ዕውቀት፣ ግንዛቤ፣ ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ ናቸው። በዚህ ጥናት ዐውድ የትምህርት ዓይነት ዓላማዎች ማለትም ለደረጃው በተዘጋጁት መርሐ ትምህርቶች የተካተቱትን የክሂል፣ የሥነ-ጽሁፍና የሰዋስው ትምህርቶች ዓላማዎች የሚመለከት ነው።

እነዚህ ሀሳቦች አንድ ፈተና በተለይም ውጫዊ/ ብሄራዊ ፈተና ከሥርዓተ ትምህርቱ ያፈነገጠ ቢሆን የታለመው ትምህርት ግቡን እንዳይመታ የሚያደርግ አሉታዊ ሚና ሊጫወት እንደሚችል የሚያመለክቱ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ በተቃራኒው አንድ ፈተና ጥሩ ማስተማርንና መማርን ሊያበረታታም ይችላል። ለምሳሌ፣ በCheng

(1997) ጥናት እንደተረጋገጠው ፈተናው ሲከለስ/ ሲሻሻል ውይይቶችን (Discussions) እና ሚና ጨዋታዎችን (Role Playes) እንዲያካትት በመደረጉ መምህራኑ ውይይቶችንና ሚና ጨዋታዎችን ሰፊ ትኩረት ሰጥተው እንዲያስተምሩ አድርጓቸዋል። የShohamy Dmitsa-Schnidt and Ferman (1996) ጥናትም እንዲሁ ጥሩ ፈተና በትምህርት ይዘትና የማስተማሪያ ዘዴ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል አሳይቷል።

የአንድን ፈተና ከሥርዓተ ትምህርቱ ማፈንገጥ አለማፈንገጥና የተጽዕኖውን አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ የፈተናዎቹን ወሽባክ በማጥናት ነው። ወደኋላ በሌላ ክፍል ዘርዘር ብሎ እንደተገለጸው፣ በዚህ ጥናት የGreen (2007) የወሽባክ ተጣጥሞሽ (Overlapping) ሞዲል የተመረጠው ከዚህ አተያይ አንጻር በኢትዮጵያ በተለይም በትምህርት ፖሊሲ ሰነዶች ከፍተኛ ትኩረት በተሰጣቸው በአዕምሯዊ ምድብ ስድስት ችሎታዎች/ዓላማዎችና በብሔራዊ ፈተናው እንዲሁም ለደረጃው በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሳሪያዎች በተካተቱት ዓላማዎችና በብሄራዊ ፈተናው መካከል ያለውን ግንኙነት ለመፈተሽ እንዲያስችል ነው። የAlderson እና Wall (1993) ትወራዊ መላምቶች፣ የHughes (1993) ወሽባክ ማዕቀፍ (Framework) እና የBailey (1996) የወሽባክ ሞዴል ደግሞ ሌሎች የወሽባክ ገጽታዎችን ለመመርመር በጥናቱ እንዲያገለግሉ ተደርገዋል።

በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ክፍል እንደተገለጸው በኢትዮጵያ የብሔራዊ ፈተና ታሪክ ለሦስት የትምህርት ዓይነቶች ብሔራዊ ፈተና ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገሪቱ መዘጋጀት ሲጀምር ከሦስቱ አንዱ የአማርኛ ቋንቋ ነበር (Madson 1976)። በብሔራዊ ፈተናዎች ላይ ከተካሄዱ ጥናቶች ማስተዋል እንደተቻለውም በተለይ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ከወሽባክ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖራቸውም የብሔራዊ ፈተናዎችን ዝግጅት ለማሻሻል የሚረዱ በራሳቸው በፈተናዎቹ ላይ ጥናቶች ማካሄድ ተጀምሮ ነበር። እንደ አጀማመሩ ግን በፈተናዎች ላይ የሚደረገው ጥናት ተጠናክሮ አልቀጠለም። ለዚህ አንዱ ማስረጃ በዚህ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ በሆነው ረጅም ጊዜ ውስጥ ከMadson (1976) ጥናት ውጭ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ማግኘት የተቻለው ስድስት ለመጀመሪያና ሁለት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት

በብሔራዊና ክልላዊ የአማርኛ ፈተናዎች ላይ የተሰሩ የመመረቂያ ጥናቶችን ብቻ መሆኑ ነው፡፡ ከስድስቱም አራቱ በ1950ዎቹና 1960ዎቹ በተሰጡ ፈተናዎች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው፡፡ አንዱ በስምንተኛ ክፍል፣ የቀሩት በሙሉ በቀድሞዎቹ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናዎች ላይ የተካሄዱ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ጥናቶቹ አንደኛ፣ በቀድሞዎቹ ሥርዓተ ትምህርቶች ላይ ተመስርተው የተካሄዱ ናቸው፡፡ ሁለተኛ፣ በእነዚህ ጥናቶች የተጠኑትን ጉዳዮች ለመለየት በተደረገው ንባብ ለማረጋገጥ እንደተቻለው ሁሉም በራሳቸው በፈተናዎቹ ባህርያት ወይም በተማሪዎች ውጤት ላይ ተመርኩዘው የተካሄዱ ናቸው፡፡ አንዳቸውም ርቱዕ (Direct)ም ሆነ ኢርቱዕ (indirect) በሆነ መንገድ ፈተናዎቹ በመማር-ማስተማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ በሚመለከት ያነሱት ምንም ነገር የለም፡፡ በመሆኑም በጥናቶቹ ስለተነሱ ጉዳዮች ዝርዝር ነገር በማቅረብ ይኸኛው ጥናት ከእነዚህ ጥናቶች በምን በምን እንደሚለይ ለማስረዳት መሞከር አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከአማርኛ ትምህርት ጋር በተያያዘ፣ ከወሽባክ ጋር በተያያዘ ማግኘት የተቻለው እ.ኢ.አ. በ1998ና በ1999 ዓ.ም. የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተናዎች ላይ ተመስርቶ በባህርዳር ዩንቨርሲቲ፣ በአበባ እ.ኢ.አ.(2000) ዓ.ም፣ <u>የ10ኛ ክፍል አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በመማር-ማስተማር ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ</u> በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ መሟያነት የተሰራውን የመመረቂያ ጥናት ብቻ ነው፡፡ ይህም ቢሆን በቀጣዩ ክፍል እንደተገለጸው፣ የመጀመሪያ ስራ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ የሚደነቅ ቢሆንም ከወሽባክ ጥናት አኳያ ሲመረመር ግን ብዙ ችግሮች የሚታዩበት ስራ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በአዲሱ አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ (1986) መሰረት የ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ከ12ኛ ክፍል ወደ 10ኛ ክፍል ከ1993 (እ.ኢ.አ) ጀምሮ ዝቅ እንዲል ተደርጓል (ውብሸት 1992)፡፡ ከ1993 (እ.ኢ.አ.) ጀምሮ እስከ 2005 (እ.ኢ.አ.) ያሉት ጊዜያት ረጅም ቢሆኑም በአማርኛ ብሔራዊ ፈተናዎችን በተመለከተ ማግኘት የተቻለው ይኸን የአበባ (2000) ጥናት ብቻ ነው፡፡ ይህም በብሔራዊ ደረጃ የሚዘጋጁ የአማርኛ ፈተናዎች በመማር-ማስተማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ምን

እንደሆነ በሳይንሳዊ መንገድ ለማጥናት እየተደረገ ያለው ጥረት ዝቅተኛ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር (Statement of the Problem)

በሌላው ዓለም በተለይ ከAlderson እና Wall (1993) የስሪ ላንካ ጥናት ወዲህ የቋንቋ ፈተናዎችን ወሽባክ (ፈተናዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ) የማጥናት አስፈላጊነት ከፍተኛ ትኩረት በማግኘቱ የተለያዩ ምርምሮች እየተካሄዱ ነው። የተለያዩ ምርምሮች መካሄዳቸውም በፈተናዎች ላይ የሚታዩ ችግሮችን በወቅቱ እየፈቱና የተሻሉ ፈተናዎችን እያዘጋጁ ፈተናዎች የመማር-ማስተማሩን ሂደት የሚያጠናክሩ፣ አልፎ ተርፎም ተገቢ አቅጣጫ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ለማድረግ እስከመቻል ተደርሷል (Alderson እና Hamplyons 1996፣ Cheng 2005፤ Shohmy እናሌሎች 1996)።

የወሽባክ መሰረታዊ (Worthwhile) ዓላማም መማርን ማሻሻል (Improved Learing) ነው። መማር የሚሻሻለውም የማስተማር ሂደትን በማሻሻል ጭምር መሆኑ ግልጽ ነው። የወሽባክ ጥናትና ምርምር ተልዕኮም የወሽባክ አከሳሰት መንገዶችን (Mechanism) በተሻለ ደረጃ በመረዳት መማርን ለማሻሻል የሚረዱ የምዘና ስልቶችን ለማዳበር /ለመቅረጽ(in order to design assessments that will help improve learing) ነው (El-Ebyary 2009)። (Alderson እና Wall 1993፣ Andrew እና ሌሎች 2002፣ Baily 1996፣ Ching እና Curtis 2004፣ Hughes 2003፣ Shohamy እና ሌሎች 1996፣ Watanabe 2004) ይህን ሀሳብ ይጋራሉ።

እንደተባለውም የወሽባክ ጥናት የማስተማርና መማር ሂደቶችን በማሻሻል/ በመለወጥ መማርን ለማሻሻል ቢሆንም በኢትዮጵያ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ይህን የሚያሳይ አይመስልም። ምክንያቱም በአማርኛም ሆነ በሌሎች የትምህርት መስኮች (በእንግሊዝኛ ቋንቋ እየተሞከሩ ካሉት አንዳንድ ጥናቶች በስተቀር)ትኩረት ያገኘ የጥናት መስክ እየሆነ ነው ለማለት የሚያስችል ተጨባጭ ነገር ገና አየታየ አይደለም።

በእርግጥ በፖሊሲ ደረጃ የፈተናና ምዘና ጉዳይ ትኩረት ተነፍጎታል ለማለት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ፤ በ1986 እ.ኢ.አ. የተዘጋጀውና አሁንም እየተሰራበት ያለው **አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ** ገጽ 11 <u>የትምህርት ምዘና</u> በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር 3.3.7 "ብሔራዊ ፈተናዎችን ለመምራትና በጠቅላላ ስለ ትምህርትና ሥልጠና ምዘናና ፈተና ሳይንሳዊ አመራር ለመስጠት አስፈላጊውን የሥለጠነ የሰው ኃይል በጀት ቁሳቁስ የሚያደራጅ ራሱን የቻለ ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር የሆነ የብሔራዊ የትምህርት ምዘና ፈተናዎች ድርጅት ይቋቋማል›› ይላል፡፡ በዚህም መሠረት ድርጅቱ ተቋቁሞ ተግባሩን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ድርጅት አማካኝነት እየተዘጋጀ ስላለው የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና እንደተባለው በሳይንሳዊ መንገድ እየተዘጋጀ መሆንና አለመሆኑን፣ ወሽባኩ አዎንታዊ ይሁን አሉታዊ ለማረጋገጥ በቀዳሚው ክፍል እንደተጠቆመው ከአምስት ዓመት በፊት በአበባ(2000) ከተሞከረ አንድ የመመረቂያ ጽሑፍ በስተቀር ሌላ የተካሄደ ጥናት ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይኸም ጥናት የመጀመሪያ ሙከራ በመሆኑ የሚደነቅ ቢሆንም ከወሽባ ጥናት አሰራር አንጻር ሲታይ ብዙ የሚቀረው/ የማያሟላቸው ነገሮች የሚታዩበት ነው፡፡

ስለዚህ ይኸኛው ጥናት በአበባ ጥናት የታዩትን ክፍተቶች ለመሙላት የሚያስችልም ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በአበባ (2000) ጥናት ከታዩት ክፍተቶች መካከልም አንደኛ፣ ርዕሱ ራሱ ግልጽ አይደለም፡፡ ለምሳሌ በኢትጵያ የትምህርት ሥርዓት የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና እንጂ የ10ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ የሚባል አይታወቅም፡፡ ሁለተኛ፣ ጥናቱ በአንድ ቦታ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ተመስርቶ የተካሄደ በመሆኑ ስለፈተናው ወሽባክ ሰፋ ያለ ምስል አያሳይም፡፡ ሦስተኛ፣ የጥናቱ ርዕስ የፈተና ተጽዕኖ የሚል ቢሆንም እንኳ በጥናቱ ለመመለስ የተሞከረው፣ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ይዘቶችና በ10ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ይዘቶች፤ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የአጠያየቅ ስልት/ ቅርጽ (Format) እና በ10ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ የማለማመጃ መንገዶች፣ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ይዘቶችና በክፍል ፈተናዎች ይዘቶች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ነው፡፡ አራተኛ፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው የሚመሰረተው በዘጠነኛና በ10ኛ ክፍል ትምህርት ላይ ሆኖ እያለ አጥኝዋ የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ላይ ብቻ በመመሰረት ያካሄዱት

ጥናት ነው፡፡ አምስተኛ፣ በጽሑፍ መጠይቅ ተጨማሪ መረጃ ከመምህራንና ከተማሪዎች ለመሰብሰብ የሞከረ ጥናት ቢሆንም በመጠይቆቹ ከስምንት መምህራንና ፈተናውን ከወሰዱና ካልወሰዱ (የ10ኛ፣ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል) ተማሪዎች የተሰበሰበ መረጃ በመሆኑና የተገኘው መረጃ ተቀላቅሎ የተተነተነ ስለሆነ የወሸባክ አጠናንን የተከተለና የወሸባክ ውጤትን የሚያንጸባርቅ ጥናት ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከአበባ ጥናት በብዙ መልኩ ይለያል ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቀዳሚው ጥናት በ1998 እና 1999 ዓ.ም የክፍልና ብሔራዊ ፈተናዎች ላይ ተመስርቶ የተካሄደ ሲሆን ይኸኛው ከ2000 ዓ.ም.(እ.ኢ.አ.) ወዲህ በተዘጋጁት የአምስት ተከታታይ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችና እነዚህ ፈተናዎች በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ እንዲሁም ሌሎች ውጫዊ ክፍሎች ላይ እያሳደሩት ባለው ተጽዕኖ ላይ የሚካሄድ በመሆኑ ከቀዳሚው ይለያል፡፡ በሌላ አባባል በተለያዩ የጥናቱ ክፍሎች እንደተገለጸው በዚህ ጥናት በፈተናዎቹና በመርሐ ትምህርቶቹ መካከል ያለው መጣጣም (Overlap)፣ በGreen (2007) ሞዴል መሰረት የሚፈተሽ ቢሆንም በቀዳሚው ጥናት ያልተካተቱትና የወሸባክ ጥናት ዋነኛ ጉዳዮች የሆኑት የተሳታፊዎች ግንዛቤ (Perceptions) እና የመማር ማስተማር ሂደቶች (Processes) ባህርያት በዚህኛው ጥናት ዋነኛ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑ ይህን ጥናት ከቀዳሚው የተለየ ያደርገዋል፡፡ በተጠቀሰው ርዕስ ጥናት ለማካሄድ ካነሳሱ ምክንያቶች መካከል ዋነኛው/ ቀዳሚውም የወሸባክ አጠናን መንገድ ተከትሎና የወሸባክ ጥናት ተተኳሪ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ የተካሄደ የወሸባክ ጥናት አለመኖርን ክፍተት ለመሙላት ነው፡፡

ሌላው ምክንያት አጥኝው ሲሰራበት በነበረበት ተቋም የተከታታይ ምዘና ዩኒት ኮሜቴ አባል ሆኖ ባገለገለባቸው ዓመታት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን እንዴት እንደሚገመገሙ የሚፈትሹ ጥናቶችን የማካሄድ ዕድል ማግኘቱ ነው፡፡ በእነዚህ ወቅቶች አጥኝውም ሆነ የሥራ ባልደረቦቹ ያካሄዷቸው ጥናቶች ውጤት ያሳየው በየትምህርት ቤቶቹ የሚካሄዱት ግምገማዎችም ሆኑ የትምህርት አሰጣጡ ችግር የበዛባቸውና የማስተማር-መማር ሂደቶችን በጎ በሚባል ጎን የማይደግፉ መሆናቸውን ነው፡፡ የዚህ አንዱ ምክንያት ብሔራዊ ፈተናዎች በመማር ማስተማር ሂደቶችና በመምህራን በሚዘጋጁ ፈተናዎች ላይ እያሳደሩት ያለው ተጽዕኖ ሊሆን

ይችላል፡፡ ውጫዊ/ ብሔራዊ ፈተናዎች በማስተማር- መማር ሂደቶችና መምህራን በሚዘጋጁ ፈተናዎች ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ደግሞ የተለያዩ ጥናቶች (ለምሳሌ ስማቸው 2012፣ Chen 2002፣ Gohabani 2008፣ Spratt 2005) አመልክተዋል፡፡ በምዘና ሥርዓቱ ላይ የሚታዩ ችግሮች ደግሞ የመማር-ማስማር ሂደቶች ችግሮች ነጸብራቅ መሆናቸው አይቀርም፡፡ ይህም ከክፍል ፈተናዎች ይልቅ በብሔራዊ ፈተናዎች ወሽባክ ላይ ጥናት ለማካሄድ እንደሚገባ ያነሳሳ አንድ ምክንያት ነው፡፡

አጥኝው ጎንደር መምህራን ኮሌጅ በሚያስተምርበት ጊዜ 10ኛ ክፍል አጠናቀው በአማርኛም ሆነ በሌሎች ትምህርት ክፍሎች ለስልጠና የሚመደቡ ሀሳባቸውን በቃልና በጽሑፍ አቀናብረው መግለጽ የሚቸገሩ ብቻ ሳይሆን የቋንቋውን ፊደሎች እንኳ በትክክል የማይለዩ ተማሪዎች ሲያጋጥሙት የነበረ መሆኑም እንዲሁ የችግሩን ምንጭ ከፈተናው አሉታዊ ተጽዕኖ ሳይሆን አይቀርም ከሚለው ሀሳብ ጋር ለማያያዝ የገፋፋ ሌላው ምክንያት ነው፡፡

ከዚህ በፊት ሲዘጋጁ የነበሩት ፈተናዎች ብቃት ሳይመረመር በብሔራዊ ደረጃ የሚዘጋጁ የቋንቋ ፈተናዎች ከሁለት ወደ12 እንዲያድጉ ተደርገዋል፡፡ እንደ ፈተናዎች ድርጅት ኃላፊዎች አነጋገር ቋንቋዎችን፣ በብሔራዊ ፈተናነት የማካተቱ ሂደት ሊቀጥል የሚችል ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከድርጅቱ ኃላፊዎች ጋር ከተካሄዱት ውይይቶች መረዳት እንደተቻለው በድርጅቱ በኩል እየተዘጋጁ ያሉ ፈተናዎችን ችግሮች ለመለየትና ችግሮችን እያጠኑ/ እያስጠኑ በወቅቱ ለመፍታት የተደረገም ሆነ ለማድረግ የታሰበ ነገር የለም፡፡ በእርግጥ ትምህርት ሚኒስቴር የሰው ሀይል የሚመድብላቸው ከሆነ ወደፊት የጥናት ክፍል የሚባል መዋቅር የማቋቋም ሀሳብ አለ፡፡ በፈተናዎቹ ላይ የሚታዩ ችግሮች እየተጠኑ መፍትሄ የማይፈለግላቸው ከሆነ ደግሞ የአዳዲስ ቋንቋዎች ፈተናዎች አዘገጃጀት ከባዶ ስለማይነሳ በብዙ አቅጣጫ ቀደም ብለው ሲሰጡ የነበሩ ቋንቋዎችን ፈተና አዘገጃጀት በሞዴልነት መከተሉ አይቀርም፡፡ ይህም የቀዳሚዎቹ ፈተናዎች አዘገጃጀት በመማር-ማስተማር ሂደቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር አይነት ከሆነ የአዳዲሶችም ተመሳሳይ መሆኑ አይቀርም፡፡ በመሆኑም በአማርኛ ቋንቋ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ

ፈተናዎች ላይ ጥናት አካሂዶ ከፈተና ወሽባክ አንጻር የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መለየትና አማራጭ ስልቶችን ማሳየት መቻሉ በሌሎች ሀገርኛ ቋንቋዎች ፈተናዎች አዘገጃጀት ላይም አስተዋፅኦ ሊኖረው ይችላል የሚለው ሐሳብ ሌላው በዚህ ርዕስ ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳ ምክንያት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በዚሁ መርሐ ግብር ለ‹‹ቴሰቲንግ› ኮርስ ማሟያ በተለያዩ ቡድኖች የተገመገሙት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ሞዴልና ብሔራዊ ፈተናዎች ላይ የታዩት ጥሩ መማርን የማያበረታቱ ጉልህ ጉልህ ችግሮች (ለምሳሌ ሰዋሰው ላይና ስነ-ጽሑፍ ላይ ማተኮር) በፈተናዎች ላይ ጥናት ለማካሄድ የሚገፋፉ ነበሩ።

አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑትም ሆኑ ቋንቋውን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው ያላቸው ችሎታ እጅግ ደካማ እየሆነ መጥቷል፣ የሚለው በጥናቶች ጭምር የተደገፈ ሮሮም የዚህ ችግር አንዱ ዋና ምክንያት እኮ ፈተናዎቹ ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ ለማሰብ ይገፋፋል፤ ወይም የፈተናዎቹ አሉታዊ ወሽባክ የሚፈጥረው ችግር ሊሆን ይችላል የሚለውን ሀሳብ የሚያሳስብ ሆኖ ተገኝቷል።

ከላይ በቀረቡት አነሳሽ ምክንያቶች በዚህ ጥናት ለመመርመር የተሞከረው **የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናን ‹ወሽባክ”** ነው።

1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ጥናቱ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ወሽባክ ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው። በዚህ አጠቃላይ ጥያቄ መሰረትነትም ለሚከተሉት ዝርዝር ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የሚሞክር ነው፤

1. የፈተናዎች ኤጀንሲ የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን አዎንታዊ ተጽዕኖ ከፍ ለማድረግ ምን ምን ስትራቴጂ ይጠቀማል / የሚጠቀምባቸው ስትራቴጂዎች ምንድን ናቸው?
2. የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና፣

2.1 ከአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) የትምህርት ዓላማዎች ጋር ይዛመዳል?

2.2 ከቋንቋው ትምህርት ዓላማዎች ጋር ይዛመዳል?

3 የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው የሚፈጥረውን ተጽዕኖ እንዴት ይገነዘቡታል?

ለዚህ ሰፊ ጥያቄ መልስ ለማግኘትም ለሚከተሉት ዝርዝር ጥያቄዎች ትኩረት ይሰጣል፡፡

3.1 የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው (በክፍል ውስጥ ተግባራት፣ በማስተማር ዘዴ፣ በትምህርት ይዘቶች፣ በትምህርት ማቴሪያሎችና በክፍል ትምህርት ምዘና) ላይ ስለሚያደርሰው ተፅዕኖ ያላቸው ግንዛቤ (Perceptions) ምንድነው?

3.2 በጥናቱ ዐውድ የወሸባክ መከሰቻ (መምህራን ማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግባራቸው ላይ በሚያሳድረው ተጽዕኖ ላይ ላዳበሩት ግንዛቤ) ምክንያቶች (Factors) ምንድን ናቸው?

3.3 በመምህራን ባሕርያት (የመምህራን የትምህርት ደረጃ፣ ጾታ፣ የሥራ ልምድ፣ ለማስተማር ሙያ ያላቸው ከበሬታ፣ ከፈተናው ጋር ያላቸው ትውውቅ፣ በፈተናው ጠቀሜታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ በሥራ ላይ ሥልጠና መርሐ ግብሮች ያላቸው ተሳትፎ) እና መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጦው (Variable) መካከል ያሉት ተዛምዶዎች ምንድናቸው?

3.4 በትምህርት ቤቶቹ ዐውድ (context characterstics)_መምህራን በተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ላይ ባላቸው ግንዛቤ፣ በውጫዊ ተጽዕኖዎች ላይ ባላቸው አመለካከት፣ ለቋንቋው ትምህርት በተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠንና የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ /ዳራን በተመለከተ ባላቸው ግንዛቤ፣ በተማሪ-ክፍል ጥምርታ) እና መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ

ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጦው) መካከል ያሉት ተዛምዶዎች ምንድናቸው?

3.5 በጥገኛ ተላውጦው ላይ ተጽዕኖ በሚያደርስ በእያንዳንዱ የመምህራን ባህርያት (ዐቢይ ተላውጦ) ላይ ጣልቃ የሚገቡ ተላውጦዎች ምንድን ናቸው?

3.6 በእያንዳንዱ ነጻ ተላውጦ (የወሽባክ መከሰቻ ምክንያት) ሊገለጽ የሚችለው የጥገኛ ተላውጦው ልዩነት ምን ያህል ነው?

4 የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር መማር ሂደቶች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ተማሪዎች ያላቸው ግንዛቤ ምንድነው?

5 የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድራቸው ተጽዕኖዎች ምንድን ናቸው?

6 የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ውጫዊ (Macro) ወሽባክ (በውጫዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ የሚያሳድሯቸው ተጽዕኖዎች) ምንድን ናቸው?

7 በማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት ምን ምን አዎንታዊ የወሽባክ አላባዎች (elements) ይበረታታሉ (encouraged)?

8 በማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት ምን ምንስ አሉታዊ የወሽባክ አላባዎች ይበረታታሉ?

1.4 የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

ሀ.አጠቃላይ ዓላማ (General Objective)

የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናን ወሽባክ ለመፈተሽ ነው፡፡

ለ. ዝርዝር ዓላማዎች (Specific Objectives)

ከአጠቃላይ ዓላማው የመነጩት ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤

1. የፈተናዎች ኤጀንሲ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ታላሚ ተፈታኞችን አዎንታዊ ወሽባክን ከፍ ለማድረግ የሚጠቀምባቸውን ስትራቴጂዎች መፈተሽ፣
2. የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች፤ ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር ያላቸውን ዝምድና (Overlapping) መፈተሽ፣
3. .የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በሚፈጥረው ተፅዕኖ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ (Perceptions) መለየት፣
4. የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ተማሪዎች ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር፣
5. የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድራቸውን ተጽዕኖዎች መለየት፣
6. የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ በውጫዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ የሚያሳድሯቸው ተጽዕኖዎች መለየት፣
7. በማጠናቀቂያ ፈተናው መኖር ምክንያት ምን ምን አዎንታዊ የወሽባክ አላባዎች (elements) እንደሚበረታቱ (encouraged) መፈተሽ፣
8. በማጠናቀቂያ ፈተናው መኖር ምክንያት ምን ምን አሉታዊ የወሽባክ አላባዎች እንደሚበረታቱ መፈተሽ።።

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

በኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ወሽባክ ላይ የሚካሄደው ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፤

1. በየዓመቱ የሚዘጋጁት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች አዘገጃጀትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለመለየት አንድ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፤

2. በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና በአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች እንዲሁም በፈተናዎቹና በቋንቋው ትምህርት መካከል፣ ያለውን ተጣጥሞሽ ለመለየት ያስችላል፤
3. የአማርኛ ብሔራዊ ፈተና በቋንቋው ትምህርት ላይ በተለይም በአማራ ክልል የሚያሳድረው ተጽእኖ ምን እንደሚመስል ለመለየት የሚያስችል መረጃ ይሰጣል፤
4. ለፈተናዎች ኤጀንሲ በየዓመቱ የሚዘጋጁ የቋንቋው ፈተናዎችን ታላሚ ተፈታኞችን የመመዘን ደረጃና አዎንታዊ ወሽባክ ለማሻሻል የሚያግዛቸው ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል፤
5. በአማራ ክልል የማጠናቀቂያ ፈተናው በቋንቋው ትምህርት ላይ እያሳደረ ያለውን ተጽዕኖ በማሳየት ለትምህርት ባለድርሻ አካላት የቋንቋውን ትምህርት አሰጣጥ ለማሻሻል የሚያግዝ መረጃ ይሰጣል፤
6. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን አስልጣኝ ተቋማት የአማርኛ መምህራን ቋንቋውን እንዴት እያስተማሩ እንዳሉ ለማወቅና የአሰለጣጠን ሂደታቸውን ለመከለስ የሚያግዛቸው መረጃ ያስገኛል፤
7. ወደፊት ለሚካሄዱ ጥናቶች መነሻ ይሆናል።

1.6 የጥናቱ ወሰን (Scope of the Study)

ይህ ጥናት ዋነኛ ትኩረቱን የአማርኛ ቋንቋን በሥራና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማስተማሪያ ቋንቋነት በሚገለገለው በአማራ ክልል ላይ አድርጎ የተካሄደ ነው። በአማራ ክልል ውስጥ ከተካተቱ 11 ዞኖች ውስጥም ከተማሪዎች የሚሰበሰውን መረጃ ተመሳሳይ ዳራ ካላቸው ተሳታፊዎች መሰብሰብ እንዲቻል የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋና የዞኖቹ የስራ ቋንቋ አሮምኛ፣ አዊኛና ሃምጥኛ የሆኑት ሦስት ዞኖች በጥናቱ አልተካተቱም። በሌላ በኩል ሀገራዊ የሆኑት የቋንቋው መርሐ ትምህርቶች፣ የመማሪያና የማስተማሪያ መጽሐፎችና ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችም ተመርምረዋል። ከፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና ከቋንቋው ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ጋር የተካሄዱት ውይይቶችም ሀገራዊ ናቸው። ሆኖም በትምህርት

ቤቶች ደረጃና በዞን ከተማና ዞን ትምህርት መምሪያዎች ፈተናው የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በተመለከተ ለማጥናት የተሞከረው በአማራ ክልል ውስጥ በሚገኙ ዞኖችና ትምህርት ቤቶች ላይ በማተኮር ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች (ለምሳሌ ጥናቱ የሚካሄድበት ጊዜ ውስን በመሆኑ፣ በሁሉም ቦታዎች ለማካሄድ የፋይናንስ ችግር ስላለ...) የማጠናቀቂያ ፈተናው በሀገሪቱ ውስጥ /በሁሉም ክልሎች በሚገኙ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች፣ የቋንቋው መምህራንና ሌሎች ወገኖች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለማጥናት አልተሞከረም፡፡

Bailey (1996) የHughes (1993) የወሸባክ ማዕቀፍና የAlderson እና Wall (1993) የወሸባክ መላምቶች በማቀናጀት በነደፉት ባለሦስት ክፍል የወሸባክ ሞዴል ይህ ጥናት ያተኮረውም በሁለቱ ክፍሎች ማለትም በተሳታፊዎችና በሂደቶች ላይ ብቻ ነው፡፡ ውጤቶች የሚለው ክፍል አልተካተተም፡፡ ከምክንያቶቹ አንደኛው በድርሳናት ክለሳ ክፍል እንደተገለጸው በዚህ ሞዴል በሦስተኛ ክፍልነት (ውጤት በሚል ስያሜ) የቀረበው የወሸባክ ጥናት ዋነኛ ትኩረት እየሆነ ባለመምጣቱ ነው፡፡ ሁለተኛ፣ በተለይ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ እንጂ በፈተናው የሚያስመዘግቡት ውጤት እንደመሰረታዊ ችግር የሚታይ ባለመሆኑ ነው፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች በዚህ ጥናት ውጤት የሚለው ክፍል አልተካተተም፡፡

በወሸባክ ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች መካከልም በጥናቱ እንዲካተቱ የተደረጉት ከመምህራንና ከዐውድ ጋር የሚያያዙት ብቻ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በድርሳናት ክለሳ ክፍል እንደተገለጸው በዋነኛ ተጸዕኖ ፈጣሪ ምክንያትነት የሚታወቁት እነዚህ ሆነው በመገኘታቸው ነው፡፡ ከመምህራን ጋር የሚያያዙ በመባል ከሚታወቁት ተላውጠዎች/ ምክንያቶች መካከልም ዋና ዋናዎቹ ማለትም የመምህራኑ ጾታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የማስተማር ልምድ፣ የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ፣ ለማስተማር ሙያ የሚሰጡት ክብር፣ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው እውቂያና ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ (Perceptions) የሚሉት ተካተዋል፡፡ ከዐውድ ጋር በተያያዘ ደግሞ መምህራን አንደኛ፣ ስለተማሪዎች የመማር ዝንባሌ፣ ሁለተኛ፣ ውጫዊ ተጽዕኖዎችን በሚመለከት ያላቸው ግንዛቤ፣ ሦስተኛ፣ ለቋንቋው ትምህርት

በተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን ላይ ያላቸው አመለካከት፣ አራተኛ፣ የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ/ ዳራን በተመለከተና አምስተኛ፣ በተማሪ-ክፍል ጥምርታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ የሚሉት ብቻ በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡

1.7. የጥናቱ ውስንነት (Limitation of the Study)

የጥናቱ ግኝቶች ለተለያዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ጠቃሚ ግብአቶችን እንደሚሰጡ ቢታመንም ጥናቱ ውሱንነቶችም አለበት፡፡ ከነዚህ ውሱንነቶች መካከልም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በጊዜ እጥረት፣ በፋይናንስ አቅምና በመሳሰሉት ምክንያቶች በትምህርት ቤት፣ በወረዳና በዞን ደረጃ የተካሄደው ጥናት በአማራ ክልል ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ግኝቶች በሌሎች ክልሎች ያለውን የወሽባክ ገጽታ ላያንጸባርቁ ይችላሉ፡፡
- የመማር ማስተማር ሂደቶችን ለማጥናት የተካሄዱት የክፍል ምልከታዎች በሙከራ ጥናቱ ለአንድ ወር፣ በዋናው ጥናት ለሁለት ወር ከ15 ቀናት ያህል ብቻ መሆኑ ሌላው ውስንነት ነው፡፡
- በታቀደው መሰረት በክፍል መምህራን የተዘጋጁ የ2004 እና 2005 ዓ.ም የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የአንደኛና የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ የክፍል ፈተናዎች ለማግኘት ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም የክፍል ፈተናዎችን በተመለከተ የተካሄደው ጥናት፣ አንደኛ፣ ከሰባት ትምህርት ቤቶች በተሰበሰቡ 15 የዘጠነኛና 12 የ10ኛ ክፍል ፈተናዎች፣ ሁለተኛ፣ በአምስት በዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች በተዘጋጁ የ10ኛ ክፍል ፈተናዎች፣ ሦስተኛ፣ በሁለት የዘጠነኛና በአራት የ10ኛ ክፍል በዞን ትምህርት መምሪያዎች በተዘጋጁ ፈተናዎች፣ በድምሩ በ17 የዘጠነኛና በ21 የ10ኛ ክፍል ፈተናዎች ላይ ተመስርቶ የተከናወነ ነው፡፡

1.8. የቁልፍ ቃላት (ጽንሰ ሀሳቦች) አጠቃቀም ብያኔ

በዚህ ጥናት ውስጥ የሚከተሉት ቃላት የሚኖራቸው ፍቺ በዚህ ክፍል የተሰጣቸው ብያኔ ይሆናል፡፡

- **ለማስተማር ሙያ የሚሰጥ ክብር** (Professinalism in Teaching)

በAldesan እና Wall (1993) ሥራ እንደተብራራው፣ መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው አተያይ/ ክብር የሚለው በአንድ በኩል መምህራን ተማሪዎቻቸው በውጫዊ/ ብሔራዊ ፈተናዎች በሚያስመዘግቧቸው ደካማ (Poor) ውጤቶች የተነሳ የሚፈጠርባቸውን የፍርሀት፣ የዝቅተኝነትና የጥፋተኝነት/ የበታችነት ስሜት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎቻቸው በፈተናዎች ጥሩ ውጤት ሲያስመዘግቡ የሚሰማቸውን የጥሩ አስተማሪነት፣ የኩራት /የደስታ ስሜት የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ለማስተማር ሙያ የሚሰጥ ክብር የሚለው የሚወክለው ይህንኑ፣ መምህራን የሙያ ብቃታቸውን ለመለካት ተማሪዎቻቸው በማጠናቀቂያ ፈተናው ከሚያስመዘግቡት ውጤት ጋር የሚያያዘውን ጽንሰ ሀሳብ ይመለከታል፡፡

- **በማስተማር ላይ የሚፈጠር ውጫዊ ጫና** (External Pressure in Teaching)

የHerman እና Golan (1993) ጥናት እንደሚያሳየው፣ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የፈተና ውጤት ከፍ እንዲያደርጉ በተለያዩ ወገኖች ጫና ይደረግባቸዋል፡፡ በኢትዮጵያም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በአንዳንድ ቦታዎች መምህራን በየዓመቱ የተማሪዎቻቸውን ውጤት እስከምን ደረጃ እንደሚያሳድጉ በእቅዳቸው እንዲያካትቱ እንደሚጠየቁ መምህራኑ ራሳቸው ሲናገሩ ይሰማል፡፡ በዚህ ጥናት ውጫዊ ጫና የሚለው መምህራን የተማሪዎቻቸውን ብሔራዊ /የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት የሚያሻሽል ስራ እንዲሰሩ በተማሪዎች ወላጆች፣ በትምህርት ቤቶቻቸው አስተዳዳሪዎችና በሌሎች ያገባናል በሚሉ ወገኖች የሚደረግባቸውን ተጽዕኖ የሚመለከት ነው።

- **መምህራን ስለማጠናቀቂቂያ ፈተናው ያላቸው እውቂያ** (Awareness)

በዚህ ጥናት **መምህራን ስለማጠናቀቂቂያ ፈተናው ያላቸው እውቂያ** የሚለው የአማርኛ መምህራን በኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ/ ብሔራዊ ፈተና አቀራረብና በፈተናው ስለሚመዘኑት የቋንቋው ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች ሰዋስው (ሰዋስው፣ ቃላት) እና ሥነ-ጽሑፍ ያላቸውን እውቂያ/ ግንዛቤ የሚያመለክት ነው።

- **ወሽባክ**

በዚህ ጥናት ዐውድ፣ "ወሽባክ" የሚለው ጽንሰ ሀሳብ የያዘው ትርጉም አንደኛ፣ የማጠናቀቂያ/ ብሔራዊ /ውጫዊ ፈተናው በመማር-ማስተማር ሂደቶች ላይ በተለያዩ ምክንያቶች የሚያሳድረውን ተጽዕኖና የተጽዕኖውን ደረጃ እንዲሁም የተጽዕኖውን አዎንታዊነትና/ አሉታዊነት ነው፤ ሁለተኛ የማጠናቀቂያ ፈተናው ከመምህራንና ተማሪዎች ውጭ በሆኑት የትምህርት ባለድረሻ አካላት(Stake holders) ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ፣ የተጽዕኖውን ደረጃና የተጽዕኖውን አዎንታዊነትና/ አሉታዊነት ነው።

- **የመምህራን /የተማሪዎች ግንዛቤ** (Perceptions)

በዚህ ጥናት **የመምህራን ግንዛቤ** (Perceptions) የሚለው መምህራኑ የማጠናቀቂያ /ብሔራዊ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ በተመለከተ ያላቸውን እውቀት፣ አመለካከት (Attitudes)፣ እምነት (Beliefs) እና አስተያየት የሚያመለክት ሲሆን የተማሪዎች ግንዛቤ የሚለው ደግሞ በመማር-ማስተማር ሂደቱ ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ያላቸውን እውቀት፣ አመለካከት፣ እምነትና አስተያየት የሚመለከት ነው።

- **የማስተማር ልምድ** (Teaching Experience)

በዚህ ጥናት የማስተማር ልምድ የሚለው የሚያመለክተው የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን ቋንቋውን በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያስተማሩበትን ዓመታት ብዛት ነው። ያላቸውን ልምድ በደረጃ ለመመደብም

በኢትዮጵያ ያለውን የመምህራን የዕድገት መሰላልና የChen (2002) አከፋፈል መሰረት ተደርጓል፡፡

- **የማጠናቀቂያ ፈተና**

በዚህ ጥናት የማጠናቀቂያ ፈተና፣ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናን ይወክላል፡፡

- **የሥራ ላይ ሥልጠና ተሳትፎ** (Participation in In-Service Treaning/ Education)

በዚህ ጥናት የስራ ላይ ስልጠና የሚለው ጽንሰ ሀሳብ መምህራኑ (መረጃው የሚሰበሰብበትን ዓመት ጨምሮ) ላለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ቋንቋውን የማስተማር ዕውቀታቸውንና ክሂላቸውን ለማዳበር /ለማሻሻል የተከታተሏቸውን የሥራ ላይ ሥልጠናዎች ብዛት ይመለከታል፡፡

- **የክፍል ፈተናዎች**

በዚህ ጥናት ዐውድ፣ የክፍል ፈተናዎች የሚለው የሚያመለክተው በክፍል መምህራን ወይም በዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች ወይም በዞን ትምህርት መምሪያዎች በየሴሚስተሩ የሚዘጋጁ የአንደኛና የሁለተኛው ሴሚስተር የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን ነው፡፡

- **የዓመተ ምህረት አጠቃቀስ**

በዚህ ጥናት እ.ኤ.አ. የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሲሆን ያልታከለበት ደግሞ የጎርጎረሳውያን ነው፡፡

- የፈተና ዝግጅት ባለሙያ

በፈተናዎች ኤጀንሲ አሰራር የፈተና ዝግጅት ባለሙያ የሚባለው በየትምህርት ዓይነቱ በብሔራዊ ደረጃ የሚዘጋጁ ፈተናዎችን በሚመለከት ከኤጀንሲው ኃላፊዎች ጋር በመተባበር ጥያቄ አዘጋጆችን/ ፀሐፊዎችን ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን መካከል በኤጀንሲው መስፈርቶች መሰረት የሚመለምል፣ ከመለመለ በኋላ ደግሞ የአዘገጃጀት ስልጠና (Orientation) የሚሰጥ፡ ከዚያም ጥያቄ ጸሐፊዎች

በአዕምሯዊ ምድብና በመርሀ ትምህርቶቹ ዓላማዎች መሰረት መዘጋጀታቸውን የሚፈትሽ፡ በመጨረሻም በተለያዩ ጥያቄ አዘጋጆች ከተዘጋጁ ጥያቄዎች መካከል (በፈተና ልየታዎች ሰንጠረዥ(Table of Specifications) መሰረት) አውጣጥቶና አስፈላጊ ማሻሻያዎችን አድርጎ ፈተናውን ለሕትመት ዝግጁ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት የኤጀንሲው መደበኛ ሰራተኛ ነው።

- **የፈተናዎች ኤጀንሲ**

የፈተናዎች ኤጀንሲ የሚለውን የብሔራዊ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ የሚለው በአጭሩ ይወክላል።

- ጥያቄ አዘጋጅ/ ፀሐፊ

በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በመምህርነት የሚሰራና በፈተናዎች ኤጀንሲ በሚያስተምረው የትምህርት ዓይነት ለጥያቄ አዘጋጅነት በምስጢር ተመርጦ ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ ወይም ለ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና ጥያቄ የሚያዘጋጅ ባለሙያ ነው።

ምዕራፍ ሁለት፤የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ (Review of Related Literature)

2.1. መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር የተያያዙ ተዛማጅ ድርሳናት የተከለሱበት ክፍል ነው፡፡ በክለሳ ድረሳኑም መጀመሪያ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዳራ እና የቋንቋና የአማርኛ ፈተና ታሪካዊ ዕድገት ቅኝት ይቀርባል፡፡ ከዚያም በትምህርትና በፈተና መካከል ሊኖር ስለሚገባው ትስስር የሚያትተው ክፍል ይከተላል፡፡ ቀጥሎ ከወሽባክ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በተለያዩ ንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍለው ይቀርባሉ፡፡

2.2. የጥናቱ ዐውድ (Context) ፤ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኢትዮጵያ

የዚህ ጥናት ትኩረት የአማርኛ ብሔራዊ /የማጠናቀቂያ ፈተና በቋንቋው ትምህርት ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ/ ወሽባክ ነው፡፡ ቀደም ብሎ በምዕራፍ አንድ እንደተወሳው ቋንቋን ማስተማርና ፈተና፣ ፈተናና ትምህርት ደግሞ የተሳሰሩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር በቅድሚያ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት ታሪካዊ ዳራ በአጭሩም ቢሆን መቃኘት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ከዚህ በታች በቀረቡት አንቀጾች ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

አንዳንድ ጥናቶች (ለምሳሌ እ.ኢ.አ. አምሳሉ 1976፣ ዮናስና ሌሎች 1966 ዓ.ም.) እንደሚያመለክቱት፣ የአማርኛ ቋንቋ በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ኢትዮጵያውያን የወል መግባቢያ ሆኖ ማገልገል የጀመረው በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ነው፡፡ የወል መግባቢያ እየሆነ መምጣቱም ቀስ በቀስ አገልግሎቱ ወደ መንግሥት ቋንቋነት እንዲያድግ አድርጎታል (አምሳሉ 1976 እ.ኢ.አ.)፡፡ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ደግሞ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ወደ ጽሑፍ ቋንቋነት ለመሸጋገር ችሏል (አምሳሉ 1976፣ ዮናስና ሌሎች 1966 እ.ኢ.አ.)፡፡ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተለይም በአፄ ቴዎድሮስ ንግሥና ዘመን ደግሞ የንጉሡ ታሪክ፣ የመንግሥት ደብዳቤዎችና ሌሎች ጉዳዮችን በአማርኛ መጻፍ ተጀምሯል (አምሳሉ 1976፣ ዮናስና ሌሎች 1966 እ.ኢ.አ.)፡፡ ይህም የአማርኛ ቋንቋ በተሻለ ደረጃ አገልግሎት መስጠትና በቀጣዮቹ ዘመናት የወል መግባቢያነቱና የጽሑፍ ቋንቋነቱ እያደገ እንዲመጣ አግዟል፡፡ በዚህ መንገድ እያደገ መምጣቱ በአፄ ምንይልክ ፣ በአፄ

ጎይለ ሥላሴም ሆነ በደርግ ዘመን ልዩ ልዩ ጉዳዮችን (ጎን-መንግሥቶችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ ወዘተ. መጻፊያነትና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተለያዩ ቋንቋዎች አፍ ለፊቱ የሀገሪቱ ዜጎች የጋራ መግባቢያነት የሚሰጠው አገልግሎት እየሰፋ እንዲሄድና ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል አድርጎታል፡፡

በመደበኛ ትምህርት አማርኛ የነበረውን ቦታ በተመለከተ የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (1940፣ 1944፣ 1950፣1951 እና 1956 እ.ኢ.አ.) ሰነዶች፣ የተስፋዬና ታይለር (1976) ‹‹የቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት›› የሚለው ጥናትና የአዳነ (1993) “በኢትዮጵያ የመንግስት ትምህርት ታሪካዊ ቅኝት” የሚለው ጽሑፍ እንደሚያመለክቱት በኢትዮጵያ፣ መደበኛ ትምህርት፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቁጥጥር ስር በቆየባቸው ዘመናት የመማሪያና ማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ ሲያገለግል የኖረው ግዕዝ ነው፡፡ በእርግጥ ቀደም ብሎ በነበረው ሥርዓተ ትምህርት በየደረጃው የመማሪያ መጻሕፍቱ በግዕዝ ቋንቋ የተፃፉ ቢሆኑም በቃል የሚሰጠው ማብራሪያና የመምህር-ተማሪ ውይይቶች በአብዛኛው ይካሄዱ የነበሩት በአማርኛ ቋንቋ ነበር (አምሳሉ 1976)፡፡ ከዚህም አማርኛ በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ዜጎች የወል መግባቢያና የመንግስት አስተዳደር ቋንቋ ሆኖ ከማገልገሉ በተጨማሪ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በማስተማሪያ ቋንቋነት አስተዋፅየ እንደነበረው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቀዳሚ ዓላማውን የውጭ ቋንቋዎችን ማስተማር ያደረገው የዳግማዊ ምንይልክ ትምህርት ቤት ሲከፈትም አዳነ (1993) ከውጭ ቋንቋዎች ጎን ለጎን በ1903 (እ.ኢ.አ.) ቀደም ብለው መሰጠት ከጀመሩት ቋንቋዎች በተጨማሪ አማርኛ፣ ዐረብኛና ጣሊያንኛ መጨመራቸውን መግለጣቸው የአማርኛ የትምህርት ቋንቋነት አጀማመር ቀደም ያለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከትምህርትና ሥነ-ጥበብ ሚኒስቴር ሰነዶች መረዳት እንደሚቻለው በዘመናዊ መልኩ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ቀረፃ በኢትዮጵያ የተጀመረው እ.ኢ.አ በ1939 ዓ.ም ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በ1940 ዓ.ም. *(በዚህ ጥናት ዓ.ም. የሚለው ዓመተ ምህረት የሚለው አሕጽሮተ ቃል ነው)* ሥርዐተ ትምህርት ከተቀረጸላቸው የትምህርት ዓይነቶች አንዱ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ነው፡፡ ተማሪዎች ለስምንት ዓመታት /1-8/ በየክፍል ደረጃው ሊማሯቸው የሚገቧቸውን የትምህርት ይዘቶች ዝርዝር የያዘ

ሥርዓተ ትምህርት ነው፡፡ በዚህ ሥርዓተ ትምህርት በቋንቋው ትምህርትነት እንዲሸፈኑ የተካተቱት ዋና ዋና ይዘቶችም መደበኛ ሰዋስው፣ ንባብ (በድምፅና በለሆሳስ)፣ ፅሕፈት(የቃል-ፅሕፈት፣ ድርሰት፣ የእጅ-ጽሑፍ)፣ ንግግር (ማመንጨትና ዘገባ) ናቸው (ተስፋዬና ታይለር 1976)፡፡

በተስፋዬና ታይለር (1976) ግምገማ መሰረት እ.ኤ.አ. በ1940 ዓ.ም. የተዘጋጀው የ፩ኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓት ትምህርት፤ 1ኛ መደበኛ ሰዋስውን ማስተማር ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ተማሪዎችን በቋንቋው ትምህርት ስኬታማ ለማድረግ የሚቻለው ሰዋስውን በማስተማር ነው፤ የሚል መነሻ ሀሳብ የያዘ ነበር፡፡ 2ኛ የቋንቋውን ዋና ዋናና ንዑሳን ክሂሎች ነጣጥሎ የሚያቀርብ ነበር፤ ንባብ፣ የእጅ ፅህፈት፣ የቃል ፅሕፈት፣ ሰዋስውና የፈጠራ ጽሑፍ በተናጠል ለየራሳቸው ክፍለ ጊዜ ተመድቦላቸው የቀረቡ ነበሩ፡፡ ይህ ሥርዓተ ትምህርት የ፩ኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ እስከ ተቀየረበት እስከ 1951 (እ.ኤ.አ.) ድረስ አገልግሏል (ተስፋዬና ታይለር 1976)፡፡

የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ተቀርፆ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገው እ.ኤ.አ. በ1944 ዓ.ም ነው፡፡ ይህም እንደ አንደኛ ደረጃው ሁሉ ለመደበኛ ሰዋስው፣ የበለጠ ትኩረት የሰጠ ነበር (ተስፋዬና ታይለር 1976)፡፡ ይህ ሥርዓተ ትምህርት በ1956 ዓ.ም ተሻሽሎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ እንደ ተስፋዬና ታይለር (1976) ግምገማ፣ ፈቃደ (1999)ም እንደሚጋሩት ተሻሽሎ የወጣው ሥርዓተ ትምህርት ከቀዳሚው ጋር ሲነፃፀር፤ 1. የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች ተካተውበታል፡፡ 2. ከቀዳሚው ሥርዓት ትምህርት በተለየ ሁኔታ ይኸኛው ስለቋንቋ ማብራሪያ ያቀረበ፣ የተለያዩ የትምህርት ርዕሶችን/ ይዘቶችን ለምንና እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ሀሳቦችንና ምሳሌዎችን የሚሰጥ ነው፡፡ በቀጣዮቹ ዓመታት የተዘጋጁት የሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ ሰነዶች ውስጥም እንዲህ ያሉ ማብራሪያዎችና ሀሳቦች እየተጨመረባቸው እስከ 1960ዎቹ (እ.ኤ.አ.) መጨረሻ አካባቢ ድረስ አገልግለዋል (ተስፋዬና ታይለር 1976፣ ፈቃደ1999)፡፡

በ1956 (እ.ኤ.አ.) እንደገና ተሻሽሎ ከወጣውና እስከ 1960ዎቹ መጨረሻ ካገለገለው ሥርዓተ ትምህርት ተስፋዬና ታይለር (1976) ቀጥሎ የመጡት በጎብረተሰባዊነት

ፍልስፍና የተቃኙና ከ1968-1986 (እ.ኢ.አ.) ያገለገሉት ሥርዓተ ትምህርቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ተነድፈው የነበሩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች፣ ሥርዓተ ትምህርቶችና በሥርዓተ ትምህርቶቹ መሠረት የተዘጋጁት የመማሪያ መፃሕፍት የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ በማሳደግ ረገድ የተጫወቱት ሚና ከዚህ ግባ የሚባል አይደለም (ዮናስ 1999፣ ፈቃደ 1999፣)፡፡ ብዙዎቹ ስለዚህ ዘመን ሥርዓተ ትምህርት ዓላማዎች፣ መርሐ ትምህርቶችና የመማሪያ መጻሕፍት፣ እንዲሁም መምህራንና ተማሪዎች በሥርዓተ ትምህርት መሣሪያዎቹ ላይ ያላቸውን አመለካከት ያጠኑ ሰዎች የቋነቋው ሥርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች ቋንቋን በማስተማር ረገድ ብቃት የሌላቸው ናቸው፣ የተዘጋጁትም ቋንቋን በዋናነት ሳይሆን ‹‹እግረ መንገዳቸውን›› እንዲያስተምሩ ነው የሚል ማጠቃለያ ላይ የደረሱ ናቸው፡፡

እ.ኢ.አ በ1986 አዲስ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ እንዲሁም በ1995 ዓ.ም አዲስ ህገ መንግሥትና የቋንቋ ፖሊሲ ሲወጣ፣ እነዚህ ሥርዓተ ትምህርቶችና የመማሪያ መጻሕፍት በሌላ ሥርዓተ ትምህርትና የመማሪያ መጻሕፍት እንዲተኩ ተደርገዋል፡፡ የቋንቋ ፖሊሲው ከልሳነ ዋህድ ወደ ልሳነ ብዙ የተለወጠ በመሆኑ አማርኛ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ቋንቋዎችም በሚነገሩበት አካባቢ የትምህርት፣ የአስተዳደር፣ የችሎትና የሚዲያ ቋንቋዎች እንዲሆኑ የሚያበረታታ ነው (ጌታቸውና ደርብ 2006)፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ ቦታ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ደርግ ዘመን ከነበሩት ጊዜያት የተለየ ሆኗል፡፡ የወል መግባቢያነቱና የሀገሪቱ መንግሥት የሥራ ቋንቋነቱ እንዳለ ቢቀጥልም ክልሎች የራሳቸውን የሥራ ቋንቋ የመወሰን መብት በሕገ መንግሥቱ ስለተፈቀደላቸው አማርኛ በመላው ሀገሪቱ ይሰጥ በነበረው አገልግሎቱ አልቀጠለም፡፡ በዚሁ መሠረት የፌድራል/ የማዕከላዊ መንግሥቱ፣ የአራት ክልሎች፣ የአዲስ አበባና የድሬደዋ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ማገልገሉን ሲቀጥል የቀሩት ክልሎች ሌሎች ቋንቋዎችን መርጠው እየተጠቀሙ ነው (ጌታቸውና ደርብ 2006)፡፡

በትምህርት መስክም በአጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው (1986) መሠረት የአማርኛ ቋንቋ እንደ ቀደሙት ዘመናት በመላው የሀገሪቱ ትምህርት ቤቶች የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ ቋንቋነቱ አልቀጠለም፡፡ በእርግጥ ቀደም ብለው በተጠቀሱት ክልሎች፣ በአዲስ አበባና ድሬደዋ እንዲሁም በሌሎች ክልሎች አንዳንድ ከተሞች

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማስተማሪያ ቋንቋ እንደሆነ ቀጥሏል። በትምህርት አይነትነት ደግሞ በተወሰኑ ክልሎችና ከተሞች ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ የሚሰጥ ሲሆን በሌሎች ክልሎች በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ገፅ 13 ላይ ‹‹በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደርገው ግንኙነት የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት ይሰጣል›› ተብሎ በተገለፀው መሰረት በአንዳንዳቹ ከአንደኛ (ለምሳሌ በአፋር) በአንዳንዶቹ ደግሞ ከሦስተኛ (ለምሳሌ በትግራይ፣ በአንዳንዶቹ ከአምስተኛ (ለምሳሌ በኦሮሚያ) ክፍል ጀምሮ ይሰጣል። የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው እንደ እንግሊዝኛው የአማርኛ ትምህርት በየትኛው ክፍል ላይ መጀመር እንዳለበት አለመግለጹ በየክልሎቹ ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖር ያደረገ ይመስላል። ይህም በየክልሉ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ተመሳሳይ ችሎታ እንዳያዳብሩ ሊያደርግ ይችላል።

በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው መሠረትም የተገለፀውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግሉ መርሐ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል። የአንደኛ ደረጃዎቹም ሆኑ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃዎቹ መርሐ ትምህርቶችና የመማሪያ መጻሕፍቱ አዘገጃጀት ተግባቦታዊ የቋንቋ ችሎታን በማስተማር ላይ ያተኮረ ነው። በምዕራፍ አራት በሰጠረዥ 4.1 ከቀረበው መረጃ ማስተዋል እንደሚቻለው፣ በመርሐ ትምህርቶቹም ሆነ በመማሪያ መጻሕፍቱ ለዋና ዋናና ንዑሳን የቋንቋው ክሂሎች ተገቢ ቦታ ለመስጠት ተሞክሯል ማለት ይቻላል። በመሆኑም ከቀደሙት ይልቅ እነዚህኛዎቹ የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያ አዘገጃጀት ሂደትን የተከተሉ ይመስላሉ። እንደ ቀዳሚዎቹ የቋንቋውን ትምህርት በእግረ መንገድነት አላቀረቡም። ሆኖም ቀደም ብለው የተጠቀሱት የፊቃደ (1999)፣ የዮናስ (1999) እና ሌሎች በቀዳሚው ሥርዓተ ትምህርት ምክንያት የተፈጠሩ ናቸው ተብለው የተገመቱት ችግሮች ወይም ጥሩ የቋንቋ ችሎታ ያላቸውን ወጣቶች ያለማፍራት ሁኔታ አሁንም ተጠናክሮ እንደቀጠለ የተለያዩ ጥናቶች እያሳዩ ነው። ለምሳሌ ብዙ የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ያረጋገጡት በዚህ ሥርዓተ ትምህርት ያለፉ አብዛኞቹ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ከመቼውም ጊዜ በላይ ደካማ እየሆነ መምጣቱን ነው። ለዚህ ችግር መከሰት አንዱ መንስኤ የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርት ሥርዓቱ ላይ የሚያሳድረው

አሉታዊ ወሽባክ/ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል የሚለው ግንዛቤ የመነጨው እንዲህ ካሉ ችግሮች ነው።።

2.3 የቋንቋና የአማርኛ ፈተና ታሪካዊ ዕድገት

Brown (1996)፣ Spolsky (1979)ንና Himfotis (1981) በመጥቀስ እንዲሁም Miyata and Langham(2000፣ Oller (1979) ፣ Weir(1990) እንደሚያስረዱት የቋንቋ ፈተና ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማርና መፈተን ስልቶች ተቀባይነት እያገኙ ከመምጣታቸው በፊት ሦስት የተለያዩ የእድገት ደረጃዎችን አልፏል።። ከነዚህ ቀዳሚውና ከሰዋስው ወትርጉም (Grammar-Translation) ቋንቋን የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ ጋር ተዛምዶ የነበረው ቅድመ ሳይንስ (Pre-Scientific stage) የሚባለው የፈተና ስልት ነው።። ለብዙ ዘመናት ያገለገለና እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድረስ በስፋት ሲሠራበት የነበረ ስልት ነው (Baker 1989,29):: ይዘጋጅ የነበረውም በመምህራን ሲሆን መምህራኑ የተለያየ የአፈታተን ዘዴዎች ዕውቀት ስላልነበራቸው ፈተናዎቹ በጽሑፍ የሚመለሱ /ሳቭጀክቲቭ የሆኑ፣ አስተማማኝነትና አግባብነት ያልነበራቸው ነበሩ።። እንዲለኩ የሚጠበቅባቸውም የትርጉምና የመጻፍ ችሎታን ሲሆን በጊዜው ይሰራበት የነበረውም በጽሑፍ (Essay) የሚመለስ የአጠያየቅ ዘዴ ነበር (Miyata and Langham 2000፣ Oller 1979፣ Weir1990)።።

ቀጣዩና ከ1940ዎቹ--1960ዎቹ ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው የሳይኮሜትሪክ-መዋቅራውያን የቋንቋ ፈተና ስልት ነው።። ከመዋቅራውያን የቋንቋ አላባዎችን እየነጣጠሉ መፈተን፣ ከሳይኮሜትሪክ አኳያ ደግሞ ምርጫ-ሰጭ /ዝግ/ አብጀክቲቭና አስተማማኝ የፈተና ዘዴዎች መንጭተዋል (Miyata and Langham 2000):: በዚህም የተነሳ ይህ ዘመን የቋንቋ ፈተናዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይንሳዊ መርሆዎችን መከተል የጀመሩበትና ዝግጅታቸው ከመምህራን ወደ የሰለጠኑ የቋንቋና የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች የተሸጋገረበት ነው (Brown 1996)።። ከመነጨበት የሥነ-ልሳን ቲዎሪ ተፅዕኖ የተነሳ የቋንቋ አላባውያንን ነጣጥሎ መፈተን፤ ዐውዳዊ አለማድረግ፤ ለቋንቋ አጠቃቀም ትኩረት አለመስጠት የዚህ ዘመን ፈተናዎች ባሕርይ ነው (Baker 1989,):: በዚህም የተነሳ "ቋንቋ ከአላባዎቹ ድምር ውጤት በላይ ነው" (Oller 1979)፣ ይህ የፈተና ስልት ለነባራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ሁናቴዎች፣ ለዐውድ፣ ለቋንቋ

ተግባቦታዊ ገፅታዎች ትኩረት የማይሰጥ የአፈታተን ስልት ነው፤ የቋንቋ ችሎታ በሥነ-ልሳናዊ ዕውቀት ብቻ የሚመዘን አይደለም፤ የሚሉ ትችቶች ተነስተውበታል (Baker 1989፣ Brown 1996፣ Weir 1990)። በመሆኑም ይህ አይነት አካሄድ ቀስ በቀስ ቦታውን ለመልቀቅ ተገዷል።

ሦስተኛው፣ በWeir (1990) **የሥነ-ልቦናዊ ሥነ-ልሳናዊ---ማህበረ ሥነ-ልሳናዊ ዘመን** ተብሎ የተጠቀሰው ውሁዳዊ የቋንቋ ፈተና ስልት ነው። ይህ ስልት በቀዳሚው ስልት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የነበረውን ነጣጥሎ የመፈተን ስልት ተቃውሞ የተነሳ በመሆኑ የተለያዩ የቋንቋ ችሎታዎችን ባንድ ጊዜ ለመመዘን የሚሞክር አተያይ ነው (Oller 1979)። ለዚህም የቃል ጽሕፈትንና ክሎዝ ቴስትን (Cloze test) ተመራጭ የቋንቋ ችሎታን አዋህዶ መመዘኛ ስልቶች አድርጎ ወስዷል(Miyata and Langham 2000፣ Oller 1979፣ Weir1990):: ሆኖም ይህም ስልት ብዙም ሳይቆይ ተግባቦታዊ የቋንቋ ችሎታን ለመገምገም የሚያስችል አይደለም፤ የሚል ትችት ተነስቶበታል። Weir(1990) የተለያዩ ተመራማሪዎችን ጥናቶች ጠቅሰው እንደገለጹት **በሥነ-ልቦናዊ ሥነ-ልሳን አተያይ ቋንቋ ተለዋዋጭ፣ ፈጠራ ያለበት፣ የሚተገበር** ሥርዓት ያለው ነው_ ከተግባቦት ተነጥሎ የሚታይ ሥነ-ልሳናዊ አሀድ አይደለም። **ከማህበራዊ ሥነ-ልሳን** አስተዋፅኦ አንጻርም ተግባቦታዊ **የቋንቋ** ችሎታ ቾምስኪ የቋንቋ ብቃት (competence) ከሚሉት የሰፋ ነው_ የቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት ብቻ አይደለም። ኮምፒተንስ እነዚህን የቋንቋ ህግጋት በአግባቡ በተለያዩ ዐውዶች መጠቀም መቻልም ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ ክሎዝ ቴስትና የቃል ጽሕፈት እንዲህ ያሉትን የቋንቋ ችሎታዎች ለመለካት የሚያስችሉ ሆነው አልተገኙም። በውሁዳዊ የፈተና ስልትና ዘዴዎች እርካታ መታጣቱም እስካሁን ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ ለመጣው **ተግባቦታዊ የቋንቋ ፈተና ስልት** ብቅ ማለት አስተዋጽኦ አበርክቷል።

ከሦስቱ የቋንቋ ፈተና ስልቶች በኋላ የመጣውና ከፍተኛ ተቀባይነት ማግኘት የቻለው ተግባቦታዊ የቋንቋ ፈተና ስልት ነው። ከተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ስልት ጋር ተያይዞ እያደገ የመጣ ስልት ነው። በቀዳሚው አንቀጽ የተገለጹት **የሥነ-ልቦናዊ ሥነ-ልሳንና የማህበራዊ ሥነ-ልሳን** አስተዋፅኦዎች በተግባር በፈተናዎች ዝግጅት ሂደት ትኩረት ማግኘት የቻሉት በዚህ ጊዜ ነው። ይህ ስልት ከቀዳሚዎቹ የሚለየውም

በዋነኛነት በዚሁ ለቋንቋ ተግባቦታዊ ገጽታዎች/ ለቋንቋ ዋና ዋናና ንዑሳን ክሂሎች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት በመቻሉ ነው። እንደ Brown (2007)፣ Fulcher እና Davidson (2007)፣ Weir (1990) በዚህ ረገድ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው የHymes (1972፣ 1967) አስተዋጽኦ ነው። የማህበራዊ ሥነ-ልሳን ተመራማሪ የሆኑት Hymes፣ የChomsky (1965) የቋንቋ ብቃት (ኮምፒተንስ) ሰፋ ያለ ትርጉም እንዲይዝ አድርገውታል። ከእኒህ ምሁር ቀጥሎ በተግባቦታዊ ቋንቋ ማስተማርና ፈተና ፋና ወጊነት የሚጠቀሰው የCanale እና Swains (1980) ትዎራዊ የቋንቋ ችሎታ ሞዴል ነው (Fulcher እና Davidson 2007)። ከዚህ ሞደል በፊት በቋንቋ ፈተናም ሆነ ማስተማር በሥነ-ልሳን ችሎታ ላይ ከማተኮር መውጣት አልቻሉም ነበር። የቋንቋ ችሎታን ከቋንቋ አጠቃቀም/ ክሂሎች አንጻር የማየት ሰፊ በር የተከፈተው በዚህ ጥናት ነው። በዚህ ጥናት አዲስ አተያይ መሰረትም ተግባቦታዊ ብቃት (ኮምፒተንስ) ሰዋስዋዊ ኮምፒተንስ፣ የዲስኩር ኮምፒተንስ፣ ማህበረ-ሥነ-ልሳናዊ ኮምፒተንስና ስትራቴጂዊ ኮምፒተንስ የሚባሉ አራት አላባዎች (Components) አሉት (Brown 2007፣ Fulcher እና Davidson 2007፣ Weir 1990)። እያንዳንዳቸው የራሳቸው ይዘቶችና ወሰኖች አሏቸው።

ይህን ሞዴል መነሻ በማድረግ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘ ሌላ የተግባቦታዊ የቋንቋ ሞዴል ያዳበሩት Bachman (1990) ናቸው (Brown 2007፣Weir 1990)። ሞዴሉን የሰየሙት የቋንቋ ኮምፒተንስ በሚል ርዕስ ነው። ከእሳቸው በኋላም ሌሎች ሙከራዎች ተደረገዋል። ለምሳሌ፣ Alderson(2000) የBachman (1990) አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ሞዴልን መሰረት በማድረግ የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ሞዴል ለማዳበር ሞክረዋል። በቀዳሚው ምዕራፍ እንደተጠቆመው በዚህ ጥናት እነዚህን የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት ሞዴሎች ለጥናቱ ከተመረጡት የወሽባክ ሞዴሎች ጋር በማቀናጀት ለመጠቀም ተሞክሯል።

በኢትዮጵያም የMadson(1976) ጥናት እንደሚያሳየው የአማርኛ ቋንቋን ጨምሮ በሀገሪቱ የቋንቋ ፈተና ሥርዓት የምዕራባውያን የፈተና ሥርዓት ከፍተኛ ተፅዕኖ የነገሰበት ነው። ከሳቸው ጥናት በኋላ ከዚህ ዓይነት ተፅዕኖ ለመውጣት የተደረገ ጥረት መኖሩን የሚያሳይ ጥናት የለም። ምንም እንኳ ከ1500 ዓመታት በላይ

በሀገሪቱ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲመራ የነበረ የመደበኛ ትምህርት ሥርዓትና የግምገማ ስልት የነበረ ቢሆንም (Madson 1976፣ አዳነ 1993) ከዚህ የምዘና ስልት የተወሰደ ልምድ እንደሌለ የእነዚህ ሁለት ምሁራን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ Madson (1976) እንደሚሉት፣ ለብዙ ዘመናት በቤተ ክህነት እየተመራ በቆየው መደበኛ ትምህርት ይካሄድ የነበረው የግምገማ ሥርዓት በየትምህርት ቤቶቹ መደበኛ ፈተናና ሌሎች የሚፈለገው የባህርይ ለውጥ መምጣቱ የሚረጋገጥባቸው የምልከታ ስልቶች ነበሩ፡፡ በእርግጥ የምዘና ስልቶቹ ጥልቅ የሆነ የሽምደዳና የማስተዋል ችሎታን የሚለኩ ነበሩ፡፡ ፈተናዎቹ የሚዘጋጁትና የሚሰጡትም በየትምህርት ቤቶቹ መርጌቶች ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የአውሮፓውያን የፈተና ሥርዓቶች ባለፈው ምዕተ ዓመት የመጀመሪያ ሁለት አሰርት ዓመታት በዳግማዊ ምንይልክ ዘመን ከዘመናዊ ትምህርት ቤት መከፈት ጋር አብረው ገብተዋል (Madson 1976)፡፡ ከነፃነት በኋላ ደግሞ በየትምህርት ቤቶቹ የሚሰጠው ትምህርት ደረጃውን የጠበቀ ይሁን አይሁን የሚረጋገጥበት መንገድ ስላልነበረ የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን የካቲት 2 ቀን 1944 ዓ.ም አማርኛ፣ እንግሊዝኛና ሂሳብ የተካተቱበት የ፩ኛ ደረጃ ትምህርት መልቀቂያ ፈተና እንዲሰጥ ሐሳብ ለማቅረብ ተገፋፍተዋል(Madson 1976)፡፡ ይህም ሐሳብ ለመጀመሪያው የብሔራዊ ፈተና ተግባራዊ መሆን በመነሻነት አገልግሏል፡፡ ከዚህም በትምህርት ሥርዓቱ ብቻ ሳይሆን በብሄራዊ ፈተናነት በመካተትም ከቀዳሚዎቹ ሦስት የትምህርት አይነቶች አንዱ አማርኛ እንደነበረ መረዳት ይቻላል፡፡ ለሁለት አሰርት ዓመታት አካባቢ የስድስተኛና የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናዎችን ሲያዘጋጅና ሲያስተዳድር የነበረውም በትምህርት ሚኒስቴር የፈተናና ምዘና ክፍል ነው (Madson 1976)፡፡

ከስድስተኛና ከስምንተኛ ክፍል በተጨማሪ ሌላው በብሔራዊ ደረጃ ይዘጋጅ የነበረው የኢትዮጵያ ፪ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በሚል ስያሜ ይታወቅ የነበረው የ12ኛ ክፍል ፈተና ነው፡፡ ይህ ፈተና የ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ከእንግሊዝ ሀገር ትምህርት ጋር በነበረው ግንኙነት ምክንያት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናን ጨምሮ እንዲዘጋጅ የተደረገው በእንግሊዝ ዩንቨርሲቲዎች ነበር (Madson 1976)፡፡ ከዚህ

ገለጻ የኢትዮጵያ ትምህርት የምዘና ሥርዓት ምን ያህል በአውሮፓውያኑ ስልት ተፅዕኖ ስር እንደወደቀና ከሀገር በቀሉ ስልት ምንም ዓይነት ልምድ ሳይወሰድ እንደተሰደደ መገንዘብ ይቻላል።

የዚህ ፈተና ዝግጅት ከነፃነት (ከጣሊያን ሽንፈት) በኋላ ወደ ሀገር ቤት እንዲዛወር ተደርጓል። ከተዛወረ በኋላ እንዲዘጋጅ የተደረገው በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን የየትምህርት ዘርፉ ባለሙያዎች ነው። በዚህ ጊዜ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና እንዲቀርብ የተደረገው በአብዛኛው በጽሑፍ ፈተናነት ነበር። የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በጽሑፍ ከሚመለስ ስልት ወደ ምርጫ ጥያቄዎች የተለወጠውም ቀስ በቀስ ነው። በለውጡም፣ መጀመሪያ የተደረገው ሁለቱም ዓይነት የአጠያየቅ ስልቶች እንዲካተቱበት ነበር (Madson 1976)።

በእነዚህ ጊዜያት ይሰጥ የነበረው የአማርኛ ብሔራዊ ፈተና ያካትታቸው የነበሩት ይዘቶች ድርሰት፣ **አህፅሮተ ጽሑፍ፣ አንብቦ መረዳት፣ ሰዋሰውና ቃላት** ነበሩ። በጊዜው ይዘጋጅ የነበረው የሦስት ሰዓት ፈተና ሲሆን 45ቱ ደቂቃ ለድርሰት መጻፊያ የሚሰጥ ነበር። የአንብቦ መረዳት ክፍሉ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ አንድ ረጅምና ተፈታኞችን ሊፈታተን የሚችል ምንባብ ይይዛል። ተፈታኞቹም ምንባቡን ተከትለው ለሚቀርቡት ተከታታይ በጽሑፍ የሚመለሱ ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። የቀሩት የሰዋስውና የቃላት ክፍል ናቸው። እነዚህኛዎቹ አብዛኛውን ጊዜ ምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች ናቸው። ከ10-20 የሚደርሱ ጥያቄዎች ይቀርቡባቸው ነበር (Madson 1976)።

ከዚህም በዚያ ዘመን ፈተናውን ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር ለማዛመድ ወይም የሥርዓተ ትምህርቱ ነጸብራቅ እንዲሆን ለማድረግ ምን ያህል ጥረት ይደረግ እንደነበረ፣ ቀደም ሲል የቋንቋ ትምህርት ታሪክ ከተቃኘበት ክፍል ጋር በማገናዘብ መረዳቱ አይከብድም።

መኮንን (1968) ጠቅሰው Madson (1976) እንደገለፁት በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ላይ የአሜሪካ የትምህርት ባለሙዎች ተፅዕኖ እየጨመረ ሲመጣ የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ በጽሑፍ የመመለስ ሥርዓት ይከተል የነበረውን የ፪ኛ ደረጃ መልቀቂያ

ፈተና ወደ ምርጫ ሰጭ አጠያየቅ/ አብጀክቲቭነት እንዲቀየር አድርጎታል። በጽሑፍ ከሚመለስ / ከሳብጀክቲቭነት ወደ ምርጫ ሰጭ /አብጀክቲቭነት የመቀየሩን ሂደት አያሌ አውሮፓውያንና ኢትዮጵያዊያን ቢቃወሙትም ወደነበረበት የአፈታተን መንገድ እንደገና እንዲመለስ ሳይደረግ ቀርቷል። ከዚህ በተጨማሪ Madson (1976፣ 493) በማጠቃለያቸው ‹‹ብዛት ያላቸው የቋንቋ ኤክስፐርቶች በኢትዮጵያ እየተዘጋጁ ያሉት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ብሔራዊ የቋንቋ ፈተናዎች [አማርኛና እንግሊዝኛን ይመለከታል] የሚጠበቀውን የአግባብነትና አስተማማኝነት ደረጃ ማሟላት እንዳልቻሉ እየገለጹ ስለሆነ የግድ መሻሻል ይኖርባቸዋል›› የሚል አስተያየት ሰጥተው የነበረ ቢሆንም በተሰጠው አስተያየት መሰረት ባለፉት ጊዜያት ፈተናዎቹ በተሻለ ደረጃ የጥሩ ፈተና ባሕርያት የሚንጸባረቅባቸውና አዎንታዊ ወሽባክን የሚያበረታቱ እንዲሆኑ የተደረገ ጥረት መኖሩን የሚያሳይ ምንም ሰነድ አልተገኘም። እንዲያውም የአማርኛ ፈተና ከነበረበት የጽሑፍና የዝግ/ አብጀክቲቭ ጥያቄ አይነትነት ሙሉ በሙሉ ወደ ምርጫ ሰጭነት /አብጀክቲቭነት አንዲቀየር ነው የተደረገው። ይህም በፈተናው ይካተቱ የነበሩ መሰረታዊ የመጻፍ ክሂሎች እንዳይመዘኑ ያደረገ አሉታዊ ሚና እንዲጫወት አድርጎታል። ከዚያ በኋላም በቀድሞዎቹ ፈተናዎች ትኩረት ይሰጣቸው የነበሩትና ኋላም በተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርትና ፈተና አስተሳሰብ ይበልጥ ተቀባይነት እያገኙ የመጡት (Brown 2004፣ Weir 1990) የጽሑፍ ፈተናዎች (ድርሰት፣ አሕጽሮተ ጽሕፈት፣ ወዘተ.) በኢትዮጵያ ትምህርት የፈተና ሥርዓት እንደዋዛ እንደወጡ ቀርተዋል። በዚያን ጊዜ በአሜሪካ የትምህርት ሥርዓት ሰፊ ተቀባይነት የነበረው የምርጫ ፈተና የነበረውን ተቀባይነት እያጣ መጥቶ አሁን አሁን በራሷ በአሜሪካ ስለ እውናዊ (Authentic) ፈተና፣ ክወና (Performance) ተኮር ምዘና ወዘተ እየተዘመረና ተግባራዊ እየተደረገ ቢመጣም በኢትዮጵያ ቀድሞ የነበረው በጽሑፍ የመመለስ የቋንቋ ፈተና አጠያየቅ ስልት በቀዳሚው ዐረፍተ ነገር እንደተገለጸው እንደዋዛ (ያለ ጥናትና ያለ በቂ ምክንያት) እንደወጣ እንደቀረ ነው። በብዙ ሀገሮች (ለምሳሌ በቦትስዋና፣ ሆንግ ኮንግ፤ እስራኤል) እየተደረገ እንዳለው የጽሑፍ ፈተና ከምርጫ ፈተና ጋር አብሮ የሚካተትበትን መንገድ ለመፈለግ የሚደረግ መነሳሳት/ ጥረት ስለመኖሩም ተጨባጭ መረጃ የለም። ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው የትምህርት ፖሊሲው፣ የሥርዓተ

ትምህርት ማስፈጸሚያ ማዕቀፉና የቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት የተመሰረቱባቸውን የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት መርሆዎች የሚያበረታታ/ የሚያንጸባርቅ እንዳይሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡

2.4 በፈተናና በትምህርት ዓላማዎች መካከል ያለ ተጣጥሞሽ/ ዝምድና (Overlapping)

ቀደም ብሎ በተወሰነ ደረጃ እንደተጠቆመው በአንድ የትምህርት ሥርዓት አንዱ የአዎንታዊ ወሽባክ ማበረታቻ ስልት ፈተናዎች ከአጠቃላይ የትምህርት ዓላማ ምድቦች ጋርም ሆነ ከትምህርቱ ዓይነት ሥርዓተ ትምህርት ጋር ተገቢ ዝምድና እንዲኖራቸው ማድረግ መቻል ነው፡፡ ስለዚህ ውጫዊ/ ብሄራዊ ወይም የክፍል ፈተናዎች ከአጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎች ጋርም ሆነ ከትምርቱ ዓይነት ሥርዓተ ትምህርት ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዲኖራቸው ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ፈተናዎች እንዲኖራቸው የሚጠበቀው ተዛምዶ ሁለት አቅጣጫ ያለው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛው ከአጠቃላይ የትምርት ዓላማዎች ጋር ሲሆን ሁለተኛው ከራሱ ከትምህርት ዓይነቱ ዓላማዎች ጋር ነው፡፡ ወደኋላ በዝርዝር እንደተገለጸው፣ በተለይ የምርጫ ፈተና ከሆነ ደግሞ በአጠቃላይ ትምህርት ዓላማነት ከሚታወቁት ሦስት ምድቦች (Domains) መካከል ከአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) ስድስት የትምህርት ዓላማ ክፍሎች/ ችሎታዎች ጋር ፈተናዎች ተገቢ የሚባል ዝምድና እንዲኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በዚህ ጥናት የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ከአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት በተለይም ከአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሐ ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ/ ዝምድና ለመመርመር የሚሞከረው ከሁለቱም ማለትም ከአጠቃላይ ትምህርት አዕምሯዊ ምድብ ክፍሎችና ለደረጃው ከተዘጋጁት መርሐ ትምህርቶች ጋር ይሆናል፡፡ ስለዚህ ስለእያንዳንዳቸው ምንነት፣ መሰረታዊ ባህርያትና ከፈተና ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት የተወሰኑ ነጥቦችን እያነሳን መመልከት ይኖርብናል፡፡ በመሆኑም መጀመሪያ ስለአጠቃላይ አዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎችና ፈተና ግንኙነት ቀጥሎ የቋንቋ ትምህርትና ፈተና ዝምድና ይቀርባል፡፡

2.4.1 የአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) ክፍሎች ዓላማዎች/ ችሎታዎችና የፈተና ተጣጥሞሽ (Overlapping)

ቀደም ብሎ እንደተወሳው በመደበኛ ትምህርት የክፍልም ሆነ የማጠናቀቂያ (public) ፈተናዎች የሚዘጋጁት በአብዛኛው የትምህርት ዓላማዎች ምን ያህል እንደተሳኩ /ለስኬት እንደበቁ ለማረጋገጥ ነው። በአጠቃላይ ትምህርት መስክ ምሁራን በተለይም በምዘናና ግምገማ (measurement and evaluation)፣ በሥርዓተ ትምህርትና መሰል መስኮች ባለሙያዎች ተደጋግሞ እንደሚገለፀው መደበኛ ትምህርትን መሰረት የሚያደርግ ምዘና በተለይም የችሎታ መለኪያ ፈተና ሲዘጋጅ የትምህርትን ባሕርያዊ ዓላማዎች (Taxonomy of behavioral objectives) (ከትምህርት ዓይነቱ ዓላማ ምድቦች በተጨማሪ ማለት ነው) ማንፀባረቅ ይኖርበታል (ደሳለኝ 2005)። በዚህ ረገድ በተለያዩ ምሁራን (ለምሳሌ አበበ 1990፣ Ebel 1979፤ Gronlund 1976፤ሙሉና ዳንኤል 2005፤ Munzenaier እና Rubin፣ 2013፣ Rani እና ሌሎች 2004፤ Sax 1974) እንደተገለፀው ዋነኛው የመማር ታላሚ/ተጠባቂ ውጤቶችን (Learning outcomes) ለመለካት የሚያገለግለውና ለብዙ ዓመታት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ሰፊ ተቀባይነት እንዳገኘ የቀጠለው Bloom እና ባልደረቦቻቸው ያዳበሩት አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማዎች ምድብ (cognitive domain) የሚባለው ማዕቀፍ (framework) ነው።

ዘግየት ብሎ ደግሞ አመለካከታዊ (affective) እና ክውን አካላዊ (psychomotor) የሚባሉት ምድቦች ዳብረዋል። ከሦስቱ የትምህርት ዓላማ ምድቦች ቀዳሚውና መሰረታዊ የትምህርት ጉዳይ ተደርጎ የሚወሰደው የBloom (1956) አዕምሯዊ ምድብ እንደሆነም Ebel (1979) እንዲሁም ሙሉ እና ዳንኤል 2005) ያስረዳሉ:: አዕምሯዊ ምድብ የሚባለው የዕውቀት፣ የማስታወስና የማሰብ ችሎታን በማዳበር ላይ የሚያተኩር ነው። አዕምሯዊ ምድብ ከተራ ማስታወስ እስከ ውስብስብ ግምገማ የሚደርሱ በመማር የሚመጡ የማሰብ ችሎታ ክሂሎች (intellectual skills) ተዋረዳዊ (hierarchical) እድገቶች የተካተቱበት ነው (Sax፣ 1974)። በሌላ አገላለፅ አዕምሯዊ ምድብ አዕምሯዊ ክሂሎችን (mental skills) በማዳበር ላይ የተመሰረተ የትምህርት ዓላማ ምድብ ነው ማለት ይቻላል። ይህ አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማ ምድብ

ለማስተማር፣ ለመማርና ለግምገማ መሰረት ሆኖ የሚያገለግል ነው (Munzenmaier እና Rubin፣ 2013)። ምድቡ በውስጡ ዕውቀት፣ ግንዛቤ፣ ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ የሚባሉ ስድስት መሰረታዊ ክፍሎች (categories) የተካተቱበት ሲሆን ክፍፍሉም ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተራ ወደ ውስብስብነት እያደገ የሚሄድ ነው። በውስብስብነት ደረጃ ተከታዩ ከቀዳሚው ላቅ ያለ ብቻ ሳይሆን በቀዳሚው ላይ የሚመሰረትም ነው። በRani እና ሌሎች (2004) አገላለጽ አንደኛው ለሁለተኛው፣ አንደኛውና ሁለተኛው ደግሞ ለሦስተኛው እንዲሁም ከ1-5 ያሉት ለስድስተኛው ቅድመ ተከዋኞች (prerequisites) ናቸው።

በSax (1974) ጥናት እንደተገለጸው Bloom እና የስራ ባልደረቦቻቸው (1956) እነዚህን የአዕምሯዊ ስድስት ክፍሎች ዓላማዎች በዚህ መንገድ ከፋፍለው ለማቅረብ ከተገፋፉባቸው ምክንያቶች አንዱ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት ሥርዓት በማለፍ በግል ማከናወን ወይም ማሰብ የሚኖርባቸውን የታለሙ ባህሪያት በግልፅ ለማሳየት ነው። የክፍፍሉ ሂደትም የክፍሎችን (የሚገለፁትን ጉዳዮች) ውስጣዊና ውጫዊ (ይፋዊና ስውራዊ) ባህርያት (Implicit and overt behaviors)፣ እንዲሁም የውስብስብነት (complexity) ደረጃ መሰረት ያደረገ ነው። Sax (1974) አክለው እንደገለፁት ተማሪዎች ምን እንደሚማሩ ሳይታወቅ የፈተና ጥያቄንና ምድብን (domain) ለመመርመር መምከር አስቸጋሪ ነው። በነBloom (1956) የተካሄደው የአዕምሯዊ ምድብ ክፍፍል ይህን ችግር ለመፍታት ጠቃሚ ዘዴ ሆኖ ተገኝቷል። ለመምህራንም ከፈተና በፊት ሲያስተምሩ ሊያተኩሩባቸው የሚገቧቸውን ዓላማዎች እንዲያውቁ የሚያስችላቸው ስራ ሆኖ አግኝተውታል። ይህም ሌላው የአዕምሯዊ ትምህርት ዓላማዎችን በተለያዩ ክፍሎችና ደረጃዎች የመመደባቸው ተግባር ውጤት ነው (Sax፣ 1974)።

በተለያዩ የመስኩ ምሁራን፣ በተለይም በMunzenmaier እና Rubin (2013) ስራ በዝርዝር እንደቀረበው Bloom የትምህርት ዓላማዎችን ድልድል (Taxonomy of educational objectives) ለማዳበርና በደረጃ ለመከፋፈል ሲጀምሩ ዋነኛ ዓላማቸው የነበረው የትምህርት ምዘና ባለሙያዎች (experts) ግኝቶቻቸውን (findings) እንዲጋሩና የፈተና ጥያቄዎቻቸውን እንዲቀያየሩ (ሐሳብ እንዲለዋወጡ) የሚያስችል

የጋራ መግባቢያ እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። በዚህ ሐሳብ መነሻነት የዳበረው አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማዎች ክፍፍልም ተቀባይነት አግኝቶ ከ22 በማያንሱ ቋንቋዎች ተተርጉሞ እስከዛሬ ድረስ በዓለማችን የትምህርት ሥርዓት ሰፊ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል:; የመማር ክፍሎች (categories) ገለፃም ሆነ የውስብስብነት ደረጃቸውን የሚያሳየው ተዋረድ (levels of cmplexity) እስካሁን ሰፊ ተቀባይነት እንዳገኘ ነው (Munzenmaier እና Rubin፣ 2013)። አንድ ፈተና አዎንታዊ የመማር ማስተማር ሂደትን ሊያበረታታ የሚችለውም እነዚህን በአዕምሯዊ ምድብ ስር የተካተቱ የመማር ደረጃዎችን በአገናዘበ መልኩ መዘጋጀት ሲችል ነው።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ለማስተማር፣ ለመማርና ለምዘና (ግምገማ) መሰረት ሆኖ እያገለገለ ያለው ይህ የBloom አዕምሯዊ ምድብ (Bloom's cognitive domain) ከመዳበሩ በፊት Bloom ካከናወኗቸው ተግባራት አንዱ የፈተና ጥያቄዎች ትኩረት በምን ላይ እንደሆነ መመርመር ነበር። በምርምራቸውም ከ95% በላይ በፈተናዎች የሚካተቱ ጥያቄዎች ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ ማስታወስ መቻላቸውን የሚለኩ ሆነው አግኝተዋቸዋል (Bloom found that over 95% of the test questions students encounter require them to think only at the lowest possible level the recall of information) የሚለው አገላለፅ ይህን የሚያሳይ ነው። ይህ አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማዎች ድልድል በትምህርት ሥርዓት ትኩረት እያገኘና የማስተማር፣ የመማርና የምዘና ማዕቀፍ እየሆነ ከመጣ ከ40 ዓመት በኋላ ደግሞ ዝቅተኛ የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃን የሚመዝኑ ጥያቄዎች (lower-order assessment questions) መጠን ወደ 70% ዝቅ እንዳለ Bloom ማመልከታቸውን በMunzenmaier እና Rubin (2013) ሥራ ተገልጧል። ይህም ፈተና አዘጋጆች የሚያወጧቸው ጥያቄዎች የተማሪዎችን የማስታወስ ችሎታና ጥልቅ አስተሳሰብ Retentions of knowledge and critical thinking) የሚያካትቱና መካተታቸውን የሚያበረታቱ እየሆኑ መምጣታቸውን የሚያሳይ ነው (Munzenmaier እና Rubin 2013)።

እነዚህ የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓትም በፖሊሲ ደረጃ ሳይቀር ትኩረት ተሰጥቷቸዋል። ስለዚህ በተለይ በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውና

በሥርዓተ ትምህርት ማስፈጸሚያ ማዕቀፉ የተሰጣቸውን ትኩረት በተመለከተ በደምሳሳውም ቢሆን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በፊት ግን የስድስቱን የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች ምንነት፣ መለያ ባሕርይ/ ገፅታና የሚጠቀሙባቸውን መስረታዊ ወይም ቁልፍ ቃላት በአጭር በአጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ሀ. ዕውቀት (Knoweledge)

"ዕውቀት" የሚባለው ችሎታ ከስድስቱ አዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች የመጀመሪያውና ዝቅተኛ የመማር ደረጃን (የመማር ውጤትን) የሚወክል ክፍል (category) ነው፡፡ በዚህ በእውቀት ደረጃ ዓላማ፣ ከተማሪዎች የሚጠበቀው ችሎታ ቀደም ብለው የተማሩትን ማስታወስ መቻል ነው፡፡ እንዲያስታውሱ የሚጠበቀውም የተማሯቸውን እውነታዎች (facts)፣ መረጃዎች፣ መርሆዎች፣ ቲዎሪዎችና መሰል ጉዳዮች ነው፡፡ በዚህ ዝቅተኛ በሚባለው አዕምሯዊ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች መልስ መስጠት እንዲችሉ የሚጠበቅባቸውም ማን፣ ምን፣ መቼ፣ የት፣ ወዴት... ለሚሉት ጥያቄዎች ሲሆን የጥያቄዎቹ አቀራረብም፣ መልሱ፣ ዘርዝሩ፣ አስታውሱ፣ ደግማችሁ ተናገሩ የሚሉ ዓይነት ናቸው((አበበ 1991፣ Gronlund 1976፤ ሙሉና ዳንኤል 2005፣ Munzenmaier እና Robin 2013፣ Sax 1974)፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ደረጃ ከተማሪዎች የሚጠበቀው ችሎታ የተለመዱ ቃላትን፣ የተወሰኑ እውነታዎችን፣ አንዳንድ ዘዴዎችንና ቅደም ተከተሎችን (procedures)፣ መሰረታዊ ፅንሰ ሐሳቦችንና መርሆዎችን ማወቅ መቻል ነው (አበበ 1991፣ Gronlund 1976፤ ሙሉና ዳንኤል 2005፣ Munzenmaier እና Robin 2013፤ Sax 1974):: የዚህ ምድብ ቅድመ ተከውኖ (prerequisite) እስካሁን አይታወቅም (Rani እና ሌሎች 2004)፡፡

ለ.ግንዛቤ (Comprehension)

ግንዛቤ ከዕውቀት ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃነት የሚመጣ ችሎታ ነው፡፡ በአብዛኛው ተማሪው ያዳመጠውን ወይም ያነበበውን (የተላለፈውን መልዕክት) ምን ያህል ተረድቶታል? የሚለውን የሚመለከት ክፍል ነው፡፡ ስለዚህ ከማስታወስ (ከመሸምደድ) አንድ ደረጃ ከፍ ቢልም በዝቅተኛ ችሎታነት የሚመደብ ነው፡፡ እውነታዎችንና

መርሆዎችን፣ ሰንጠረገሮችንና ግራፎችን፣ እንዲሁም የቃላትን ፍቺ መረዳት፣ በቋንቋ (በቃላት) የተገለፀ ሐሳቦችን ወደ ቁጥር መቀየር፣ ከቀረበው መረጃ ተነስቶ ቀጥሎ ሊከሰት የሚችልን ጉዳይ መተንበይ፣ የዘዴዎችንና አሰራሮችን ተገቢነት ወዘተ ማስረዳት መቻል በዚህ በሁለተኛው አዕምሯዊ ምድብ ክፍል እንዲዳብሩ የሚጠበቁ የትምህርት ዓላማዎች ናቸው (አበበ 1990፤ Gronland 1976፤ Monzenmaier እና Rubin 2013፤ Rani እና ሌሎች 2004፤ Sax 1974)።

በዚህ በሁለተኛው አዕምሯዊ ደረጃ በተማሪዎች እንዲመለሱ የሚጠየቁ ጥያቄዎችም የተረዱትን በራሳቸው አባባል መግለፅን፣ እንደገና መጻፍን፣ ምሳሌ መስጠትን፣ መበየንን፣ ጨምቆ ማቅረብን (summarizing)፤ ለምሳሌ በቋንቋ ትምህርት ዋና ዋና ሐሳቦችን ከጽሑፍ ውስጥ መለየት፣ ለቃላት ፍቺ መስጠት፣ ወዘተ. መቻላቸውን የሚያረጋግጡ ዓይነት ናቸው (አበበ 1990፣ Gronlund፣ 1976)::

በተማሪዎች በግንዛቤ ደረጃ እንዲዳብሩ የሚጠበቁ የትምህርት ዓላማዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚሰራባቸው የተለመዱ ቃላት/ ግሶችም አነፃፅሩ፣ አስፋፉ፣ ለዩ፣ አስረዱ፣ በራሳችሁ አባባል ግለፁ፣ ምሳሌ(ዎች) ስጡ፣ እንደገና ጻፉ፣ ተንብዩ የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው (አበበ 1990፤ Gronland 1976፤ Sax 1974)።

ሐ. ትግበራ (Application)

ትግበራ ተማሪዎች የተማሯቸውን ዘዴዎች፣ ፅንሰ ሀሳቦችና መርሆዎች፣ ህጎችና ቲዎሪዎች በሌላ አዳዲስ ሁኔታዎች መጠቀም የመቻል አቅምን/ ወይም ችሎታን/ ደረጃን ማዳበርን የሚመለከት ነው። ከግንዛቤ ከፍ ያለ ችሎታን የሚያመለክት የመማር ውጤት ነው (አበበ 1990፤ Gronlund 1976፤)። በዚህ ደረጃ የሚጠየቁት ጥያቄዎችም ተማሪዎች ጽንሰ ሀሳቦችንና መርሆዎችን በአዳዲስ ነባራዊ ሁኔታዎች ላይ እንዲተገብሩ ወይም መተግበር መቻላቸውን፣ ህጎችንና ቲዎሪዎችን በአዳዲስ ሁኔታዎች ላይ እንዲጠቀሙ ወይም መጠቀም መቻላቸውን፣ ችግሮችን (problems) እንዲፈቱ ወይም መፍታት መቻላቸውን፣ ቻርቶችንና ግራፎችን እንዲሰሩ ወይም መስራት መቻላቸውን፣ የተለያዩ ዘዴዎችን ትክክለኛ አጠቃቀም ሰርተው እንዲያሳዩ

ወይም መስራት መቻላቸውን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ይጠበቃል (አበበ 1990፤ ሙለና ዳንኤል 2005፤ Rani እና ሌሎች 2004)።

በትግበራ ክፍል የሚያገለግሉ የተለመዱ ቃላት ደግሞ ቀይሩ፣ አስሉ፣ ፈልጋችሁ አግኙ፣ አቃኑ፣ አዘጋጁ፣ ሰርታችሁ አሳዩ፣ ተጠቀሙ የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው (Gronland 1976፤ ሙለና ዳንኤል 2005፣ Monzenmair እና Rubin፣ 2013፤ Sax 1974፤)።

መ. ትንተና (Analysis)

ትንተና ከግንዛቤና ከትግበራ ከፍ ያለ አዕምሯዊ ችሎታ ነው። በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ይዘትና የአወቃቀር ቅርጽ በአግባቡ መረዳት፣ እውነታዎችን/ መረጃዎችን መመርመር፣ የአንድን ሙሉ ማቴሪያል ለምሳሌ ጽሑፍ አላባዎች (components) መለየት፣ መከፋፈል እንዲሁም በክፍሎቹ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች መተንተንና ግንኙነቶቹ የተመሰረቱባቸውን መሰረታዊ መርሆዎች መገንዘብ መቻል ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ ችሎታዎች ደግሞ ነገሮችን በጥልቀት መረዳትንና ማገናዘብን የሚጠይቁ ናቸው። ይህም ትንተና ከፍተኛ የማገናዘብ/ የማሰብ ደረጃን የሚወክል ችሎታ መሆኑን ያሳያል። ከቀዳሚዎቹ ከግንዛቤና ከትግበራ ላቅ ያለ አዕምሯዊ ችሎታ ነው (አበበ 1990፤ Grounland 1976፤ ሙለና ዳንኤል 2005፤ Munzenmaier እና Rubin 2013፤ Rani እና ሌሎች 2004)።

በትንተና ክፍል ደረጃ የሚቀርቡ ጥያቄዎችም የተማሪውን በግልፅ ያልቀረቡ ሀሳቦችን መረዳት፣ ተጠየቃዊ (logical) የሆኑና ያልሆኑ ሀሳቦችን /ምክንያቶችን መገንዘብ፣ እውነታዎችን ከአንድምታዎች (inferences) መለየት፣ የመረጃዎችን ተገቢነት መመርመር፣ የአንድን ስራ ለምሳሌ ጽሑፍን መዋቅር፣ አደረጃጀት፣ ወዘተ መተንተን፣ ውስጣዊ አወቃቀርን መፈለግ፣ ገፋፊ ምክንያቶችን መለየት፣ የአንድን ነገር አላባዎች (elements) መለየትና መከፋፈል መቻል የሚጠይቁ ናቸው (አበበ 1990፤ Grounland 1976)።

በትንተና ክፍል ብዙ ጊዜ የሚሰራባቸው ቁልፍ ቃላትም ተንትኑ፣ ከፋፍሉ፣ ለዩ፣ አንድምታውን ግለፁ፣ ቢጋር ንደፉ፣ አመልክቱ፣ አዛምዱ፣ በየክፍላቸው መድቡ

የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው (Gronland 1976፤ ሙሉና ዳንኤል 2005፤ Monzenmair እና Robin፣ 2013፤ Rani እና ሌሎች 2004፤ Sax 1974)።

ሠ. ቅንበራ (Synthesis)

"ቅንበራ" የፈጠራ ባሕርያትን በማዳበር ላይ የሚያተኩር አዕምሯዊ ችሎታ ነው። በመሆኑም በከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታነት ይገለፃል። አዳዲስ ንድፎችን፣ አደረጃጀቶችን፣ ዕቅዶችን ወዘተ መቀመር በቅንበራ ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው የትምህርት ዓላማዎች ናቸው። ስለዚህ ቅንበራ ከትንተና በተለየ መልኩ አዲስና ሙሉ ነገር ለማዋቀር /ለመስራት፣ የአንድን ነገር ወይም ጉዳይ የተለያዩ ክፍሎች አቀናጅቶ ወደ አንድ ሙሉ ነገር ማምጣትን፣ የተፈታቱ ነገሮችን መልሶ መግጠምን (መገንባትን)፣ ማዋቀርን፣ አዳዲስ ተግባቦትን ለምሳሌ የንግግር ጭብጥ ወዘተ ማፍለቅን፣ ምርምር ማካሄድን፣ የምርምር ንድፍ ማዘጋጀትን፣ ወዘተ ተማሪዎች የሚለማመዱበት የአዕምሯዊ ትምህርት ክፍል ነው (አበበ 1990፣ Grounland 1976፣ Rani እና ሌሎች 2004)።

በአጠቃላይ በዚህ በነBloom አዕምሯዊ ምድብ በአምስተኛ ደረጃነት በቀረበው ቅንበራ በሚባለው ክፍል ከተማሪው ተጠባቂ የመማር ውጤቶች (learning outcomes) ትኩረት፣ ከዕውቀት እስከ ትንተና ባሉት ደረጃዎች ያዳበሯቸውን ችሎታዎች መሰረት በማድረግ የፈጠራ ባህርያትን በተለይም አዳዲስ ንድፎችንና አወቃቀሮችን፣ አዳዲስ ሐሳቦችን፣ ወዘተ. የማመንጨት፣ ዕቅድ የመንደፍና የመሳሰሉትን ችሎታዎች ማዳበር ነው (ሙለና ዳንኤል 2005፣ Rani እና ሌሎች 2004)። ይህም የቅንበራ ደረጃ ከቀዳሚዎቹ ጋር ሲነፃፀር ውስብስብነቱ ላቅ ያለ/ ጠለቅ ያለ የማመዛዘንና የመፍጠር ችሎታን የሚጠይቅ እንደሆነ ያሳያል።

በአዲስ መንገድ አዲስ ነገር በሚፈጠርበትና በሚዋቀርበት በዚህ ቅንበራ በሚባለው አዕምሯዊ ደረጃ የሚጠየቁ ጥያቄዎችም አዛምዱ፣ አሳጥሩ፣ ቀንሱ፣ አስፋፉ፣ መስርቱ፣ ተንብዩ፣ ድርሰት ጻፉ፣ አዲስ ሀሳብ አቅርቡ፣ ገንቡ (construct)፣ ፍጠሩ፣ ንደፉ፣ ለ... ችግሮች መፍትሄ አቅርቡ፣ አብራሩ፣ ፈትኑ (test)፣ አሻሽሉ፣ የተደራጀ ንግግር አድርጉ፣ አጭር ልቦለድ ወይም ግጥም ፈጥራችሁ ጻፉ፣ እቅድ አቅርቡ፣ የሚሉትና

የመሳሰሉት ናቸው። በዚህ ክፍል የሚያገለግሉ መሰረታዊ (ቁልፍ) ቃላትም አቀናጁ፣ ከፋፍሉ፣ አሚሉ፣ ድርሰት ጻፉ፣ ፍጠሩ፣ ቀይሱ (ተልመ)፣ ንደፉ፣ አብራሩ፣ እንደገና አዋቅሩ፣ እንደገና አደራጁ፣ ከልሱ፣ ጭመቁ፣ ተናገሩ የሚሉት ናቸው (አበበ 1990፣ Gronland 1976፣ Monzenmaier እና Robin፣ 2013)።

ረ. ግምገማ (Evaluation)

በነBloom ደረጃ አሰጣጥ ከፍተኛውና የመጨረሻው አዕምሯዊ ደረጃ /ችሎታ ግምገማ ነው። ለዚህ ችሎታ መገንባት ቀደም ሲል የቀረቡት አምስቱ አዕምሯዊ የችሎታ ክፍሎች በቅድመ ተከዋኝነት (prerequisite) ያገለግላሉ። ምንነቱን በተመለከተ፣ ጥቅል በሆነ አገላለፅ ግምገማ የአንድን ማቴሪያል /ጉዳይ ለምሳሌ ልቦለድ፣ ግጥም፣ የምርምር ሪፖርት፣ ሀሳብ ወይም ሌላ ነገር ለሆነ ዓላማ የመመርመርና አዎንታዊ /አሉታዊ ገፅታው ላይ ዳኝነት /ፍርድ ወይም ሀሳብ የመስጠት ችሎታ ነው። የማቴሪያሉን ወይም የጉዳዩን ወይም የሀሳቡን ጠቃሚ መሆን አለመሆን በተመለከተ ዳኝነት/ ፍርድ ወይም ሚዛናዊ የሆነ ሀሳብ ወይም ውሳኔ ለመስጠትም ግልፅ የሆኑ መስፈርቶችን መጠቀምን ግድ ይላል። መስፈርቶቹም ውስጣዊ ለምሳሌ የማቴሪያሉን አደረጃጀት፣ ወይም ውጫዊ ለምሳሌ ከዓላማው ጋር ያለውን ተገቢነት (relevance) መጠቀም ሊሆን ይችላል። መስፈርቶቹም በራሳቸው በተማሪዎቹ የተወሰኑ ወይም ከውጭ በሌላ ክፍል ለተማሪዎች የተሰጡ ሊሆኑ ይችላሉ (አበበ 1990፣ Gronlund 1976፤ Sax 1974)።

ስለዚህ ተማሪው በተወሰነ መለኪያ መስፈርትነት አንድን ሐሳብ ወይም ሌላ ጉዳይ በጥልቀት በመመርመር እንዲገመግም ወይም እንዲሄስ ወይም ዳኝነት/ ፍርድ እንዲሰጥ፣ ወይም ሚዛናዊ የሆነ የውሳኔ ሐሳብ እንዲያቀርብ፣ ወዘተ የሚያዙ ተግባሮች በዚህ በግምገማ የትምህርት ዓላማ ስር የሚካተቱ ናቸው ማለት ነው። በዚሁ መሰረት ተማሪው የአንድን ማቴሪያል ለምሳሌ ጽሑፍ ተጠየቃዊ አደረጃጀት፣ የአንድን ማጠቃለያ በቂነት ወዘተ የተወሰኑ መስፈርቶችን ተጠቅሞ ዳኝነት ወይም ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ ወይም ውሳኔ ላይ እንዲደርስ የሚያዙ ጥያቄዎች በዚህ አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማ ስር የሚካተቱ ናቸው (አበበ 1990፤ Gronland፣ 1976)።

በዚህ ክፍል በቁልፍ ቃልነት የሚታወቁትም አወዳድሩ፣ ገምግሙ፣ አጠቃሉ፣ አነፃፅሩ፣ ተቹ፣ ምክንያት ስጡ (justify)፣ ተርጉሙ፣ አዛምዱ፣ አጠቃሉ፣ ድጋፋችሁን (ተቃውሟችሁን) አስረዱ፣ መስፈርት አውጡ፣ ደረጃ ስጡ፣ መዝኑ (assess)፣ ቅደም ተከተል ስጡ (በቅደም ተከተል አደራጁ)፣ ጠቀሜታቸውን አሳዩ የሚሉት ናቸው (Gronland፣ 1976፣ ሙለና ዳንኤል፣ 2005፤ Monzenmaier እና Robin፣ 2013)።

አንዳንድ ተመራማሪዎች ደግሞ እነዚህን ስድስት የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች እንደገና ዝቅተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታዎችና ከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታዎች በማለት በሁለት ክፍል ይመድቧቸዋል። በዝቅተኛ ደረጃነት የተካተቱት የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ማለትም እውቀትና ግንዛቤ የተባሉት አዕምሯዊ ችሎታዎች ናቸው። በከፍተኛ አዕምሯዊ ችሎታነት የተመደቡት ደግሞ ከትግበራ እስከ ግምገማ ያሉት አራቱ ክፍሎች ናቸው (Gronlund 1976፤ Munzenmaier እና Robin 2013፣ Sax 1974፣ Siddick 2010)።

ቀደም ብሎ እንደተወሳው ከላይ የቀረቡት ስድስት የአዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች በኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማጠናቀቂያ ፈተና በምን ያህል ደረጃ እንደሚወከሉ መመርመር የዚህ ጥናት አንድ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው እነዚህ ስድስት የአዕምሯዊ ችሎታ ክፍሎች በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት የተሰጣቸውን ቦታ በቅድሚያ በደምሳሳውም ቢሆን መመልከት ያስፈልጋል።

እ.ኢ.አ. በ1986 ዓ.ም በወጣውና እስካሁን እየተሰራበት ባለው አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ ውስጥ አምስት አጠቃላይ ዓላማዎች ተካተዋል። ከእነዚህ አምስት ዓላማዎች፣

2.1.2. ይበልጥ ክሂሎታዊ (psychomotor) ምድብ ላይ ያተኮረ ሲሆን ከአዕምሯዊ ምድብ ትግበራ አብሮ ተካቷል።

2.1.3. ስሜታዊ/ አመለካከታዊ (affective) ምድብ ላይ ያተኮረ ነው። የቀሩት ሦስት ዓላማዎች አዕምሯዊ ምድብ ስር በሚካተቱት አምስት ችሎታዎች ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። ይህም በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ለአዕምሯዊ ምድብ ላቅ ያለ ትኩረት እንደተሰጠ የሚያመለክት ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA

እነዚህ ዓላማዎችም፡-

“2.1.1 ... የግለሰብን፣ የአካልና የአዕምሮ ተሰጥዖ በማጎልበት፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን የማወቅና የመፍታት... ችሎታ ያዳበሩ ዜጎች ማፍራት”›፣

“2.1.4. የማመዛዘን፣ የመፍጠርና የመመርመር ችሎታን ማዳበር...”›፣

“2.1.5. ... አካባቢያቸውን የማወቅ፣ የማጤንና የመገንዘብ፣ የመመዘንና የመገምገም፣ የመተንተንና የመለወጥ...ችሎታ ያላቸው ዜጎች ማፍራት” የሚሉና የአዕምሯዊ የትምህርት ምድብን የተለያዩ የችሎታ ደረጃዎችን ማዳበርን የሚመለከቱ ናቸው(የትምህርት ሥልጠና ፖሊሲ 1986፣10)

በዓላማዎቹ ውስጥ የተካተቱ ቁልፍ ቃላትና ቃላቱን ያጀቧቸው ሀረጎች በግልፅ እንደሚያሳዩት፤

በ2.1.1፣ በ2.1.4. እና በ2.1.5. በቀረቡት አጠቃላይ ዓላማዎች ከትግበራ በስተቀር ሁሉም የአዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች ተካተዋል፡፡ ለምሳሌ ዕውቀት የሚባለው የመጀመሪያውና ዝቅተኛው የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃ በዓላማ “2.1.1 ... ችግሮችን ማወቅ” እና በ“2.1.5 ... አካባቢያቸውን ማወቅ” በሚሉት ሀረጎች ተገልጿል፡፡

ሁለተኛው፣ የአዕምሯዊ ምድብ ችሎታ ግንዛቤ ሲሆን በፖሊሲው ዓላማ “2.1.5.... አካባቢያቸውን ... የማጤንና የመገንዘብ... ችሎታ ያላቸው ዜጎች ማፍራት” በሚለው ሀረግ ውስጥ “ማጤንና መገንዘብ” በሚሉት ቁልፍ ቃላት ተገልጿል፡፡ በዚህ ምድብ በአራተኛ ደረጃነትና ከፍተኛ/ ውስብስብ ችሎታነት የሚታወቀው ትንተና ደግሞ በዓላማ ቁጥር “2.1.4. የማመዛዘን... የመመራመር ችሎታን ማዳበር፣ በሚለው፣ በ2.1.5. ‹‹አካባቢያቸውን... የማጤን፣ የመገንዘብ፣ **የመመዘን፣ የመተንተን** ችሎታ ያላቸው ዜጎች ማፍራት” በሚለው ውስጥ ደምቀው (Bold ተደርገው) በተጻፉት ቃላት ተመልክቷል፡፡

አምስተኛውና በከፍተኛው አዕምሯዊ ችሎታነት ከሚታወቁት አንዱ የሆነው ቅንበራም እንዲሁ በፖሊሲው ዓላማ ቁጥር 2.1.1 “... “የሚያጋጥሙ ችግሮችን... **የመፍታት** ችሎታ ያዳበሩ ዜጎችን ማፍራት›” በሚል፣ በ2.1.4. “**የመፍጠርና የመመራመር** ችሎታን ማዳበር፣” በ“2.1.5. “አካባቢያቸውን... **የመለወጥ** ችሎታ ያላቸው ዜጎችን ማፍራት” በሚሉት ውስጥ ደምቀው በተጻፉት ቃላት ተገልጿል፡፡

በስድስተኛ ደረጃ የአዕምሯዊ ችሎታነት የሚታወቀው ግምገማ ደግሞ በፖሊሲው አጠቃላይ ዓላማ "2.1.5. ...አካባቢያቸውን ... **የመመዘንና የመገምገም**... ችሎታ ያላቸው ዜጎች ማፍራት" በሚለው ውስጥ የመመዘንና የመገምገም ችሎታ በሚሉት ቃላት ተገልጿል።

ሁለተኛው የሀገሪቱ መሰረታዊ የትምህርት ሰነድ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን ለማስተግበር በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ (Curriculum Framework for Ethiopian Education (KG-Grade 12) የሚለው ነው።

ከአፀደ-ሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍል የሚሰጠው ትምህርት የሚከተላቸውን መርሆዎች (prinicples)፣ እሴቶች (values)፣ ቁልፍ ብቃቶች (competencies) እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የያዘ ሰነድ ነው። ቁልፍ ብቃቶች በሚለው ክፍል ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱና ዋናው በBloom እና ባልደረቦቻቸው (1956) ስራ የቀረቡት የአዕምሯዊ ምድብ (cognitive domain) ክፍሎች ናቸው። በዚህ ቁልፍ ብቃቶች በሚለው ክፍል በሕይወት ክሂሎት (life skills) ጀምሮ በጊዜ አጠቃቀም (Time Management) የሚቋጨ ሰባት ቁልፍ ብቃቶች (competencies) የተካተቱ ሲሆን የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች በየብቃቱ ተቀላቅለው እንዲቀርቡ ከመደረጉ በተጨማሪ ሦስተኛውና ከፍተኛ-ደረጃ-የማሰብ ችሎታ (Higher-Order-Thinking) የሚለው ሙሉ በሙሉ በዚህ አዕምሯዊ ምድብ ስር የሚካተቱ ክፍሎችን ብቻ የያዘ ነው። በዚህ ክፍል ከአዕምሯዊ ችሎታዎች ትኩረት የተሰጠውም ከፍተኛ ደረጃ ለሚባሉት አዕምሯዊ ችሎታዎች ማለትም ለትግበራ፣ ለትንተና፣ ለቅንበራና ለግምገማ ነው። በቁልፍ ብቃትነት ከቀረቡት ሰባት ክፍሎች በሦስተኛ ደረጃ ላይ በቀረበው ከፍተኛ-ደረጃ- የማሰብ ችሎታ የሚለው ስር ሁለት ክፍሎች የተካተቱ ሲሆን የመጀመሪያው ሥርዓተ ትምህርቱ እውቀትን ተግባራዊ የማድረግ ችሎታን በሚያዳብር፣ ትንተናን፣ ቅንበራን፣ ግምገማንና አዳዲስ አሰራርን በሚያሳድግ መንገድ ሊቀርብ እንደሚገባው አቅጣጫ የሚያሳይ ነው። ("The curriculum should be taught in a way that engenders and promotes the development of application of knowledge,

analysis, synthesis, evaluation and innovation" ትምህርት ሚኒስቴር 2011፣10) የሚለው ዐረፍተ ነገር፣ የተገለጸውን ሀሳብ በግልጽ የሚያሳይ ነው።።

ሁለተኛው ተማሪዎች ችግሮችን በመፍታት ዐውድ ጠለቅ (ላቅ ያለ) አስተሳሰብንና አዳዲስ ነገሮችን የማመንጨት (የፈጠራ) ክሂሎችን (Critical Thinking and Creative Thinking Skills) ማዳበር እንደሚኖርባቸው የተገለፀበት ክፍል ነው።። በሁለቱም ክፍሎች የተገለፁት ሀሳቦች የሀገሪቱ ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታዎችን ማዳበር ላይ ሊያተኩር እንደሚገባው የሚያሳስቡ/ የሚያስገነዝቡ ናቸው።። የዚህም አንድምታ በሀገሪቱ ትምህርት ቤቶች በየትምህርት አይነቶቹ የሚሰጠው ትምህርት ለአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች በተለይም ለከፍተኛ ደረጃ ችሎታዎች ከፍተኛ ትኩረት የሰጠ ሊሆን እንደሚገባው የሚያመለክት ነው።። በቂ እርሾ (መሰረታዊ ችሎታ) ይዘው ለሚመጡ ተማሪዎች የሚሰጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ደግሞ ይህን የማድረግ የበለጠ ግዴታ ይኖርበታል።። ከሕይወት ክሂሎት ጀምሮ በሥርዓተ ትምህርቶቹ እንዲዳብሩ የተካተቱት አብዛኞቹ ብቃቶች (Comptencies) በጥልቀት ሲታዩ በቋንቋ ትምህርቶች ሊዳብሩ የሚችሉ ብቃቶች ናቸው።። የትምህርት ዓላማዎች ከግብ መድረስ አለመድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚዘጋጁ የክፍልም ሆነ ብሔራዊ ፈተናዎችም የዚህ ነፀብራቅ መሆን ይጠበቅባቸዋል (Hughes, 2003)።።

የአጠቃላይ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውም ሆነ የሥርዓተ ትምህርት ማስፈጸሚያ ማዕቀፉ እንዲሁ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው ሊያዳብሯቸው የሚገቧቸውን ብቃቶች (competencies) ትኩረት ሰጥተው እንዳቀረቡት ሁሉ ስለምዘናም አንስተዋል።። ለምሳሌ በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው በክፍል 3.3 **የትምህርት ምዘና፣ በሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፉ ምዘናና ዝውውር** (Assessment and Promotion) በሚሉት ርዕሶች ውስጥ የቀረቡት ነጥቦች ይህንኑ የሚመለከቱ ናቸው።።

በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው **የትምህርት ምዘና** በሚለው ስር ከቀረቡት ሰባት ነጥቦች መካከል ለምሳሌ በ3.3.1፣ 3.3.2፣ 3.3.3፣ 3.3.5 እና 3.3.6 የተገለፀው ስለክፍልና ብሔራዊ ምዘና ነው።። ለምሳሌ "3.1 ተማሪዎች በየክፍሉና በየደረጃው የሚሰጠውን ትምህርትና ሥልጠና በሚገባ ያጠናቀቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ

በአጠቃላይ፣ በቀለምና በተግባራዊ ትምህርት ተከታታይ ምዘና ይኖራል፡" (አጠቃላይ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ 1986፣ 10) የሚል ሲሆን 3.2 ደግሞ "በስምንተኛና በአሥረኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ላይ የአጠቃላይ የቀለምና ተግባራዊ ትምህርቶችን ያካተተ አገር አቀፍ (ብሔራዊ) ምዘና ይኖራል፣" በማለት እግረ መንገዱንም በአገሪቱ ይሰጡ የነበሩ ብሔራዊ ፈተናዎች ከሦስት ወደ ሁለት ዝቅ ማለታቸውን ያስታውቃል፡፡ 3.3.3. ተማሪዎች ከአንድ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ለመዛወር "ቢያንስ ሃምሳ በመቶ የሚሆነውን በዕውቀት፣ በችሎታና በክህሎት ጨብጠው" መገኘታቸው እንደሚረጋገጥ የሚገልጽ ነው፡፡ በ3.3.7 ላይ ብሔራዊ ፈተናዎችን በሳይንሳዊ መንገድ የሚመራ የፈተናዎች ድርጅት ይቋቋማል ተብሎ የተገለፀውም በተዘዋዋሪ በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ የምዘና ጉዳይ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን የሚያሳይ ነው (አጠቃላይ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ 1986፣ 10-11)፡፡

የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲውን ለማስፈጸም በወጣው የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፉ ውስጥም ምዘና ከዝውውር ጋር አንድ ራሱን የቻለ ምዕራፍ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በዚህ ምዕራፍ እንደተገለፀውም በክፍልም ሆነ በብሔራዊ ደረጃ የሚሰጥ ምዘና በየደረጃው ያሉ ተማሪዎች የሚጠበቁትን ብቃቶች (competencies) በአግባቡ ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ‹‹It should ensure that students at all levels are generally able to achieve the competencies expected of them›› (Curriculum Framework 2010፣ 59) የሚለው ዓረፍተ ነገር ከላይ የተባለውን በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡ ብሔራዊ ፈተናዎችን ጨምሮ በየደረጃው የሚሰጡ ፈተናዎች ቀደም ብለው የተዘረዘሩትን ብቃቶች የሚመዝኑ ሊሆኑ እንደሚገባቸው የሚያስገነዝብ መግለጫ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በየደረጃው በክፍልና በብሔራዊ ደረጃ የሚሰጡ ፈተናዎች/ ምዘናዎች በቃል፣ በጽሑፍና በተግባር ሊከናወኑ እንደሚገባቸው በዚሁ ሰነድ በዝርዝርና በግልፅ ቀርቧል (Curriculum Framework 2010፣ 60-62)፡፡

ይህም እነዚህ በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውና በሥርዓተ ትምህርት ማስፈጸሚያ ሰነዱ የተካተቱ የአዕምሯዊ ምድብ ባሕርያዊ ዓላማዎች በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ

ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎች በአግባቡ ሊወከሉ/ ሊንጸባረቁ እንደሚገባቸው የሚያሳይ ነው።።

የዚህ ጥናት አንደኛው ትኩረትም እነዚህ ስድስት ደረጃዎች በፈተናዎቹ በተገቢ ናሙና የሚሸፈኑ /የሚወከሉ መሆን አለመሆናቸውንና አወካከላቸው በBloom እና በሀገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት በተሰጣቸው ትኩረት መሰረት አዎንታዊ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማበረታታት በሚያስችል መልኩ መሆን አለመሆኑን መመርመር ነው።። በሚመዘነው/ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ምድቦች (Target Language Domains) እና በፈተና የሚካተቱ ችሎታዎች መካከል ተጣጥሞሽ (Overlaping) ሊኖር እንደሚገባው የሚገልጸው የGreen (2007) የወሽባክ ሞዴልም ይህንኑ የሚያበረታታ ነው።።

2.4.2 በመሰረታዊ የቋንቋ ትምህርት ምድብ (Domain) ክፍሎች እና በፈተና መካከል ያለ ተጣትሞሽ (Overlap)

የወሽባክ ሞዴሎች በሚለው ክፍል እንደተገለጸው አራተኛውና በቅርቡ የዳበረ ነው ሊባል የሚችለው የGreen (2007) ወሽባክ ሞዴል ነው።። ይህ የወሽባክ ሞዴል፣ በቋንቋ ፈተና ተግባራት (የአቀራረብ መንገዶች፣ አይነቶች...) እና በታላሚው ቋንቋ እንዲዳብሩ በሚፈለጉ የችሎታ ምድቦች መካከል በሚፈጠር መጣጣም የሚመነጭ ነው ከሚል ሐሳብ ይነሳል።። በዚሁ መጽሐፍ እንደተብራራው ይህ መገጣጠም (ተዛምዶ) በፈተናዎቹ ተግባራትና በታላሚው ቋንቋ (ከዚህ ጥናት አንጻር ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ) መካከል በሚኖር/ በሚፈጠር ቅርበት/ርቀት የሚከሰት ጉዳይ ነው።። (The model proposes that the nature of washback from language tests flows from overlap,the distance between test method characterstics (the range and types of test tasks) and the characterstices of the target language use (TLU)domain) (Green 2007፣ 25) የሚለው አገላለጽ ይህንኑ የሚያስረዳ ነው ማለት ይቻላል።።

በዚሁ መሰረት በሁለቱ ማለትም በፈተናው ተግባራትና እንዲዳብሩ በሚፈለጉት የቋንቋው ክሂሎች/ ችሎታዎች መካከል ከፍተኛ ርቀት/መራራቅ ካለ ያልታለመ/

የማይፈለግ የወሽባክ ውጤት የመከሰት እድሉ ከፍተኛ ይሆናል። በተቃራኒው ደግሞ በሁለቱ መካከል ከፍተኛ ተዛምዶ ካለ ደግሞ አዎንታዊ ወሽባክ የመገኘቱ አጋጣሚ ከፍተኛ ይሆናል (The greater the distance between test tasks and the skills required for success in the TLU domain the greater the potential for unintended washback. The greater the congruence, the more likely positive washback becomes) ይላሉ (Green 2007፣25)። ይህ አተያይ በAlderson፣ Clapham እና Wall (1995)፣ Hughes (2003)፣ Mesick (1996)፣ Siddick (2010)) የይዘት ተኮር መረጃ አግባብነት (Content related evidence /validity) ከሚለው ጋር የሚዛመድ ነው። Green (2007) ራሳቸው በዚሁ ስራቸው የፈተናና በታላሚው ቋንቋ እንዲዳብር የሚጠበቅ የቋንቋ ችሎታ ተዛምዶ ጥናት ከይዘት ተኮር አግባብነት ማስረጃ ስብሰባ (the gathering of content-related evidence for test validity) ጋር የተያያዘ ነው ይላሉ። በወሽባክ ጥናትም አንዱ ተተኳሪ ጉዳይ በሁለቱ መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ መመርመር ሊሆን እንደሚገባው ሞዴላቸውና ስለሞዴሉ የተሰጡት ማብራሪያዎች ያመለክታሉ።

በተለይ በችሎታ መለኪያ (Achievement) ፈተና የፈተናና ለትምህርት የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ክፍሎች/ ምድቦች ተዛምዶ ወይም የይዘት አግባብነት የሚባለው፣ የይዘት ተገቢነት (relevance) እና የይዘት ሽፋን (Content coverage) በሚባሉ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የፈተና አግባብነት ዓይነት ነው (Bachman 1990)። ከAlderson፣ እና ሌሎች (1995)፣ Brown (2004)፣ Hughes (2003) እንዲሁም Weir (1990) ማብራሪያ መገንዘብ እንደሚቻለው በተለይ በችሎታ መለኪያ ፈተናና በትምህርት ዓላማዎች /ይዘቶች መካከል የሚኖር ተዛምዶ መሰረታዊ የሆነ የአግባብነት አይነት (ማስረጃ) ነው። የተዛምዶው ደረጃ ከፍና ዝቅ ማለት ፈተናዎቹ ለሚኖራቸው ወሽባክ አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት የራሱን ሚና ይጫወታል።

ይህንኑ፣ የፈተናና ለትምህርት የቀረቡ የቋንቋ ክፍሎች ተዛምዶ ምንነት በተመለከተ Alderson፣ እና ሌሎች (1995)፣ Hughas (2003) የአንድን ትምህርት ክፍሎች/ ምድቦች (Domains) ወይም የመርሐ ትምህርት ይዘቶች ሁሉ በተመጣጠነ ሁኔታ

የመወከል/ የማካተት ችሎታ ነው ሲሉ፣ Bachman (1990)ም አስፈላጊ ባሕርያዊ ምድቦችን በፈተና ተግባራት በጥያቄዎች በበቂ ደረጃ መወከል ነው በማለት በተመሳሳይ ሁኔታ በይነውታል። Weir (1990) ደግሞ ፈተናዎች ጠቃሚ ወሸባክን እንዲያዳብሩ በተቻለ መጠን ከመርሐ ትምህርቱ/ቶቹ ሰፊና ተገቢ ናሙናዎችን የማካተት እንዲሁም ተጠየቃዊና ተግባቦታዊ ጥያቄዎችን የማዘጋጀት ሂደት መሆኑን ይገልፃሉ። የWeir (1990) አገላለጽ፣ ፈተናዎች ተማሪዎች በስፋት በተማሯቸው የመርሐ ትምህርት መሰረታዊ ክፍሎች (ዓላማዎችና ይዘቶች) ላይ ማተኮር ይጠበቅባቸዋል ከሚለው የSiddiek (2010) አገላለፅ ጋር የሚመሳሰል ነው። Siddick (2010) አያይዘው እንደሚገልፁት፣ ፈተናዎች በዚህ መንገድ (መሠረታዊ የትምህርት ክፍሎች ላይ አተኩረው) ሳይዘጋጁ ሲቀሩ የይዘት አግባብነት የሚባለውን መሰፈርት ማሟላት ይሳናቸዋል። ውጤቱም አብዛኛው የማስተማር ሂደት ከትክክለኛ ማስተማር ይልቅ በፈተና አሰራር ቴክኒኮች ላይ እንዲያተኩር የሚያደርግ ሊሆን ይችላል። ሁለቱ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዲኖራቸው ተገቢ ትኩረት የማይሰጡ ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ሁኔታ ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፎቻቸውን እንደ ዕውቀት ምንጭ ተመልክቶ በመሳሪያዎቹ ለመጠቀም ከመምከር ይልቅ ማርክ የሚያገኙባቸው ስልቶች ላይ ማተኮርን እንደሚመርጡ የSiddiek (2010) ጥናት ያመለክታል። ይህም "ፈተና ተማሪዎች የመርሐ ትምህርቱን አንኳር (cores) ክፍሎች መማር ችለዋል? በሚለው ላይ አተኩሮ ሊዘጋጅ ይገባዋል" የሚለውን የHughes (2003:58) ሐሳብ አስፈላጊነት የሚያጠናክር ነው። Siddiek (2010:1) "የፈተና ጥያቄዎች ሁሉንም የትምህርት ርዕሶች (topics) በተመጣጣኝ ውክልና መሸፈን ይኖርባቸዋል" የሚለው ማጠቃለያም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው።

Brown (2004) እንደሚያስረዱት አንድ ፈተና ከተለያዩ መደምደሚያዎች ላይ የሚያደርሱ ትክክለኛ ናሙናዎችን ከተጠቀመና ተፈታኙን ለመለካት የታሰበውን ባህርይ እንዲከውን ካስቻለ አግባብነት ያለው ነው ሊባል ይችላል። ለምሳሌ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል በውይይት ዐውድ ሐሳብን በቃል የመግለፅ ችሎታ ለመመዘን በወረቀት የምርጫ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ቢደረግ ፈተናው ከትምህርቱ ጋር አግባብ ያለው ግንኙነት እንዳይኖረው ማድረግ ነው። ምክንያቱም ለመመዘን

የታሰበውና የተመዘነው የማይገናኙ ናቸው። የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ የሚመዝን ፈተና አግባብነት የሚኖረው ተፈታኞቹ በእውናዊ (Authentic) ዐውድ እንዲናገሩ እድል የሚሰጥ ሲሆን ነው። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ትምህርት /ኮርስ አስር አላማዎች ያሉት ሆኖ በፈተናው ሁለቱ ብቻ የሚሸፈኑ ከሆነ ፈተናው ከይዘት ጋር በተያያዘ የመረጃ አግባብነት ችግር የሚታይበት ይሆናል (Brown 2004)።

ከሁለቱ ተዛምዶ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ነገር በርቱዕ/ቀጥተኛና ኢርቱዕ /ኢቀጥተኛ (direct and indirect) አፈታተን መካከል ያለው ልዩነት ነው። ቀጥተኛ የሚባለው ተፈታኙን ለመመዘን በታለመው የቋንቋ ክሂል በትክክል እንዲከውን (እንዲጠቀም) የሚያስችል የአፈታተን ስልት ነው። በአንፃሩ ኢቀጥተኛ የሚባለው አፈታተን ደግሞ ተፈታኙ በቋንቋው በቀጥታ እንዲገለገል በማድረግ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመመዘን የመሞከር ሂደት ነው (Brown 2004)። ለምሳሌ አንቀፅ የመጻፍ ክሂልን አንቀፅ በማጻፍ መፈተን ቀጥተኛ ሲሆን ስለአንቀፅ ምንነት ወይም ባህርያት እንዲገልፁ በማድረግ መፈተን ግን ኢቀጥተኛ አፈታተን ነው። በዚህ ኢቀጥተኛ በሆነው መንገድ የቋንቋ ችሎታን ለመፈተን መሞከርም ፈተናዎች የይዘት አግባብነት ችግር የሚታይባቸው እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው (Brown 2004)::

የፈተናዎችና የትምህርቱ ተጣጥሞሽ/ ተዛምዶ ወይም የይዘት አግባብነት ደረጃ ከፍ ያለ (አዎንታዊ) እንዲሆን ማድረግ የሚቻለው እንዴት ነው? ለሚለው ጥያቄ አብዛኞቹ ቀዳሚ መፍትሄ አድርገው የሚጠቅሱት የፈተና ዓላማና/ይዘት ልየታዎች (Specifications) አስፈላጊነት ነው።

ለምሳሌ Hughes (2003) እንደሚያስረዱት፣ አንድን ፈተና አዎንታዊ የይዘት-ተኮር መረጃ አግባብነት አለው ወይም የለውም ብሎ ለመወሰን/ ለመፍረድ በፈተናው መሸፈን ያለባቸውን የቋንቋው ክሂሎች ወይም መዋቅሮች የሚያሳይ ልየታ ያስፈልጋል። ልየታውም ከፈተናው ቀደም ብሎ የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል። ከዓላማና ይዘት ልየታ በተጨማሪ የፈተናንና ለትምህርት የቀረበ ይዘትን ተዛምዶ አግባብነት ከፍ ለማድረግ የሚረዱ ስልቶች ተደርገው የሚወሰዱት በWeir (1990) ስራ የተዘረዘሩት የሚከተሉት የAnastasi (1982) መመሪያዎች ናቸው፤

ሀ. ሁሉም መፈተን የሚገባቸው ዋና ዋና ክሂሎች በፈተናው ጥያቄዎች እንዲሸፈኑና ተመጣጣኝ ውክልና እንዲያገኙ የሚመዘኑ የባህርይ ክፍሎች (The behavior domain to be tested) ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ የግድ መተንተን አለባቸው፤

ለ.ትኩረት የሚሰጠው ምድብ (domain) በሚገባና በተሟላ መልክ በቅድሚያ (ፈተናው ከመዘጋጀቱ በፊት) መገለፅ አለበት፤ እና

ሐ.የሁለቱ ተዛምዶ /የይዘት አግባብነት የሚመሰረተው የየተፈታኙ የፈተና መልሶች ከትኩረት የተሰጣቸው የባህርይ ክፍሎች (The behavior areas) ጋር ባላቸው ተገቢ ዝምድና (ግንኙነት) ነው (Weir 1990:25)::

የአንድ ፈተና በትምህርት እንዲዳብሩ ከሚጠበቁ የቋንቋ ምድቦች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ከፍተኛ (አዎንታዊ መሆን የሚያስገኘው ጠቀሜታ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ከላይ ለሌላ ዓላማ በተገለፁት ሐሳቦች ውስጥ አብረው መመለሳቸው እንዳለ ሆኖ ከእነሱ በተጨማሪ Hughes (2003) ሁለት ነጥቦችን ያነሳሉ:: አንደኛው በሁለቱ መካከል ያለው የተዛምዶ ደረጃ ከፍተኛ በሆነ ቁጥር ለመለካት የታሰበውን ዕውቀት/ ክሂል በትክክል መለካቱን ያረጋግጣል:: በሌላ አባባል የችሎታ/ የ"ኮንስትራክት" አግባብነት መኖሩን ያሳያል:: በእርግጥ በፈተና ልየታው ዋና ዋና የትምህርቱ ክፍሎች ከሚጠበቀው በታች ታቅደው ከሆነ ወይም ጭራሽ አልተካተቱ ከሆነ መለኪያው ትክክል አይሆንም::

Hughes በሁለተኛ ደረጃ ያነሱት የፈተናዎቹን የወሸባክ ጉዳይ ነው:: በዚህ ረገድ የሚነሳው ጠቀሜታ የሁለቱ የተዛምዶ (የፈተናዎቹ የይዘት አግባብነት) ደረጃ ከፍተኛ ከሆነ ማለትም መመዘን ያለባቸው የትምህርቱ ክፍሎች(Areas) ሁሉ በወካይ ናሙና ከተሸፈኑ ወሸባኩ አዎንታዊ ይሆናል የሚለው ነው:: በአንፃሩ መሸፈን ያለባቸው መሰረታዊ ክፍሎች በበቂ ናሙና መወከል ካልቻሉ ደግሞ ወሸባኩ አሉታዊ ወይም ጎጂ (harmful) ይሆናል ማለት ነው:: ምክንያቱም በፈተና ችላ የተባሉ የትምህርቱ ክፍሎች (areas that are not tested) በማስተማርና መማር ሂደቱም ችላ መባላቸው አይቀርም:: ቀደም ብሎ የተገለጸውን የGreen (2007) ሞዴል ንድፈ-ሀሳብ የሚጋራ

አተያይ ነው። Hughes (2003፣ 27) ከዚሁ ጉዳይ ጋር አያይዘው እንዳወሱት ብዙውን ጊዜ የፈተና ይዘቶች የሚወሰኑት በፈተናዎቹ ከመካተታቸው አስፈላጊነት ይልቅ ለመፈተን ቀላል ከመሆናቸው አኳያ ነው። ይህም ፈተናዎች የይዘት አግባብነት መስፈርትን የማያሟሉና በማስተማር መማር ሂደቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ እንዲሆኑ ያደረጋቸዋል።

ሌላው ከዚሁ ከተዛምዶ /ይዘት አግባብነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ በፈተናዎችና በአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች፣ በፈተናዎችና እንዲዳብሩ በሚጠበቁት የቋንቋ ትምህርት ክፍሎች መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ እንዴት ማጥናት ይቻላል? የሚለው ነው። ፈተናዎች ከትምህርቱ ጋር ያላቸውን ተዛምዶና የተዛምዶ ደረጃ ለማጥናት /ለመገምገም የሚረዱ ሦስት ያጠናን ስልቶች አሉ (Alderson፣ ሌሎች 1995)። አንደኛው፣ በራሱ በአጥኝው የፈተናውን ይዘት ከልየታዎቹ ወይም ከመርሐ ትምህርቱ(ቶቹ) ይዘቶች ጋር የማወዳደር ስልት ነው(Compare test content with specifications/ syllabus):: Simachew (2012) የተጠቀሙት ይኸኛውን ዘዴ ነው። ሁለተኛው መምህራን፣ በሙያው የላቀ ችሎታ ያላቸው ምሁራንና የተግባራዊ ሥነ-ልሳን ሊቃውንት የሚሞሏቸው መጠይቆችና አስተያየታቸውን የሚገልፁባቸው ቃለ መጠይቆችን በማዘጋጅት ነው። Green (2007) በፈተናዎችና በታላሚው ቋንቋ እንዲዳብሩ በሚፈለጉ መሰረታዊ ችሎታዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ ለማጥናት የተጠቀሙት ይኸኛውን ሁለተኛውን ስልት ነው። ሦስተኛው፣ በፈተናው ጥያቄዎችና ጽሑፎች (texts) ላይ ባለሙያዎች ዳኝነት እንዲሰጡ_ የትኛው ጥያቄ የትኛውን ክሂል እንደሚለካ እንዲገልፁ (Experts judgment) እድል የሚሰጠውን ስልት መጠቀም ነው። አብዛኛውን ጊዜ አገልግሎት ላይ እየዋለ ያለውና በWeir እና ሌሎች (1990) ስራ ተመራጭ ዘዴ ሆኖ የቀረበው ሦስተኛው ስልት ነው። ስለዚህ በዚህ ጥናት በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና በአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ባህሪያዊ ዓላማዎች እንዲሁም በፈተናዎቹና በቋንቋው ትምህርት ዓላማዎችና ይዘቶች መካከል ያለውን ተዛምዶ ለማጥናት ዋነኛ ዘዴ ተደርጎ የተመረጠው ሦስተኛው ስልት ነው። በሁለተኛው ዘዴ ደግሞ ከመምህራን ጋር በተካሄዱ ቡድን ተኮር ውይይቶችና ለመምህራን በተዘጋጀው የጽሑፍ መጠይቅ ከፎኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከትምህርት ቤት ውጭ ካሉ ተሳታፊዎች ደግሞ ከፈተናዎች ኤጀንሲ ኀላፊዎችና

የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ በመምህራን የሚዘጋጁ የክፍል ፈተናዎች ከትምህርቱና ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ያላቸው ግንኙነት ለመፈተሽ ደግሞ በአንደኛው ስልት መሰረት በራሱ በአጥኚው ጥያቄዎቹ በየክፍላቸው እንዲመደቡ ተደርገዋል፡፡ ከራሳቸው ከመምህራኑም (የፈተና አዘገጃጀታቸውን በተመለከተ) በቡድን ተኮር ውይይቶች ተጨማሪ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

ከዚሁ ከወሸባክ የተዛምዶ ጥናት ጋር በተያያዘ ሌላው የሚነሳው የፈተናዎቹ ጥያቄዎች የሚዛመዱት ከየትኛዎቹ ችሎታዎች ጋር ነው? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስም አንደኛ፣ ፈተናው የብቃት (Proficency) መለኪያ ከሆነ በፈተናዎችና በሚፈተኑት አካላት ዳብረው እንዲገኙ በሚጠበቀው የቋንቋ ችሎታ ክፍሎች (TLU Domain) መካከል ያለው ግንኙነት የሚጠናው በ Green (2007) ስራ እንደተደረገው የፈተናውን ጥያቄዎች ከሚጠበቀው ችሎታ (TLU) አንጻር በማዛመድ ይሆናል፡፡ ሁለተኛ፣ ተፈታኞቹ የተማሩትን ትምህርት ችሎታ ለመመዘን የሚሰጥ ፈተና ከሆነ ደግሞ የተለመደው የአጠናን መንገድ የፈተናውን አቀራረብና ይዘት ከትምህርቱ ዓላማዎችና/ ይዘቶች ጋር በማነጻጸር ይከናወናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ከፈተናዎች ኤጀንሲ በተገኘው መረጃ መሰረት የማጠናቀቂያ ፈተናው የችሎታ መለኪያ (Achivement Test) በመሆኑ የጥያቄዎቹንና የፈተናውን ግንኙነት በዋነኛነት ለመመርመር የተሞከረው በዚሁ በሁለተኛው የአጠናን ስልት መሰረት ለጥናት በተመረጡት ዓመተ ምህረቶች የተዘጋጁትን ፈተናዎች ጥያቄዎች በመርሐ ትምህርቶቹ ከቀረቡት ዓላማዎችና ይዘቶች ጋር በማነጻጸር ነው፡፡ በመምህራኑ የተዘጋጁትን ፈታዎች ከትምህርቱ ጋር ለማዛመድ የተሞከረውም በተመሳሳይ ሁኔታ በመርሐ ትምህርቶቹ ከቀረቡት ዓላማዎችና ይዘቶች ጋር ነው፡፡ ፈተናዎች ከአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች ጋር ያላቸው ተዛምዶ የሚጠናው ደግሞ የአጠቃላይ ትምህርት መስክ ተመራማሪዎች የሚጠቀሙበትን የፈተናዎችን ጥያቄዎች ከአዕምሯዊ ምድብ ስድስት ክፍሎች/ ችሎታዎች ጋር (ከሙያው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም) በማዛመድና (ደሳለኝ 2005) በተዛምዶው መሰረት ግንኙነታቸውንና የግንኙነታቸውን ደረጃ በመመርመር ነው፡፡

በዚህ ጥናት የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጥያቄዎች ከአዕምሯዊ የትምህርት ዓላማዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጥናት ተግባራዊ የተደረገውም ይኸው ስልት ነው።

በዚሁ መሰረት የውጤት ትንተናዎችን በተዛማጅ ጽሑፎች ክለሳ ከቀረቡት አተያዮች ጋር በማገናዘብም የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች እና ከቋንቋው ትምህርት ጋር ያላቸው ግንኙነትና ግንኙነታቸው አዎንታዊ ወሽባክን ለማዳበር የሚረዳ ከመሆን አለመሆኑ አንጻር ለመመርመር ጥረት ተደርጓል። የክፍል ፈተናዎቹ የትምህርቱ ነጸብራቅ ናቸው ወይስ የማጠናቀቂያ ፈተናው? የሚለው ጉዳይም አብሮ ተፈትሿል።

2.5. የወሽባክ ምንነት/ ብያኔዎችና ታሪካዊ ዳራ

ወሽባክ በተግባራዊ ሥነ-ልሳን አንድ የጥናት መስክ (discipline) ሲሆን ፈተናዎች ቋንቋ ማስተማርና መማር ላይ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ነው፤ በሚለው ብያኔ አብዛኞቹ የቋንቋ ፈተና በተለይም የፈተና ወሽባክ ተመራማሪዎች ይስማማሉ።

ታሪካዊ ዳራው እንደሚያሳየውም ፈተና በማስተማር-መማር ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ በአጠቃላይ ትምህርትና በተግባራዊ ሥነ-ልሳን ጽሑፎች/ literature ከፍተኛ ቦታ እያገኘ የመጣው ከ1990ዎቹ ወዲህ ቢሆንም በተለይ በአጠቃላይ ትምህርት መስክ ግን ከተጠቀሰው ጊዜ ቀደም ያለ የፈተና ጥናት አንድ ገጽታ ነው። ይህም ጉዳይ በአጠቃላይ ትምህርት መስክ አብዛኛውን ጊዜ "ባክዋሽ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን በተግባራዊ ሥነ-ልሳን "ወሽባክ" በሚል ስያሜ ይጠራል (Cheng 2004)። በሁለቱም መስኮች የትምህርት ባለሙያዎች ፈተናዎች በክፍል ውስጥ መማር-ማስተማር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚፈጥሩ ጽፈዋል (Alderson እና Wall1993)። (በዚህ ጥናት የተመረጠው ስያሜ ወሽባክ የሚለው ነው።)

ከነዚህ የትምህርት ባለሙያዎች መካከል Pearson (1988) አንዱ ናቸው። በAlderson እና Wall (1993) እና Fulcher & Davidson (2007) ተጠቅሶ እንደምናገኘው በPearson (1988፡98) ብያኔ መሰረት ወሽባክ ውጫዊ ፈተናዎች (ውጫዊ ፈተና የሚለው ብሔራዊ (public) ፈተናዎች፣ ከፍተኛ ውሳኔ የሚወሰንባቸው ፈተናዎች (high-stake tests) የሚባሉትን ይመለከታል) በመምህራን፣ በተማሪዎችና

በወላጆች አመለካከት፣ ባህርይና ተነሳሽነት ላይ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ነው። ይህም ተፅዕኖ ቀደም ባሉት ጊዜያት፣ በአብዛኛው፣ ፈተናዎች ሥርዓተ ትምህርትን የሚያዛቡ (distort the curriculum) ናቸው ከሚለው አተያይ ጋር ይያያዝ ነበር። ለምሳሌ በAlderson እና Wall (1993) ስራ የተጠቀሱት Vernon(1956፡166) ያስቡት የነበረው ፈተናዎች "ፈተናውን ለማለፍ አስተዋፅኦ የማይኖራቸውን የትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች መምህራን ችላ እንዲሏቸውና በፈተና ለሚካተቱት ደግሞ መጠን ያለፈ ትኩረት እንዲሰጧቸው የሚያደርጉ ናቸው"።

በእርግጥ ቀደም ባሉት ጊዜያት የነበረው አተያይ ይኸ ብቻ ነበር ማለት ግን አይደለም። ፈተና በሚፈጥረው ተፅዕኖ ላይ ከዚህ የተለየ አተያይም ነበር። ለምሳሌ ፈተናዎች ሥርዓተ ትምህርቶች በአግባቡ መተግበራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አስፈላጊ መሣሪያዎች እንደሆኑ አድርገው የሚመለከቷቸው ምሁራንም ነበሩ። አንዳንዶቹ እንዲያውም ከአሁኑ ዘመን አተያይ ጋር በሚመሳሰል ሁኔታ ፈተናዎች ሥርዓተ ትምህርት መተግበሩን የሚያረጋግጡ ብቻ ሳይሆኑ ጠቃሚ የማስተማርና መማር ሂደቶችን የሚያበረታቱም ናቸው በማለት ይገልጿቸውም ነበር። ከዚህም በላይ አንዳንድ ተመራማሪዎች የፈተናዎች አግባብነት (Validity) ሊለካ የሚገባው በማስተማር ላይ በሚፈጥሩት ጠቃሚ (beneficial) ተፅዕኖ ደረጃ ሊሆን እንደሚገባው ይገልፁ ነበር (Alderson እና Wall 1993)።

በተለይ በቋንቋ ትምህርት ፈተና ስለሚኖረው ተፅዕኖ በተለያዩ ስያሜዎች የተለያዩ ጥናቶች ሲካሄዱ የነበረ መሆኑ እንዳለ ሆኖ በወሸባክ ስያሜና ብያኔ መሰረት በተግባራዊ ሥነ-ልሳን ጉልህ ጥናቶች መካሄድ የቻሉት ካለፉት አራትና አምስት አሠርት ዓመታት ወዲህ በተለይም ከAlderson እና Wall (1993) ጥናት በኃላ ነው ማለት ይቻላል። "ወሸባክ... በአጠቃላይ ትምህርትም ሆነ በቋንቋ ፈተና ዋነኛ የጥናት መስክ እየሆነ መጥቷል" የሚለው የAlderson (2004፡ix) አገላለፅም ይህንኑ የሚያሳይ ነው።

በቋንቋ ፈተና ተፅዕኖ፣ "ወሸባክ" የሚለው ስያሜ ተቀባይነት እያገኘ ይምጣ እንጅ ለቃሉ በሚሰጠው ብያኔና ወሰን (scope) ረገድ ግን በመስኩ ምሁራን መካከል ልዩነት የለም ማለት አይቻልም። ይሁን እንጅ በተግባራዊ ሥነ-ልሳን በስፋት አገልግሎት

ላይ እየዋለ ያለው ወሸባክ የሚለው ቃል ዋነኛና ጠባብ (Micro) ትርጉም፣ የቋንቋ ፈተና በቋንቋ ማስተማርና መማር ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ነው (Alderson 2004፣ Cheng 2005፣ Cheng እና Curtis 2004) የሚለው ነው፡፡ በዚህ ብያኔ አብዛኞቹ የተግባራዊ ሥነ-ልሳን ተመራማሪዎች ይስማማሉ ማለት ይቻላል፡፡

Cheng (2004) አያይዘው እንደሚገልፀት በቋንቋ ፈተና ምርምሮች ዋነኛ ጉዳይና ችግር ተደርገው የሚወሰዱት የፈተናዎቹ አስተማማኝነት (consistency) እና አግባብነት (validity) ናቸው፡፡ ሁለቱም በራሳቸው በፈተናዎቹ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ወሸባክ ግን ፈተናዎች በተማሪዎች፣ በመምህራን፣ በትምህርት ይዘት፣ በማስተማሪያ ማቴሪያሎች ወዘተ. ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ እንጂ ከራሳቸው ከፈተናዎቹ ባህርያት ላይ የሚያተኩር አይደለም፡፡ በመሆኑም የወሸባክ ጥናት በአስተማማኝነትና በአግባብነት ላይ ከሚካሄድ ጥናት ይለያል ማለት ነው፡፡ በእርግጥ Green (2007) በተወሰነ ደረጃ ከCheng (2004) ሀሳብ የሚለይ አተያይ አላቸው፡፡ እንደሳቸው እምነት የፈተና ወሸባክ በትምህርት እንዲዳብሩ በሚፈለጉ ችሎታዎችና በፈተናዎች መካከል ከሚኖር ተዛምዶ ላይ የሚነሳ ነው፡፡

የወሸባክ ጥናት ፈተና በአዎንታዊም በአሉታዊም አቅጣጫ በክፍል ውስጥ ለሚከናወኑ ነገሮች ከፍተኛ ጫና የሚፈጥርና የወሳኝነት ሚና ያለው ነው፤ ከሚለው የAlderson እና Wall (1993) አተያይ የሚነሳ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ አተያይ በመነሳት Cheng (2000)፣ የWall እና Alderson (1993:41)ን አባባል ጠቅሰው “ወሸባክ ፈተና በቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ላይ የሚፈጥረውን ጫና የሚመለከት ነው” ይላሉ፡፡ ወሸባክ “የቋንቋ ፈተና በማስተማርና መማር ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ነው፤” የሚለው የBailey (1996፣195) እንዲሁም “ባጠቃላይ አነጋገር ወሸባክ ፈተናዎች በማስተማር ላይ ተማሪዎች ለፈተና እንዴት መዘጋጀት እንዳለባቸው የሚፈጥሯቸውን ተፅዕኖዎች የሚመለከት ነው” የሚለው የBrown (2004:28) ትርጉም ቀደም ብለው የቀረቡትን ብያኔዎች የሚጋሩ ናቸው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በካሄዷቸው ጥናቶች ስለወሸባክ ሲያነሱ የኖሩት Mesickም በተለይ ከቋንቋ ፈተና ጋር አያይዘው ባካሄዱት የ(1996) ጥናታቸው ወሸባክ በተግባራዊ ሥነ-ልሳን ትልቅ ቦታ የተሰጠው ፅንሰ ሀሳብ መሆኑን አውስተው ምንነቱን ሲገልፁ “...የቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ፈተናው ባይኖር

ላይሰሯቸው የሚችሏቸውን ነገሮች እንዲያከናውኑ ጫና የሚያደርግ ነው፤ የጫናው ውጤትም ቋንቋ መማርን የሚያጎለብት ወይም የሚያቀጭጭ ሊሆን ይችላል፤" ይላሉ (Mesick 1996:241)::

ወሸባክን ከዚህ በተለየና በሰፋ መልኩ የሚያዩትም አሉ:: ወደኋላ የወሸባክ ወሰን በሚለው ክፍል ከቀረበው ማብራሪያ ማስተዋል እንደሚቻለው ከነዚህ አንዱና ብዙዎቹ የሚጋሩት ፈተና በመምህራን፣ በተማሪዎች፣ በወላጆች፣ በትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች፣ በሥርዓተ ትምህርትና መርሐ ትምህርት ቀራጮች፣ በፓሊሲ ነዳፊዎችና በመሳሰሉት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ እንደሆነ ተደርጎ የሚሰጠው ትርጉም ነው (Bachman and Palmer 1996፤ Bailey 1996)::

በዚህ ጥናት፣ በBachman እና Palmer (1996) እና Bailey (1996) የተገለጹት የተወሰኑ ክፍሎች እንዲካተቱ ቢደረግም የበለጠ ትኩረት የተሰጠው አስተሳሰብ፣ ወሸባክ የቋንቋ ፈተናዎች በቋንቋ ማስተማርና መማር ወይም በቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ነው የሚለው ነው::

ከዚህ በቋንቋ ማስተማርና መማር ሂደት ላይ ፈተና ከሚያሳድረው ተፅዕኖ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ የወሸባክ ደረጃ (quality) ከፈተናው ጥራት ጋር ሁልጊዜ የሚተሳሰር ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ ነው:: ይህን በሚመለከተ የሚሰጠው አስተያየት ሊተሳሰሩም ላይተሳሰሩም የሚችሉ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው:: እንደAlderson እና Wall (1993) እምነት ወሸባክ ፈተናዎች የቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ፈተናው ባይኖር የማይሰሩትን እንዲሰሩ ማድረግ ከሆነ ጥሩ የሚባሉ ፈተናዎች ይህን ማድረግ ሊሳናቸው፣ ደካማ (Poor) የሆኑት ደግሞ ተማሪዎችና መምህራን ጠቀሚ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ሊያደርጉ ይችላሉና ግንኙነታቸው ሁልጊዜ ቀጥታ ላይሆን ይችላል:: በዚሁ መሰረት ጥሩ የማይባሉ ፈተናዎች ሆነው መምህራንና ተማሪዎች የማስተማርና መማር ሂደቱን የሚያፋጥኑ (ፈተናዎቹ ባይኖሩ የማያከናውኗቸውን) ነገሮች እንዲያከናውኑ የሚያደርጉ ሊሆኑ ይችላሉ:: ለምሳሌ መምህራኑ የሚያስተምሩትን ትምህርት በጥንቃቄና በጥልቀት አቅደው እንዲያስተምሩ፣ ተማሪዎች ለመማር እንዲነሳሱ፣ የቤት ስራዎቻቸውን በአግባቡ እንዲሰሩ፣ እንዲያነቡና እንዲያጠኑ፣ በየዕለቱ የሚቀረብላቸውን ትምህርት

ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉ... የሚያደርጓቸው ከሆኑ ፈተናዎቹ ደካማ ቢሆኑም ተፈላጊ ባህርይ እንዲያዳብሩ አድርገዋቸዋል ማለት ነው(Alderson እና Wall 1993: 117)።

በሌላ በኩል ደግሞ ፈተናዎቹ ጥሩ ሆነው የማስተማርና የመማር ሂደቱን በማበረታት ፈንታ ተማሪዎቹ ለጭንቀት እንዲጋለጡ የሚያደርጉ፣ መምህራኑ ተማሪዎቻቸው ደካማ ውጤት አምጥተው እንዳያሳፍሯቸው በስጋትና በፍርሃት እንዲዋጡ የሚያደርጉና በዚሁም ስጋትና ፍርሃት የተነሳ ለፈተና እንዲያስተምሩ (Teaching for test)፣ ሥርዓተ ትምህርቱን በማይፈለግ ሁኔታ እንዲያዛቡት (Narrowing of the Curriculum) የሚያስገድዱ ሊሆኑ ይችላሉ (Alderson and Wall 1993)።

ከላይ በቀረበው ሀሳብ መሰረት ከታየ በፈተናዎችና በተፅዕኖዎቻቸው መካከል ያለው ግንኙነት በቀላሉ የሚለይ ወይም ጥሩ ፈተናን ከጥሩ ተፅዕኖ ፈጣሪነት፣ ደካማ ፈተናን ከጎጂ ተፅዕኖ ፈጣሪነት ጋር ማያያዝ አዋጭ አተያይ ላይሆን ይችላል። የተፅዕኖው ዓይነት ከፈተናዎች የጥራት ደረጃ ጋር ተሳስሮ ላይገኝና የፈተናው ጥራት ጥገኛ ላይሆን/ ነፃ (Independent) ሊሆን ይችላል (Alderson እና Wall 1993)። ከፈተናዎቹ ጥራት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ላይኖረው የሚችልበት ሁኔታ ካለ ደግም ራሱን ችሎ ሊጠና ይገበዋል። ስለዚህ የተፅዕኖውን ዓይነትና ደረጃ ለመለየት የክፍል ትምህርቱን በጥልቀት ማጥናትን የሚጠይቅ ነው።

አንዳንዶቹ ለምሳሌ Green (2007)፣ Howkey (2006) ይህን ሀሳብ የሚጋሩ አይመስሉም። እንደነሱ አተያይ ፈተናዎች ጥሩ ፈተና የሚባሉት የጥሩ ትምህርት ነጸብራቅ ሲሆኑ ነው፤ ሁሉቱ አግባብ ያለው ተጣጥሞሽ/ ዝምድና (Overlap) ካላቸው ደግሞ ወሸባኩ አዎንታዊ ይሆናል። በብዙ ጥናቶች የተረጋገጠውም የጥሩ ፈተና ባሕርያትን ተከትለው የሚዘጋጁ አዎንታዊ ወሸባክን፣ ደካማ የሚባሉ ፈተናዎች ደግሞ አሉታዊ ወሸባክን የሚያበረታቱ መሆናቸው ነው።

ሌላው ከወሸባክ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሀሳብ የፈተናዎች ተነሳሽነትን ከመፍጠር፣ ሥርዓተ ትምህርትን ከማሻሻል ብሎም ለለውጥ ከማብቃት ጋር የሚኖራቸው ሚና ነው (Cheng 2005፣ 2004፣ 2000)። ለምሳሌ Alderson እና Wall (1993)

እንደሚገልፁት ፈተና ለመማር ያለን የመነሳሳት ደረጃ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የመማር ሂደትም እየጨመረ ይሄዳል። Cheng (2005)ም ይህን ሀሳብ ይጋራሉ።

2.6 በወሽባክ ጫና ሊደርስባቸው የሚችሉ ጉዳዮች (Areas Affected by Washback)

በተለያዩ በወሽባክ ላይ ምርምር ባካሄዱ ምሁራን ስራዎች እንደተገለጸው ፈተናዎች በክፍል ትምህርት የተለያዩ አቅጣጫዎች ላይ የተለያዩ ተፅዕኖዎችን ያደርሳሉ። በፈተናዎች ተፅዕኖ የሚደርስባቸው ዋና ዋና ጉዳዮችም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የትምህርቱ ተግባራት/ የጊዜ ድልደላ (Activities or Time Arrangement)

በቅርብ ጊዜ የተካሄዱ ጥናቶች እንዳረጋገጡት መምህራን በውጫዊ ፈተና የሚካተቱ (ሊካተቱ ይችላሉ ብለው የሚገምቷቸውን) ክሂሎች/ የትምህርት ክፍሎች የሚመለከቱ ተግባራትን የተለየ ትኩረት ሰጥተው ወይም የተሻለ ጊዜ መድበው ያስተምራሉ (Chen 2002፣ Shohamy እና ሌሎች 1996፣ Spratt 2005)። Cheng (1995፣ 2005) ደግሞ በሆንግ ኮንግ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የክፍል ምልከታ በማካሄድ፣ ይህንኑ መምህራን በፈተና የሚሸፈኑ/ ሊሸፈኑ ይችላሉ የሚባሉ ተግባራትን የበለጠ ትኩረት ሰጥተው /የተሻለ ጊዜ መድበው የሚያስተምሩ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። ይህም ተማሪዎቻቸው በፈተና ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡላቸው /ለስኬት እንዲበቁላቸው ከመሻት የሚያከናውኑት ተግባር እንደሆነ መገመቱ አይከብድም።

ለ. ሥርዓተ ትምህርት (Curriculum)/ የትምህርት ይዘት

በተለያዩ ጥናቶች እንደተረጋገጠው፣ በፈተናዎች ተፅዕኖ ከሚደርስባቸው ጉዳዮች አንዱ ሥርዓተ ትምህርት ወይም የትምህርት ይዘት ነው። ሥርዓተ ትምህርት ላይ ብዙውን ጊዜ የሚከሰቱት ተፅዕኖዎችም ሥርዓተ ትምህርትን የማጥበብ ነገር ነው። ይኸውም ፈተናው ሊያተኩርባቸው ይችላል ወደሚባሉት ይዘቶች በማተኮርና ሌሎች ይዘቶችን ባለማስተማር የሚከሰት የተፅዕኖ ዓይነት ነው(Alderson እና Hamp-Lyons 1996፣ Alderson እና Wall 1993፣ Chen 2002ሀ)። የዚህም ተጽዕኖ አንዱ መገለጫ በፈተና ለሚካተቱ ይዘቶች የበለጠ ጊዜ የመመደብ ነገር የሚታይ መሆኑ ነው (Spratt

2005:9):: Alderson ((2004) ፈተና በትምህርት ይዘት ላይ ተጽዕኖ ማድረሱ አጠያየቅ አይደለም፤ ማለታቸውም ፈተና በትምህርት ይዘት ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀሬ መሆኑን ለማመልከት ነው። በተለያዩ ሀገራት የተካሄዱ አብዛኞቹ ተግባራዊ ጥናቶችም (ለምሳሌCheng 2004፣ 2005፣ Hayes እና Read 2004፤ Wall እና Alderson 1993) ይህንኑ በፈተናዎች ተጽዕኖ ምክንያት አብዛኞቹ መምህራን ለትምህርት ይዘቶች የሚሰጡት ትኩረት እኩል እንደማይሆን (የመማር ማስተማር ሂደቱ በፈተና ሊካተቱ በሚችሉ ይዘቶች ላይ እንዲያተኩር እንደሚያደርጉ) አረጋግጠዋል።

ሐ. የትምህርት መሣሪያዎች/ ማቴሪያሎች

Alderson (2004) ሌላው አይቀሬ የፈተና ተጽዕኖ አድርገው የገለጹት ፈተና በትምህርት ማቴሪያሎች ላይ የሚያሳድረውን ጫና ነው። በወሸባክ ጥናት የትምህርት መሣሪያዎች የሚለው የሚያመለክተውም ፈተና-ነክ መጻሕፍትንና ያለፉ ዓመታት የፈተና ወረቀቶችን ነው (Spratt 2005)። በዚህም ረገድ በፈተናዎች ተፅዕኖ እንደሚከሰት የሚያሳዩ ግኝቶች አሉ (Spratt 2005)። ለምሳሌ የAlderson እና Wall (1993)፣ Cheng (1997) ጥናቶች ፈተናዎች መምህራንና ተማሪዎች ከፈተና ጋር የተያያዙ ወይም ለፈተና የሚጠቅሙ ተጨማሪ መሣሪያዎችን/ ማቴሪያሎችን እንዲጠቀሙ እንደሚያደርጉ አሳይተዋል። Howkey (2006) ደግሞ ተግባቦታዊ ትምህርትን የሚያበረታታ ፈተና ባጠኑበት ጥናት መምህራን ከመማሪያ መጽሐፎቹ በተጨማሪ ከሌሎች ምንጮች (Sources) የተለያዩ ተጨማሪ ማቴሪያሎችን (ይዘቶችንና ተግባሮችን) እየተጠቀሙ እንዲያስተምሩ እንዳበረታታቸው አስረድተዋል። ይህም ብዙ ጊዜ መምህራን ፈተናው የሚያበረታታ ከሆነ ተማሪዎቻቸውን ለውጤት የሚያበቁላቸውን ተጨማሪ ማቴሪያሎች ከመጠቀም ወደኋላ እንደማይሉ የሚያሳይ ነው።

መ. የማስተማሪያ ዘዴዎች

የማስተማሪያ ዘዴ የማስተማሪያ ስልቶችን ወይም ቴክኒኮችን የሚመለከት ነው።

በዚህ በማስተማሪያ ዘዴ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ግኝቶችም ወጥነት የላቸውም፤ የተለያዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የAlderson እና Wall (1993:127) የስሪ ላንካ ጥናት፣ ፈተናዎች በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ተፅዕኖ እንደሚፈጥሩ አላሳየም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የ Howkey(2006) እና Shohamy እና ሌሎች (1996) ጥናቶች ከፍተኛ ውሳኔ የሚወሰንባቸው (High-stakes) ፈተናዎች በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይም ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ አመልክተዋል፡፡

ሠ. በመምህራን የሚዘጋጁ የክፍል ፈተናዎች/ ምዘናዎች (Assessment)

በChen (2002)፣ Spratt (2005)፣ Wall እና Alderson (1996)፣ ሥራዎች እንደተገለጸው ብሄራዊ /ውጫዊ ፈተናዎች በመምህራን የክፍል ትምህርት የምዘና ሂደት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ የተጽዕኖው ዓይነትም በሌሎች ክፍሎች ላይ ሊታይ እንደሚችለው ሁሉ፣ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ወይም ሁለቱም ገጽታዎች የሚታዩበት ሊሆን ይችላል፡፡ ፈተናዎች በክፍል ትምህርት ምዘና ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉም ለምሳሌ በShohamy ሌሎች (1996) በእስራኤል ሀገር የተካሄደ ተግባራዊ የወሸባክ ጥናት አሳይቷል፡፡ የAlderson እና Wall (1993) የስሪላንካ ጥናት ሌላው ያሳየው ግኝትም እንዲሁ ውጫዊ/ ብሔራዊ ፈተናዎች መምህራን በሚያዘጋጇቸው የክፍል ፈተናዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ መቻላቸውን ነው፡፡

ረ. የመምህራንና ተማሪዎች ስሜትና አመለካከት (Feelings & Attitudes)

ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን ለፈተናዎችና ፈተናዎቹ ለሚዘጋጁባቸው ትምህርቶች በፈተናዎቹ ምክንያት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ስሜትና አመለካከት ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የAlderson እና Hamp-Lyons (1996)፣ Read እና Hayes (2003)፣ Shohamy እና ሌሎች (1996) ጥናቶች እነዚህ ተቃራኒ ስሜቶችና አመለካከቶች በፈተናዎቹ ተፅዕኖ የተነሳ ሊከሰቱ የሚችሉ መሆናቸውን አሳይተዋል፡፡

ሰ. መማር (Learning)

ፈተናዎች በተማሪዎች መማር ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ? ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ከሆነ እንዴት? በሚለው ጉዳይ ላይም አንዳንድ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ የጥናቶቹ ግኝቶች

እንደሚያመለክቱትም በተማሪዎች የመማር ስትራቴጂዎችና የመከወን ችሎታ ላይ ፈተናዎች ተፅዕኖ መፍጠር እንደሚችሉና የተፅዕኖዎቹ ዓይነትም አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን እንደሚችል አመላክተዋል(Alderson እና Hamp-lyons 1996)። ለምሳሌ ፈተናዎች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች ከማዳበር ይልቅ ቃላትና ሰዋስው ሽምደዳ ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግ በመማር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ። ሁለተኛ ከዚህ በተቃራኒ የነShohamy(1993) ጥናት ግኝት እንዳመለከተው ችላ ተብለው የነበሩ የቋንቋ ክሂሎች በፈተና በመካተታቸው ፈተናዎች፣ ተማሪዎች እነዚህን ክሂሎች ለመማር እንዲነሳሱና በነዚህ ክሂሎች ያላቸውን ችሎታ እንዲያዳብሩ በማድረግ አዎንታዊ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ (Shohamy እና ሌሎች 1996)::

2.7. በወሽባክ ላይ ጫና የሚያሳድሩ ምክንያቶች (Factors Affecting Washback)

ፈተና በመምህራንና ተማሪዎች (በመማር ማስተማር ሂደት) ላይ እንዲሁም በሌሎች የትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር በሳይንሳዊ መንገድ የተካሄዱ ተግባራዊ ጥናቶች (ለምሳሌ Alderson እና HampLyons 1996፣ Alderson እና Wall 1993፣ Andrews እና ሌሎች 2002፣ Cheng 1997፣ 2005፣ Shohamny እና ሌሎች 1996፣ Qi 2004፣ Watanahe 1997) አረጋግጠዋል። ሆኖም ፈተናዎች በትምህርት /በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳድሩ የሚያደርጉ ሌሎች ምክንያቶች እንዳሉም የታወቀ ነገር ነው (Alderson እና Wall 1993፣ Chen 2002፣ Spratt 2005)።

ፈተናዎች በተለይም ውጫዊ/ብሔራዊ ፈተናዎች በትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ ወይም ከBaily (1996) እና Hughes (1993) ስያሜ አንፃር በተሳታፊዎች ግንዛቤና ተግባር ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ በተለያዩ ምክንያቶች (factors) ላይ የሚመሰረት ነው (Chen 2002፣ Ghobani 2008፣ Spratt 2005)። ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል ዋነኛዎቹ ከመምህራን ጋር የተያያዙ (የመምህራን ባህርያት) ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃነት የሚጠቀሱት ደግሞ ከዐውድ (Context) ጋር የተያያዙ ምክንያቶች ናቸው።

2.7.1 ከመምህራን ጋር የተገናኙ/ የተያያዙ ምክንያቶች (Teacher related factors/Teachers` Characterstics)

በተከታታይ የተካሄዱ ጥናቶች እንዳሳዩት ለወሽባክ መከሰት፣ ለአከሳሰቱ መንገድ /እንዴትነትና ደረጃ /degree) ዋነኛውን ሚና የሚጫወቱት መምህራን ናቸው (Spratt 2005)። ከነዚህ ከመምህራን ጋር ከተያያዙ ምክንያቶች መካከል ጉልህ ጉልህ የሆኑትን በአጭር በአጭሩ ከዚህ ቀጥሎ ለመቃኘት ተሞክሯል።

ሀ. የመምህራን የትምህርት ደረጃ

መምህራኑ ያጠኑት ትምህርት ወይም የትምህርት ዳራቸው በተለይም በትምህርት ላይ በቆዩባቸው ወቅቶች የወሰዷው ሥነ-ዘዴያዊ ስልጠናዎች ስለ ፈተና ተፅዕኖ ለሚያዳብሩት ግንዛቤ አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል (Spartt 2005፣ Wall እና Alderson 1993፣ Watanabe 1997)። ይህም አንዳንድ ስልጠናዎች ሠልጣኞቹ ይበልጥ ለፈተና ተፅዕኖ እንዲጋለጡ፣ ሌሎቹ ደግሞ እንዲህ ያለ ጫና ስር እንዳይወድቁ ሊያደርጉ እንደሚችሉ የሚያመለክት ነው።

ለ. የመምህራን የማስተማር ልምድ

Chen (2002)፣ Cheng (1995)፣ Watanabe (1996ሀ) እና (1996ለ) በመጥቀስ እንዳስረዱት በውጫዊ ፈተናዎችና በማስተማር ሥራ መካከል ያለን ግንኙነት የመረመሩ ብዙ ጥናቶች የመምህራን የማስተማር ልምድ በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ለሚከሰት የፈተና ወሽባክ አንድ ምክንያት እንደሆነ አረጋግጠዋል። ልምድ ባላቸውና በጀማሪ መምህራን ላይ ፈተናዎች የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ልዩነት የተመረመረበት ሌላው ስራ የShohamy እና ሌሎች (1996) ጥናት ነው። በዚህም ጥናት የተገኘው ውጤት ቀደም ሲል ከተገለጹት የጥናት ውጤቶች ጋር የሚመሳሰል ነው። በዚህ ጥናት ሪፖርት እንደተመለከተውም ከጀማሪ መምህራን ይልቅ ልምድ ያላቸው መምህራን ይበልጥ ለፈተና ተፅዕኖ የተጋለጡ ናቸው። በመሆኑም እነዚህኛዎቹ (ልምድ ያላቸው) ብዙ ጊዜ ከፈተና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን

ማስተማር ላይ ያተኩራሉ። የሚጠቀሙባቸው ማቴሪያሎችም ፈተና ተኮር ናቸው (Shohany እና ሌሎች (1996)።

ሐ. ለማስተማር ሙያ የሚሰጥ ክብር (Professional Dignity)

በተለያዩ የወሽባክ ተመራማሪዎች እንደተገለፀው ለሙያ የሚሰጥ ክብር፣ የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ከፈተና ውጤት ጋር እንዲያያዝ ሊያደርግ ይችላል። ለምሳሌ Ghorbani (2008) Khawya (1990)ን በመጥቀስ እንደገለፁት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መምህራን ተማሪዎቻቸው በፈተናዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ማገዝን/ ለፈተና ማዘጋጀትን የጥሩ መምህርነት መገለጫ አድርገው ያዩታል። በAlderson እና Wall (1993) ሥራም መምህራን ተማሪዎቻቸው በፈተናዎች ጥሩ ውጤት ሲያመጡ ጥሩ እንዳስተማሩ ወይም ሙያዊ ግዴታቸውን በአግባቡ እንደተወጡ፣ በአንፃሩም ተማሪዎቻቸው ዝቅተኛ ውጤት ሲያመጡ ወይም ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ ወይም ሥልጠና ሳያልፉ ሲቀሩ መሥራት የነበረባቸውን ተግባር በአግባቡ ያልሠሩ ሆኖ እንደሚሰማቸው ወይም እንደሚከፉ ተገልጿል።

ይህም መምህራን ስለሙያቸው ያላቸው ግንዛቤ በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግባራቸው ላይ ለሚከሰት ወሽባክ አስተዋፅኦ እንዳለው የሚያሳይ ነው። በዚህም ምክንያት መምህራን ከፈተና ጋር የተያያዙ ትምህርቶችንና የፈተና አሠራር ስትራቴጂዎችን ትኩረት ሰጥቶ ማስተማርን ሙያዊ ግዴታን/ ኃላፊነትን በአግባቡ እንደመወጣት ሊያዩት እንደሚችሉ፣ በአንፃሩም በፈተና የማይካተቱ የትምህርቱ ክፍሎች/ ይዘቶችና ክሂሎች ችላ እንዲባሉ እንደሚያደርግ የተለያዩ ጥናቶች ውጤት (ለምሳሌ የGhorbani 2008) አሳይቷል። እንዲህ ያለ ተፅዕኖ ደግሞ በተለይ ፈተናው ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር የማይያያዝ ወይም የሥርዓተ ትምህርቱ ዓላማዎች ነፀብራቅ ካልሆነ አሉታዊ ወሽባክን የሚያበረታታ ሊሆን የመቻሉን አጋጣሚ የሰፋ ያደርገዋል።

በእርግጥ የGhorbani (2008) ጥናት ውጤት እንዳመለከተው ለሙያ የሚሰጥ ክብር እንደየዐውዱ/ እንደየሀገሩ ወይም እንደየአካባቢው/ ቦታው ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ በኢራን የማስተማር ሙያ ክብር የሚገለጸው ተማሪዎችን በፈተና ለጥሩ ውጤት/

ለስኬት ማብቃት በመቻል ሲሆን በጃፓንና ማሌዥያ ባሉ የኢራናውያን ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የጥሩ መምህርንነት መገለጫ ተማሪዎችን በፈተና ለውጤት ከማብቃት በተጨማሪ በሚማሩት ቋንቋ የመጠቀም/ የመግባባት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማስቻልን የሚያካትት ነው፡፡ በእነዚህ ቦታዎች ለማስተማር ሙያ ያለው ግንዛቤ ትንሽ ለየት ይላል፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳ በእነዚህም ቦታዎች አንዱ የሙያ ብቃት መለኪያ ተማሪዎችን በፈተና ለስኬት ማብቃት ቢሆንም ከዚህ በተጨማሪ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ማዳበር ማስቻልም ሁለተኛው የሙያ ብቃት መለኪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚሁ መሠረት በእነዚህ ቦታዎች የተማሪዎችን የተግባቦት (communicative) ችሎታ የሚያዳብር ትምህርት ማስተማር አንዱ የመምህርነት ግዴታ ነው፡፡ ይህን ተግባር ማከናወን መቻልም ጥሩ መምህር ወይም የሙያ ግዴታውን የተወጣ መምህር ያሰኛል (Ghorbani 2008))፡፡ ይህም መምህራን ሁለቱንም ኀላፊነቶች ከግብ ለማድረስ ጥረት እንዲያደርጉ የሚያበረታታ ነው (Gohaboni 2008)፡፡

በአጠቃላይ በሁሉም አቅጣጫ ያለው ግንዛቤ መምህራን ሙያዊ ክብራቸውን አስጠብቀው ለመቀጠል ፈተና ተኮር ስራ ይሰራሉ፡፡ ይህም የማስተማር ዝግጅታቸውና ትግባራቸው ላይ ወሸባክ እንዲከሰት የሚያደርግ አንድ ምክንያት እንደሆነ የሚያሳይ ነው (Alderson እና Hamplion 1996፣ Chen 2002)፡፡

መ. መምህራን ስለፈተናው ያላቸው ዕውቂያ (Awarness)

መምህራን ስለውጫዊ ፈተናዎች ወይም በፈተናዎቹ ስለሚመዘኑ ጉዳዮች (ክሂሎችና ሌሎች ይዘቶች) እና የአጠያየቅ ስልቶች (formats) እያወቁ በሄዱ ቁጥር ለፈተናው ተዕዕኖ ይበልጥ እየተጋለጡና የሚያስተምሩት ትምህርት ይበልጥ ፈተና ነክ /ተኮር እየሆነ ይመጣል (Alderson እና Wall 1993፣ Chen 2002ሀ እና 2002ለ)፡፡ በእርግጥ Chen(2002ለ) Hughes (1988)ን በመጥቀስ እንደገለፁት ፈተናው ከትምህርቱ/ ከሥርዓተ ትምህርቱ ላይ የተመሠረተ ከሆነ ለፈተና ማስተማር የትምህርቱን ዓላማዎች ለማሳካት ማስተማር ይሆናል፡፡ በአንፃሩ ፈተናውና ትምህርቱ አዎንታዊ ተዛምዶ የሌላቸው ከሆነ መምህራን ስለፈተናው ይዘቶች፣ ክሂሎችና የአጠያየቅ ስልቶች እያወቁ በሄዱ ቁጥር ትኩረታቸውም በፈተናው በሚካተቱ ጉዳዮች ላይ ብቻ

እየሆነ ሊመጣ ይችላል። በሁለቱ መካከል (በትምህርቱና በፈተናው) የሚኖረው ግንኙነትም አዎንታዊ ሳይሆን አሉታዊ እየሆነ ይሄዳል። ይህም መምህራኑ የትምህርቱን ዓላማዎች ለማሳካት ከመጣር ይልቅ በፈተናዎቹ በሚካተቱ ጉዳዮችና አጠያየቆች ላይ አተኩረው እንዲሰሩ የሚያደርግ ይሆናል። በሌላ አባባል የመማር-ማስተማር ሂደት የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር የማያስችል እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል። የAlderson እና Hamplyon (1996) እና የChen (2002ሀ) እና (2002ለ) ጥናት ግኝቶችም ይህንኑ ማለትም መምህራኑ ስለፈተናው ይዘትና የአጠያየቅ ስልት ይበልጥ እያወቁ ሲሄዱ የማስተማር ዝግጅታቸውንና ትግባራቸውን ይበልጥ ፈተና ላይ እንዲያተኩር እንደሚያደርጉ አሳይተዋል። መምህራኑ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያም በማስተማር ትግበራቸው ሂደት ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን በማየት እያደገ የሚመጣ ነው (Andrews እና ሌሎች 2002)።

መምህራን ስለፈተናው የሚኖራቸው እውቅና እያደገ በሄደ ቁጥር የማስተማር ዝግጅቱና ትግባራው በፈተናው በሚሸፈኑ የትምህርቱ ክፍሎች ላይ እንዲያተኩርና ሌሎች በፈተናው የማይሸፈኑ ክፍሎች ችላ እንዲባሉ የሚያደርግ መሆኑ ደግሞ የፈተና ወሽባክ፣ መምህራን ስለፈተናው በሚኖራቸው እውቅና ምክንያት እንደሚከሰት ያሳያል።

ሠ. መምህራን ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ

መምህራን ውጫዊ ፈተናዎች በተማሪዎች ቀጣይ ሕይወት ላይ ለምሳሌ ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ ማለፍ አለማለፋቸው ላይ ለሚወሰን ውሳኔ የሚያስመዘግቡት ውጤት ጠቃሚ ነው የሚል ግንዛቤ በሚያዳብሩበት ጊዜ ፈተና ነክ ጉዳዮች ላይ አተኩረው የማስተማር ነገር ይታይባቸዋል (Alderson እና Hamplyons 1996፣ Chen 2002)። ስለዚህ አንድ ፈተና የሚኖረው ሚና /የጠቀሜታ ደረጃ ከፍ ያለ በሚሆንበት ጊዜ በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግባራ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖም ከፍ ያለ እንዲሆን ያደርገዋል (Shohamy እና ሌሎች 1996)። በስማቸው (2012) ስራ የተጠቀሱት Buck (1988) እንደገለፁትም ፈተናው ለመምህራን የስራ ደረጃም ሆነ ለተማሪዎች ማለፍ አስፈላጊ ሆኖ እያገኙት በመጡ ቁጥር መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባሮች ይበልጥ ፈተና ተኮር እየሆኑ

እንዲመጡ ያደርጋቸዋል። የፈተና ውጤት ለተማሪዎች ቀጣይ ሕይወት ጠቃሚና የመምህራንን የማስተማር ብቃት መለኪያ ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ ደግሞ መምህራን የማስተማር ሥራቸውን ፈተና ላይ እንዲያተኩር እንዲያደርጉት መገፋፋቱ የማይቀር ነው ማለት ነው። ይህም የአንድ ፈተና ውጤት የጠቀሜታ ደረጃ ከፍ እያለ መሄድ አንዱ የወሸባክ መከሰቻ ምክንያት ሊሆን መቻሉን የሚያሳይ ነው።

ከእነዚህ በተጨማሪ የመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎና የመምህራኑ ያታ ለወሸባክ መከሰት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ (Chen 2002ሀ)።

2.7.2. ከዐውድ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች (Context Related Factors)

ለወሸባክ መከሰት ዋነኛ ምክንያቶች የመምህራን ባህሪያት (Characterstics) /ከመምህራን ጋር የተያያዙ ምክንያቶች ቢሆኑም ከዐውድ ጋር የተያያዙ ምክንያቶችም (factors)፣ እንዲሁ ለወሸባክ መከሰት አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ። በተለያዩ ተዛማጅ ጽሑፎችና ተግባራዊ ጥናቶች እንደተገለፀው ለወሸባክ መከሰት ጫና ሊፈጥሩ ከሚችሉ ምክንያቶች መካከልም ዋነኛዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ (Students` Learing Attitudes)

የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግባራ ላይ ተፅዕኖ ሊያደርሱ እንደሚችሉ የተለያዩ በወሸባክ ላይ ጥናት የሚያካሂዱ ተመራማሪዎች ይገልፃሉ(Chen 2002)። ብዙ ጊዜ ተማሪዎች መማር የሚፈልጉት በፈተና የሚካተቱ ትምህርቶችን/ ይዘቶችን እንደሆነና በፈተና የማይካተቱ ክሂሎችንና ሌሎች ይዘቶች መማር እንደማይፈልጉ ያመለከቱ የጥናት ውጤቶችም አሉ። የወሸባክ ጥናት በተካሄደባቸው የተለያዩ ቦታዎች (ለምሳሌ በሆንግ ኮንግ፣ ጃፓን፣ ታይዋን፣ ወዘተ.) ውጫዊ ፈተናዎች መምህራን ለፈተና እንዲያስተምሩ ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች ለፈተና እንዲማሩ የሚያደርግ ጭምር እንደሆነ አረጋግጠዋል (Chen 2002)። የእነዚህና መሰል ሌሎች ጥናቶች ግኝቶች እንዳመለከቱት ውጫዊ ፈተናዎች በአንድ በኩል ተማሪዎች ለመማር እንዲነሳሱ ያደርጋሉ። በሌላ በኩል

ደግሞ በፈተናዎቹ የማይካተቱ የትምህርቱ ክፍሎች ካሉ እነሱን ለመማር ፍላጎት እንዳይኖራቸው ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህም በተለይ በፈተና ውጤታማ ለመሆን በሚፈልጉ ተማሪዎች ላይ ጎልቶ ሊታይ ይችላል:: Chen (2002)፣ Beatie (1995)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ተማሪዎች የሚያሳድሩት ተጽዕኖ በፈተና የሚካተቱ ክፍሎችን መምህራኑ እንዲሸፍኑላቸው ጫና እስከመፍጠር ይደርሳል/ሊደርስ የሚችል ነው።

ለ. ውጫዊ ጫናዎች (External pressure in Teaching)

የHerman እና Golen (1991 እና 1993) ጥናቶች እንዳሳዩት ፈተና ከመማር ማስተማር ጋር የተያያዘ ስለሆነ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የፈተና ውጤት ከፍ እንዲያደርጉ፣ በውጫዊ ሀይሎች ለምሳሌ በርዕሰ መምህራን፣ በሌሎች የትምህርት ቤት አስተዳደር ክፍሎች፣ በወላጆችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጫና ሊደረግባቸው ይችላል። ይህም ጫና ለወሸባክ መከሰት አንዱ ምክንያት እንዲሆን ያደርገዋል። የGhorbani 2008 እና Shih (2007) ጥናት ውጤቶችም ይህን ሀሳብ ይጋራሉ። ይህም በባለድርሻ አካላት ተጽዕኖ ምክንያት መምህራን ፈተና ነክ የሆኑ ክሂሎች ወደማስተማር እንዲያተኩሩና በፈተናው የማይካተቱ የትምህርቱ ክፍሎችን ችላ እንዲሉ ሊያደርግ የሚችል አንድ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ነው።

በእርግጥ ለሙያ የሚሰጥ ክብር በሚለው ክፍል እንደተገለፀው በውጫዊ ሀይሎች በመምህራን ላይ ሊደርስ የሚችለው ተፅዕኖ የተማሪዎችን ውጤት እንዲያሻሽሉ/ ከፍ እንዲያደርጉ ጫና የሚፈጥር ብቻ ላይሆን ይችላል። የተማሪዎችን የፈተና ውጤት ከፍ ከማድረግ በተጨማሪ የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያበረታታም ሊሆን ይችላል (Ghorbani 2008)። መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለፈተና እንዲያዘጋጁም ሆነ የተማሪዎቻቸውን የቋንቋ ችሎታ እንዲያዳብሩ በውጫዊ ሀይሎች የሚደረግባቸው ጫናም ከመማሪያ መጽሐፎቹ በተጨማሪ ሌሎች ተጨማሪ አጋዥ መሣሪያዎችን /ማቴሪያሎችን እየተጠቀሙ እንዲያስተምሩና የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያስገድድም ሊሆን ይችላል (Herman እና Golon 1991 እና 1993)።

ሐ. የተማሪዎች የክፍል ደረጃ

በከፍተኛው የክፍል ደረጃ (Upper level) ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን የሚያስተምሩ መምህራን በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ላይ ከሚያስተምሩ መምህራን ይልቅ ይበልጥ ለፈተና ተፅዕኖ የተጋለጡ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህም ምክንያት እነዚህ በከፍተኛ የክፍል ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎችን የሚያስተምሩት መምህራን ትምህርት ይበልጥ ፈተና ላይ በሚመጡ የትምህርቱ ይዘቶችና ክሂሎች ላይ ያተኩሩ ሊሆኑ ይችላሉ (Shohamy እና ሌሎች 1996)።

በዚህ ጥናት ዐውድ ከፍተኛው የክፍል ደረጃ 10ኛ ክፍል ሲሆን ዝቅተኛው ዘጠነኛ ክፍል ነው። በዚሁ መሠረት ቀደም ብሎ ከቀረበው ሀሳብ አንፃር ዘጠነኛ ክፍል ከሚያስተምሩ መምህራን ይልቅ 10ኛ ክፍል በሚያስተምሩት ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ግንዛቤና ትግባራ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የጎላ ሊሆን ይችላል እንደማለት ነው።

የፈተናው ተፅዕኖ በከፍተኛ የክፍል ደረጃ ላይ በሚያስተምሩ መምህራን ላይ የጎላ እንዲሆን የሚያደርገውም በከፍተኛው የክፍል ደረጃ ላይ የሚማሩት ተማሪዎች ፈተናውን ለመውሰድ የተቃረቡ በመሆናቸው ነው (Shonamy እና ሌሎች 1996)። በተመሳሳይ ሁኔታ Alderson እና Wall (1993)ም ወደ ትምህርቱ ማጠናቀቂያ ባሉ የክፍል ደረጃዎች የሚያስተምሩ መምህራን የፈተናውን ዓላማዎች የሚያሳኩ ትምህርቶችና የትምህርት አሰጣጦች ላይ እንደሚያተኩሩ አረጋግጠዋል።

መ. የተማሪ-ክፍል ጥምርታ (Class size)

Chen 2002ሀ፣ (Watanabe 1996ሀ) ጠቅሰው እንደገለፁት የክፍል-ተማሪ ጥምርታም ኢርቱዕ በሆነ መንገድም (indirectly) ቢሆን መምህራን ፈተና ነክ ጉዳዮች/ ትምህርቶች ላይ እንዲያተኩሩ ሊያደርግ ይችላል። በAlderson እና Hamplyons (1996) ጥናትም የተማሪ-ክፍል ጥምርታ ለወሸባክ መከሰት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ተጠቁሟል። Spratt (2005) የLam (1994) የጥናት ግኝት በመጥቀስ

የተማሪ-ክፍል ጥምርታ ለወሽባክ መከሰት አንድ ምክንያት የሚሆንበት ሁኔታ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

ሠ. ለትምህርቱ የተፈቀደው/ የተመደበው ጊዜ

የትምህርት አሰጣጥ ፈተና ላይ እንዲያተኩር ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች አንዱ ለትምህርቱ የተፈቀደው ጊዜ መጠን ሊሆን ይችላል (Shohamy እና ሌሎች 1996)፡፡ በChen (2002) ጥናት መደምደሚያ ላይም ለትምህርት የተመደበ ጊዜ አንድን የትምህርት አሰጣጥ ፈተና ነክ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር እንደሚያደርገውና ወደፊት የሚካሄዱ የወሽባክ ጥናቶች ይህን ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው እንዲያጠኑት ጥቆማ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ ጥናት የተካሄዱት ሁለት የሙከራ ጥናቶች ውጤትም በChen (2002) የተጠቆመውን ሀሳብ የሚያንፀባርቁ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው የክፍል ጊዜ መጠን በዋናው ጥናት አንድ ምክንያት / ተለውጦ ሆኖ እንዲጠና ተደርጓል፡፡

የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ዳራ የሚለውም ሌላው ከሙከራ ጥናቶች ውጤት የመነጨ ምክንያት/ ተላውጦ ነው፡፡ ስለዚህ ይኸም በዋናው ጥናት በዐውዳዊ የወሽባክ መከሰት አንድ ምክንያትነት/ተላውጦነት እንዲካተት ተደርጓል፡፡

2.8 የወሽባክ መለኪያዎች (Dimennsions of Washback)

የተለያዩ የወሽባ ተመራማሪዎች (ለምሳሌ Alderson እና Wall 1993፣ Green 2007 Watanabe 2004) እንደሚገልፁት ወሽባክ ውስብስብ ክስተት ወይም የተለያዩ መለኪያዎች የተካተቱበት ውስብስብ ትምህርታዊ ክስተት ነው፡፡ ያም ሆኖ አንዳንድ ተመራማሪዎች መሰረታዊ የሚባሉ የወሽባክ መለኪያዎችን ለይተው ለማመልከት ችለዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ ቀጥሎ የቀረቡት ናቸው፡፡

2.8.1 የወሽባክ ወሰን (Scope)

በትምህርት ሥርዓት የፈተና ወሽባክ ወሰን አንዱ መለኪያ ነው፡፡ ከዚህ ከፈተና ተፅዕኖ ወሰን አንፃር ፈተና የሚያሳድረው ተፅዕኖ በሁለት ደረጃ ይመደባል፡፡ ጠባብ/

ውስጣዊ (Micro) እና ሰፊ/ ውጫዊ (macro) ተብሎ፡፡ ጠባብ የሚባለው የወሽባ ወሰን፣ ፈተና በክፍል ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ወይም በመምህራንና ተማሪዎች ግንዛቤና የማስተማር መማር ትግበራ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ነው (Bachman እና Palmer 1996፣ Bailey 1999፣ Cheng 2005፣ Watanabe 2004)፡፡ እነዚህ ተመራማሪዎች እንደሚያስረዱት ይህ ጠባብ የሚባለው የወሽባክ ወሰን ፈተናዎች በክፍል ውስጥ ዐውድ በተማሪዎችና በመምህራኑ ግንዛቤ፣ የመማር ማስተማር ትግበራና በትግበራው ውጤት ላይ ቀጥተኛና ፈጣን ተፅዕኖ የሚያሳድሩበት ሂደት ነው፡፡

ሁለተኛውና ሰፊ/ ውጫዊ (macro) የሚባለው ወሰን ከቀዳሚው በብዙ መልኩ የተለየ ነው፡፡ ይኸኛው የወሽባክ ወሰን የሚመለከተው ፈተናዎች በተማሪዎችና መምህራን ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ አይደለም፡፡ ከክፍል ውጪ ባሉ ባለድርሻ አካላት ላይ ማለትም በትምህርት ቤቶች አስተዳደር ክፍሎች፣ በወላጆች፣ በፖሊሲ አውጪዎች፣ ውሳኔ ሰጪ አካላትና የመሳሰሉት ወገኖች ላይ ፈተናዎች የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ የሚመለከት ነው (Bachman እና Palmer 1996)፡፡

ስለዚህ የፈተና ወሽባክ ከወሰን አንፃር የሚታየው በእነዚህ ሁለት አቅጣጫዎች ላይ ከሚያሳድረው ተፅዕኖ አንፃር ነው ማለት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ከኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ባለድርሻ አካላት አንፃር ሁለቱንም ወሰኖች ለመመርመር ተሞክሯል፡፡

2.8.2 የወሽባክ ጥቅል/ንጥልነት (specificity)

ፈተና በማስተማርና መማር ሂደት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ አጠቃላይ ወይም ንጥል (*general / specific*) ሊሆን ይችላል፡፡ አጠቃላይ ወሽባክ የሚባለው በማንኛውም ዓይነት ፈተና ሊከሰት የሚችል የፈተና ተፅዕኖ ዓይነት ነው፡፡ ለምሳሌ ፈተና ተማሪዎችን በርትተው እንዲያጠኑ ያነሳሳል የሚለው መላምት ለማንኛውም አይነት ቴስት/ፈተና ሊሰራ የሚችል ነው፡፡ ንጥል ወሽባክ የሚባለው የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ይኸኛው የወሽባክ ዓይነት ከአንድ ነጠላ የፈተና ዓይነት ጋር የሚያያዝ የፈተና ተፅዕኖ ዓይነት ነው፡፡ ለምሳሌ በቋንቋ ፈተና የማዳመጥ ክፍል በፈተና ቢካተት መምህራንና ተማሪዎች ይህን በፈተናው መካተት የጀመረውን የቋንቋ ክሂል ትኩረት

ሰጥተው እንዲያስተምሩና እንዲማሩ ያነሳሳል የሚለው እምነት ንጥል ወሽባክ ነው (Watanabe 2004)።

2.8.3 የወሽባክ ጥንካሬ (Intensity)

አንድ ፈተና በማስተማርና መማር ሂደት ላይ የሚያሳድረው የተፅዕኖ ደረጃ (Magnitude) ጠንካራ ወይም ደካማ (*Strong/ Weak.*) ሊሆን ይችላል (Green 2007፣ Watanabe 2004)። ጥንካሬ የሚለውም እነዚህን ሁለት ጉዳዮች የሚመለከት ነው። የፈተናው ተፅዕኖ ደረጃ ጠንካራ ነው ወይስ ደካማ የሚለውን ማለት ነው። አንድ ፈተና በማስተማርና በመማር ሂደቶች ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ የሚያሳድር ከሆነ በክፍል ውስጥ የሚከናወነውን ማንኛውንም ነገር የሚወሰንና ሁሉም ማለትም መምህራኑ የሚያስተምሩት፣ ተማሪዎቹ የሚማሩት ትምህርት ለፈተናው የሚያዘጋጅ እንዲሆን ያደርጋል። በሌላ በኩል ደግሞ የፈተናው የተፅዕኖ ደረጃ ደካማ ከሆነ በማስተማር-መማር ሂደቶች የተወሰነ አቅጣጫ ላይ ወይም በተወሰኑ መምህራንና ተማሪዎች ላይ ብቻ ተፅዕኖ የሚያሳድርና በሌሎቹ የትምህርቱ ክፍሎችና መምህራንና ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ የማያሳድር ይሆናል (Watanabe 2004)።

Watanabe (2004)ን ጥናት ውጤት ጠቅሰው እንደገለፁት ብዙ ጊዜ የፈተናዎች የተፅዕኖ ጥንካሬ ደረጃ ከፍና ዝቅ እንዲል ወይም ጠንካራ ወይም ደካማ እንዲሆን የሚያደርገው ፈተናው ከፍ ያለ ውሳኔ የሚወሰንበት ወይም የማይወሰንበት (High stakes or low stakes) ከመሆኑ ጋር ይያያዛል። በኢትዮጵያ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎች ከዚሁ ከፍተኛ ውሳኔ የሚወሰንባቸው (High stakes) ከሚባሉ የፈተና ዓይነቶች /ደረጃዎች የሚመደቡ ናቸው(ሀላፊ፩)። በሌላው ዓለምም አብዛኛውን ጊዜ ከፍተኛ ውሳኔ የሚወሰንባቸው ፈተናዎች ተደርገው የሚወሰዱት ውጫዊ (ብሔራዊ/ ዓለም ዐቀፋዊ) ፈተናዎች ናቸው። እነዚህ ፈተናዎች በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው (Watanabe 2004)። በዚህ አስተሳሰብ መሰረትም የአንድ ፈተና ወሽባክ/ በመማር ማስተማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ደረጃ ጠንካራ ወይም ደካማ ሊሆን ይችላል ማለት ነው።

2.8.4 የወሽባክ አቅጣጫ/ ዓይነት (Direction/ Value)

የፈተና ወሽባክ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ታላሚ ወሽባኮች ከአዎንታዊ ወሽባክ ጋር የሚያያዙ ሲሆኑ ያልታለሙት ደግሞ አዎንታዊም አሉታዊም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የፈተና ተጽዕኖዎች/ ወሽባክ ከዚህ ከአዎንታዊነትና አሉታዊነት ጋር ተያይዘው በሚጠኑበት ጊዜም የወሽባክ ጥናቱን የፈተና ተገቢነት ዳኝነት (Validity Judgment) ወይም ግምገማ ጉዳይ አድርጎ ማየትን ይጠይቃል፡፡ ይህም የወሽባክ ጥናቱን በግምገማ ጥናት ክፍልነት እንዲታይ ያደርገዋል (Watanabe 2004)፡፡

እነዚህ ሁለቱ የወሽባክ ዓይነቶች በጥናቱ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች እንደመሆናቸው መጠን ቀጥሎ በተናጠል እየተነሱ ከተለያየ አቅጣጫ ተብራርተው እንዲቀርቡ ተደርገዋል፡፡

2.8.4.1 *አሉታዊ ወሽባክ*

የአጠቃላይ ትምህርት መስክም ሆኑ የቋንቋ ፈተናዎች ብዙውን ጊዜ በማስተማር ላይ በሚያሳድሩት አሉታዊ ተፅዕኖ ይተቻሉ (Cheng እና Curtis 2004):: አንዱና ዋነኛው የፈተናዎች አሉታዊ ወሽባክ መገለጫም መምህራን በፈተናዎቹ የማይካተቱ ይዘቶችንና ክንውኖችን ችላ የማለት ዝንባሌ እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ መሆናቸው ነው፡፡ ፈተናዎች መምህራን ሥርዓተ ትምህርቱን አዛብተው እንዲያቀርቡት (Distort the curriculum) የሚያደርጉ ከሆነ ደግሞ የፈተናዎቹ ተፅዕኖ አሉታዊ ነው ማለት ነው (Cheng እና Curtis 2004)፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት አንዳንድ ፈተናዎች መምህራን በክፍል ትምህርቱ ተማሪዎቻቸው የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ከመጣር ይልቅ የትምህርት ጊዜውን ተማሪዎችን ለፈተና ለማዘጋጀት ተግባር ሲያውሉት ተስተውሏል (Cheng እና Curtis 2004)፡፡ በተጨባጭም ተማሪዎች ጊዜያቸውን ያለፉ ፈተናዎችን ለመሥሪያነት፣ የፈተና አሠራር ቴክኒኮችን ለመለማመጃነት ማዋልን እንዲመርጡ ሲያደርጉ ተስተውሏል፡፡ የትምህርት ልምዶችን አጥብበውና የማይሰቡ አድርገው እንዲያቀርቡ የሚጫኑባቸው አጋጣሚዎችም ተከስተዋል (Cheng and Curtis 2004)፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARY
P. BOX 1176

በአጠቃላይ በAlderson እና Wall (1993) አገላለፅ አሉታዊ ወሽባክ በፈተና ምክንያት በማስተማርና መማር ላይ የሚከሰት የማይፈለግ ተፅዕኖ ነው። ይህም ተፅዕኖ ፈተናዎች የመማር መርሆዎችን ወይም የትምህርት ዓላማዎችን የማያንጸባርቁ ሲሆኑ ሊከሰት የሚችል ነው። በዚህ ሁኔታ መምህራንና ተማሪዎች የማስተማርና የመማር ሂደቱን መዳረሻ ፈተናው ላይ ሊያደርጉ ይችላሉ። ዓላማዎችና ትምህርቱ የሚሰጥባቸው ተጠየቆች ሊዘነጉ ሁሉ ይችላሉ (Cheng and Curtis 2004)። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በCheng እና Curtis (2004) የተጠቀሱት Smith (1991) ጥናት እንዳሳየው በፈተናዎች አሉታዊ ወሽባክ ምክንያት ለማስተማሪያነት የተመደበውን ጊዜ ለታለመው ዓላማ ማዋሉ ሊቀንስ፣ ሥርዓተ ትምህርቱ እንዲጠብ ሊያደረግ ይችላል። መምህራኑ ባላቸው አቅም መሠረት ከመደበኛ ፈተናው ጋር የማይጣጣሙትን የትምህርት ይዘቶች ችላ እንዲሏቸው፣ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ማቴሪያሎችን ተጠቅመው ከማስተማር እንዲታቀቡ ሊያደርጓቸው ይችላሉ።

ለማጠቃለል (Alderso እና Hamp-lyons 1996) የፈተናዎችን አሉታዊ ወሽባክ በተመለከተ በተለይም በሥርዓተ ትምህርት ላይ የሚከናወኑ ናቸው ያሏቸውን ዋና ዋና ባሕርያት የተለያዩ ምንጮችን በመጥቀስ ጨምቀው እንደሚከተለው አቅርበዋቸዋል።

1. ሥርዓተ ትምህርትን ያጠባሉ (Narrowing of the curriculum (Madaus 1988, Coley 1981)፣
2. የትምህርት ጊዜን ያባክናሉ /ይሻማሉ lost instructional time (Smith *et al.,* 1989)፣
3. ጥልቅ አስተሳሰብን ወይም ችግር መፍታትን የሚፈልጉና ቀዳሚ ትኩረት የሚሹ ክሂሎች ላይ የሚደረግን ትኩረት ይቀንሳሉ/ እንዲቀነስ ያደርጋሉ፤
4. የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ሳይዳብር የፈተና ውጤታቸው ከፍ ሊል ይችላል (Haladyna, Ndan እና haas 1991)።

2.8.4.2 አዎንታዊ ወሽባክ

አዎንታዊ ወሽባክ የአሉታዊ ወሽባክ ተቃራኒ ገፅታ ያለው የፈተና ተፅዕኖ ነው። በዚሁ መሰረት በክፍል ትምህርት የቋንቋ ትምህርት ለመዳውን የሚያዳብሩ ተግባሮችን በፈተናዎች ተፅዕኖ ምክንያት ማካተትና የመማር-ማስተማር ሂደቶችን የተሻለ እንዲሆን የሚያስችል ሚና ፈተናዎች ሲጫወቱ ወሽባኩ አዎንታዊ ነው ይባላል። በዚህ ረገድ Cheng እና Curtis (2004)፣ Pearson (1988)ን በመጥቀስ እንደገለፁት የፈተናዎች ተፅዕኖ ጠቃሚ (beneficial) ሆኖ ሲገኝና ተፈላጊ ለውጦች እንዲመጡ የሚያበረታታ ሲሆን የወሽባክ ዓይነቱ አዎንታዊ ነው ይባላል።

2.9 አዎንታዊ የፈተናዎች ወሽባክን እንዴት ማዳበር ይቻላል (How can we promote beneficial Washback)?

ፈተናዎች በመማር-ማስተማር ላይ ጠቃሚ ወሽባክ እንዲያስገኙ የሚያስችሉ ስልቶች በተለያዩ ምሁራን ቀርበዋል። ከእነዚህ መካከል በስፋት ተቀባይነት እያገኙ የመጡት Bailey (1996) እና Hughes (2003) ያቀርቧቸው ሐሳቦች ናቸው።

እንደ Bailey (1996) አመለካከት የፈተናዎችን ጠቃሚ (Benefilcial) የወሽበክ ገፅታ ለማዳበር ከሚያገለግሉ መንገዶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ. የቋንቋ መማር ዓላማዎች (Language Learning Goals)

ወሽባክ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን የሚችለው ፈተናዎቹ የትምህርት ዓላማዎች በተማሪዎችና መምህራን እንዲሳኩ ወይም እንዲደናቀፉ ሲያደርጉ ነው። Baily (1996) Buck (1988) ጠቅሰው እንደሚያስረዱት አብዛኞቹ የትምህርት ባለሙያዎች እንደሚያምኑት የክፍል ውስጥ ትምህርት ይዘት የሚወሰነው በግልፅ ከሰፈሩ የትምህርት ዓላማዎች ነው። የፈተናዎችም ሚና እነዚህ ዓላማዎች መሳካት አለመሳካታቸውን ማረጋገጥ ነው። ፈተናዎች ይህን ተግባር በሚያከናውኑ ጊዜ ተማሪዎችና መምህራን በእነዚህ ዓላማዎች (goals) ላይ እንዲያተኩሩ ተጽዕኖ ይፈጥሩባቸዋል። በዚህም በክፍል ትምህርቱ ላይ ፈተናዎች የሚያሳድሩት ተጽዕኖ በጣም ጠቃሚ እየሆነ ይመጣል።

ለ. እውንነትን መመስረት (Building in Authenticity)

የተለያዩ ቀደምት ተመራማሪዎችን ጥናቶች መሰረት በማድረግ Bailey (1996) እንደሚያስገነዝቡት የቋንቋ ፈተናዎች ለትምህርት የቀረበውን ቋንቋ የገሀዱ ዓለም (real life) አጠቃቀም ሊያንፀባርቁ ይገባቸዋል። በሌላ አባባል የቋንቋ ፈተናዎች የነባራዊ ሁኔታዎች የቋንቋ አጠቃቀም ይዘትና ዓላማዎች ነፀብራቅ ሊሆኑ ይገባቸዋል። በተለይ Doye (1991:104) ጠቅሰው እንደሚያስረዱት በቋንቋ ፈተናዎች ተግባሮችና (tasks) በትይዩው ባለው የገሀዱ ዓለም የቋንቋ አጠቃቀም መካከል ፍፁም የሆነ ተመሳስሎ ሊኖር ይገባል። ይህም እውንነት ፈተናዎች በማስተማርና መማሩ ላይ ጠቃሚ ወሸባክ እንዲያዳብሩ ያደርጋል። በቋንቋ እውንነት የሚለው የሚመለከተውም ሁለት ጉዳዩችን ነው። እውናዊ ቴክስትንና እውናዊ የፈተና ተግባራትን።

Messick (1996)ም ይህንኑ ሀሳብ ከሚጋሩት አንዱ ናቸው። እንደሳቸው አገላለፅ ፈተናዎች ጠቃሚ ወሸባክ እንዲኖራቸው ናሙናዎቹ መስፈርታዊ (Criterion) ናሙናዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል። እውናዊና ቀጥተኛ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ተግባቦታዊ ባሕርያት ናሙናዎች መሆን ይኖርባቸዋል። ከመማሪያ መልመጃዎች ወደ ፈተና መልመጃዎች መሸጋገር ይገባል ማለት ነው።

እውናዊነትን በፈተና በማንፀባረቅ ረገድ ሁለት ስጋቶች እንዳሉም Messick (1996) ይጠቁማሉ። አንደኛው መመዘን ያለባቸውን ችሎታዎች በሚገባ በፈተናዎች ያለማካተት_መሰረታዊና መመዘን ያለባቸውን ችሎታዎች (Construct) ያለመመዘን (Construct under-representation) ያሉት ሲሆን፣ ሁለተኛው መመዘን ከሚኖርባቸው ችሎታዎች ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸውን በፈተናው ማካተት (Construct irrelevant variance) በማለት የገለፁት ነው። እነዚህ ችግሮች በፈተናዎቹ የሚንፀባርቁ ከሆነ ፈተናዎቹ ጠቃሚ ወሸባክ እንዳይኖራቸው ያደርጋሉ ማለት ነው።

ሐ. ለተማሪዎች ነፃነትና ራስን በራስ የመገምገም ኃላፊነት መስጠት (learner autonomy and self-assessment)

ለተማሪዎች ነፃነት (Autonomy) መስጠት ሌላው አዎንታዊ ወሽባክን ከፍ ማድረጊያ መንገድ ነው። Bailey (1996) እንደሚገልጹት ነጻነት ተማሪዎች ምን፣ እንዴትና በምን ፍጥነት እንደሚማሩ የመግለፅ መብት አላቸው ከሚለው ፍልሰፍና የሚመነጭ ነው። በዚህ ፍልስፍና መሰረትም ተማሪዎች ይህን ነፃነት በማግኘታቸው የሚቀናጇቸው የተለያዩ ጠቀሜታዎች ይኖራሉ። ራስን በራስ የመገምገም ችሎታቸውን እያዳበሩ መምጣትም አዎንታዊ ወሽባክን ለማዳበር ጠቀሜታ አለው። በአጠቃላይ እንደ Bailey (1996) እምነት ነፃ ሆኖ መስራትና ራስን በራስ የመገምገም ችሎታን ማዳበር ርስበርስ የተሳሰሩና ጠቃሚ ወሽባክን የሚያዳብሩ ብሎም ተማሪዎችን ለስኬት የሚያበቁ ውስጣዊ መስፈርቶችን እንዲያዳብሩ የሚረዱ ስልቶች ናቸው።

መ. ውጤትን መግለጽ/ማሳወቅ (Score reporting)

ፈተናዎች ጠቃሚ ወሽባክ እንዲያዳብሩ ሌላው አስፈላጊ ነገር ለተማሪዎች ለራሳቸውና ለመምህራን ዝርዝር የውጤት ሪፖርት እንዲደርሳቸው ማድረግ ነው። ይህን ሀሳብ Brown (2004) ይጋሩታል። Brown (2004) እንደሚያስረዱት ጠቃሚ ወሽባክ ለማዳበር ለተማሪዎች የፈተና አሰራራቸው ላይ ተገቢ አስተያየት መስጠት ያስፈልጋል። በአብዛኛው የተለመደው አሰራር ግን በፊደል ወይም በቁጥር ገልፆ ውጤትን (Scores) ማሳወቅ ነው። እነዚህ ፊደሎች ወይም ቁጥሮች ለተማሪዎች የሚሰጡት መረጃ አለ ለማለት ግን አያስችልም።

ሁለተኛው ጠቃሚ (አዎንታዊ) ወሽባክን ማዳበሪያ ስልቶችን ያቀረቡት Hughes (2003) ናቸው። እኒህ ምሁር አዎንታዊ ወሽባክን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ናቸው በማለት የሚከተሉትን ሰባት ዘዴዎች አቅርበዋል፤

1. እንዲዳብሩ የሚፈለጉ ችሎታዎችን መፈተን (Test the abilities whose development you want to encourage).

Hughes (2003) እንደሚገልፁት በፈተና ሊካተቱ የሚገባቸውን አስፈላጊ ችሎታዎች ከመፈተን ይልቅ ለመፈተን የሚቀሉትን መርጠ የመፈተን ዝንባሌ ይታያል፡፡ ይህም ፈተናዎች ጎጂ ወሸባክ እንዲኖራቸው የሚያደርግ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

2. ናሙናውን ሰፊና ተተንባይ ያልሆን ማድረግ (Sample widely and unpridictably)

ፈተናዎችን የተለያዩ ይዘቶች እንዲያካትቱ አድርጎ በተለያዩ የአጠያየቅ ስልቶች ወካይ በሆነ መንገድ ለመተንበይ በማያመች ስልት ማዘጋጀት በመማር-ማስተማር ሂደቱ ሁሉንም ይዘቶች ለመሸፈንና በሁሉም አቅጣጫ ተማሪዎቹን ዝግጁ ለማድረግ ይረዳል፡፡

3. ቀጥተኛ አፈታተንን መጠቀም (use direct testing)

በHughes (2003) ብያኔ መሰረት ቀጥተኛ ፈተና ማለት በተቻለ መጠን እውናዊ (Authentic) በሆኑ ቴክስቶችና ተግባሮች በቋንቋው ክሂሎች መጠቀም መቻላቸውን መመዘን መቻል ነው፡፡ ኢርቱዕ (indirect) በሆነ መንገድ መፈተን ስንጀምር ወዲያውኑ ተማሪዎቹ በቋንቋው ክሂሎች ልምምድ ማድረግን እንዲያቋርጡ እያደረግን ነው፡፡ ለምሳሌ የማመንጨት ችሎታቸውን (መናገርና መፃፍ) የማንፈትን ከሆነ በመማር ማስተማር ሂደቱ እነዚህ ክሂሎች ችላ እንዲባሉ እያደረግን ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ይኸኛው በHughes (2003) የቀረበው ዘዴ በBailey (1996) እውንነትን መመስርት ተብሎ የተገለጸውን ሐሳብ የሚያጠናክር/ የሚጋራም ነው ማለት ነው፡፡

4. ፈተናን መስፈርት-ተኮር ማድረግ (Making testing criterion-referenced)

መስፈርት-ተኮር ፈተናዎች በአነሳሽነት ባህሪያቸው የተነሳ እንደ ጠቃሚ ወሸባክ ገፅታ ይታያሉ፡፡ Hughes (2003) እንደሚያምኑት ተፈታኞች በፈተና ለማለፍ በትክክል ምን እንደሚጠበቅባቸው በግልፅ ሊያውቁ ይገባቸዋል፡፡ ይህም ፈተናዎች አዎንታዊ ወሸባክን እንዲያበረታቱ ተማሪዎችን ርስበርስ ከማወዳደር (Norm Referenced) ይልቅ መስፈረት ላይ ሊመሰረቱ እንደሚገባቸው ያሳያል፡፡

5. የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን በትምህርቱ ዓላማዎች ላይ እንዲመሰረቱ ማድረግ

Hughes (2003) በተለይ የችሎታ መለኪያ (Achievment) ፈተናዎች በዝርዝር ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ ይዘት ላይ መመስረት የለባቸውም ብለው ይከራከራሉ፡፡ ማስተማርና መማርን በተገቢ ሁኔታ ለመገምገም ፈተናዎች ከትምህርት ዓላማዎች ላይ መመስረት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህም ጠቃሚ ወሸባክን ማዳበር ይቻላል፡፡

6. ፈተናው ተማሪዎችና መምህራን የሚያውቁትና የተረዱት መሆኑን ማረጋገጥ

ጠቃሚ ወሸባክ ለማዳበር ፈተናው ያስፈለገበትን ተጠየቅ (rationale) ተፈታኞች ለፈተና የሚዘጋጁበት ዝርዝር ልየታዎች (Specifications) እና ናሙና ጥያቄዎችን የሚመለከታቸው አካላት (ተማሪዎች፣ መምህራን) የሚያውቁበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

7. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለመምህራን ድጋፍ ማድረግ/መስጠት

በተለይ በፈተናዎች ውጤታማ ለመሆን አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለመምህራን ይህን አቅጣጫ ማሳየትና ትምህርቱን ተገቢ በሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎች እንዲያቀርቡት አስፈላጊ ድጋፍ መስጠት ይገባል፡፡ ይህም ፈተናዎች አዎንታዊ ወሸባክ እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

እነዚህ አዎንታዊ ወሸባክን የሚያበረታቱ መንገዶች በኢትዮጵያ በተለይም የአማርኛ ቋንቋን በተመለከተ ተግባራዊ እየተደረጉ ነው? የሚለውን በጥናቱ ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡

2.10 በወሸባክ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች

በተለያዩ መጽሔቶች/ ጆርናሎች ላይ ከታተሙ መጣጥፎች/ አርቲክሎችና በኢንተርኔት ድህረ ገጾች ከተለቀቁ ጽሑፎች መረዳት እንደሚቻለው በተለያዩ ሀገሮች የተለያዩ የቋንቋ ፈተናዎች ወሸባክ ላይ የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ ለዲግሪ ማሟያነት የተሰሩ ናቸው፡፡ ከነዚህ ለዲግሪ ማሟያነትም

ሆነ ለጆርናል አርቲክልነት የተካሄዱ ጥናቶች መካከልም አብዛኞቹ በልዩ ልዩ ዓለማቀፋዊና ሀገራዊ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፈተናዎች ወሽባክ ላይ የተሰሩ ናቸው፡፡ በሌሎች ቋንቋዎች ፈተናዎች ወሽባክ ላይ የተካሄዱ ብዙ ጥናቶችን ማግኘት ያልተቻለው ምናልባትም ጥናቶቹ በራሳቸው በቋንቋዎቹ ስለተካሄዱ ሊሆን ይችላል፡፡

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ፈተናዎች ወሽባክ ላይ ከተካሄዱ ጥናቶች በቀዳሚነት የሚጠቀሰው Aldeson እና Wall በ(1993) በስሪ ላንካ ያካሄዱት ሰፋ ያለ ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት በስሪ ላንካ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጫዊ ፈተና በቋንቋው ትምህርት ላይ ምን ምንና በምን በምን ዘርፎች ተጽዕኖ እንደሚያደርስና እንደማያደርስ ያሳየና ቲዎሪን በተግባራዊ ((emprical) ጥናት ለማሳየት የሞከረ ጽሑፍ ነው፡፡ ጥናቱም መጠይቅንና የክፍል ምልከታን በመጠቀም በተሰበሰበ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተካሄደ ነው፡፡ ከዚህ ጥናት በኋላ በሆንግ ኮንግ፣ ኮርያ፣ ጃፓን፣ ኒውዝላንድ፣ እስራኤል፣ ታይዋን፣ ቻይናና ኢራን በሚሰጡ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፈተናዎች ወሽባክ ላይ የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ባጠቃላይ ከ1990ዎቹ በኋላ የቋንቋ ፈተና የተግባራዊ ሥነ-ልሳን አንዱ የጥናት ዘርፍ አየሆነ ሲመጣ ወሽባክ አንዱ ዋነኛ የጥናት መስክ እየሆነ መጥቷል፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆኑ የተለያዩ ጥናቶችን በማስረጃነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ Cheng (199፪፣ 2000፣ 2004፣ 2005) በሆንግ ኮንግ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፈተና በቋንቋው ትምህርት ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ ያጠኑ ሲሆን Hayes (2003) በኒው ዝላንድ፣ Chen (2002) በታይዋን፣ Caine (2005) በጃፓን፣ Shohamy (1992) እና Shohamy እና ሌሎች (1996)፣ በእስራኤል የሚሰጡ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፈተናዎችን ወሽባክ በማጥናት ተጽዕኖዎችን፣ የተጽዕኖዎችን ደረጃና ዓይነት ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

ከነዚህ ጥናቶች ለየት የሚለውና ለሁለተኛና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚዘጋጁ ውጫዊ/ ብሔራዊ ፈተናዎች ወጣ በማለት በዩኒቨርስቲ ደረጃ የሚሰጥን የአንድ ቋንቋ ኮርስ (ውጫዊ ያልሆነ _low stake የሚባል) ፈተና ተጽዕኖ በማጥናት አዲስ የወሽባክ ጥናት አቅጣጫ ያስተዋወቁት Fournier-kowabski ናቸው፡፡ እኒህ ሰው በዚህ በ (2005) ባካሄዱት የሦስተኛ ዲግሪ ማሚያነት በአሜሪካ ኦሀዎ ዩንቨርስቲ የሚሰጠውን የእስፓኒሽ ቋንቋ አንድ ኮርስ (Spanish 104) ወሽባክ ነው ያጠኑት፡፡

በጥናታቸው ዋነኛ የመረጃ መስብሰቢያነት የተጠቀሙት የክፍል ምልከታን ሲሆን የአምስት የኮርሱ መምህራንን አንዳንድ ክፍል በተርም 8 በሁለት ተርም 16 ክፍለ ጊዜያትን ተመልክተው በጊዜ ልዩነትና በመምህራኑ መለያየት ምክንያት የፈተናውን ተጽዕኖ ዓይነትና ደረጃ እንደሚለያይና ምክንያቶቹ ምን ምን እንደሆኑ አሳይተዋል፡፡ ውጫዊና ውስጣዊ (low stake) የሚባሉ ፈተናዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ በአብዛኛው ተመሳሳይ እንደሆነ ያሳየ ጥናትም ነው፡፡

የወሽባክ ሞዴሎች በሚለው ክፍል እንደቀረበው ከላያ ከተጠቀሱት ጥናቶች ትኩረቱን ለየት ባለ ጉዳይ ላይ አድርጎ የተካሄደው የGreen (2007) የወሽባክ ጥናት ነው፡፡ Green (2007) በዚህ ጥናታቸው በወሽባክ ጥናት ችላ እየተባለ መጥቶ የነበረውን ማለትም በፈተናና ሊመዘኑ በሚገባቸው ችሎታዎች (Constructs/TLD_Tareget Language Domains) መካከል ሊኖር የሚገባውን ተጣጥሞሽና በሁለቱ መካከል አግባብ ያለው ዝምድ የማይኖር ከሆነ ለአለታዊ ወሽባክ በር እንደሚከፍት አሳይተዋል፡፡ በዚህም ለአዎንታዊ ወሽባክ መዳበር በፈተናና ሊመዘን በሚገባው የቋንቋ ችሎታ መካከል ተገቢ መጣጣም ሊኖር ይገባዋል የሚለው አስተሳሰብ እንደገና እንዲያንሰራራ አድርገዋል ማለት ይቻላል፡፡

ቀደም ብለው ከተጠቀሱት በእንግሊዝኛና በእስፓንኛ ቋንቋዎች ላይ ከተካሄዱት የወሽባክ ጥናቶች በተጨማሪ በእስራኤል በሁለተኛ ቋንቋነት በሚሰጠው ዐረብኛና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትነት በሚሰጠው ሂብሩ ቋንቋ ብሄራዊ ፈተናዎች ወሽባክ ላይ Shohamy በ(1992) ፣ Shohamy እና ሌሎች በ(1996) ጥናቶች አካሂደዋል፡፡

በኢትዮጵያ በአጠቃላይ ትምህርት መስክ ብሔራዊ ፈተናዎችን በሚመለከት አንደኛ የሱፍ(1976) ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያነት 12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ላይ በሚሰጠው ብሔራዊ የታሪክ ፈተና የይዘት አግባብነት (Content Validity) ላይ ጥናት ያካሄዱ ሲሆን በዚህ ጥናታቸው ፈተናው የይዘት አግባብነት ችግር እንደሚታይበት አሳይተዋል፡፡ ሁለተኛ፣ ጥላሁን(1994) ደግሞ <u>ብሔራዊ ፈተናዎች በኢትዮጵያና በደቡብ አውስትራልያ</u> በሚል ርዕስ ንጽጽራዊ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸውም ኢትዮጵያ በትምህርት ሥርዓቷ ከ40 ዓመታት በላይ በሦስት የተለያዩ ደረጃዎች ብሔራዊ ፈተናዎች ስትሰጥ የቆየች ሀገር ብትሆንም እነዚህ ፈተናዎች መመዘን

ያለባቸውን ችሎታ መመዘን የሚችሉ እንዲሆኑ ለማድረግ የተደረገ/ የሚደረግ ነገር አለመኖሩን አመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ደቡብ አውስተራልያ እንደኢትዮጵያ ሁሉ ሦስት ዓይነት ብሔራዊ ፈተናዎች (Public Examinations) የማስተዳደር ልምድ ያላትና እንደኢትዮጵያ ሁሎ ፈተናዎቿ ለተለያዩ ችግሮች የተጋለጡባት ሀገር እንደነበረች በጥናታቸው አሳይተዋል፡፡ አያይዘውም እውናዊ ምዘና (Athunthic Assessment) በብዙ ሀገሮች (ከ1920ዎቹ ጀምሮ የምርጫ ፈተና አቀንቃኝ በነበረችው አሜሪካ ሳይቀር) ተቀባይነት እያገኘ ሲመጣ ደቡብ አውስትራልያም የምዘና ሥርዓቷን ወደ እውናው (Athunthic) ወይም የተግባር (Performance) /ርቱዕ (Direct) የምዘና ስልት መቀየር በመቻሏ ከኢትዮጵያ የምዘና ሥርዓት የተሻለና ጥሩ መማርን የሚያበረታታ የምዘና ሥርዓት ባለቤት መሆን እንደቻለች የጥናታቸው ውጤት ያሳያል፡፡ በመደምደሚያቸውም ኢትዮጵያም እንደደቡብ አውስትራልያ ከነባሩ የምርጫ ፈተና ሥርዓት መውጣትና ወደዘመናዊ የምዘና ሥርዓት መሻገር እንደሚጋባት ያስገነዝባሉ (ጥላሁን1994)፡፡

ከእነዚህ በአጠቃላይ ትምህርት መስክ ከተካሄዱት ሁለት ጥናቶች የመጀመሪያው አጥኝ ስለፈተና ወሽባክ/ ተጽዕኖ ያነሱት ነገር የለም፡፡ ሁለተኛው ግን የጥናታቸው አራተኛ ጉዳይ ራሱ የእውናው ፈተና ተጽዕኖ በትምህርት ላይ (The Effects of Authentic Assessment on Instruction) የሚል ነው፡፡ ስለዚህ የፈተናን ተጽዕኖ አንድ ክፍል አድርገው አንስተውታል ማለት ይቻላል፡፡ በእርግጥ የእሳቸው ጥናት በተለይ በቋንቋ ፈተና ላይ የተካሄደ አይደለም፡፡ በሁሉም፣ በሁለቱ ሀገራት በሚሰጡ የቋንቋና ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ፈተናዎች ላይ ተመስርቶ የተካሄደ ጥናት ነው፡፡ ስለዚህ የጥላሁን(1994) ጥናት ከዚህኛው በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ ከሚያተኩረው ጥናት አንደኛ የፈተናዎች ተጽእኖ አንድ ክፍል እንጂ ብቸኛና ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ ባለመጠናቱ፣ ሁለተኛ በተለይ በቋንቋ ፈተናዎች ላይ ያተኮረ ባለመሆኑ፣ ሦስተኛ ጥናቱ ከተካሄደ ብዙ ጊዜ(ከ10 ዓመት በላይ) የሆነው ስለሆነ ይለያል፡፡

ሌላው ከሌሎች የትምህርት መስኮች ይልቅ በኢትዮጵያ በተሻለ ደረጃ በፈተናዎች ወሽባክ ላይ ጥናቶች ለማካሄድ የተሞከረው በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ነው፡፡ በዚህ ክፍል ወሽባክ የጥናት ርዕስ አካል ሆኖ መነሳት

የጀመረው ቀደም ብሎ ደጀኔ (1990) ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ ባካሄዱት ጥናት ነው። በእርግጥ ገና እንዳሁኑ ስለወሽባክና የወሽባክ ጥናት አካሄድ ብዙ ባልተጻፈበትና ባልታወቀበት ጊዜ የተካሄደ ጥናት በመሆኑ በ12ኛ ክፍል የእንግሊዘኛ መልቀቂያ ፈተናና በትምህርቱ መካከል ያለውን ዝምድና ከመመርመርና በምርመራው የተለዩትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ተጨባጭ መፍትሄ ከማሳየት ባለፈ ከፈተና ወሽባክ አንጻር ፈተናው በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ እያሳደረ ያለውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ወይም ተጽዕኖ አልባነት እሰከማሳየት ገፍቶ የሄደ ጥናት ነው ለማለት ያስቸግራል። በሌላ አገላለጽ የተሳታፊዎችን ግንዛቤና ተግባር አካቶ እስከማጥናት የደረሰ ነው ሊባል የሚችል አይመስልም። ከዚህ ጥናት በኋላ ደግሞ አንደኛ፣ ደረጀ (2002) በቀድሞው የ12ኛ ክፍል መለቀቂያ የእንግሊዘኛ ፈተና ወሽባክ ላይ፣ ሁለተኛ፣ ካሳ (2007) በዩንቨርሲቲ መግቢያ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፈተና ወሽባክ ላይ፣ ሦስተኛ፣ መልካሙ(2007)በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ/ብሔራዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፈተና ወሽባክ ላይ ለሁለተኛ ዲግሪ መሟያነት ጥናቶች አካሂደዋል። ከእነዚህ በተጨማሪ ስማቸው(2012) ደግሞ ከርዕሳቸው ማስተዋል እንደሚቻለው ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያነት እንዲሁ የዩንቨርሲቲ መግቢያ የእንግሊዘኛ ፈተና በማስተማር-መማር ትግበራ(Practice) ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ አጥንተዋል። ከእነዚህ ጥናቶች መካከል ከስማቸው (2012) በፊት የተካሄዱት ጥናቶች በፈተናዎቹና በመርሐ ትምህርቶቹ፣ በፈተናዎቹና በመማሪያ መጽሀፎቹ መካከል ያለውን ተዛምዶ በመመርመር ላይ ያተኮሩ ናቸው። ከዚያ ባለፈ ፈተናዎቹ በክፍል ትምህርቱ ላይ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ ለማጥናት የሞከሩ አይደሉም። በእርግጥ በጽሑፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የመምህራኑንና የተማሪዎቹን አመለካከት ለማወቅም ጥረት አድርገዋል። የስማቸው(2012) ጥናት በፈተናዎቹና በትምህርቱ መካከል ያለውን ተዛምዶ ሳይሆን የክፍል ውስጥ ትግበራው ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ከቀዳሚዎቹ ይለያል። በዚህኛው ጥናት የክፍል ምልከታን ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በመጠቀም በ11ኛና በ12ኛ ክፍል ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዴት እየተሰጠ እንዳለና የዩንቨርሲቲ መግቢያ ፈተናው በማስተማር-መማር ሂደቱ ላይ ጠንካራ የሚባል አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ እንደሆነ ለማሳየት ተችሏል።

በአማርኛ ቋንቋ የማጠናቀቂያ ፈተና ወሽባክ ላይ የሚካሄደው ይኸኛው ጥናት በማጠናቀቂያ ፈተናውና በትምህርቱ ዓላማዎች መካከል ያለውን ተጣጥሞሽ (Overlapping) የሚፈትሽ ጭምር በመሆኑ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ፈተና ወሽባክ ላይ ለ፪ኛ ዲግሪ መሟያነት ከተሰሩት ጥናቶች ጋር ተመሳስሎ ቢኖረውም የዚህኛው ጥናት ዋነኛ ትኩረት የተሳታፊዎች ግንዛቤ (Perceptions)ና ተግባራት (Processes) በመሆናቸው ይለያል። ከስማቸው (2012) ጋር ደግሞ ሁለቱም ለማስተማር-መማር ትግበራው ትኩረት በመስጠታቸው፣ ይህንም ለማጥናት የክፍል ምልከታን ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ አድርገው በመጠቀማቸው የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖርም ይኸኛው (በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ የተካሄደው ጥናት) አንደኛ፣ የወሽባክ ጥናት የማዕዘን ድንጋይ ነው (Green 2007) ለሚባለው የተሳታፊዎች ግንዛቤም ትኩረት በመስጠቱ፣ ሁለተኛ፣ በፈተናውና በትምህርቱ መካከል ያለውን መጣጣም አለመጣጣምም የሚያጠና በመሆኑ፣ ሦስተኛ ይኸኛው በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና ላይ የተካሄደ ሲሆን ያኛው በዩኒቨርሲቲ መግቢያ የእንግሊዝኛ ፈተና ላይ የተካሄደ በመሆኑ በሁለቱ መካከል ሰፊ ልዩነትም አለ።

2.11. የወሽባክ መላምቶችና ምዴሎች (Models)

የተለያዩ ምሁራን ወሽባክ እንዴት እንደሚከሰትና የተከሰተበትን ደረጃ ለመለየት የሚያገለግሉ አማራጭ ሞዴሎችን ለማዳበር (to develop) የተለያዩ ሙከራዎችን አድርገዋል። ከነዚህ መካከል Green (2007) ተማሪዎች እንዲያዳብሩዋቸው በሚጠበቁ መሰረታዊ የቋንቋ ችሎታዎችና በፈተናዎች መካከል ያለን ዝምድና (Overlap) በመመርመር ላይ የሚያተኩር ሞዴል ከማዳበራቸው በፊት ሰፊ ተቀባይነት ያገኙትና ላለፉት ዓመታት የተለያዩ ተመራማሪዎች የተጠቀሙባቸው 15 መላምቶች ያካተተው የAlderson እና Wall (1993) ስራና ሁለት የወሽባክ ሞዴሎች ናቸው። ከሞዴሎቹ ደግሞ ቀዳሚው በBailey (1996; 1999) የቀረበው የHughes (1993) የወሽባክ ሞዴል/ ማዕቀፍ (Framework) ነው። ቀጥሎ መጀመሪያ መላምቶቹን ከዚያም ሞዴሎቹን የሚመለከተው ቅኝት በቅደም ተከተል ይቀርባል።

በቋንቋ ትምህርት ፈተና የወሸባክ ሳይንሳዊ ጥናት ታሪክ ቀዳሚው የAlderson እና Wall (1993) አስራ አምስት መላምቶችን ያካተተው ስራ ነው። አንዳንዶች እነዚህን መላምቶች የወሸባክ ቲዎሪ እያሉም ይጠሯቸዋል (Ghorbani 2008)። መላምቶቹ ወሸባክ በተግባር እንዴት እንደሚሰራ /እንደሚከሰት የሚያሳዩ በመሆናቸውና ለጥናት ምቹ መነሻ ሆነው በመገኘታቸው አብዛኞዎቹ በወሸባክ ላይ ጥናት ያካሄዱ ተመራማሪዎች ተጠቅመውባቸዋል። በBailey (1996) አከፋፈል መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡት አምስቱ (ተራ ቁጥር 2፣5፣6፣8 እና 10) መላምቶች ተማሪው (learner) ላይ፣ ስድስቱ ፕሮግራም (መምህሩ) ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። መላምቶቹ የሚከተሉት ናቸው፤


1. ፈተና በማስተማር ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
2. ፈተና በመማር ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
3. ፈተና በማስተማሪያ ይዘቶች ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
4. ፈተና በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
5. ፈተና ተማሪዎች ምን ይማራሉ (በመማር ይዘቶች) ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
6. ፈተና ተማሪዎች እንዴት ይማራሉ (በመማሪያ ዘዴዎች) ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
7. ፈተና በማስተማር ደረጃና ቅደም ተከተል ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
8. ፈተና በመማር ደረጃና ቅደም ተከተል ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
9. ፈተና በማስተማር ጥልቀትና መጠን ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
10. ፈተና በመማር ጥልቀትና መጠን ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
11. ፈተና በመማር ማስተማር ይዘት፣ ዘዴ ወዘተ በሚኖሩ አመለካከቶች ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል።
12. ጠቃሚ ውጤት የሚያስከትሉ ፈተናዎች ተፅዕኖ ሊኖራቸው ይችላል።
13. ጠቃሚ ውጤት የማያስከትሉ ፈተናዎች ወሸባክ((ተጽዕኖ) አይኖራቸውም።
14. ፈተናዎች በሁሉም ተማሪዎችና መምህራን ላይ ተፅዕኖ ሊኖራቸው ይችላል።
15. ፈተናዎች በተወሰኑት ተማሪዎችና መምህራን ላይ ተፅዕኖ ሊኖራቸው ይችላል።

እነዚህ መላምቶች እስካለንበት ዘመን ድረስ በወሽባክ ጥናት ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህም ጥናት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ወሽባክ ለመመርመር አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ እንዲያገለግሉ ተደርገዋል፡፡

በዚህ ክፍል መግቢያ እንደተጠቆመው በወሽባክ ሞዴል ቀዳሚነት የሚታወቀው የHughes (1993) የወሽበክ ማዕቀፍ (Framework) ነው(Bailey 1996; 1999)፡፡ ይህ ሞዴል ተሳታፊዎች (Participants)፣ ሂደቶችና (Processes) ውጤቶች (Products) የሚሉ ሦስት አላባዎች (elements) ያሉት ሲሆን ሦስቱም በፈተናዎች ተዕዕኖ ሊደረስባቸው የሚችሉ ክፍሎች ናቸው፡፡

በምስል1 እንደተመለከተው ተሳታፊዎች የሚለው ክፍል ተማሪዎችን፣ መምህራንን፣ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችን፣ የትምህርት መሳሪያ/ ማቴሪያል አዘጋጆችን ወዘተ ሊያካትት ይችላል፡፡ ሁለተኛው ሂደቶች የሚል ነው፡፡ ሂደቶች ማናቸውም ለመማር ማስተማር ሂደቱ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ በተሳታፊዎች የሚከናወኑ ድርጊቶችን የሚያመለክት የወሽባክ ክፍል ነው፡፡ እነዚህም ሂደቶች ማቴሪያሎችን ማዘጋጀትን፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መቀየርን፣ የመማር እና/ ወይም የፈተና አሰራር ስትራቴጂዎችን መጠቀምን ወዘተ የሚያካትቱ ናቸው፡፡ ሦስተኛው ውጤት ነው፡፡ ውጤት የሚለው የሚያመለክተው ተማሪዎች ምንድነው የተማሩት (እውቀት፣ ክሂሎት ወዘተ) ? እና የመማሩን ጥራት ደረጃ (ርቱዕነት (Fluency)፣ ትክክልነት...) እና የሌሎች ተሳታፊዎችን የስራ ውጤት ነው፡፡

ሦስተኛው Bailey (1996) የHughes (1993)ን የወሽባክ ማዕቀፍና የAlderson እና Wall (1993)ን መላምቶች አቀናጅተው የነደፉት ሞዴል ነው፡፡ ሞዴሉ የሚከተለው አይነት ቅርፅ አለው፤



ምስል 2.1. በ Bailey (1996) የቀረበ የወሸባክ ሞዴል

በዚህ በBailey (1996) ስራ በተገለጸው የHughes (1993) የወሸባክ ማዕቀፍ (Framework) እና Bailey (1996) ከነAlderson መላምቶች ጋር አቀናጅተው ባዳበሩት ሞዴል መሰረት አንድ ፈተና መጀመሪያ ተጽእኖ የሚያሳድረው በተሳታፊዎች ግንዛቤ (Percepions እና Attitudees) ላይ ነው። ለምሳሌ ፈተና በተለይም ውጫዊ /ብሔራዊ ፈተና በመማር ማስተማር ሂደት መምህራንና ተማሪዎች በሚሰሩት ስራ ላይ በሚኖራቸው ግንዛቤ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። በፈተና ተጽዕኖ ምክንያት ተሳታፊዎች የሚያዳብሩት ግንዛቤ ደግሞ ተሳታፊዎች በሚሰሩት ስራ ላይ የበኩሉን ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህም በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት በፈተናው የሚካተቱ ጥያቄዎች ዓይነት መልመጃዎችን በክፍል ውስጥ እየሰሩ/ እያሰሩ

ማለማመድን ያካትታል፡፡ በዚህ መንገድ የሚካሄድ የመማር ማስተማር ተግባርም በሚገኘው ውጤት ላይ የራሱን ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

ይህ ጥናት ከሦስቱ የBailey (1996) ሞዴል ክፍሎች በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች (በተሳታፊዎችና በሂደቶች) ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ለሦስተኛው ክፍል / ለውጤት ስኬትም ሆነ ውድቀት ወሳኞቹም እነዚህ ሁለቱ ቀዳሚ ክፍሎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ሞዴሉን መሰረት በማድረግም፣ ተሳታፊዎችን በተመለከተ ከኢትዮጵያ የትምህርት ዐውድ አንጻር በዚህ ጥናት እንዲካተቱ የተደረገው አንደኛ በጥናቱ የታቀፉት የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች፣ የአማርኛ መምህራንና ርዕሳነ/ምክትል ርዕሳነ መምህራን፣ ሁለተኛ፣ በጥናቱ የተካተቱት የአማራ ክልል ዞኖች ትምህርት መምሪያዎችና የዞን ከተማ አስተዳደሮች ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች የሥርዓተ ትምህርት፣ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተና ክፍል ኀላፊዎች ናቸው፡፡ ሦስተኛ፣ ከአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ እንዲሁ የሥርዓተ ትምህርት፣ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተና ክፍል ኀላፊዎችን ለማካተት ጥረት ተደርጓል፡፡ አራተኛ በፌድራል ደረጃ ደግሞ ከትምህርት ሚኒስቴር አንደኛ በፈተናዎች ኤጀንሲ ከፈተና ዝግጅትና አስተዳደር ጋር ግንኙነት ያላቸው ኀላፊዎችን፣ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎችንና የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጥያቄ ጸሐፊዎችን፣ ሁለተኛ ከትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምርት ዳሪክቶሬት ክፍል ደግሞ የሥርዓተ ትምህርት ክፍል ኀላፊውንና የአማርኛ ሥርዓተ ትምህርት ክፍል ተጠሪን ለማካተት ተሞክሯል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በወሽባክ ሞዴሉ በተሳታፊነት የተካተቱት የማቴሪያል ፀሐፊዎችና ተመራማሪ የሚሉት ክፍሎች በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ዐውድ መዋቀር ተፈጥሮላቸው በግልጽ የሚንቀሳቀሱ ክፍሎች መሆናቸውን የሚያሳይ መረጃ ባለመገኙቱ እንዚህን ክፍሎች የሚወክል ተሳታፊ በጥናቱ ለማካተት አልተሞከረም፡፡

በተለያዩ ጥናቶች (ለምሳሌ Cheng 1997፣ 2004፣ 2005፣ Chen 2002ሀ፣ 2002ለ) እንደተመለከተው ለፈተና ተጽዕኖ ይበልጥ ከተጋለጡት ወገኖች/ተሳታፊዎች መካከል ዋነኛዎቹ መምህራንና ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት በተሳታፊዎች ግንዛቤና

በሂደቶች ላይ የሚካሄዱ አብዛኞቹ የወሸባክ ጥናቶች በእነዚህ ሁለት ወገኖች በተለይም ደግሞ በመምህራን ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ለምሳሌ Chen (2002) የተለያዩ የቅርብ ጊዜ ተዛማጅ ጽሑፎችንና የጥናት ውጤቶችን በማጣቀስ እንዳቀረቡት መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናዎች በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ በተመለከተ የተለያየ ምላሽ (reactions) ይሰጣሉ። ከምላሾቻቸው ማረጋጋጠ የተቻለውም በብዙ ቦታዎች ለምሳሌ በኔፓል፣ እንዲሁም በአንዳንድ የእስያ ሀገሮች ለምሳሌ በሆንግ ኮንግ፣ ታይዋን፣ ጃፓን፣ ቻይና፣ የሚያስተምሩ አብዛኞቹ መምህራን ብሔራዊ ፈተናዎች በማስተማር ክፍሎች/ ምድቦች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ የሚል ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን ነው። ፈተናዎቹ ተጽእኖ የሚያሳድሩባቸው የትምህርት ምድብ ክፍሎች ናቸው እየተባሉ የሚገለጹትም መምህራኑ የሚያዘጋጇቸው መርሐ ትምህርቶች(Syllabus)፣ የትምህርት ይዘቶች፣ በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባሮች/ ጊዜ አመዳደብ፣ ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ማቴሪያሎች/ ድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎች፣ የማስተማሪያ ዘዴዎቻቸውና ተማሪዎቻቸውን የሚመዝኑባቸው መንገዶች ናቸው።


ከዚህ በመነሳትም በዚህ ጥናት የመምህራን ግንዛቤና የክፍል ውስጥ የማስተማር ባህርያት የተለየ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲመረመሩ ተደርገዋል። በምርመራውም ከተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝትና ከሁለቱ የሙከራ ጥናቶች ልምድ በመነሳት በኢትዮጵያ ዐውድ በማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ሊደርስባቸው ይችላል የተባሉ አምስት የማስተማር ምድብ ክፍሎች እንዲካተቱ ተደርጓል። እነሱም አንደኛ፣ የክፍል ውስጥ ተግባራት/ጊዜ አደላደል፣ ሁለተኛ የማስተማሪያ መሳሪያዎች/ ማቴሪያሎች፣ ሦስተኛ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ አራተኛ የትምህርት ይዘቶችና አምስተኛ የመምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና የሚሉት ናቸው። ቀደም ሲል በሌሎች ሀገሮች በተካሄዱ ጥናቶች እንደሚካተት የተገለጸው መርሐ ትምህርት የሚለው ክፍል በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ለመምህራን የሚሰጥ ተግባር ስላልሆነ በዚህ ጥናት አልተካተተም። የእነዚህ አምስት የትምህርት/ የማስተማር ምድብ ክፍሎች ምንነት፣ ባህርያትና ወሰን በሌሎች ሀገሮች ከተካሄዱ ጥናቶች ውጤቶች ጋር እየተገናዘበ ጭምር በፈተና ተጽዕኖ የሚደርስባቸው ክፍሎች በሚለው ርዕስ ስር ቀርቧል። ቀደም ብሎ እንደተወሳው

ከቋንቋ መምህራን በተጨማሪ ተማሪዎች ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ያላቸው ግንዛቤም ሌላው በጥናቱ የተፈተሸ ጉዳይ ነው።

በምስሉ ከተካተተው ከሞዴሉ ሁለተኛ ክፍል ማለትም ከሂደቶች ጋር በተያያዘ በተለይ የማጠናቀቂያ ፈተናው በከፍል ትምህርቱ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በሚመለከት ደግሞ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የክፍል ምልከታዎችን በማካሄድ፣ ምልከታ ከተካሄደባቸው መምህራንና ከሌሎች የተለያዩ ውጫዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ጋር ቃለመጠይቆችን በማካሄድና በጽሑፍ መጠይቅ ተጨማሪ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ ለማጥናት ተችሏል።

የፈተናዎች ኤጀንሲ ኀላፊዎችና በኤጀንሲው የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በተለይ ታላሚ ወሽባክና የፈተናውን አዎንታዊ ወሽባክ ከፍ ለማድረግ የሚጠቀሙባቸው ስትራቴጂዎች በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤና አሰራራቸውን ለማጥናት የሚያስችል መረጃ በከፊል-የተዋቀረ ቃለ መጠይቅ በመሰብሰብ ለመመርመር ተሞክሯል።

አራተኛውና በGreen (2007) የዳበረው የወሽባክ ሞዴል/ (Model of Washback) ደግሞ የሚከተለው ነው።




አዎንታዊ (positive) ወሽባክ

ምስል 2.2. የGreen የወሽባክ(ትምህርት-ፈተና) ተጣጥሞሽ (Overlapping) ሞዴል

ከHowkey (2006) ስራ መረዳት እንደተቻለው Green ይህን ሞዴል አዳብራው ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት በ2003 ነው። Howkey (2006) ሞዲሉ ላይ መጠነኛ ለውጥ አድርገው ግልጽነቱ ከፍ እንዲል አድገውታል። ከምስሉ ማስተዋል እንደሚቻለው ሞዴሉ በአጠቃላይ አራት መሰረታዊ ጉዳዮችንና በመካከላቸው ያለውን ተዛምዶ የሚያነሳ ነው። የመጀመሪያው ክፍል እንደ Green (2007) እና Misick (1996) አሰያየም መሰረታዊ የቋንቋ ችሎታዎችን (construct) ወይም በBachman (1990) መሰረት ከታየ ደግሞ የቋንቋ ብቃቶችን (Language Competencies) መለየትን የሚመለከት ነው። በመደበኛ ትምህርት የቋንቋ ችሎታዎች ተብለው የሚወሰዱት በሥርዓተ ትምህርቱ በተለይም በመርሐ ትምህርቶቹ ውስጥ ሰፍረው የሚገኙት ክፍሎች ናቸው ማለት ነው። የችሎታ መለኪያ ፈተናም መሰረት እንዲያደርግ የሚጠበቀው እነዚህን የቋንቋ ችሎታዎች ነው (Hughes 2003):: ሦስተኛው፣ የሞዴሉ ክፍል እነዚህን ችሎታዎች ለመመዘን ስለሚዘጋጀው ፈተና የሚሸፍናቸው ይዘቶች/ ችሎታዎችና የውስብስብነት ደረጃቸው እንዲሁም የጥያቄዎቹ አቀራረብ ምን መሆን እንዳለበት (እውነት/ሀሰት፤ ምረጫ፣ አዛምድ፣ ጻፍ (ዐረፍተ ነገር፣አንቀጽ፣ ድርሰት...) የመለየትንና የመወሰንን ተግባር የሚገልጽ ነው። ተጣጥሞሽ (Overlap) የሚለው ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በሁለቱ መካከል በይዘት፤ በይዘት ውስብስብነት ደረጃና በቅርጽ (Format) ያለውን መመሳሰል የሚመለከት ነው። አራተኛውና ተጣጥሞሽ በሚለው ትይዩ የተመለከተው አዎንታዊ ወሽባክ የሚለው ደግሞ በክፍል አንድና ሦስት ተጣጥሞሽ (Overlapping) ካለ ወሽባኩ አዎንታዊ ይሆናል፤ በተቃራኒው በሁለቱ መካከል ተጣጥሞሽ/ ተዛምዶ ከሌለ ወሽባኩ አሉታዊ ይሆናል የሚል ነው።

ከነዚህ ሞዴሎች መካከል ከ3-7 ያሉትን የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ ሦስተኛውን ሞዴል፣ ከ1-2 ያሉትን ጥያቄች ለመመለስ ደግሞ አራተኛው የወሽባክ ሞዴል መሰረት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ አጥኝው ከሁለቱ የወሽባክ ሞዴሎች ላይ ተመስርቶ የሚከተለውን ሞዴል ለዚህ ጥናት አዳብሮ ተጠቅሟል።



ምስል 2.3 የትምህርት ዓላማዎችና የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ተጣጥሞሽ እና ፈተናዎች በተሳታፊዎች ግንዛቤና ተግባራት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ሞዴል (ከBaily 1996 እና Green 2007 የወሸባክ ሞዴሎች ላይ ተመስርቶ የዳበረ)

ምዕራፍ ሦስት፤ የአጠናን ዘዴ (METHODOLOGY OF THE STUDY)

3.1 መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ጥናቱ የተጠቀመበት የአጠናን ዘዴ የሚገለጽበት ነው። በዚሁ መሰረት መጀመሪያ ጥናቱ የተጠቀመበት የምርምር ንድፍ ዓይነት ተመልክቷል። ቀጥሎ ጥናቱ የተካሄደበት ቦታና የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ ተገልጿል። ከዚያም በመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገሉት መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ የሚገልጸው ክፍል ይከተላል። ከዚያ በመቀጠል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችንና የመረጃ አሰባሰብ ሂደቶች (Procedures) አግባብነትና አስተማማኝነት እንዴት እንደተፈተሸ ተገልጿል። የመጨረሻው ክፍል ደግሞ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን ጥናቱ የተጠቀመባቸው የዓይነታዊና መጠናዊ ቴክኒኮች ምን ምን እንደሆኑ የተገለጸበት ነው።

3.2 የምርምሩ ንድፍ ዓይነት (Type of Research Design/ Study Design)

በዚህ ጥናት የተመረጠው የምርምር ንድፍ ዓይነት ቅይጥ (mixed) የሚባለው ነው። ይህ የጥናት ንድፍ ዓይነት የሁለቱን የምርምር ንድፍ ዓይነቶች (ዓይነታዊና መጠናዊ /Qualitative & Quantitative የሚባሉትን) የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴዎች ባንድ ጥናት የመጠቀም ሂደት ነው (Dornyei 2007፣ Creswell 2007፣ 2014፣ Robson 2002):; Creswell (2007፣ 2014) እንደሚያስረዱት፣ ሁለቱን የምርምር ንድፍ ዓይነቶች (መጠናዊና አይነታዊን) ቀይጦ መጠቀም የምርምር ችግርን በጥልቀትና በተሻለ ደረጃ ለመረዳት ያግዛል።

በተለይ ስለወሽባክ ጥናት የሚገልጹ ተመራማሪዎችም (ለምሳሌ Alderson እና Hamp-Lyons, 1996□ Wall እና Alderson 1996፣ እንዲሁም Watanabe 2004) ወሽባክ ውስብስብ የሆነ የትምህርት ክስተት ስለሆነ የተለያዩ መረጃዎችን በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች መሰብሰብንና መተተንተን የሚጠይቅ እንደሆነ ያስረዳሉ። ከAlderson እና Wall (1993) ጀምሮ በተለያዩ ሀገሮች የተካሄዱ አብዛኞቹ የወሽባክ ጥናቶችም ይህን አስተሳሰብ መሠረት ያደረጉ ናቸው ማለት ይቻላል። በዚህ ጥናት በተለይ ከወሽባክ ተሳታፊዎችና ሂደቶች (Processes) ጋር ተያይዘው የሚጠኑት ተላውጠች

(Variables) ቅይጥ የምርምር ንድፍ መጠቀምን የሚጠይቁ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የኢምፓክት(impact) ጥናት እራሱ በዚህ የምርምር ንድፍ ስር የሚካተትም ነው (Rebson 2002):: ወሸባክ ደግሞ የኢፓክት ጥናት አካል ነው። በእነዚህ ምክንያቶችም በዚህ ጥናት ቅይጥ በመባል የሚታወቀው የምርምር ንድፍ ዓይነት ሊመረጥ ችሏል።

በዚሁ መሠረት በዚህ ጥናት ከዓይነታዊ ስልት ሰነድ (Document) ፍተሻን፣ (የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን፣ መርሐ ትምህርቶችን፣ የማስተማሪያና መማሪያ መጽሐፎችን፣ የፖሊሲ ሰነዶችን)፣ የቡድን ተኮር ውይይቶችንና ቃለ መጠይቆችን፤ ከመጠናዊ ደግሞ መጠይቅንና የተደራጀ የክፍል ምልከታን በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ለመጠቀም ተችሏል። በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡት ዓይነታዊና መጠናዊ መረጃዎችም እንዲሁ በቅይጥ የጥናት ንድፍ አሰራር (Procedure) መሰረት ዓይነታዊ የሆኑት በክፍል በክፍል (categories) በመመደብ፣ መጠናዊ የሆኑት ደግሞ በገላጭና በድምዳሜያዊ(Inferencial) ስታትስቲክስ ተተንትነዋል።

3.3 የምርምር ቦታና የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ

ሀ. የምርምር ቦታ (Site) አመራረጥ

ምርምሩ የተካሄደበት ዋነኛ ቦታ አማራ ክልል ሲሆን፣ ከአማራ ክልል ውስጥ የፈተናውን ውስጣዊ (Micro) /በትምህርት ቤት ደረጃ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለማጥናት ደግሞ በዞን ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ የሚገኙ የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል። የዞን ከተማ አስተዳደሮች የተመረጡትም በወሳኝ፣ በተለይም በዓላማ-ተኮር ንሞና (purposeful) ዘዴ ነው። ወሳኝ የንሞና ዘዴ የተመረጠበት ምክንያትም ከዞን አስተዳደሮች ይልቅ የዞን ከተማ አስተዳደሮች የከተማ፣ የከፊል ከተማና የገጠር ትምህርት ቤቶች የሚገኙባቸው በመሆናቸው በሦስቱም ቦታዎች የሚያስተምሩ መምህራንና የሚማሩ ተማሪዎችን በጥናቱ ለማካተት እንዲያስችል ታስቦ ነው። በዚህ በአማራ ክልል 11 ዞኖችና 11 የዞን ከተማ አስተዳደሮች ያሉ ሲሆን ከእነሱ መካከል ስምንቱ የአማርኛ ቋንቋን በሥራና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማስተማሪያ ቋንቋነት የሚጠቀሙ ናቸው። የቀሩት ሦስቱ

ደግሞ በሌሎች (አሮምኛ፣ ሀምጥኛና አዊኛ) ቋንቋዎች የሚገለገሉ ናቸው። ከነዚህ 11 የዞን ከተማ አስተዳደሮች መካከል ጥናቱ ያተኮረው አማርኛ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትነት በሚሰጥባቸውና የስራ ቋንቋ ሆኖ በሚያገለግልባቸው ስምንቱ ላይ ነው። ጥናቱን በእነዚህ ቦታዎች ለማካሄድ የተፈለገው በተለያዩ ምክንያቶች ነው። ከምክንያቶቹ መካከል አንደኛው ቀደም ብሎ እንደተወሳው እነዚህ ዞኖች ቋንቋውን በስራ ቋንቋነት ስለሚገለገሉበት ቋንቋው የሚኖረው የአገልግሎት ደረጃ የተለየ ስለሚሆን የመማር-ማስተማሩ ሂደትም በተለያየ የክፍል ደረጃ ላይ ከሚጀመርበት፣ በሁለተኛ ቋንቋነት ከሚሰጥበት አካባቢ የተለየ ገጽታ ሊኖረው ይችላል የሚለው ነው። ሁለተኛው በ1986 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ.) በወጣው በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና በትምህርት ሚኒስቴር በ2010 በታተመው የሥርዓተ ትምህርት ማስፈጸሚያ ማዕቀፍ (Curriculum Frame-work) አማርኛ በአፍ መፍቻነትና በሁለተኛ ቋንቋነት የሚሰጥበት ዓላማና ነባራዊ ሁኔታ የተለያየ በመሆኑ የማጠናቀቂያ ፈተናው በሁለቱ (ቋንቋውን በአፍ መፍቻነትና በሁለተኛ ቋንቋነት) በሚያስተምሩ መምህራንና በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ሊፈጥር የሚችለው ተጽዕኖ ሊለያይ ስለሚችል ነው። ሦስተኛ፣ በክልሉ ብዙሀኑ ሕዝብ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት የሚገለገሉት በዚሁ ቋንቋ ስለሆነ ትኩረት ሊሰጠውና ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ተያይዞ የትምህርቱ አሰጣጥ ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊጠና የሚገባው ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

በክልሉ ከሚገኙ ከእነዚህ ስምንት የዞን ከተማ አስተዳደሮች መካከልም ጥናቱ የተካሄደባቸውን ከእድል ሰጭ የንሞና ዘዴ ዓይነቶች ቀላል/ ተራ የእጣ ንሞና (Simple Random Sampling) በተለይም እጣ የማውጣት ዘዴ (Lottery System) የሚባለውን በመጠቀም እንዲመረጡ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት በአማራ ክልል የአማርኛ ቋንቋ የሥራና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ ከሚያገለግልባቸው ስምንት የዞን ከተማ አስተዳደሮች መካከል በግማሾቹ/ አራቱ የዞን ከተማ አስተዳደሮች ላይ ጥናቱን ለማካሄድ ተችሏል። (ከጥናቱ ውጭ ከሆኑት ዞኖች አንዱ በሆነው በደቡብ ጎንደር ዞን ደግሞ ዋናውና ሁለተኛ የመስክ ጥናት እንዲካሄድ ተደርጓል።) ዋናው ጥናት የተካሄደባቸው የዞን ከተማ አስተዳደሮችም፣ አንደኛ ባህር ዳር፣ ሁለተኛ ጎንደር፣ ሦስተኛ ደብረ ብርሀንና አራተኛ ደሴ ናቸው። ቀጥሎ

በእነዚህ አራት የዞን ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ የሚገኙ 20 የመንግስት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች **ጠቅላይ የንሞና ዘዴን** (Comprehensive Samling)ን በመጠቀም ሁሉም ትምህርት ቤቶች ተመርጠው በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡ በጥናቱ የተካተቱት የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም በሚከተለው ሰንጠረዥ የቀረቡት ናቸው፤

ተ.ቁ	የዞን ከተማ አስተዳደር	በጥናቱ የተካተቱት ትምህርት ቤቶች
1	ባህርዳር	1. ግዮን ፣ 2. ጣና ሀይቅ፣ 3. ፋሲሎ፣ 4.መሸንቲ፣ 5.ዘጌ፣ 6.ጢስ አባይ ፏፏቴ እና 7. ባህርዳር ዙሪያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣
2.	ጎንደር	1.አዘዞ፣ 2. አንገረብ፣ 3. እድገት ፊለግ፣ 4. ፋሲለደስ ፣ 5. ሀዳሴ ጠዳ 6. ሀዳር 11 እና 7. ጎንደር ዙሪያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ት/ቤት፣
3.	ደብረ ብርሃን	ደብረ ብርሃንና ባሶ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ት/ቤት፣
4	ደሴ	1.ሆጤ፣ 2. ገራዶ፣ 3.ንጉሥ ሚካኤልና 4. ቅዳሜ ገበያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፡፡

ቀደም ብሎ እንደተወሳው እነዚህ ቦታዎችና ትምህርት ቤቶች የተመረጡት የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርት ቤት ደረጃ ወይም በመምህራንና ተማሪዎች ግንዛቤና ተግባራት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለማጥናት ነው፡፡

ከላይ እንደተጠቆመው በዚህ ጥናት የተካተቱት ትምህርት ቤቶች ደረጃ ከተማ፣ ከፊል ከተማና ገጠር ተብሎ በሦስት ተመድቧል፡፡ በዚህ ጥናት ዐውድ ትምህርት ቤቶቹን በእነዚህ ሦስት ደረጃዎች ለመመደብ ዋነኛ መስፈርት ሆኖ ያገለገለውም ተማሪዎቹ የሚመጡበት አካባቢ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶቹ የሚገኙባቸው ቦታዎች ደግሞ ተጨማሪ መስፈርት ሆነው አገልግለዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ትምህርት ቤቱ ከተማ ውስጥ የሚገኝና የሚቀበላቸው አብዛኛዎቹ (80% እና ከዚያ በላይ የሚሆኑት) የሚመጡት በከተማ ውስጥ ከሚገኙ መጋቢ የ፩ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሆነ ከተማ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ከከተማ ዳር አካባቢ የሚገኝ ሆኖ 50% አካባቢ የሚሆኑት ተማሪዎች በገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበራት አስተዳደር ሥር ከሚገኙ የ፩ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ግማሽ አካባቢ (50%) የሚሆኑት ደግሞ በከተማ ቀበሌዎች ውስጥ ካሉ የ፩ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚመጡ ተማሪዎች የሚስተናገዱበት የ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት **በከፊል ከተማነት** እንዲመደቡ ተደርገዋል፡፡ 80% ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑት በገጠር ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት አስተዳደር ስር ከሚገኙ የ፩ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

የሚመጡ ተማሪዎች የሚስተናገዱባቸው ትምህርት ቤቶች ደግሞ ገጠር በሚል ስያሜ እንዲጠሩ ተደርገዋል፡፡

ከእነዚህ በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች መካከል ደግሞ ከተማን፣ ከፊል ከተማንና ገጠርን መስፈርት በማድረግ በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ የክፍል ምልከታ የሚካሄድባቸው በሦስት የዞን ከተማ አስተዳደሮች ስር ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከጎንደር ፋሲለደስ፣ አዘዞና ጠዳ፤ ከባህር ዳር ፋሲሎና መሸንቲ፤ ከደሴ ሆጤና ቅዳሜ ገበያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ ከሦስቱ ዞኖች መካከል ሰፋ ያለውን የምልከታ ተግባር ለማከናወን የተመረጠው ጎንደር ነው፡፡ ምልከታ የሚካሄድበትን ዋነኛ ቦታ ጎንደርን ለማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት ደግሞ ከፋይናንስ አቅምና ከጊዜ ችግር በተጨማሪ ሌሎች ምክንቶችም አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ማንኛውም የክፍል ትምህርት ምልከታ፣ ምልከታ የሚካሄድባቸውን መምህራን ትብብር የሚጠይቅ ቢሆንም በተለይ ለወሽባክ ጥናት የሚካሄድ ክፍል ምልከታ ደግሞ ለረጅም ጊዜ/ ለወራት የሚከናወን በመሆኑ መምህራን ፈቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ (Cheng 2005)፡፡ በመሆኑም አጥኝው ፈቃደኛ መምህራንን ሊያገኝባቸው የሚችልባቸውን አማራጮች /ቦታዎች በአመች ንሞና ዘዴ ለመምረግ ግድ ሆኖበታል፡፡ በዚሁ ምክንያት በጥናቱ ከተካተቱት አራት የዞን ከተማ አስተዳደሮች መካከል የተሻለ ትብብር ሊያገኝ የሚችለው በዚሁ በጎንደር የዞን ከተማ አስተዳደር ሆኖ ተገኝቷል ማለት ነው፡፡ በዚህ ቦታ የተሻለ ትብብር ሊገኝ እንደሚችል እምነት ተጥሎ የነበረውም አጥኝው በጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ይሰራ በነበረበት ወቅት ተቋሙ ከነዚህ ትምህርት ቤቶች ጋር መስርቷቸው በነበሩት የኮሌጅ-ትምህርት ቤት ግኙነቶች (College-School Link) እና የዲግሪ ተማሪዎች ለማስተማር ልምምድ (ለፕራክቲከም) ይመደቡ የነበረው በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ስለነበረ፣ በእነዚህ ምክንያቶች ወደእነዚህ ትምህርት ቤቶች የማስተማር ልምምዱን ለመከታተል፣ የክፍል ምልከታ ለማካሄድና ሌሎች ተግባራት በተደጋጋሚ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ ከመምህራኑና ከትምህርት ቤቶቹ ኀላፊዎች ጋር የመተዋወቅ እድል አግኝቶ ስለነበረ ረዘም ላለ ጊዜ ምልከታ ለማካሄድ ትብብር እንደሚደረግለት በመተማመን ነው፡፡ በመሆኑም በታቀደው መሰረት በጥናቱ

ከተካተቱት የዞን ከተማ አስተዳደሮች መካከል ሰፋ ያለውን የምልከታ ጊዜ (ስምንቱን ሳምንታት ወይም ሁለት ወር የሚሆነውን ጊዜ) በጎንደር የዞን ከተማ አስተዳደር ስር ከሚገኙ በጥናቱ የተካተቱ ሰባት አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ በተመረጡ በአንድ የከተማ (ፋሲለደስ)፣ በአንድ የከፊል ከተማ (አዘዞ) እና በአንድ የገጠር ትምህርት ቤት (ጠዳ) ለማካሄድ ተችሏል፡፡ የቀሩት ሦስት ሳምንታት ደግሞ ሁለቱ በባህርዳር (ፋሲሎና መሸንቲ) አንዱ በደሴ (ሆጤና ቅዳሜ ገበያ) ትምህርት ቤቶች የክፍል ምልከታ ለማከናወን ውለዋል፡፡

የማጠናቀቂያ ፈተናው በመማር ማስተማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ፣ የተፅዕኖ ዓይነትና ደረጃ ትምህርት ቤቶቹ ከሚገኙባቸው ቦታዎችና ተማሪዎቹ ከሚመጡባቸው አካባቢዎች ጋር የተያያዙ ልዩነቶች መኖር አለመኖራቸውን ለመመርመር እንዲያመች /እንዲያስችል ደግሞ ከባህርዳር የዞን ከተማ አስተዳደር፣ ከከተማ ፋሲሎ፣ ከገጠር መሸንቲ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ከወሎ_ደሴ፣ ከከተማ ሆጤ፣ ከከፊል ከተማ ቅዳሜ ገበያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁ በዓላማ ተኮር ንምና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ቀጥሎም በእነዚህ ለክፍል ምልከታ በተመረጡ ሰባት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ 34 መምህራን መካከል አንደኛ ፈቃደኝነትን፣ ሁለተኛ ጾታን፣ ሦስተኛ የሥራ ልምድን፣ አራተኛ የክፍል ደረጃን፣ አምስተኛ ክፍለ ጊዜያቱ ለአጥኝው በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ሲያስተምሩ ምልከታ ለማካሄድ ያላቸውን አመቺነት ዋነኛ መስፈርት በማድረግ እንዲሁ በዓላማ ተኮር የተመረጡ 17 መምህራንን ሲያስተምሩ የክፍል ምልከታዎችን ለማካሄድ ተችሏል፡፡

የፈተናውን ውጫዊ (Macro) ተጽዕኖ ለማጥናት ደግሞ አንደኛ ከትምህርት ሚኒስቴር የፈተናዎች ኤጀንሲና የአማርኛ ሥርዓተ ትምህርት ክፍል፣ ሁለተኛ በጥናቱ ከተካተቱት የአማራ ክልል ትምህርት መምሪያዎችና የዞን ከተማ አስተደዳር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች መካከል ደግሞ የደቡብ ወሎና የሰሜን ጎንደር ትምህርት መምሪያዎች፣ ከዞን ከተማ አስተዳደር፣ የደሴና ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

ለ. የጥናቱ ተሳታፊዎች

የወሽባክ ሞዴሎች በሚለው ክፍል በመጠኑ እንደተጠቆመው ተሳታፊዎችን በተመለከተ ከኢትዮጵያ የትምህርት ዐውድ አንጻር በዚህ ጥናት እንዲካተቱ የተደረገው አንደኛ በጥናቱ የተካተቱት የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በእድል ሰጭ የንሞና ዘዴ በተመረጡ ክፍሎች (ሴክሽኖች) የሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ በጠቅላይ ንሞና ዘዴ የተመረጡ 20 ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራንና በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ የተመረጡ ትምህርት ቤቶች ምክትል/ ርዕሳነ መምህራን ናቸው። ሁለተኛ፣ ከትምህርት ሚኒስቴር በፈተናዎች ኤጀንሲ ከፈተና ዝግጅትና አስተዳደር ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁለት ኃላፊዎችና ሁለት የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች፣ ሦስተኛ፣ በጥናቱ ከተካተቱት የአማራ ክልል ዞኖች ትምህርት መምሪዎችና የዞን ከተማ አስተዳደሮች ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች መካከል ደግሞ እንዲሁ በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ የተመረጡት የደቡብ ወሎና የሰሜን ጎንደር ትምህርት መምሪያዎችና የደሴና የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች የሥርዓተ ትምህርት፣ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተና ክፍል ኃላፊዎች ናቸው።

እነዚህ ተሳታፊዎች እንዴት እንደተመረጡ ግልጽ ለማድረግ ያህል፣ በዚህ ጥናት ለተለያየ ዓላማ ዋነኛ የጥናቱ ተሳታፊ ሆነው የተመረጡት በጥናቱ የተካተቱት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን ናቸው። ከዚህ አንጻር አንደኛ፣ ከላይ በተዘረዘሩት አራት የዞን ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሚገኙት 20 አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያስተምሩ ሁሉም /104 የአማርኛ መምህራን **ጠቅላይ የንሞና ዘዴ** (Comprehensive Samling)ን በመጠቀም የጽሑፍ መጠይቅ በመሙላት እንዲሳተፉ ተመርጠዋል። ለእነዚህ መምህራን 104 የጽሑፍ መጠይቅ ተበትኖም 89ኙ በትክክል ሞልተው መልሰዋል። ሁለተኛ፣ ከእነዚህ በጥናቱ ከተካተቱት 20 ትምህርት ቤቶች መካከል ከተማን፣ ከፊል ከተማንና ገጠርን የሚወክሉ **በዓላማ ተኮር ንሞና** (purposive Sampling) ዘዴ የተመረጡ አምስት ትምህርት ቤቶች (ከከተማ ትምህርት ቤቶች ፋሲለደስና ሆጤ፣ ከከፊል ከተማ አዘዞና ቅዳሜ ገበያ ከገጠር ሕዳሴ ጠዳ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ

ትምህርት ቤቶች) የሚያስተምሩ 25 የአማርኛ መምህራን በቡድን ተኮር ውይይቶች እንዲሳተፉ ተመርጠዋል፡፡

ሌሎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ለክፍል ምልከታ የተመረጡት የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል መምህራን ናቸው፡፡ ለዚህ ተግባር የተመረጠውም የንሞና ዘዴ ዓላማ ተኮር የሚባለው ነው፡፡ በዚህ በዓላማ ተኮር ዘዴም ፈቃደኝነትን፣ ጾታንና የስራ ልምድን መሠረት ባደረገ ምርጫ በጎንደር፣ በባህርዳርና በደሴ ከተማን፣ ከፊል ከተማንና ገጠርን በሚወክሉ በፋሲለደስ፣ አዘዞ፣ ጠዳ፣ ፋሲሎ፣ መሸንቲ፣ ሆጤና ቅዳሜ ገበያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ 19 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተመርጠዋል፡፡ ከ19ኙ መካከል አስሩ ሴት፣ ዘጠኙ ወንድ ሲሆኑ፣ አንድ ወንድና አንድ ሴት ሁለተኛ ዲግሪ፣ 17ቱ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ናቸው፡፡ ሁሉም አምስትና ከዚያ በላይ ልምድ ያላቸው ናቸው፡፡

ሌሎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች በዕድል ሰጭ ንሞና ዘዴ በተመረጡ ቀደም ሲል ከተገለጹት ትምህርት ቤቶች መካከል በስምንት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ስምንት አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ምድቦች (Sections) ውስጥ በDornyei (2007) መስፈርት መሰረት ከ1-10% የሚደርስ ናሙና ለማካተት ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከ15 በላይ የ10ኛ ክፍል ምድቦች /ሴክሽኖች ያላቸው ትምህርት ቤቶች ሁለት ሁለት ሴክሽን፣ ከ15 ሴክሽን በታች ያላቸው ትምህርት ቤቶች ደግሞ አንድ አንድ ሴክሽን ተማሪዎች በዕድል ሰጭ የንሞና ዘዴ በተለይም በእጣ ተመርጠው በእነዚህ እጣው በወጣላቸው ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች መጠይቅ በመሙላት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ የክፍሎቹ ብዛት በDornyei (2007) የተገለጸውን ከ100 ያላነሱ ተሳታፊዎች የተካተቱበት ከ1-10% የሚደርስ የናሙና መጠን ተገቢነት ያለው ነው የሚለውን ሀሳብ ያሟላ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ከ*አተማ* ከፋሲለደስ ሁለት (ሲክሽን ሰባት እና አስር)፣ ከጣና ሀይቅ ሁለት (ሲክሽን አምስት እና ሃያ) ፣ ከ*ደብረ ብርሀን* አንድ፤ ከ*ሰፊል አተማ* ከአዘዞ (ሲክሽን 13) ከ*ቅዳሜ ገበያ* (ሲክሽን 12) ፣ ከ*ገጠር* ከጠዳ (ሲክሽን አምስት)፣ ከ*መሸንቲ* (ሲክሽን ሰባት) እና ከ*ገራዶ* (ሲክሽን አንድ) እንዲሁ አንድ አንድ ክፍል/ ሴክሽን ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በመሙላት እንዲሳተፉ

ተደርጓል፡፡ በእነዚህ በእጣ በተመረጡት 10 ክፍሎች/ ሴክሽኖች ለሚማሩ ተማሪዎች 400 (40*10) የጽሑፍመጠይቆች ተበትነው 303 ወይም 75.75% መጠይቆቹ በተሞሉባቸው ቀናትና ክፍለ ጊዜያት በክፍላቸው ተገኝተውና ፈቃደኛ ሆነው በትክክል በመሙላት ተሳትፈዋል፡፡

በመግቢያ አንቀጹ እንደተጠቆመው ሌላው የጥናቱ ተሳታፊዎች የፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ናቸው፡፡ በኤጀንሲው ውስጥ ከሚሰሩት ሰራተኞች መካከልም በዚህ ጥናት የተሳተፉት ሁለት ከፈተና ዝግጅት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው/ የነበራቸው ኃላፊዎችና ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተመረጡትም በሥራ ልምዳቸውና ከፈተናው ዝግጅት ጋር ባላቸው ቀጥተኛ ግንኙነት በመስፈርትነት በመጠቀም በዓላማ-ተኮር ንሞና ዘዴ ነው፡፡ በጥናቱ በመረጃ ምንጭነት እንዲሳተፉ የተደረገውም በከፊል የተዋቀሩ ቃለ መጠይቆች (Semi-strcutured Interview) ነው፡፡ በእቅዱ ላይ የፈተና ጥያቄ አዘጋጆችን/ ፀሐፊዎችን በቃለ መጠይቅ ለማሳተፍ ታስቦ የነበረ ቢሆንም በኤጀንሲው የቋንቋው ፈተና ዝግጅት ክፍል ኃላፊ እንደማይቻል በመግለጻቸው ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች ወደጽሑፍ መጠይቅ በመቀየር በክፍሉ ኃላፊ አማካኝነት እንዲሞሉ ለማድረግ ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር፡፡ በስምምነቱ መሰረትም የጽሑፍ መጠይቁ በወቅቱ ተዘጋጅቶ ለክፍሉ ኃላፊ ተሰጥቶ ለአንድ ዓመት ያህል ቢጠበቅም ተሞልቶ ሊመለስ ባለመቻሉ የጥያቄ ጸሐፊዎችን ሀሳብ በጥናቱ ማካተት ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ስለዚህ ተፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተቻለው የሚከተለው ዳራ (Background) ካላቸው ሁለት የኤጀንሲው ኃላፊዎችና ሁለት የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ነው፡፡

ከሁለቱ ኃላፊዎች አንዱ (በዚህ ጥናት ኃላፊ፩ ተብለው የተሰየሙት) የፈተናዎች ኤጀንሲን (በቀድሞው አጠራር የፈተናዎች ድርጅትን) የተቀላቀሉት ገና ድርጅቱ ሲቋቋም ነው፡፡ በድርጅቱ ውስጥ በፈተና ዝግጅት ባለሙያነት ሁለት ዓመት ተኩል አካባቢ፣ በፈተና ዝግጅት ቡድን መሪነት (በዚያን ጊዜ በመምሪያ ደረጃ የፈተና ዝግጅት ማስተባበሪያ ይባል በነበረው) ለስድስት ዓመታት፣ በተጠባባቂ ስራ-አስኪያጅነት አንድ አመት አገልግለዋል፡፡ የፈተናዎች ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት

ደግሞ በ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህርነት ለአንድ ዓመት ተኩል፣እንዲሁም በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም በሳይኮሎጂ መምህርነት አገልግለዋል፡፡ ከ1982- 1988 ዓ.ም ባለው ጊዜ ደግሞ በትምህርት ሚኒስቴር የስድስተኛና የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናዎች ቦርድ ውስጥ ከብሔራዊ ፈተናዎች ጋር የተያያዙ ስራዎች ሰርተዋል፡፡ ቀጥሎም ይሰሩበት የነበረው ቦርድና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የ፪ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናን ሲያስተዳድር የነበረው ተቋም ተዋህደው የፈተናዎች ድርጅት ሲቋቋም ድርጅቱን በፈተና ዝግጅት ባለሙያነት ተቀላቅለዋል፡፡ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በትምህርት ምዘናና ፈተና (Educational Assessment and Examination) እንግሊዝ ሀገር ሰርተው መመለሳቸው በፈተናዎች ድርጅት ውስጥ መስራት የነበረባቸውን ስራ በአግባቡ ለመስራት እንዳገዛቸው ያምናሉ፡፡

ሁለተኛው የኤጀንሲው ከፍተኛ ጎላፊ፣ (በጥናቱ ጎላፊ፪ የተባሉት) በአሁኑ ጊዜ በኤጀንሲው የፈተና ዝግጅትና አሰጣጥ የስራ ሂደት ባለቤት ሆነው በመስራት ላይ ናቸው፡፡ በዚህ ድርጅት መስራት የጀመሩት ድርጅቱ እንደተቋቋመ አካባቢ እ.ኤ.አ. በ1990 ዓ.ም. ነው፡፡ በድርጅቱ ውስጥ ስራ የጀመሩትም በፈተና ዝግጅት ባለሙያነት ነው፡፡ በጊዜ ሂደትም አሁን ካሉበት የጎላፊነት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡

ለአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች የተዘጋጁ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎችን በመመለስ የተሳተፉት የድርጅቱ የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች አንድ ሴትና አንድ ወንድ ሲሆኑ ሁለቱም በ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ከ10 ዓመት በላይ ያገለገሉና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን አማርኛ በማስተማር (TEAM-Teaching Amharic) የሰሩ ናቸው፡፡ የመጀመሪያዋና በጥናቱ ባለሙያ"ሀ" የተባሉት አሁን ድርጅቱን ለቀው በኮሌጅ መምህርነት እየሰሩ ሲሆን ሁለተኛውና ባለሙያ "ለ" የተባሉት አሁንም በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያነት በኤጀንሲው ውስጥ እየሰሩ ነው፡፡ ከሁለቱ ጎላፊዎችና አሁንም የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያነት እየሰሩ ካሉት ጋር የተካሄዱት ውይይቶች/ ቃለመጠይቆች) በቴፕ ካሴት ተቀርፀው ወደ ፅሑፍ ተመልሰዋል፣ (አባሪ 13 ይመለከቷል)፡፡ ከሴቷ ባለሙያ ጋር ቃለመጠይቅ ሲካሄድ ግን በጉንፋን ምክንያት ድምጻቸው ተቀይሮ

ስለነበረና የሕመም ስሜት ይሰማቸው በነበረበት ጊዜ ስለተገናኘን በቴፕ ለመቅርጽ አመቺ ሆኖ አልተገኘም፤ ቀጠሮውን ወደሌላ ጊዜ ለማሸጋገር እንዳይቻል ደግሞ አጥኝው ወደ ክፍለ ሀገር የሚሄድበት ጊዜ ደርሶ ነበር። ስለዚህ ከእሳቸው ጋር የተካሄደው ውይይት በመስክ ማስታወሻ ብቻ የተያዘ ነው።

እንዲሁም ከትምህርት ሚኒስቴር ሥርዓተ ትምርት ዳይሪክቶሬት ክፍል የሥርዓተ ትምህርት ክፍል ኀላፊውንና የአማርኛ ሥርዓተ ትምህርት ክፍል ተጠሪን በጥናቱ ለማሳተፍ የተሞከረ ቢሆንም፣ አንደኛ የሥርዓተ ትምህርት ክፍል ዋና ኀላፊው መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ እንደሆኑና የሚመቻቸውን ጊዜ በጸሐፊያቸው በኩል ለአጥኚው እንደሚያሳውቁ ገልጸውለት ስለነበረ ከሦስት ወራት በላይ (አንዳንዴ ወደ ቢሯቸው እየተመላለሰ በማስታወስ ጭምር) እየተጠባበቀ እንዳለ ስራውን /ኀላፊነቱን መልቀቃቸው ተነግሮታል። ይህም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የሚያሳይ ስለሆነ በሄዱበት ቦታ አፈላልጎ ለመጠየቅ የሚያስፈልግ ሆኖ አልተገኘም። በሌላ በኩል፣ በምክትልነትም ሆነ በሌላ የኀላፊነት ደረጃ ያለ አብሯቸው የሚሰራ፣ ሰለሥርዓተ ትምህርት ክፍሉ አሰራር በቂ ዕውቀት ያለው ሌላ ባለሙያ ማግኘት ስላልተቻለ፣ እንደታሰበው ፈተናው ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር ስላለው ግንኙነትና ሊያሳድረው ስለሚችለው ተጽዕኖ ቃለመጠይቁን ማካሄድ ሳይቻል ቀርቷል። ሁለተኛ የአማርኛ ሥርዓተ ትምህርት ክፍል ተጠሪው ጋር ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው ቃለመጠይቁን ማካሄድ ቢቻልም በቅርቡ ከሌላ ክፍል ተዛውረው የመጡ በመሆናቸውና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚዘጋጁ ሥርዓተ ትምህርቶች አተገባበር እንዲሁም ስለአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት (ለምሳሌ መርሐ ትምህርቶችና የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፎች አዘገጃጀት) የሚያውቁት ነገር አነስተኛ በመሆኑ፣ በክፍሉ ውስጥም እንደ ድሮው ሁለት ሦስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ባለሙያዎች ስለሌሉ በቂ መረጃ ለማግኘት ተችሏል ማለት አይቻልም። ከአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ የሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር እንዲሁ ውይይት ለማካሄድ ተሞክሮ አጥኚው ለዚሁ ዓላማ ወደ ባህርዳር በሄደባቸው ወቅቶች የሚመለከታቸውን ክፍሎች ማግኘት ባለመቻሉ የታሰበው ሳይሳካ ቀርቷል።

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች (Data Collection Instruments)

ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው ቅይጥ ጥናት የተለያዩ የዓይነታዊና መጠናዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን መጠቀምን የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት በዚህ ጥናት የሚከተሉትን ስድስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም የተለያዩ መረጃዎችን ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

ሀ. የማመሳከሪያ ቅጾች (Checklists)

በዘህ ጥናት ሁለት የማመሳከሪያ ቅጾች መረጃ ለመሰብሰቢያነት አገልግለዋል፡፡ አንደኛው የቋንቋው ትምህርት ባለሙያዎች የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ጥያቄዎች ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር የሚያዛምዱበት የቋንቋውን ትምህርት ዋና ዋና ክፍሎች የያዘ ማመሳከሪያ ቅጽ/ዝርዝር (Check list) ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በሥነ-ልቦናና በሥርዓተ ትምህርትና ማስተማር ባለሙያዎች እንዲሁ የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ጥያቄዎች ከአዕምሯዊ ምድብ ስድስት የትምህርት ባህሪያዊ ዓላማዎች ጋር ለማዛመድ የተገለገሉበት ስድስቱን ዓላማዎች የያዘው ቅጽና የእያንዳንዳቸውን ምንነት፣ ባህርያትና የሚጠቀሙባቸውን ቁልፍ ቃላት በማስረጃዎች አስደግፎ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ነው፡፡ የቅጾችን አዘገጃጀት በተመለከተም የቋንቋው መምህራን የፈተና ጥያቄዎቹን ለማዛመድ የተጠቀሙበት ቅጽ መጀመሪያ በዘጠነኛና በ10ኛ ክፍል መርሐ ትምህርቶች የቀረቡትን የክሂል፣ የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችና ለየትምህርቶቹ የተመደላቸውን የክፍለ ጊዜያት መጠን በመደመር በአጥኝው ተለይተዋል፡፡ ቀጥሎም መርሐ ትምህርቶቹንና በአጥኝው የተለዩትን የትምህርቱ ዓላማዎችና የተመደበላቸውን የክፍለ ጊዜያት መጠን የያዘው ቅጽ በአራት አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸውና የትምህርት መሳሪያዎች አዘገጃጀት ኮርስ ሲሰጡ በነበሩ የኮሌጅ መምህራን እንዲገመገም ተደርጓል፡፡ ገምጋሚዎቹ በሰጡት አስተያየት መሰረትም አስፈላጊው ማሻሻያ ከተደረገበት በኋላ በሙከራ ጥናቱ ተፈትሾ ተገቢ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስድስት ክፍሎችን/ ችሎታዎችን የያዘው

የአዕምሯዊ ምድብ ክፍል ደግሞ በተለያዩ የምዘናና ግምገማ መጽሐፎች በግልጽ የሚገኝና ደሳለኝ (2005) ሦስተኛ ዲግሪያቸውን ሲሰሩ የተጠቀሙበት ቅጽ በመሆኑ፣ የመስኩ ምሁራንን ለማነጋገር በተደረገው ጥረትም የሚለወጥ ነገር እንደሌለው ለማወቅ በመቻሉ እንዳለ ተወስዶ ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያነት እንዲያገለግል ተደርጓል፡፡

ለ. የክፍል ምልከታ_ የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት መገለጫ ምልከታ ንድፍ ሀ COLT_Communctive Orientation Language Teaching Obsrvation Scheme A)

ወሽባክ ፈተና በክፍል ትምህርት፣ በማስተማርና መማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚካሄድ ጥናትም የክፍል ምልከታን ያካተተ እንዲሆን የተለያዩ ምሁራን ለምሳሌ Alderson እና Wall (1993)፤ Cheng እና Curtis (2004)፤ Green (2007) እንዲሁም Watanabe (2004)) ይመክራሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት በተለይ የጥናቱን አምስተኛ፣ ሰባተኛና ስምንተኛ መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆኖ የተመረጠው የክፍል ምልከታ ነው፡ የክፍል ምልከታው ሁለተኛውን የምርምር ጥያቄ በሚመለከትም ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል፡፡

ምልከታውም ለመጀመሪያ ጊዜ Spad and Frehilich (1984) ዳብሮ፣ እንደገናም በእነዚሁ ምሁራን በ(1995) ተከልሶ (Revised ተደርጎ) የተዘጋጀውንና አስተማማኝነቱ በተለያዩ የቋንቋ ትምህርቶች የተፈተሸውን፣ እንዲሁም የተለያዩ ተመራማሪዎች የወሽባክ ጥናት ለማካሄድ የተጠቀሙበትን የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት መገለጫ (Communicative Orientation of Language Teaching_ COLT) የሚባለውን የተለመደ የምልከታ ንድፍ (Scheme) እና በGreen (2007) የተጨመሩትን አክሎ በመጠቀም የተከናወነ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በአባሪ 12 እንደተመለከተው የምልከታ ንድፉ ተግባራት፣ ይዘት፣ የይዘት ቁጥጥር፣ ፈተና መጥቀስ፣ የመማር ዘዴና ማቴሪያሎች የሚሉት ዋና ዋና ክፍሎች እንዲካተቱበት ተደርጓል፡፡

በCheng (2005) ስራ እንደተጠቆመው፣ እነዚህ በምልከታ ንድፉ የተካተቱት ክፍሎች የመነጩት ከግንባታውያን (Constructivism) የትምህርት ፍልስፍናና የዚህ ፍልስፍና

ነጸብራቅ ከሆነው ቋንቋ አጠቃቀም/ ክሂሎች ላይ ትኩረት ከሚያደርገው ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አተያይ ነው። በዚህ በተጠቀሰው የትምህርት ፍልስፍና እና የቋንቋ ትምህርት አተያይ መሰረትም አንደኛ፣ መምህራን ተማሪዎቻቸው እየሞከሩ የሚለማመዱባቸውን የመለማመጃ ዕድሎች ይፈጥራሉ። ሁለተኛ፣ መምህራን አብዛኛውን የትምህርት ጊዜያት ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታቸውን ለሚያዳብሩባቸው የቡድን ስራዎች፣ የቡድን ውይይቶች፣ ሚና ጨዋታዎች፣ ወዘተ. ያውሏቸዋል። በዚህም ተማሪዎች ሀሳብን የመግለጽ ችሎታቸውን ያዳብራሉ። የቋንቋ ችሎታቸውን እንዴት ባሉ ልምምዶች ማዳበር እንደሚችሉ ይማራሉ፤ ለመማርም የተነሳሱ ይሆናሉ። ሦስተኛ፣ መምህራን የሚናገሩት ትንሽ ይሆናል (the teacher will talk less)፣ አራተኛ መምህራኑ የመናገር ዕድል የሚያገኙባቸው አጋጣሚዎች እያነሱ ይመጣሉ። አዲስ ርዕስ ሲያስተዋውቁና በተወሰኑ ምክንያቶች ብቻ ጣልቃ የሚገቡ እየሆኑ ይመጣሉ። አምስተኛ፣ መምህራን ብዙ ጊዜ እውናዊ መሳሪያዎችን (Authenthic Materials) ከገሀዱ ዓለም እየወሰዱ መጠቀም ያዘወትራሉ።

በዚህ የምልከታ ንድፍ/ ቅጽ የተካተቱት ክፍሎች እነዚህ የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት መገለጫዎች ምን ያህል እየተተገበሩ እንደሆነ ለማጥናት የሚያስችሉ ናቸው ማለት ነው።

ሐ. የጽሑፍ መጠይቆች

Green (2007፣26) እንደገለጹት "የተሳታፊዎች ግንዛቤ የወሽባክ ጥናት የማዕዘን ድንጋይ ነው (The area of participant perceptions has long been a cornerstone of washback studies)":: Green 2007 Madaus 1998, Halayna እና ሌሎች 1981፣ Somes እና ሌሎች 1999) በመጥቀስ እንደሚገልጹት ከሰዎች ግንዛቤ (Perceptions) ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን/ተላውጦዎችን ለማጥናት ደግሞ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ መጠይቅ ነው። መጠይቅ የተሳታፊዎችን አመለካከት/ ግንዛቤ ለማወቅ/ ለመለየት ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ እያገለገለ ነው፤ (Survey remains the most effective means of accessing the views of Participants. Green 2007፣69) የሚለው ዐረፍተ ነገር ይህንኑ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም በዚህ ጥናት ከተሳታፊዎች ግንዛቤ ጋር የተያያዙ ተላውጦዎችን ለማጥናት ዋነኛ የመረጃ

መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ የተመረጡት በጥናቱ በታቀፉት ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ የቋንቋው መምህራንና ቋንቋውን በሚማሩ ተማሪዎች የሚሞሉ የጽሑፍ መጠይቆች ናቸው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ሁለት ዓይነት የጽሑፍ መጠይቆች ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል፤ የመምህራንና የተማሪዎች መጠይቆች ማለት ነው፡፡ ቀጥሎ እያንዳንዳቸው ለምንና እንዴት እንደተዘጋጁ የሚያስረዳው ክፍል ይቀርባል፡፡

የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ (Questionnaire)

በአጠቃላይ የዚህ መጠይቅ መሠረታዊ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው ከአምስት የትምህርት ምድቦች (ተግባራት/ ጊዜ አደላደል፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ የሚያስተምሯቸው የትምህርት ይዘቶችና በክፍል ውስጥ ተማሪዎቻቸውን ከሚመዝኑበት ሂደት) አንጻር በማስተማር ዝግጅታቸው (ለምሳሌ በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት) እና ትግበራቸው ላይ ስለሚያደርሰው ተጽዕኖ ያላቸውን ግንዛቤ ለማጥናት የሚያስችሉ መረጃዎች ለማግኘት፣
2. መምህራን ማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግታቸውና ትግበራቸው ላይ ላዳበሩት ግንዛቤ ምክንያቶቹ ምን ምን እንደሆኑ ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣
3. መምህራን ስለፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጦውና በመምህራን ባህርያት/ በዐቢይ ነጻ-ተላውጠዎች፣ እንዲሁም መምህራን ስለፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጦውና በትምህርት ቤቶች ዐውድ (Cotext Characterstics) /በንዑሳን ተላውጠዎች መካከል ያሉትን ተዛምዶዎች ለመለየት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣
4. የመምህራንን የክፍል ውስጥ ባሕርያት (Teachers' Classroom Behaviours) ለማጥናት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብና
5. አጠቃላይ መረጃዎችን (የመምህራኑን ዕድ፣ የትምህርት ዳራ፣ የማስተማር ልምድ፣ የክፍል ተማሪ-ጥምርታ፣ የሥራ ላይ ሥልጠና ተሳትፎን) የሚመለከቱ መረጃዎችን ለማግኘት ነው፡፡

ከዓላማዎቹ መረዳት እንደሚቻለውም ይህ መጠይቅ በጥናቱ የሚመለሱ አብዛኞቹን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰቢያነት የሚያገለግል ነው። በመሆኑም ቀደም ብሎ በተገለጹት አራት የዞን ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን በሙሉ ይህን መጠይቅ በመሙላት እንዲሳተፉ ተደርጓል። በመምህራን የሚሞላው ይህ የጽሑፍ መጠይቅ በተለይ ከተራ ቁጥር 3.1-3.6 የተመለከቱትን የምርምሩን ጥያቄዎች ለመመለስ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰብ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል።

የጽሑፍ መጠይቁ ሲዘጋጅም የሚከተሉትን ዋና ዋና ምንጮች (Sources) ተጠቅሟል።

- የChen (2002ሀ) እና የCheng (2005) የጽሑፍ መጠይቆች፣ (በተለይ ከ Chen (2002ሀ) መጠይቅ ላይ ተወስደውና ከጥናቱ ዐውድ ጋር በማዛመድ ተሻሽለው በዚህ ጥናት ያገለገሉትም ከክፍል አንድ መመሪያ አንድ፤ ጥያቄ ቁጥር 1፣2፣5-15፣17-21፣ 23፣24 እና 27 ከመመሪያ ሁለት፤ ከ28-37፣ 40-50 ያሉት ከክፍል ሦስት ጥያቄ ቁጥር 1፣7 እና 9 ሲሆኑ የCheng (2005) መጠይቅ መሰረት አድርገው የተዘጋጁት ጥያቄዎች ደግሞ ከክፍል ሁለት መመሪያ አንድ ጥያቄ 1 እና 2 ከመመሪያ ሁለት፣ ከ3-5 ያሉት ናቸው።)
- በተዛማጅ ድርሳናት ቅኝት የቀረቡ ወሸባክ ነክ ጽሑፎች፣
- የአማርኛ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት መርሐ ትምህርቶችንና የመማሪያ መጽሐፎችን፣
- በፈተናዎች ወሸባክ ላይ የተካሄዱ የምርምር ሥራዎች፣
- ከፈተናዎች አጀንሲ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር የተካሄዱ ቃለ መጠይቆችና
- በሙከራ ጥናት አንድና ሁለት የተገኙ ልምዶች።

የመጠይቁ ዋነኛ ዓላማ የተሳታፊዎችን ግንዛቤ ለማጥናት እንዲያስችል በመሆኑ፣ የአብዛኞቹ ጥያቄዎቹ አቀራረብ/ አጠያየቅ የሊከርት የስምምነትና የድግግሞሽ (Frequency) ስኬል በመጠቀም እንዲሆን ተደርጓል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎችና ምንጮች መሠረት በማድረግ የተዘጋጀው የጽሑፍ መጠይቅ የመጀመሪያ ክፍል፣ (መመሪያ /ንዑስ ክፍል አንድ) 27 ጥያቄዎችን አካቷል። ከ27ቱ ጥያቄዎች መካከል ከ1-6 የቀረቡት ተግባራትን/ ጊዜ አደላደልን፤ ሰባተኛውና ስምንተኛው የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ ከ9-11 እና ከ14-15 ያሉት የማስተማሪያ መሣሪያዎችን፤ ከ12-13 እና ከ16-19 ያሉት የትምህርት ይዘቶችን፤ ከ20-27 ያሉት የክፍል ምዘናን ይመለከታሉ። የጽሑፍ መጠይቁ የመጀመሪያ ክፍል ንዑስ ክፍል/ መመሪያ ሁለት ደግሞ (ከጥያቄ ቁጥር 28-52 ያሉትን ይመለከታል) መምህራኑ የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ ላይ ላዳበሩት ግንዛቤ ምክንያቶች (Factors) ናቸው የሚባሉ ክፍሉችን የያዘ ነው። በተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ እንደተገለፀው በተለያዩ ጽሑፎች መምህራን በፈተና ተጽዕኖ ላይ ለሚያዳብሩት ግንዛቤ ሰበብ/ ምክንያት ናቸው ከሚባሉት መካከል በተደጋጋሚ የሚጠቀሱት፣ እንዲሁም በሙከራ ጥናቶቹ የተገኙ አንዳንድ ልምዶች/ ጉዳዮች በዚህ መጠይቅ ጥያቄዎች እንዲካተቱ ተደርገዋል። መምህራን በፈተና ተፅዕኖ ላይ ላዳበሩት ግንዛቤ/ አጢኖት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ከሚባሉት ተላውጦዎች መካከልም አንደኛው የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ላይ ያላቸው ግንዛቤ (Percived Students' Learning Attitudes) ሲሆን ይህ ክፍል ከጥያቄ ቁጥር 28-32 ባሉት ጥያቄዎች ተወክሏል። ሁለተኛው መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ የሚለው ነው። ይኸኛው ደግሞ በሰባት ጥያቄዎች (33-38) ተወክሏል። ሦስተኛው ውጫዊ ጫናዎችን (ጥያቄ ቁጥር 39- 41) የሚመለከት ነው። አራተኛው ስለፈተናው ይዘትና ቅርፅ ያላቸው እውቂያ (42-44) ነው። አምስተኛው የፈተናውን የጠቀሜታ ደረጃ የሚመለከት ነው (45-49)። ስድስተኛው ለትምህርቱ የተመደበውን ጊዜ ተመጣጣኝ መሆን አለመሆን (ጥያቄ ቁጥር 50 እና 52)፣ ሰባተኛውና የመጨረሻው ደግሞ የተማሪዎችን ችሎታ ለደረጃው ብቁ መሆን አለመሆን (ጥያቄ ቁጥር 51) የሚመለከቱ ናቸው።

ሁለተኛው የጽሑፍ መጠይቁ ዐቢይ ክፍል የመምህራኑን የክፍል ውስጥ ባሕርያት (በክፍል ውስጥ ምን እንደሚያከናውኑና እንዴት እንደሚያከናውኑ) አንደኛ ከትምህርት አደረጃጀት/ ማን እንደሚያቅድና እንዴት እንደሚያቅድ (1-2)፣ ሁለተኛ ከትምህርት አዘገጃጀት (Lesson Preparation) (ጥያቄ ቁጥር 3(31-37) ፣ ሦስተኛ ከመምህራኑ ንግግር (Teacher Talk) (4 (4.1-4.4)) አንባርና አራተኛ ከማስተማሪያ ተግባራት (5 (5.1-5.9))

አኳያ ለመመርመር የሚያስችሉ መረጃዎች የተሰበሰቡበት ነው። የመጨረሻው ክፍል ከመምህራኑና ከሚሰሩባቸው አካባቢዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎች የተሰበሰቡበት ነው።

የጽሑፍ መጠይቁ የመጀመሪያና ሁለተኛ ክፍሎች ጥያቄዎች በሊከርት ስኬል (ከበጣም እስማማለሁ እስከ ጭራሽ አልስማማም) በሚሉት አማራጮች መሠረት የቀረቡ ስለሆኑ የመምህራኑ ምላሽ ለመረጃ ትንተና ወደ ኮምፒውተር ሲገባ ከፈተናው ተጽዕኖ አንጻር አሉተዊ (Negative) የሆኑት ዐረፍተ ነገሮች ላይ የሰጡት መልስ ተገልብጦ እንዲገባ ተደርጓል፤

ማለትም 1 የተባለው 5 4 የተባለው 2 3 የተባለው 3 2 የተባለው 4 5 የተባለው 1 እየተባለ እእንዲገባ ተደርጓል።

በዚህ መንገድ የተቀየሩት ጥያቄዎችም ጥያቄ ቁጥር 6፣16 :18፣22፣26፣37፣43፣44፣51 እና 52 ናቸው።

መረጃው ለትንተና ወደ ኮምፒውተር ከገባ በኋላ የተዛምዶና የህብረ-ድህረት (Multiple Regressions) ስታትስቲክስ ትንተናዎች በሚሰሩበት ጊዜ ደግሞ የተላውጦዎቹ ጥያቄዎች ተደምረው አማካያቸው እንዲወጣ ተደርጎ ነው።

የመጀመሪያው ክፍል ጥያቄዎች ማለትእከጥያቄ ቁጥር 1 እስከ 52 ያሉት እሙን የተደረጉት እንደቀጣይ ተላውጦ ነው (assumed to be interval (Meyers እና ሌሎች 2005፣ Weiss እና Leats 1998 Mark እና Janina 2010):: በመጨረሻው ክፍል የተጠየቁት ማለትም የትምህርት ዳራን፣ የማስተማር ልምድን፣ የተማሪ-ክፍል ጥምርታን፣ የስራ ላይ ስልጠናን የሚመለከቱ ተላውጦዎች መለኪያ ሆኖ የተወሰደው ደግሞ ደረጃዊ (Ordinal scale) ነው። ጾታና የመሳሰሉት ደግሞ ስማዊ (Nominal) ስኬል ናቸው። በህብረ-ድህረት ትንተና ስማዊ ስኬል የሆኑት የMuijs (2004) የአቀያየር ሂደቶችን (Steps) በመከተል ቁጥራዊ ተላውጦ (Dummy Varible) እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል።

ይህ የጽሑፍ መጠይቅ በዚህ ሁኔታ ተዘጋጅቶ በተለያዩ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ተገምግሞ አስፈላጊ ማሻሻያዎች ከተደረጉበት በኋላ በሙከራ ጥናት ተፈትሾና ከሙከራ ጥናቱ በተገኘው ግብረ-መልስ መሰረት ተሻሽሎ በዋናው ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት እንዲያገለግል ተደርጓል።

የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ

ከላይ ስለተጠቀሱት ጉዳዮች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘትና ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለማጥናት የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። በዚህኛው መጠይቅ የተካተቱት ጥያቄዎች ደግሞ በተለይ ከጥያቄ 3-6፣ 8፣10፣12፣13፣14 እና 15 የCheng (2005)ን የጽሑፍ መጠይቅን ዋነኛ መነሻ በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው። የቀሩት ደግሞ ከGreen (2007) እና Ferman (2004)፣ መጠይቆች የተወሰኑ ልምዶችን በመውሰድና ወሸባክ ነክ ጽሑፎችንና የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የቋንቋው መርሐ ትምህርቶችን ዓላማዎችና ይዘቶች መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው።

የተማሪው የጽሑፍ መጠይቅ አስፈላጊ ከሆነባቸው ምክንያቶች አንደኛው ከቋንቋው ማስተማርና መማር ተግባራት ጋር በተያያዘ በፈተናው ምክንያት ያዳበሩት ግንዛቤ (Perceptions) ካለ ለመመርመር ነው። ሁለተኛው በተማሪው መማር ላይ የፈተናው ተፅዕኖ (ካለ) ምን እንደሆነ ለመለየት/ የፈተናው ተፅዕኖ ከተማሪዎች አተያይ አንፃር ምን እንደሚመስል ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ነው። በዚህ መጠይቅ የተካተቱት ጭብጦችና የጭብጦቹ ምንጮች ከመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ ክፍል ሦስት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ስለዚህ ከተማሪው የሚገኘው መረጃ በመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ የሚገኘውን መረጃ ለማጠናከርና ለማመሳከሪያነትም (Triangulation) ያገለግላል። በዚህ የጽሑፍ መጠይቅ የተካተቱት ጭብጦችና በየጭብጦቹ የተጠየቁት ጥያቄዎችም የሚከተሉት ናቸው።

የጽሑፍ መጠይቁ የመጀመሪያ ክፍል ስለተማሪዎች ጸታ፣ ዕድሜ፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በክፍል ውስጥ እንደሚነሳና ለፈተናው ለመዘጋጀት ምን እንደሚያደርጉ የሚጠይቁ (ከ1-4 ያሉትን) ጥያቄዎችን የያዘው ዳራዊ መረጃ የሚለው ነው። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በውስጡ የሚከተሉትን ሦስት ዋና ዋና ጭብጦችንና በዋና ዋና ጭብጦች ስር ሌሉች ንዑሳን ክፍሎችን የያዘ ነው።

ጭብጥ (theme) ፩ ክፍል ውስጥ የማስተማሪያና መማሪያ ተግባሮች (Classroom Teaching and Learning Activities) **የሚል ነው (ጥያቄ ቁጥር** 5 (5.1-5.4፣ 6(6.1-6.8)፣ 7 (7.1-7.6)፣ 8 (8.1-8.5)፣ 10 (10.1-10.5 እና 11 (11.1.1-11.5.4 ይመለከታል) ።

በዚህ ምድብ ስር የተካተቱት ንዑሳን ጭብጦች የሚከተሉት ናቸው፤

- መምህራቸው በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ንግግር መጠን፤
- የክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ተግባሮች፤
- ራሳቸው ተማሪዎቹ ቋንቋውን የሚማሩባቸው ተግባሮች ማለትም የአማርኛ ቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያግዟቸው በክፍልና ከክፍል ውጭ የሚያከናውኗቸው ልምምዶች/ ተግባሮች፤

ጭብጥ ፪ በመማር ገፅታዎች ላይ ያላቸውን ግንዛቤ (Perceptions of aspects of learning) **የሚመለከት ነው፡፡ ጥያቄዎቹ፣ 12 (12.1-12.5)፣ 13 (13.1-13.7) እና 14እ(14.1-14.9) ናቸው፡፡ በዚህ ስር የተካተቱት ንዑሳን ጉዳዮችም የሚከተሉት ናቸው፤**

- የአማርኛ ትምህርቶች፣
- ቋንቋውን ለመማር ያላቸው መነሳሳት (Motivation)፣
- ቋንቋውን ለመማር/ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማሻሻል የሚመርጧቸው የመማሪያ ስትራቴጂዎች፣
- የማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ አሳድሮባቸው እንደሆነ ወይም ተፅዕኖ እእንደሌለው፣

ጭብጥ ፫ ተማሪዎች ለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸውን አመለካከት የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ክፍል የተካተቱ ጥያቀዎችም ጥያቄ ቁጥር 9 (9.1-9.6) እና 15 (15.1-15.6) ናቸው፡፡፡፡

እነዚህን ጭብጦችና ቀደም ብለው የተገለጹትን ምንጮች መሰረት በማድረግ በጽሑፍ መጠይቁ የተካተቱት ጥያቄዎች ከተዘጋጁ በኋላ እንደመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ ሁሉ ይኸኛውም በተለያዩ ባለሙያዎች እየታየ እንዲገመገም ተደርጎና በዋናው የሙከራ ጥናት ተፈትሾ አስፈላጊው ማሻሻያ ከተደረገበት በኋላ ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት እንዲያገለግል ተደርጓል (አባሪ 9 ይመለከቷል)፡፡

መ. ተተኳሪ ቡድን ውይይቶች (Focus Group Discussion)

ጥናቱ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ሁለት ዓይነት ተተኳሪ ቡድን ውይይቶቹ ተጠቅሟል፡፡ የመጀመሪያው ከመምህራን መረጃ ለመሰብሰብ ያገለገለው ነው፡፡ የዚህ ውይይት ዋና ዓላማ በክፍል ምልከታና በጽሕፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በተሻለ ደረጃ ለመረዳትና ለመተርጎም ነው፡፡ ለምሳሌ በመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ የሚሰበሰበው መረጃ ሊያሳይ የሚችለው መምህራን ስለፈተናው ተፅዕኖና ተፅዕኖ ፈጣሪ ምክንያቶች ያላቸውን ግንዛቤ ጥቅል ስዕል ነው፡፡ ተተኳሪ □ቡድን ውይይቶቹ ደግሞ ጥልቅ (in-depth) እና ሰፊ መረጃ ለማግኘት ያስችላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተተኳሪ የቡድን ውይይቶቹ የሚሰበሰቡት መረጃዎች በሌሉች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ለማመሳከሪያነት (Triangulation) ያገለግላሉ፡፡ በጥናቱ የተወሰኑ ጉዳዮችን (ለምሳሌ የፈተናውንና የትምህርቱን ተጣጥሞሽ) በተመለከተ ደግሞ በዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለግላሉ፡፡ በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተሰበሰበው ዓይነታዊ (qualitative) መረጃ ዋነኛ ዓላማ ግን በመጠናዊ (quantitiaitve) (በመምህራን የጽሑፍ መጠይቅና በክፍል ምልከታ) የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተርጎም፣ በጥልቀት ለመረዳትና ለማመሳከር እንዲያገለግል ነው፡፡

በመሆኑም በይሁነኝ የንሞና ዘዴ በተመረጡ አንደኛ ሁለት በከተማ (በአንደኛው አምስት፣ በሁለተኛው ስድስት መምህራን የተሳተፉበት)፣ ሁለተኛ፣ ሁለት በከፊል ከተማ (በአንደኛው አምስት በሁለተኛው ስድስት መምህራን የተሳተፉባቸው)፣ ሦስተኛ በአንድ የገጠር ትምህርት ቤት ሦስት መምህራን የተሳተፉበት፤ በድምሩ 25 መምህራን የተሳተፉባቸው አምስት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች በአምስት የተለያዩ ቦታዎች ተካሂደዋል፡፡ ውይይቶቹም መምህራኑ የማጠናቀቂያ ፈተናው በቋንቋው ትምህርት አሰጣጥ ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ምንነት፣ ዓይነትና ደረጃ በሚመለከት ያላቸውን ሀሳብና ግንዛቤ ለመግለጽ የሚያስችሉ Chen (2002) የተጠቀሙባቸውን ጥያቄዎች መነሻ ባደረጉ በአባሪ 7 በተካተቱትና በባለሙያዎች በተደጋጋሚ እንዲገመገሙ በተደረጉት፣ እንዲሁም ሁለት ጊዜ በመስክ በተፈተሹትና በግብረ መልሶች መሰረት እንዲሻሻሉ በተደረጉት ጥያቄዎች መነሻነት ተካሂደዋል፡፡

ሁለተኛው ተተኳሪ የቡድን ውይይት የብሄራዊ ፈተናዎችን ውጫዊ (macro) ተጽዕኖ ለመፈተሽ፣ በጥናቱ ከታቀፉት ዞኖች መካከል ከአራቱ ትምህርት መምሪያዎችና የዞን ከተማ አስተዳደሮች ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች የሥርዓተ ትምህርት፣ የትምህርት ጥራት ማረጋጋጫና የፈተና ክፍል ኀላፊዎች ጋር የተካሄዱት ናቸው፡፡ በእነዚህኛዎቹ ደግሞ እንደቀዳሚው ሁሉ በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ ከተመረጡት ሁለት የዞን ከተማ አስተዳደርና ሁለት የዞን ትምህርት መምሪያዎች 12 ኃላፊዎች (3*4) ጋር ከቋንቋ ትምህርትና ከማጠናቀቂያ ፈተናዎች ተጽዕኖ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ በአራት ቦታ አራት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል (አባሪ 11 ይመለከቷል)፡፡

ሠ.ቃለ መጠይቆች (Interviews)

የወሽባክ ጥናት ሲካሄድ ከዚህ ቀደም በወሽባክ አጠናን መንገድ የተካሄዱ ለአዲሱ ጥናት መሰረት የሚሆኑ ጥናቶች (Base line Studies) ከሌለ የወሽባክ ጥናት ከፈተና አዘጋጆቹ ታላሚ ወሽባክ መነሳት ያስፈልጋል(Qi 2004):: በመሆኑም የብሔራዊ ፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎች እና በኤጀንሲው የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በየዓመቱ የሚዘጋጁት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ምን ዓይነት ወሽባክ እንዲኖራቸው እንደሚያልሙ፣ ያለሙት (their Intention) ወሽባክ እንዲሳካ ምን ምን ስትራቴጂዎችን እንደሚጠቀሙ ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ጥያቄዎች በተካተቱበት **በከፊል የተዋቀረ ቃለ መጠይቅ** (Semi-strcutured Interview) ተዘጋጅቶ ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ሁለተኛ፣ አዲስ በመሆናቸው ለጥናቱ የሚያገለግል መረጃ ማግኘት ባይቻልም በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምህርት ዳይሬክቶሬት የአማርኛ ሥርዓተ ትምህርት ክፍል ተጠሪ ጋር የቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት በአግባቡ እየተተገበረ መሆን አለመሆኑንና ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋራ ያለውን ግንኙነት በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ ተዘጋጅቶ በቃለ መጠይቁ እንዲሳተፉ ተደርጓል (አባሪ 5 እና 6 ን ይመለከቷል)፡፡

ሦስተኛ፣ የክፍል ምልከታ ከተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች ከእያንዳንዱ ምልከታ በኋላ በእለቱ ከቀረበው ትምህርት ላይ የሚያተኩሩ Green (2007) የተጠቀሙባቸውን አምስት ጥያቄዎች መነሻ ያደረገ **በከፊል-የተዋቀረ ቃለ መጠይቅ** ለመምህራኑ

ለማቅረብ በታቀደው መሰረት አምስት ጥያቄዎች ተዘጋጅተው በሙከራ ጥናቱ እንዲፈተሹ ተደርገዋል። ከዚያም ከሙከራ ጥናቱ በተገኘው ትምህርት መሰረት በጥያቄዎቹ ላይ የተወሰኑ ማሻሻያዎች ተደርጎባቸው ከየዕለቱ ትምህርት አቀራረብ የሚመነጩ ጥያቄዎች እየታከሉባቸው በዋናው ጥናት የክፍል ምልከታ ከተካሄደባቸው የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የቋንቋው መምህራን ጋር ቃለ መጠይቆች ተካሂዶባቸዋል። በእርግጥ በተለያዩ ምክንያቶች (ለምሳሌ ስብሰባ የሚገቡ በመሆናቸው፣ ከክፍል በኋላ ያሉ ጊዜያት በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ቀደም ብለው የተያዙ በመሆናቸው፣ ከከተማ እየተመላለሱ የሚያስተምሩ የከፊል ከተማና የገጠር መምህራን ለቃለ ምልልሱ ቢቆዩ መጓጓጥ/ መኪና እናጣለን የሚል ስጋት ስላለባቸው፣ ወዘተ.) ከሁሉም የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው መምህራን ጋር እና ከሁሉም ምልከታ በኋላ ውይይት ማካሄድ አልተቻለም። ስለዚህ ከአራት የዘጠነኛና ከአምስት የ10ኛ ክፍል መምህራን ጋር ምልከታ ከተካሄደባቸው 170 ትምህርቶች መካከል 27ቱን በተመለከተ ቃለ መጠይቆች ተካሂደዋል። በአብዛኛዎቹ ውይይቶች የተጨመረው ጥያቄም ብዙዎቹ መምህራን ሲያስተምሩ የሚዘሏቸው የመማሪያ መጽሐፉ ክፍሎች ስላሉ እነዚህ፣ እነዚህ ጥያቄዎች/ መልመጃዎች ለምን ተዘለሉ? የሚለው ነው።

አራተኛ፣ በተለይ የፈተናውን ውጫዊ ተጽዕኖ በሚመለከት ተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በጥናቱ ከታቀፉት ትምህርት ቤቶች መካከል በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ/ምክትል ርዕሳነ መምህራን የሚሳተፉበት በከፊል የተዋቀረ ቃለመጠይቅ ተዘጋጅቶ መረጃ ለመሰብሰቢያነት አገልግሏል (አባሪ 10ን ይመለከቷል)።

ረ. *ሰነዶች (Documents)*

በፈተናዎች ድርጅት በየዓመቱ የሚዘጋጁ ፈተናዎች ከትምህርቱ መማሪያዎች ዓላማዎችና ይዘቶች ጋር ተገቢ ዝምድና እንዲኖራቸውና በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚታለመውን ተጽእኖ (ወሽባክ) ከፍ ለማድረግ የሚያዘጋጇቸው ሰነዶች እንደሚኖሩ በማሰብ እነዚህን ሰነዶች በመረጃ ምንጭነት ለመገልገል ታስቦ የነበረ ቢሆንም በድርጀቱ ውስጥ ማግኘት የተቻለው አንደኛ የድርጅቱን ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች የሚገልጽ ጽሑፍ፣ ሁለተኛ፣ በየትምህርት ዓይነቱ ፈተና አዘጋጆች/ ጥያቄ

ጸሐፊዎች እንዲጠቀሙባቸው የሚዘጋጁ ልየታዎች (Specifications)፣ እና የየደረጃው መርሐ ትምህርቶችን ብቻ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከልም ልየታዎቹን ለጥናት መጠቀም እንደማይቻል በአማርኛ ፈተና ዝግጅት ክፍል ኃላፊው በመገለጹ በእነሱ ላይ ተመስርቶ ሀሳብ መስጠት ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ከሌሎቹ ሰነዶች የተገኙ መረጃዎችን ግን በጥናቱ ውስጥ እንዳስፈላጊነቱ ለመጠቀም ተሞክራል፡፡

በGreen (2007) የወሽባክ ሞዴል መሰረት በተለይ የፈተናዎችንና የትምህርቱን ተጣጥሞሽ (Overlapping/) ማጥናት የሚቻለው ፈተናዎቹን ራሳቸውን በማጥናትና ከተለያዩ መለኪያዎች አንጻር ለምሳሌ ከትምህርቱ ዓላማዎች ወይም ከሌሎች መስፈርቶች አንጻር በመገምገም ነው፡፡ በመሆኑም ከ2000-2004 ዓ.ም. ባሉት ጊዜያት የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ሁለተኛው በሰነድ የመረጃ ምንጭነት ያገለገሉ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መርሐ ትምህርቶችም፣ ከፈተናው ጋር ያላቸውን ዝምድና ለማጥናት እንዲቻል በተለይ ከዓላማዎቻቸው፣ ከይዘቶቻቸውና ከተመደበላቸው የክፍለ ጊዜ መጠን አንጻር በጥልቀት ተመርምረዋል፡፡ እንዲሁም የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የመማሪያ መጻሕፍትና የመምህሩ መምሪያዎች ከክፍል ምልከታው ጋር በተያያዘ መልኩ በመረጃ ምንጭነት እንዲያገለግሉ ተደርገዋል፡፡

ከሰነድ ጋር በተያያዘ ሌላው የመረጃ ምንጭ የክፍል ፈተናዎች ናቸው፡፡ ከዞን ትምህርት መምሪያዎችና ከዞን ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች ኃላፊዎች ጋር በተካሄዱት ውይይቶች ማረጋገጥ እንደተቻለው በአማራ ክልል የክፍል ፈተናዎችን በተመለከተ ሁለት ዓይነት አሰራር ነው ያለው፡፡ አንደኛው አሰራር ቀደም ሲል እንደነበረው የክፍል ፈተናዎች በትምህርት ቤት ደረጃ በራሳቸው በትምህርት ዓይነቶቹ መምህራን የሚዘጋጁበት ሁኔታ ሲሆን፤ ሁለተኛው በሁሉም የዞን ከተማ አስተዳደር ስር ላሉ ትምህርት ቤቶች በዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች እንዲሁም በዞን ትምህርት መምሪያዎች ስር በሚገኙ ወረዳዎች ስር ለሚገኙ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዞን ትምህርት መምሪያዎች ፈተናዎቹን አዘጋጅተው ለየትምህርት ቤቶቹ የሚያሰራጩበት አሰራር ነው፡፡ በእርግጥ በዞን ትምህርት መምሪያዎችም ሆነ በዞን ከተማ አስተዳደሮች ፈተናዎች የሚዘጋጁት ከየትምህርት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

ቤቶቹ (በልምድ፣ በስራ አፈጻጸምና በመሳሰሉት መስፈርቶች) በሚመረጡ የየትምህርት ዓይነቶቹ መምህራን ነው። ስለዚህ በዚህ ጥናት በሦስቱም ወገኖች የሚዘጋጁት እነዚህ ፈተናዎች በውስጣዊ ወይም በክፍል ፈተናነት ተመድበው እንዲታዩ ነው የተደረገው። በዚሁ መሰረት በጥናቱ በታቀፉት ዞኖች በትምህርት ቤት፣ በዞን ከተማ አስተዳደርና በዞን ትምህርት መምሪያዎች በ2004 እና 2005 ዓ.ም. የተዘጋጁ የ፩ኛና የ፪ኛ መንፈቀ ዓመት የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል ፈተናዎችን ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል። በተደረገው ጥረትም የተፈለገውን ያህል ማግኘት ባይቻልም (ፈተናዎች ፋይል የማያደርጉ ትምህርት ቤቶች በመኖራቸው ምክንያት) በተገኙት 17 የዘጠነኛና 21 የ10ኛ ክፍል የ2004 እና የ2005 ዓ.ም. እ.ኢ.አ.) የ፩ኛና የ፪ኛ መንፈቀ ዓመት ፈተናዎች መሰረትነት ከክፍል ፈተናዎች ጋር የተያያዘውን ጉዳይ ለመመርመር ተችሏል። ይህም አብዛኞቹ ፈተናዎች በዞን ደረጃ የሚዘጋጁ ሆነው ከመገኘታቸው አንጻር ሲታይ በክልሉ ያለውን የክፍል ፈተና ገጽታ የሚያሳይ /የሚወክል ነው ማለት ይቻላል።

3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አግባብነትና አስተማማኝነት (Validity and Reliability)

የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹ ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት ከማገልገላቸው በፊት አግባብነታቸውና አስተማማኝነታቸው በሁለት መንገድ እንዲፈተሽ ተደርጓል። አንደኛው፣ በባለሙያዎች (Reviewers) በተደጋጋሚ እንዲገመገሙ መደረጋቸው ነው። ሁለተኛው፣ በተለይ የመምህራኑና የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቆች፣ ከመምህራንና ከዞን የትምህርት ኃላፊዎች ጋር ለሚካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተዘጋጁት ሁለት መምሪያዎች (Guidelines) የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ከቋንቋው ትምህርት ዓላማዎች/ ይዘቶች ጋር ለማዛመድ የተዘጋጀው የዓላማና ዝርዝር ቅጽ፣ የክፍል ምልከታ ንድፉ/ ቅጹና ከምልከታ በኋላ ከመምህራኑ ጋር ቃለመጠይቅ ለማካሄድ የተዘጋጁት ጥያቄዎች፣ እንዲሁም ከትምህርት ቤቶቹ ርዕሳነ/ ምክትል ርዕሳነ መምህራን ጋር ለሚካሄደው ቃለ መጠይቅ የተዘጋጁት ጥያቄዎች በመስክ በዋናው ጥናት ባልተካተቱ ከታች በተዘረዘሩት ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሞከሩ

ተደርገዋል፡፡ በተለይ የመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅና ከመምህራን ጋር ለሚካሄደው ተተኳሪ የቡድን ውይይቶቹ የተዘጋጀው መምሪያ በተለያየ ጊዜና በተለያዩ ቦታዎች ሁለት ጊዜ እንዲሞከሩ ተደርገዋል፡፡ ቀጥሎ መጀመሪያ መሣሪያዎቹ እንዴት እንደተገመገሙና በግምገማዎቹ በተገኙት ግብረ-መልሶች መሰረት የመሣሪዎቹን የላህይና የይዘት አግባብነት (Face and Content Validity) ከፍ ለማድረግ በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪዎቹ ላይ ምን ምን ለውጥ እንደተደረገ፣ ምን ምን እንደተቀነሰና ምን ምን እንደተጨመረ ይቀርባል፡፡ ከዚያም በመስክ መሣሪያዎቹ የት የት እንደተሞከሩ፣ ምን ምን ውጤትና ትምህርት እንደተገኘ ይገለጻል፡፡

3.5.1. ከገምጋሚ ባለሙያዎች (Reviewers) የተገኙ የአግባብነት መረጃዎች (Evidences of Validity)

ቀደም ባለው ክፍል በተገለጸው መሠረት የመሣሪያዎቹ የላህይና የይዘት አግባብነትና አስተማማኝነት ከባለሙያዎች ግምገማ አንጻር ለመመርመር የተሞከረው ሁለት ጊዜ ሲሆን የመጀመሪያውና የሁለተኛው ደረጃ ገምጋሚዎችም የተለያዩ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ግምገማ ከሙከራ አንድ በፊት በሚያዚያ ወር 2004 ዓ.ም ላይ አንደኛ በጎንደር ዩንቨርሲቲ በሚያስተምሩ አንድ አማርኛን በማስተማር፣ አንድ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ያጠኑ፣ ሁለተኛ በጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በሚያስተምሩ ሁለት አማርኛን ማስተማር፣ አንድ ሥነ-ልሳን በአጠኑ የቋንቋው መምህራንና ሁለት ትምህርታዊ ሥነ-ልቦና ያጠኑ የምዘና (Measuremnt) ባለሙያዎች/ የኮሌጁ መምህራን የመጠይቆቹን፣ የቡድን ተኮር ውይይቶችንና የቃለ መጠይቆቹን ጥያቄዎች የላህይና የይዘት አግባብነት እንዲመረምሩ ተደርጓል፡፡ እነዚህ የቋንቋና የትምህርታዊ ሥነ-ልቦና ባለሙያዎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ሲገመግሙም Cheng (2002) እንዳደረጉት አንደኛ በመሣሪያዎቹ ውስጥ የተካተቱ መመሪያዎችን፣ ጥያቄዎችንና (Items) አማራጮቹ የተገለፀበትን ቋንቋ ግልፅነትና የይዘቶቻቸውን ተገቢነትና መሰል ጉዳዮች ትኩረት ሰጥተው እንዲገመግሙና ሊሻሻሉ/ ሊቀየሩ ይገባቸዋል ባሏቸው ክፍሎች ላይ አስተያየታቸውን እንዲገልፁ፣ ሁለተኛ በእያንዳንዱ ተላውጦ (Variable) ስር ከቀረቡ ጥያቄዎች መካከል ስለተላውጦው መረጃ ለማግኘት የማያስችሉ/ ከተላውጦው ጋር ዝምድና የሌላቸው የመሰሏቸውን ጥያቄዎች

(Items) ለይተው እንዲያመለክቱ፣ ሦስተኛ ሊጠየቅ ሲገባው የቀረ ጉዳይ ካለ እንዲጠቁሙ ተጠይቀዋል::

በቀዳሚው አንቀፅ በተገለፀው መሰረት በተጠቀሱት ባለሙያዎች በተካሄዱት ግምገማዎች ከባለሙያዎቹ ከተገኙት ግብረ መልሶች/ አስተያየቶች መካከል አሳማኝ/ ተጠየቃዊ የሆኑትን በመቀበል በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹ ከተካተቱት ጥያቄዎች ውስጥ የተወሰኑት እንዲወጡ፣ የተወሰኑት እንዲሻሻሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በሌሉች ጥያቄዎች እንዲተኩ፣ የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ደግሞ የተወሰኑ ጥያቄዎች እንዲጨመሩ በማድረግ የተሻሉ መሣሪያዎች ሆነው እንዲዘጋጁ ተደርገዋል::

የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹ በዚህ መንገድ ተሻሽለው እንዲዘጋጁ ከተደረጉ በኋላ በተለይ በመምህራኑ የሚሞላው የጽሑፍ መጠይቅ ስለአብዛኛዎቹ ተላውጠዎች መረጃ የሚሰበሰብበትና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክሶች መሰረት የሚያደርጉበት ስለሆነ ከዋናው የመከራ ጥናት በፊት በጥናቱ ባልታቀፉት በ3.5.2.1 ስር በተዘረዘሩት ወረዳዎች በሚያስተምሩ 40 የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን እንዲሞላ በማድረግ እንዲሞከር ተደርጓል:: (አባሪ አንድ በእነዚህ መምህራን የተሞከረውን መጠይቅ የያዘ ነው)::

ከመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ በተጨማሪ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መምህራኑ ያላቸውን ግንዛቤ በጥልቀት ለመመርመር ያስችላል ተብሎ የተዘጋጀው ተተኳሪ የቡድን ውይይት መምሪያውም እንዲሁ መጠይቅ በመሙላት ከተሳተፉት መምህራን መካከል ከ10 የሁለት ትምህርት ቤቶች መምህራን ጋር በአባሪ ሁለት በቀረቡት ጥያቄዎች መሰረትነት ውይይት በማካሄድ ራሱንም ሆነ ሌሎች መሣሪያዎችን ለማሻሻል የሚረዱ መረጃዎችን ለማግኘት አስችሏል::

በመከራ አንድ የመምህራኑ መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይቱን መነሻ ጥያቄዎች የያዘው መምሪያ በመስክ ከተሞከሩ በኋላ ከመከራው በተገኘው ትምህርት መሰረት መሣሪያዎቹ እንዲከለሱ ተደርገዋል:: ከመከራው በተገኘው ግብረ-መልስ መሰረት እንዲሻሻሉ ከተደረጉ በኋላ ደግሞ እንደገና በሌሎች ባለሙያዎች እንዲታዩ /እንዲገመገሙ ተደርገዋል:: በዚህኛው ግምገማ የተሳተፉትም አንደኛ ቋንቋውን በዩንቨርሲቲ ደረጃ ለረጅም ዓመታት ያስተማሩ አንድ ተባባሪ ፕሮፌሰር፣ ሁለተኛ፣ ሁለት

የአጥኝው የትምህርት ባልደረቦች፣ ሦስተኛ፣ አንድ የአራተኛ ዓመት የዶክትሬት ተማሪ (የትምህርታዊ ሥነ-ልቦና ባለሙያ) ናቸው። እነዚህ ባለሙያዎችእአንደኛ ከላይ በተገለጸው ሂደት መሰረት የተሻሻሉትንና በሙከራ የተፈተሹትን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ ሁለተኛ፣ የተማሪዎችን መጠይቅ፣ ሦስተኛ፣ ለፈተናዎች ኤጀንሲ ጎላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች፣ ለትምህርት ቤቶች ርዕሳነ/ ምክትል ርዕሳነ መምህራን የተዘጋጁትን ቃለመጠይቆች፣ አራተኛ፣ ለዞን ትምህርት መምሪያዎችና የዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች የሥርዓተ ትምህርት፣ የፈተናና የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ክፍል ጎላፊዎች የተዘጋጁ የቡድን ውይይት ጥያቄዎችን፣ አምስተኛ፣ የሥነ-ትምህርትና የቋንቋው ትምህርት ባለሙያዎች የፈተናዎቹን ጥያቄዎች ከአዕምሯዊ ምደብ የትምህርት ዓላማዎችና ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችና ይዘቶች ጋር የሚያዛምዱባቸውን/ የሚያመሳክሩባቸውን ቅፆች እና ስድስተኛ፣ የምልከታ ንድፉን በመገመገም ጠቃሚ አስተያየቶችን ሰጥተዋል። በእነዚህ ባለሙያዎች የተሰጡ ጠቃሚ አስተያየቶችን በጽሑፍ መጠይቆቹ፣ በቃለመጠይቆቹ፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት መምሪያዎቹና ሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እንዲካተቱ ከተደረገ በኋላ ሁሉም የመረጃ መሰበሰቢያ መሳሪያዎች በአጥኝው አማካሪ ተገምግመዋል። በአጥኚው አማካሪ የተሰጡ አስተያየቶችና ማስተካከያዎች በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ እንዲካተቱ ከተደረገና የመሳሪያዎቹ የላህይና የይዘት አግባብነት ከተፈተሸ በኋላ ደግሞ ሁለተኛውና ዋናው የሙከራ ጥናት ተካሂዷል።

3.5.2 ከሙከራ ጥናቶቹ የተገኙ የአግባብነትና አስተማማኝነት ማስረጃዎች

3.5.2.1 የሙከራ ጥናት አንድ

በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከሚገኙት 19 ወረዳዎች መካከል አስራ አንዱ (ደባርቅ፣ ዳባት፣ ወገራ፣ ደንቢያ፣ ጣቁሳ፣ ሻውራ፣ ጭልጋ፣ ገንዳ ውሃ፣ መተማ፣ ላይ አርማጭሆ እና ጃን አሞራ) የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን በማስፈተን ከአምስት ዓመት በላይ እንደሆናቸው ከዞኑ ትምህርት መምሪያ የተገኘው መረጃ ያሳያል። ከእነዚህ መካከል በስምንቱ ወረዳዎች (ደባርቅ፣ ዳባት፣ ወገራ፣ ደንቢያ፣ ጣቁሳ፣ ሻውራ፣ ጭልጋ እና ላይ አርማጭሆ) የሚገኙ 10 ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን (ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ ቢያንስ አንዱን ዓመት የ10ኛ ክፍል

ተማሪዎችን ያስተማሩ) የየትምህርት ቤቶቹ ርዕሳነ መምህራን ለስልጠና ወደ ጎንደር መጥተው በነበረ ጊዜ መጠይቆችን አስሞልተው ለአጥኝው ወይም ለዞን ትምህርት መምሪያው እንዲልኩ ፈቃደኝነታቸውን ተጠይቀው ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልጸዋል። በዚሁ መሰረት 47 የጽሑፍ መጠይቆችን ተረክበው ወስደው አስሞልተው ልከዋል። በርሳነ መምህራኑ አማካይነት በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ 47 መምህራን 47 የጽሁፍ መጠይቅ ተበትኖ 40ው በትክክል ተሞልቶ ተመልሷል። የጽሑፍ መጠይቅ በመመላት ከተሳተፉት 40 መምህራን መካከል 23ቱ (57.5) ሴቶች 17ቱ (42.5) ወንዶች ናቸው። የሴቶቹ ቁጥር ከወንዶቹ ቢበልጥም ልዩነቱ ጠባብ ነው።

አብዛኞቹ መምህራን ሁለትና ከዚያ በላይ ዓመት ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን ያስተማሩ ሲሆን አንድ ዓመት ብቻ ያስተማሩት በጣም ውስን ናቸው። በመቶኛ ሲሰላ 17.5% ናቸው። በመሆኑም መረጃ በመስጠት የተሳተፉት መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በመማር ማስተማር ሂደቶች ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ወይም እንደሌለው ለመግለፅ በቂ ልምድ የነበራቸው ነበሩ ማለት ነው። በዚህ የመጀመሪያ ሙከራ ጥናት የተሳተፉት መምህራን ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆኑ የአብዛኛዎቹ (60%) ዲግሪ ቢ.ኢ.ዲ ነው። የቀሩት (40%) ቢ.ኤ ዲግሪ ያላቸው ናቸው። ሁለተኛ ዲግሪ ያለው ወይም ከመጀመሪያ ዲግሪ በታች የሆነ አንድም መምህር በመረጃ ምንጭነት አልተሳተፈም። አብዛኞቹ (57.5%) የዚህ ሙከራ ጥናት ተሳታፊዎች ከ6-10 ዓመት የማስተማር ልምድ አላቸው። 32.5% የማስተማር ልምዳቸው ከአምስት ዓመት በታች ነው። በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ደግሞ አብዛኞቹ (57.5%) ከአምስት ዓመት በታች የማስተማር ልምድ ያላቸው ሲሆኑ ከ6-10 ዓመት የማስተማር ልምድ ያላቸው 42.5% ናቸው።

በዚህ የመጀመሪያ ሙከራ የጽሑፍ መጠይቅ በመመላት ከተሳተፉት መምህራን መካከል 10 መምህራን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በአባሪ ሁለት በቀረቡት ጥያቄዎች መሰረትነት በተካሄዱት ሁለት የቡድን ተኮር ውይይቶች እንዲሳተፉ ተደርገዋል።

ከመካራ ጥናት አንድ የተገኘ ትምህርት

በአርባው መምህራን ተሞልቶ በተመለሰው የጽሑፍ መጠይቅና ከተወሰኑ መምህራን ጋር በተካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የጽሑፍ መጠይቁንም ሆነ የቡድን ውይይት ጥያቄዎችን ለማሻሻል የሚረዱ ጠቃማ ሀሳቦችን ማግኘት ተችሏል። ለምሳሌ በዚህ መጀመሪያ በተሞከረው የጽሑፍ መጠይቅ የሥነ-ጽሁፍ ትምህርትን በሚመለከት መነሳት የነበረባቸው ጉዳዮች ተዘንግተው ነበር። የቋንቋው ትምህርት ተደርገው ታስበው የነበሩት አራቱ ክሂሎች፣ ሰዋስውና ቃላት ብቻ ነበሩ። ከመምህራኑ ጋር በተካሄዱት ውይይቶች ግን የሥነ-ጽሑፍ ትምህርት አንዱና ዋነኛ የቋንቋው ትምህርት አካል ሆኖ እንደሚታይ (እንደተመደበ) ማረጋገጥ ተችሏል። የቃላት ትምህርት ደግሞ በአጥኝው እንደተገመተው ራሱን ችሎ ሳይሆን በሰዋስው ትምህርትነት እንደተካተተ ማወቅ ተችሏል። ልዩነቱ ሊከሰት የቻለውም በተዛማጅ ጽሑፎች በተገኙ ሐሳቦች ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጎ ስለነበረ ነው።

ሁለተኛው የመጀመሪያው የጽሑፍ መጠይቁ ሙከራና ከመምህራን ጋር የተካሄዱት የቡድን ውይይቶች ካስገኙት ጠቀሜታ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችለው ከመምህራኑ ጋር የቡድን ውይይት ሲካሄድ ስለፈተናው ይዘት (በምን በምን ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩር) እና አጠያየቁን በደንብ እንደሚያውቁ ማንጸባረቃቸውና በጽሑፍ መጠይቁ ደግሞ (አባሪ አንድን ይመለከታል) ለጥያቄ ቁጥር 26፣ 56ና 57 አብዛኛዎቹ መላሾች የሰጡት ምላሽ በተተኳሪ የቡድን ውይይቶቹ ከተገኘው መረጃ የሚቃረን ሆኖ መገኘቱ ነው። እነዚህ ሁለት የተቃረኑ ሀሳቦች ሲመረመሩም ምክንያቱ የጽሑፍ መጠይቁ ጥያቄዎች አጠያየቅ የፈጠረው ችግር መሆኑን ማስተዋል ተችሏል። በሌላ አገላለጽ በመምህራኑ ስለፈተናው ማወቅና የፈተናውን ዓላማና ፖሊሲ ማወቅ አንድነት የላቸውም ተብሎ እንደሚታመን ማረጋገጥ ተችሏል። ይህም ጥያቄዎቹ ሲዘጋጁ የተዛማጅ ፅሑፎች ላይ በተገኙ ሐሳቦችና ልምዶች ላይ ብቻ በመተኮሩ የተፈጠረ ችግር ነበር። በአንዳንድ አገሮች እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች የሚጠየቁት የፈተና መርሐ ትምህርቶች /ልየታዎች/ Test syllabus/ Test specifications/ በምስጢር ስለማይያዙና ትምህርት ቤቶቹ እንዲያውቋቸው ስለሚደረግና በውስጣቸውም የፈተናዎቹ ዓላማዎችና ፖሊሲዎች ስለሚካተቱባቸው (ፍንጭ የሚሰጡ ክፍሎች ስለሚኖራቸው) ነው (Alderson እና ሌሎች 1995)። በኢትዮጵያ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ግን ከዚህ የተለየ ነው፤ እነዚህ ሰነዶች የሚያዙት

በምስጢር ነው፤ መምህራኑ እንዲያውቋቸው አይደረግም፡፡ በዚህ ሁኔታ እንዲህ ያሉ በጽሑፍ መጠይቁና ከመምህራኑ ጋር በተካሄዱት ውይይቶች የተገኙ ጠቃሚ ሀሳቦችን/ ትምህርቶችን በማገናዘብ የመምህራኑ መጠይቅና የተተኳሪ ቡድን ውይይት መመሪያው እንዲሻሻሉ ተደርገዋል፡፡

3.5.2.2 የሙከራ ጥናት ሁለት

የዚህ ሙከራ ጥናት መሰረታዊ ዓላማ በባለሙያዎቹ አስተያየት መሰረት ተሻሽለው ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተዘጋጁትን መሣሪያዎች የላህይና የይዘት አግባብነት (Face & Content Validity) እንደገና ከጥናቱ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ዐውድ ለመሞከር፣ አስተማማኝነታቸውን (Reliability) ለመፈተሽና ዋናውን ጥናት ለማካሄድ የሚያስችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡

የሙከራ ጥናቱ የተካሄደውም ዋናው ጥናት ከሚካሄድባቸው ዞኖች ውጭ በሆነው በደቡብ ጐንደር መስተዳድር ሲሆን ሙከራው የተካሄደውም ከጥቅምት 25 እስከ ታኅሳስ የመጀመሪያ ሳምንት 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ በዚህ ዞን ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሏቸው 12 ወረዳዎች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ወረዳዎች መካከል የጽሑፍ መጠይቅ የሚሞሉ የአማርኛ መምህራን ለመምረጥ ሰባት ወረዳዎች (እብናት፣ ደራ፣ ሊቦ ከምከም፣ ፎገራ፣ ምዕራብ እስቴ፣ ፋርጣና ደብረታቦር) ተመርጠዋል፡፡ በእነዚህ ወረዳዎች ውስጥ 12 አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ መምህራን የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ 55 የጽሑፍ መጠይቆች ተበትነው 45ቱ በሦስት ሳምንት ውስጥ በትክክል ተሞልተው ተመልሰዋል፡፡ ከመምህራኑ መጠይቅ በተጨማሪ የተማሪዎች መጠይቅ፣ ከመምህራንና ከዞን የትምህርት ባለሙያዎች ጋር ለሚካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተዘጋጁት መምሪያዎች (Guidelines) እና ከክፍል ምልከታ በኋላ ከመምህራኑ ጋር የሚካሄደው ቃለመጠይቅ ጥያቄዎች፣ ለርዕሳነ /ምክትል ርዕሳነ መምህራን የተዘጋጀው ቃለ መጠይቅ፣ የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት መገለጫ ንድፍ/ ቅጽ እንዲሁ ለዋናው የሙከራ ጥናት በተመረጠው በዚሁ በደቡብ ጎንደር ዞን በዕድል ሰጭ የንምና ዘዴ በተመረጡት ወረዳዎች አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ

ትምህርት ቤቶች እንዲሞክሩ ተደርገዋል። የማጠናቀቂያ ፈተናውን ጥያቄዎች ከቋንቋው ትምህርት ዓላማዎች ጋር ለማዛመድ የተዘጋጀው (የቋንቋውን ትምህርት ዓላማዎች ዝርዝር የያዘው) ቅጽ ደግሞ በዋናው ጥናት ያልተካተተውን እ.ኢ.አ በ1999 ዓ.ም. የተሰጠውን የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተናን አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው፡ አራት የጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራን እንዲሞከር ተደርጎ ለዋናው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በተለይ የመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ በዕድል ሰጭ ንምና ዘዴ በተመረጡት ወረዳዎች ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሞላ ከተደረገ በኋላ በሊከርት ስኬል መሰረት የተዘጋጁት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች (ከጥያቄ 1- 55 ያሉት) የአስተማማኝነት ደረጃ (Internal Consistency) በክሮቫሽ አልፋ (Cronhaoh's alpha) ስታትስቲክስ እንዲረጋገጥ ተደርጓል (አባሪ 16 ይመለከቷል)። በዚሁ ስሌት መሰረትም የመጀመሪያው ክፍል 29 ጥያቄዎች፣ የአስተማማኝነት ደረጃ (Reliiablity cofficant) /የጥገኛ ተላውጦው ማለት ነው) 0.814 ሲሆን የሁለተኛው ክፍል/ መምህራኑ ላዳበሩት ግንዛቤ ምክንያት ናቸው የተባሉት ተላውጦዎች (ከጥያቄ ቁጥር 30-55 ያሉት) የአስተማማኝነት ደረጃ 0.765 ሆኖ ተገኝቷል። በHinton እና ሌሎች (2004) ስታትስቲክስ አተረጓጎም ደግሞ 0.75 እና በላይ የሆነ ውጤት ተቀባይነት ያለው የአስተማማኝነት ደረጃ ነው፡ : ሌሎቹ የመጠይቁ ክፍሎች በሊከርት ስኬል መሠረት የተዘጋጁ ስላልሆኑ ክሮቫሽ አልፋን መጠቀም አልተቻለም፡፡

ስለዚህ ሌሎቹ የጽሑፍ መጠይቁ ክፍሎች፣ የተማሪዎች መጠይቅ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይቶች መምሪያዎቹ፣ ቃለመጠይቆቹና የማመሳከሪያ ቅፆቹን አስተማማኝነት ለመመርመር የተሞከረው መሣሪያዎቹን የተለያዩ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ እንዲገመግሟቸውና በግምገማዎቹ መሰረት እየተከለሱ እንዲዘጋጁና በመጨረሻም በመስክ እንዲሞከሩ በማድረግ ነው፡፡ መርሐ ትምህረቶቹና ሌሎች ሰነዶች ግን የሚሻሻሉ ነገሮች ስላልሆኑ በባለሙያዎቹ አልተገመገሙም፡፡

ከሙከራ ጥናት ሁለት የተገኘ ትምህርት

እንደ ሙከራ ጥናት አንድ ሁሉ ከሙከራ ሁለትም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹን፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱንና የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችን በሚመለከት ጠቃሚ ትምህርቶች ተገኝተዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በፈተናው ጥያቄዎችና በመርሐ ትምህርቶቹ ዓላማዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ ለማጥናት Green (2007) እንዳደረጉት በቃለ መጠይቅና በመጠይቅ ብቻ ለማረጋገጥ ከመሞከር በAlderson እና ሌሎች (1995) Weir እና ሌሎች (1990) ሥራ በተገለጸው መሠረት የባለሙያዎችን (expert judgment) መጠቀሙ ጥናቱን የተሻለ ሊያደርገው እንደሚችል ለመረዳት ተችሏል። በዚሁ መሰረት በዋናው ጥናት አራት የጎንደር መምህራን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እ.ኢ.አ. ከ2000-2004 ዓ.ም የተዘጋጁ ጥያቄችን ከትምህርቱ ጋር እንዲያዛምዱ ተደርጓል። ተጨማሪ መረጃም በተተኳሪ የቡድን ውይይቶችና በመጠይቆች እንዲሰበሰብ ተደርጓል። የፈተናዎቹ ጥያቄዎች ከአዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ደግሞ በዋናው ጥናት አራት የሥነ-ትምህርት ባለሙያዎች ጥያቄዎቹን ከስድስቱ ባህርያዊ የትምህርት ዓላማዎች ጋር እንዲያዛምዱ በማድረግ ለማጥናት ተችሏል።
2. በመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ ከተካተቱት ጥያቄዎች መካከል ደግሞ አንድ ግልፅ ያልሆነና ሁለት አሻሚነት ያላቸው ጥያቄዎች ተገኝተዋል። ቁጥራቸውም የበዛ መስሎ ታይቷል። ስለዚህ አሻሚ የሆኑት ግልጽ እንዲሆኑ ተደርገው፣ አምስት ጥያቄዎች (ከክፍል አንድ ጥያቄ ቁጥር 2፣19 እና 39፤ ከክፍል ሁለት ጥያቄ ቁጥር 5 እና 10) ተቀንሰው አንድ ጥያቄ (ጥያቄ ቁጥር 22) እንዲሁም የአጥኝው የስልክ አድራሻ ተጨምሮበትና የተወሰኑ ጥያቆችን በማሻሻል ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት እንዲያገለግል ተደርጓል።
3. የተማሪዎች መጠይቅ ጥያቄዎቹ በዝተውና ብዙዎቹ ረጃጅም ሆነው በመገኘታቸው በዋናው ጥናት 21 ጥያቄዎች እንዲቀነሱ፣ ረጃጅሞቹና ግልጽነት የሚጎድላቸው (ለምሳሌ ትዕዛዞቹና ጥያቄ ቁጥር 3፣ 4፣ 5 ፣7፣ 11፣ 12) ተሻሽለው እንዲዘጋጁ ተደርገዋል። ሁለት ጥያቄዎች ደግሞ (ክፍል ሁለት 11.1.2 እና 11.1.4) ተጨምረዋል።
4. ለክፍል ምልከታ ማካሄጃነት የተዘጋጀው ንድፍ/ ቅፅ በሌሎች ሀገሮች በወሸባክ ላይ ጥናት ለማካሄድ የተጠቀሙባቸውን የተግባቦታዊ ቋንቋ ማስተማሪያ ምልከታ ንድፍ እንዳለ ከመጠቀም ለሙከራ ጥናት አጥኝው መጠነኛ ለውጥ አድርጎ የተጠቀመበት ንድፍ/ ቅጽ ለጥናቱ ዐውድ የሚያመች ሆኖ ተገኝቷል። በዚህ ንድፍ/ ቅጽና በቅጹ

መሰረት ከተካሄዱት ምልከታዎች በኋላ ከመምህራኑ ጋር የተካሄዱት ቃለ መጠይቆችም ጥናቱ በተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች የማጠናቀቂያ ፈተናው ጠንካራ የሚባልና በአብዛኛው አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ እያሳደረ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ በዋናው ጥናት በይዘት ምድብ ስር ፈተና የሚል አንድ ክፍል፣ በመጨመር ለሙከራ ያገለገለውን የምልከታ ንድፍ በመጠቀም ሳፋ ባለዐውድ፣ ከሁለት ወር በላይ የሚሆን ጊዜ በመጠቀም በሙከራ ጥናቱ የተገኘውን ውጤት አካባቢያዊነት ወይም ክልላዊነት ለመለየት የሚያስችል በዋናው ጥናት በክፍል ምልከታ ሰፋ ያለ መረጃ እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡ በሙከራ ጥናቱ የክፍል ምልከታውም ከምልከታ ቅፁ በተጨማሪ በመስክ ማስታወሻና በቪዲዮ መቀረፁ የተሰበሰበውን መረጃ መላልሶ ለማመሳከር ጠቃሚ ሆኖ በመገኘቱ ሁለቱም በዋናው ጥናትም እንዲያገለግሉ ተደርገዋል፡፡

5. ከመምህራን ከዞን የትምህርት ኃላፊዎች ጋር ለሚካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተዘጋጁት ጥያቄዎች ጠቃሚ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ሆነው በመገኘታቸው የጎላ ለውጥ ሳይደረግባቸው በዋናው ጥናት እንዲያገለግሉ ተደርገዋል፡፡
6. ከክፍል ምልከታ በኋላ የክፍል ምልከታ ከተካሄደባቸው መምህራን ጋር ለመወያየት የGreen (2007) ጥያቄዎችን ብቻ ከመጠቀም በየዕለቱ ከቀረበው ትምህርት የሚመነጩ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ማንሳት የተሻለ መረጃ ሊያስገኝ እንደሚችል የሙከራ ጥናቱ ውጤት በማመልከቱ በዋናው ጥናት ከየዕለቱ ትምህርት ጋር የተያያዙ ጥያቄችን በመጠየቅ ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብሰበዋል፡፡
7. ለዓይነታዊም ሆነ ለመጠናዊ መረጃዎች መተንተኛነት የተመረጡት ዘዴዎች የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን ተገቢና አመቺ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ስለዚህ በዋናው ጥናት ዓይነታዊ የሆኑትን በጭብጥ፣ በጭብጥ፣ መጠናዊ የሆኑትን በገላጭ (መቶኛ፣ አማካይና፣ መደበኛ ልይይት) እና በድምዳሜያዊ (በተዛምዶና በህብረ ድህረት) ስታቲስቲክስ መተንተንና ከትንተናው በመነሳትም ተገቢ ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

3.6. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት (Data Collection Procedures)

ከተለያዩ ምንጮች መረጃ ለመሰብሰብ ከመሞከሩ በፊት መጀመሪያ በጥናቱ የተካተቱት ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን በዩንቨርሲቲው የተጻፈን የትብብር

ደብዳቤ በማሳየትና የጥናቱን ዓላማ በማስረዳት ፈቃደኝነታቸው ተጠይቋል። እንዳጋጣሚ የሁሉም ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን በትምህርት ቤቶቻቸው ጥናቱ እንዲካሄድ ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸውና ከአማርኛ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎች ጋር በማስተዋወቅ ለአጥኝው አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግለት በማሳሰባቸው፤ አንዳንዶቹም የጽሑፍ መጠይቆቹን ራሳቸው ርዕሰ/ ምክትል ርዕሳነ መምህራኑ፣ መምህራኑን በማስሞላታቸው፣ በታቀደው መሰረት በጥናቱ በታቀፉት ትምህርት ቤቶች ሁሉ በአብዛኛው የታሰበውን መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል።

የመረጃ ስብሰባ ሂደቱ የተጀመረውም በክፍል ምልከታ ነው። የክፍል ምልከታው የተካሄደውም ለሙከራ ጥናቱ ከጥቅምት 25 እስከ ህዳር 30 ቀን 2005 ዓ.ም.ሲሆን ለዋናው ጥናት ደግሞ ከመጋቢት 24 እስከ ሰኔ 5 ቀን 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። በምልከታውም መረጃዎቹ ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት መገለጫ ንድፍ"ሀ" (COLT_ Communctive Orientation Language Teaching Obsrvation Scheme A) በመጠቀም፣ በመስክ ማስታወሻና (field notes) እንዲሁም አብዛኞቹ በቪዲዮ እየተቀረጹ ጭምር ተሰብስበዋል።

ዋናውን ጥናት ለማካሄድም አንደኛ፣ ከፋሲለደስ፣ ዘጠነኛ ክፍል ከሚያስተምሩ የቋንቋው መምህራን አንድ ወንድና አንድ ሴት፣ 10ኛ ክፍል ከሚያስተምሩ እንዲሁ አንድ ወንድና አንድ ሴት፣ ሁለተኛ፣ ከአዘዞ መነሻው ላይ እንዲሁ ሁለት ወንድና ሁለት ሴት፣ መምህራን ለምልከታው ፈቃደኛ ሆነው ተገኝተው ነበር። ሆኖም ከአዘዞ አንዲ ምልከታው ከተጀመረ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሀሳባቸውን በመቀየራቸው በእሳቸው ላይ የተጀመረው የክፍል ምልከታ ተቋርጧል። ሦስተኛ በህዳሴ ጠዳ የሚያስተምሩት መምህራን ሁሉም ፈቃደኛ በመሆናቸውና ቁጥራቸውም አነስተኛ /ሦስት ብቻ በመሆኑ ሦስቱም በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጎ ሲያስተምሩ የክፍል ምልከታዎችን በታቀደው መሰረት ለማካሄድ ተችሏል። ቀደም ብሎ እንደተወሳው በቦታ መራራቅ /በአካባቢ መለያየት የሚታይ የማጠናቀቂያ ፈተናው የሚፈጥረው የተጽዕኖ ልዩነት ይኖር እንደሆነ ለማረጋገጥ ደግሞ በሌሎች በጥናቱ በተካተቱት ሁለት የዞን ከተማ አስተዳሮች ስር በሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ ሰባት መምህራን ሲያስተምሩ የተወሰኑ ክፍለ ጊዜያት ትምህርቶች ላይ ተጨማሪ የክፍል ምልከታዎች

ተካሂደዋል፡፡ ተጨማሪ ምልከታዎች የተካሄዱትም አንደኛ፣ ከባህር ዳር ከከተማ በፋሲሎ ከገጠር በመሸንቲ፣ ሁለተኛ፣ ከደሴ ከከተማ በሆጤ፣ ከከፊል ከተማ በቅዳሜ ገበያ፣ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነው፡፡ የእነዚህ ትምህርት ቤቶች ጎላፊዎችና የአማርኛ መምህራን ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው ፈቀደኝነትን፣ ጸታንና የሚያስተምሩበትን የክፍል ደረጃ መሰረት በማድረግ የተመረጡ ሰባት መምህራን ሲያስተምሩ የክፍል ምልከታዎችን ለማካሄድ ተችሏል፡፡ በእርግጥ እንደ አዘዞዋ ሁሉ ፋሲሎ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩት መምህራን መካከል አንድ የአስረኛና አንድ የዘጠነኛ ክፍል መምህራን መጀመሪያ ላይ ፈቃደኛ ሆነው ቢገኙም የዘጠነኛ ክፍል መምህሯ የመጀመሪያው ምልከታ ከተካሄደ በኋላ የተለያዩ ሰበቦችን እያነሱ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በማንጸባረቃቸው ምልከታው በአንድ መምህር ላይ ብቻ እንዲካሄድ ስለተደረገ እንጅ ለምልከታው ተመርጠው የነበሩት ስምንት መምህራን ነበሩ፡፡ መሸንቲ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ የሚያስተምሩት የአማርኛ መምህራን ሁለት ብቻ ስለሆኑና ሁለቱም ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው በዚህ ትምህርት ቤት በዕቅዱ መሰረት እነዚህ መምህራን ሲያስተምሩ ለሁለት ሳምንታት ያህል የክፍል ትምህርት ምልከታ ለማካሄድ ተችሏል፡፡ በደሴም ምንም እንኳን የ10ኛ ክፍል ትምህርት ከተጠናቀቀ፣ የዘጠነኛ ክፍል መምህራንም ቢሆኑ የሲሚስተሩን ትምህርት እያጠናቀቁ የነበረበት ወቅት ቢሆንም ሁሉም መምህራን ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው በጥዋቱ ፈረቃ ቅዳሜ ገበያ፣ ከሰዓት ሆጤ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ከየትምህርት ቤቱ አንድ ወንድና አንድ ሴት መምህራን ሲያስተምሩ የክፍል ምልከታ ለማካሄድ ተችሏል፡ በሀዳሴ ጠዳና በመሸንቲ የሚያስተምሩት ሁሉም መምህራን ሴቶች በመሆናቸው ምልከታው ወንድ መምህራንን አላሳተፈም፡፡

ሁለተኛ፣ ከግንቦት አንድ እስከ ግንቦት 20/ 2005 ዓ.ም በዕጣ የተመረጡ ክፍሎች/ ሴክሽኖች የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ሦስተኛ፣ ከግንቦት 25/2005 - ሰኔ 8/2005 ደግሞ በጥናቱ የተካተቱት ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ አራተኛ፣ ከሰኔ 1/2005- ሰኔ15 /2005 ዓ.ም ከአምስት አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን ጋር ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ ስድስተኛ፣

ከርዕሳነ/ ምክትል ርዕሳነ መምህራን፣ ከዞን ትምህርት መምሪያዎችና ከዞን ከተማ አስተዳደሮች ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች የሥርዓተ ትምህርት፣ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተና ዝግጅት ኃላፊዎች ጋር ደግሞ ከግንቦት 15 ቀን 2005 እስከ መስከረም 10 ቀን 2006 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ቃለ መጠይቆችና ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል። ሰባተኛ፣ ከግንቦት መጀመሪያ እስከ ሰኔ 25/2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ በትምህርት ቤት፣ በዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶችና በዞን ትምህርት መምሪያዎች የተዘጋጁ የ2004 እና የ2005 ዓ.ም.(እ.ኤ.አ.) የ፩ና የ፪ኛ መንፈቀ ዓመት ፈተናዎች ተሰብስበዋል።

3.7 የመረጃ ትንተና ሂደቶች (Data Analysis Procedures)

የምርምሩ ንድፍ ዓይነት በሚለው ክፍል እንደተወሳው ከላይ በተዘረዘሩት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መረጃዎች ከተሰበሰቡና ከተደራጁ በኋላ በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች፣ በቃለ መጠይቆችና ከፖሊሲ ሰነዶች ምርመራ የተሰበሰቡ መረጃዎች በዓይነታዊ የመረጃ አተናተን ስልት መሰረት በሚያሳዩት ተመሳስሎና ልዩነት በክፍል በክፍል እየተመደቡ ተተንትነዋል። እነዚህን ዓይነታዊ መረጃዎች ለመተንተንና ለመተርጎምም በTaylor እና Bogdan (1998) ስራ የቀረቡት (በተለይም ደጋግሞ ማንበብ(Read & Reread)፣ ጠቃሚ ሀሳቦችን መመዝገብ (Recod more important idea)፣ በመረጃዎች ውስጥ ለሚከሰቱ ጭብጦች/ ሥርዓቶች (Emerging themes /Patterns) ትኩረት መስጠት፣ ለጭብጦቹ የተለያዩ ምድቦችን መመስረት/ ማዋቀር (Constrct Typologies)፣ ተዛማጅ ጽሑፎችን ማንበብ፣ የትንተና ሚሞ መጻፍ፣ መረጃዎችን ኮድ ማድረግና መተርጎም የሚሉትን ሂደቶች ለመከተል ተሞክሯል። ከእነዚህ የዓይነታዊ የመረጃ አተናተንና አተረጓጎም ስልቶች በተጨማሪ ደግሞ በተለይ በቡድን ተኮር ውይይቶች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተንና ለመተርጎም በKrueger (1994 እና 2002) ስራዎች ስለ በቡድን ተኮር ውይይት የሚሰበሰብ መረጃ አተናተንና አተረጓጎም የተገለጹት ሀሳቦች መሰረት ተደርገዋል። እንዲሁም በከፊል የተዋቀሩ ቃለ መጠይቆች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተንና ለመተርጎም በSchmidt (2004) በከፊል በተደራጁ ቃለመጠይቆች የተሰበሰቡ መረጃች ትንተና (“The Analysis of Semi-Structured Interviews.”)

በሚለው ስራ ውስጥ የተካተቱ የአተናተንና የአተረጓጎም ደረጃዎችን (Stages) ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ/ ዐውድ ጋር በማዛመድ ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡

ከተለያዩ ወገኖች በተተኳሪ ቡድን ውይይቶችና በቃለ መጠይቆች በቴፕ ካሴት ተቀርፀው የተሰበሰቡት ሙሉ መረጃዎች (ጥያቄና መልሶች) ከማጠናቀቂያና ከክፍል ፈተናዎች ጋር በጥራዝ ሁለት ቀርበዋል፡፡

መጠናዊ የሆኑትን መረጃዎች በሚመለከት ደግሞ አንደኛ፣ በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጥያቄዎችና በአዕምሯዊ ትምህርት ባሕርያዊ ዓላማዎች እንዲሁም በፈተናዎቹ ጥያቄዎችና በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርቶች ዓላማዎችና ይዘቶች መካከል ያለውን ተጣጥሞሽ ለመፈተሽ የተሞከረው የባለሙያዎችን ዳኝነት (experts judgment) በመጠቀም ነው፡፡ በቀዳሚው ምዕራፍ እንደቀረበው የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች የሚባሉት ዕውቀት(knowledge)፣ ግንዛቤ፣ ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ በመባል የሚጠሩት የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃዎች ናቸው፡፡ በ3.3 በተገለጸው መሰረት በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና በስድስቱ የአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች መካከል ያለውን ዝምድና ለመፈተሽም የሦስት ተከታታይ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናው 270 (90*3) ጥያቄዎች በአራት የሥነ-ትምህርት ባለሙያዎች በእነዚህ ስድስት ክፍሎች እንዲመደቡ ተደርገዋል፡፡ ባለሙያዎቹ ሁለቱ በትምህርታዊ ሥነ-ሥነ-ልቦና (Educational Psychology) ሁለቱ በሥርዓተ ትምህርትና ማስተማር ፪ኛ ዲግሪ ያላቸው የኮሌጅ መምህራን ናቸው፡፡ የአንዱ የመጀመሪያ ዲግሪ አማርኛ ነው፡፡ ከእነዚህ ባለሙያዎች ጋር በግንቦት ወር መጀመሪያ ላይ አሰራሩን በተመለከተ በአጥኝው በቀረቡት አማራጭ ሀሳቦች ላይ ውይይት አካሂደዋል፡፡ በውይይቱ በተፈጠረው ስምምነት መሰረትም መጀመሪያ የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ጥያቄዎች ከስድስቱ ዓላማዎች ጋር በግላቸው አዛምደዋል፡፡ በመቀጠልም /ከወር በኋላ ሰኔ ወር ላይ 2005 ዓ.ም በጋራ በመገናኘት ከ4፡00 — 6፡30 ባለው ሰዓት በልዩነቶቻቸው ላይ በመወያየት ሁሉንም ጥያቄዎች እየተስማሙ በስድስቱ ክፍሎች መመደብ ችለዋል፡፡ አጥኝው ደግሞ በአወያይነት ተሳትፏል፡፡ የምደባው ውጤትም በምዕራፍ አራት በሰንጠረዥ 4.3 ቀርቧል፡፡

በቋንቋው መርሐ ትምህርቶቹ ዓላማዎችና በማጠናቀቂያ ፈተናዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጥናት ደግሞ አራት ቋንቋውን በጎንደር መምህራን ኮሌጅ የሚያስተምሩ መምህራን ከ2000-2004 ዓ.ም እ.ኢ.አ.) የተዘጋጁትን የአምስት ተከታታይ ዓመታት

የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎችን የማመሳከሪያ ቅጹን በመጠቀም ከትምህርቱ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ጋር እንዲያዛምዱ ተደርጓል፡፡ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎችን ከትምህርቱ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ጋር እንዲያዛምዱ የተመረጡት እነዚህ ባለሙያዎች ከ10-15 ዓመት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህርነት እንዲሁም ከ5-10 ዓመት በኮሌጅ መምህርነት (የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ መምህራን አሰልጣኝነት) ያገለገሉና አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ናቸው፡፡ በመነሻ ላይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማስተማር ልምዳቸውን፣ ያጠኑት ትምህርት ለጉዳዩ ያለውን ቅርበትና ፈቃደኝነታቸውን መሠረት በማድረግ አራት ባለሙያዎች ተመርጠው የነበረ ቢሆንም አንደኛዋ የጋራ ውይይት በሚካሄድበት ሰሞን ለመገኘት የማያስችላቸው ችግር ስላጋጠመቸው ትንተናው ሦስቱ ባለሙያዎች (ሁለት ወንድና አንድ ሴት) ባካሄዱት ምደባ ላይ ብቻ እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡ ሂደቱም በሙከራ ጥናቱ እንደተደረገው መጀመሪያ ለሁለት ሳምንታት ያህል የፈናዎችን ጥያቄዎች ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር በግላቸው አዛምደዋል፡፡ አዛምደው ካጠናቀቁና ሁሉም ባለሙያዎች ያካሄዱት ምደባ ከተሰበሰበና በመካከላቸው የታዩት ልዩነቶች ከተለዩ በኋላ ደግሞ በመስከረም ወር 2006 ዓ.ም በሁለተኛው ሳምንት መጨረሻ ላይ በጋራ በመገናኘት በAlderson እና ሌሎች (1995) እና በWeir እና ሌሎች (1990) በተመለከተው የጥያቄ-ክሂል አመዳደብ ስልት መሰረት ጥያቄዎቹን በግል ሲያዛምዱ በተለያዩባቸው ክፍሎች ላይ ተወያይተዋል፡፡ ውይይቱ ግማሽ ቀን የወሰደ ሲሆን በዚህ ግማሽ ቀን (ከ3፡00- 7፡00 ሰዓት) በወሰደው ውይይትም ሁሉንም ጥያቄዎች እየተስማሙ መመደብ ችለዋል፡፡

የማጠናቀቂያ ፈተናው ጥያቄች ከአዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች ጋርም ሆነ ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር ያላቸው ዝምድና የምደባ ውጤትም በሚወክሉት የትምህርት ዓላማ ክፍል በሰንጠረዦች ተደራጅተውና ተጠቃለው በቁጥርና በመቶኛ ተገልጸዋል፡፡ እንደቀዳሚዎቹ ሁሉ በ2004 እና በ2005 ዓ.ም.(እ.ኢ.አ.) የተዘጋጁት የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የ፩ኛና የ፪ኛ መንፈቀ ዓመት በጥናቱ የተካተቱት ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ፈተናዎች ጥያቄዎችም እንዲሁ ከመርሐ ትምህርቶቹና

ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጥያቄዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በሚወክሉት የትምህርት ዓላማ ክፍል በሰንጠረዥ ተደራጅተውና ተጠቃለው በቁጥርና በመቶኛ ተተንትነዋል፡፡ ከዚያም በመርሐ ትምህርቶቹና በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ፣ በመርሐ ትምህርቶቹና በክፍል ፈተናዎቹ፣ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና በክፍል ፈተናዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት እየተነጻጻረ ተተንትኖና ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

ሁለተኛ፣ የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት መገለጫ ንድፍን /ቅጽን በመጠቀም በክፍል ምልከታ የተሰበሰበው መረጃ ደግሞ እንዲሁ በሰንጠረገሮች ተደራጅቶና ተጨምቆ/ ተጠቃልሶና በአማካይ (Mean) ተተንትኗል፡፡ አማካዩም በማስተማር-መማር ሂደቱ የትምህርቱ ጊዜ ከመምህራኑና ከተማሪዎቹ ይበልጥ በማን እንደሚያዝ፣ ለየትኛዎቹ የትምህርቱ ተግባራት፣ ይዘቶች፣ የማስተማሪያ ዘዴች የተሻለ ትኩረት እንደሚሰጥና ከፈተና ጋር የተያያዙ ተግባራትን ለማከናወን ምን ያህል ጊዜ እንደሚሰጥ አመልክተዋል፡፡

ሦስተኛ፣ በመጠይቆቹ የተሰበሰበው መረጃ ደግሞ ከተጣራና ኮድ ከተደረገ በኋላ “SPSS 16” የሚባለውን የመረጃ መተንተኛ ፕሮግራም በመጠቀም በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡ ይኸውም መጀመሪያ የተሰሰበሰበው መረጃ ወደዚህ SPSS 16” ፕሮግራም ገብቶ እንዲደራጅና እንዲጠቃለል ተደርጎ በገላጭ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡ ከዚያም የትንተና ውጤቱን አማካይ በመጠቀም አንደኛ በተማሪዎች መጠይቅ፣ ተማሪዎች የማጠናቀቂያ ፈተናው በመማር-ማስተማር ሂደቱ ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ያላቸውን ግንዛቤ ለመለየት/ ለማጥናት ተችሏል፡፡

ሁለተኛውና ብዙ ጥያቄዎች የተመለሱበት በመምህራን እንዲሞላ የተዘጋጀው የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ በዚህ የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የመጀመሪያውን የግንዛቤ ጥያቄ (3.1ን ማለት ነው) ለመመለስ የሚያስችል መረጃ የተሰበሰበው በመጠይቁ የመጀመሪያ ክፍል በተካተቱ 27(1-27) ጥያቄዎች Items) ነው፡፡ ሁለተኛውን የምርምር ጥያቄ (3.2) ደግሞ ከ28-52 ባሉት ጥያቄዎች መሰረትነት በመመርመር፣ የወሸባክ መከሰቻ ምክንያቶችን በኢትዮጵያ በተለይም በአማራ ክልል ዐውድ መነሻነት ለማጥናት ተችሏል፡ እነዚህ በመምህራን መጠይቅ የተካተቱ ጥያቄዎች በሊከርት የስምምነት መለኪያ ስኬል መሰረት የቀረቡ ስለሆኑ የምርምር ጥያቄ 3.1 ን እና 3.2 ን

ለመመለስ በእነዚህ 52 ጥያቄዎች የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን የተመረጠው ዘዴ ገላጭ ስታትስቲክስ ነው። ከገላጭ ስታትስቲክስ ደግሞ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሚሰጡት ምላሽ አማካይ (mean) ዋነኛ የመተንተኛ ስልት እንዲሆን ተደርጓል። ለየጥያቄው የተሰጠውን መልስ ከግማሽ በላይ (በታች) ወይም አብዛኛዎቹ፣ ይህን ያህል በመቶ የሚሆኑት እያሉ ከመግለጽ የሚሻል ሌላ አማራጭ/ ስልት ይገኝ እንደሆነ ለማረጋገጥ የጎንደር ዩንቨርስቲ የስታትስቲክስ ክፍል መምህራንን ሀሳብ ለመጠየቅ (ለማማከር) ተሞክሯል። በተደረገው ሙከራም የተሻለ አማራጭ ተደርጎ የተገለጸው አማካይ መጠቀምና አማካዩን በአራት ደረጃ ከፍሎ የተፅኖውን ደረጃ ለማሳየት መሞከር ነው። ቆይቶም በእነዚህ የስታትስቲክስ ባለሙያች የተገለጸው ዘዴ በሌሎች ሀገሮችም እየተሰራበት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል። ለምሳሌ በጆርዳን የውታሃ ዩንቨርሲቲ የሚሰሩ Al-Jamal, እና Ghdy የሚባሉ ምሁራን በ(2008) አል-ካርክ በሚባል ግዛት የወሽባክ ጥናት ለማካሄድ በመጠይቅ የሰበሰቡትን መረጃ የተነተኑትና ያብራሩት ስምንት የስታትስቲክስ ባለሙያዎችን (experts) አማክረው ያሳዩአቸውን ከላይ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይነት ያለውን የሚከተለውን የመረጃ መተንተኛና የጥንካሬ ደረጃ ማመልከቻ ዘዴ በመጠቀም ነው። ይህ ዘዴ አጥኚው በ2005 ዓ.ም በካሄደው የሙከራ ጥናትም ተፈትሾ ጠቃሚ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህ ዘዴ መሰረት አራቱ የመረጃ ትንተና ውጤቶችና የውጤት ደረጃ ማሳያ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ከ1 — 1.49 ያለ አማካይ ውጤት፣ የማይለካ (Immeasurable)
2. 1.5 — 2.49 ደካማ //ዝቅተኛ ውጤትን የሚያሳይ አማካይ (as having little effect)
3. 2.5 — 3.49 መካከለኛ ውጤትን የሚያሳይ አማካይ (as having moderate effect)
4. 3.5 — 5 ጠንካራ ውጤትን የሚያሳይ አማካይ (as having strong effect)

ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው በዚህ ጥናት የ3.1 እና የ3.2ን የምርምር ጥያቄዎች እንዲሁም በተማሪው መጠይቅ በተራ ቁጥር 12፣ 13፣ 14 እና 15 የቀረቡትን

በተመለከተ የእያንዳንዱን ጥያቄ አማካይ ውጤትና የአማካዩን ደረጃ በዚህ መንገድ በሰንጠረዥ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡፡

ከዚያም በጥገኛ ተላውጦውና በነጻ ተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመግለጽ (Explain) እና ለመተንበይ (Predict) የተዛምዶ (Correlation) እና የጎብረ-ድጎረት (Multiple Regrations) ትንተናዎች ተካሂደዋል፡፡ የተዛምዶ ትንተናው ያገለገለው በጥገኛ ተላውጦውና በነጻ ተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመግለጽ ሲሆን፣ የጎብረ-ድጎረት ትንተናዎቹ ያገለገሉት ደግሞ የጥናቱን 3.5 እና 3.6 መላምቶች/ ጥያቄዎች ለመመለስ ነው፡፡ በመሆኑም፣ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ተዋረዳዊና (Hierarchical) መደበኛ (Simultaneous) የሚባሉት የጎብረ-ድጎረት መረጃ መተንተኛ ስልቶችን በመጠቀም መረጃዎቹ እንዲተነተኑና እንዲተረጎሙ ተደርገዋል፡፡

ምዕራፍ አራት፤ የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

4.1 መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ቅደም ተከተል መሰረት የተካሄደው የውጤት ትንተናና ማብራሪያ የሚቀርብበት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በክፍል አንድ ከፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ጋር በተካሄዱ ቃለመጠይቆች፣ በአጠቃላይ በኤጀንሲው የሚዘጋጁ ሀገር አቀፍ ፈተናዎችና በተለይ ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናን፣ ታላሚ ተፈታኞችን የመመዘን ደረጃና አዎንታዊ ወሽባክ ከፍ ለማድረግ ስለሚጠቀሙባቸው ስትራቴጂዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ይቀርባል፡፡ ክፍል ሁለት በአዕምሯዊ ምድብ የትምህት ዓላማዎችና በማጠናቀቂያ ፈተናውና በቋንቋው መርሐ ትምህርቶች ዓላማዎችና በማጠናቀቂያ ፈተናው፣ በቋንቋ መርሐ ትምህርቶች ዓላማዎችና በክፍል ፈተናዎች እንዲሁም በክፍል ፈተናዎችና በማጠናቀቂያ ፈተናው መካከል ያሉትን ተዛምዶዎች በተመለከተ ከሰነዶችና ከተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተገኙ መረጃዎች ውጤት ትንተናና ማብራሪያ የሚቀርብበት ነው፡፡

ክፍል ሦስት ደግሞ በጥናቱ ሦስተኛ ጥያቄ ስር የተካተቱት ንዑሳን ጥያቄዎች መሰረት፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ (ከስድስት የትምህርት ምድቦች ላይ በማተኮር) የሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ የቋንቋው መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ በጽሑፍ መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች ውጤት ትንተናና ማብራሪያ የሚቀርብበት ነው፡፡ ከዚያም ተማሪዎች የማጠናቀቂያ ፈተናው በመማር-ማስተማር ሂደቶች ላይ እያሳደረ ስላለው ተፅዕኖ ያላቸውን ግንዛቤ በሚመለከት ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ውጤት ትንተና ይከተላል፡፡

በመቀጠልም የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ እያሳደረ ያለውን ተፅዕኖ በተመለከተ በጽሑፍ መጠየቅ፣ በተደራጀ የክፍል ምልከታና ከክፍል ምልከታ በኋላ ከመምህራን ጋር በተካሄዱ ቃለ መጠይቆች የተሰበሰቡ መረጃዎች

ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ይቀርባል። ከዚያም ከውጫዊ (macro) የትምህርት ባለድርሻ አካላት ስለማጠናቀቂያ ፈተናዎች ተፅዕኖ በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተሰበሰቡት መረጃዎች ከሰነዶች ከተገኙ መረጃዎች ጋር እየተገናዘበ የተካሄደው የውጤት ትንተና ይከተላል። በመጨረሻው ክፍል ደግሞ በማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት የተበረታቱ አዎንታዊና አሉታዊ የወሸባክ ገጽታዎች ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ይቀርባል።

4.2. የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ታላሚ ተፈታኞችን የመመዘን ደረጃና አዎንታዊ ወሸባክ ከፍ ለማድረግ የፈተናዎች ኤጀንሲ የሚጠቀምባቸው ስትራቴጂዎች

ይህ ክፍል በፈተናዎች ኤጀንሲ ውስጥ ቀደም ሲል ከሰሩና በመሥራት ላይ ከሚገኙ ሁለት ኃላፊዎችና ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ጋር በተካሄዱ ቃለመጠይቆች የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን የመመዘን ደረጃና አዎንታዊ ወሸባክ ከፍ ለማድረግ ስለሚጠቀሙባቸው ስትራቴጂዎች የተገኙ መረጃዎች ውጤት ትንተናና ማብራሪያ የቀረበበት ነው። በድርሳናት ከለሳ እንደተጠቆመው የተለያዩ በፈተና ወሸባክ ላይ ጥናት ያካሄዱ ተመራማሪዎች ለምሳሌ Green (2007)፣ Qi (2004)፣ Wall (2006)፣ Alderson (2004)፣ እንደሚገልጹት በተለይ ውጫዊ ፈተናዎች (Public Exams / High Stakes Tests) የቋንቋ ትምህርት ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ ይፈጥራሉ።

የተጽዕኖው ዓይነትና ደረጃም ብዙ ጊዜ በፈተናው ዝግጅት ላይ የሚመሰረት ነው። ዓይነቱ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ወይም አዎንታዊና አሉታዊ ሊሆን ይችላል። ከሚኖራቸው አዎንታዊ ሚናዎች መካከል Wall (2006) የተለያዩ ተመራማሪዎችን በማጣቀስ ስድስት ዋና ዋና የውጫው ፈተናዎችን ተግባሮች አመልክተዋል። ከስድስቱ አንዱ በየትምህርት ቤቶች የሚሰጥ ትምህርት ወጥነት እንዲኖረው/ የተማከለ እንዲሆን ወይም በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተለያየ ትምህርት እንዳይሰጥ የሚያደርግ መሆኑ ነው። ይህ የውጫዊ ፈተና ተግባር ሊሳካ የሚችለው ግን ፈተናው የጥሩ ፈተና ባሕርያትን እንዲያሟላ ፈተና የማዘጋጀት አቅም ባላቸው ባለሙያዎች የሚዘጋጅና የሚመራ ሲሆን ነው። ይህ ተግባር ደግሞ በሀገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ኃላፊነት የተሰጠው ለፈተናዎች ድርጅት (በአዲሱ ስሙ ኤጀንሲ) ነው።

ስለዚህ በኤጀንሲው ከፈተና ዝግጅት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካላቸው ኃላፊዎችና ከአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ጋር በፖሊሲው በተገለጸው አቅጣጫ መሰረት የፈተናውን የመመዘን ደረጃና አዎንታዊ ወሽባክ ከፍ ለማድረግ በኤጀንሲው ስለሚሰሩ ስራዎች ውይይቶችን በማካሄድ መረጃዎች ተሰብሰበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት ትንተናና ማብራሪያም ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

ከአራቱ የጥናቱ ተሳታፊዎች ጋር ከተካሄዱት ውይይቶች ማረጋገጥ የተቻለው በኤጀንሲው የሚዘጋጁት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ሥርዓተ ትምህርቶቹን የመመዘን ደረጃቸውንና በመማር-ማስተማሩ ሂደቶች/ ተግባራት ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ አዎንታዊነት ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ እየተደረጉ ነው፡፡ ቀጥሎ እነዚህን ስትራቴጅዎች እያንዳንዳቸውን በተናጠል እያነሳን እንመለከታለን፡፡

4.2.1. በኤጀንሲው የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች (Experts) እና የጥያቄ አዘጋጆች አመራረጥ /አመላመል

በኤጀንሲው የሚዘጋጁ ፈተናዎችን የመመዘን ደረጃና አዎንታዊ ተጽዕኖ የመፍጠር አቅም ከፍ ለማድረግ በሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና የፈተናዎች ኤጀንሲ እንደ አንድ ስትራቴጂ የተወሰደው የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎችና የጥያቄ ፀሐፊዎች አመራረጥ ላይ የሚደረገው ጥንቃቄ ነው፡፡ በተለይ በኤጀንሲው በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ከሰሩት ኃላፊ፩ እና ኃላፊ፪ የተገኘው መረጃ እንዳረጋገጠው፣ ድርጅቱ ከተቋቋመ ጀምሮ በድርጅቱ የየትምህርት ዓይነቶቹ የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች (ከአንድ አጋጣሚ በስተቀር) ድርጅቱን እንዲቀላቀሉ የተደረገው በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው፡፡ ጥንቃቄውም የተሻሉ ባለሙያዎችን ለማሰባሰብ ወይም ለሥራው የሚመጥኑ ባለሙያዎችን ለመቅጠር እንዲቻል ነው፡፡ የተሻለ አቅም ያላቸውን ባለሙያዎች ለማሰባሰብ ከተከናወኑት ተግባሮች መካከልም አንደኛው ለየትምህርት ዓይነቱ የፈተና ዝግጅት ባለሙያነት የሚመረጡት /የሚወዳደሩት መምህራን ብቻ እንዲሆኑ መወሰኑ ነው፡፡ ይህም በሌላ የስራ ዘርፍ ከተሰማሩት ይልቅ መምህራን የትምህርት ዓላማዎችን የሚያውቁና የፈተና አዘገጃጀት ልምድ ያላቸው ናቸው ከሚል እሳቤ የመነጨ ነው፡፡

ሁለተኛው ከተወዳዳሪዎች መካከል የተሻሉ ባለሙያዎችን ለመምረጥ የመግቢያ (Entrance) ፈተና እንዲኖር መወሰኑና ተግባራዊ መደረጉ ነው። ፈተናው የተሻለ መመዘኛ እንዲሆንም የጽሑፍና የቃል ፈተና እንዲካተቱበት ተደርጓል።

ከዚሁ ከባለሙያዎቹ አመራረጥ ጋር በተያያዘ ኃላፊ ሲገልጹ፣ "መምህራንን የመግቢያ ፈተና አዘጋጅተን ነው የፈተነው። ስለዚህ ጥሩ ጥሩ የፈተና አዘጋጆችን በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት አንዳንድ ባለሙያ ቀጥረን ነበር። የፅሑፍ ፈተና ነበረው፣ የቃል ፈተና ነበረው... በእነዚህ ፈተናዎች አንደኛ አንደኛ የወጡትን ስለመረጥን ጥሩ ካሊቨር (ጥሩ ችሎታ)፣ የነበራቸውን ልጆች አሰባስበን ነበር፤" ብለዋል። ኃላፊዋም፣ "አንድ ጊዜ በ ቢ.ፒ.አር (BPR) ጥናት ከዋናው መሥሪያ ቤትና ከትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ወደዚህ ተቀይረው ከመጡ... (አንድ ሁለት) ሶስት አራት ሰዎች ውጭ ሌሎቹ ሁሉ ተፈትነው ነው ከዚህ የደረሱት፣ ተፈትነው ነው ከዚህ የገቡት፤" በማለት ቀዳሚውን ሀሳብ አጠናክረዋል።

አንድ አጋጣሚ ያሉት ግን በመቶሽዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ቀጣይ፣ የሕይወት ዕጣ ፈንታ በሚወስን የስራ ዘርፍ፣ ያለ ከስራው ጋር ግንኙነት ያለው ተገቢ መስፈርትና ውድድር በምደባ ቦታውን እንዲይዙ መደረጉ ያስከተለው ወይም ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ግን በውይይቱ በግልጽ ተብራርቶ አልተገለጸም። በጥቅሉ በውድድር የተሻሉ ሰዎች ያልተመረጡበት አንድ አጋጣሚ መኖሩን ብቻ በመጠቁም ለሚገባ ይግባው በሚል አይነት አማርኛ ብቻ ተጠቁሞ ታልፏል። እነዚህ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ተወዳድረውና የተሻሉ ሆነው በመገኘታቸው ለስራው የተመደቡ ባለሙያ ባለመሆናቸው በተመደቡበት የትምህርት ዓይነት የፈተና ዝግጅት፣ ጥሩ ስራ የመስራት ወይም ፈተናዎቹ ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲዘጋጁ የማድረግ አቅም ላይኖራቸው ይችላል። የኤጀንሲው ኃላፊዎችም በድርጅቱ መስፈርት መሰረት አወዳድረውና ፈትነው ተቋሙን እንዲቀላቀሉ ያደረጓቸው ባለመሆናቸው ኃላፊነቱን የጋራ ለማድረግና በሂደት ለሚከሰቱ ችግሮቹ በጋራ መፍትሄ ለመፈለግ አስቸጋሪ ሊሆንባቸው ይችላል። ባጠቃላይ ለስራው ይሻል የነበረው ግን እንዲህ ያሉ የባለሙያ ችሎታን የግድ የሚጠይቁ/ የሚፈልጉ የስራ ዘርፎች ውስጥ የሰው ኀይል ምደባን በሚመለከት ሌላ ክፍል ጣልቃ ባይገባ ነው።

የጥያቄ አዘጋጆች (Item Writers) አመላመልም የተወሰኑ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ እንደሚከናወን ሁሉም ተሳታፊዎች ተናግረዋል። በተሳታፊዎቹ እንደተገለፀው ጥያቄ አዘጋጆች የሚመለመሉት በከፍተኛ ተቋማት (በዩኒቨርሲቲና በኮሌጅ) እያስተማሩ ካሉ መምህራን መካከል ነው። መምህራኑ ለጥያቄ ፀሐፊነት/ አዘጋጅነት የሚመረጡትም ሦስት መሰረታዊ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ነው። መስፈርቶቹም አንደኛ ቢያንስ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው፣ ሁለተኛ በሙያ ብቃታቸውና ሦስተኛ በሥነ-ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ወይም ታማኝ/ ምስጢር ጠባቂ የሆኑ የሚሉት ናቸው። ለጥያቄ አዘጋጅነት የሚመረጡት መምህራን እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆናቸው በተለያየ ዘዴ (ለምሳሌ ከስራ ባልደረቦቻቸው፣ ከተማሪዎቻቸው፣ ወዘተ. መረጃ በማሰባሰብ) ከተጠናና ከተመለመሉ በኋላም ስራ ከመጀመራቸው በፊት ጥያቄ አጻጻፍ (ፈተና አዘገጃጀት) ዘዴን በሚመለከት የተወሰነ ስልጠና /ኦረንቴንሽን (Orientation) እንዲያገኙ ይደረጋል። ባለሙያ ‹ለ› ስለዚሁ ስለ ጥያቄ ፀሐፊዎች ስልጠና ሲያስረዱ፣ “ በፈተና ዝግጅት ልምድ ያላቸው፣ በመምህርነት ሙያ ላይ ያሉ እነዚህ ናቸው እንዲሳተፉ የሚደረገው። እና ሁል ጊዜ ከዝግጅት በፊት አጠቃላይ ስልጠና ይሰጣል፣ ወደ ዝግጅት ከመግባታቸው በፊት ኦረንቴንሽን በሚገባ ይሰጣል።” ይላሉ።

ከእኒህኛው ተሳታፊ ገለጻ መረዳት እንደተቻለው፣ አንደኛ ጥያቄ አዘጋጆች ከመምህራን መካከል ብቻ እንዲመረጥ የሚደረገው መምህራን ፈተና የማዘጋጀት ልምድ ስላላቸው ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው። ሁለተኛ ልምዱ ብቻ ጥሩ ጥያቄ ለማዘጋጀት አያስችላቸውም ተብሎ ስለሚታሰብ ስለፈተና ጥያቄ አጻጻፍ አቅማቸውን የሚያጎለብት አጠቃላይ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል። ከስልጠናው በተጨማሪም የሥርዓተ ትምህርቶቹ መሳሪያዎች፣ የአዘገጃጀት መርሆ ሰነዱና የሚመዘኑ ክፍሎችን የያዙ ልየታዎች (specifications) ለጥያቄ ፀሐፊዎቹ/ አዘጋጆቹ እንደሚሰጡ በውይይቶቹ ተገልጿል። (እነዚህን ሰነዶች እዚያው በቢሯቸው ውስጥ ለመመልከት ተችሏል። ነገር ግን በምስጢር የሚያዙ/ መውሰድ ወይም ኮፒ ማድረግ የማይፈቀድ በመሆኑ በሰነዶች ላይ ተመስርቶ ዝርዝር ሀሳብ ለመስጠት ሳይቻል ቀርተዋል።)

4.2.2. የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎችን አቅም ማጎልበት

የኤጀንሲው ኃላፊዎች እንዳስረዱት፣ ባለሙያዎቹም እንዳረጋገጡት በየጊዜው የሚዘጋጁ የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን የመመዘን ደረጃና በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚፈጥሩትን አዎንታዊ ተፅዕኖ ከፍ ለማድረግ እንደ አንድ መሰረታዊ ስትራቴጂ ተደርጎ እየተሰራበት ያለው ሁለተኛ ስልት የባለሙያዎችን አቅም በተለያየ መንገድ ማጎልበት ነው፡፡ የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎችን አቅም ለማጎልበት ከሚጠቀሙባቸው ስልቶቹም ቀዳሚው ለባለሙያዎቹ ከፈተና ዝግጅት፣ አርታኢነትና አስተዳደር ጋር የተያያዙ የተለያዩ ሥልጠናዎችን መስጠት ነው፡፡ ይህም ድርጅቱ ከተመሰረተና ባለሙያዎቹ ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው እየተከናወነ ያለ ተግባር እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ስለዚሁ ጉዳይ ኃላፊዎቹ በገለጹበት ከፍል እንዳስረዱትም ለምሳሌ በ1990 ዓ.ም(እ.ኢ.አ.) አካባቢ የአማርኛን ጨምሮ የተቀጠሩት የመጀመሪያዎቹ የየትምህርት ዓይነቶቹ የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በመግቢያ ፈተና ከተመረጡ በኋላ ወደፈተና ዝግጅት ከመግባታቸው በፊት አንደኛ፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሳይኮሎጂ ትምህርት ክፍል ጋር በመነጋገር ባለሙያዎቹ ‹‹የወራት አንድ ወይም ሁለት ወር የወሰደ ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል››(ኃላፊ፩)፡፡ ሁለተኛ፣ ከአሜሪካ የትምህርት ፈተና አገልግሎት (Educational Testing Service_ETS) ጋር በመነጋገር ለአስራ አምስት ቀናት የፈተና ዝግጅትን በተመለከተ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ሦስተኛ፣ በሳምንት አንድ ቀን በፈተና ዝግጅትና አስተዳደር ዙሪያ ከ2-3 ሰዓት የሚወስድ የውይይት መርሐ ግብር እንዲዘጋጅ ተደርጓል(ኃላፊ፩)፡፡

ለባለሙያዎቹ የሚሰጡት ስልጠናዎች አሁንም እንዲሰጡ እየተደረገ ነው፡፡ ለምሳሌ በ2005 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) መጀመሪያ አካባቢ ከአሜሪካ የትምህርት ፈተና አገልግሎት (ETS) በመጡ ባለሙያዎች የድርጅቱ የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በሙሉ ለ22 ተከታታይ ቀናት በፈተና አዘገጃጀት፣ አስተዳደርና አስተራረም/ ውጤት አሰጣጥ (Scoring) ላይ እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡ በቅርቡ ደግሞ ከጃፓን በዚሁ በፈተና ዝግጅት፣ አስተራረምና አሰጣጥ ላይ ከሚሰራ ተቋም ጋር እንዲሁ ሌላ “ስልጠና ለባለሙያዎቹ ለመስጠት የትምህርት ምክትል ሚኒስትሩ ተፈራርመዋል፤” (ኃላፊ፪)፡፡

በቅርቡም የተወሰኑ የኤጀንሲው ባለሙያዎች የገፅ ለገፅ (face to face) ስልጠና ወደ ውጪ ሀገር ይላካሉ (ኃላፊ ፪)፡፡

ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ በተለይ በኃላፊ፪ እንደተዘረዘረውና ተብራርቶ እንደቀረበው የኤጀንሲውን የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች አቅም ለማጎልበት፣ አንደኛ፣ በኤጀንሲው የባለሙያ የትምህርት ደረጃ (በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች) ሁለተኛ ዲግሪ ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ ሁለተኛ፣ ሁለተኛ ዲግሪ የሌለው ባለሙያ ካለ ድርጅቱ ከፍሎ ያስተምረዋል፡፡ ሦስተኛ፣ እያንዳንዱ ባለሙያ ለስራው የሚያስፈልገው ማንኛውም ነገር እንዲሟላለት ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ ላፕቶፕ (laptop) ኮምፒውተር እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ አራተኛ፣ ለእያንዳንዱ ባለሙያ የሚያስፈልገው ሶፍትዌር ይገዛለታል፡፡ አምስተኛ የ24 ሰዓት የብሮድባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት አለ፤ የፈለጉትን "ዳውንሎድ" (download) ማድረግ እንዲችሉ ተመቻችቶላቸዋል፡፡ ባለሙያዎቹም የተባሉት ነገሮቹ ሁሉ ተግባራዊ እየተደረጉ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

የእነዚህ የአቅም ማጎልበቻ ስትራቴጂዎች ዓላማም የየትምህርት ዓይነቶችን የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች አቅም አጎልብቶ በኤጀንሲው የሚዘጋጁትን ፈተናዎች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ‹‹የሀገሪቱን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና ሥርዓተ ትምህርት መሰረት ያደረጉ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ማዘጋጀትና ማስተዳደር...››(የፈተናዎች ኤጀንሲ ራዕይ፣ ተልዕኮና አሴቶች 2000)፡፡ የሚለውን የኤጀንሲውን ተልዕኮ ተግባራዊ በማድረግ የፈተናዎቹን አዎንታዊ ተፅዕኖ ከፍ ለማድረግ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡ ይህም በHughes (2003) እና Green (2007) ስራዎች የቀረቡ የፈተናን የጥራት ደረጃና አዎንታዊ ወሽባክን ማጉልበቻ ሐሳቦች የሚጋራ አስተሳሰብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

4.2.3. የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎች ዓላማ/ዎች

የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ዓላማ በተመለከተ በአባሪ 13 በቀረበው የተሳታፊዎች ምላሽ ተብራርቶ እንደተገለፀው የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት

ማጠናቀቂያ ፈተና መሰረታዊ ዓላማ የተማሪዎችን ችሎታ መለካት ነው፡፡ ስለዚህ ፈተናው ስለተማሪዎች ችሎታ ምስክርነት ለመስጠት የሚያገለግል የችሎታ መለኪያ ፈተና /Achivement Test) ነው ማለት ነው፡፡ በኃላፊ እምነት ደግሞ የማጠናቀቂያ ፈተናው ከችሎታ መለኪያነቱ በተጨማሪ ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ የሚዛወሩትን ለመምረጥም ያገለግላል፡፡

የመጀመሪያውንና ዋነኛ ያሉትን ዓላማ በሚመለከት ኃላፊ ‹‹የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት አጠናቀዋል›› የሚለውን ለመመስከር ነው ሲሉ፣ ሌሎቹም በተመሳሳይ ሁኔታ ፈተናው የችሎታ መለኪያ (achievement) ፈተና ስለሆነ በመርሐ ትምህርቶቹ የተካተቱትን አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች መሳካታቸውን ማረጋገጥ ወይም የተማሪዎችን ችሎታ (በመማር-ማስተማር ሂደቱ ያመጡትን ለውጥ) መመስከር የፈተናው ዋና ዓላማ ነው ብለዋል፡፡ ለምሳሌ ኃላፊ፣ ስለዚሁ ዓላማ ሲገልጹ ‹‹ተፈታኙ ወይም ተማሪው ሁለት ዓመት ተምሮ ምን ያህል ይዟል? ወይም አቺቭ አድርጓል? የሚለውን ለመለየት ነው" ብለዋል፡፡ አክለውም ስያሜው ራሱ የችሎታ መለኪያ ፈተናነቱን የሚያመለክት ነው የሚል ሐሰብ ሰንዝረዋል፡፡

በተሳታፊዎቹ እንደተገለጸው ፈተናው የችሎታ መለኪያ ፈተና አዘገጃጀትን መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅ ቢሆንም ትምህርት ሚኒስቴር ይህን ውጤት ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ የሚሸጋገሩ ተማሪዎችን ለመምረጥ እንደሚጠቀምበት ገልጸዋል፡፡ ኃላፊ ይህን እንደፈተናው ሁለተኛ ዓላማ ያዩታል፡፡ ለምሳሌ ስለዚሁ ጉዳይ ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ፤

> በሀገራችን የትምህርት ሲስተም [ሥርዓት] 10ኛ ክፍል ያጠናቀቁ በሙሉ ወደሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ ለማሸጋገር አይቻልም፡፡ ስለዚህ በሙሉ ማሸጋገር ስለማይቻል መምረጥ ግዴታ ነው፡፡ መምረጥ ግዴታ ከሆነ ደግሞ የተሻለ መምረጫ መስፈርቱ ፈተና ነው፡፡ ስለዚህ የእኛ ሀገር ፈተና ዓላማ አንዱ ወደሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ የሚዛወሩትን ተማሪዎች መምረጫ ነው፡፡

የፈተናው ዝግጅት የችሎታ መለኪያ ፈተናን ብቻ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ላይ ግን ኃላፊን ጨምሮ ሁሉም ተሳታፊዎች ይስማማሉ፡፡ ለምሳሌ ፈተናው ሁለት ዓላማ

የትምህርት ደረጃ እንዲያልፉ ቢደረግ ችግር አይኖረውም። በHenning (1987] ስራ የቀረበው ሀሳብ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው። የሀገሪቱ አቅም ፈቅዶ ለየራሳቸው የተለያየ ፈተና ማዘጋጀት እስከሚቻል ድረስ ሀገሪቱ እየተጠቀመችበት ያለው ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ አይነት አሰራር ተገቢነት ያለው ነው ማለት ይቻላል።

በኃላፊው የተገለፁት ሐሳቦች በሀገሪቱ የሚሰጡት የ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ምንም እንኳ ሁለት ተግባር ቢኖራቸውም ሁለተኛውን በሚመለከት ግን በፈተናው ዝግጅት ወቅት የሚደረግ የተለየ ጥረት አለመኖሩን የሚያሳይ ነው። ፈተናዎችን ለማዘጋጀት የሚጠቀሙባቸው ሰነዶች ራሳቸው የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል መርሐ ትምህርቶች፣ ዝቅተኛ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች (Minimum Learning Competencies)፣ የመማሪያና የማስተማሪያ መጽሐፎች እና በእነዚህ መሳሪያዎች ውስጥ የሰፈሩትን ዓላማዎችና ይዘቶች መሰረት በማድረግ የሚያዘጋጇቸው የፈተና ልየታዎች (Specifications) ሰንጠረገሮች መሆናቸው የፈተናው ትኩረት ችሎታን መለካት እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ከዚህም ምንም እንኳ በፈተናው የሚመዘገበውን ውጤት ትምህርት ሚኒስቴር ወደመሰናዶ፣ ወደቴክኒክና ሙያና ሌሎች ፕሮግራሞች የሚያልፉ ተማሪዎችን ለመለየት/ ለመወሰን ጭምር የሚጠቀምበት ቢሆንም በፈተናዎች ኤጀንሲ የሚታመነውና የፈተናው ዝግጅት የሚከናወነው ግን የችሎታ መለኪያ ፈተናነቱን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት/ መሰረት በማድረግ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚያምኑት ፈተናዎቹ የችሎታ መለኪያ ፈተና አዘገጃጀትን ተከትለው መዘጋጀታቸውም ሥርዓተ ትምህርቶቹ እንዲሸፈኑ ስለሚገፋፉ በመማር ማስተማር ሂደቱ መምህራኑና ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመሸፈን እንዲጥሩ ያበረታታል። ይህም ፈተናዎቹ በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ/ ወሸባክ እንዲያሳድሩ የሚያግዝ ስትራቴጂም ነው ማለት ነው።

ሁሉም ተሳታፊዎች በፈተናዎች ውጤታማ ለመሆን ከተማሪዎች ምን ይጠበቃል? ለሚለው ጥያቄ በሥርዓተ ትምህርቶቹ የተካተቱ ትምህርቶችን መከታተል፣ በመማሪያ መጽሐፎቻቸው የቀረቡ ትምህርቶችን ማጥናት፣ ክፍል ውስጥ መከታተልና መልመጃዎችን መስራት ነው፤ ፈተናዎች በሥርዓተ ትምህርቶቹ ላይ የተመሰረቱ ስለሆኑ ይህን ያላደረገ ተማሪ ውጤታማ አይሆንም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም

የሚዘጋጁት ፈተናዎች በችሎታ መለኪያ ፈተና አዘገጃጀት ላይ እንዲመሰረቱ ሲደረግ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዲያሳድሩ በማለትም ጭምር እንደሆነ የሚያሳይም ነው።።

4.2.4 የማጠናቀቂያ ፈተናው ታላሚ (intended) ወሽባክ

በተለያዩ ሀገሮች ውጫዊ /ብሔራዊ ፈተናዎች ሲዘጋጁ በመማር- ማስተማር ሂደቶች ላይ እንዲያሳድሩት የሚፈለገው ተፅዕኖ ይታለማል (Cheng 2005፣ Hawkey 2006፣ Qi.2004፣)። ቀደም ብሎ የተገለጸው የኤጀንሲው ተልዕኮ ራሱ ይህንኑ የሚያሳይ ቢሆንም፣ ታላሚ ወሽባክን በተመለከተ (በአጠቃላይና በተለይ ደግሞ ስለአማርኛ ቋንቋ) የጥናቱ ተሳታፊዎች ያላቸውን ሀሳብ እንዲገልጹ ተጠይቀው ነበር። በዚህ ረገድ አገላለጻቸው ቢለያይም በየዓመቱ የሚሰጡት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ወሽበክ እንዲኖራቸው ይታለማል የሚል እምነት አላቸው። አዎንታዊ ወሽባክ እንዲኖራቸው ጥረት የሚደረግ ቢሆንም ፈተናው በምርጫ ብቻ የሚቀርብ በመሆኑ በተለይ የቋንቋ ፈተናዎቹ ያልታለሙ አሉታዊ የወሽባክ ገጽታዎች ሊኖራቸው እንደሚችልም ተሳታፊዎቹ ይገምታሉ።

ስለዚሁ ስለታላሚ ወሽባክ ለምሳሌ ኃላፊ፪ ሲናገሩ ፈተናው የሚታለም ወሽባክ እንዳለው ከገለጹ በኋላ በተግባርም ፈተናዎች ወሽባክ እንዳላቸው እንደሚታወቅ ተናግረዋል። ፈተናው ወሽባክ አለው ያሉበትን ምክንያት በማስረጃ ሲያቀርቡም የሚከተሉትን ነጥቦች ጠቅሰዋል፡- አንደኛ፣ አንድ ትምህርት ቤት ለምሳሌ በፊዚክስ ወይም በእንግሊዝኛ ወይም በሌላ የትምህርት ዓይነት በኤጀንሲው በሚዘጋጅ ፈተና ብዙ ተማሪ ዝቅተኛ ውጤት ሲያመጣ በዚህ የትምህርት ዓይነት የማስተማር ሂደታችንን እናጠናክር ብለው የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰዳቸው የማይቀር መሆኑን (ትምህርት ቤቶች በማጠናቀቂያ ፈተናው ውጤታማ መሆን ስለሚፈልጉ ለዚህ ሲሉ ጠንክረው እንደሚሰሩ)፣ ሁለተኛ፣ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ለክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎች በጥያቄ ትንተናና ሌሎች መረጃዎች ላይ በመመስረት ስለተማሪዎቻቸው ውጤት ሪፖርት ሲያቀርቡላቸው ወይም በኤጀንሲው ተልዕኮ መሰረት ግብረ-መልስ ሲሰጧቸው ከሪፖርቱ በየትምህርት ዓይነቱ ከዘጠኙ ክልሎች

ያሉበትን ደረጃ ሲያውቁ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማጠናከር እንዲነሳሱ እንደሚያደርጋቸው፤ ይህም የፈተናው አዎንተዊ ተፅዕኖ ውጤት ነው ብለው እንደሚያምኑ ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ ስለዚህ ስለሁለተኛው ምሳሌ እኒሁ ኃላፊ ሲያስረዱ እንዲህ ብለዋል፤

> ለክልል ትምህርት ቢሮ ኀላፊዎች በየትምህርት ዓይነቱ የተማሪዎቻቸውን ውጤት ሪፖርት ስናደርግላቸው ለምሳሌ ኦሮሚያ በፊዚክስ ትምህርት ከዘጠኙ ሪጅኖች [ክልሎች] ስድስተኛ ነው ወይም ሰባተኛ ነው፤ ትግራይ በእንግሊዝኛ ትምህርት ስድስተኛ ነው ብለን ሪፖርት ስናደርግላቸው ለምን ሌሎቹ ክልሎች ቀደሙን ብሎ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ይሰራል፡፡

ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው አዎንታዊ ተፅዕኖ/ ወሽባክ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በእርግጥ ኃላፊ ስለዚህ ጉዳይ በገለፁበት ክፍል እንዳንፀባረቁት ፈተናው በመማር ማስተማር ሂደቶች ይበልጥ አዎንታዊ ተፅዕኖ የሚኖረው በቋንቋ ሳይሆን በሌሎች የቀለም ትምህርቶች ነው፡፡ ምክንያቱም በቋንቋ በምርጫ ፈተና አብዛኞቹን ክሂሎች በቀጥታ መመዘን ስለማይቻል ነው፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር መዋቅሮች በአብዛኛው ተቀባይነት አግኝቶ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ የሚመስለው ታላሚ የወሽባክ ዓይነት ግን በኃላፊ የተንጸባረቀው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ በስሩ ላሉት የዞን ትምህርት መምሪያዎችና ከተማ አስተዳደሮች በክልሉ ውስጥ ያሉ ትምህርት ቤቶች በየትምህርት ዓይነቶቹ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ያገኙትን ውጤትና ደረጃ የሚያሳይ/ የሚገልፅ ሰነድ እንዲደርሳቸው፤ እንዲሁም እያንዳንዱ ትምህርት ቤት በየትምህርት ዓይነቱ የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል በየዓመቱ መጀመሪያ በመቶኛ ግብ እየያዘ እንዲሰራ ማድረጉ አንዱ ምክንያት የተማሪዎችን የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት ለማሻሻል እንደሆነ መገንዘቡ አይከብድም፡፡ ይህም ፈተናዎቹ በትምህርቶቹ ዓላማዎች ላይ የማይመሰረቱ ከሆነ ጥሩ የመማር ማስተማር ሂደቶችን የማያበረታቱ ወይም አሉታዊ ወሽባክን የሚያበረታቱ ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚጠቁምም ነው፡፡ ኃላፊ ይህን ሀሳብ ነው የሚጋሩት፤ እንደሳቸው ዕምነት በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥሩ ውጤት ማምጣትና በሥርዓተ ትምህርቶቹ የተካተቱት ዓላማዎችን ከግብ ማድረስ ሁልጊዜ ትይዩ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ በተለይ በቋንቋ ሀሳብን በቃልም ሆነ በጽሑፍ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARY
P. O. BOX
ADDIS ABABA

አቀናብረው በአግባቡ መግለፅ የማይችሉ ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጥሩ ውጤት ሊያስመዘግቡ፣ በአንፃሩም ጥሩ ተናጋሪና ጥሩ ጸሐፊ የሆኑ ተማሪዎች በፈተናዎቹ የሚያዝመዘግቡት ውጤት ዝቅተኛ/ ጥሩ የማይባል ሊሆን ይችላል።

በተለያዩ ወገኖች (ለምሳሌ በክልል ደረጃም ሆነ በክልሉ ስር ባሉ መዋቅሮችና ትምህርት ቤቶች) ተቀባይነት እያገኘ የመጣው አስተሳሰብ ግን በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ የጥሩ ማስተማርና መማር ሂደት ውጤት ነው የሚለው ነው። ለዚህም አንዱ ማስረጃ ጥሩ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎችና ትምህርት ቤቶች የሚሰጡት ማበረታቻዎችና ድጋፎች ናቸው። ይህም በሀገሪቱ የፈተና አዎንታዊ ተፅዕኖ ነው ተብሎ በአብዛኛው የሚታሰበው ተማሪዎችን ለፈተና ዝግጁ የሚያደርግ ትምህርት አሰጣጥን እንደሆነ የሚያሳይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በክለሳ ድርሳናት ክፍል እንደተገለጸው እንዲህ ያለ ግንዛቤ ባለበት ሁኔታ ፈተናዎቹ በሥርዓተ ትምህርቶቹ የተካተቱ/ የቀረቡ የትምህርት ዓላማዎችን ለመመዘን የማያስችሉ ወይም የትምህርቶቹ ዓላማዎች ከግብ መድረስ አለመድረሳቸውን የማይለኩ ዓይነት ከሆኑ ወሽባካቸው ጠቃሚ ላይሆን ይችላል።

ቀደም ብሎ እንደተወሳው ኃላፊ፩ በሀገሪቱ የሚሰጡ የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ታላሚ ወሽባክና ውጤቱን የሚያዩበት መንገድ ከቀዳሚዎቹ ለየት ይላል። የእሳቸው አተያይ ከዚህ የሚከተለው ነው፤

> በመጀመሪያ ደረጃ በድርጅቱ የሚዘጋጁት ፈተናዎች፤ ከፍተኛ ውሳኔ የሚወሰንባቸው (High-stakes test) ናቸው። እነዚህን ፈተናዎች በዚህ ደረጃ እንዲመደቡ የሚያደርጋቸውም፣ ተማሪዎቹ ይህን ፈተና ከወደቁ የሚያጡት ነገር ስላለ ነው።... ሕይወታቸውን፣ የወደፊት ዕጣ ፈንታቸውን የሚወሰን ነው። ለዚህም ነው High stake exam [ከፍተኛ ውሳኔ የሚወሰንበት ፈተና] የምንለው ...በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ፈተናዎች (Public Examinations) ቀጣዩን የተማሪዎች አቅጣጫ የሚወሰኑ ስለሆኑ የሚመደቡት በዚህ ደረጃ ነው።

በመቀጠልም እነዚህ ፈተናዎች ደረጃቸውን ጠብቀው ወይም የጥሩ ፈተና ባህርያትን አሟልተው ከተዘጋጁ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አዎንታዊ (positive) ተፅዕኖ ማሳደራቸው እንደማይቀር ገልፀዋል። የግል ገጠመኞቻቸውን ባወሱበት ክፍል ደግሞ በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ባካሄዷቸው ምልከታዎች ተማሪን ለፈተና ማዘጋጀት ዋነኛ

ተግባር ሆኖ እንዳገኙት፣ ህብረተሰቡ ራሱ ጥሩ ትምህርት ቤት የሚለው በሥርዓተ ትምህርቶቹ የታለሙትን ዓላማዎች ከግብ የሚያደርስን ሳይሆን በፈተና ጥሩ ውጤት የሚያስመጣን እንደሆነ፣ አመልክተዋል። አክለውም እንዲህ ያለ አስተሳሰብ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ባደጉት አገሮችም ሳይቀር የሚታይ እንደሆነ በማስረጃነት በእንግሊዝ ሀገር ያለውን እንዲህ ያለ እውነታ ያንጸባርቃል ያሉትን የDoreን Diploma Disease የሚል ስራ /መጽሐፍ ሀሳቦች በመጥቀስ አስረድተዋል።

ከዚህ አንፃር በፈተናዎች ኤጀንሲ ለክልል ትምህርት ቢሮ ኀላፊዎች ከሚሰጠው ግብረ መልስ (feedback) በመነሳት ክልሎቹ የሚወስዷቸው እርምጃዎች ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርቶቹ ላይ አተኩረው እንዲሰሩና ፈተናዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አዎንታዊ ሚና እንዲጫወቱ የሚያደርግ ነው የሚለው ሀሳብ አከራካሪ ነው፤ ዝርዝር ጥናት ማካሄድን ይጠይቃል።

በኤጀንሲው ስለሚታየው አጠቃላይ ወሽባክና ታላሚ ወሽባክን ከግብ ለማድረስ ስለሚከናወኑ ተግባራት ያለውን አስተሳሰብና አሰራር ጥቅል በሆነ መንገድ ከላይ የቀረበውን ይመስላል። ቀጥሎ ደግሞ የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎቹ የቋንቋው ፈተናዎችን ታላሚ ወሽባክ በተመለከተ የሰጡት ሐሳብ ይከተላል።

በዚህ ረገድ በተለይ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በቋንቋው ትምህርት ላይ እንዲያሳድረው የሚጠበቅ ታላሚ (intended) ወሽባክ እንዳለ፣ ካለ ምን እንደሆነና ታላሚው ወሽባክ ከግብ እንዲደርስ እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግ ለተጠየቁት ጥያቄዎች የቋንቋው ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች የሰጡት መልስ ከቀዳሚዎቹ ለየት ይላል። በእነዚህ ባለሙያዎች እምነት የቋንቋው ፈተና በማስተማር መማር ሂደቱ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዲያሳድር ታልሞ ነው የሚሰራው/ የሚዘጋጀው። የፈተናውን አዎንታዊ ወሽባክ ከፍ ለማድረግ ታልመው ከሚከናወኑት መካከል ዋነኛ ስትራቴጂ ተደርጎ የተወሰደውም በፈተናው የሥርዓተ ትምህርቱ (የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል መርሐ ትምህርቶች) ሁሉም ክፍሎች እንዲሸፈኑ /እንዲወከሉ መደረጉ ነው። ለምሳሌ ባለሙያ ‹ለ› ስለዚሁ ጉዳይ ለስድስተኛው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ እንዲህ ብለዋል፤

አዎ! ምንድነው፣ ሁሉንም እንትኖች [የትምህርቱ ክፍሎች] አካቶ ነው የሚቀርበው፣ ፈተናው ሁሉንም የክሂል ዘርፎች እንደገና ደግሞ ሁለቱን የዕውቀት ዘርፎች ማለት ነው፡፡ እና በዚህ ላይ ደግሞ በተቻለ አቅም በየክፍል ደረጃው ያሉ ወይም በሥርዓተ ትምህርቱ የተዘረዘሩ ይዘቶች ማለት ነው፣ ዓላማዎች፡፡ እነዚህ እንዲሸፈኑ ነው ጥረት የሚደረገው ስለዚህ የግድ መምህራን ሁሉንም ይዘቶች በየዓመቱ እንዲሸፍኑ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ እንደዚህ ሆኖ መዘጋጀቱ ለተማሪውም እንደዚሁ ነው፡፡ ድሮ ከዚህ በፊት... ይቀርቡ የነበሩ ፈተናዎች ይዘታቸው በተወሰኑ ክፍሎች ወይም በእውቀት ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ምናልባትም ደግሞ ከሥርዓተ ትምህርቱ ውጪ የሚሆኑበት ዓይነት ነገር ነበር ማለት ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ነገር ስለነበር በቃ አማርኛ ምን ችግር አለው ሳንዘጋጅ ምን ሳንል ልንፈተነው የምንችለው ነው፤ የሚል ዓይነት ግንዛቤ በተማሪዎች ዘንድ ነበር፡፡... አሁን ግን የግድ በአማርኛ ውጤት ማምጣት የሚፈልግ ተማሪ...መጻሕፍቶችንም፣ ትምህርቱንም በሚገባ መከታተል አለበት፣ ይህን እንዲያደርግ ያስገድደዋል፤ የሚዘጋጁት እንትኖች [ፈተናዎች] ማለት ነው፡፡ እና ያላጠና ወይም ያልተዘጋጀ ተማሪ በነሲብ የሚያገኘው አይደለም እና ከዚህ አንፃር የሆነ አስተዋፅኦ አለው፤ ለመምህራንም ለተማሪዎችም ባጠቃላይ ለመማር ማስተማሩ ሂደት፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና፣ መምህራኑም ተማሪዎችም ሥርዓተ ትምህርቱን ተከትለው እንዲያስተምሩና እንዲማሩ የሚያበረታታ ዓይነት ሆኖ እየተዘገጀ ነው፤ የሚል የባለሙያዎች እምነት እንዳለ የባለሙያ ‹ለ› ገለፃ ያመለክታል፡፡ የባለሙያ ‹ሀ› ሃሳብም ተመሳሳይ ነው፡፡ የሁለቱም ሀሳብ በኃላፊ፪ ከቀረበው ጥቅል ሀሳብና በአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ለዞኖች፣ ወረዳዎችና ለትምህርት ቤቶች እያመላከተ ካለው አቅጣጫ ለየት ያለና ከወሸባክ ፅንሰ ሀሳብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አስተሳሰብና ተግባር ነው፡፡ አስተሳሰቡና እየተሰራ ነው የተባለው ነገር በተግባር ሲታይ ምን ይመስላል የሚለው በሌላ ክፍል ቀርቧል፡፡ በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ ሲታይ ግን፣ ቀደም ሲል ኃላፊ፪ እንደገለጹት፣ የቋንቋው ፈተና፣ የቋንቋ መምህራን ሥርዓተ ትምህርቱን እንዲሸፍኑ፣ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፎቻቸው የቀረቡላቸውን ትምህርቶች ሁሉ የግድ እንዲያነቡ፣ እንዲያጠኑ፣ መልመጃዎችን እንዲሰሩ፣ የክፍል ትምህርቱን በሚገባ እንዲከታተሉ የሚያበረታታ ብቻ ሳይሆን የሚያስገድድ ጭምር ተፅዕኖ የሚፈጥር ሆኖ እንደሚዘጋጅ የባለሙያዎቹ ማብራሪያ ያስገነዝባል፡፡ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ከተማሪዎች ምን ይጠበቃል ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

4.2. 5 የማጠናቀቂያ ፈተናውና ሥርዓተ ትምህርቱ ተዛምዶ/ ተጣጥሞሽ (Overlap)

በክለሳ ድርሳናት ክፍል እንደተገለፀው አዎንታዊ ወሽባክን ለማበረታታት እንደ አንድ ስትራቴጂ የሚታየው በሥርዓተ ትምህርቱና በፈተናው መካከል ቀጥተኛ ተዛምዶ ወይም የይዘት አግባብነት (Content Validity) እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊዎች በቀዳሚዎቹ ክፍሎችም ሆነ በዚህ የፈተናና የሥርዓተ ትምህርትን ተዛምዶ በሚመለከተው ክፍል ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ እንዳስረዱት፣ በኤጀንሲው ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች አንዱና ዋናው ይኸው በፈተናዎቹና በሥርዓተ ትምህርቶቹ መካከል ሊኖር የሚገባውን ተገቢ ዝምድና መፍጠር የሚለው ነው፡፡ ለምሳሌ ኃላፊ፪ ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልፁ፣ ‹‹የእኛ ፈተና ብዙ ድክመቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ ግን አንድ ጠንካራው ነገሩ የፈተና-ሥርዓተ ትምህርት ተዛምዶው (Exam- curriculum Alignment) ነው›› ይላሉ፡፡ እኒሁ ኃላፊ አፅንኦት ሰጥተው እንደገለፁትም የፈተና ዝግጅቱ የመጀመሪያ ተግባርም የሥርዓተ ትምህርት ክለሳ (Curriculum review) ማካሄድ ነው፡፡ በክለሳውም በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የተቀየረ ነገር አለ? ለምሳሌ ‹‹አማርኛ አምና ከሰራንበት ስፔስፍኬሽን ዘንድሮ የተለወጠ ነገር አለ ወይ? የሚለውን እናያለን›› ብለዋል፡፡

በዚህ ሂደት ከሥርዓተ ትምህርቱ ላይ የተጨመረ ወይም የተቀነሰ ክፍል መኖር አለመኖሩ እንደሚረጋገጥ፣ ከተረጋገጠ በኋላም እያንዳንዱ የሥርዓተ ትምህርት ዓላማ እንደሚቆጠር (ታሊ እንደሚደረግ)፣ በቆጠራውም የትኛው ዓላማ የትኛው የዕውቀት ክፍል (category) ላይ (የትኛው በዕውቀት ላይ፣ የትኛው በመረዳት ላይ፣ የትኛው በትንተና ላይ...) እንደሚያርፍ የሚለይ መሆኑን ኃላፊው አስረድተዋል፡፡

እኒሁ ኃላፊ፪ አያይዘው እንዳስረዱትም የትምህርት ዓይነቶቹ የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎችና ጥያቄ አዘጋጆች/ ፀሐፊዎች የሚጠቀሙባቸው ወካይ የሆኑ የልየታ ሰንጠረዦች (Table of specifications) የሚዘጋጁትም በዚሁ በሥርዓተ ትምህርቶቹ ዓላማዎች መሰረት ነው፡፡ ሁለቱ ባለሙያዎችም ይህንን ሀሳብ ይጋራሉ፡፡ ጥያቄ ፀሐፊዎች የሚያዘጋጇቸው ጥያቄዎች በየትምህርት ዓይነቱ የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች የሚመረመሩትም በዚሁ የትኞቹ ጥያቄዎች መረዳትን፣ ትግበራን፣ ትንተናን፣ ወዘተ. እንደወከሉ እየተጠና ነው፡፡ ጥያቄ ፀሐፊዎቹ አንድን ምድብ

ይመዝናሉ ብለው ባወጧቸው ጥያቄዎች ላይ ባለሙያዎቹ ካላመኑበት ደግሞ ከጥያቄ ፀሐፊዎቹ ጋር እየተነጋገሩ ጥያቄዎችን እንደገና አሻሽሎ በመጻፍ ወይም በሌላ ጥያቄ በመተካት ችግሮቹ እንዲፈቱ ይደረጋል (ኃላፊ ፪)፡፡

ለአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በተዘጋጀው ቃለመጠይቅ ጥያቄ ቁጥር ሰባት ላይ (በተለይ) የአማርኛ ቋንቋን የማጠናቀቂያ ፈተናና የሥርዓተ ትምህርቱን ተዛምዶ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁለቱም ባለሙያዎች የሰጡት ምላሽ በኃላፊዎቹ የተሰጡትን አስተያየቶች የሚያጠናክር ነው፡፡ ለምሳሌ ባለሙያ‹ለ› ስለዚሁ ጉዳይ ባስረዱበት ክፍል፡-

> ፈተናው የሚመሰረተው በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ ነው፡፡ እና ሥርዓተ ትምህርቱ ላይ የተጠቀሱ፣ የተዘረዘሩ ዓላማዎችን... መለካት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ እ... እንዲቀርቡ የሚደረገው፣ እንዲካተቱ የሚደረገው እና ሁሉም በተቻለ አቅም እንዲለኩ/ ሊለኩ የሚችሉ ዓላማዎች በፈተናዎች ይሸፈናሉ፡፡ ስለዚህ በሁለቱ መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለ ማለት ነው፤ ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ፈተናው በምርጫ ብቻ የሚቀርብ መሆኑ ሰፊ ይዘቶችን ለመሸፈን ቢረዳም በተለይ የማዳመጥ፣ የመናገርና የመጻፍ ክሂሎችን በተግባር እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩና እንዲጽፉ በማድረግ ለመመዘን እንዳይቻል ማገዱን ሁሉም የውይይቶቹ ተሳታፊዎች አንፀባርቀዋል፡፡ በተለይ ሀላፊ፪ እና ባለሙያ‘ለ’ ስለዚሁ ጉዳይ ባነሱበት ክፍል እንደገለፁት ይህን ችግር ለመፍታት ቢያንስ የመጻፍ ክሂልን በፈተናው ለማካተት በኤጀንሲው ፍላጎት እንዳለና ጽሑፍ ለማረም የሚችሉ የኮምፒውተር ሶፍትዌሮችን ማፈላለግ ላይ እንዳሉ አውስተው መፍትሄ ተገኝቶ ከምርጫ በተጨማሪ የጽሑፍ ፈተና እስኪካተት ድረስ ግን ችግሩ መቀጠሉ እንደማይቀር ገልፀዋል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የክፍል ፈተና ውጤቶች በአንዳንድ ሀገሮች እንደሚደረገው ከማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት ጋር እንዲካተቱ በማድረግ በማጠናቀቂያ ፈተናው የማይሸፈኑት ክሂሎች እንዲካተቱ ለማድረግ የማይሞክረው ለምንድን ነው? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ፣ ሁለቱ ኃላፊዎች የሰጡት መልስ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የማይካተቱ ክሂሎች በክፍል መምህራን በሚዘጋጁት ፈተናዎች የሚመዘኑ በመሆናቸው ላይ ጥርጣሬ እንዳላቸው ያሳየ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በየትምህርት ቤቶቹ የሚሰጡ ፈተናዎች የተማሪዎችን ትክክለኛ ችሎታ የሚያሳይ ውጤት ሊላክ

እንደማይችል ያምናሉ፡፡ ለምሳሌ ኃላፊ፩ ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ እንዲህ ብለዋል፤

> እኔም ...ለፖሊሲ ኮሚቴ push)[ግፊት] አድርገው የነበረው የትምህርት ቤት ውጤት የተወሰነ ፐርሰንት ይካተት ነው፡፡ የትምህርት ቤት ውጤት ሲመጣ ነበር፡፡ አንድም በየትምህርት ዓይነቱ ከ40% ወይም ከ30% አምጡ ተብሎ ሲላክ ሁሉም ሃያ ሰባት፣ ሃያ ስምንት ነው፡፡ ምክንያቱም ለዚያኛው ይጠቅማቸዋል በሚል ትምህርት ቤቶች አሻሽለው ይልካሉ እንጂ (actual) [ትክክለኛውን] የልጆችን ውጤት አይደለም፡፡ እውነቱን ለመናገር፣ እና አንዱ እሱ ነው፡፡ ሁለተኛው የትምህርት ቤቶች ፈተና አሁን የምንለውን የብሔራዊ ፈተናዎችን ድክመት የሚያሻሽል የጽሑፍ፣ የንግግር ወይም የመጻፍ ወይም የማዳመጥ ክሂሎችን የማይጠይቅ ፈተና እስከሆነ ድረስ እነሱም የሚጠቀሙት የምርጫ ፈተና እስከሆነ ድረስ የምርጫ ፈተናን እንደገና አምጥተህ ከዚህ ላይ ብትደምረው የልጆቹን ውጤት ያሻሽለው ይሆናል እንጂ ልጆቹ ለትምህርት ቤት ፈተና የሚሰጡት ክብደት ይጨምር እንደሆነ እንጂ አሁን የምንለው ይህ ብሔራዊ ፈተና የማይሸፍናቸውን ክሂሎች ሊሸፈን አይችልም፡፡

በአባሪ 13 ለዚሁ ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ መመልከት እንደሚቻለው የኃላፊ፩ ሐሳብም በኃላፊ፩ ከተገለፀው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ከዚህም አንደኛ የክፍል ምዘናዎች/ ፈተናዎች ውጤት የተጋነነ ስለሚሆን ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጋር ደምሮ በመስራት እውነተኛ የተማሪዎችን ችሎታ የሚያሳይ የምዘና ውጤት ማግኘት እንደማይቻል፣ ሁለተኛ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የማይመዘኑ ክሂሎች በመምህራን በሚዘጋጁ የክፍል ፈተናዎችም አይካተቱም የሚል ዕምነት በኤጀንሲው ኃላፊዎች እንዳለና በእነዚህ ዋና ዋና ምክንያቶች የክፍል ፈተና ውጤቶችን ከማጠናቀቂያ ፈተናዎች ውጤት ጋር ለማካተት ፍላጎት እንደሌለ የውጤት ትንተናዎቹ አሳይተዋል፡፡ በምርጫ ላይ ብቻ በመመስረቱ በማጠናቀቂያ ፈተናው የማይካተቱ የቋንቋው ክሂሎችን በመማር ማስተማር ሂደቱ ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችል ስትራቴጂ በኤጀንሲው እንዳልተካተተም እንዲሁ ከተገኘው የጥናቱ ውጤት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በእርግጥ ባለሙ.ያ‹ለ› እንዳስረዱት በማጠናቀቂያ ፈተናው በጽንሰ ሐሳብ ደረጃም ቢሆን ስለማዳመጥ፣ መናገርና መጻፍ የሚጠየቁ ጥያቄዎች አሉ፤ የእነዚህ ጥያቄዎች መኖርም የክፍል መምህራኑ የተጠቀሱትን ክሂሎች በተግባር ጭምር ትኩረት ሰጥተው

እንዲያስተምሩ ይገፋፋሉ/ ያበረታታሉ ተብሎ ይታመናል ፡፡ ለምሳሌ ስለዚሁ ጉዳይ ባነሱበት ክፍል ባለሙያ “ለ” የሚከተለውን ተናግረዋል፤

> በተቻለ አቅም ስለድርሰት ካነሳን ከጽሕፈት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚያ ውስጥ የዕውቀት ዶሜን እንትን ሊያደርግ ይችላል፡፡ ትግበራ ነው? ኮምፕሬሽን [መረዳት] ነው? ምና ምን የሚለው እንትን ሊል ይችላል፡፡ ግን ጽሕፈት ነው፡፡ ከጽሕፈት ጋር የምታነሳው ጽሕፈት ውስጥ የሚጠቃለል ነው፡፡ ስለዚህ ጽሕፈት በቀጥታ አይፈተኑም ግን በተዘዋዋሪ መንገድ ይጠየቃሉ፡፡ ...ስለሕይወት ታሪክ ብንጠይቅም እንደዚያ ነው፤ ስለቃለ ጉባኤ ከሌሎች ፅሑፎች ጋር እያነፃፀረ፣ ወይም ቃለ ጉባኤ ምንድን ነው የሚያካትታቸው ነገሮች ዓይነት ጥያቄ ቢቀርብ ያው ስለ ቃለጉባኤ ግንዛቤ ይኖረዋል ማለት ነው፤ እና የሚጽፍ ቢሆን ቅርፁን ጠብቆ ሊጽፍ ይችላል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ንግግር፣ ማዳመጥና ጽሕፈት በቀጥታ አይኑሩ እንጂ በተዘዋዋሪ አሉ... እና ተሸፍነዋል ማለት ይቻላል፡፡ አሁን ለምሳሌ ስለክርክር ብታነሳ አንድ ተከራካሪ /በክርክር የሚሳተፍ ወይም የክርክር አዳማጭ ወይም ተከራካሪ ምንድነው ማድረግ ያለበት? የሚል ዓይነት ከዚያ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ቢቀርቡ እነዚያን ነገሮች ተማሪው ተገንዝቧል ማለት ነው፤ እና ወደፊት ተከራካሪ ቢሆን እነዚያን ነገሮች ጠብቆ ነው፣ ተራ መጠበቅ እንዳለበት ‹ኢንሰልት› ማድረግ [መሳደብ] እንደሌለበት እንዲህ እንዲህ ዓይነት ነገሮችን የሚያውቅ ከሆነ ከሞላ ጎደል ተከራካሪ መሆን ይችላል፡፡

በማጠናቀቂያ ፈተናው በጽሑፍ የሚመለሱ /የመጻፍ ክሂልን የሚመዝኑ ጥያቄዎች መካተት እስኪችሉ ድረስም መምህራን በክፍል ምዘናዎቻቸው በማጠናቀቂያ ፈተናው የማይካተቱትን ክፍሎች እያካተቱ ክፍተቱን በመሙላት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እንደሚገባቸው ባለሙያዎቹ ያምናሉ፡፡ ለምሳሌ ባለሙያ‹ለ› ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፤

> ይህን... መምህራኑ በሚያደርጉት ነገር ማስተካከል ይቻላል፡፡ ለጊዜው ፈተናው ወደዚያ እስከሚሄድ ድረስ እና በተቻለ አቅም መምህራን ምዘናዎቻቸውን እነዚህን ነገሮች ያካተቱ እንዲሆኑ፣ እንዲጽፍ ወይም እንዲናገር በተለያዩ አክቲቪቲዎች [ተግባሮች] ሊሆን ይችላል፣ በየጊዜው በሚሰጧቸው ኮንቲኔስ አሰስመንቶች [ተከታታይ ምዘናዎች] ሊሆን ይችላል፣ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቻቸው ሊሆን ይችላል፣ እና ከዚያ እንደዚህ የሚደረግ ከሆነ ምናልባት ይህን ችግር የፈተናውን ድክመት ማለት ነው ... እንደዚህ አድርጎ ማቃለል የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ ከዚያ አካባቢ እንዲህ ያለ ስራ መሰራት አለበት፡፡

ባጠቃላይ በዚህ የትምህርቱንና የፈተናውን ተዛምዶ በሚመለከተው ክፍል ከኤጀንሲው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ማብራሪያ መረዳት የተቻለው፣ አንደኛ፣ በሁለቱ መካከል

አዎንታዊ ተዛምዶ እንዲኖር ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል። ሁለተኛ፣ በማጠናቀቂያ ፈተናው አንዳንድ የቋንቋውን ክሂሎች በቀጥታ ለመመዘን ባይቻልም፣ በBrown (2004) እንደተገለፀው፣ በተዘዋዋሪ/ኢርቱዕ በሆነ መንገድ በፈተናው እንዲሸፈኑ እየተደረገ ነው የሚል እምነት አለ። ሦስተኛ፣ የቋንቋ ክሂሎችን በተለይም ማዳመጥን፣ መናገርንና መፃፍን በምርጫ ጥያቄ መመዘኑ በቂና ተገቢ ነው ተብሎ በአንዳንዶቹ የኤጀንሲው ኃላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች አይታመንም። አራተኛ የማጠናቀቂያ ፈተናው በምርጫ በሚመለሱ ጥያቄዎች ላይ ብቻ የተመሠረተ ማለትም ፈተናው ተማሪዎች የማዳመጥ፣ ድርሰት የመጻፍና የመናገር ብቃታቸውን በክወና (በተግባር) እንዲያሳዩ የሚያስገድድ ባለመሆኑ፣ እነዚህ መመዘን ያልቻሉ የቋንቋው ክሂሎች የክፍል መምህራን በክፍል ትምህርቱ ትኩረት ሊሰጧቸውና በተለያየ መንገድ በምዘናዎቻቸው ሊያካትቷቸው (በተግባር ሊመዝኗቸው) ይገባል የሚል ግንዛቤ አለ። ከዚህም እንዲህ ያለው ችግሩ በኤጀንሲው ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ወገኖች/ ክፍሎች ተሳትፎ ጭምር ሊፈታ ይገባዋል የሚል አስተሳሰብ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል።

ይህን ክፍል ለማጠቃለል፣ 'የሀገሪቱን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ያደረጉ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች የማዘጋጀትና የማስተዳደር...፣ ምዘናና ጥናትና ምርምር በማካሄድ ለባለድርሻ አካላት ግብረ-መልስ በመስጠት ተግባሩን ይወጣል፤' በሚል ተልዕኮና 'ለፈተናና ምዘና ጥራት ቅድሚያ እንሰጣለን'፤ በሚልና ሌሎችም እሴቶች (የአሰራር ፍልስፍና) የሚመራው የፈተናዎች ኤጀንሲ በተልዕኮውና በእሴቶቹ መሠረት፣ የሚያዘጋጃቸውን ሀገር አቀፍ ፈተናዎች በተለይ ደግሞ የአማርኛን የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ታላሚ ተፈታኞችን የመመዘን ደረጃቸውንና አዎንታዊ ተጽዕኖቸውን ከፍ ለማድረግ የሚያግዙ የተለያዩ ስትራቴጂዎችን እንደሚጠቀም የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

ከስትራቴጂዎቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ፣ አንደኛ፣ በየትምህርት ዓይነቱ የተሻለ አቅም ያላቸውን የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎችና ጥያቄ ጸሐፊዎች/ አዘጋጆች ለማግኘት የሚያስችሉ የምልመላ መስፈርቶችን መጠቀም፣ ሁለተኛ፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር የፈተናና ምዘና ባለሙያዎችን በተለያየ ጊዜ በመጋበዝ የኤጀንሲው የፈተና

ዝግጅት ባለሙያዎች ስለፈተና አዘገጃጀት፣ አስተዳደርና አስተራረም ተከታታይ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ ማድረግ፣ ሦስተኛ፣ በኤጀንሲው ተልዕኮ ላይ በተገለጸው መሰረት በየክልሉ የሚማሩ ተማሪዎችን ተወዳዳሪ ለማድረግ ለክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎች የተማሪዎቻቸውን የውጤት ትንተናና በየትምህርት ዓይነቱ የሚገኙበትን ደረጃ የሚሳይ ግብረ-መልስ በመስጠት ለመማር-ማስተማሩ ሂደት የተሻለ ትኩረት እንዲሰጡ ማነቃቃትና አራተኛ፣ በዓመቱ የሚዘጋጁት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ ፈተና ባህርያት ላይ የተመሰረቱና አዎንታዊ ወሽባክን ታሳቢ ያደረጉ(ያለሙ) እንዲሆኑ ማድረግ፤ ይህንም ለማሳካት ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ የሥርዓተ ትምህርቶቹ ዓላማዎች ነጸብራቅ፣ ወይም በመርሐ ትምህርቶቹና በመማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፎቹ የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ እንዲሆኑ ማድረግ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ስትራቴጂዎች በአብዛኛው በወሽባክ ድርሳናት (ለምሳሌ በGreen 2007፣ Hughes 2003 እና Wall 2006) ከቀረቡ የአዎንታዊ ወሽባክ ማነልበቻ ጽንሰ ሀሳቦች ጋር የሚዛመዱ ናቸው፡፡ በጥናቱ በመረጃ መንጭነት የተሳተፉት ኃላፊዎችና ባልሙያዎች እንደሚታመነው እነዚህ ስትራቴጂዎች በመማር-ማስተማር ሂደቶች የሥርዓተ ትምህርቶቹን ዋና ዋና ክፍሎች መምህራኑ ትኩረት ሰጥተው እንዲያስተምሩ፣ ተማሪዎቹ ደግሞ ትኩረት ሰጥተው እንዲማሩ/ እንዲከታተሉ የሚያደርጉ/ የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ በጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚታመነው ስትራቴጂዎቹ በእርግጥ የታሰበውን ውጤት እያስገኙ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ደግሞ በቀጣዮቹ የጥናቱ ክፍሎች ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በአጠቃላይ የቋንቋን በተለይ ደግሞ የአማርኛ ማጠናቀቂያ ፈተናን በተመለከተ በምርጫ ብቻ የሚዘጋጅ መሆኑ በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ፤ ከአሉታዊ ተጽዕኖዎች መካከልም ዋነኛው መምህራንና ተማሪዎች በፈተናው የማይካተቱ የመጻፍ፣ የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎችን በክፍል ትምህርቱ ችላ እንዲሏቸው ሊያደርግ የሚችል መሆኑ እንደሆነ ከተሳታፊዎች የተገኘው መረጃ ውጤት ትንተና አሳይቷል፡፡ ይህም በቀጣዮቹ ክፍሎች ትኩረት ተሰጥቶት የተፈተሸ ጉዳይ ነው፡፡

4.3 የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ከአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) የትምህርት ባህርያዊ ዓላማዎች፣ ከቋንቋው ትምህርት ዓላማዎችና ከክፍል ፈተናዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት (Overlapping) ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በምዕራፍ ሁለትና ሦስት እንደተገለፀው አንደኛ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጥያቄዎችና በአዕምሯዊ ምድብ □ትምህርት ባህርያዊ ዓላማዎች፣ ሁለተኛ በፈታዎቹ ጥያቄዎችና በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርቶች ዓላማዎች መካከል ያለውን ተጣጥሞሽ የባለሙያዎችን ዳኝነት (experts judgment) በመጠቀም ተፈትሿል፡፡ የክፍል ፈተናዎች ከመርሐ ትምህርቶቹና ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነትም ተመርምሯል፡፡ በመሆኑም፣ በዚህ ክፍል መጀመሪያ ፈተናዎቹ ከአዕምሯዊ ምድብ ስድስት የትምህርት ባህርያዊ ዓላማዎች ጋር ያላቸው ተጣጥሞሽ የውጤት ትንተናና ማብራሪያ ይቀርባል፡፡ ቀጥሎ በመርሐ ትምህርቶቹ የተካተቱት አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ተተ᎓ትነውና ተብራርተው ይቀርባሉ፡፡ ከዚያም በባለሙያዎቹ ለጥናቱ የተመረጡትን እ.ኤ.አ. ከ2000-2004 ዓ.ም የተዘጋጁ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና (90*5) 450 ጥያቄዎች ከቋንቋው ትምህርት መርሐ ትምህርቶች ከወጡ የትምህርቱ ዓላማዎች ጋር ያዛመዱበት የውጤት ትንተናና ማብራሪያ ይከተላል፡፡ በአራተኛ ደረጃ ስለፈተናዎቹና የቋንቋው ትምህርት ተዛምዶ መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ በሚመለከት በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ከመምህራን የተሰበሰበው መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ይከተላል፡፡' በመጨረሻው ክፍል ደግሞ በ2004 እና በ2005 ዓ.ም. በመምህራን የተዘጋጁት የአንደኛና የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት የክፍል ፈተናዎች ትንተናና ከመርሐ ትምህርቶቹና ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል የሚያሳየው የውጤት ትንተናና ማብራሪያ ይቀርባል፡፡

4.3.1 የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎችና የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ተዛምዶ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ይህ ክፍል "የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) የትምህርት ባሕርያዊ

ዓላማዎች ጋር ይዛመዳሉ/ አዎንታዊ ተዛምዶ አላቸው? የሚለውን ጥያቄ በሚመለከት የተሰበሰው መረጃ ተተንትኖና ውጤቱ ተብራርቶ የቀረበበት ነው።

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች የሚባሉት ዕውቀት፣ ግንዛቤ፣ ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ በመባል የሚጠሩት የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃዎች ናቸው። በኢትዮጵያም በፖሊሲና በፖሊሲ ማስፈፀሚያ ሰነድ ደረጃ እነዚህ ጉዳዮች ከፍተኛ ቦታ እንዳገኙ ተረጋግጧል። በፖሊሲ ሰነዶች ብቻ ሳይሆን በክፍል ውስጥ የመማር- ማስተማር ሂደትም በተግባር ሲተገበሩ መታየትም ይኖርባቸዋል። በመማር-ማስተማር ሂደቶቹ የሚፈለጉት ለውጦች መምጣትና አለመምጣታቸው የሚፈተሸው ደግሞ በክፍልና በብሔራዊ ደረጃ በሚካሄዱ ምዘናዎች ነው። የዚህ ጥናት አንዱ ትኩረትም ይኸው የአዕምሯዊ ምድብ ትምህርት ዓላማዎች በመባል የሚታወቁት ስድስት ክፍሎች/ የችሎታ ደረጃዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ተገቢ ውክልና ያገኛሉ? የሚለውን ጥያቄ መፈተሽ ነው። ይህን ጥያቄ ለመመለስም የሦስት ተከታታይ ዓመታት (እ.አ.አ. ከ2002-2004 ዓ.ም የተዘጋጁት) የማጠናቀቂያ ፈተናው 270 (90*3) ጥያቄዎች በአራት የሥነ-ትምህርት ባለሙያዎች በእነዚህ ስድስት ክፍሎች እንዲመደቡ ተደርገዋል። የምደባው ውጤትም በሰንጠረዥ 4.1 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 4.1፣ የፈተና ጥያቄዎች ስርጭት ከአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች አንፃር ጠቅላላ ድምር በቁጥርና በመቶኛ ስሌት

የአዕምሯዊ ምድብ ደረጃዎች	ዓመተ ምሕረት							
	2002		2003		2004		ድምር	
	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%	ብዛት	%
ዕውቀት	27	30	25	27.77	14	15.58	66	24.44
ግንዛቤ	57	63.33	55	61.11	68	75.55	180	66.67
ትግበራ	4	4.4	5	5.55	5	5.55	14	5.18
ትንተና	-	-	5	5.55	2	2.22	7	2.53
ቅንበራ	2	2.2	-	-	1	1.11	3	1.11
ግምገማ	-	-	-	-	-	-	-	-
ድምር	90	100	90	100	90	100	270	100

ከላይ በሰንጠረዥ 4.1 የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው በ2002 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ግንዛቤ (comprehension) በ63.33%፣ ዕውቀት (knowledge) በ30%፣ ትግበራ በ4.44%፣ ቅንበራ በ2.2% ተወክለዋል። ትንተናና ግምገማ በአንድም ጥያቄ አልተወከሉም። በ2003 ዓ.ም. በተመሳሳይ ሁኔታ ግንዛቤ በ61.11%፣ በጥያቄ ብዛት አንደኛ፣ ዕውቀት 27.27%፣ ሁለተኛ እንደሆኑ ቀጥለዋል። ትግበራና ትንተና በተመሳሳይ የጥያቄ ብዛት በ5.55% ተወክለው ልዩነቱ ሰፊ ቢሆንም የሦስተኛነትን ደረጃ ይዘዋል። ቅንበራና ግምገማ በአንድም ጥያቄ አልተወከሉም። በ2004 ዓ.ም. ደግሞ እንዲሁ ግንዛቤ ከቀዳሚዎቹ ዓመታት ከፍ ባለ የጥያቄ ቁጥር በ68 ጥያቄ በ75.55% በቀዳሚነት ደረጃ ላይ ሲገኝ ዕውቀት ከአንደኛው በከፍተኛ ፐርሰንት ስሌት አንሶ በ15.55% አሁንም በሁለተኛነት ይከተላል። ትግበራ ከቀዳሚው ዓመት ጋር ተመሳሳይ በሆነ የጥያቄ ብዛት በ5.55% ሦስተኛነቱን እንደያዘ ቀጥሏል። ትንተና በ2.22% በአራተኛ ደረጃ ላይ ሲገኝ፣ ቅንበራ በ1.11% በመወከል የመጨረሻውን ደረጃ ይዟል። ግምገማ በዚህም ዓመት በአንድም ጥያቄ አልተወከለም።

የሦስቱ ዓመታት ድምርና አማካይ ሲታይም ተመሳሳይ መልክ ይታይበታል። ማለትም ግንዛቤ በከፍተኛ ፐርሰንት (66.67%) ሲወከል እውቀት በ24.44% በርቀት በሁለተኛ ደረጃነት ይከተላል። ትግበራ በ14 ጥያቄ በ5.14% ሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በሰባት ጥያቄ በ2.53% በመወከል በአራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ደግሞ ትንተና ነው። ቅንበራ በሦስት ጥያቄ በ1.11% የመጨረሻውን ደረጃ ይዟል። ግምገማ በየትኛው ዓመት ፈተና ጥያቄዎች በአንድም ጥያቄ ያልተወከለ ክፍል ነው።

የየዓመቱም ሆነ በጥናቱ የተካተቱት የሦስት ዓመታት ጥያቄዎች ድምርና አማካይ ትንተና ውጤት የሚያሳየው ሰፊ ሽፋን በማግኘት (በብዙ ጥያቄዎች በመወከል) የአንደኛነትን ደረጃ የያዘው ግንዛቤ ሲሆን ሁለተኛው ዕውቀት ነው። በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውና በሥርዓተ ትምህርት ማስተግበሪያ ማዕቀፉ ቁልፍ ብቃቶች (Competencies) ፤ በቋንቋው ትምህርት ዓላማዎችም ልዩ ትኩረት የተሰጣቸውና ለBloom (1956) አዕምሯዊ ምድብ ስድስት ክፍሎች መዳበር ምክንያት የሆኑት የቀሩት አራት ክፍሎች /ችሎታዎች/ በፈተናዎቹ ያገኙት ሽፋን በጣም ዝቅተኛ ነው

የሚባል ብቻ ሳይሆን ተዘንግተዋል ለማለት የሚያስደፍር ነው። የየክፍሎቹን የሦስት ዓመታት ድምርና አማካይ የያዘው የሰንጠረዡ የመጨረሻ ክፍል እንደሚያሳየው ትግበራ በ5.18%፣ ትንተና በ2.53%፣ ቅንበራ በ1.11% ብቻ ተወክለዋል። በውስብስብነት ደረጃው ስድስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ግምገማ ደግሞ በየትኛውም ዓመት በአንድም ጥያቄ የመወከል አጋጣሚ ያላገኘ ነው። ዝቅተኛና ከፍተኛ የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃ እየተባለ ከሚካሄደው ባለሁለት ክፍል አመዳደብ አንፃር ሲታይም በዝቅተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታነት የሚመደቡት ዕውቀትና ግንዛቤ በ246 ጥያቄ ወይም በ91.11% ሲወከሉ በከፍተኛ የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃነት የሚመደቡትና በሀገሪቱ የጆሊሲ ሰነዶች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ትግበራ፣ ትንተናና ቅንበራ ደግሞ በ24 ጥያቄ /በ8.88% ብቻ ተወክለዋል። ግምገማ በአንድም ጥያቄ አለመወከሉ ቀደም ብሎ ተገልጿል። ይህም በድርሳናት ክልሳ ክፍል ከተነሱት የፈተና ዝግጅቱ ከሽፋንም ሆነ ከተገቢነት ወይም ከተመጣጣኝ ውክልና አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ችግር እንዳለበት ያሳያል።

4.3.2 በዘጠነኛና በ10ኛ ክፍል መርሐ ትምህርቶች የተካተቱ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችና የተመደበላቸው ክፍለ ጊዜ መጠን ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በመርሐ ትምህርቶቹ (በመማሪያ መጽሐፎቹ ውስጥም ይገኛሉ) የተካተቱት አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ስድስት ሲሆኑ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፤

ተማሪዎች፤

1. የማዳመጥ ክሂላቸውን አዳብረው የተረዱትን ይገልፃሉ።
2. የመናገር ክሂላቸውን አዳብረው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ንግግር ያደርጋሉ።
3. የንባብ ክሂላቸውን አዳብረው የተረዱትን በተለያየ መልኩ ይገለፃሉ።
4. የጽሕፈት ክሂላቸውን አዳብረው ሃሳባቸውን ተነባቢ በሆነና በሚስብ ጽሑፍ ያስተላልፋሉ።

5. ስለፈጠራ ጽሑፍ ዘርፎች በመረዳት ሀሳባቸውን ሥነ-ጽሑፋዊ በሆነ መልኩ ይገልፃሉ፡፡ የሚያነቡትንም ሆነ የሚያዳምጡትን ሂሳዊ በሆነ መንገድ በመመልከት የመግለፅ ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡
6. የአማርኛ ሰዋስው ዕውቀታቸውን ያጎለብታሉ (የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት 1996)፡፡

(ከዚህ በታች የቀረበው (ሰንጠረዝ 4.2) በመርሐ ትምህርቶቹ የተካተቱ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችን የሚያሳይ ነው፡፡ ቁጥሮቹም በመርሐ ትምህርቶች ውስጥ ለክሂሎቹ የተመደበውን ክፍል ጊዜ ብዛት ድምርና የድምሩን መቶኛ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ መቶኛው የተሰላውም ለክሂሉ የተመደበለት ክፍለ ገዜ ብዛት ለጠቅላላ ክፍለ ጊዜ/ ለ147 ተካፍሎና በመቶ ተባዝቶ ነው፡፡)

ሰንጠረዥ 4.2፣ በ9ኛና 10ኛ ክፍል መርሐ ትምህርቶች የቀረቡ ዓጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችና የተመደበላቸው የክፍለ ጊዜያት መጠን በቁጥርና በመቶኛ

ተራ ቁጥር	የትምህርቱ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች	በ9ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት	በ10ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት የተመደበለት ክፍለጊዜ ብዛት	ለሁለቱ ክፍሎች የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት ድምር	%
1.	*የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች ማዳበርን በተመለከተ (የተመደበለት ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ)*	13	17	30	20.83
1.1	በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ጭውውቶችን ማካሄድ፣		2	2	1.36
1.2	በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ውይይቶችን ማካሄድ፣	2	2	4	2.78
1.3	አካባቢያዊ፣ ወቅታዊና አገራዊ ጉዳዮች ላይ በቂ መረጃዎችን ከልዩ ልዩ ምንጮች አሰባስቦ ክርክር ማካሄድ፣		3	3	2.08
1.4	በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች መልዕክትን ግልፅ የሚያደርጉ የድምፅና የአካል እንቅስቃሴዎችን... በመጠቀም የዱብዳ ንግግር ማድረግ፣		3	3	2.08
1.5	በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዝግጅት በማድረግና መልዕክትን ግልፅ የሚያደርጉ የድምፅ እና የአካል እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር ማድረግ፣		3	3	2.08
1.6	በተወሰነ ርዕስ ንግግር ማድረግ	4		4	2.78
1.7	ሌላ(ከላይ ያልተጠቀሰ የማዳመጥና የመናገር ክሂል)	7	4	11	7.64
2.	*የንባብ ክሂልን ማዳበር (የተመደበለት ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ)*	14	11	25	17.00
2.1	በፅሁፍ የቀረቡ ሀሳቦችን ሀቅና የግል አስተያየት እያሉ መለየት፣		1	1	0.69
2.2	በፅሁፍ የቀረቡ ሀሳቦችን መንስኤ(ምክንያት) እና ውጤት መለየት፣	1	-	1	0.69

2.3	በሚነበብ ፅሁፍ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋናና ጠቃሚ ዝርዝር ሀሳቦችን መለየት	3	1	4	2.78
24	በተለያዩ ጽሁፎች ውስጥ የሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላት በአገባባቸው መነሻነት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን መስጠት	3		3	2.08
2.5	በግርፍ ንባብ (Skimming) የአንድን ፅሁፍ አጠቃላይ ሀሳብ መረዳት፣	1	-	1	0.69
2..6	መተንበይ ማለትም ቀጣይ ሀሳብን /ይዘትን ከንባብ በፊትና በንባብ ጊዜ መገመት		1	1	0.69
2.7	ከልዩ ልዩ መግለጫዎች (ከስዕል፣ ከሰንጠረዥ...) መረጃዎችን ማግኘት፣	1	2	3	2.08
2.7	ነባር ዕውቀትን ከሚነበበው ጋር ማስተሳሰር፣		1	1	0.69
2.8	በአንድ ፅሁፍ ውስጥ በግልፅና በውስጠ ታዋቂነት የቀረቡ ሀሳቦችን መረዳት፣	1		1	0.69
2.9	እንድምታ ንባብ፣ ማለትም በግልፅ ያልሰፈሩ ሀሳቦችንና መረጃዎችን መረዳት፣		1	1	0.69
2.10	ከጽሑፉ ሀሳብና ከግል ልምድ በመነሳት ድምዳሜ ላይ መድረስ		1	1	0.69
2.11	ማጠቃለል / በፅሁፉ ዋና ዋና ሀሳቦች ላይ በመመርኮዝ ማጠቃለል፣		1	1	0.69
2.12	ያነበቡትን ፅሁፍ አስተዋፅኦ አሟልቶ ማቅረብ፣	1		1	0.69
2.13	ሌላ (ከላይ ያልተጠቀሰ የንባብ ክሂል)	3	2	5	3.47
3	***የመጻፍ ክሂሂልን ማዳበር (የተመደበለት ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ)***	21	20	41	28.47
3.1.	ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው ማስገባት/ መጠቀም፣	1	2	3	2.08
3.2	ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን በመገልገልና የአንቀጽ አጻጻፍ መርህን በመከተል የተለያዩ (ተራኪ፣ አወዳዳሪ፣ ገላጭ ...) አንቀፆችን መፃፍ፣	3	4	7	4.86
3.3.	የተለያዩ የስራና ንግድ ነክ ደብዳቤዎችን መፃፍ	3	3	6	4.17
3.4	በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ዘገባ መፃፍ ፣	1	2	3	2.08
3.5	ማርቀቅ፣ረቂቁን ማረም ፣ መከለስና የድርሰቱን ዋና ፅሁፍ መፃፍ ፣		6	6	4.17
3.6	ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ተገልግሎ መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ ያላቸው የተለያዩ (ተራኪ፣ ስዕላዊ፣ ገላጭና አመዛዛኝ) ድርሰቶች መጻፍ፣	4		4	2.78
3.7	የአንድን ፅሑፍ ወይም ንግግር መልዕክት ሳያዛቡ አሳጥሮና አስፋፍቶ በራስ አባባል መፃፍ፣	2		2	1.36
3.8	ግለ ታሪክ መፃፍ (የራስን ወይም የሌላን ሰው)፣	2		2	1.36
3.9	ከተለያዩ ንግግሮችና ፅሑፎች የሚገኙ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ፣	2	2	4	2.78
3.10	ቃለ ጉባኤ መያዝ / መጻፍ(በስብሰባዎች)፣	2		2	1.36
	ሌላ (ከላይ ያልተጠቀሰ የጽሕፈት ክሂል)	1	1	2	1.36
4	***የሰዋሰው ዕውቀትን ማጎልበት(የተመደበለት ጠቅላላ ክ/ጊዜ)***	15	7	22	15.28
4.1	የቋንቋ መሰረታዊ ሀሳቦች(ምንነት፣ አጀማመርና ባህሪያት)	2	2	4	2.78
4.2	ነባና ጥገኛ ምዕላዶችን (ቅጥያዎችን) ማውጣት፣		2	2	1.36
4.3	የሚጠብቁና የሚላሉ ድምፆችን መለየት፣	2		2	1.36
4.4	የቃላት ቅርፅን በመደብ፣ በያታና በቁጥር መለየት፣	2		2	1.36
4.5	ገላጮችን (የስምና የግስ) መለየት፣	1		1	0.69
4.6	የአማርኛ ቃላት ክፍሎችን (ስም፣ ቅጽል፣ ግስ...) መለየት፣	1		1	0.69
4.7	የሀረግ አይነቶችን (ቅፅላዊ፣ ስማዊ፣ መስተዋድዳዊ፣ ተውሳክ ግሳዊ፣ ግሳዊ) መለየት፣	1	3	4	2.78

4.8	ተራና ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን መለየት ፣	2		2	1.36
4.9	በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ ያሉ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጎችን መለየትና ተግባራቸውን መግለፅ፣፣	2	-	2	1.36
4.10	ለቃላትና ሀረጎች ተመሳሳይና ተቃራኒያቸውን (እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች) መስጠት፣	2	-	2	1.36
5	***ሐሳብን ስነ-ፅሁፋዊ በሆነ መልክ መግለፅ (የተመደበለት ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ)***	12	17	29	20.14
5.1	የፈጠራ ስነ-ፅሁፍ ዘርፎችን (ስነ-ቃል፣ ግጥም፣ ልቦለድ፣ ድራማ) መለየት፣	2	3	5	3.47
5.2	የሥነ-ቃል አይነቶችንና ባህሪያትን መለየት ፣	2		2	1.39
5.3.	በምሳሌያዊ ንግግሮች የሚቀርቡ አስተያየቶችንና ልምዶችን መረዳትና የራስን ንግግርና ፅሁፍ በምሳሌያዊ ንግግሮች አጉልቶ ማቅረብ፣		2	2	1.36
5.4	በአካባቢያቸው የሚነገሩ የፍቅርና የስራ ቃል ግጥሞች አሰባስቦ ማቅረብ፣	-	2	2	1.36
5.5	የግጥም ባህርያትን መግለፅ፣	2	-	2	1.36
5.6	የግጥም ስልቶችን ከምጣኔና ከምት አንፃር መለየት፣		2	2	1.36
5.7	ግጥምን ወደዝርው ፅሁፍ መለወጥ፣	-	1	1	0.69
5.8	የፈሊጣዊ ንግግሮችን መልዕክት መረዳት፣	2	1	3	2.08
5.9	በተለያዩ ዘይቤዎች (በአነፃፃሪ፣ ተለዋጭ፣ ሰውኛ፣ ግነት...) የቀረቡ አባባሎችን/ ሀሳቦችን መረዳት ፣	1	2	3	2.08
5.10	የተለያዩ ዘይቤዎችን በመጠቀም ሀሳብን በንግግርና በፅሁፍ አጉልቶ ማቅረብ፣	-	1	1	0.69
5.11	የልቦለድ አይነቶችን፣ አሳባውያንና ቴክኒኮችን መለየት፣	2	3	5	3.47
5.12	ረጅምና አጭር ልቦለዶችንና ድራማዎችን በማንበብ ባህሪያቸውን መግለፅ፣	1		1	0.69

በሰንጠረዥ 4.2 እንደተመለከተው እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካትም በሁለቱ የትምህርት ደረጃዎች ((9ነኛና 10ኛ ክፍሎች) በጥቅሉ፣ ለመጻፍ ክሂል 41(28.47%)፣ ለሥነጽሑፍ 29(20%)፣ ለንባብ ክሂል 25(17.36%)፣ ለሰዋስው 22(15.27%) እና ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች 30 (20.8%) ክፍለ ጊዜያት ተመድቧል፡፡ ለክሂሎቹና በተለምዶ የፅውቀት ዘርፎች ለሚባሉት (ለሰዋሰውና ለሥነ-ጽሑፍ) የትምህርቱ ክፍሎች የተመደበው ጊዜ ሲነጻጸር ደግሞ ከሰንጠረዥ 4.2 ማስተዋል እንደሚቻለው ከጠቅላላው 147 ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ለአራቱ ክሂሎች 96 (65%) ለእውቀት ዘርፎች ደግሞ 51 (34.69%) ክፍለ ጊዜያት ተመድቦላቸዋል፤ (የአማርኛ መርሐ ትምህርቶች 1996)፡፡ ከዚህም በመርሐ ትምህርቶቹ ሰፊ ሽፋን የተሰጠው ከዕውቀት ዘርፎች ይልቅ ለቋንቋ አጠቃቀም ወይም ለቋንቋው ክሂሎች እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም መርሐ ትምህርቶቹ በድርሳናት ክለሳ ክፍል እንደቀረበው ለተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት ትኩረት በመስጠት እንደተዘጋጁ የሚያሳይ ነው፡፡ የትምህርት ፖሊሲውና

የሥርዓተ ትምህርቱ ማስፈጸሚያ ማዕቀፍም ይህንኑ የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ በሥነ-ጽሑፍ ዓላማነት የቀረበውንና የተሰጠውን ማብራሪያ ልብ ብሎ ለሚያስተውል ደግሞ ከዕውቀት /የሥነ-ጽሑፍ ጽንሰ ሀሳብ ትምህርትነቱ ይልቅ ክሂልነቱ ይጎላል፡፡ በተለይም ወደ ሂሳዊ ንባብ፣ ወደሂሳዊ ንግግርና ወደ ሂሳዊ አጻጻፍ ክሂሎች የሚያተኩር ዓላማ ነው፡፡ በቋንቋው ክሂሎች መካከል ያለው የትኩረት ደረጃ ልዩነት ሲታይ ደግሞ ሰፊ ቦታ የተሰጠው ለመጻፍ ክሂል ነው፡፡ የንባብ ክሂል በሁለተኛ ደረጃነት ይከተላል፡፡ ለንግግርና ማዳመጥ ክሂሎች የተመደበላቸው የክፍለ ጊዜ መጠን እኩል ለሁለት ቢካፈል እንኳ አስራ አምስት አስራ አምስት ክፍለ ጊዜ ስለሚደርሳቸው በመርሐ ትምህርቶቹ የተሰጣቸው ትኩረት ዝቅ ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ለእነዚህ ክሂሎች የተመረጡላቸው ይዘቶችም በአብዛኛው ጭውውት፣ ውይይት፣ ክርክር የሚሉ ዓይነቶች ስለሆኑ በመርሐ ትምህርቶቹ በአብዛኛው ተጣምረው እንዲቀርቡ ነው የተደረጉት፡፡ በተለይ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አንጻር ሲታይም (ታስቦበት የተደረገ ከሆነ) ለእነዚህ ሁለት ክሂሎች የተመደበው ጊዜ አነስተኛ እንዲሆን መደረጉ አግባብነት ወይም ተጠየቃዊነት ያለው ይመስላል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ክሂሎች ተማሪዎቹ ገና ትምህርት ቤት ሳይገቡ ያዳበሯቸው ብቻ ሳይሆኑ ከቋንቋው ተናገሪ ማህበረሰብ ጋር በመኖርም በቀላሉ ሊያዳብሯቸውም ይችላሉ፡፡ የመጻፍና የንባብ ክሂሎች ግን በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ በትምህርት የሚዳብሩ ናቸው፡፡ በተማሪዎች በወደፊት የስራ ሕይወታቸው ለተለያየ ዓላማ ይጠቀሙባቸዋል ተብለው ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ለእነዚህ ሁለት ክሂሎች ሰፋ ያለ ጊዜ መሰጠቱ አግባብነት ያለው ይመስላል፡፡ በተለይ ደግሞ ለመጻፍ ክሂል የተሻለ ጊዜ መመደቡ ጥሩ ጸሐፊ ለመሆን ሰፋ ያለ ጊዜና ብዙ ልምምድ ያስፈልጋል ተብሎ ታልሞ የተደረገ ስለሚመስል ተገቢነት ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ቋንቋውን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩት ተማሪዎችም ቋንቋው በብዙ ቦታ ስለሚነገር እነሱም በማዳመጥና በመናገር ክሂሎች በኩል በተወሰነ ደረጃ ችሎታው ይኖራቸዋል፤ በሚል አስተሳሰብ ክሂሎቹ ችላ እንዲባሉ ተደርጎ ከሆነ ግን ተገቢነቱ አከራካሪ ነው፤ በጥናት ሊደገፍ ይገባዋል፡፡ በሳምንት ፪ ክፍለ ጊዜ ለተመደበለት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ግን ሁሉንም ክሂሎች በአግባቡ ለማስተማር ከሚኖረው የጊዜ እጥረት

አንጻር የግድ ለተወሰኑ በጣም አስፈላጊ ክሂሎች የተለየ ትኩረት መሰጠት ተገቢ መስሎ ይታያል፡፡

4.3.3 የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና የመርሐ ትምህርቶቹ ዓላማዎች ተጣጥሞሽ/ ተዛምዶ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል መጀመሪያ ፪ኛ ዲግሪያቸውን አማርኛ በማስተማር የሰሩ የኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እ.ኢ.አ. ከ2000-2004 ዓ.ም. የተዘጋጁትን የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎች በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርቶች ከተካተቱት ዓላማዎች ጋር ያዛመዱት፤ ቀጥሎ ከመምህራን ጋር በተካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተገኙ ውጤቶች ትንተናና ማብራሪያ ይቀርባል፡፡

4.3.3.1. በባለሙያዎቹ የተካሄደ የፈተናዎቹ ጥያቄዎችና የትምህርቱ ዓላማዎች ተዛምዶ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ሰንጠረዥ 4.3 እንደሚያሳየው በባለሙያዎቹ በተካሄደው የጋራ ምደባ 30 (6.67%) **የማዳመጥና የመናገር፣** '100 (22.22%) **የንባብ፣** 100 (22.22%) **የመጻፍ** ክሂል ንዑሳን ክሂሎችን፣ እንዲሁም 109 (24.22%) **የሰዋስው፣** 111 24.67%) **የሥነጽሑፍ** ክፍሎችን የሚመዝኑ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ሰንጠረዥ 4.3፣ ባለሙያዎች /Lecturers እ.ኢ.አ. ከ2000-2004 ዓ.ም የተዘጋጁ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎችን ከአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ ትምህርት ዓላማዎች ጋር በግልና በተለያዩባቸው ክፍሎች ላይ በጋራ በመወያየት ያካሂዱት የጥያቄዎች ምደባ ውሳኔ (EXPERT JUDGMENT) ስሌት በአማካይ

ተ.ቁ		በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ በቀጥታ(Direct) ወይም በተዘዋዋሪ (indirect የተወከሉበት ጥያቄ ብዛት አማካይ						
	በዘጠነኛና10 ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች የተካተቱ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች	2000 አማ ካይ	2001 አማ ካይ	2002 አማ ካይ	2003 አማ ካይ	2004 አማካይ	የ5ቱ ዓመት ጥያቄ ድምር	የ5ቱ ዓመት አማካይ%
1.	የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ማዳበር በተመለከተ	7.78	6.37	8.89	5.6	4.4	30	6.00
1.1	በተለያዩ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሞውውቶችን ማካሄድ፣	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
1.2	በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ውይይቶችን ማካሄድ፣	1.1	1.1	1.1	1.1	1.1	5	1.00
1.3	አካባቢያዊ፣ ወቅታዊና አገራዊ ጉዳዮች ላይ በቂ መረጃዎችን ከልዩ ልዩ ምንጮች አሰባስቦ ክርክር ማካሄድ፣	1.1	1.1	1.1	1.1	1.1	5	1.00
1.4	በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች መልዕክትን ግልፅ የሚያደርጉ የድምፅና የአካል እንቅስቃሴዎችን... በመጠቀም የዱብዳ ንግግር ማድረግ፣	0	1.1	0	1.1	0	2	0.4
1.5	በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዝግጅት በማድረግና መልዕክትን ግልፅ የሚያደርጉ የድምፅ እና የአካል እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር ማድረግ፣	1.1	3.3	1.1	1.1	1.1	7	1.4
1.6	በተወሰነ ርዕስ ንግግር ማድረግ	0	0	1.1	1.1	0	2	0.4
1.7	ሌላ(ከላይ ያልተጠቀሰ የማዳመጥናየመናገር ክሂል)							
2.	የንባብ ክሂልን ማዳበር በሚመለከት	26.7	20	16.67	21	26.7	100	22.22
2.1	በጽሑፍ የቀረቡ ሀሳቦችን ሀቅና የግል አስተያየት እያሉ መለየት፣	2.2	3.3	1.1	2.2	1.1	9	1.8
2.2	በጽሑፍ የቀረቡ ሐሳቦችን መንስኤ(ምክንያት) እና ውጤት መለየት፣	1.1	1.1	2.2	3.3	3.3	10	2.0
2.3	በሚነበብ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋናና ጠቃሚ ዝርዝር ሐሳቦችን መለየት፣	13.3	4.4	4.4	6	6	32	6.4
2.4	በሚነበቡ ጽሑፎች ውስጥ ለሚገኙ አዳዲስ ቃላትና ሐረጋት በአገባባቸው መሰረት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን መስጠት፣	5.5	4.4	3.3	4.4	5	21	4.2
2.5	በዳሰሳ ንባብ(Scanning) በፅሁፍ ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር መረጃዎችን መፈለግ፣	0	1.1	0	1.1	1.1	3	0.6
2.6	በግርፍ ንባብ (Skimming) የአንድን ጽሑፍ አጠቃላይ ሐሳብ መረዳት፣	0	0	0	0	0	0	0.0
2..7	መተንበይ ማለትም ቀጣይ ሐሳብን /ይዘትን ከንባብ በፊትና በንባብ ጊዜ መገመት	0	0	0	0	0	0	0.0
2.8	ከልዩ ልዩ መግለጫዎች (ከስዕል፣ ከሰንጠረዥ...) መረጃዎችን ማግኘት፣	0	0	0	0	0	0	0.0
2.9	ነባር ዕውቀትን ከሚነበበው ጋር ማስተሳሰር፣	1.1	0	1.1	0	2.2	4	0.8

2.10	በአንድ ጽሑፍ ውስጥ በግልፅና በውስጠ ታዋቂነት የቀረቡ ሐሳቦችን መረዳት፣	1.1	0	0	1.1	3.3	5	1.0
2.11	እንድምታ ንባብ፤ ማለትም በግልፅ ያልሰፈሩ ሐሳቦችንና መረጃዎችን መረዳት፣	1.1	4.4	3.3	1.1	3.3	12	2.4
2.12	ከጽሑፉ ሀሳብና ከግል ልምድ በመነሳት ድምዳሜ ላይ መድረስ፣	0	0	0	0	0	0	0.0
2.13	ማጠቃለል / በጽሑፉ ዋና ዋና ሐሳቦች ላይ በመመርኮ ማጠቃለል፣	1.1	1.1	1.1	1.1	0	4	0.8
2.14	ያነበቡትን ጽሁፍ አስተዋፅኦ አሟልቶ ማቅረብ፣	0	0	0	0	0	0	0
2.15	ሌላ (ከላይ ያልተጠቀሰ የንባብ ክሂል)							
3	***የመጻፍ ክሂልን ማዳበር በተመለከተ***	18.9	21.1	24.4	23.3	23.3	100	22.22
3.1.	ሥርዓተ ነጥቦችን (በጽሑፍ ውስጥ) በተገቢ ቦታቸው ማስገባት/ መጠቀም፣	4.4	5.5	5.5	5.5	5.5	24	4.8
3.2	ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን በመገልገልና የአንቀጽ አጻጻፍ መርህን በመከተል የተለያዩ (ተራኪ፣ አወዳዳሪ፣ ገላጭ ...) አንቀፆችን መፃፍ፣	5.5	4.4	3.3	4.4	4.4	20	4
3.3.	የተለያዩ የሥራና ንግድ ነክ ደብዳቤዎችን መፃፍ ፣	2.2	0	2.2	1.1	1.1	6	1.2
3.4	በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ዘገባ መፃፍ ፣	1.1	1.1	2.2	2.2	2.2	8	1.6
3.5	ማርቀቅ.፣ ረቂቁን ማረም ፣መከለስና የድርሰቱን ዋና ጽሑፍ መጻፍ ፣	0	0	0	0	0	0	0.0
3.6	ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን ተገልግሎ መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ ያላቸው የተለያዩ (ተራኪ፣ ሥዕላዊ፣ ገላጭና አመዛዛኝ) ድርሰቶች መጻፍ፣	1.1	1.1	3.3	2.2	1.1	8	1.6
3.7	የአንድን ጽሑፍ ወይም ንግግር መልዕክት ሳያዛቡ አሳጥሮና አስፋፍቶ በራስ አባባል መፃፍ፣	1.1	2.2	1.1	2.2	1.1	7	1.4
3.8	ግለ ታሪክ መጻፍ (የራስን ወይም የሌላን ሰው)፣	1.1	1.1	2.2	1.1	2.2	7	1.4
3.9	ከተለያዩ ንግግሮችና ዕሑፎች የሚገኙ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ፣	0	1.1	1.1	1.1	1.1	4.4	0.8
3.10	ቃለ ጉባኤ መያዝ / መጻፍ(በስብሰባዎች)፣	1.1	0	1.1	1.1	1.1	4.4	0.8
3.11	ሌላ (ከላይ ያልተጠቀሰ የጽሕፈት ክሂል)	0	3.3	1.1	1.1	3.3	8	1.6
4	***የሰዋሰው ዕውቀትን ለማነልበት ከሚረዱ መሠረታዊ ሐሳቦች ጋር መተዋወቅን በተመለከተ***	21.1	26.7	23.3	22.2	27.8	109	24.22
4.1	የቋንቋ ምንነትን፣ አጀማመርንና ባሕርያትን መግለጽ ፣	3.3	2.2	3.3	3.3	2.2	13	2.6
4.2	ነባና ጥገኛ ምዕላዶችን (ቅጥያዎችን) ማውጣት፣	2.2	7	2.2	4.4	4.4	21	4.2
4.3	የሚጠብቁና የሚላሉ ድምፆችን መለየት፣	1.1	1.1	3.3	1.1	1.1	7	1.4
4.4	የቃላት ቅርፅን በመደብ፣ በዐቃና በቁጥር መለየት፣	2.2	0	2.2	1.1	2.2	7	1.4
4.5	ገላጮችን (የስምና የግስ) መለየት፣	1.1	2.2	2.2	2.2	2.2	9	1.8
4.6	የአማርኛ ቃላት ክፍሎችን (ስም፣ ቅጽል፣ ግስ...) መለየት	2.2	2.2	2.2	2.2	1.1	9	1.8
4.7	የሐረግ ዓይነቶችን (ቅዕላዊ፣ ስማዊ፣ መስተዋድዳዊ፣ ተውሳከ ግሳዊ፣ ግሳዊ) መለየት፣	3.3	2.2	5.5	4.4	7	21	4.2
4.8	ተራና ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን መለየት ፣	1.1	2.2	0	1.1	2.2	6	1.2
4.9	በተለያዩ ጽሑፎች ውስጥ ያሉ መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጎችን መለየትና ተግባራቸውን መግለፅ፣፣	0	0	0	0	0	0	0.0
4.10	ለቃላትና ሐረጎች ተመሳሳይና ተቃራኒያቸውን መስጠት	2.2	4.4	2.2	0	3.3	11	2.2

4.11	ሌላ (ከላይ ያልተጠቀሰ የሰዋስው ዕውቀት)	0	3.3	0	2.2	1.1	6	1.2
5	***ሐሳብን ሥነ-ጽሑፋዊ በሆነ መልክ የመግለፅ ችሎታን በተመለከተ***	23.3	25.6	27.8	28.9	17.8	111	24.67
5.1	የፈጠራ ሥነ-ጽሑፍ ዘርፎችን (ሥነ-ቃል፣ ግጥም፣ ልቦለድ፣ ድራማ) መለየት፣	2.2	3.3	0	1.1	1.1	7	1.4
5.2	የሥነ-ቃል ዓይነቶችንና ባሕርያትን መለየት ፣	2.2	1.1	2.2	1.1	1.1	7	1.4
5.3.	በምሳሌያዊ ንግግሮች የሚቀርቡ አስተያየቶችንና ልምዶችን መረዳትና የራስን ንግግርና ፅሁፍ በምሳሌያዊ ንግግሮች አጉልቶ ማቅረብ፣	2.2	2.2	4.4	4.4	2.2	14	2.8
5.4	በአካባቢያቸው የሚነገሩ የፍቅርና የስራ ቃል ግጥሞች አሰባስቦ ማቅረብ፣	0	0	0	0	0	0	0.0
5.5	የግጥም ባህርያትን መግለፅ፣	0	0	0	1.1	0	1.1	0.2
5.6	የግጥም ስልቶችን ከምጣኔና ከምት አንፃር መለየት፣	0	1.1	3.3	2.2	1.1	7	1.4
5.7	ግጥምን ወደዝርው ፅሁፍ መለወጥ፣	0	1.1	0	0	0	1.1	0.2
5.8	ግጥሞችን ከይዘትና ከቅርጽ አንጻር መግምገም፣	0	0	5.5	0	0	5.5	1
5.9	ግጥም መግጠም/መጻፍ፣	0	0	0	0	0	0	0.0
5.10	የፈሊጣዊ ንግግሮችን መልዕክት መረዳት፣	5.5	4.4	2.2	4.4	2.2	17	3.4
5.11	በተለያዩ ዘይቤዎች (በአነፃፃሪ፣ ተለዋጭ፣ ሰውኛ...) የቀረቡ አባባሎችን/ ሀሳቦችን መረዳትና ማብራት	5.5	7	3.3	5.5	4.4	24	4.8
5.12	የልቦለድ አይነቶችን፣ አላባውያንና ቴክኒኮችን መለየት፣	5.5	3.3	3.3	8	1.1	20	4.0
5.13	ረጅምና አጭር ልቦለዶችንና ድራማዎችን በማንበብ ባሕርያቸውን መግለፅ፣	0	1.1	3.3	0	3.3	7	1.4
5.14	የኢትዮጵያን ታዋቂና ቀዳሚ የሥነ-ፅሁፍ ሰዎችና ሥራዎቻቸውን መለየት፣	0	0	0	0	0	0	0.0
5.15	ሌላ (ከላይ ያልተጠቀሰ ሥነጽሁፋዊ ችሎታ)	0	0	0	0	1.1	1.1	0.2

በዚሁ በሰንጠረዥ 4.3 የቀረበው ዝርዝር መረጃ እንደሚያሳየው በአምስቱ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎች በተሻለ የጥያቄ ብዛት በመወከል አንደኛው ሥነ-ጽሑፍ ነው፡፡ በ111 ጥያቄ ወይም በአማካይ በ24.67% ተወክሏል፡፡ በ109 ጥያቄ (በ24.22%) በመወከል በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሰዋስው ነው፡፡ የንባብና የመጻፍ ክሂሎች በተመሳሳይ የጥያቄ ብዛት በመወከል በ(22.22%)፣ በሦስተኛ ደረጃ ላይ ተገኝተዋል፡፡ የማዳመጥና የመናገር ክሂል በጋራ በሦስተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙት ክሂሎች በጣም ርቀው በ30 ጥያቄዎች ወይም በአማካይ በ6.67% በመወከል የመጨረሻውንና አራተኛውን ደረጃ ይዘዋል፡፡ ይህም እነዚህ ሁለት ክሂሎች በመርሐ ትምህርቶቹ ከተሰጣቸው ዝቅተኛ ትኩረት በጣም ያነሰ ሽፋን በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ እንደሚያገኙ የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ደረጃዎች በያዙት ክፍሎች መካከል ያለው የውክልና ልዩነት ጠባብ ነው፡፡

እዚህ ላይ በምርጫ ጥያቄ/ ፈተና የመጻፍና የመናገር ክሂሎች እንዴት ነው ሊመዘኑ የሚችሉት? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ስለዚህ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ከመገባቱ በፊት ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት ያስፈልጋል። በእርግጥም የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና መሠረታዊ ችግሮች እየተባሉ ከሚጠቀሱት መካከል አንዱና ዋናው ይኸው የማመንጨት ክሂሎችን (መናገርና መጻፍን) ለመመዘን የማያስችል መሆኑ ነው (Madson1976)። ይሁን እንጂ Brown (2004)ን በመጥቀስ በድርሳናት ክለሳ ክፍል እንደተገለፀው በተግባር ለመመዘን በማያመችበት ጊዜ በጽንሰ ሐሳብ ደረጃ ኢርቱዕ (indirct) በሆነ መንገድ የቋንቋ ክሂሎችን ለመመዘን መሞከር የተለመደ ነገር ነው። አልፎ አልፎም ቢሆን በሌሎች አገሮችም ይኸ ልማድ አለ (Hughes 2003፣ Watanabe 1997)። በእነዚህ አምስት ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችም የተማሪዎችን የመጻፍ፣ የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎች ለመመዘን የተሞከረው በተግባር እንዲጽፉ፣ እንዲናገሩና እንዲያዳምጡ በማድረግ ሳይሆን ኢርቱዕ በሆነ መንገድ ስለእነዚህ ክሂሎች ያላቸውን ዕውቀት በመጠየቅ ነው። በፈተናዎቹ የሚለካው ወይም የሚመዘነው ተማሪዎቹ በተግባር ምን ያህል አዳምጠው መረዳትና ሐሳባቸውን በንግግርና በጽሑፍ አቀናብረው መግለፅ ይችላሉ? የሚለው አይደለም።

በየዓመቱ ከሚዘጋጁት የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጥያቄዎችና ከፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ገለጻ መረዳት የተቻለውም ክሂሎችን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመመዘን እየተሞከረ ነው የሚል እምነት ያለ መሆኑን ነው። ለምሳሌ የመጻፍ ክሂልን ለመመዘን የሚሞከረው ዐረፍተ ነገር መጻፍ መቻላቸውን፣ ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቀ የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን በማቅረብ ተማሪዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን አወቃቀር የተከተለውን እንዲመርጡ በመጠየቅ፣ አንቀፅ መጻፍን በሚመለከትም እንዲሁ ቅደም ተከተላቸው የተፋለሰ ዐረፍተ ነገሮችን አቅርቦ ትክክለኛውን ቅደም ተከተል የያዘውን አማራጭ እንዲመርጡ በመጠየቅ፣ ወዘተ. ነው። በተለይ ከፈተናዎች ኤጀንሲ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያ 'ለ' ማብራሪያና ምሳሌዎች መረዳት እንደተቻለው አንቀፅ ሰጥቶ አንቀጹ በምን ስልት እንደተሰፋፋ እንዲለዩ መጠየቅ፤ የሥርዓተ ነጥብን ተገቢ ቦታ፤ የደብዳቤን፣ የዘገባን፣ የሕይወት ታሪክን፣ የቃለ ጉባኤን ወዘተ ቅርጽ፣ ባህርያትና

የመሳሰሉ ጉዳዮች የሚመለከቱ ጥያቄዎች ሁሉ ዓላማ የመጻፍ ክሂልን ለመመዘን ነው። በሠንጠረዥ 4.3 ለዳኝነት ሰጪ (ለጥያቄ መዳቢ) ባለሙያዎች የተሰጠው ትዕዛዝ/ መመሪያም ይህንኑ ያገናዘበ ነው።

በዚህ አስተሳሰብ መሠረትም በእነዚህ ፈተናዎች የተካተቱት ጥያቄዎች የንባብ፣ የመጻፍ፣ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችና የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች ተብለው በአምስት ክፍሎች ተመድበዋል። በሠንጠረዥ 4.3 ከቀረበው መረጃ ማስተዋል እንደሚቻለውም፣ ከእነዚህ መካከል ከአራቱ ክሂሎች ሁለቱ (የንባብና የመጻፍ) ክሂሎች ከሰዋስውና ከሥነ-ጽሑፍ ቀጥሎ የተሻለ ውክልና አግኝተዋል።

ከመርሐ ትምህርቶቹ ጋር ያላቸው ተዛምዶ ሲፈተሽ ግን አሉታዊነታቸው ቢበዛም አዎንታዊ ተዛምዶዎችም ይታያሉ። ከአሉታዊዎቹ መካከል በመርሐ ትምህርቶቹ ከተመደቡት 147 ክፍለ ጊዜያት ውስጥ አርባ አንዱን (28.47%) በመያዝ በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የመጻፍ ክሂል በፈተናው ያገኘው ውክልና ትይዩ አለመሆን አንዱ ማስረጃ ነው። ይህ ክሂል በፈተናው በ100 ጥያቄ በ22.22% ተወክሎ በሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ሁለተኛ፣ የንባብ ክሂል በመርሐ ትምህርቶቹ በ25 ክፍለ ጊዜ ወይም በ17% በመወከል ከመጻፍና ከሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች ቀጥሎ በሦስተኛ ደረጃ ላይ ቢገኝም፣ እንዲሁም በውስጡ የተካተቱት ንዑሳን ክሂሎች በምርጫ ጥያቄ/ ፈተና ለመመዘን አመቺ በመሆናቸው በተሻለ የጥያቄ መጠን ሊወከል የሚችል ቢሆንም በመርሐ ትምህርቶቹ 22 ክፍለ ጊዜ የተመደበለት የሰዋስው ትምህርት ከተወከለበት በሚያንስ የጥያቄ መጠን/ብዛት እንዲወክል እንደሚደረግ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ይህም ፈተናዎቹ በጥንቃቄና የትምህርቱ ክፍሎች፣ በሥርዓተ ትምህርቱ /በመርሐ ትምህርቶቹ ባገኙት ትኩረት መሰረት እንዲወከሉ በማድረግ ነው የሚዘጋጁት እየተባለ በኤጀንሲው ኃላፊዎችና በቋንቋው ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ሲገለጽ የነበረውን ሀሳብ የሚያጠናክር ሳይሆን የሚጻረር ነው።

በአዎንታዊ ዝምድ ሊጠቀስ የሚችለው ደግሞ የዕውቀት ዘርፎች እየተባሉ የሚጠሩት ክፍሎች ውክልና ነው። እነዚህ ክፍሎች በመርሐ ትምህርቶቹ በሁለተኛና በአራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፤ በፈተናዎቹም የተሻለ ውክልና አግኝተዋል። እርስ በርስ

ያላቸው ውክልና ሲነጻጸርም ከሁለቱ አንደኛው ሥነ-ጽሑፍ ነው፡፡ ሰዋስው በጣም ተቀራራቢ በሆነ ፐርሰንት ማለት በሁለት ጥያቄ ወይም 0.45% ከሥነ-ጽሑፍ አንሶ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በእርግጥ በመርሐ ትምህርቶቹ የተመደበላቸው የክፍለ ጊዜ መጠን እንደዚህ በጥያቄዎቹ እንዳገኙት ውክልና ያለ ተቀራራቢ አይደለም፡፡ ይህም በአንድ በኩል በአሉታዊ ግንኙነትም ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ ምክንያቱም፣ ሥነ-ጽሑፍ በመርሐ ትምህርቶቹ 29 ክፍለ ጊዜ (19.73%) የተመደበለት ሲሆን በፈተናዎቹም በ24.67% ተወክሏል፡፡ ሰዋስው ደግሞ በመርሐ ትምህርቶቹ 22 ክፍለ ጊዜ (14.96%) የተደለደለለት ሲሆን በፈተናዎቹ ከሚገባው በላይ ሊባል በሚችል ደረጃ ከሥነ-ጽሑፍ በጣም ተቀራራቢ በሆነ በ109 ጥያቄ ወይም በ24.22% ተወክሏል፡፡

የቋንቋው ክሂሎችና በተለምዶ የዕውቀት ዘርፎች በመባል የሚጠሩት የሥነ-ጽሑፍና የሰዋስው ይዘቶች ውክልና ሲነጻጸር ደግሞ አራቱ መሠረታዊ የቋንቋው ክሂሎች በ230 ጥያቄ (51.11%)፣ የሥነ-ጽሑፍና የሰዋስው ዘርፎች በ220 ጥያቄ (48.89%) በፈተናዎቹ ውክልና ማግኘታቸውን በሰጠነረኸ 4.3 የቀረበው የውጤት ትንተና ያሳያል፡፡

በእያንዳንዱ ዓ.ም. ያለው የውክልና ገፅታ ሲፈተሽ ደግሞ በ2000 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ክሂሎቹ በ50 (55.56%)፣ የዕውቀት ዘርፎቹ በ40 (44.44%) ጥያቄ፣ በ2001 ዓ.ም ከቀዳሚው በተቃራኒ ክሂሎቹ በ42 (46.67%)፣ ሥነ-ጽሑፍና ሰዋስው በ48 (53.33%) ጥያቄ ተወክለዋል፡፡ በ2002 ዓ.ም ደግሞ የቋንቋው ክሂሎች በ44 (48.89%)፣ ሥነ-ጽሑፍና ሰዋስው በተቀራራቢ ቁጥር በ46 (51.11%) ጥያቄ፣ በ2003 ዓ.ም ክሂሎችም፣ የዕውቀት ዘርፎችም በተመሳሳይ የጥያቄ መጠን በአርባ አምስት በአርባ አምስት ጥያቄ ተወክለዋል፡፡ በ2004 ዓ.ም ደግሞ ክሂሎቹ በ49 ጥያቄ (54.44%) በመሸፈን ቀዳሚውን ደረጃ ሲይዙ ሥነ-ጽሑፍና ሰዋስው በ41 ጥያቄ በ45.56% የሁለተኛነት ደረጃን ይዘዋል፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋው ክሂሎች በ2000 እና በ2004 ዓ.ም ከሥነ-ጽሑፍና ከሰዋስው የተሻለ ውክልና ሲያገኙ በ2003 ዓ.ም ተመጣጣኝ/ እኩል ውክልና አግኝተዋል፡፡

በቀሩት ሁለት ዓመታት ደግሞ የሥነ-ጽሑፍና የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች ከክሂሎቹ የበለጠ ውክልና አግኝተዋል፡፡ በአምስቱ ዓመታት አማካይ ደግሞ ክሂሎቹ በጠባብ ልዩነት የተሻለ ውክልና አግኝተዋል፡፡ ከመርሐ ትምህርቶቹ ጋር ያለው ዝምድና ደግሞ በተለይ ከመጻፍ እና ከንባብ ክሂል ጋር ያለው ግንኙነት አሉታዊነቱ የጎላ ነው፡፡

በእያንዳንዱ ዐቢይ ክሂልና በሥነ-ጽሑፍና በሰዋስው ክፍል ስር የቀረቡ ንዑሳን ክፍሎች በፈተናዎቹ ያገኙትን ውክልናና ከመርሐ ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ዝምድና ስንመለከት ደግሞ በሠንጠረዥ 4.3 ከቀረበው ዝርዝር የመረጃ ትንተና ማስተዋል እንደሚቻለው ከማዳመጥና መናገር ንዑሳን ክሂሎች በየዓመቱ ቢያንስ በአንድ ጥያቄ (0.2%) የመወከል ዕድል ያገኙት በተራ ቁጥር 1.2 (ውይይቶችን ማካሄድ)፣ 1.3 (ክርክር ማካሄድ) እና 1.5 (የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር ማድረግ) የተመለከቱት ናቸው፡፡ ሌሎቹ ሁለቱ ማለትም 1.4 (የዱብዳ ንግግር ማድረግ) እና 1.6 (በተወሰነ ርዕስ ንግግር ማድረግ የሚሉት) በአማካይ በ0.4% የተወከሉ ሲሆን አንደኛው (1.1 /ጭውውቶችን ማካሄድ የሚለው) በየትኛውም ዓመተ ምህረት ምንም ውክልና አግኝቶ የማያውቅ ነው፡፡ በ1.6 ከተመለከተው በስተቀር የሌሎቹ ውክልና በአብዛኛው በመርሐ ትምህርቶቹ ከተመደበላቸው የክፍለ ጊዜ መጠን ጋር አዎንታዊ ግንኙነት /ዝምድ ያለው ነው፡፡ በመርሐ ትምህርቶቹ ሦስት ክፍለ ጊዜ የተመደበለት በ1.5 የተመለከተው ንዑስ ክሂል በሰባት ጥያቄ (1.4%) ተወክሎ፣ በመርሐ ትምህርቶቹ አራት ክፍለ ጊዜ የተመደበለት በ1.6 ስር የተመለከተው ንዑስ ክሂል በሁለት ጥያቄ (በ0.4%) ብቻ መወከሉ ግን በሁለቱ መካከል ያለውን አሉታዊ ግንኙነት የሚያሳይ ነው፡፡

በሰንጠረዥ 4.2 እንደተመለከተው በዘጠነኛና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርቶች በንባብ ትምህርትነት የተካተቱት ዋና ዋናና ንዑሳን ክሂሎች 11 ሲሆኑ እነዚህ ክሂሎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው ውክልናም ወጥ አይደለም፤ የተለያየ ነው፡፡ በተሻለ ጥያቄ በመወከል የመጀመሪያው በ32 ጥያቄ ወይም በአማካይ በ6.4% የተወከለው በ2.3 የተመለከተው ‹‹በሚነበብ ጽሑፍ ውስጥ ዋና ዋናና ጠቃሚ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት›› የሚለው ክሂል ነው፡፡ ሁለተኛው በ21 ጥያቄ (4.2%) የተወከለው

በ2.4 የተመለከተው ለቃላትና ሀረጋት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን የሚመዝነው ክፍል ነው። ሦስተኛው በ10 ጥያቄ (በ2%) የተወከለው በ2.2 የተመለከተው በጽሑፍ ውስጥ መንስኤና ውጤት የሆኑ ሀሳቦችን መለየትን የሚጠይቀው ክሂል ነው። በ2.6 (የጽሑፍን አጠቃላይ ሐሳብ መረዳት)፣ በ2.7 (መተንበይ) እና በ2.8 (ከልዩ ልዩ መግለጫዎች (ከስዕል፣ ወዘተ) መረጃዎችን ማግኘት) የተመለከቱት የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች ደግሞ በየትኛውም ዓመተ ምህረት በአንድም ጥያቄ ተወክለው የማያውቁ ናቸው። የቀሩት አራቱ ንዑሳን ክሂሎች አልፎ አልፎ በአንድ ወይም በሁለት ቢበዛ በሦስት ጥያቄ የመወከል አጋጣሚ አግኝተው የሚያውቁ ናቸው።

የእነዚህ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች ውክልና በመርሐ ትምህርቶቹ ከተሰጣቸው ትኩረት አንፃር ሲገናዘብ ደግሞ በሁለቱ ሰንጠረዦች ከቀረበው መረጃ ማስተዋል እንደሚቻለው የተወሰኑት ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ ቀጥተኛ ተዛምዶ የማይታይባቸው ናቸው። ለምሳሌ በ2.3 የተመለከተው 'ዋና ዋናና ጠቃሚ ዝርዝር ሐሳቦችን መለየት' የሚለው ክሂል በመርሐ ትምህርቶቹም ከፍተኛ ሽፋን የተሰጠው ነው፤ በፈተናውም በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ስለዚህ በዚህ ረገድ በሁለቱ መካከል ቀጥተኛ /አዎንታዊ ተዛምዶ አለ ማለት ነው። በሌላ በኩል በመርሐ ትምህርቶቹ ትኩረት በማግኘት በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው በ2.6 የተመለከተው 'የጽሑፍን አጠቃላይ ሐሳብ መረዳት' የሚለው ክሂል በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ በአንድም ጥያቄ ተወክሎ የማያውቅ ነው። እንዲሁም በ2.4 የተመለከተው 'ለአዳዲስ ቃላትና ሐረጋት በአገባባቸው መሰረት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን መስጠት' የሚለው የንባብ ክሂል በመርሐ ትምህርቶቹ አንድ ክፍለ ጊዜ ብቻ የተመደበለት ቢሆንም በፈተናዎቹ ከንባብ ንዑሳን ክሂሎች በ21 ጥያቄ /በአማካይ በ4.2% በመወከል በሁለተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ አለውታዊ ተዛምዶን አጉልቶ ያሳያል።

በመጻፍ ክሂል ስር የቀረቡ ንዑሳን ክሂሎች ውክልናና ከመርሐ ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ዝምድና በሰንጠረዥ 4.3 በቀረበው መሰረት ለመመርመር ስንሞክርም በአምስቱ ዓመታት ውስጥ በአንድም ጥያቄ የመወከል አጋጣሚ አግኝቶ የማያውቀው

በ3.5 የቀረበው 'ማርቀቅ፣ ረቂቅን ማረም፣ መከለስና የድርሰቱን ዋና ጽሑፍ መጻፍ' የሚለው ክሂል ብቻ ነው። ሌሎቹ በሙሉ ከአምስቱ ዓመታት ቢያንስ በአራቱ በአንድ ጥያቄ የመወከል ዕድል ያገኙ ናቸው። በአርግጥ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው በ3.5 የተጠቀሰው ክሂል አንድም ጊዜ በአንድም ጥያቄ ያለመወከሉ ምክንያትም በተግባር ተማሪዎችን በማጻፍ ካልሆነ በስተቀር በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ለመመዘን የሚያስቸግር ሆኖባቸው ሊሆን ይችላል። ይህም ጥያቄ ጸሐፊዎቹና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎቹ በተለይ በመርሐ ትምህርቶቹ የተካተቱትን የጽሑፍ ክሂል ትምህርት ክፍሎች በቀጥታም ባይሆን ኢርቱዕ በሆነ መንገድ ከሞላ ጎድል በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ውክልና እንዲያገኙ ለማድረግ ጥረት እንደሚያደርጉ የሚጠቁም ነው።

በእርግጥ እንደቀዳሚዎቹ ሁሉ በዚህም ክሂል ስር የተካተቱ ንዑሳን ክሂሎች ከመርሐ ትምህርቶቹ ጋር አንዳንዶቹ አዎንታዊ፣ አንዳንዶቹ አሉታዊ ግንኙነት /ዝምድና ያላቸው ናቸው። ለምሳሌ ሥርዓተ ነጥብን የሚመለከተው በ 3.1 ላይ የቀረበው ንዑስ ክሂል በፈተናው በ24 ጥያቄ በመወከል ከመጻፍ ክሂል ንዑሳን ክሂሎች በአንደኛ ደረጃ ላይ ሲገኝ፣ በመርሐ ትምህርቶቹ የተመደበለት ክፍለ ጊዜ መጠን ግን ሦስት ብቻ ነው። በአንጻሩም በመርሐ ትምህርቶቹ ስድስት ክፍለ ጊዜ የተመደበለት በ3.5 የተመለከተው ክሂል በፈተናዎቹ በአንድም ጥያቄ ተወክሎ የማያውቅ ነው። በአዎንታዊ ዝምድና በኩል ደግሞ በፈተናው በመወከል በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው አንቀፅ አጻጻፍን የሚመለከተውና በ3.2 የተመለከተው ንዑስ ክሂል በፈተናው ብቻ ሳይሆን በመርሐ ትምህርቶቹም ከፍተኛ ሽፋን ያገኘ /ሰባት ክፍለ ጊዜ የተመደበለት ነው። ይህም በፈተናዎቹ ጥያቄዎችና በመርሐ ትምህርቶቹ ዓላማዎች መካከል በተወሰነ ደረጃ ይታያል ለተባለው አዎንታዊ ተዛምዶ አንድ ማስረጃ ይሆናል።

ወደ ሰዋስውና ሥነ-ጽሑፍ ክፍሎች ስንሻገር ደግሞ በመርሐ ትምህርቶቹ በቀረቡት የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍሎችና በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጥያቄዎች መካከል ያለው ተዛምዶም እንደቀዳሚዎቹ ሁሉ ወጥነት የማይታይበት/ ዝብርቅርቅ ያለ ነው። በዚህም በአንዳንዶቹ ቀጥተኛ (አዎንታዊ) ተዛምዶ ሲታይ በሌሎቹ አሉታዊ ሆኖ ይታያል። ለምሳሌ የሰዋስው ትምህርትን በሚመለከት በሰንጠረዥ 4.2

እና 4.3 ከቀረቡት መረጃዎች ማስተዋል እንደሚቻለው በ4.1፣ 4.3፣ 4.4፣ 4.7 እና 4.8 የተካተቱት ዓላማዎች በፈተናው ያላቸው ውክልና በመርሐ ትምህርቶቹ ከተመደበላቸው የክፍለ ጊዜ መጠን ጋር ተዛምዶ ያለው ሲሆን በአንፃሩም በ4.2፣ 4.5፣ 4.6 እና 4.9 የቀረቡት ክፍሎች በፈተናዎቹ ያገኙት ውክልና በመርሐ ትምህርቶቹ የተመደበላቸውን የክፍለ ጊዜ መጠን የሚያንፀባርቅ አይደለም፣ አሉታዊ ተዛምዶ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ በሥነ-ጽሑፍ ክፍል የቀረቡት ንዑሳን የትምህርቱ ክፍሎች እንዲሁ በመርሐ ትምህርቶቹ ከተሰጣቸው ትኩረት ጋር ሲነጻጸር በፈተናው የተሰጣቸው ትኩረት እንደሰዋስው ሁሉ ዝብርቅርቅ ያለ ነው፤ ወጥነት ያለው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ዝምድና አይታይም፣ የአንዳንዶቹ ውክልና በመርሐ ትምህርቶቹ መሰረት ነው፡፡ አንዳንዶቹ በመርሐ ትምህርቶቹ ትኩረት ቢያገኙም በፈተናዎቹ ችላ የተባሉ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ በመርሐ ትምህርቶቹ ከተሰጣቸው ትኩረት በላይ በፈተናዎቹ የመወከል ዕድል ያገኙ/ የተሰጣቸው ናቸው፡፡ ይህም አንድም ፈተና ከማዘጋጀት አቅም ማነስ፣ ሁለት ፈተናው በምርጫ ብቻ የሚዘጋጅ በመሆኑ እየተከሰተ ያለ ችግር ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ተማሪዎች በቋንቋው ፈተና ጥሩ ውጤት የሚያስመዘግቡትም አንደኛ ከመምህራኑ ጋር ከተካሄዱት ውይይቶች መረዳት እንደተቻለው ፈተናው ተተንባይ ነው፡፡ ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራኑ ጥያቄዎቹ የሚያተኩሩባቸውን ክፍሎች በደንብ ያውቋቸዋል፡፡ ሁለተኛ አብዛኛዎቹ በትምህርቱ የተካተቱት ክፍሎች በምርጫ ፈተና የሚመዘኑ ስላልሆኑ ለፈተና ለመዘጋጀት የሚጠኑት ክፍሎች ውስን እንዲሆኑ በማድረጉ ነው ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

ከዚህ ከፈተናዎቹና ከትምህርቱ ግንኙነት ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ሌላው ጥያቄ፣ የፈተናው የሥነ-ጽሑፍና የሰዋስው ክፍሎች ጥያቄዎች በትምህርቱ ዓላማዎችና በመርሐ ትምህርቶቹ የትምህርቱ አቀራረብ ክፍል የተመለከተውን እንዲያንጸባርቁ፣ የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች በሚያዳብሩት ክፍሎች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው ወይ? የሚለው ነው፡፡ ይህን ጥያቄ በተመለከተም የውጤት ትንተናው የሚያሳየው ለሥነ-ጽሑፍና ለሰዋስው ትምህርት ክፍሎችም ቢሆን ትኩረት የተሰጠው ክሂሎችን ለማዳበር ለሚረዱት ሳይሆን ጥያቄ ለማውጣት አመቺ ለሆኑት ክፍሎች ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከሰንጠረዥ 4.3 ማስተዋል እንደሚቻለው በእነዚህ ክፍሎች ንዑሳን ይዘትነት ከተካተቱት ትምህርቶች መካከል በፈተናዎቹ የተሻለ ውክልና እንዲያገኙ

የተደረጉት የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር ለሚያግዙትና የላይኛዎቹን የአዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች (መተግበር፣ መተንተን፣ ማቀናበርና መገምገም) ለሚመለከቱት ክፍሎች አይደለም፡፡ ለምሳሌ በሰዋስው ክፍል ከተካተቱት 11 ንዑሳን የትምህርቱ ክፍሎች/ ይዘቶች የተማሪዎቹን የቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር በተሻለ ደረጃ ሊያግዝ የሚችለው ዐረፍተ ነገር ነክ ክፍል በፈተናዎቹ ያገኘው ውክልና ዝቅተኛ ነው፡፡ በአምስቱ ዓመታት ውስጥ በስድስት ጥያቄዎች ((በ1.2%) ተወክሎ ከ11ዱ የሰዋስው ትምህርቶች በዘጠነኛ ደረጃ ላይ ነው የሚገኘው፡፡ በአንጻሩም ስለሥነ-ልሳን የሚኖራቸውን ዕውቀት ከማዳበር ባለፈ በቋንቋው ያላቸውን ተግባቦታዊ ችሎታ ለማዳበር ሚና ላይኖራቸው የሚችሉት የቋንቋ ምንነት፣ አጀማመርና ባህርያት የሚሉት ትምህርቶች በፈተናዎቹ የተሻለ ውክልና አግኝተዋል፡፡ በሥነ-ጽሑፍ ትምህርትም አንድ ግጥም አቅርቦ የተማሪዎችን ጠለቅ ያለና የማገናዘብና የመረዳት ችሎታን በተለያዩ ጥያቄዎች ለመጠየቅ/ ለመገምገም ለሚያስችለው “ግጥምን ከቅርጽና ከይዘት አንጻር መገምገም” የሚለው ዓይነት የትምህርቱ ክፍሎች በፈተናዎቹ ተገቢ ውክልና እንዲያገኙ አልተደረገም፡፡ በአንጻሩም ሌሎች የተማሪዎችን ተራና ዝቅተኛ የማስታወስ ችሎታ የሚመዝኑ የሰዋስውም ሆነ የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች በፈተናዎቹ የተሻለ ውክልና እንዲያገኙ ተደርገዋል፡፡ ይህም በሰዋስውና በሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች ላይ ተመስርተው የሚዘጋጁት የማጠናቀቂያ ፈተናው ጥያቄዎች፣ አንደኛ፣ በትምህርት ፖሊሲው የተገለጸውን ቋንቋው በትምህርት ዓይነትነት የሚሰጠው ለጋራ መግባቢያነት ነው የሚለውን፣ ሁለተኛ በሥርዓተ ትምህርቱ ማስፈጸሚያ ማዕቀፍ፣ በሀገሪቱ የሚሰጡ የቋንቋ ትምህርቶች ዓላማ አራቱን ክህሎች ማዳበር ላይ የሚያተኩሩ ሊሆኑ ይጋባቸዋል የሚለውን፣ ሦስተኛ ራሱ የቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ለቋንቋው ክሂሎች የሰጠውን ክብደት የሚያገናዝቡ አለመሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ በትምህርቱ መሰረት የሚደጋገፉ ሆነው አለመቅረባቸው ደግሞ በፈተናዎቹ እና በትምህርቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አሉታዊነት የሚያጎላ ብቻ ሳይሆን ፈተናዎቹ የቋንቋው ትምህርት ወደ ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት እንዳይሻገር የበኩላቸውን አሉታዊ ሚና እየተጫወቱ መሆናቸውን የሚያሳይም ነው፡፡

በአጠቃላይ፣ አንዳንዶቹ የቋንቋው ክሂሎች ንዑሳን ክሂሎችና የሥነ-ጽሑፍና የሰዋስው ክፍሎች በፈተናው ያገኙት ውክልና በመርሐ ትምህርቶቹ ከተሰጣቸው ትኩረት ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ ያላቸው ሆነው ቢገኙም አብዛኞቹ ግን አሉታዊ ግንኙነት እንዳላቸው የጥናቱ ግኝት አሳይቷል፡፡ የአሉታዊ ግንኙነቶች ጎልቶ መታየት መንስኤ Hughes (2003) እንዳሉት ጥያቄዎቹ የሚዘጋጁት ለመጠየቅ ያላቸውን አመቺነት ወይም አስቸጋሪነት መሰረት በማድረግ ነው ወይስ በትምህርቱ በተሰጣቸው ትኩረት መሰረት ነው ? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ለመመርመር ሲሞከር የተገኘው ምላሽ በአብዛኛው Hughes እንዳሉት ለመጠየቅ አመቺ ለሆኑት ትኩረት ከመስጠትና ጥያቄ ለማውጣት አስቸጋሪ የሆኑትን ክፍሎች ችላ ከማለት የመነጨ እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡ በማስረጃ ማየቱ ሐሳቡን ይበልጥ ግልፅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ለምሳሌ ከመጻፍ ክሂሎች በ3.1 (ሥርዓተ ነጥቦችን (በጽሑፍ ውስጥ) በተገቢ ቦታቸው ማስገባት/ መጠቀም) እና በ3.2 (ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን በመገልገልና የአንቀጽ አጻጻፍ መርህን በመከተል የተለያዩ (ተራኪ፣ አወዳዳሪ፣ ገላጭ ...) አንቀፆችን መጻፍ የተመለከቱት ክፍሎች በብዙ ጥያቄ የተወከሉት Hughes እንዳሉት በቀላሉ ጥያቄ ለማውጣት የሚያስችሉ ስለሆኑ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በ3.4 (በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ዘገባ መጻፍ) ፣ በ3.6 እና 3.11 የተመለከቱት የመጻፍ ክሂሎች በመርሐ ትምህርቶቹ በተሰጣቸው ትኩረት መሰረት በፈተናዎቹ መሸፈን/ መወከል ያልቻሉት በቀላሉ ጥያቄ ለማውጣት ስለማያመቹ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህም ጥያቄ ለማውጣት አመቺ የሆኑትን በተሻለ የጥያቄ ቁጥር የመወከልና አስቸጋሪ የሆኑትን በውስን ጥያቄ ብቻ መወከል ወይም ጭራሽ ችላ ብሎ ማለፍ በሁለቱ (በትምህርቱና በፈተናው) መካከል ተመጣጣኝ ውክልና ወይም ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳይኖር እያደረገ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

ይህን ክፍል ለማጠቃለል የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናን ከዘጠነኛና አስረኛ ክፍል የቋንቋው ትምህርት መርሐ ትምህርቶች ዓላማዎች ጋር የምርጫ ፈተና ሊፈቅድ የሚችለውን ያህል/ በሚፈቅደው መጠን ለመወከልና አዎንታዊ ተዛምዶ ለመፍጠር ጥረት እንደሚደርግ የሚጠቁሙ ማስረጃዎች ማግኘት ቢቻልም ሚዛኑ ደፍቶ የተገኘው ግን እያንዳንዱ ዐቢይ ክሂልና የዕውቀት ዘርፍ እንዲሁም በእያንዳንዱ ዐቢይ ክሂልና የዕውቀት ዘርፍ ስር የተካተቱ

ንዑሳን ክሂሎችና ትምህርቶች በመርሐ ትምህርቶቹ ከተሰጣቸው ትኩረትና ሽፋን ጋር ሲገናዘብ አዎንታዊ የሚባል ግንኙነት ሆኖ አልተገኘም፡፡ የጥናቱ ዝርዝር ግኝቶች እንዳሳዩት የተወሰኑ የመርሐ ትምህርቶቹን ዓላማዎች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በፈተናዎቹ ለመሸፈን ጥረት ቢደረግም ከተዛምዶ አንጻር የሚከተሉት ጉልህ ጉልህ ድክቶችም ታይተዋል፡-

አንደኛ የቋንቋው ክሂሎች በመርሐ ትምህርቶቹ ከተመደበላቸው የክፍለ ጊዜ ጋር የሚዛመድ ውክልና አያገኙም፡፡ በተግባር ለመመዘን አመቺ ባለመሆናቸው የተፈጠረ ችግር ነው እንዳይባል ደግሞ የሚገመተው ችግር የማይመለከተው የንባብ ክሂል ንዑሳን ክሂሎችም በአግባቡ እንዲወከሉ አልተደረገም፡፡ ይህም የችግሩ ምንጭ ከክሂሎች ለምዘና አመቺ አለመሆን ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል የሚል ሐሳብ ለማሰብ እንዳይቻል ያደርገዋል፡፡ ሁለተኛ፣ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት የተወሰኑ በመርሐ ትምህርቶቹ የተካተቱ የቋንቋው ንዑሳን ክሂሎች/ ትምህርቶች በተወሰኑ ዓመታት ፈተናዎች ብቻ እንዲሸፈኑ በሌሎቹ ደግሞ እንዲዘለሉ ይደረጋሉ፡፡ የተወሰኑት ደግሞ በየትኛውም ዓመት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመወከል (የመሸፈን) እድል እንዳያገኙ ይደረጋሉ፡፡ ሦስተኛ የተወሰኑ በመርሐ ትምህርቶቹ የተካተቱ የቋንቋው ንዑሳን ክሂሎች/ ትምህርቶች በፈተናዎቹ ጥያቄዎቹ ቢሸፈኑም ውክልናቸው ግን በመርሐ ትምህርቶቹ የተሰጣቸውን ትኩረት ያገናዘበ አይደለም፡፡ አራተኛ፣ በፈተናዎቹ የሚካተቱት አብዛኞቹ የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ክፍል ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር የሚያግዙ ክፍሎች ላይ የሚያተኩሩ ሆነው አልተገኙም፡፡ ይህም በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና በመርሐ ትምህርቶቹ መካከል ያለው ዝምድና በተዛማጅ ድርሳናት ከለሳ ከቀረቡት አስተሳሰቦች ጋር የሚጣላ፣ አሉታዊነቱ የሚጎላና ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርትን የማያበረታታ እንደሆነ ያሳያል፡፡

4.3.3.2 የማጠናቀቂያ ፈተናውንና የትምህርቱን ተዛምዶ በተመለከተ ከመምህራን በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተገኘ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ከተለያዩ በአማራ ክልል ከሚገኙ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ በተመረጡ አምስት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ጋር በተካሄዱ ተተኳሪ የቡድን

ውይይቶች ከተሰበሰቡ የተለያዩ መረጃዎች አንዱ የቋንቋው ትምህርትና የማጠናቀቂያ ፈተናውን ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ ተተኳሪ የቡድን ውይይት ጥያቄ ቁጥር 7.1-7.4 ያሉት ይህንኑ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በእነዚህ ጥያቄዎች የፈተናውንና የትምህርቱን ተዛምዶ በተመለከተ ተሳታፊዎቹ የማጠናቀቂያ ፈተናው አንደኛ፣ ተማሪዎችን ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ/ መሰናዶ ትምህርት ከማሸጋገር አንፃር፣ ሁለተኛ ለወደፊቱ የስራ ሕይወት መዘጋጀታቸውን ከመለካት/ በቋንቋው ክሂሎች መገልገል መቻል አለመቻላቸውን ከማረጋገጥ/ አኳያ፣ ሦስተኛ፣ ከቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ጋር በመጣጣም /Overlap በማድረግ ረገድ እና አራተኛ፣ ከመማሪያ መጽሐፎቹ ተግባሮች /መልመጃዎች ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር ተሳታፊዎቹ ያላቸውን አስተየያት እንዲናገሩ ተጠይቀዋል፡፡ ቀጥሎ ለእነዚህ ጥያቄዎች የውይይቶቹ ተሳታፊዎች የሰጡት ምላሽ ውጤት ተተንትኖና ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

ሀ. የማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎችን ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ ለማለፍ ከመርዳት አንጻር ያለው ሚና

የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና ተማሪዎችን ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ በማሳለፍ ረገድ ያለውን ሚና በተመለከተ ተሳታፊዎቹ ሁለት ዓይነት ሀሳብ አንጸባርቀዋል፡፡ አንደኛውና በሁሉም ውይይቶች የተገለጸው፣ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማጠናቀቂያ ፈተና የሚያስመዘግቡት ውጤት (ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ሲነጻጸር) የተሻለ በመሆኑ ወደመሰናዶ ትምህርት የሚያልፉ ብዙ ተማሪዎችን በማሳለፍ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው የሚል ነው፡፡ እንደተሳታፊዎቹ እምነት ተማሪዎች በአማርኛ የማጠናቀቂያ ፈተና የሚያስመዘግቡት ጥሩ ውጤት ብዙ ጊዜ ወደመሰናዶ ትምህርት ለማለፍ ከሚያስችሏቸው ሰባት የትምህርት አይነቶች አንዱ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ለምሳሌ መምህር$_{25}$ ስለዚሁ ጉዳይ በተናገሩበት ክፍል፣ “በእኛ ትምህርት የተሻለ ውጤት ነው የሚያመጡት፡፡ እኛም በጣም ነው የምንሰራ፡፡ በእኛ ትምህርት ኤ(A)ዎች ሲቆጠሩ ሁልጊዜ አንደኛ ነን፡፡ አይደል? [ወደ ስራ ባልደረቦቻቸው በመዞር]፡፡ ስለዚህ እነዚህ ለልጆቹ በጣም እየጠቀሟቸው ነው፤ በጣም፡፡ ወደ መሰናዶ ለመግባት፡፡ አምናም ቆጥሬዋለሁ፤ ወደ 90 ‘ኤ’ ፤ወደ 150 ‘ቢ’ ነው ያገኙት፡፡” በማለት ሲያስረዱ፣ መምህርት$_{7}$ ደግሞ ተማሪዎችን ወደ ቀጣዩ

የትምህርት ደረጃ ለማሻሻገር በአንጻራዊነት ከሌሎቹ የትምህርት ዓይነቶች ይልቅ የአማርኛ ውጤት እንደሚሻል ገልጸዋል።

የየትምህርት ቤቶቹ ምክትል/ ርዕሳነ-መምህራንም ሀሳቡን ይጋራሉ፣ በየትምህርት ቤቶቹ የተማሪዎችን ውጤት የሚያሳዩት ስታትስቲኮችም፣ የክልሉ ቢሮ በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ክልሉ ስንተኛ እንደወጣ ለማሳወቅ ለዞን ትምህርት መምሪያዎችና የዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች የላካቸው ሰነዶችም የተባለውን ያንጸባርቃሉ። ለምሳሌ በ2004 ዓ.ም ከክልሉ ትምህርት ቢሮ የተላከው ሰነድ በተጠቀሰው ዓመት በሀገሪቱ ካሉ ክልሎች በአማርኛ ውጤት የአማራ ክልል ሁለተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያሳያል። በቡድን ውይይቶች የተሳተፉት የዞን ትምህርት መምሪያዎችና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች ኀላፊችም እነሱ በሚመሯቸው ትምህርት ቤቶች በየዓመቱ ጥሩ ውጤት የሚመጡባቸው የትምህርት አይነቶች ናቸው ብለው የጠቀሷቸው ሲቪክስን፣ ሥነ-ሕይወትንና አማርኛን ነው። እነዚህ ሁሉ ማስረጃዎች የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የሚያሳዩ ባይሆኑም፣ ከፈተናው ውጤት አንጻር የመምህራኑን ሀሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው።

ለ. የማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎችን ለመሰናዶ ትምህርት ብቁ/ዝግጁ መሆናቸውን ከመመዘን አንጻር ያለው ሚና

በተጣጥሞሽ/ ተዛምዶ ርዕስ ስር በውይይቶቹ የተነሳው ሁለተኛ ነጥብ ፈተናው ተማሪዎቹ ለቋንቋው የመሰናዶ ትምህርት ዝግጁ መሆን አለመሆናቸውን ከመመዘን አንጻር ያለውን ተገቢነት በተመለከተ ነው። በዚህ ረገድ አንዳንዶቹ ከሞላ ጎደል ይመዝናል የሚል አስተያየት ሲሰጡ አብዛኞቹ ደግሞ አይመዝንም የሚል አቋም አንጸባርቀዋል። አይመዝንም ካሉት መካከል ለምሳሌ መምህር15፣ "አይመስለኝም፤ ...ለ11ኛ ክፍል ብቁ ናቸው ለማለት ትንሽ ይከብደኛል።... ምክንያቱም አራቱም የቋንቋው ክሂሎች ሳይመዘኑ እንደዚያ ብሎ ለመናገር የሚያስደፍር አይመስለኝም፣" ሲሉ፣ መምህር 11 ደግሞ፣ "10ኛ ክፍል ላይ የሚሰጠው የማጠቃለያ ፈተና ከምርጫ ውጭ የልባቸውን እንዲሉ መንገድ የሚሰጥ ነገር አይደለም። ምረጥ ብለህ... ለመሰናዶ በቂ የሆነ ዕውቀት ይዘው ይመጣሉ ብለህ ማለት አትችልም።" በማለት

የማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎች ለመሰናዶ ትምህርት ዝግጁ መሆን አለመሆናቸውን የሚለካ ነው፤ ለማለት እንደማያስችል አስረድተዋል፡፡

ሐ. ለሥራ ሕይወት መዘጋጀታቸውን/በቋንቋው መግልገል መቻል አለመቻላቸውን ከመለካት አንጻር የማጠናቀቂያ ፈተናው ተገቢነት

የአማርኛ ቋንቋ የክልሉና የማዕከላዊ መንግሥቱ የሥራ ቋንቋ ነው፡፡ በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ቋንቋው በሀገር አቀፍ ደረጃ በትምህርት ዓይነትነት እንዲሰጥ የተደረገው ለጋራ መግባቢያነት እንዲያገለግል ነው፡፡ በክልል ቋንቋነት፣ በክልሉ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ዓይነትነት የሚሰጥበት ምክንያትም ከዚህ የተለየ እንዳልሆነ በሥርዓተ ትምህርት ማስተግበሪያ ማዕቀፉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው በቋንቋው ትምህርት የሥርዓተ ትምህርት መሳሪያዎችም ለቋንቋው ተግባቦታዊ ክፍል የተሻለ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ ስለዚህ የሚሰጠው ትምህርት ተማሪዎችን ከትምህርት በኋላ በቋንቋው በተሻለ ደረጃ ለመጠቀም የሚያስችል ሊሆን ይገባዋል፡፡ የማጠናቀቂያ ፈተናውም ይህን ችሎታ የሚለካ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ በዚሁ መሰረት በሁለተኛ ደረጃ የፈተናውን ተገቢነት/ ከትምህርቱ ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር የተሞከረው ከዚህ፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎች ከትምህርት በኋላ በስራ ዓለም ሲሰማሩ በቋንቋው በአግባቡ መጠቀም መቻል አለመቻላቸውን ከመመዘን አንጻር የሚገኝበትን ደረጃ በተመለከተ ነው፡፡ ይህን ጥያቄ በሚመለከትም በተወያዮቹ የተንጸባረቀው ሁለት ዓይነት ሀሳብ ነው፡፡ አንደኛው ይመዝናል የሚል ሲሆን ሁለተኛው አይመዝንም የሚል ነው፡፡ በመጀመሪያው ጎራ ከተሰለፉት መካከል አንዱ የሆኑት መምህር[20] ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፣

> አሁን በዚህ በቃለ ጉባኤ አያያዝ፣ በማስታወሻ አያያዝ፣ በሌሎችም አሁን በየመስሪያ ቤቱ የሚሰራባቸው እነዚህ ናቸው፡፡ በደብዳቤ አጻጻፍ በዚህ በዚህ ላይ እኔ እንዳየሁት ከሆነ ጥሩ እንትን አለው፡፡ ...እኔ ለራሴ በፊት ..ሥነ-ልሳኑ፣ ሥነ-ጽሑፉ ላይ ነበር እንጂ እዚህ ላይ ብዙም እንትን አልሰጥም ነበር፡፡ እዚህ ላይ ሳይ ግን [ፈተናው ላይ ማለታቸው ነው] እኔም ትኩረት እንድሰጥ አድርጎኛል፡፡ እና ፈተናው እዚያ ላይ ጥያቄዎቹ አውነቴን ነው ከቅርብ ቀን ወዲህ ጥሩ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

የዚሁ ሀሳብ ተጋሪ የሆኑት የትምህርት ቤት፱ መምህር የሆኑት፣ መምህር[7]ም፣ "የቀረቡት ክሂሎች ጥሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንብቦ መረዳትን ...ንግግርን ተመልክቶ ሊሆን

ይችላል፡፡...እና ከተነኩት አንጻር ጥሩ ነው፤" ይላሉ:: የእነዚህ መምህራን ሀሳብ ከፈተናዎች ኤጀንሲ የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ሀሳብ ጋር የሚደጋገፍም ነው፡፡

አብዛኞቹ ተሳታፊዎች በዚህ ፈተናው የተማሪዎችን ለሕይወት/ ለሥራ ዓለም ዝግጁ መሆናቸውን ይለካል በሚለው ሀሳብ አይስማሙም፡፡ ከዚህ ተቃራኒ የሆነ አመለካከት አላቸው፡፡ በእነዚህኛዎቹ እምነት የማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎች ወደፊት በሕይወታቸው/ በሥራ ዓለም በቋንቋው መጠቀም መቻል አለመቻላቸውን ለመለካት የሚያስችል አይደለም፡፡ ዋነኛ ምክንያታቸውም ከንባብ/ ከአንብቦ መረዳት በስተቀር ሌሎቹን የቋንቋው ክሂሎች በምርጫ ፈተና ለመመዘን እየተቻለ አይደለም የሚል ነው፡፡

ይህንም በሚመለከት በተወያዮቹ ከተሰነዘሩት አስተያየቶች የተወሰኑትን መመለከቱ የመምህራኑን ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት ያግዛል፡፡ "ፈተናው...የትግበራ ስራ ይቀረዋል፡፡ የትግበራ፡፡...በትግበራ እየለካናቸው አይደለም፡፡ ጥሩ አንባቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ጥሩ ፀሐፊ ላይሆን ይችላል፡፡ እንዴት ነው ያን Evaluate እያደረግን [እየገመገምን] ያለው? ፈተናው እዚያ ላይ የለም፤" (መምህር$_{11}$)፤ ሲሉ፣ መምህርት$_{18}$ ደግሞ፣ "አንድ ልጅ ስለማመልከቻ አጻጻፍ አብራርቶ ይነግርሃል፡፡ ማመልከቻ ምን ምን አሟልቶ ይይዛል? ብትለው ይህን፣ ይህን ይይዛል ይልሃል፡፡ ማመልከቻውን ጻፍ ብትለው ግን አይጽፍም፡፡... ስለዚህ እየለካቸው ነው ብዬ እኔ አላስብም፡፡" በማለት በተግባር ባልተደገፈ ፈተና ተማሪዎች በቋንቋው ለመግልገል ወይም ለሕይወት/ ለስራ ዝግጁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለካት እንደማያስችል አስረድተዋል፡፡ ሌሎች ብዙ ተሳታፊዎችም በተለይም ስለመናገር፣ መጻፍና ማዳመጥ ምንነት፣ ባህርያትና የመሳሰሉ ጉዳዮች በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ያላቸውን ዕውቀት በመመዘን በተግባር በሚጠበቀው ደረጃ መናገር ፣መጻፍና አዳምጦ መረዳት መቻላቸውንም ለማወቅ ያስችላል በሚለው አስተሳሰብ አይስማሙም፡፡ እንደነዚህኛዎቹ እምነት ስለቃለ ጉባኤ አያያዝ፣ ደብዳቤ አጻጻፍ፣ እንዲሁም የንግግር፣ የውይይት፤ የክርክርና የመሳሰሉት ምንነት፣ ባህርያትና የመሳሰሉ ጉዳዮች በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ማወቅና በተግባር ንግግር ማድረግ፣ ውይይት ወይም ክርክር ማካሄድ፤ ቃለ ጉባኤ መያዝ፣ ደብዳቤ መጻፍ ወዘተ መቻል ዝምድና ቢኖራቸውም ይለያያሉ፡፡ በእነዚህኛዎቹ አስተሳሰብ መሰረት

ለምሳሌ ስለቃለ ጉባኤ አያያዝ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ በደንብ የሚያውቅ ተማሪ፣ በተግባር ቃለ ጉባኤ መያዝ ላይችል ይችላል፡፡ ሁለቱም አስተሳሰቦች ምክንያታዊ ቢሆኑም ከተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት መርህ አንጻር ሲታይ ግን ተማሪዎችን በተግባር የማይመዝን ፈተና ተገቢነቱ አጠያያቂ ነው፡፡

ይህን ክፍል ለማጠቃለል፣ ተማሪዎችን ለሥራ ሕይወት መዘጋጀታቸውን ከመመዘን/ ከመለካት አንፃር ለተጠየቁት ማለትም ፈተናው ተማሪዎች ወደ ፊት በሚሰማሩበት የስራ ሕይወት በቋንቋው መገልገል መቻል አለመቻላቸውን (ብቁ አቅም መፍጠር መቻል አለመቻላቸውን) ከመለካት አንፃር የሚገኝበትን ደረጃ አንዲገልጹ ለተጠየቁት ጥያቄ አብዛኛ ዎቹ ተሳታፊዎች የማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎች ለሕይወት ዝግጁ መሆን አለመሆናቸውን አይለካም ብለዋል፡፡ አንዳንዶቹ አክለው እንደገለፁት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፈተናው የሚደነቅ ገፅታታእየታየበት ነው፡፡ ይኸውም በየመስሪያ ቤቱ የሚሰራባቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር፤ ደብዳቤ አጻጻፍን፣ የዱብዴና በዝግጅት የሚደረግ ንግግርን ለመመዘን እየሞከረ ነው፡፡ ሆኖም እንዲህ ያለው ሙከራ ተማሪዎች ስለክሂሎች ያላቸውን ዕውቀት ከመለካት የዘለለ አይደለም፡፡ በፈተናው የሚጠየቀው ዕውቀት/ ጽንሰ ሀሳብ ብቻ ነው፡፡ ውይይት መምራትን፣ በውይይት መሳተፍን፣ ቃለ ጉባኤ፣ ማመልከቻ... መጻፍን አያደፋፍርም፡፡ ስለውይይት፣ ክርክር፣ ንግግር ስርዓት፤ ማመልከቻ፣ ቃለ ጉባዔ ወዘተ አሟልቶ የሚይዛቸውን ማወቅና በተግባር መወያየት፣ መከራከር፣ ንግግር ማድረግ፤ ማመልከቻ፣ ቃለጉባኤና ሌሎች ጽሑፎችን መጻፍ መቻል የተለያዩ ችሎታዎች ናቸው ብለው ተከራክረዋል፡፡

ከዘን ትምህርት መምሪያዎችና ትምህርት ጽሕፈት ቤት ኃኃኃላፊዎች ጋር በተካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተሳተፉት ኃኃላፊዎችም 10ኛ ክፍልን ያጠናቀቁት ቀርቶ ከዩንቨርሲቲ ዲግሪ ይዘው የሚመጡት እንኳ በዞናቸው ለመቀጠር ሲፈልጉ ማመልከቻ እንኳ ለመጻፍ የሚቸገሩ ናቸው ያሉት ሀሳብም ፈተናው ተማሪዎች ለሕይወት ዝግጁ መሆናቸውን የሚለካ አይደለም የሚለውን ሐሳብ የሚደግፍ ሌላ አስረጅ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ጋር በመጣጣም /overlap በማድረግ ረገድ

በማጠናቀቂያ ፈተናውና በትምህርቱ መካከል ስላለው ግንኙነት ያላቸውን ግንዛቤ /አጢኖት ለማወቅ ለተጠየቁት ሁለት ጥያቄዎች አብዛኞቹ ተሳታፊዎች የሰጡት ምላሽ በአብዛኛው የሚጣጣም ነው የሚል ነው። በመምህራኑ አመለካከት የሚጣጠም ነው፣ ማለትም ሁሉም ጥያቄዎች ከሥርዓተ ትምህርቱ ላይ በተለይም ከዘጠነኛና 10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፎች ላይ ተመስርተው የሚዘጋጁ/የሚወጡ ናቸው ማለት ነው። በትምህርቱ በተሰጣቸው ትኩረት መሰረት ተመጣጣኝ ውክልና ያገኛሉ ወይስ አያገኙም? የሚለውን አያካትትም።) እንደተወያዩቹ እምነት በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የማጠናቀቂያ ፈተናው ጥያቄዎች በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ በተለይም በመማሪያ መጽሐፈቹ ላይ ተመስረተው እየተዘጋጁ ነው። ይህም ፈተናዎቻችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሥርዓተ ትምህርቱን መሠረት እያደረጉ መጥተዋል በማለት በኤጀንሲው በባለሙያ 'ለ' የተገለጸውን ሀሳብ የሚደግፍ ነው:: ለምሳሌ መምህር$_{12}$ ስለዚህ፣ ስለሁለቱ ዝምድና ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፤

> ፈተናው ከቴክስቱ [ከመማሪያ መጽሐፉ] አይወጣም፤ በአብዛኛው። ከቴክስቱ በምንም አይወጣም። ያላነሳነው ነገር ምንም አይወጣም። እኔ እንግዲህ 10ኛ ክፍል ወደ 10 ዓመት ይኖረኛል። 10 ዓመት ሳስተምር አይቸዋለሁ፤ እያንዳንዱን ፈተና። ምንም ከይዘቱ ሽርተት የሚል የለም። ይዘቱን ነው። አመጣጥ መንገዱ ሊለያይ ይችላል። ይዘቱ ግን ከዚያው ነው የሚያጠነጥነው። ዘጠነኛና 10ኛ ቴክስት ላይ ነው።

ፈተናው በትምህርቱ ላይ እንደሚመሰረትና በሁለቱ መካከል አወንታዊ ዝምድና እንዳለ የሚያስረዳ ገለጻ ነው።

ሌላው ተሳታፊ ደግሞ "የመግለጽ ችሎታቸውን የማይመዝን መሆኑ ነው ልዩነቱ እንጂ ይጣጣማል፤" (መምህር$_{24}$) ብለዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ መምህር$_{15}$ም "በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ይወክላል። ችግር የለም ከዚያ ላይ፤ ይነካካሉ፤ የጥያቄው ቁጥር ቢለያይም ይነካካሉ። መናገርን የሚያደናቅፍ የቱ ነው? ይልና ያው መናገርን እንደጠየቀ ያስባል።" ብለዋል።

ከዚሁ ከተዛመዶ ጋር በተያያዘ የማጠናቀቂያ ፈተናው ከመማሪያ መጽሐፎቹ መልመጃዎች ጋር ያለውን ተዛምዶ በተመለከተም ተሳታፊዎቹ አስተያየታቸውን እንዲገልጹ ተጠይቀው ነበር። ለዚህም ጥያቄ አንዳንዶቹ የሰጡት መልስ አወንታዊ

ዝምድና እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። ለምሳሌ መምህር15 ብዙ ጊዜ የፈተናዎቹ ጥያቄዎች ከመልመጃዎቹ ጋር እንደሚያያዙ ከገለጹ በኋላ፣ "አንዳንዶቹ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንዲያውም ቀጥታ ከዚያ ይወጣሉ። አንድ ምንባብም ቀጥታ ከዚያ የተገለበጠ... የ10ኛ ክፍል ምንባብ ነው። ብሔራዊ ፈተናው ላይ ምንባብ ሆኖ መጥቷል፡" በማለት በሁለቱ መካከል ቀጥተኛ የሆነ ተዛምዶ መኖሩን አስረድተዋል። ሌሎቹ የትምህርት ቤታቸው አምስት ተወያዮችም በእሳቸው ሀሳብ የሚስማሙ መሆናቸውን አንጸባርቀዋል።

ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ተቀብለው ፈተናው በምርጫ ብቻ የሚቀርብ በመሆኑ ክሂሎችን በመፈተን ረገድ ችግሮች እንዲፈጠሩ አድርጓል ብለው የተከራከሩ ተወያዮችም አሉ። ለምሳሌ መምህር5፣ "ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር ይጣጣማል። ምክንያቱም መሰረት የሚያደርገው ሥርዓተ ትምህርቱን... ስለሆነ። ነገር ግን ተማሪዎቹ ፈተናው ላይ ፕራክቲካል የሆነ ነገር አይሰሩም። ምክንያቱም የፈተናው አጠያየቅ ምርጫ መሆኑ ተማሪዎቹ በተግባር እንዳይሰሩ ገድቧቸዋል። መጽሐፎቹ ላይ ካሉት መልመጃዎች ጋር ግን ለማጣጣም ይሞከራል።" በማለት ሲገልጹ መምሕርት13 ደግሞ፣ "ከይዘቶቹ ጋር በብዛት ተመሳሳይ ነው ብዬ አስባለሁ። ከመልመጃዎቹ ጋር ግን... አሁን ለምሳሌ ፈተናው ላይ የሚመጣ ምርጫ ነው፤ ከዚህ ጋ ግን ጻፉ ነው የሚለው አይደል? ተወያዩ የሚል ይኖራል፣ መልመጃዎቹ ላይ። ስለዚህ ከመልመጃዎቹ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ አይመጣም። ይዘቶቹ ግን በብዛት... ከመጽሐፎቹ የወጡ ናቸው።" በማለት በይዘት ቢመሳሰሉም በአቀራረብ (በአጠያየቅ ስልት) ግን እንደሚለያዩ ገልጸዋል። ከጥቅሶቹ ማስተዋል እንደሚቻለው እኒህኛዋ መምህርት የፈተናዎቹንና የመልመጃዎችን ተዛምዶ ያዩበት መንገድ ከመምህር20 የሚለይ እንዲሁም የመምህር13ንና የፈተናዎች አጠያየቅ ተማሪዎች በክፍል ትምህርት የሚለማመዱባቸው መልመጃዎች ነጻብራቅ መሆን ይገባቸዋል የሚለውን Missick (1996) የአዎንታዊ ወሽባክ ማበረታቻ ሀሳብ የሚጋራ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ክሂሎችም ቢሆኑ የፈተናው ባህርይ በሚፈቅደው መሰረት እንዲወከሉ እየተደረገ ነው የሚል አቋም ያንጸባረቁ ተሳታፊዎችም አሉ። ለምሳሌ መምህር22 ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፤

ክሂሎችም ቢሆኑ እኮ እምልህ በፈተና ተናገር ብለህ እንደማትለው ይታወቃል፡፡ ግን እነዚያን የሚጠይቅበት አለው፡፡ የትኛው ነው ከንግግር ዝግጅት የሚካተተው/ የማይካተተው? የሚለው አለ፣ እዚያ ውስጥ፡፡ መጻፍን በተመለከተ ለምሳሌ ቅደም ተከተል ይሰጥሃል፡፡ ወይ የጊዜ ወይ የድርጊት ቅደም ተከተል፡፡ አስተካክልና እስቲ መልክ አስይዘህ አንድ ተራኪ ድርሰት ጻፍባቸው ይልሃል፡፡ ስለዚህ የጽሑፍ ክሂል በዚያ ውስጥ እኮ አለ፡፡

መምህር$_{24}$ም በማጠናቀቂያ ፈተናው ለተማሪዎች የተዘበራረቁ ዐረፍተ ነገሮች እየተሰጣቸው የተስተካከለ አንቀጽ እንዲመሰርቱ የሚደረገው የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለመመዘን ነው የሚል ተጨማሪ ምሳሌ ሰጥተዋል፡፡ የሁለቱም ሀሳብ በተቻለ መጠን የቋንቋው ክሂሎችንም በፈተናው ለመሸፈን/ ለማካተት ጥረት ይደረጋል የሚል ነው፡፡ አጠያየቁ የምርጫ ስልትን ብቻ የሚጠቀም መሆኑ ክሂሎችን በተግባር ለመመዘን አለማስቻሉን ግን እነዚህኛዎችም ይጋራሉ፡፡ በፈተናዎች ኤጀንሲ ግን ክሂሎችን ኢርቱዕ በሆነ መንገድ ለመመዘን መሞከሩን እንደተገቢ አሰራርና የምዘና ሂደት የሚታይ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀደም ብሎ በሌላ ክፍል እንደተገለጸው በኤጀንሲው የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች እንደሚታሰበው ተማሪዎች ስለቋንቋው ክሂሎች ኢርቱዕ በሆነ መንገድ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን መመለስ የሚችሉ ከሆነ በክሂሎቹ በተግባር መጠቀም የሚችሉ መሆናቸውንም ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ በቋንቋው ክሂሎች ምዘና ረገድ በፈተናዎች ኤጀንሲ ጎላፊዎችና በአማርኛው የፈተና ዝግጅት ክፍል የሚታመነውን የሚጋሩም የሚቃወሙም መምህራን እንዳሉ ከቡድን ውይይቶቹ የተገኘው መረጃ ውጤት ትንተና አሳይቷል፡፡ ለምሳሌ ቀደም ብሎ እንደተወሳው በፈተናዎች ኤጀንሲ የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ዕምነት ለምሳሌ ከተከራካሪ ምን ምን እንደሚጠበቅእየሚያውቅ ተማሪ ከማያውቅ ተማሪ በተሻለ ደረጃ በአግባቡ ሊከራከር ይችላል፡፡ በመሆኑም ማዳመጥን፣ መናገርንና መጻፍን ለመመዘን የሚያስችሉ የአጠያየቅና የመልስ አሰጣጥ መንገዶች መጠቀም የሚቻልበትን ሥርዓት ትምህርት ሚኒስቴር እስከሚዘረጋ/እእስከሚፈቀድ ድረስ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ መጠየቁ ተገቢ ነው የሚል ዕምነት ከድርጅቱ ባለሙያዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ሲካሄድ ተንፀባርቋል፡፡ ይህ ዕምነት በተወሰኑ መምህራን/ የውይይት ተሳታፊዎችም ተቀባይነት ሲያገኝ በተወሰኑት ደግሞ ተነቅፏል፡፡ እነዚህን ክሂሎች በሚመለከት በጽንሰ ሀሳብ/ ዕውቀት ደረጃም ቢሆን በጥያቄ ከመወከልና ከመዝለል የቱ ይሻላል? የሚለው በዕውነትም አከራካሪ ይመስላል፡፡ በBrown (2004)፣ Hughes (2003)፣ Watanabe (1997) መሰረት

ሲታይ ደግሞ በሌሎች አንዳንድ ሀገሮችም ክሂሎችን ኢርቱዕ (Indirect) በሆነ መንገድ መመዘን በተግባር ሲሰራበት የሚታይ፣ ነገር ግን ክሂሎችን በቀጥታ ከመፈተን ጋር የማይመጣጠን/ ያነሰ የመመዘኛ መንገድ ነው። በመሆኑም ክሂሎች በተግባር እስካልተመዘኑ ድረስ የምዘና ሥርዓቱ በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ አሉታዊ ወሽባክ ማሳደሩ የማይቀር ነው።

4.3.3.3 የክፍል ፈተናዎች ከመርሐ ትምህርቶቹ ዓላማዎችና ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ቀደም ብሎ በሌላ ክፍል እንደተጠቆመው የማጠናቀቂያ ፈተናዎች በክፍል ፈተናዎቹ (Class Room Tests) ዝግጅት ላይ ተፅዕኖ ማሳደር አለማሳደራቸውን፣ እንዲሁም የክፍል ፈተናዎች የሥርዓተ ትምህርቱ ዓላማዎች ነፀብራቅ መሆን አለመሆናቸውን መፈተሽ የማጠናቀቂያ ፈተናውን ተጽዕኖ መፈተሻ አንዱ ጉዳይ ነው። ለዚህ ዓላማም በጥናቱ በታቀፉት ትምህርት ቤቶች የተዘጋጁ እ.ኤ.አ. የ2004 እና የ2005 ዓ.ም የ፭ኛና የ፪ኛ መንፈቀ ዓመት የክፍል ፈተናዎች ተሰብስበዋል። ፈተናዎቹ፣ የተወሰኑት በትምህርት ቤት ደረጃ፣ የተወሰኑት በዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች፣ የተወሰኑት ደግሞ በዞን ትምህርት መምሪያዎች የተዘጋጁ ናቸው። በእርግጥ ሁሉም ለክፍል ትምህርት ችሎታ መለኪያነት የተዘጋጁ ናቸው። በአባሪ 18 ከተካተቱት ፈተናዎች መካከል የመጨረሻው ብቻ የብቃት ፈተና (Proficency test) በመሆኑ በትንተናው አልተካተተም።

ሰንጠረዥ 4.4 የክፍል ፈተናዎች ከመርሐ ትምህርቶቹ ዓላማዎችና ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት በቁጥርና በአማካይ ስሌት

ተራ ቁጥር	የቋንቋው ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች	በ9ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት የተመደበ ላቸው ክፍለ ጊዜ ብዛት	በ10ኛ ክፍል መርሐ ትምህርት የተመደበላ ቸው ክፍለ ጊዜ ብዛት	ለሁለቱ ክፍሎቸ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት ድምር	%	በ5ቱ ዓ.ም የማጣናቀቂ ያ ፈተናዎች የተካተቱ ጥያቄዎች ብዛት	የ5ቱ ዓመታት የፈተና ዎቹ ጥያቄዎ ቹ ብዛት አማካይ	የ2004 ና 2005 የክፍል ፈተናዎ ች ጥያቄ ብዛት	የሁለቱ ዓመታ ት የክፍል ፈተናዎ ች አማካይ
1.	የማዳመጥና የመናገር ክሂላቸውን አዳብረው፣ የተረዱትን ይገልፃሉ/. በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ንግግር ያደርጋሉ፡፡	13	17	30	20.83	30	6.00	43	2.43
2	የንባብ ክሂላቸውን አዳብረው የተረዱትን በተለያየ መልኩ ይገልፃሉ፡፡	14	11	25	17.00	100	22.22	327	18.49
3	የጽሕፈት ክሂላቸውን አዳብረው ሃሳባቸውን ተነባቢ በሆነና በሚስብ ጽሑፍ ያስተላልፋሉ፡፡	21	20	41	28.47	100	22.22	179	10.12
4	የአማርኛ ሰዋስው ዕውቀታቸውን ያጎለብታሉ	15	7	22	15.28	109	24.22	685	38.74
5	ስለፈጠራ ጽሑፍ ዘርፎች በመረዳት ሀሳባቸውን ሥነ-ጽሑፋዊ በሆነ መልኩ ይገልፃሉ፡፡ የሚያነቡትንም ሆነ የሚያዳምጡትን ሂሳዊ በሆነ መንገድ በመመልከት የመግለፅ ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡	12	17	29	20.14	111	24.67	534	30.20
	ድምር	75	72	147	100	450	100	1768	100

በሰንጠረዥ4.4 ከቀረበው የክፍል ፈተናዎቹ የጥያቄዎች ስርጭት ማስተዋል እንደሚቻለው በዘጠነኛም ሆነ በ10ኛ ክፍል በፈተናዎቹ የተሻለ ትኩረት/ ውክልና በማግኘት አንደኛው ሰዋሰው፣ ሁለተኛው ሥነ-ጽሑፍ፣ ሦስተኛው የንባብ ክሂል ነው፡፡ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች በጋራ በዘጠነኛ ክፍል ከ630 ጥያቄ በ28 ጥያቄ (4.4%)፣ በ10ኛ ክፍል ከ1138 ጥያቄ በ15 ጥያቄ (1.32%) ተወክለው እንደማጠናቀቂያ ፈተናው ሁሉ በዚህም የመጨረሻውን ደረጃ ይዘዋል፡፡ የክሂሎቹ ጥቅል ውክልና ከሰዋስው ጋር ብቻ እንኳ ሲነፃፀር በዘጠነኛ ክፍል በ257 (በ40.79%)፣ በ10ኛ ክፍል በ365 ጥያቄ ወይም በ32% የሰዋስው ፈተና ውክልና ከአራቱ ክሂሎች

ይበልጣል፡፡ በሥነ-ጽሑፍና በክሂሎቹ መካከል ያለው የውክልና ልዩነትም በሰዋስውና በሥነ-ጽሑፍ መካከል ያለውን ያህል የሰፋ ባይሆንም የሥነ-ጽሑፍ ትምህርት በክፍል ፈተናዎች የተሻለ ውክልና እንደሚያገኝ ሰንጠረዥ4.4 ያሳያል፡፡ ይህም የክፍል ፈተናዎች ከቋንቋው ትምህርት ዓላማዎች ጋር ብዙ ዝምድና እንደሌላቸውና የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ነጸብራቅ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡ የዚህም አንድምታ መምህራኑ የሚያስተምሩት፣ ተማሪዎቹ የሚማሩት በማጠናቀቂያ ፈተናው ለሚካተቱት የትምህርቱ ክፍሎች ትኩረት በመስጠት ነው ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከመምህራን ጋር በተካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ሰፊ ሽፋን/ ውክልና በማግኘት አንደኛው ሰዋስው፤ ሁለተኛው ሥነ-ጽሑፍ፣ ሦስተኛው የንባብ ክሂል ነው፡፡

የውጤት ትንተናው በግልፅ ያሳየውም፣ የክፍል ፈተናዎች የመምህራኑን ሀሳብ በሚያንፀባርቅ መልኩ እየተዘጋጁ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህም ከላይ ከተገለጸው አንድምታ በተጨማሪ የክፍል ፈተናዎች መምህራኑ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረት/ ይዘት ያላቸውን ግንዛቤ በሚያንፀባርቅ መልኩ እንደሚዘጋጁ የሚያመላክት ነው፡፡ የክፍል ፈተናዎቹ በቋንቋ ትምህርት መርሐ ትምህርቶች ዓላማዎች መሰረት የሚዘጋጁ ቢሆኑ ኖሮ ግን በተሻለ የጥያቄ ብዛት በመወከል አንደኛው የመጻፍ ክሂል፣ ሁለተኛው የሥነ-ጽሑፍ ትምህርት፣ ሦስተኛው የንባብ ክሂል ይሆኑ ነበር፡፡ በቅርጽ ረገድም የክፍል ፈተናዎች ጥያቄዎች በመማሪያ መጽሐፎቹ ያሉት መልመጃዎች በቀረቡበት መንገድ በጽሑፍ በሚመለስ መልክ ሳይሆን እንደማጠናቀቂያ ፈተናው በምርጫ ሰጭ አጠያየቅ መንገድ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ይህም የክፍል ማጠቃለያ ፈተናዎች በይዘት ብቻ ሳይሆን በቅርፅም ከትምህርቱ ያፈነገጡና የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጥገኛ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

4.3.3.4 ተጣጥሞሽን በተመለከት በመጠናዊና ዓይነታዊ ዘዴዎች የተካሄዱ ትንተናዎች ውህዳዊ ውጤትና ማብራሪያ

እስካሁን፣ ተጣጥሞሽን/ ተዛምዶን በተመለከተ አንደኛ በአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማ ስድስት ክፍሎችና በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ፣ ሁለተኛ ለደረጃው በተዘጋጁት የቋንቋው መርሐ ትምህርቶችና በማጠናቀቂያ ፈተናዎች፣ ሦስተኛ በመርሐ ትምህርቶቹና በክፍል ፈተናዎች፣ በክፍል ፈተናዎችና በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች የተለያዩ መረጃዎች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተሰብስበው ዓይነታዊ የሆኑትን በጭብጠቻቸው መሰረት በተለያዩ ምድቦች ተከፋፍለው፣ መጠናዊ የሆኑት ደግሞ በቁጥርና በመቶኛ ስሌት ውጤታቸው ተተንትኖና ተብራርቶ ቀርቧል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በእነዚህ መጠናዊና ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች በጣምራ የተገኙት የጥናቱ ውጤቶችና ማብራሪያ ይቀርባል።

በአጠቃላይ ተጣጥሞሽን በተመለከተ በዓይነታዊና በመጠናዊ ዘዴዎች የተካሄዱት የውጤት ትንተናዎች በጣምራ እንዳሳዩት፤ አንደኛ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና በአዕምሯዊ ምድብ ስድስት ችሎታዎች መካከል ያለው ተዛምዶ አሉታዊ ወሽባክን የሚያበረታታ ነው። አሉታዊነቱም በጣም ጉልህና ጠንካራ የሚባል ጭምር ነው። ከአምሳና ስልሳ ዓመታት በፊት ሲተቹ እንደነበሩት ፈተናዎች ከ90% በላይ የሚሆኑት ጥያቄዎች የተማሪዎችን ዕውቀትና ግንዛቤ የሚለኩ ሆነው ነው የተገኙት። በዚህ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊመዘኑ ይገባቸው የነበሩት የመተግበር፣ የመተንተን፣ የማቀናበርና የመገምገም ችሎታዎች ከ10% በሚያንሱ ጥያቄዎች ብቻ እንዲወከሉ እየተደረገ ነው። ይህም የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና አንደኛ Bloom እና ሌሎች (1956) እንዲህ ያለውን በዝቅተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታ ላይ የሚያተኩር የፈተና ዝግጅት ችግር ለማስወገድ ያዳበሩትን የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች እንደሚጻረር፤ ሁለተኛ፣ ቀደም ብለው የተገለፁትን በሀገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና በሥርዓተ ትምህርቱ ማስተግበሪያ ማዕቀፍ የተሰጡ የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ ሦስተኛ፣ በቋንቋው ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት የቀረቡ የትምህርቱ ዓላማዎችን በሚቃረን መልኩ

እየተዘጋጀ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የዚህም አንድምታ የፈተናዎች ኤጀንሲ አንደኛ፣ የሚመርጣቸው ጥያቄ አውጭዎች/ ጸሐፊዎች እነዚህን ዓላማዎች ያገናዘቡ ጥያቄዎች የማውጣት/ የመጻፍ አቅም/ ክሂል የላቸውም፤ ሁለተኛ፣ በኤጀንሲው ለየትምህርት ዓይነቶቹ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በተደጋጋሚ እየተሰጠ ያለው የፈተና አዘገጃጀት አቅም ማጎልበቻ ስልጠና በባለሙያዎቹ ላይ የሚፈለገውን ለውጥ አስገኝቶ ፈተና አዘጋጆቹ (ጥያቄ ጸሐፊዎች) የሚያወጧቸው ጥያቄዎች፣ እነዚህን ዓላማዎች በፖሊሲውና በቋንቋው ትምህርት በተሰጣቸው ትኩረት መሰረት የሚወከሉበትን አቅጣጫ ማሳየት አላስቻላቸውም የሚል ነው፡፡ ይህም የፈተናዎች ኤጀንሲ በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ላይ በተለይ የአማርኛ ፈተና ዝግጅትን በሚመለከት ሊያስብበት እንደሚገባ የሚያመላክት ጭምር ነው፡፡

ሁለተኛ፣ ለደረጃው በተዘጋጁት የቋንቋው መርሐ ትምህርቶችና በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት ላይ በተካሄደው ፍተሻ ምንም እንኳ በትምህርቱ ያልተካተተ ጥያቄ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ እንደማይጨመር በጥናቱ ቢረጋገጥም በመርሐ ትምህርቶቹና በፈተናዎቹ ጥያቄዎች መካከል ያለው ግንኙነት በአብዛኛው አሉታዊ (ተመጣጣኝነት የሌለው) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው በተዛማጅ ድርሳናት ክፍል የተጠቀሱትን በAlderson እና ሌሎች (1995)፣ Brown (2004) Hughes (2003) Green (2007)፣ siddick (2010) የቀረቡ ጠቃሚ የአፃንታዊ ተዛምዶና አፃንታዊ ወሽባክ መመስረቻ ሀሳቦች እያገናዘበ እንደማይዘጋጅ የሚጠቁም ነው፡፡ ለዚህ አንዱ አስረጅ በቋንቋው መርሐ ትምህርቶች ይበልጥ ትኩረት የተሰጠው ለክሂሎች ቢሆንም በፈተናዎቹ ጥያቄዎች ያገኙት ውክልና ግን በመርሐ ትምህርቶቹ ከተመደበላቸው የክፍለ ጊዜ መጠን ጋር የሚመጣጠን ሆኖ አለመገኘቱ ነው፡፡ ክሂሎች በተግባር እንጂ በምርጫ ፈተና ለመመዘን አመቺ ባለመሆናቸው የተፈጠረ ችግር ነው እንዳይባል ደግሞ የሚገመተው ችግር የማይመለከተው የንባብ ክሂል ንዑሳን ክሂሎቹም በፈተናዎቹ በአግባቡ እንዲወከሉ አልተደረጉም፡፡ ይህም የችግሩ ምንጭ ከክሂሎች ለምዘና አመቺ አለመሆን ጋር ብቻ የተያያዘ ነው ብሎ ለማሰብ እንዳይቻል አድርጎታል፡፡ ችግሩ ከክሂሎች ለምዘና አመች ካለመሆን ጋር ብቻ የተያያዘ ካልሆነ ደግሞ ሌላው የችግሩ ምንጭ ሊያያዝ የሚችለው ከጥያቄ አዘጋጆችና ከፈተናው ዝግጅት ባለሙያዎች አቅም ማነስ ጋር ነው፡፡ በእርግጥ የግንኙነታቸው

አሉታዊነት እንዲጎላ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ፈተናው በምርጫ ጥያቄ ብቻ የተገደበ በመሆኑና አብዛኛዎቹን በትምህርትነት የተካተቱ ክሂሎች በምርጫ ጥያቄ ለመመዘን ባለመቻሉ ነው ማለት ይቻላል። ሦስተኛው በትምህርቱና በማጠናቀቂያ ፈተናው አሉታዊ ግንኙነት ምክንያት በሥነ-ጽሑፍና በሰዋስው ትምህርትነት ከተካተቱት ክፍሎች መካከል ከክሂሎች ጋር የሚደጋገፉት ላይ ማተኮር አለመቻሉ ነው። የዚህ ችግር መንስኤም ሊመዘኑ ከሚገባቸው ክፍሎች ላይ ከማተኮር ይልቅ Hughes (2003) እንዳሉት ጥያቄ ለማውጣት/ ለማዘጋጀት አመቺ በሆኑት ላይ በመተኮሩ የተፈጠረ ችግር ነው ብሎ መደምደም ይቻላል። እነዚህ በሁለቱ ክፍሎች መካከል የተፈጠሩት አሉታዊ ግንኙነቶችም የማጠናቀቂያ ፈተናው ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርትን የሚያበረታታ ሳይሆን የሚያዳክም እንደሆነ የሚያመላክቱ ናቸው። የእነዚህ ችግሮች ዋነኛ ምንጭም መፍቻ ቁልፍም በፈተናዎች ኤጀንሲ፣ በኤጀንሲው የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎችና ጥያቄ አዘጋጆች አካባቢ ያለ ነው ማለት ይቻላል።

በዚህ በሁለተኛው የጥናቱ ክፍል የተመረመረው ሦስተኛ ጉዳይ በመርሐ ትምህርቶቹና በክፍል ማጠቃለያ ፈተናዎች፣ በክፍል ፈተናዎቹና በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት ነው። በዚህ በኩል የተደረገው ፍተሻ እንዳሳየው የክፍል ፈተናዎቹ እንደማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ሁሉ የቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ነጸብራቅ ወይም አዎንታዊ የሚባል ተዛምዶ የሚታይባቸው ሆነው አልተገኙም። ይልቁኑ በይዘትም በቅርጽም ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጋር ትይዩ ወይም አዎንታዊ ተዛምዶ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። የዚህም አንዱ ምክንያት ውጫዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት፣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥሩ ውጤት እንዲያስመጡ ርቱዕና ኢርቱዕ በሆነ መንገድ የሚያሳድሯቸው ጫና ውጤት ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው፣ ሥርዓተ ትምህርቶቹ እንዲተገበሩና በክፍል ፈተናዎቹ እንዲገመገሙ የሚያበረታታ የትምህርት ክትትል፣ ቁጥጥርና ግምገማ ሥርዓት ስለሌለ ሊሆን ይችላል። ሦስተኛ፣ የተማሪዎች የመማር ፍላጎትና ስለምዘና ያላቸው ግንዛቤ የሚያሳድረው ጫና ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም መምህራኑ የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት ማዕከል ካላደረጉ የስራ አፈጻጸማችን ሲሞሉ ሊጎዱን ይችላሉ ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹም ሆኑ የክፍል ፈተናዎቹ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA

ከቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት መለየት ማለት ደግሞ የክፍል ትምህርቱ/ የማስተማር-መማር ሂደቶቹ የሥርዓተ ትምህርቱ ሳይሆን የፈተናዎቹ ነጸብራቅ እንደሚሆኑ ያመለክታል፡፡

ከዚሁ ከቋንቋው ትምህርትና ከፈተናው ተዛምዶ ጋር ተያይዞ በተለይ ከመምህራን ጋር የተካሄዱ ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተገኙ መረጃዎች የውጤት ትንተናዎች ይበልጥ ግልጽ እንዳደረጉት አንደኛ የአማርኛ ቋንቋ የማጠናቀቂያ ፈተና ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ሲነጻጸር ተማሪዎች የተሻለ ውጤት የሚያመጡበትና ብዙ ጊዜ ለአብዛኞቹ ተማሪዎች ወደ መሰናዶ ትምህርት ለማለፍ ከሚያስፈልጓቸው ሰባት የትምህርት ዓይነቶች አንዱ በመሆን እያገለገላቸው ያለ የትምህርት ዓይነት ነው፡፡ በዚህ ሀሳብ የየትምህርት ቤቶቹ ምክትል/ ርዕሳነ መምህራን እንዲሁም የዞን የትምህርት ባለሙያዎች ይስማማሉ፡፡ ሁለተኛ የማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎችን ለመሰናዶ ትምህርት ዝግጁ መሆናቸውንም ሆነ ለሕይወት ወይም ከትምህርት በኋላ ለሚሰማሩበት ሥራ በቋንቋው መገልገል የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን ለመመዘን ብዙም በቂ ያለመሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ የዚህም ዋነኛው ምክንያት ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ተማሪዎች በመሰናዱ ትምህርታቸውና በሕይወታቸው ወይም ወደፊት ሊሰማሩበት በሚችሉት የስራ መስክ የሚያስፈልጋቸውን/ ሊያጋጠማቸው የሚችለውን የቋንቋ አጠቃቀም በብቃት የማይመዝኑ በመሆናቸው ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እንደ የፈተና ጥያቄች ትንተናና የጽሑፍ መጠይቆቹ ሁሉ በቡድን ውይይቶቹም ከይዘት አንጻር የፈተናዎቹ ጥያቄዎች በትምህርቱ ላይ ተመስረተው የሚዘጋጁ ናቸው የሚል ግንዛቤ እንዳለ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ በመጠናዊም ሆነ በዓይነታዊ ስልቶች የተተነተኑት መረጃዎች ውጤት እንዳመለከተው የፈተናዎቹ ሁሉም ጥያቄዎች ከሥርዓተ ትምህርቱ በተለይም ከመማሪያ መጽሐፎቹ ይዘት ላይ የሚወጡ/ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ይህም በአንዳንድ መምህራን ዘንድ በአዎንታዊነት የታየ ነው፡፡ ለምሳሌ በመጻፍ ክሂል ስለቃለ ጉባኤ፣ ማመልከቻ፣ ደብዳቤ፣ ዘገባ፣ በጥቅሉ ስለድርሰት የሚጠይቁ ጥያቄዎች መካተታቸው አጠያየቁ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ የተገደበ ቢሆንም እነዚህን ጉዳዮች መምህራኑ ለማስተማር፣

ተማሪዎቹ ለመማር ፍላጎት እንዲያድርባቸው አድርገዋል። ፈተናዎቹ ከመልመጃዎቹ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ደግሞ ከአብዛኞቹ ተሳታፊዎች የተገኘው መረጃ በሁለቱ መካከል ያለው ተዛምዶ አሉታዊ እንደሆነ አሳይቷል። የዚህም መሰረታዊ ምክንያት የአብዛኞቹ መልመጃዎች አቀራረብ በተግባር መጻፍን፣ መናገርን፣ መከራከርንና ማዳመጥን የሚጠይቅ መሆኑ ነው። ይህም የፈተናዎች አጠያየቅ ተማሪዎች በክፍል ትምህርት የሚለማመዱባቸው መልመጃዎች ነጻብራቅ መሆን ይገባቸዋል፤የሚለውን Missick (1996) የአዎንታዊ ወሽባክ ማበረታቻ ሀሳብ እንደሚቃረን ያሳያል።

ከዚህም የማጠናቀቂያ ፈተናው ምንም እንኳ ይዘቱ በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ቢገኝም፣ አንደኛ፣ በመርሐ ትምህርቶቹ ትኩረት ለተሰጣቸው ክፍሎች ትኩረት የሚሰጥ ሳይሆን ለመጠየቅ አመች በሆኑት ክፍሎች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ፣ ሁለተኛ፣ የቋንቋው ትምህርት መሰረታዊ ጉዳዮች ከሆኑቱ መልመጃዎች ጋር የማይጣጣም በመሆኑ፤ ሦስተኛ ተማሪዎቹ የ፪ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ለሕይወት/ ለስራ ዓለም ወይም ለቀጣዩ የትምህርት ደረጃ ዝግጁ መሆን አለመሆናቸውን በብቃት ስለማይመዝን በMadaus (1988)፣ Siddiek (2010) ስራዎች እንደተገለጠው በአብዛኛዎቹ አዎንታዊ ሳይሆን አሉታዊ ወሽባክን የሚያበረታታ ነው ብሎ ማጠቃልል ይቻላል።

4.4 የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ ያላቸው ግንዛቤ (Perceptions)

በምዕራፍ ሦስትና በዚሁ ምዕራፍ መግቢያ እንደተጠቆመው፣ በጥናቱ የሚመለሱ የመምህራን ግንዛቤን (Perceptions) የሚመለከቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለገለው የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ነው። በመሆኑም ይህ ክፍል በዚህ የጽሑፍ መጠይቅ በምርምሩ ሦስተኛ ጥያቄ ስር የተካተቱትን ስድስት ጥያቄዎች በሚመለከት የተሰበሰቡት መረጃዎች የውጤት ትንተናና ማብራሪያ ጥያቄዎቹ በቀረቡበት ቅደም ተከተል መሰረት የቀረቡበት ነው። በዚሁ መሰረት መጀመሪያ የጽሑፍ መጠይቁን በመመላት የተሳተፉት መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው (በክፍል

ውስጥ ተግባራት/ ጊዜ አመዳደብ፣ በማስተማሪያ ዘዴ፣ በትምህርት ይዘቶች፣ በትምህርት መሣሪያዎችና በክፍል ትምህርት ምዘና) ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ያላቸው ግንዛቤ (Perceptions) በገላጭ ስታትስቲክስ ተተንትኖና ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ ቀጥሎ የማጠናቀቂያ ፈተናው መምህራኑ በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ላዳበሩት ግንዛቤ/ ለወሸባክ መከሰት ምክንያቶች (Factors) ይሆናሉ የሚባሉ ጉዳዮች እንዲሁ በገላጭ ስታትስቲክስ ተተንትነውና ተብራርተው ቀርበዋል፡፡ ቀጣዮቹ ክፍሎች ደግሞ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጦውና በመምህራን ባህርያት፣ እንዲሁም መምህራን ማጠናቀቂያ ፈተናው ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጦው) እና በዐውዳዊ ባህርያት መካከል ያሉት ተዛምዶዎች በተዛምዶና ጎብረ ድኅረት (Multiple Regression) ስታትስቲክስ ተተንትነውና ተብራርተው የቀረቡባቸው ናቸው፡፡ እነዚህኑ ጉዳዮች በሚመለከት ከመምህራን ጋር በተካሄዱ ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች የውጤት ትንተናዎችና ማብራሪያዎችም በምርምር ጥያቄዎቹ ቅደም ተከተል መሰረት ከመጠናዊ ውጤት ትንተናዎች ቀጥለው እንዲቀርቡ ተደርገዋል፡፡

4.4.1. መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ ያላቸው ግንዛቤ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

4.4.1.1 መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በሚመለከት ስላላቸው ግንዛቤ በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው (በተግባራት / ጊዜ አደላደል፣ በማስተማሪያ ዘዴዎች፣ በማስተማሪያ መሣሪያዎች፣ በትምህርት ይዘቶችና በክፍል ምዘናዎች) ላይ ስለሚሳድረው ተጽዕኖ ያላቸው ግንዛቤ ምንድነው? የሚለው ከሦስተኛው መሰረታዊ ጥያቄ ስር ከተካተቱ በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች የመጀመሪያው ነው፡፡ በቅንፍ ውስጥ ከተዘረዘሩት ነጥቦች መረዳት

እንደሚቻለውም በዚህ ጥያቄ ትኩረት የሚሰጠው ፈተናው ተጽዕኖ ሊያሳድርባቸው በሚችሉ አምስት የትምህርት ምድቦች (domains) ወይም መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ እነሱም:- ሀ. ተግባራት /ጊዜ አደላደል፣ ለ. የማስተማሪያ ዘዴዎች ሐ. ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች መ. የሚያስተምሯቸው ይዘቶችና ሠ. የክፍል ትምህርት ምዘናዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ አምስት የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ምድቦች ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለማጥናትም እያንዳንዱ ምድብ በውስጡ ከአንድ በላይ የሆኑ ጥያቄዎች ተካተውበታል፡፡ ቀጥሎ በእያንዳንዱ ምድብ ስር የቀረቡ ጥያቄዎችና ለየጥያቄዎቹ የተሰጡትን ምላሾች ተናጠላዊና የጋራ አማካይና የየአማካዩ ተፅዕኖ የመፍጠር ደረጃ ይቀርባል፡፡

ሀ. የማጠናቀቂያ ፈተናው በተግባራት /ጊዜ አደላደል (Activity/Time Arrangement) ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ

ሰንጠረዥ4.5፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በተግባራት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ አማካይ

	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ Mean	መደበኛ ልይይት/ Std. Deviation	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ /Item Effect
1. የማጠናቀቂያ ፈተናው የተማሪዎችን የፈተና አሰራር ችሎታ ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትን እንዳከናውን ያነሳሳኛል የሚል እምነት አለኝ፡፡	89	3.8427	.87774	ጠንካራ
2. የማጠናቀቂያ ፈተናው መሰጠቱ ቢቋረጥ ወይም የሚያተኩርባቸው ይዘቶች ቢቀየሩ፣ አጠያየቁም ምርጫ ብቻ መሆኑ ቢቀር ለየትምህርቱ (ለእያንዳንዱ ክሂል፣ ለሰዋሰው ና ለሥነጽሁፍ ክፍሎች) የምመድበው ጊዜ፣ የማስተማር ዘዴዬና የክፍል ፈተና አዘገጃጀቴ ከበፊቱ የተለየ ይሆናል፡፡	89	3.4270	1.29586	መካከለኛ
3. የክፍል ውስጥ ተግባራትን/ መልመጃዎችን ሳዘጋጅና ተማሪዎቼን ሳሰራ የማጠናቀቂያ ፈተናውን መሰረት አደርጋለሁ ፡፡	89	3.9213	1.06840	ጠንካራ
4. በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የበለጠ ሽፋን የሚሰጠው ለሰዋሰውና ለስነጽሑፍ ትምህርቶች ነው ብዬ ስለማሰብ ተግባቦታዊ (የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ) ክሂሎችን ለማስተማር ከማውለው የበለጠ ጊዜ ለሁለቱ እሰጣለሁ፡፡	89	3.4270	1.21438	መካከለኛ
5. የተወሰኑ ክፍለ ጊዜያትን በተለይም የፈተናው ጊዜ እየቀረበ ሲመጣ የፈተና አሰራር ስልቶችን /ስትራቴጅዎችን ለማስተማሪያነት አውላለሁ ፡፡	89	3.9101	1.08335	ጠንካራ
6. አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ውስጥ ትምህርት ተግባራትን የማቅደውና የማዘጋጀው የማጠናቀቂያ ፈተናውን ሳይሆን ሌሎች ምክንያቶችን መሰረት አድርጌ ነው፡፡	89	2.7528	1.10042	መካከለኛ
ፈተናው በተግባራት/ጊዜ አመዳደብ ላይ በሚኖረው ተፅዕኖ ላይ የመምህራን ግንዛቤ አማካይ	89	3.55		ጠንካራ

በሰንጠረዥ 4.5 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው ይህን ክፍል በሚመለከት ለቀረቡት ስድስት ጥያቄዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጡት መልስ አማካይ 3.7 ነው። ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ጠንካራ (strong) ተጽዕኖ እንደሚያሳድር የሚያሳይ ነው። በተናጠል ሲታይም ለአብዛኞቹ ጥያቄዎች (ለጥያቄ ቁጥር 1፣ 2፣ 4 እና 6) የተሰጠው መልስ አማካይ ጠንካራ በሚለው የውጤት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ለቀሩት ሦስት ጥያቄዎች የተሰጠው ምላሽ መካከለኛ በሚለው ምድብ ውስጥ የሚገኝ ነው። የማይለካ ወይም ዝቅተኛ በሚለው የአማካይ ምድብ ውስጥ የገባ ምላሽ የለም። ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርቱ ተግባራት ላይ ጠንካራ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ያመላክታል።

ለ. የማጠናቀቂያ ፈተናው የማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ የመምህራን ግንዛቤ

ሰንጠረዥ 4.6፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ውጤት አማካይ

ጥያቄ (Item)	የተሳታፊዎች ድምር //N	አማካይ Mean	መደበኛ ልይይት/Std. Deviation	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ /Item Effect
7. የማስተማሪያ ዘዴዎችን የምመርጠው ተማሪዎቼን በማጠናቀቂያ ፈተናው ለስኬት የሚያበቁልኝ መሆናቸውን ግምት ውስጥ አስገብቼ ነው።	89	3.6067	1.20244	ጠንካራ
8.ተማሪዎቼን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት የማያስችሉ አንዳንድ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለማስተማሪያነት አልገለገልባቸውም።	89	2.5730	1.26030	መካከለኛ
ፈተናው በማስተማሪያ ዘዴ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ላይ መምራን ያላቸው ግንዛቤ አማካይ	89	3.09		መካከለኛ

በሰንጠረዥ 4.6 የቀረበው ውጤት እንደሚያሳየው የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫ ላይ መካከለኛ በሚባል ደረጃ ተፅዕኖ ያሳድራል። ይህም አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ጠንካራ ባይባልም የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና አጠቃቀም ሂደታቸው ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው።

ሐ. የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማሪያ መሣሪያዎች ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ የመምህራን ግንዛቤ

ሠንጠረዥ4.7፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ የመምህራን ግንዛቤ አማካይ

ጥያቄ (Item)	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
9. ከመማሪያ መፅሐፎቹ በተጨማሪ ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው ስኬታማ እንዲሆኑ የሚረዱ ናቸው የምላቸውን አጋዥ መፃሕፍትና ጽሑፎች እጠቀማለሁ	89	4.3708	.81717	ጠንካራ
10. ተማሪዎቼ ለማጠናቀቂያ ፈተናው ዝግጁ እንዲሆኑልኝ በማሰብ በፈተናው ሊካተቱ ይችላሉ ከምላቸው ምንጮች (መጽሐፎች...) ጥያቄዎችን እያዘጋጀሁ አለማምዳቸዋለሁ ፡፡	89	4.2584	.76170	ጠንካራ
11. ተማሪዎቼ ከማጠናቀቂያ ፈተናው አቀራረብ ጋር እንዲተዋወቁ ለማገዝ ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን እየሰሩ እንዲለማመዱ አደርጋለሁ ፡፡	89	4.3933	.68454	ጠንካራ
14. የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎችን ደጋፊ ዕሁፎች /መጽሐፎች መጠቀም እንዳለብኝ ተፅዕኖ ያሳድርብኛል፡፡	89	3.3820	1.10274	መካከለኛ
15. በመማሪያ መጽሐፉ የተካተቱትን ይዘቶችና ተግባሮች በሙሉ በትምህርት ዓመቱ ለቋንቋው ትምህርት በተመደበው ክፍለ ጊዜ ለመሸፈን እንኳ አስቸጋሪ ቢሆንም ጊዜውን አብቃቅቼ ለማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያግዙ ሌሎች መፃሕፍትን በአጋዥነት እጠቀማለሁ ፡፡	89	4.1236	.90227	ጠንካራ
ፈተናው በማስተማሪያ መሳሪየዎች ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ የመምህራን ግንዛቤ አማካይ	89	4.1056		ጠንካራ

በጥናቱ የተሳተፉ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው ለማስተማር በሚጠቀሙባቸው ተጨማሪ/ አጋዥ መሣሪያዎች (መጻሕፍት፣ ጥያቄዎች...) ምርጫ ላይ ጠንካራ (4.1056) ተጽዕኖ ያደርሳል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው ሰንጠረዥ 4.7 ያመለክታል፡፡ ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው መምህራንና ተማሪዎች ለፈተና የሚያግዙ መጻሕፍት፣ ያለፉ ዓመታት የፈተና ወረቀቶችና መሰል ማቴሪያሎች ላይ እንዲያተኩሩ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ያሳያል፡፡ ለየጥያቄው በአብዛኞቹ መላሾች የተሰጠው ምላሽ እንደሚያመለክተውም ከ14ኛው ጥያቄ በስተቀር ለሁሉም ጥያቄዎች የሰጡት መልስ ደረጃ ፈተናው በማስተማሪያ መሳረያዎች ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል ነው፡፡ ከዚህም በማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽእኖ ምክንያት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በፈተናው ውጤታማ ያደርጉልናል/ ለስኬት ያበቁልናል የሚሏቸውን አጋዥ መጻሕፍትና ሌሎች ማቴሪያሎች ለማስተማሪያነት እንደሚጠቀሙ፣ ከተለያዩ ምንጮች (sources) ጥያቄዎችን

እያዘጋጁ ተማሪዎቻቸውን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት እንዲለማመዱ እንደሚያደርጉ፣ እንዲሁም ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ጥያቄዎች እያሰሩ ተማሪዎቻቸው ከማጠናቀቂያ ፈተናው አቀረራረብ ጋር እንዲተዋወቁ እንደሚያደርጉ መረዳት ይቻላል፡፡

መ. የማጠናቀቂያ ፈተናው በቋንቋው ትምህርት ይዘቶች ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የመምህራን ግንዛቤ

ሰንጠረዥ 4.8፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው የትምህርት ይዘቶች ምድብ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ አማካይ ውጤት

ጥያቄ (Item)	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
12. የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛውን የቋንቋ ትምህርት ክፍል (ክሂል፣ ሰዋስው፣ ሥነጽሑፍ) ነው የበለጠ ትኩረት ሰጥቼ ማስተማር ያለብኝ? የሚለውን ለመወሰን ተፅዕኖ ያሳድርብኛል	89	3.1573	1.21449	መካከለኛ
13.አንዳንድ የመማሪያ መጽሐፉ/ፎቹ ክፍሎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ስለማይሸፍኑ ሳስተምር እዘላቸዋለሁ ወይም እንደነገሩ ነካክቼ አልፋቸዋለሁ፡፡	89	2.8090	1.24203	መካከለኛ
16.በማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረት የሚሰጠው ለአራቱ የቋንቋው ክሂሎች ነው፤ የሰዋስውና የስነጽሑፍ ትምህርቶች ችላ የተባሉ ናቸው፡፡	89	4.1011	.94201	ጠንካራ
17.ቋንቋውን ሳስተምር በማጠናቀቂያ ፈተናው የመካተት አጋጣሚያቸው ክፍተኛ ነው ብዬ በማስባቸው የመማሪያ መጽሐፉ(ፎቹ) ክፍሎች ላይ አተኩራለሁ፡፡	89	3.8090	1.07531	ጠንካራ
18.ምንም እንኳ አንዳንድ ርዕሰ ጉዳዮች /ይዘቶች በማጠናቀቂያ ፈተናው ላይጠየቁ እንደሚችሉ ባውቅም ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ በቂ ስለሆነ በመማሪያ መጽሀፉ(ፎቹ) የተካተትን ሁሉ እሸፍናለሁ፡፡	89	3.7416	.99462	ጠንካራ
19. የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርቱ ይዘቶች ምርጫ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡	89	3.4157	1.16589	መካከለኛ
መምህራን ቋንቋውን የሚያስተምሩባቸው ይዘቶች ላይ ፈተናው የሚያሳድረው ተጽዕኖ ላይ ያላቸው ግንዛቤ አማካይ	89	3.5056		ጠንካራ

Alderson (2004) ውጫዊ ፈተናዎች በቋንቋ ትምህርት ይዘት ላይ ተጽዕኖ ማድረሳቸው አይቀሬ ነው ከሚል እምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ ዐውድ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለውን እውነታ ለመመርመር ለጥናቱ ተሳታፊዎች ስድስት ጥያቄዎች ቀርበውላቸው በሰንጠረዥ4.8 እንደተመለከተው ለስድስቱም ምላሽ

ሰጥተዋል፡፡ ምላሻቸውም Alderson (2004) እንዳሉት የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርቱ ይዘቶች ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል እምነት እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ በእርግጥ በዝርዝር ለየጥያቄው የሰጡት ምላሽ የጥንካሬ ደረጃ ሲታይ መካከለኛ እና ጠንካራ የተባሉት እኩል ሦስት ሦስት ናቸው፡፡ ሆኖም መካከለኛ የተባሉት አማካይ ጠንካራ ወደሚለው የተጠጋ ስለሆነ የጠቅላላው አማካይ ጠንካራ በሚለው ደረጃ ላይ ሊያርፍ ችሏል፡፡ በተለይ ጠንካራ በሚለው ምድብ ውስጥ የገቡት፤ አንደኛ ለአራተኛው ጥያቄ ከሰጡት መልስ ጋር ወጥነት እንዳለው ለማረጋገጥ ለሚያግዘው ለ16ኛው ጥያቄ ማለትም በማጠናቀቂያ ፈተናው ክሂሎች ችላ እንደሚባሉ፣ የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች ደግሞ የተሻለ ቦታ/ ትኩረት እንደሚያገኙ፣ ለሚጠይቀው ጥያቄ መሆኑ፣ ሁለተኛ ቋንቋውን ሲያስተምሩ በማጠናቀቂያ ፈተናው በተሻለ ደረጃ ለሚካተቱት የመማሪያ መጽሐፎቹ ክፍሎች የተሻለ ጊዜ ወይም ትኩረት ሰጥተው እንደሚያስተምሩ፤ የገለጹባቸው ክፍሎች መሆናቸው፣ መምህራኑ ፈተናው በትምህርቱ ይዘት ረገድ ጠንካራ ተፅዕኖ ይፈጥራል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡

ሠ. የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራኑ የክፍል ትምህርት ምዘና ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ የመምህራን ግንዛቤ

የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የክፍል ምዘና ተግባር ላይ ተፅዕኖ እንደሚፈጥርና የተፅዕኖው ደረጃም ጠንካራ እንደሆነ በሰንጠረዥ 4.9 የቀረበው መረጃ ያሳያል፡፡ ይህም በአብዛኞቹ መምህራን የሚከናወኑት የምዘና ሂደቶች ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር እንደሚመሳሰሉና ተማሪዎቻቸውን ለማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያዘጋጁ ዓይነት እንደሆኑ ያሳያል፡፡ በሌሎች መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት ትንተናም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእርግጥ በዚህ በጽሑፍ መጠይቁ ለጥያቄ 22፣ 23 እና 24 የሰጧቸው ምላሾች ግን የተጋነኑ ይመስላሉ፡፡ ምናልባትም ሊሰሩ የሚገባቸው ተግባሮች እንደሆኑ ከማመን የመነጩ ምላሾች ይመስላሉ፤ ወይም አንዳንዶቹ ስለክሂሎች የፅንሰ ሃሳብ ጥያቄዎችን ስለሚጠይቁ በፅንሰ ሃሳብ ደረጃም ቢሆን ክሂሎችን እንደሚመዝኑ ከማሰብ የሰጡት ምላሽ ታክሎበት ሊሆን ይችላል፡፡ በአጠቃላይ በአባሪነት ከተያያዙት የክፍል ፈተናዎች

ማስተዋል እንደሚቻለው፣ ለእነዚህ ጥያቄዎች የተሰጠው ምላሽ በተግባር በየትምህርት ቤቱ እየተሰራ ያለውን የምዘና ሂደት የሚያንጸባርቅ አይደለም ማለት ግን ይቻላል።

ሰንጠረዥ 4.9፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በክፍል ትምህርት ምዘና ምድብ ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ የመምህራን ግንዛቤ

ጥያቄ (Item)	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
20.የተማሪዎችን የቤትና የክፍል ስራ እንዲሁም ፈተናዎች ለመገምገም የምጠቀምባቸው መስፈርቶች ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት የሚያግዙ ናቸው።	89	4.0337	.92256	ጠንካራ
21. ለተማሪዎቼ ሙከራ(quiz)፣ ቴስትና ፈተና ሳዘጋጅ ጥያቄዎቼ ባለፉት ዓመታት በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ውስጥ ከተነሱ ጉዳዮች ጋር የሚዛመዱ እንዲሆኑልኝ ጥረት አደርጋለሁ።	89	3.6517	1.07768	ጠንካራ
22. አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቼን የምገመግመው በምርጫ ሳይሆን እንደ ጻፉ (ዐረፍተነገር፣ አንቀጽ፣ ድርሰት፣ ዘገባ...)፣ግለጹ፣ አብራሩ፣ ተንትኑ፣ አስረዱ...የሚሉ አጠያየቆችን በመጠቀም ነው።	89	2.9438	1.21879	መካከለኛ
23. በክፍል ፈተናዎች የተማሪዎቼን የማዳመጥ ክሂል እፈትናለሁ።	89	3.0787	1.09984	መካከለኛ
24. በክፍል ፈተናዎች የተማሪዎቼን የንግግር ክሂል እፈትናለሁ።	89	3.2022	1.10967	መካከለኛ
25. በማዘጋጃቸው የክፍል ፈተናዎች ውስጥ ተማሪዎቼ ልዩ ልዩ ድርሰቶችን (አንቀጽ፣ ዘገባ፣ ደብዳቤ፣ ድርሰት...) በተግባር እንዲፅፉ በማድረግ የመጻፍ ክሂልን እመዝናለሁ።	89	3.5393	1.14868	ጠንካራ
26. በማዘጋጃቸው የክፍል ፈተናዎች ውስጥ የተማሪዎቼን የተለያዩ ንዑሳን አንብቦ የመረዳት ክሂሎች (ሀቅን ከግል አስተየየት፣ ምክንያትን ከውጤት፣ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን መለየትን ፣ እንድምታ፣ ማጠቃለል፣ መደምደም...) ለመገምገም የሚያስችሉ ክንውኖችን አሳካትትም።	89	3.6067	1.01822	ጠንካራ
27. ተማሪዎቼን የምመዝንበት ስልት በአብዛኛው ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ይመሳሰላል።	89	3.6742	1.01997	ጠንካራ
ፈተናው በክፍል ፈተናዎች ላይ የሚሳድረው ተጽዕኖ ላይ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ አማካይ		3.5548		ጠንካራ

ይህን ክፍል ለማጠቃለል፣ ከላይ በተለያዩ ሰንጠረገሮች የቀረቡት የውጤት ትንተናዎች፣ የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ አምስት ምድቦች ላይ በአራቱ ጠንካራ፣ በአንዱ መካከለኛ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው

አሳይተዋል፡፡ በእያዳንዱ ምድብ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ደረጃ ሲታይም በ4.1056 አማካይ በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ፈተናው በማስተማሪያ መሣሪያዎች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ሲሆን በ3.554 አማካይ፣ ሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው በመምህራን የክፍል ትምህርት ግምገማ ላይ የሚሳድረው ተጽዕኖ ነው፡፡ በ3.55 አማካይ በሦስተኛነት የሚከተለው ደግሞ ፈተናው በተግባራት/ ጊዜ አደላደል ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ነው፡፡ ፈተናው በተግባራት ላይ ከሚያሳድረው ተጽዕኖ በትንሽ ልዩነት በ3.5056 አማካይ አራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ደግሞ ፈተናው በትምህርቱ ይዘቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ነው፡፡ ፈተናው በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ግን መካከለኛ ነው ወይም ጠንካራ አይደለም፡፡

4.4.1.2 መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በሚመለከተ ስላላቸው ግንዛቤ በቡድን ተኮር ውይይቶች የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ይህ ክፍል በቡድን ተኮር ውይይቶች በተገኘ መረጃ ላይ በመመስረት የማጠናቀቂያ ፈተናው በስድስት የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ምድቦች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በተመለከተ መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ ለመመርመር የተሞከረበት ነው፡፡ ስድስቱ ምድቦችም የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት፣ የትምህርቱ ተግባራት/ መልመጃዎች፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ አጋዥ የማስተማሪያ መሳሪያዎች/ ማቴሪያሎች፣ የትምህርት ይዘቶችና የክፍል ትምህርት ምዘናዎች የሚሉት ናቸው፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል በጥልቀት ለመፈተሽ የተሞከረው በተተኳሪ የቡድን ውይይቶቹ ከተሳተፉት መምህራን ከተገኘው መረጃ በመነሳት የማጠናቀቂያ ፈተናው በእነዚህ ስድስት የትምህርት ምድቦች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ፣ የተጽዕኖ ዓይነትና ደረጃ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት በአጠቃላይ በአምስቱ ቦታዎች /ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ 25 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር የተካሄዱት የቡድን ተኮር ውይይቶች የተገኘው መረጃ ውጤት ትንተና አብዛኞቹ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው ከላይ በተጠቀሱት ስድስት የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ምድቦች ላይ አዎንታዊም አሉታዊም ተዕዕኖዎች እያሳደረ ነው የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ ቀጥሎ ከእቅድ በመነሳት በእያንዳንዱ የቋንቋው ትምህርት ምድብ (Domain) ላይ የማጠናቀቂያ

ፈተናው የሚያሳድረውን ተጽእኖ፣ የተጽዕኖ ዓይነትና ደረጃ በተመለከተ የተገኘው የመረጃ ትንተና ውጤትና ማብራሪያ በተናጠል ቀርቧል፡፡

ሀ. የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ

የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የትምህርት ዕለታዊ/ሳምንታዊም ሆነ ዓመታዊ ዕቅድ አዘገጃጀት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በተመለከተ ወይም ዓመታዊና ሳምንታዊ (ዕለታዊ) ዕቅድ ሲያዘጋጁ ፈተናው ተፅዕኖ እንዳለው ወይም እንደሌለው እንዲገልጹ ለተጠየቁት ጥያቄ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች የሰጡት መልስ በሁለቱም ደረጃ ፈተናው ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል ነው፡፡ ለምሳሌ መምህር$_{21}$ “ዓመታዊና ዕለታዊ ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ አንድ መምህር ሲያቅድ ፈተናውን እያሰበ ነው፤” ሲሉ መምህር$_{7}$ በተመሳሳይ ሁኔታ “ዕለታዊና ዓመታዊ ዕቅድ ስናዘጋጅ የማጠናቀቂያ ፈተናውን ታሳቢ አድርገን ነው ... ተማሪዎች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር የእኛ ስራ ስለሆነ ያንን ታሳቢ አድርገን ነው የምናዘጋጀው” ብለዋል፡፡ በእነዚህ ሁለት ትምህርት ቤቶችና በሌላ አንድ ትምህርት ቤት የተሳተፉ መምህራን በሙሉ በዕቅድ ዝግጅት ሂደት ላይ ፈተናው ተጽእኖ እንደሚሳድር የገለጹ ሲሆን በሌላ አንድ ትምህርት ቤት ከተሳተፉት አምስት መምህራን መካከል ሁለቱ፣ በትምህርት ቤት አንድ ከተሳተፉት መካከል ደግሞ አብዛኞቹ እቅድ የምናዘጋጀው የመማሪያ መጽሐፎቹን ቅደም ተከተል ተከትለን ስለለሆነ የፈተናው ተፅዕኖ ግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም የሚል ሀሳብ አንጸባርቀዋል፡፡ ለምሳሌ ከትምህርት ቤት አንድ መምህር$_{1}$ ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ “እኔ እንኳን ዓመታዊ ዕቅድ የምሰራው ያሉትን ይዘቶች /እውቀታቸው እንዲጨምር ነው እንጅ ፈተና የማለፍ ያለማለፍ ነገር እኔ አስቤው አላውቅም” ብለዋል፡፡ መምህር$_{3}$ ም እንዲሁ “ዓመታዊ ዕቅድ ስናዘጋጅ መሰረታዊ መነሻችን የሚሆነው የመማሪያ መጽሐፎቹ፤ ሲለበሶቹና የመምህሩ መምሪያ ናቸው፡፡” በማለት የቀዳሚዋን መምህርት ሀሳብ ደግፈዋል፡፡ መምህር$_{12}$ ደግሞ ከዚህ በተጻራረ እንዲህ ይላሉ፤

> እኔ ትኩረት የማደርገው ፈተናውን ነው፡፡ ማለት መጽሐፉን እለቃለሁ ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ፈተናው ከመጽሐፉ ነው የሚወጣ፡፡ ግን ከመጽሐፉ ለፈተናው የሚጠቅመውን ክፍል እንድጠቀም እገደዳለሁ፡፡

ምክንያቱም መጽሐፉ ላይ ያለውን ነገር ሁሉ እጠቀማለሁ ካልኩ እነሱን ላዘጋጃቸው አልችልም። መጽሐፉ ላይ መጻፍ አለ፤ ክሂሎችን እያንዳንዱን ያያል። ዋናው ፈተናው ላይ የሚያስፈልጉት ክሂሎች ማንበብና ምናልባት፣ ዋናው ማንበብ ነው። ስለዚህ እኔ ትኩረት የምሰጠው ማንበቡን ነው፤...ሦስቱን ክሂሎች የተወሰነ ጊዜ ካሳየሁ በኋላ ወደ መጨረሻ አካባቢ ግን ለፈተናው ይዘት ይጠቅማሉ የምላቸውን ጉዳዮች ብቻ አያለሁ፤ የመጻፉንም፣ ዓመታዊ እቅዱንም ሳልስት...እነዚያ ላይ በማተኮር ያው ለማዘጋጀት እጥራለሁ።

ሌሎች ተሳታፊዎች ደግሞ ፈተናው ከመማሪያ መጽሐፎቹ የማይወጣ/ ከመማሪያ መጽሐፎቹ ላይ የሚመሰረት ስለሆነ በመማሪያ መጽሐፎቹ ላይ ተመስረተን ነው የምናቅደው የሚል ሀሳብ በውይይቶቹ አንጸባርቀዋል። በእነዚህኛዎቹ አስተሳሰብ በመማሪያ መጽሐፎቹ መሰረት ማቀድና ፈተናውን ታሳቢ አድርጎ ማቀድ ልዩነት የለውም። ምክንያቱም ፈተናው በአብዛኛው የሚዘጋጀው በትምህርቱ መሰረት ነው። የፈተናዎቹ ጥያቄዎች በመማሪያ መጽሐፎቹ ላይ የሚመሰረቱ ከሆነ ደግሞ እቅድን በመጽሐፎቹም ሆነ በፈተናው ላይ አተኩሮ ማዘጋጀት ብዙም ልዩነት አይኖረውም። ለምሳሌ መምህር$_{25}$ ስለዚሁ ጉዳይ በገለጹበት ክፍል "በዚህ ሁለት ሦስት ዓመት ፈተናዎቹ በመጽሐፉ ላይ መሰረት አድርገው ነው የሚዘጋጁት 95%፣ 96%ቱ መቼም ባለካውም እስከዚያ የሚደርስ ነገር መጽሐፉን መሰረት ያደረገ ነው ማለት ነው። ስለዚህ መጽሐፉን ማስተማር ለፈተና ዓልሞ ማስተማር ነው ብዬ እገምታለሁ። እቅዱም በዚያ መሰረት ነው የሚታቀደው፣ በመጽሐፉ ላይ ነው።" ብለዋል።

በአጠቃላይ የመረጃ ትንተና ውጤቱ፣ አንደኛ፣ የፈተናው ተፅዕኖ የሚጀምረው ዓመታዊ እቅድ ዝግጅት ላይ ነው፤ የሚል ግንዛቤ ያላቸው መምህራን መኖራቸውን፣ ሁለተኛ፣ ከዚህ በተለየ ሁኔታ የዕቅድ መነሻ የምናደርገው የሥርዓተ ትምህርት መሳሪያዎችን (መርሐ ትምህርቶቹን፣ የመማሪያና የማስተማሪያ መጽሐፎቹን) እንጅ ፈተናውን አይደለም የሚልና ሦስተኛ በመማሪያ መጽሐፎቹ መሰረት ማቀድ ተማሪዎችን ለፈተና ለማዘጋጀት ዓልሞ ከማቀድ የሚለይ አይለይም የሚል ዕምነት ያላቸው መምህራን እንዳሉ መገንዝብ ተችሏል። ሁለቱም ሀሳቦች ፈተናዎቹ

በመምህራን ላይ ተጽዕኖ ማሳደር የሚጀምሩት ገና ዓመታዊ እቅድ ማዘጋጀት ሲጀምሩ እንደሆነ የሚያመለክቱ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን እቅድ አዘገጃጀትና በአጠቃላይ በክፍል ትምህርት አቀራረብ ላይ ተጽዕኖ እንዲፈጥርባቸው ካደረጉ ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ የተማሪዎቻቸው ዝንባሌ እንደሆነም በውይይቶቹ ተመልክቷል፡፡ በውይይቶቹ ተደጋግሞ እንደ ተነሳው ተማሪዎች መማርና በታዘዙት መሰረት መልመጃዎችን መስራት የሚፈልጉት ከፈተናው ጋር የሚገናኙ ይዘቶችንና መልመጃዎችን ነው፡፡ መምህራኑ እራሳቸው ተማሪዎቻቸው በማጠናቀቂያ ፈተናው ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ እንደሚፈልጉም አልሸሸጉም፡፡

ለ. የማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ በክፍል ውስጥ ተግባራት/ መልመጃዎች ላይ

የማጠናቀቂያ ፈተናው በክፍል ውስጥ ተግባራት ላይ በሚፈጥረው ተፅዕኖ ምክንያት የተለየ አሰራር የሚከተሉ መሆን አለመሆናቸውን በተመለከተ ለተጠየቁት ጥያቄ ተወያዮቹ የሰጡት ምላሽ ተመሳሳይ አይደለም፤ በመካከላቸው መጠነኛም ቢሆን የሀሳብ ልዩነት አለ፡፡ የሚከተሉት በተወያዮቹ የተሰጡ ዋና ዋና አስተያየቶች ይህንኑ ልዩነት ያሳያሉ፡፡

- ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ዝግጁ ለማድረግ መማሪያ መፅሐፎቹ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች በቂ ናቸው፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ መልመጃዎችን እያዘጋጀን ለተማሪዎች አናቀርብም፡፡

- ከቀረቡበት ዓላማ አንፃር በመማሪያ መጽሐፎቹ የቀረቡት መልመጃዎች በቂ ስለሆኑ ሌሎች ተጨማሪ መልመጃዎችን እያዘጋጀን ወይም ከተለያዩ መጽሐፎች እየወሰድን ተማሪዎችን ማስራት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይሁን እንጅ ተማሪዎች በደንብ እንዳልተረዷቸው በምንገምታቸው ክፍሎች/ ይዘቶች ላይ ግን በመማሪያ መጽሐፎቹ ከተካተቱት በተጨማሪ በግል ወይም በቡድን የሚሰሩ የተወሰኑ ተግባራትን/ መልመጃዎችን ልንሰጥ እንችላለን፡፡

- እንደይዘቱ ክብደት- ቅለት ተጨማሪ መልመጃዎችን እናሰራን፡፡

-መልመጃ ስናሰራ በብሔራዊ ፈተናው የሚካተቱ ሲሆኑ ሰፋ ያለ ጊዜ እንሰጣቸዋለን፣ ተጨማሪ መልመጃዎችንም እናሰራለን፤ ከፈተናው ጋር በማዛመድም እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች በፈተናው ሲያጋጥሟቸው እንዴት መስራት እንደሚኖርባቸውም እናስረዳቸዋለን፡፡ ተማሪዎች መልመጃዎችን ደስ እያላቸው የሚሰሯቸው በዚህ መንገድ ሲቀርቡላቸው ነው፡፡ በአንጻሩም ከፈተናው ጋር ዝምድና የሌላቸውንና በመማሪያ መጽሐፎቹ ውስጥ የተካተቱ አንዳንድ መልመጃዎችን ለምሳሌ የንግግር፣ የውይይት፣ የቡድን ስራ መልመጃዎችን ተማሪዎቹም ለመስራት ፈቃደኛ ስለማይሆኑ ጊዜውም ስለማይበቃ፣ ለፈተናውም ስለማይጠቅሟቸው ሳይሰሩ ሊዘለሉ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎችም በፈተናው የማይካተቱ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ከተጠየቁ ይህ እኮ አይጠቅመንም፤ በፈተና አይመጣም ይሉናል፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፎቹ የቀረቡ መልመጃዎችን ሁሉ እንዲሰሩ ማድረግ አይቻልም፡፡ የሚሉ ሀሳቦች በውይይቶቹ ተንሸራሽረዋል፡፡ የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ በመልመጃዎቹ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በመሆናቸው ላይ ግን የተፈጠረ ክርክር የለም፡፡ ሁሉም ተጽዕኖ ያሳድራሉ በሚለው ሀሳብ ይስማማሉ፡፡

ሐ. የማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ

አብዛኞቹ ተሳታፊዎች በቋንቋው ትምህርት የተካተቱ ይዘቶችን ለማስተማር የሚጠቀሙት መምህር ተኮር ዘዴን በተለይም ገለጻን እንደሆነና ማስታወሻም እንደሚያጽፏቸው በውይይቶቹ ተናግረዋል፡፡ በተሳታፊዎቹ እንደተገለጸው፣ በእርግጥ በቋንቋው ትምህርትነት የተካተቱ ትምህርቶችን ይበልጥ በገለጻና ማስታወሻ በማጻፍ ስልት እንዲያቀርቡ በማድረግ ረገድ ፈተናው ድርሻ ቢኖረውም/ አንዱ ምክንያት ቢሆንም ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶችም አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱ ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው ጊዜ አነስተኛ መሆን ነው፡፡ ሁለተኛው በትምህርቱ ትኩረት የሚሰጣቸው ትምህርቶች ርዕስ/ ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሦስተኛው ተማሪዎች ራሳቸው እንደ ቡድን ስራ ባሉ ተማሪ አሳታፊ ዘዴዎች ለመማር ስለማይፈልጉ ነው፡፡ ለምሳሌ መምህርት[21] ስለዚሁ ስለማስተማሪያ ዘዴ ምርጫ ባነሱበት ክፍል እንዲህ ብለዋል፤ "ተማሪዎች ብዙ ጊዜ በቡድን ስሩ ስትላቸው ይሽ አንድ ለአምስት የሚባል አደረጃጀት አለ፡፡ አሁን ያን ደስተኞች አይደሉም፡፡"

ተማሪዎች በአሳታፊ ዘዴ መማርን እንዲጠሉ ካደረጓቸው ምክንያቶች አንዱ የፈተናው አቀራረብ ራሱ እንዲህ ያሉ ኢአሳታፊ ዘዴዎችን መጠቀምን የሚያበረታታ በመሆኑ ነው የሚል እምነት ያላቸው መምህራንም አሉ፡፡ ለምሳሌ መምህርት$_1$ እንዲህ ይላሉ፣

> አንዳንዶቹ ይዘቶች ተማሪዎች ችሎታቸውን የሚያዳብሩባቸው እንጂ ፈተና የማይሰጥባቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ ጥሩ ገጣሚ እንዲሆኑ እያስተማርናቸው ካለፍን ፈተናው ላይ አይፈተኑም [ግጥም መጻፍ] ስለዚህ ጥላቻ ያድርባቸዋል፡፡ ትኩረት አያደርጉበትም ፡፡ ክርክር ለምሳሌ እያስተማርን ከሆነ በተግባር ነው የሚሰሩት ክፍል ውስጥ፡፡ ያንን በተማሪ ተኮር እናስተምራለን... ፈተናው ላይ ግን ቲወረቲካል ነው እንጅ በተግባር አይፈተኑትም፡፡ ያንን ክፍለ ጊዜ በጣም ይጠሉታል፤ ፈተና ላይመጣ ላንፈተነው ዓይነት፡፡ ውይይት ስናስተምር ውይይት እንዴት እንደሚያደርጉ እናስተምራቸዋለን፡፡ ፈተናው ላይ ግን Direct [በቀጥታ] ይህንን ነገር አይጠየቁም፤ የሚጠየቁት ቲወረቲካል ነው፤ ስለዚህ ተግባሩን በጣም ይጠሉታል፡፡ ለምን ፈተናውን ለማንፈተነው የሚል ጥላቻ ያድርባቸዋል፡፡

መምህርት$_{23}$ም እንዲሁ የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫ ላይ ፈተናው ተጽዕኖ እንደሚሳድር ሲያስረዱ የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡

> ትምህርቱን የምንሸፍነው በዘዴ ነው፡፡ ለአጠቃላይ ዕውቀትና ለፈተና ነው፡፡ ፈተናን ማሰብ የግድ ነው ብየሃለሁ ቅድም፡፡... ዘዴው ደግሞ በቀጥታ ነው እንጅ ለፈተና የሚሆነው በተዘዋዋሪ አይደለም፡፡ በገለጻ ስንገልጽላቸው፣ ሀሳቡን ስናስተላልፍላቸው ተማሪዎቹ ይረዳሉ፡፡ የተረዱት ነገር በፈተና ይመጣል፡፡ በገለጻ ባንገልጸው ኑሮ፣ ባይገባቸው ኑሮ፣ ፈተናውን ሊሰሩት አይችሉም ነበር፤

የተወሰኑ ተሳታፊዎች ደግሞ በማስተማሪያ ዘዴ ምርጫ ላይ ፈተናው የሚያሳድረው ተጽዕኖ ጉልህ አይደለም፤ የማስተማሪያ ዘዴዎቻችን መምህር ተኮር እንዲሆኑ ያደረጉት ምክንያቶች የተማሪዎች ፍላጎት፣ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚመደቡ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ እንዲሁም የተመደበው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ መሆን ነው፤ የሚል አቋም አንጸባርቀዋል፡፡

ተማሪዎችን ለፈተና ለማዘጋጀት የበለጠ የገለጻ /ሌክቸር ዘዴን እንደሚጠቀሙ በገለጹት ተወያዮች እምነት ደግሞ ፈተናው የሚያተኩረው አንደኛ ሰዋስው ላይ ነው፡፡ ሁለተኛ በሥነ- ጽሑፍ ትምህርት፣ ሦስተኛ በአንብቦ መረዳት ላይና አራተኛ ሌሎች ክሂሎችን በሚመለከቱ ጽንሰ ሀሳቦች ላይ ነው፡፡ እነዚህን ትምህርቶች በወቅቱ ሸፍኖ ተማሪዎችን ለፈተና ዝግጁ ለማድረግ ደግሞ አዋጭ የማስተማሪያ መንገድ

አሳታፊ የሚባሉ ዘዴዎች ሳይሆኑ ገለጻ ነው፡፡ እንደነዚህ መምህራን እምነት በአብዛኛው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚጋብዙት ክሂሎች /የክሂል ርዕሶች ናቸው፡፡ ክሂሎች ደግሞ በፈተናው በቀጥታ ስለማይካተቱ እነሱን ርቱዕ (Direct) በሆነ መንገድ ለማስተማር መሞከር የተማሪዎችን የዝግጅት ጊዜ እንደማባከን የሚቆጠር/ የሚታይ ነው፡፡ አንዳንድ ተሳታፊዎች እንዲያውም ተማሪዎቻቸው የንባብ ትምህርቶች (የአንብቦ መረዳት ክሂሎች) በፈተናው የሚካተቱ ቢሆኑም በመማሪያ መጽሐፎቹ የተካተቱት ምንባቦችና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በፈተናው አይመጡም በሚል አስተሳሰብ እንዲህ ያሉ ትምህርቶችን ሳይቀር መማር ጊዜ እንደማባከን እንደሚቆጥሩት በውይይቶቹ አንጸባርቀዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የንባብ ትምህርትንም ቢሆን በሚፈለገው ደረጃ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅመው ለማስተማር እንደሚቸገሩ የገለጹ ተወያዮች አሉ፡፡

መ. የማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ በማስተማሪያ መሳሪያዎች አመራረጥ ሂደት ላይ

በአምስቱም ቦታዎች የተካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ተሳታፊዎች ከመማሪያ መጽሐፎቹ በተጨማሪ አንደኛ፣ የሥነ- ልሳን (ሰዋስው) ትምህርት ሲያስተምሩ የባየ ይማምን፣ <u>የአማርኛ ሰዋሰው</u>ና የጌታሁን አማረን <u>ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው</u> የሚሉ መጽሐፎች፣ ሁለተኛ፣ የሥነ-ጽሑፍ ይዘት ያላቸውን የትምህርቱ ክፍሎች ሲያስተምሩ ደግሞ የዘሪሁን አስፋውን <u>የሥነ-ጽሑፍ መሰረታውያን</u> ፣ የብርሀኑ ገበየሁን <u>ሥነ-ግጥም</u> እና <u>የአማርኛ ቅኔዎችና ፍችዎቻቸው</u> የሚሉ መጻሕፍትን፣ ሦስተኛ፣ ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ዝግጁ ለማድረግ ያለፉ ዓመታትን የማጠናቀቂያ ፈተናዎች (የጥያቄ ወረቀቶች)፤ አራተኛ፣ ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት ተብለው የታተሙ ሌሎች መጽሐፎችን ለምሳሌ <u>አማርኛ ሁሉ ለሁሉ</u>፣ <u>ቅድመ ኮሌጅ</u>፣ የብርሀኑ ገብረ ጻድቅን <u>ከ7-10</u> እና <u>ከ9-10</u> የሚሉ መጻሕፍት እነሱም፣ ተማሪዎቻቸውም፣ በዋና ዋና የትምህርቱ አጋዥ መሳሪያነት እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ ስለዚሁ ጉዳይ መምህር$_2$ በገለጹበት ክፍልም እንዲህ ብለዋል፣ "...ጥያቄዎቹንም እኛ ስናያቸው ከመማሪያ መጽሐፎቹ በተጨማሪ የተወሰኑ ነገሮችን አንድናይ ይጋብዙናል፡፡ በተለይ ከ9-10ኛ ክፍል አጋዥ መጽሐፍ ተብለው የፈተና ጥያቄዎችን በውስጣቸው ይዘው በተለያዩ ደራሲያን የሚዘጋጁ መጽሐፎች ለዚህ

ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡" መምህርት$_{21}$ም እነዚህን አጋዥ መጻሕፍት መጠቀማቸው ተማሪዎቻቸውን ለብሄራዊ ፈተናው ለማዘጋጀት እንዴት እንደሚረዳቸው ሲገልጹ የሚከተለውን ምሳሌ ሰጥተዋል፡፡

> የተለያዩ መጻሕፍትን ማየት ከዚያ ከፈተናው ጋር ተያያዥነት አላቸው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት ለምሳሌ ከዘሪሁን አስፋው ላይ የወሰድነው /ግጥም እንዳለ ተናገር አንተ ሀውልት የሚለው ሞዴል ፈተና ላይ አውጥተነው ነበር፣ እኛ፡፡... ማትሪክ ላይ ያ ግጥም እንዳለ በፈተናነት መጣ፡፡ አይ ሆኜ የተደሰትኩት መደሰት! በጣም ነው ደስ ያለኝ፡፡ ሞዴል ፈተናችን ነበር፤ ማትሪክ ፈተና ላይ ያ ግጥም መጣ፡፡ ... እና እነዚያን [ከላይ የተዘረዘሩትን መጻሕፍት ማለታቸው ነው] ማየቱ በጣም ተገቢ ነው፤ አጋዥነትም አለው፡፡

መምህር$_{11}$ም እንዲሁ የሚከተለውን ከላይ የተገለጹትን ሀሳቦች የሚያጠናክር ሀሳብ ተናግረዋል፤

> የብዙ ዓመት የብሄራዊ ፈተና ጥያቄዎችን የሚሰሩ...መጽሐፎች አሉ፡፡ እነሱን እንጠቀማለን፡፡ እነሱን እንድንጠቀም የሚያዘን የእኛ የመጽሀፉ ይዘት ነው፡፡ ስለሥነ-ጽሑፍ የምታስተምር ከሆነ፣ ስለሥነ-ጽሑፍ፣ ስለልቦለድ አላባውያን ወደዚያ እንድትሄድ የሚያደርግህ የራሱ የመጽሐፉ ይዘት ነው፡፡ መቼት ምንድነው? ገጸባህሪ ምንድነው? የሚለውን እኛ ከምናደርገው የክፍል ገለጻና የክፍል ግንኙነት ባሻገር ተማሪዎቹ በቤተ መጻሕፍት ውስጥ እንዲያነቡ 'ሊድ' የምናደረጋቸው [የምንመራቸው] እኛ ነን፡፡ እዚያ ውስጥ ባይኖር ኖሮ እኮ እኛም አናስተምራቸውም... የዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍም ሆነ የ10ኛ ክፍል እዚያው ይዘቱ ወደነኝህ መርጃ መሳሪያዎች እንድንሄድ ያደርገናል፡፡

በተለይ የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ መጽሐፎች ላይ ማተኮር ለምን እንደመረጡ እንዲያብራሩ ለተጠየቁት ጥያቄም ተሳታፊዎቹ የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች በእነዚህ መጽሐፎች ይዘቶች ላይ ስለሚያጠነጥኑና ተማሪዎቻችንም የፈተናውን የትኩረት አቅጣጫ በመገንዘብ ትምህርቱ በእነዚህ ይዘቶች ላይ እንዲያጠነጥን ጫና ስለሚፈጥሩ ነው፤ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ እንደተዋያዮቹ እምነት ከመማሪያ መጽሐፎቹ በተጨማሪ እነዚህን ማጣቀሻ መጽሐፎች ተጠቅሞ ማስተማር ካልተቻለ ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ዝግጁ ማድረግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ብዙ ተሳታፊዎች የመማሪያ መጽሐፎቹ የሥነ-ልሳንና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍሎች አቀራረብ ራሱ እነዚህን የማጣቀሻ መጽሐፎች መጠቀም ግድ የሚልም ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ዋነኛ አጋዥ መሳሪየዎቻቸው ብቻ ሳይሆኑ መደበኛ የትምህርት ይዘት ሆነው፣ ጊዜ ተመድቦላቸው በክፍል ትምህርትነት እንደሚቀርቡ በሁሉም ውይይቶች ተገልጿል። ሁሉም በሚባል ደረጃ በተለይ በ10ኛ ክፍል ላይ ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን በማስተማር ሂደቱ ለተማሪዎች እንደሚሰሩላቸው ገልጸዋል። የፈተና ጥያቄዎችን ለተማሪዎቻቸው በክፍል ውስጥ በሚሰሩበት/ በሚያሰሩበት መንገድ ግን ሊለያዩ ይችላሉ። ለምሳሌ አንዳንዶቹ ትምህርቱን ከሸፈኑ በኋላ መስራትን /ማሰራትን ሲመርጡ፣ አንዳንዶቹ ከትምህርቱ ጋር በማቀናጀት ይሰሩላቸዋል/ ያሰሯቸዋል። በአጠቃላይ በሁለቱም አቅጣጫ ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተና ወረቀቶችን ጥያቄዎች ለተማሪዎች መሰራት በመምህራኑ ዘንድ መደበኛ የማስተማር ስራ አካል ተደርጎ እንደሚታይ ተሳታፊዎቹ በውይይቶቹ ሂደት አንጸባርቀዋል። ለምሳሌ መምህር$_{12}$ ስለዚሁ ጉዳይ ባነሱበት ክፍል፣ "ብዙ ጊዜ 'ሽት' እሰራላቸዋለሁ፤ ግድ ነው።" ሲሉ፤ መምህር$_{20}$ ደግሞ የሚከተለውን ተናግረዋል፤

> "እንግዲህ ተማሪዎችን ብሄራዊ ፈተናው ላይ የተሻለ ውጤት እንዲያመጡ በግሌ የማደርገው ...ብዙ ጊዜ ጥያቄዎችን ቀድመው እንዲያዩቸውና ከዚያ በኋላ በየጊዜው የሚማሯቸውን ትምህርቶች ከጥያቄዎቹ ጋር እያገናዘቡ እንዲሄዱ ይህን እመክራለሁ። እንደገና ለምሳሌ 10ኛ ክፍል በማስተምርበት ሰዓት እንዴት ነው ሳደርግ የነበረው ሥነ-ጽሑፍ አስተምርና በዚያ ባስተማርኩት ስር የወጡ ጥያቄዎች ካሉ እነዚያን ጥያቄዎች ቢያንስ የሦስት አራት ዓመት ሰርተው እንዲመጡ አደርግ ነበር። ሥነ-ልሳንም... ካስተማርኩ በኋላ፣ አሁንም እነዚያን የሦስት አራት ዓመት ጥያቄዎች ሰርተው እንዲመጡ አደርጋለሁ።"

በሌላ ክፍል ለሌላ ዓላማ ከተገለጸው ማስረጃ ማስተዋል እንደሚቻለው የየትምህርት ቤታቸው አስተዳደርም መምህራን ያለፉ ዓመታት ጥያቄዎችን ለተማሪዎቻቸው እንዲሰሩላቸው ግፊት ያደረጋል። የየትምህርት ቤቶቻቸው ርዕሳነ/ምክትል ርዕሳነ መምህራንም ተማሪዎቻቸውን ለማጠናቀቂያ ፈተናዎች ለማዘጋጀት እየተሰሩ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት ብለው ከሚገጿቸው ተግባራት አንዱ ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ እንዲሰሩላቸው የሚደረግ መሆኑን ነው።

ሠ. የማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ በትምህርት ይዘቶች ላይ

በሁሉም ውይይቶች በይዘት ምርጫ ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው ላቅ ያለ ተፅዕኖ አለው፡ የሚል ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ አንጻር በውይይቶቹ በአብዛኞቹ ተወያዮች የተንፀባረቀው ሀሳብ በክፍል ትምህርቱ ትኩረት የሚሰጠው በአንደኛ ደረጃ ለሥነ-ልሳን(ሰዋስው) ነው፡፡ ቀጥሎ ለሥነ-ጽሑፍ፣ በሦስተኛ ደረጃ በመማሪያ መጽሐፎቹ በየምዕራፉ ለተካተተውና በፈተናውም ቢያንስ በሁለት ምንባቦች ለሚወከለው ለንባብ/ አንብቦ መረዳት ክሂል ነው፡፡ በአራተኛ ደረጃ ለመጻፍ ክሂል ነው፡፡ የንግግርና የማዳመጥ ክሂሎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ትኩረት የማይሰጣቸው ወይም በሚሰጣቸው ትኩረት መጨረሻ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በተወያዮቹ እንደተገለጸው የመጻፍ፣ የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎች በተግባር በትምህርቱ ትኩረት አያገኙም፡፡ እንደተወያዮቹ እምነት እነዚህ ክሂሎች ለተማሪዎች ሕይወት አስፈላጊ ስለሆኑ ብቻ አልፎ አልፎ ለማስተማር ቢሞከርም በመማሪያ መጽሐፎቻቸው የቀረቡ ጽንሰ ሀሳቦችን (በሳጥን ውስጥ የተቀመጡ ማስታወሻዎችንና መመሪያዎችን) እንዲገነዘቡ ከማድረግ የዘለለ የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ የሚደረግበት ሁኔታ አነስተኛ ነው፡፡ ተማሪዎችም በፈተናው አይካተቱም በሚል፤ እንዲሁም ከታች ጀምረው በእነዚህ ክሂሎች እየተለማመዱ ባለመምጣታቸውና በመሳሰሉት ምክንያቶች እነዚህን የትምህርቱ ክፍሎች ልምምድ እያደረጉ ለመማር በአብዛኛው ዝግጁና ፈቃደኛ አይደሉም፣ የሚልም ሀሳብ አብሮ ተንጸባርቋል፡፡ አንዳንዶቹ ተወያዮች አንዳመለከቱት ተማሪዎቻቸው ለዕውቀት ሳይሆን ለፈተና የሚማሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ በፈተና የማይካተቱ ክፍሎችን ለመማር አይፈልጉም፤ የማይፈልጉትን ማስተማር ደግሞ ይከብዳል፣ የሚል ሀሳብ አላቸው፡፡ ለምሳሌ መምህር$_{15}$ ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፣ “የተማሪዎቻችን ዝንባሌ መሰረት ካላደረግን እንዳስተማርን ራሱ ላይቆጠር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ደንበኞቻችን እነሱ ናቸው፡፡ እነሱ ከረኩ ነው ሰራን የምንል፡፡ እና የነሱን ዝንባሌ መሰረት አድርጌ ነው የማስተምረው፤ እነሱን ካልተመቻቸው መቼም ትምህርት ስለሆነ ማስገደድም ስለማይቻል፡፡ ስለዚህ ጫና ያለው ይመስለኛል፡፡” በማስተማሪያ ዘዴ ምርጫ ላይ የተማሪዎች ፍላጉት ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ መምህርት$_1$ የገለጹት ሀሳብም ከዚሁ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

ረ. የማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ በክፍል ትምህርት ግምገማ ላይ

የማጠናቀቂያ ፈተናው በክፍል ትምህርቱ የግምገማ ሂደት ላይ ተፅዕኖ እንዳለው የአብዛኞቹ ተወያዮች እምነት ነው፡፡ ለምሳሌ መምህር$_{15}$ ሁለቱ የተያያዙ መሆናቸውን ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፣ “ምንም ጥያቄ የለውም! አሁን አምና ከ10 የፈተናቸውን፣ ከ60 የፈተናቸውን ብታያቸው ከምንባቡ ጥያቄ ውጭ እንዲያውም ብዙ ጊዜ ሆን ብለን ብሄራዊ ፈተናው ላይ ያሉ ጥያቄዎችን እንዳለ ራሱ እናመጣለን፡፡... አንዳንድ/ የተወሰነ ለውጥ ነው የምናደርግ እንጅ ብዙዎቹ ከምንባብ ጥያቄዎች ውጭ እነሱን ነው የምንደግመው” ይላሉ፡፡ ይህም ፈተናው በመምህራኑ በሚዘጋጁ ፈተናዎች ላይ ጉልህ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር የሚያሳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ አብዛኞቹ የውይይቶቹ ተሳታፊዎች ያንጸባረቁት የሚያዘጋጇቸው የክፍል ፈተናዎች ከማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጋር ተመሳሳይ እንደሆኑና ተማሪዎቻቸውን ለመገምገም አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙበት የአጠያየቅ ዘዴም ምርጫ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎችን ከብሔራዊ ፈተናው አጠያየቅ ጋር ለማስተዋወቅ ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተወያዮች እንደተገለጸው ተማሪዎች የማጠናቀቂያ ፈተናውን ሲፈተኑ ለመመለስ የማይቸገሩት ያለፉ ዓመታት ፈተናዎች ጥያቄዎችን በክፍል ውስጥ በመስራትና በክፍል ፈተናዎች ቀደም ብለው አጠያየቁን በመለማመዳቸው ነው፡፡ የማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ በ10ኛ ክፍል የክፍል ግምገማ ላይ የጎላ ቢሆንም በተወሰነ ደረጃ በ9ኛ ክፍል ላይም እንደሚንፀባረቅ በውይይቶቹ ተገልጿል፡፡ ከየትምህርት ቤቶቹ የተሰበሰቡት የክፍል ፈተናዎች የሚያሳዩት ግን ለሁለቱ የክፍል ደረጃዎች በሚዘጋጁ ፈተናዎች መካከል ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡ ልዩነት አለ ከተባለ በጥያቄ ቁጥር/ብዛት ብቻ ነው፡፡ ባብዛኛው ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚዘጋጁት ፈተናዎች ጥያቄዎች ቁጥር ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከሚዘጋጁት በዛ ይላል፡፡

4.4.1.3 የማጠናቀቂያ ፈተናውን ተጽዕኖ በተመለከተ በዓይነታዊና መጠናዊ ዘዴዎች የተካሄዱ የውጤት ትንተናዎች ውህዳዊ ግኝትና ማብራሪያ

የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ ያላቸው ግንዛቤ (Perceptions) የሚለውን የጥናቱ ክፍል በተመለከተ በተለይ ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅና ተተኳሪ የቡደን ውይይቶች የተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ በመመስረት ለየብቻ የተካሄዱት የውጤት ትንተናዎች በተመሳሳይ ሁኔታ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርት ምድቦች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡ በዚህ ጥናት በትምህርት ምድብነት (Domains) የተካተቱት ክፍሎችም የትምህርት ዕቅድ፣ ተግባራት/ጊዜ አመዳደብ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ የትምህርት ይዘቶችና የክፍል ትምህርት ምዘናዎች/ ፈተናዎች የሚሉት ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ ፈተናው በእነዚህ የትምህርት ምድቦች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ በሁለቱ መንገዶች በተካሄዱት ትንተናዎች የተገኙት ውጤቶችና ማብራሪያ ተዋህደው ቀርበዋል፡፡

በዓይነታዊና መጠናዊ ዘዴዎች የተካሄዱት የውጤት ትንተናዎች እንዳሳዩት፤ አንደኛ አብዛኞቹ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በሚያዘጋጇቸው ዓመታዊና ሳምንታዊ/ ዕለታዊ ዕቅዶች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው በመጭው አዲስ ዓመት ተግባራዊ በሚደረግና በቀዳሚው ዓመት ሰኔ ወር ላይ በሚዘጋጅ ዓመታዊ ዕቅድ ዝግጅት ላይ ሳይቀር ተጽዕኖ እንደሚየሳድር ወይም ተጽዕኖ ማሳደር እንደሚጀምር የሚያመላክት ነው፡፡ በእርግጥ የተወሰኑ መምህራን ዓመታዊ ዕቅድ የምናቅደው ፈተናውን እያሰብን ሳይሆን የመማሪያ መጽሐፎችን ቅደም ተከተል በመከተል ነው የሚል አቋም አንጸባርቀዋል፡፡ ሆኖም ከመካከላቸው አንዳንዶቹ በሳምንታዊ /ዕለታዊ ዕቅድ ላይ ግን ፈተናው ተጽዕኖ እንደሚያሳድር የሚያምኑ ናቸው፡፡ ከአብዛኞቹ መምህራን የተገኘው መረጃ ውጤት ትንተና ፈተናው በዕቅድ ዝግጅት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚለው መሆኑም በAlderson እና Wall(1993) ስራ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በፈተናው ውጤታማ

ማድረግን/ ጥሩ ውጤት ማስመጣትን እንደ አንድ የማስተማር ኃላፊነት/ ግዴታ ያዩታል የሚለውን ሀሳብ የሚያንጸባርቅ ነው ማለት ይቻላል::

ሁለተኛ በጽሑፍ መጠይቁም ሆነ በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት ትንተና መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በተግባራት/ ጊዜ አመዳደብ ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው አሳይቷል:: በአጠቃላይ ከዚህ ከተግባራት/ ጊዜ አመዳደብ ጋር በተያያዘ በመጠናዊም ሆነ በዓይነታዊ ዘዴ የተካሄዱት ትንተናዎች ውጤት የቋንቋው መምህራን የተማሪዎቻቸውን የፈተና አመላለስ ዘዴ ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትን እንዲያከናውኑ፣ የተለያዩ መልመጃዎችን ሲያዘጋጁና ተማሪዎቻቸውን ሲያሰሩ እንዲሁ የማጠናቀቂያ ፈተናውን መሰረት እንዲያደርጉ፣ የተወሰኑ ክፍለ ጊዜያትን የፈተና አሰራር ስልቶችን ለማስተማሪያነት እንዲያውሉ የማጠናቀቂያ ፈተናው ጠንካራ በሚባል ደረጃ ተጽእኖ ያሳድራል የሚል እምነት/ግንዛቤ እንዳላቸው አሳይቷል:: በክፍል ትምህርት ምልከታና ከምልከታ በኋላ ከመምህራኑ ጋር በተካሄዱት ቃለ መጠይቆች የተሰበሰበው መረጃ ውጤት ትንተናም ከዚህኛው ውጤት ጋር ተመሳሳይ ነው:: በዚህ ጥናት ይህን ፈተናው በተግባራት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በሚመለከት የተገኘው ውጤትም ቀደም ብለው ከተካሄዱት ከChen (2002)፣ Cheng (1995፣ 2005)፣ Shohamy እና ሌሎች (1996)፣ Simachew (2012)፣ Spratt፣ (2005)፣ ጥናቶች ግኝት ጋር ይደጋገፋል::

ሦስተኛ፣ የጥናቱ ግኝት የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች ምርጫ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር አሳይቷል:: በእርግጥ የተጽዕኖው ደረጃ በሌሎቹ የትምህርት ምድቦች ላይ እንደታየው ጠንካራ የሚባል አይደለም:: በዚህ ጥናት የጥናቱ ውጤት ያሳየው በጽሑፍ መጠይቁ መካከለኛ በሚባል ደረጃ፣ በቡድን ውይይቶቹ እንዲሁ በአብዛኞቹ መምህራን ፈተናው በዘዴ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው ነው:: ይህም ግኝት ከAlderson & Hamp-lions (1996) Howeky (2006)፣ Simachew (2012)፣ የጥናት ውጤቶች ጋር ተደጋጋፊ ሲሆን ከሌሎቹ ማለትም ፈተና በዘዴ ምርጫ ላይ ተጽዕኖ እንደማያሳድር ካመለከቱት የጥናት ውጤቶች ጋር (ለምሳሌ፣ Alderson እና Wall 1993 ፣ Cheng 2004፣ Wall 2005) ደግሞ ይቃረናል:: በተለይ በተተኳሪ የቡድን ተኮር ውይይቶቹ በአብዛኞቹ

ተሳታፊዎች የተንጸባረቀው መምህራኑ ብዙ ጊዜ የሚያስተምሩት መምህር ተኮር በሚባሉት ዘዴዎች በተለይም በገለጻና አልፎ አልፎ ደግሞ ማስታወሻ በማጻፍ እንደሆነ ነው። ሲያስተምሩ በአብዛኛው የገለጻ ዘዴን እንዲጠቀሙ ካደረጓቸው ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ የማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረትና አቀራረብ እንደሆነም የጥናቱ ግኝት አመላክቷል። በእርግጥ በዚህም ጥናት ከፈተናው በተጨማሪ የተመደበው ክፍለ ጊዜ መጠን፣ የተማሪዎች ፍላጎት (ከታች ባሉት የክፍል ደረጃዎች እየተናገሩ፣ ክርክር፣ ውይይት እያካሄዱ እንዲሁም አንቀጽ፣ ዘገባ፣ ማመለከቻ፣ ደብዳቤ፣ ረቂቅ፣ ድርሰት መጻፍን እየተለመማመዱ አለመምጣት፣ አሳታፊ ተግባራትን ለማከናወን ፍላጎቱም ችሎታውም የሌላቸው መሆን) መምህራኑ በአሳታፊ ዘዴዎች ላለመጠቀማቸው ምክንያቶች ሆነው ተገኝተዋል። በተለይ በማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ምክንያት በመማሪያ መጽሐፎቹ ውስጥ የቀረቡ በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚጠይቁ መልመጃዎች በተደጋጋሚ እንደሚዘለሉ በክፍል ምልከታዎች የተገኙት መረጃዎች ውጤት ትንትናዎችም አሳይተዋል። ከዚህም መምህራን በተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት መርህ መሰረት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ እንዳያስተምሩ እያደረጓቸው ካሉት ምክንያቶች አንዱ የማጠናቀቂያ ፈተናው የሚሳድረው ጫና እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

አራተኛ፣ የጥናቱ ግኝቶች የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርት መሳሪያዎች፣ ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር አመላክተዋል። በጽሑፍ መጠይቁም ሆነ በቡድን ተኮር ውይይቶች የተገኘው ውጤት ትንተና እንዳሳየው ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መሳሪያዎችን በመምረጥና በመጠቀም ሂደት የማጠናቀቂያ ፈተናው ጠንካራ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው። ይህም በክፍል ምልከታዎችም ተረጋግጧል። ከዚህ ቀደም በሌሎች ሀገሮች የተካሄዱ ጥናቶች ውጤትም (ለምሳሌ፣ የAlderson እና Hamp-lions (1996) Alderson እና Wall (1993)፣ Cheng (1997)፣ Read & Hayes (2004,)) Shohamy et al (1996) በኢትዮጵያ ደግሞ የSimachew (2012) ከዚህኛው ግኝት ጋር ተደጋጋፊ ነው።

አምስተኛ፣ የጥናቱ ውጤት የጥናቱ ተሳታፊዎች የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርቱ ይዘቶች ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል እምነት እንዳላቸው አሳይቷል። ይህም በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ሂደቶች በማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረት የሚሰጣቸው

የትምህርቱ ክፍሎች ብቻ ትኩረት እንዲያገኙና በፈተናው ትኩረት የተነፈጋቸው የትምህርቱ መሰረታዊ ጉዳዮች የሆኑት የቋንቋው ክሂሎች ችላ እንዲባሉ አድርጓል። በዚህም ምክንያት በመማር-ማስተማር ሂደቶቹ የሰዋስው፣ የሥነ-ጽሑፍ፣ አንብቦ የመረዳት ክፍል ትምህርቶች ከፍተኛ ትኩረት ሲያገኙ የመጻፍ፣ የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎች ትኩረት አጥተዋል። ይህም በክፍል ምልከታዎችና ከምልከታ በኋላ በተካሄዱት ቃለመጠይቆችም ተረጋግጧል። በተለያዩ ሀገራት የተካሄዱ አብዛኞቹ ተግባራዊ ጥናቶች (ለምሳሌ የ Alderson እና Wall (1993)፣ Cheng (2004)፣ (2005)፣ Freeman (2004)፣ Hayes እና Read (2004)፣ Howakey (2006))፣ Freeman (2004)፣ Wall (2005)፣ Wal እና Alderson (1996) ግኝትም እንዲሁ ውጫዊ ፈተናዎች በትምህርት ይዘት ምርጫ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ አሳይተዋል።

ስድስተኛ፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የክፍል ምዘና ተግባር ላይ ተፅዕኖ እንደሚፈጥርና የተፅዕኖው ደረጃም ጠንካራ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ውጤቱም ከAlderson እና Wall (1993) Chen (2002)፣ Shohamy እና ሌሎች (1996)፣ Spratt (2005)፣ Simachew (2012)፣ Wall (2005)፣ Wall እና Alderson (1996)፣ ጥናቶች ግኝቶች ጋር የሚደጋገፍ ነው። ለዚሁ ጥናት የተሰበሰቡት የክፍል ፈተናዎችም ይህንኑ የሚያረጋግጡ ሆነው ተገኝተዋል።

ይህን ክፍል ለማጠቃለል፣ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በተመለከተ የቋንቋው መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ ከስድስት የትምህርት ምድቦች አንጻር ለመመርመር ተሞክሯል። ስድስቱ ምድቦችም አንደኛ የትምህርት እቅድ፣ ሁለተኛ የትምህርቱ ተግባራት/ መልመጃዎች፣ ሦስተኛ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ አራተኛ የማስተማሪያ መሳሪያዎች/ ማቴሪያሎች፣ አምስተኛ የትምህርት ይዘቶችና ስድስተኛ የመምህራን የክፍል ትምህርት ግምገማ የሚሉት ናቸው። እነዚህን ስድስት መሰረታዊ የትምህርት ምድቦች መሰረት በማድረግ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚሳድረውን ተጽዕኖ በተመለከተ የተካሄዱት የውጤት ትንተናዎችም አብዛኞቹ መምህራን ፈተናው በእነዚህ የትምህርት ጉዳዮች/ ምድቦች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል ግንዛቤ

እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡ ፈተናው በእነዚህ ምድቦች ላይ የሚያሳድረው የተጽዕኖ ደረጃና አይነት ሲታይም አንደኛ በትምህርት መሳሪያዎች፣ በትምህርት ይዘቶች፣ በተግባራትና በክፍል ትምህርት ግምገማ/ምዘና ላይ ጠንካራ /ላቅ ያለ በአብዛኛው አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር፣ ሁለተኛ በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና በማስተማሪያ ዘዴዎች ምርጫ ላይ ደግሞ የሚያሳድረው ተጽዕኖ መካከለኛና አሉታዊነቱ የጎላ እንደሆነና ተጽዕኖው በዝርዝር ከቀረቡት የውጤት ትንተናዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

4.4.2 የወሸባክ መከሰቻ (መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ላዳበሩት ግንዛቤ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ) ምክንያቶች (Factors) ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

"በጥናቱ ዐውድ የወሸባክ መከሰቻ (መምህራን ማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ በሚያሳድረው ተጽዕኖ ላይ ላዳበሩት ግንዛቤ) ምክንያቶቹ (Factors) ምንድን ናቸው?" የሚለውን ጥያቄ በዚህ ክፍል ለመመለስ ተሞክሯል፡፡ በክለሳ ድርሳናት ክፍል እንደተገለጸው፣ ለወሸባክ መከሰት ወይም መምህራን ከፈተና ተጽዕኖ ጋር ተያይዞ ለሚያዳብሩት ግንዛቤና ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ምክንያት ናቸው የሚባሉ ጉዳዮች አሉ፡፡ ከነዚህ መካከል የተወሰኑት ከመምህራኑ ባህርያት፣ የተወሰኑት ከትምህርት ቤቶቻቸው አካባቢ/ ዐውድ ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ከእነዚህ መምህራን በፈተና ተጽዕኖ ስር እንዲወድቁ ሊያደርጉ ይችላሉ ከሚባሉ ምክንያቶች ወይም ተላውጦዎች መካከል መምህራን፤ ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው ዕውቂያ፣ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ፣ ውጫዊ ተጽዕኖዎች ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ለቋንቋው ትምህርት በተመደበው ክፍለ ጊዜ መጠን ላይ ያላቸው አመለካከት፣ የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታን /ዳራን በተመለከተ ያላቸው ግንዛቤ የሚሉትና የመሳሰሉት ተካተዋል፡፡

ቀጥሎ እነዚህን ለወሸባክ መከሰት ምክንያቶች (Factors) ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉ ጉዳዮችን/ ተላውጦዎችን በተመለከተ መጀመሪያ በጽሑፍ መጠይቅ ቀጥሎ ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ይቀርባል፡፡

ከዚያም በሁለቱ (ዓይነታዊና መጠናዊ) ዘዴዎች የተተነተኑት ውህዳዊ ውጤትና ማብራሪያ ይከተላል፡፡

4.4.2.1 የወሸባክ መከሰቻ ምክንቶችን በሚመለከት በጽሑፍ መጠይቅ ከመምህራን የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ሀ. መጠይቅ በመሙላት የተሳተፉ መምህራን ዳራና ዳራዎቹ ለወሸባክ መከሰት ያላቸው ሚና

ሰንጠረዥ 4.10 መጠይቅ በመሙላት የተሳተፉ መምህራን አጠቃላይ መረጃ

ጥያቄ	ተላውጦ	ብዛት Count	መቶኛ %
1. የተሳታፊዎች ጸታ	ወንድ	36	40.4
	ሴት	50	56.2
	ድምር	86	96.6
	ጸታቸውን ያልገለጹ	3	3.4
	ጠቅላላ ድምር	89	100.0
2. ተሳታፊዎች በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያላቸው የማስተማር ልምድ (2005 ን ጨምሮ)	5 ወይም ከ 5 በታች	32	36.0
	6-10	31	34.8
	11-15	9	10.1
	ከ 16 በላ\ይ	17	19.1
	ጠቅላላ ድምር	89	100.0
3. የክፍለ ጊዜ መጠን (Teaching Load) በሳምንት	ከ 10 ክፍለ ጊዜ በታች	6	6.7
	□10-16	38	42.7
	k 18 -22	44	49.4
	□ 24 -28	1	1.1
	ጠቅላላ ድምር	89	100.0
4. የተሳታፊዎቹ የትምርት ደረጃ	ቢኤ	34	38.2
	ቢኢዲ	45	50.6
	ኤም ኤ(TEAM)	5	5.6
	ኤም. ኤ በሌላ መስክ	5	5.6
	ጠቅላላ ድምር	89	100.0
5. የክፍል- ተማሪ ጥምርታ	40-49	7	7.9
	50-59	32	36.0
	60-69	35	39.3
	ከ 70 በላይ	14	15.7
	ድምር	88	98.9
	ያልገለጹ	1	1.1
	ጠቅላላ ድምር	89	100

6. በመደበኛ የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸው የቋንቋ ፈተናን(ምዘናን) የሚመለከት ኮርስ ስለመውሰዳቸው	አዎ(ወስጃለሁ)	62	69.7
	አልወሰድኩም	27	30.3
	ጠቅላላ ድምር	89	100.0
7. . የስራ ላይ ስልጠና/ትምህርት መርሀ ግብሮች ተሳትፎ	ተሳትፌ አላውቅም፤	74	83.1
	ከ1-3 ጊዜ	14	15.7
	ድምር	88	98.9
	ያልገለጹ	1	1.1
	ጠቅላላ ድምር	89	100.0

ጾታ፣ የማስተማር ልምድ፣ የትምህርት ደረጃ የተማሪ-ክፍል ጥምርታና የሥራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ ለወሸባክ መከሰት ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ በክለሳ ድርሳናት ክፍል ተገልጿል፡፡ በዚህ ጥናት ዐውድም እነዚህ ጉዳዮች ለወሸባክ መከሰት ምክንያት መሆን አለመሆናቸው በተለይ ከመምህራን ጋር በተካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶችና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ በተካሄዱት የውጤት ትንተናዎች ተፈትሿል፡፡ ስለዚህ በዚህ ክፍል የሚቀርበው ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ የሆኑት ከመምህራንና ከዐውድ ጋር የሚያያዙት ሌሎች የወሸባክ መከሰቻ ምክንያቶች የውጤት ትንተና ይሆናል፡፡

ለ. መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ከበሬታ (Dignity) ያለው ተፅዕኖ

ሰንጠረዥ 4.11፣ መምህራን ለሙያቸው ያላቸው ከበሬታ ምድብ (Domain) ውጤት

ጥያቄ (Item)	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
33. ብዙውን ጊዜ ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው ጥሩ ውጤት ያመጣሉ ብዬ እጠብቃለሁ፡፡	89	3.8090	.70512	ጠንካራ
34. ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው በሌላ መምህር ከተማሩ ሌሎች ተማሪዎች ያነሰ ውጤት ቢያመጡ ቅር ይለኛል፡፡	89	3.8427	1.09647	ጠንካራ
35. ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው ስኬታማ ባይሆኑ /ጥሩ ውጤት ባያመጡ መስራት የነበረብኝን ተግባር ያልሰራሁ /guilty/ ሆኖ ይሰማኛል፡፡	89	3.0899	1.25807	መካከለኛ
36. የተማሪዎቼ የፈተና ውጤቶች ሰዎች በእኔ ላይ ለሚኖራቸው አመለካከት (አዎንታዊ ወይም አሉታዊ) ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡	89	3.3596	1.07922	መካከለኛ
37. የተማሪዎችን የፈተና ውጤት ለማሻሻል በቋንቋ መምህራን ዘንድ ፉክክር ስለሌለ ተጨማሪ ነገሮችን ለመስራት ጥረት አላደርግም፡፡	89	3.8876	.92243	ጠንካራ
38. የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎቹን ክሂሎችና የሰዋስውና የስነጽሑፍ ትምህርቶች ትኩረት ሰጥቼ ማስተማር እንዳለብኝ ጠቃሚ ግብረ- መልስ ይሰጠኛል፡፡	89	3.6629	1.03291	ጠንካራ
መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ አማካይ		3.6086		ጠንካራ

ሠንጠረዥ 4.11 እንደሚያሳየው፣ መምህራን ተማሪዎቻቸው በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያስመዘግቡት ውጤት የተሻለ ሲሆን ሙያዊ ኩራት ይሰማቸው እንደሆነ በተቃራኒው ደግሞ የተማሪዎቻቸው ውጤት ዝቅተኛ ከሆነ ተገቢ ስራ አልሰራሁም፣ የጠበኩት ውጤት እንዲህ ያለ አልነበረም፣ የተገኘው ውጤት ልፋቴን የሚያሳይ አይደለም፤ ሰዎች በእኔ ላይ የሚኖራቸውን አመለካከት የሚያዛባ ውጤት ነው፤ የሚል ስሜት ይሰማቸው እንደሆነ ለተጠየቁት ስድስት ጥያቄዎች የሰጡት መልስ የጥንካሬ ደረጃ አማካይ ጠንካራ (3.6086) ሆኖ ተገኝቷል:: በተናጠል ሲታይም በሁለቱ መካከለኛ፣ በአራቱ ጠንካራ በሚባል የጥንካሬ ደረጃ ፈተናው ከሙያቸው ጋር የተያያዘ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ያሳያል::

ሐ.መምህራን ለፈተናው ይዘትና የአጠያየቅ ስልቶች ያላቸው ዕውቂያ (Awareness) የሚያሳድረው ተጽዕኖ

ሰንጠረዥ 4.12፣ መምህራን ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ ምድብ ውጤት ስሌት በአማካይ

ጥያቄ (Item)	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
42.ማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎቹ የትምህርቱ ክፍሎች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ አውቃለሁ፡፡	89	3.9101	.90001	ጠንካራ
43. የማስተምረው ተማሪዎቼ የቋንቋ ዕውቀትና ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ነው፤ በማጠቃለያ ፈተናው የተሻለ ውጤት ማምጣት አለማምጣታቸው አያሳስበኝም፡፡	89	4.0337	.95880	ጠንካራ
44. የማጠናቀቂያ ፈተናው በምን በምን የትምህርቱ ክፍሎች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ስለማላውቅ በፈተናው ምክንያት በማስተማር ሂደቱ ላይ ለውጥ ለማምጣት ብዬ የማደርገው የተለየ ጥረት የለም፡፡	89	4.1573	.76721	ጠንካራ
ስለማጠናቀቂያ ፈተናው መምህራን ያላቸው እውቂያ	89	4.0337		ጠንካራ

በወሽባክ ላይ ምርምር ያካሄዱ ምሁራን እንደሚገልፁት አብዛኛውን ጊዜ መምህራን በብሄራዊ/ ውጫዊ ፈተና የሚካተቱ የቋንቋ ክሂሎችንና ሌሎች ይዘቶችን እንዲሁም የአጠያየቅ ዘዴዎቻቸውን እያወቁ በሂዱ ቁጥር ተማሪዎቻቸውን ለፈተናው የሚያዘጋጁ ትምህርቶችን ወደ ማስተማር ያዘነብላሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ተሳታፊዎች ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸውን ዕውቅያናና ዕውቅናው ተፅዕኖ ያለው መሆን

አለመሆኑን ለመለየት ለቀረቡት ሦስት ጥያቄዎች መላሾቹ የሰጡት መልስ እውቅና እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። ከተሳታፊዎቹ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተገኘው ውጤት አማካይ በቅደም ተከተል 4.08፣ 4.06 እና 4.23 ነው። በሦስቱም ጥያቄዎች የተገኘው ምላሽ ድምር አማካይ 4.0337 ነው። ይህም መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ይዘትና የአቀራረብ መንገድ ጠንካራ በሚባል ደረጃ እውቅያ እንዳላቸው ያሳያል።

መ. ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያስመዘግቡት ውጤት የጠቀሜታ ደረጃ ላይ የመምህራን ግንዛቤ

ሠንጠረዥ 4.13፣ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ውጤት ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ በአማካይ

ጥያቄ (Item)	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
45. የማጠናቀቂያ ፈተናውን ደረጃ የምረዳው በተማሪዎች የወደፊት የስራ ዕድል ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንደሆነ አድርጌ ነው ።	89	2.8652	1.21722	**መካከለኛ**
46. ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያስመዘግቡት ውጤት ለአብዛኛዎቹ መምህራን የመምህርነት ብቃት ጠቃሚ የማረጋገጫ መንገድ ነው ብየ አምናለሁ ።	89	3.0112	1.24767	**መካከለኛ**
47. ለአብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያገኙት ውጤት ጠቃሚ ማበረታቻ ነው።	89	3.8764	.86366	**ጠንካራ**
48. ተማሪዎች በአማርኛ የማጠናቀቂያ ፈተና የሚያመጡት ውጤት ወደ መሰናዶ ትምህርት ለማለፍ ተፅዕኖ እንዳለው/ የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት እረዳለሁ ።	89	3.9551	.99898	**ጠንካራ**
49. የማጠናቀቂያ ፈተናው የትምህርት ቤታችንን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት በአብዛኛው ቀይሮታል ብዬ አምናለሁ ።	89	2.8876	1.12248	**መካከለኛ**
ስለማጠናቀቂያ ፈናው ውጤት ጠቀሜታ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ	89	3.3191		**መካካለኛ**

ሠንጠረዥ 4.13 እንደሚያሳየው ተማሪዎች ወደ መሰናዶ ትምህርት ለመዛወርም ሆነ በልዩ ልዩ የዲፕሎማ፣ የሰርተፍኬትና የመሳሰሉት ፕሮግራሞች (10+1፣ 10+2፣ 10+3...) ወይም ደረጃ አንድ፣ ደረጃ ሁለት፣ ደረጃ ሦስት ገብተው ለመማር/ ለመሰልጠን የአማርኛ ቋንቋ የ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ውጤታቸው ያለውን

የጠቀሜታ ደረጃ (status) እንዲያመለክቱ ለቀረቡት አምስት ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤት መካከለኛ ነው፡፡ በእርግጥ ከአምስቱ ሁለቱ ጠንካራ በሚለው ምድብ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ ለሁሉም ጥያቄዎች የተሰጠው መልስ ድምር አማካይ ግን መካከለኛ ነው፡፡ በአጠቃላይ በሰንጠረዥ 4.13 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት የሚያስመዘግቡት ውጤት የተሻለ ከሆነ ለቀጣይ ሕይወታቸው/ የትምህርትና የስልጠና ዕድሎቻቸው አስተዋፅኦ አለው የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያስመዘግቡት ጥሩ ውጤት አንደኛ ለአብዛኞቹ መምህራን ጠቃሚ ማበረታቻ ነው፤ ሁለተኛ ወደ መሰናዶ ትምህርት ለማለፍ አዎንታዊ ተፅዕኖ አለው / የበኩሉን ሚና ይጫወታል ብለው ያምናሉ፡፡

ሠ.የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ (Learing Attitudes) በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚፈጥረው ጫና

ሰንጠረዥ 4.14፣ የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በመምህራን ላይ የሚፈጥረው ጫና

ጥያቄ (Item)	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
30. ተማሪዎቹ ወደዱትም ጠሉትም ጠቃሚ ነው ብዬ የማስበውን ሁሉ አስተምራለሁ፡፡	89	3.6854	1.05092	ጠንካራ
29. በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ያሉ ፣ ተማሪዎቹ መማር የማይፈልጓቸውን ይዘቶች ለማስተማር የማውለው ጊዜ አነስተኛ ነው፡፡	89	2.6742	1.16556	መካከለኛ
30. በተማሪዎች ፍላጐት መሰረት አብዛኛውን ጊዜ የማስተምረው በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚካተቱን ክፍሎች ነው፡፡	89	3.0674	1.20414	መካከለኛ
30. የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ (Attitudes) በማስተማር ተግባሬ ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡	89	3.7416	1.10297	ጠንካራ
31.ተማሪዎቹ የክፍል ትምህርቱ ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ተዛማጅነት ያለው እንዲሆን ይፈልጋሉ፡፡	89	4.1236	.92712	ጠንካራ
የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በመምህራን ግንዛቤ ላይ የሚፈጥረው ጫና		**3.5674**		ጠንካራ

ከAlderson እና Wall (1993) መላምቶች አንዱ ፈተና በተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል፤ የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተሳታፊዎቹ ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ተጠይቀዋል፡፡ ተሳታፊዎቹም (በሰንጠረዥ 4.14

የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች አንዱ ይኸው የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ እንደሆነ አረጋግጠዋል። ለአምስቱ ጥያቄዎች የተሰጠው ምላሽ ድምር አማካይ የጥንካሬ ደረጃም ጠንካራ እንደሆነ በዚሁ ሰንጠረዥ የቀረበው ውጤት ያሳያል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተሳታፊዎቹ የሰጡት መልስ ሲታይ ደግሞ የሦስቱ የጥንካሬ ደረጃ አማካይ ጠንካራ የሁለቱ መካከለኛ ነው። ይህም የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በመምህራኑ የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር የሚያሳይ ነው።

ረ. ውጫዊ ጫናዎች (*External Pressures*) በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚያሳድሩት ጫና

ሰንጠረዥ 4.15፣ ውጫዊ ጫናዎች በመምህራን ግንዛቤ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ

ጥያቄ (Item)	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
39. የተማሪዎቼን ፈተና ውጤት እንዳሻሽል በየደረጃው ያሉ የትምህርት ዘርፍ መዋቅሮች ለምሳሌ ወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች፣ የዞን ትምህርት መምሪያዎችና የክልሉ ትምህርት ቢሮ ተጽዕኖ የሚያሳድሩብኝ ይመስለኛል።	89	2.8539	1.32760	መካከለኛ
40. የተማሪዎቼን ፈተና ውጤት እንዳሻሽል ከተማሪዎቼ ወላጆች/ ቤተሰቦች ጫና የሚደረግብኝ መስሎ ይሰማኛል።	89	2.3933	1.06192	ዝቅተኛ
41. የትምህርት ቤታችን ርዕሳነ-መምህራን/ አስተዳዳሪዎች የተማሪዎችን የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት ከመማር ጋር ስለሚያወዳድሩ፣ የተማሪዎች የፈተና ውጤት እንዳሻሽል ተጽዕኖ የሚያሳድርብኝ ይመስለኛል።	89	2.9326	1.23212	መካከለኛ
ውጫዊ ጫናዎች በመምራኑ የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚሳድሩት ተጽዕኖ ላይ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ			**2.7266**	**መካከለኛ**

ሠንጠረዥ 4.15 እንደሚያመለክተው፣ አንደኛ በየደረጃው ያሉ የትምህርት ዘርፍ መዋቅሮች ለምሳሌ የወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች፣ የዞን ትምህርት መምሪያዎችና የክልላቸው ትምህርት ቢሮ፤ ሁለተኛ የተማሪዎች ወላጆች/ ቤተሰቦች፣ ሦስተኛ የትምህርት ቤቶቻቸው ርዕሳነ-መምህራን/ አስተዳዳሪዎች መምህራን የተማሪዎቻቸውን የፈተና ውጤት እንዲያሻሽሉ ወይም ተማሪዎቻቸውን በማጠናቀቂያ ፈተናው ጥሩ ውጤት የሚያስመጣ ስራ እንዲሰሩ የሚደርስባቸው ጫና እንዳለ

ለማረጋገጥ ለተጠየቁት ሦስት ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ መካከለኛ በሚባል ደረጃ ተጽዕኖ ይደርስብናል/ ይደረግብናል ብለው እንደሚያምኑ የሚያሳይ ነው፡፡ የተጽዕኖው ደረጃ ግን ከየትኛውም አቅጣጫ ጠንካራ የሚባል እንዳልሆነ የውጤት ትንተናው ያሳያል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጡት መልስ በተናጠል ሲታይ ደግሞ ለ40ኛው ጥያቄ የተሰጠው መልስ መምህራኑ የተማሪዎቻቸውን ፈተና ውጤት ከፍ ለማድረግ/ ለማሻሻል የሚያስችል ስራ እንዲሰሩ ከተማሪዎቻቸው ወላጆች/ ቤተሰቦች ጫና ይደርስብናል ብለው እንደማያምኑ ያሳያል፡፡ ለቀሩት ሁለት ጥያቄዎች የሰጡት መልስ ግን የተማሪዎቻቸውን ውጤት ለማሻሻል የሚያግዝ ስራ እንዲሰሩ መካከለኛ በሚባል ደረጃ ጫና እንደሚደረግባቸው የሚያመላክት ነው፡፡

ሰ. ቋንቋውን ለማስተማር የተመደበው ጊዜ በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚፈጥረው ጫና

ሰንጠረዥ 4.16፣ ቋንቋውን ለማስተማር የተመደበው ክፍለ ጊዜ የሚፈጥረው ጫና

ጥያቄ (Item)	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
51. ቋንቋውን ለማስተማር የተመደበው ጊዜ በማስተማር ቅድመ ዝግጅት (በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀቱ)ና በማስተማር ተግባሬ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡	89	3.7191	1.26121	ጠንካራ
53. ለአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት ለደረጃው የተመደበውን ትምህርት በወቅቱ ለማጠናቀቅ በቂ/ ተመጣጣኝ ነው፡፡	89	3.8989	1.14857	ጠንካራ
ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው ጊዜ ላይ የመምህራኑ ግንዛቤ አማካይ	89	3.809.		ጠንካራ

ቀደም ብሎ እንደተወሳው ከሙከራ ጥናት አንድና ሁለት የተገኘው አንዱ ግንዛቤ ለትምህርቱ በተመደበው ክፍለ ጊዜ ላይ መምህራኑ ያላቸው አመለካከት መጠናት ያለበት መሆኑን ማሳየቱ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ከዚሁ ለቋንቋው ትምህርት ከተመደበው ጊዜ ጋር ተያይዞ ለተጠየቁት ጥያቄዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጡት መልስ የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን በቋንቋው ትምህርት የተካተቱትን ትምህርቶች ተማሪዎችን በአግባቡ እያለማመዱ ለማስተማር በቂ ነው ብለው እንደማያምኑ የሚያሳይ ነው፡፡ መምህራኑ ለጥያቄዎቹ የሰጡት ምላሽ ድምርም ሆነ ለእያንዳንዱ

ጥያቄ የሰጡት መልስ አማካይ ጠንካራ በሚባለው ደረጃ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ይህም መምህራኑ የተመደበውን ትምህርት በተመደበለት ክፍለ ጊዜ ውስጥ ለመሸፈን አዳጋች ነው የሚል ግንዛቤ እንዳላቸውና የማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው በፈተናው በሚሸፈኑ ክፍሎች ላይ እንዲያተኩር ተጽዕኖ ከሚፈጥሩባቸው ምክንያቶች አንዱ ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ መጠን አነስተኛ መሆን ነው የሚል አመለካከት እንዳላቸው የሚሳይ ነው፡፡

ሸ. የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ /ዳራ በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚፈጥረው ጫና

ሰንጠረዥ 4.17፣ የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ በመምህራን ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ

ጥያቄ	የተሳታፊዎች ድምር	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
52. ተማሪዎች ወደ አጠቃለይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ ይዘውት የሚመጡት የቋንቋ ችሎታ ከደረጃቸው ጋር ተመጣጣኝ ነው፡፡	89	3.5281	1.13908	ጠንካራ
የተማሪዎች ዳራ ላይ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ አማካይ	89	3.528		ጠንካራ

በመደበኛ መርሐ ግብር የሚሰጥን የቋንቋ ትምህርት እንዲፋጠን ወይም እንዲጓተት በማድረግ ረገድ የተማሪዎች የኋላ ዳራ ወይም የቀደመ ዕውቀት ሚና እንደሚጫወት የታወቀ ነገር ነው፡፡ ከሁለቱ የሙከራ ጥናቶች ከተገኙ ግንዛቤዎች አንዱ በጥናቱ ሊካተቱ ከሚገባቸው ጉዳዮች አንዱ የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ዳራ ሊሆን እንደሚገባው አቅጣጫ ማሳየቱ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የቋንቋ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ ላዳበሩት ግንዛቤ በምክንያትነት ከተካተቱት ተላውጠች መካከል አንዱ ሆኖ እንዲመረመር ተደርጓል፡፡ ጥያቄው ተማሪዎች ወደ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ ይዘውት የሚመጡት የቋንቋ ችሎታ ከደረጃቸው ጋር የሚመጣጠን መሆን አለመሆኑን ለመለየት የሚያስችል ነው፡፡ ሰንጠረዥ4.17 እንደሚያመለክተውም የጥናቱ

ተሳታፊዎች ጠንካራ በሚባል ደረጃ ተማሪዎቻቸው የ፩ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁትና ወደ ዘጠነኛ ክፍል የሚያልፉት በቋንቋው ትምህርት ማዳበር የሚጠበቅባቸውን ችሎታ ሳያዳብሩ ወይም በቂ አቅም ሳይፈጥሩ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ከዚህም መምህራኑ ቋንቋውን ሲያሰተምሩ በተገቢው ጊዜ ለየደረጃው የተመደበውን ትምህርት በወቅቱ ለመሸፈንና የተማሪዎቻቸውን የቋንቋ ችሎታ ከሚፈለገው/ ከሚጠበቀው ደረጃ ለማድረስ ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አዳብረው መምጣት የነበረባቸውን የቋንቋ ችሎታ ሳያዳብሩ መምጣት አንዱ ተፅዕኖ ፈጣሪ ምክንያት ነው ብለው እንደሚያምኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በውይይቶቹ የተሳተፉት የዞን ከተማና ትምህርት መምሪያ ኃላፊዎችም የመምህራኑን ሐሳብ ይጋራሉ፡፡

በአጠቃላይ በተለያዩ ተመራማሪዎች በቋንቋ መምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ /የክፍል ትምህርት አቀራረብ ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ ምክንያትነት (Factors) ከሚጠቀሱት ተላውጠዎች መካከል በዚህ ጥናት አብዛኞቹ (መምህራን ለሙያቸው የሚሰጡት ክብር፣ ስለፈተናው ያላቸው ዕውቅያ፣ ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን፣ የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ፣ የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ/ ዳራ) መምህራኑ በፈተናዎቹ ወሽባክ ላይ ለሚኖራቸው ግንዛቤ ጠንካራ ተፅዕኖ ፈጣሪ ምክንያቶች ሆነው ሲገኙ የሌሎቹ ተላውጠዎች (ለምሳሌ ተማሪዎች በፈተናው የሚያስመዘግቡት ውጤት የጠቀሜታ ደረጃ፣ ውጫዊ ጫናዎች) የተጽዕኖ ደረጃ ደግሞ መካከለኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ መረጃዎቹ በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ሲፈተሹ የሚኖራቸው የተጽዕኖ ደረጃ ደግሞ በቀጣዮቹ ሁለት ክፍሎች ይቀርባል፡፡

4.4.2..2 የወሽባክ መከሰቻ ምክንቶችን በሚመለከት በቡድን ተኮር ውይይቶች ከመምህራን የተሰበሰበ ዓይነታዊ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በቀዳሚው ክፍል ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ለወሽባክ መከሰት መንስኤ የሚሆኑ/ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን የሚመለከተው የውጤት ትንተና ቀርቧል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ እነዚህኑ የወሽባክ መከሰቻ ምክንያቶች በሚመለከት፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይቶቹ

ከመምህራኑ የተገኙት መረጃዎች ውጤት ትንተና (ከመምህራን ባህርያት ጋር ከተያያዙት ምክንያቶች በመጀመር) ይቀርባል፡፡

4.4.2..2.1 የመምህራን ባህርያት፣ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ባዳበሩት ግንዛቤና ተግባራት ላይ ያሳደሩት ጫና

ሀ. ጾታ በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ

የመምህራኑ ጾታ (ወንድ ወይም ሴት መሆን) በመማር ማስተማር ሂደት ላይና ለፈተና ተጽዕኖ በመጋለጥ ረገድ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ለተጠየቁት ጥያቄ አብዛኛዎቹ ሴት ወይም ወንድ መሆን ቋንቋውን በማስተማር ሂደት የሚያሳድረው ምንም አይነት ተጽዕኖ እንደሌለ አስረድተዋል፡፡ እንደእነዚህ መምህራን እምነት፤ ዋናው የልዩነት መነሻ ጾታ ሳይሆን የመምህሩ/ሯ እውቀት ደረጃ፣ የማስተማር ችሎታና የክፍል አያያዝ ችሎታ ነው፡፡ ከተሳታፊዎቹ ሦስት ሴቶች ብቻ ተማሪዎች ለሴት መምህራን የወንዶችን ያህል አክብሮት እንደሌላቸው/ ሴት መምህራንን እንደሚንቁና በሴት መምህራን የሚታዘዙትን እንደማይሰሩ፣ አንዳንዴም እንደሚያንጓጥጡ ገልጸዋል፡፡ አንዳንድ መምህራን ደግሞ ተማሪዎች ሴት መምህራን ላይ የተለየ ባህሪ ቢሳዩም ከማቅረብና በእናትነት ዐይን ከማየት የመነጨ እንጂ የንቀት ወይም ተማሪዎችን ለፈተና ማዘጋት ከመቻል አለመቻል ጋር የተያያዘ መስሎ እንደማይታያቸው ሲገልጹ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ቀደም ባሉት ጊዜያት ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የማየት ነገር የነበረ ቢሆንም አሁን አሁን እንዲያ ያለው አመለካከት እየቀረ ነው ብለዋል፡፡ በአጠቃላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን ግንዛቤ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከጾታ ጋር ግንኙነት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ በውይይቶቹ ሂደት ትኩረት ሰጥተው በዝርዝር አልተወያዩበትም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱም ጾታዎች ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳደራል የሚል እምነት እንዳላቸው ቀደም ብሎ ከሁለቱም ጾታዎች ንግግሮች የተወሰዱት ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም ፈተናው በሁለቱም ጾታ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድርና የሚያሳድረው ተጽዕኖ ወንድ ወይም ሴት የማይለይ እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡

ለ.የማስተማር ልምድ በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ

በተሻለ ደረጃ ለማስተማርም ሆነ ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት የማስተማር ልምድ ወሳኝ እንደሆነ ሁሉም ተወያዮች ያምናሉ፡፡ ከተወያዮች መካከል የ11 ዓመት የማስተማር ልምድ ያላቸው አንድ መምህርት ለምሳሌ ስለዚህ ሰለማስተማር ልምድ ጉዳይ ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ፣

> እኔ አሁን ፍሬሽ እያለሁ የማስተምራቸውና አሁን የማስተምራቸው የተለያየ ነው፡፡ ፍሬሽ እያለሁ ጥያቄዎችንም፣ ከማትሪክ በፊት የነበሩትን ጥያቄዎች ሰርቼላቸው ስለማላውቅ ማትሪክ ምን ላይ እንደሚያተኩር ስለማላውቀው መጽሐፉን ብቻ ይዘት አድርጌ አስተምራለሁ፡፡ እንደገና ልጆቹ ደግሞ ሳስተምራቸው አልቀበለኝ የሚሉትንም ራሱ ወደ ግጭት እየሄድን ነበር እንትን የምንለው እንጂ፤ የምንፈታው... አሁን ግን የልጆቹን ፍላጎት መሰረት አድርጌ አስተምራቸዋለሁ፤(መምህርት$_{13}$)፡፡

መምህርት$_{21}$ም እንዲሁ ልምድ በተለይ ተማሪዎችን ለፈተና ለማዘጋጀት ያለውን ጠቀሜታ ሲገልጹ “እንዴ ፈተና፣ ሳላስተምራቸው፣ ማለት አይመጣም ብዬ፣ አይ ይኸ አይመጣም ሰንጠረዥ ነገር ነው እና ስታትስቲክስ መመላት ስለሆነ ይኸ የሂሳብ ትምህርት ነው በቋንቋ ፈተና የሚመጣ አይደለም፤ ስለዚህ ይህን ማስተማር ጊዜ ማባከን ነው” በማለት ሳያስተምሩ እንዳለፉትና በዓመቱ መጨረሻ ላይ ግን በማጠናቀቂያ ፈተናው እንደዚያ ያለ ሰንጠረዥና ከሰንጠረዡ የወጡ ጥያቄዎች ተካተው እንዳገኙ፣ እና በመጽሐፉ የተካተተን ይዘት በፈተናው አይካተትም ብለው ሳያስተምሩት በማለፋቸው እንደተጸጸቱ፤ ይህም ከልምድ ማነስ የተከሰተ አጋጣሚ እንደነበረ አስረድተዋል፡፡

በአጠቃላይ አብዛኛዎቹ በውይይቶቹ ሂደት እንዳንጸባረቁት የማስተማር ልምድ በተሻለ ደረጃ ለማስተማርም ሆነ ተማሪዎችን ለፈተና ለማዘጋጀት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

ሐ. መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው ዕውቂያ (Awareness) የሚያሳድረው ተጽዕኖ

ሁሉም የውይይቶቹ ተሳታፊዎች ፈተናው በምን በምን የትምህርቱ ይዘቶች ላይ እንደሚያተኩርና ምን አይነት አቀራረብ እንዳለው/ የአጠያየቅ ቴክኒክ እንደሚከተል በደንብ እንደሚያውቁ አመልክተዋል፡፡ ለምሳሌ መምህር$_6$ "ያው እኛ ከዚህ በፊት ያሉትን የማትሪክ ሽቶችን ስለምናገላብጥ፣ ለተማሪዎችም ስለምናሰራቸው ከዚያ መሰረት አድርጎ ከዚያ ተመሳሳይ በሚቀጥለው ዓመትም እንዲህ እያለ እንደሚሄድ ስለምናውቅ መረጃው አለን፤" በማለት ስለፈተናው ያላቸውን እውቂያ ሲገልጹ፣ መምህርት$_7$ ደግሞ ስለዚሁ ጉዳይ የሚከተለውን ተናግረዋል፤

> የግድ በየዓመቱ ያለፉትን ሽቶች ለማሰራት ስለምፈልግም፣ ስለማሰራቸውም በዚያ ምክንያት ጥያቄዎችን አያቸዋለሁ፡፡ ... የበለጠ ትኩረት የሚሰጣቸው እነዚህ ከሥነ-ጽሑፍ ጋር የተያያዙ ነገሮች ናቸው፤ በመቀጠል ሰዋስው፡፡ የክሂል ትምህርቶች ለምሳሌ በንግግር መካከል ማድረግ ያለብንና የሌለብን እያለ ጽንሰ ሀሳቦች ነው የሚቀርቡት፣ ምንባብ ሲሆን ደግሞ በግጥምም በዝርውም ይቀርባል፡፡ ያው የማንበብ ክሂላቸውን፣ አንብቦ መረዳትን ነው የሚገመግመው፡፡

መምህር$_{22}$ም እንዲሁ በየዓመቱ የሚዘጋጁትን የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ጥያቄዎች በማየት የት የትና እንዴት እንደሚዘጋጁ እንደሚያውቁ በገለጹበት ክፍል እንዲህ ብለዋል፤

> የማጠናቀቀያ ፈተናው በፊት የነበረውና አሁን ያለው በጣም በጣም ይለያያል፡፡ አንደኛ መጽሐፉ አሁን ለማስተማር በሚያመች መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ የዘጠኝም የ10ም፡፡ የአምናውንም ፈተና የዘንድሮውንም ፈተና በትኩረት አይቼዋለሁ፡፡ በመጻሕፍቱ ይዘቶች ላይ ነው የሚያተኩረው... አሁን ዘንድሮ የወጣው ፈተና ለሚቀጥለው በምን ላይ ማተኮር እንዳለብህ ይነግርሃል፡፡ እኛ ስለምናየው፡፡

በሁሉም መምህራን የተሰጡት አስተያየቶች ስለፈተናው ይዘትም ሆነ አጠያየቅ እንደሚያውቁና የዕውቅናቸው ምንጭም ራሳቸው በየዓመቱ የሚዘጋጁት ፈተናዎች እንደሆኑ አመልክተዋል፡፡

በውይይቶቹ መምህራኑ ብቻ ሳይሆኑ ተማሪዎቻቸውም የፈተናዎችን ይዘቶችና አጠያየቆች እንደሚያውቁ ተንጸባርቋል፡፡ ተማሪዎቻቸው ስለፈተናውና የፈተናውን

ትኩረት እንደሚያውቁ ሲያስረዱም ሰዋስው ላይ አተኩራችሁ አስተምሩን፣ ይኸኛው በፈተና ስለማይጠየቅ እንዝለለው፤ ወዘተ ይሉናል የሚል ምሳሌ ሰጥተዋል።

የማጠናቀቂያ ፈተናው በተወሰኑ የትምህርቱ ክፍሎች ላይ የሚያተኩር ቢሆንም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከመማሪያ መጽሐፎቹ ላይ እየሆነ እንደመጣና ይህም በመምህራን ዘንድ አዎንታዊ እይታ እያገኘ እንዲመጣ እንዳደረገው በውይይቶቹ ተገልጿል። ለምሳሌ ከተወሰኑ ዓመታት በፊት በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በትምህርትነት ያልተካተቱ ይዘቶች በፈተናው ይካተቱ የነበረ ቢሆንም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን እንዲህ ያሉ ጥያቄዎችን በፈተናው ማካተቱ እየቀረ እንደመጣና ሙሉ በሙሉ/ሁሉም ጥያቄዎች በሚባል ደረጃ በትምህርቱ ላይ ብቻ እንዲመሰረቱ እየተደረገ እንደመጣ በሁሉም ቦታዎች በተካሄዱት ውይይቶች ተንጸባርቋል።

ከዚህም መምህራኑ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ይዘትና አጠያየቅ በጥልቀት እንደሚያውቁና የዕውቀታቸው ምንጮችም ራሳቸው በየዓመቱ የሚዘጋጁት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል። ስለፈተናው ይበልጥ ባወቁ ቁጥርም የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ተግባራቸው ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እያደገ እንደሚሄድ መምህርት[21] ስለልምድ ጠቃሚነት በገለጹበት ክፍል፣ በመማሪያ መጽሐፉ በሰንጠረዥ የቀረበን ይዘት/መረጃ ማስተማሩ አይጠቅምም ብለው ከዘለሉት በኋላ እንደዚያ ያለ መረጃ በፈተናው ተካቶ ሲያገኙት እንዴት ያለ የቁጭትና የጸጸት ስሜት እንደተሰማቸው የገለጹት ሀሳብ አንድ ማስረጃ ነው።

መ. መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ የሚያሳድረው ተጽዕኖ

በማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎች የሚያስመዘግቡትን ውጤት ደረጃና በተማሪዎች መማኢ የትምህርት ሕይወት ላይ ያለውን አስተዋጽኦ/ የተፅዕኖ ደረጃ ምን እንደሚመስል እንዲገልጹ ለተጠየቁት ጥያቄ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች አንደኛ ደረጃውን በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ ውጤት በ ኤ(A) እና በ ቢ(B) ብዛት አብዛኛውን ጊዜ ከ1-5 ካሉት ደረጃዎች እንደማይወጣ ተናግረዋል። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ተሳታፊ

“በጣም ጥሩ ነው ባይባልም ከሌሎቹ የተሻለ ነው” (መምህርት$_7$) ሲሉ፤ መምህር$_{12}$ ደግሞ “ደረጃው ወጣ ገባ ነው” ብለዋል። በየትምህርት ቤቶቹ ምክትል ርዕሳነ መምህራን ቢሮ የተቀመጡት ስታትሲቲኮችም ብዙ ጊዜ ከ1-5 ያለውን ደረጃ ይይዛል የተባለውን ሀሳብ የሚያንጸባርቁ ናቸው። ሁለተኛ፣ ከዚሁ ጋር አያይዘው ተማሪዎቹ በፈተናዎቹ የሚያስመዘግቡት ውጤት ያለውን ጠቀሜታ ሲገልጹ እንደተናገሩት በቋንቋው ፈተና ጥሩ ውጤት የሚያመጡ በተለይም ‘ኤ’ እና ‘ቢ’ የሚያመጡ ተማሪዎችን ወደ መሰናዶ ትምህርት ለማለፍ እንደሚያግዛቸው፣ ሲ(C) እና ከዚያ በላይ ያመጡና ወደ መሰናዶ ለመሸጋገር ያልቻሉትን ደግሞ ወደ ሌሎች የስልጠና መስኮች (መምህራን ኮሌጆች፣ ቴክኒክና ሙያ፣ ጤናና የመሳሰሉት ተቋማት) ለመግባት የአማርኛ ውጤታቸው እንደሚያገለግላቸው በውይይቶቹ ተንጸባርቋል። በቃለ መጠይቆች የተሳተፉት የየትምህርት ቤቶቻቸው ምክትል ርዕሳነ መምህራንም የመምህራኑን ሀሳብ አጠናክረዋል።

ሠ. መምህራን ለሙያቸው ያላቸው ከበሬታ የሚያሳድረው ተጽዕኖ

በውይይቶቹ የተሳተፉት መምህራን ለሙያቸው ስለሚሰጡት ክብር ለተጠቁት ጥያቄ የሰጡት መልስ አንደኛ፣ በሌሎች ወገኖች ይሰጠው የነበረው ከበሬታ እየቀነሰ ቢመጣም፤ ሁለተኛ፣ በኢኮኖሚም ተጎጅ እየሆንን ቢሆንም፣ በእነዚህ ጫናዎች ውስጥ እያለፍንም ቢሆን ለሙያችን የምንሰጠው ከበሬታ እንዳለ ነው ባይ ናቸው። ለብዙ ዓመታት በዚሁ ስራ መቆየታቸውንም ለሙያቸው የሚሰጡት ከበሬታ አንዱ መገለጫ አድርገው የጠቀሱ ተሳታፊዎችም አሉ። ሌላው ለሙያቸው የሚሰጡት ከብር መገለጫ ተደርጎ የቀረበው ተማሪዎቻቸውን ለስኬት ለማብቃት የሚያደርጉት ጥረት ነው። የተማሪዎቻቸው ስኬት አንዱ መገለጫም ተማሪዎቻቸው በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ከሚያስመዘግቡት ውጤት ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ እረገድ አብዛኞቹ የውይይቶቹ ተሳታፊዎች ተማሪዎቻቸው በየዓመቱ በሚሰጡት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥሩ ውጤት ሲያመጡ እንደሚደሰቱ፣ ዝቅተኛ ውጤት ሲያመጡ ደግሞ እንደሚከፉ በውይይቶቹ አንጸባርቀዋል።ይህም የAlderson እና Wall (1993) ሀሳብ የሚጋራ ነው። ከዚሁ ሀሳብ ጋር በተያያዘ፣ ለምሳሌ መምህር$_{20}$ በእነሱ ትምህርት ቤት የሚደረገውን ሲገልጹ የሚከተለውን ብለዋል፤

> በዚህ ትምህርት ቤት 'ማትሪክ' መጥቶ እንትን እንዳለ በአማርኛ ስንት ኤ፣ ስንት ቢ እንደመጣ፣ ስንት ሲ እንደመጣ እንገመግማለን፤ እናያለን፡፡ ስንት ልጆች እንዳለፉ እናያለን፡፡ እና ልጆቹ ሲያልፉ ነው የምንደሰተው፤ ጥሩ ውጤት ሲያመጡ ነው የምንደሰተው፡፡ ተስብስበንም ይህን ያህል ተማሪ አልፏል፤ ይህን ያህል ተማሪ ወድቋል፤ ብለን እናያለን፣ እንገመግማለን፡፡ እና ልጆቹ ሲያልፉ ነው የምንደሰተው፤ ለዚያም ነው ፈተና ተኮር አሰራር የምንሰራው፤ ልጆቹ ደህና ውጤት እንዲያመጡ፣ ጥሩ ውጤት አምጥተው በቃ ለወደፊት መሰናዶ የሚገቡ ተማሪዎች በአማርኛ ምን ያህል ሰሩ፣ ምን ያህል ኤ አመጡ፣ ምን ያህል ቢ አመጡ ከሚለው አንጻር እንትን እንላለን፡፡ የዘንድሮው ዓመት ከሚቀጥለው ዓመት ራሱ እንትን ሲል የሆነ ነገር ቅር ይለናል፡፡ ምን ልናደርግ ነው ተባብለን እንደገና እንመካከራለን፡፡

መምህር[19] ደግሞ "እኔ ከውጤታቸው ይልቅ ፈተናውን ነው ቶሎ ብዬ የማየው፡፡ በቃ፣ ያልነካካሁት አለ ወይ የሚለውን ነገር ነው ቶሎ ብዬ የምመለከተው፡፡ ያልነካሁት እንትን ብሎ [ጥያቄ ወጥቶበት] ካገኘሁ በጣም ነው የሚከነክነኝ፣ የሚቆረቁረኝም" ይላሉ፡፡ ይሽኛው አስተያየት ደግሞ አንዳንድ መምህራን ሙያዊ ግዴታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን የሚመረምሩት የፈተናው ጥያቄዎች ካስተማሩት ትምህርት ጋር ካላቸው ዝምድና አንጻር እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ በቡድን ተኮር ውይይቶቹ የተሳታፉት አብዛኞቹ መምህራን ለሙያቸው ከበሬታ እንዳላቸውና ለሙያቸው የሚሰጡት ከበሬታም በአብዛኛው ተማሪዎቻቸውን በተለይ በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ለስኬት በማብቃት እንደሚገለጽ የውጤት ትንተናው አሳይቷል፡፡

ረ. የመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ

የመምህራንን የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ በተመለከተ ከአብዛኞቹ የቡድን ተኮር ውይይቶች የተገኘው መረጃ ያሳየው በተለይ ቋንቋን ለማስተማር የሚያግዝ ስልጠና አግኝተው እንደማያውቁ ነው፡፡ በውይይቶቹ ከተሳተፉት የአምስት ትምህርት ቤት 25 መምህራን መካከል የአንድ ትምህርት ቤት ሦስት ተወያዮች ብቻ በዚህ ዓመት አንድ ስልጠና እንዳገኙ ከገለጹት በስተቀር ሌሎቹ ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ብቻ ሳይሆን ቋንቋውን ማስተማር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ቋንቋ ለማስተማር በሚያግዝ የስራ ላይ ስልጠና የመሳተፍ እድል አግኝተው እንደማያውቁ ገልጸዋል፡፡ የትምህርት ቤቶቻቸው ርዕሳነ መምህራንም ይህንኑ አረጋግጠዋል፡፡ ተወያዮቹ እንኳን

የተለየ ስልጠና ልናገኝ በሁለም የትምህርት ዓይነቶች የመጽሐፍ ትውውቅ ስልጠና ሲሰጥ የአማርኛ መምህራን ብቻ ተነጥለን ነው የቀረነው በማለት በማማረር ጭምር ገልጸዋል፡፡ ከተወያዮች አስተያዬቶች መካከል የተወሰኑትን ቀንጭቦ ማቅረቡ ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ሊያደርገው ይችላል፡፡ "ስልጠና!? (ሳቅ የምጸት ሳቅ) ስልጠና ዜሮ ነው! ...አዳዲስ መጽሐፎች ተቀይረው ነበር፡፡ በርካታ መምህራን ሄደው ሰልጥነዋል፡፡... አማርኛ ሲቀየር ግን ስልጠና አልተሰጠንም፡፡ ለሌሎቹ በሙሉ ተሰጥቷል፡፡ አማርኛ አዲስ ተቀይሮ ሲመጣ ግን አልተሰጠም፤"(መምህር$_{15}$)፡፡ ይህ ሀሳብ በሁሉም ውይይቶች የተንጸባረቀ ነው፡፡ አንዳንድ መምህራን ደግሞ ቋንቋ ከጊዜ ጋር ተለዋዋጭ የሆነ፣ ፈጣን ዕድገት የሚታይበት የትምህርት መስክ በመሆኑ በየጊዜው ለመምህራኑ ስልጠና የመስጠት አስፈላጊነት የጎላ እንደሆነ ገልጸው፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ግን እንኳን በየጊዜው፣ 10 እና ከዚያ በላይ በመምህርነት በቆዩባቸው ዓመታት ተግባራዊ ሲደረግ አይተውት የማያውቁት ነገር እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ መምህር$_{12}$ ደግሞ ስለዚሁ ጉዳይ ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፤

> ከእኛ አንጻር ብዙም ስለአማርኛ ትምህርት ድጋፍ የለም፡፡ እንዲያውም አንዳንዴ ሳስብ ይዘጋል፤ ወደሚልም አቅጣጫ የሄድኩም ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ምንም የሚደረግ ድጋፍ የለም፡፡ ይኸው ስልጠናም በመጠይቁ ላይ ተነስቷል፡፡ ምንም የሚደረግ ስልጠና የለም፡፡ ...ስልጠና የተደረገው ሌሎች ... ትምህርቶች ላይ ነው፡፡ አማርኛን በተመለከተ ምንም ነገር የለም! ምንም ነገር የለም! ስለዚህ እኛ መምህራን በራሳችን ከምናነበውና ከምንታገላት ውጭ ሌላ ነገር የለም፡፡ ደግሞ የአማርኛ ችግሩ ምንድነው የሚቀርቡት ነገሮች ሁሉ ወጥ አይደሉም፡፡

4.4.2..2.2 ዐውዳዊ ባሕርያት በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግባራ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ

ሀ. የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በመምህራን ላይ የሚያሳድረው ጫና

በሁሉም ቦታዎች በተካሄዱት ቡድን ተኮር ውይይቶች ተወያዮቹ የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ሲማሩ በትምህርትነት ከተካተቱት ውስጥ ትኩረት የሚሰጧቸውና ትኩረት የሚነፍጓቸው ክፍሎች እንዳሉ አረጋግጠዋል፡፡ የዚህ ዋነኛ መንስኤ የማጠናቀቂያ ፈተናው በተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ እንደሆነ ተወያያቹ ያምናሉ፡፡ በአብዛኞቹ ተወያዮች እንደተገለፀው ተማሪዎች

በቋንቋው ትምህርት መማር የሚፈልጉትና ደስ እያላቸው የሚከታተሉት በአንደኛ ደረጃ የሰዋስውን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሥነ-ጽሑፍ ትምህርትን ነው። ከውይይቶቹ ተሳታፊዎች የተወሰኑት ደግሞ በአንደኛ ደረጃ ላይ ያስቀመጡት የሥነ-ጽሑፍ ትምህርትን ሲሆን የሰዋስው ትምህርትን ሁለተኛ ደረጃ ሰጥተውታል። ተማሪዎች የንባብ ክሂልንና የሌሎቹን ሦስቱን ክሂሎች ጽንሰ ሀሳብ ነክ ይዘቶች ለመማር ያላቸው ዝንባሌ ደግሞ በሦስተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በውይይቶቹ ተወስቷል። የውይይቶቹ ተሳታፊዎች, አብዛኞቹ ተማሪዎች በተለይ የመጻፍ፣ የንግግርና የማዳመጥ ክሂሎችን ተግባራት በተግባር እየሰሩ ለመለማመድ/ ለመማር ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ ነው የሚል ግንዛቤ አላቸው። ክሂሎቹ እርስ በርሳቸው ሲነጻጸሩ በተማሪዎች ዘንድ ያላቸውን የተቀባይነት ደረጃ እንዲገልፀ ለተጠየቁት ጥያቄ ደግሞ አብዛኞቹ የንባብ ክሂል የተሻለ ተቀባይነት አለው ብለዋል። ሁለተኛው የመጻፍ ክሂል ነው። በተወያዮቹ በተማሪዎች ዘንድ በጣም ዝቅተኛ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው ተብለው የተገለጹት ደግሞ የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎች ናቸው።

ለሰዋሰውና ለሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች የተሻለ ፍላጐት፣ ለክሂሎች ደግሞ ዝቅተኛ ፍላጐት ሊያዳብሩ የቻሉት ለምን ይመስላችኋል? ተብለው ለተጠየቁት ተጨማሪ ጥያቄ በሰጡት መልስ ተደጋግሞ የተንጸባረቀው በማጠናቀቂያ ፈተናው በስፋት የሚካተቱትና ከተማሩት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባለው መንገድ የሚጠየቁት የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍሎች ስለሆኑ ነው፤የሚለው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ለክሂሎቹ ተግባራዊ ትምህርት በተለይም ለመጻፍ፣ ለመናገርና ማዳመጥ ተግባራዊ ልምምድ ጊዜ መስጠት ለፈተናው የሚጠቅማቸውን ትምህርት የሚከታተሉበትን ጊዜ እንደማባከን እሰከማሰብ የሚደርሱ ተማሪዎች እንዳሉ አንዳንድ ተወያዮች ገልጸዋል።

ይህንን የተማሪዎችን የመማር ዝንባሌ በተመለከተ ማለትም ተማሪዎች ቋንቋውን ሲማሩ ምን መማር እንደሚፈልጉና ምን መማር እንደማይፈልጉ በተወያዮቹ ከተገለጹት ሀሳቦች መካከል አንድ ምሳሌ እንመለከት፤

> ተማሪዎች በተለይ ሰዋስውን ነው ትኩረት የሚሰጡት እንጂ ሌሎችን በተለይ አራቱ ክሂሎች ላይ ያን ያህል አይደሉም።... ከሥነ-ጽሑፍም ተግባራዊ ወደሆነው እንዲጽፉ፣ እንትን እንዲሉ ሳይሆን ይኸ በሥነ-ጽሑፍ ዙሪያ ቲዎሪውን፤ ልቦለድ፣ ኢልቦለድና ስለነሱ ቲዎሪውን በምናስተምርበት ሰዓት ያን ልቦለድ ምንድነው? ኢልቦለድ ምንድነው ? በመካከላቸው ያለው አንድነት/ ልዩነት? እነዚህን እነዚህን

> ነገሮች፤ ቲዎሪውን አስተምረን እንድናልፍ ነው እንጂ ... በተማራችሁት መሰረት ጻፉ በሚባሉበት ሰዓት ፍላጎት ያላቸው ልጆች አናሳ ናቸው፤ ብሄራዊ ፈተናውን መሰረት ስለሚያደርጉ የማንፈተነውን ለምን እንማራለን አይነት ነገር ነው፡(መምህር20)፡፡

ለማጠቃል የተማሪዎችን የመማር ዝንባሌ በተመለከተ ከውይይቶቹ የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው ፈተናው በተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው፡፡ እያሳደረ ያለው የተጽዕኖ ዓይነትም አዎንታዊም አሉታዊም ነው፡፡ በአዎንታዊነት ገጽታ ከሚጠቀሱት ዋነኛው ተማሪዎች በፈተና የሚካተቱትን (የሰዋስው፣ የሥነ-ጽሑፍ፣ በተወሰነ ደረጃ ደግሞ የአንብቦ መረዳትና በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ የሚጠየቁ የሌሎች ክሂሎችን) ክፍሎች በስፋትና በጥልቀት ለመማር የተሻለ ፍላጎትና ዝንባሌ እንዲያዳብሩ ማድረግ መቻሉ ነው፡፡ ይኽ አዎንታዊ ተፅዕኖ በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ተወስኖ የሚቀር ብቻ ሳይሆን ዘጠነኛ ክፍል ድረስ የሚዘልቅ ነው፡፡ ተወያዮች እንደገለጹት ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተና ለምን ለምን ጉዳዮች ትኩረት እንደሚሰጥ፣ የትኞቹ የትምህርቱ ይዘቶች በፈተናው እንደሚካተቱና የትኞቹ እንደማይካተቱ ማወቅ የሚጀምሩት ገና ዘጠነኛ ክፍል እያሉ ነው፡፡

የማጠናቀቂያ ፈተናው አሉታዊ ገፅታ ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የማይካተቱን የመጽሐፉ ይዘቶች/ ክፍሎች ለመማር ፍላጎት እንዳይኖራቸው ማድረጉ ነው፡፡ በተወያዮቹ እንደተንጸባረቀው የሰዋስውና ሌሎች በፈተና የሚካተቱት ክፍሎችን መምህራኑ ከመማሪያ መጽሐፎቹ በተጨማሪ ሌሎች ማጣቀሻ መጻሕፍትን እየተጠቀሙ ሁሉ እንዲያስተምሯቸው ግፊት ማድረግና ያለፉ ዓመታት ፈተናዎች እንዲሰሩላቸው ጫና መፍጠር እስከመቻል ቢደርሱም በሌላ በኩል ደግሞ በፈተናው የማይካተቱትን ለመማር ፍላጎት እንዲያጡ አድርጓቸዋል፡፡ በአጠቃላይ የተወያዮቹ ምላሽ እንዳመለከተው ተማሪዎች የማጠናቀቂያ ፈተናውን ይዘትና ትኩረት ካማወቃቸው የመነጨው ዋነኛው አሉታዊ ውጤት በፈተናው የማይካተቱትን የትምህርቱ ክፍሎች በተለይም የቋንቋውን ክሂሎች ለመማር እንዳይነሳሱ ማድረጉ ነው፡፡ ተማሪዎች በእነዚህ በፈተናው ትኩረት በማይሰጣቸው ክሂሎች ዙሪያ የክፍልም ሆነ የቤት ስራ ሲሰጣቸው ለመስራት ፈቃደኛ አይሆኑም፡፡ የዚህ መሰረታዊ ምክንያት እንዲህ ያሉ ክሂሎች በፈተናው እንደማይካተቱ ወይም ለፈተናው ለመዘጋጀት

እንደማይረዷቸው ስለሚያስቡ እንደሆነ በውይይቶቹ ተንጸባርቋል፡፡ ከተወያዮቹ የተወሰኑት ለወደፊት ሕይወታቸው በጣም የሚያስፈልጓቸው የመጻፍ፣ የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎች እንደሆኑ ለማስረዳትና ለማሳመን ጥረት ቢያደርጉም ሙከራቸው ሊሳካላቸው እንዳልቻለ በውይይቶቹ ወቅት አውስተዋል፡፡

እንደመምህራኑ እምነት ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩት በፈተናው ጥሩ ውጤት ለማምጣት ስለሆነ የሚቀርበው ትምህርት ተቀባይነት የሚኖረው ፈተና (ማትሪክ) ተኮር ሲሆን ነው፡፡ ተወያዮቹ እንደገለጹት በተቃራኒው በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚካተቱ ይዘቶች/ ጉዳዮች ከሆኑ ደግሞ በመማሪያ መጽሐፎቻቸው ባይኖሩ እንኳ አስተምረን /ሪን የሚል ጫና ይፈጥራሉ፡፡

ለ.ተማሪዎችን ውጤታማ እንዲያደርጉ ከውጭ የሚመጡ ጫናዎች

ተማሪዎቻቸውን በማጠናቀቂያ ፈተናው ውጤታማ እንዲያደርጉ የሚደርሱባቸው ውጫዊ ጫናዎች ስለመኖር አለመኖራቸው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው በየትኛውም ወገን ጉልህ የሆነ/ፊት ለፊት የሚታይ፣ አስገዳጅነት ያለው ጫና እንደሌለ የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው በትምህርት ቤቶቻቸው አስተዳደርና ከክልሉ ትምህርት ቢሮ ጀምሮ በተዘረጋው የትምህርት መዋቅር የበላይ አካላት ጫና ይደረግብናል የሚል ነው፡፡ በመጀመሪያው ጎራ ባሉት መምህራን እምነት መሰረት የተማሪዎቻቸውን ውጤት እንዲያሻሽሉ የሚያደርግ በተናጠል ከእያንዳንዱ መምህር ላይ የሚያርፍ የጎላ ጫን ከየትኛው ወገን የለም፡፡ ጫና አለ ከተባለም ጥቅል የሆነ ነው፤ በእያንዳንዱ መምህር ላይ በተናጠል የሚደርስ አይደለም፡፡ ለምሳሌ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ክፍል ደረጃ በማጠናቀቂያ ፈተናው ጥሩ ውጤት በማምጣት 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ የወጡ ተብሎ እንደሚገለጽ፣ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ደግሞ እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል ተማሪዎችን ለውጤት በማብቃት ረገድ በስንተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚገልጽ ዝርዝር መረጃ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ እንደሚለጠፍና ይህም ጥቅል የሆነ ተጽዕኖ እንጅ በእያንዳንዱ መምህር ላይ ጫና የሚፈጥር ነው ብለው እንደማያስቡ በውይይቶቹ ተወስቷል፡፡

በተቃራኒው አብዛኞቹ ተሳታፊዎች የተማሪዎችን ውጤት 70 አደርሳለሁ፣ 80 አደርሳለሁ! ካለፈው ዓመት ውጤት በ10% ከፍ እንዲል አደርጋለሁ፤ በማጠናቀቂያ ፈተናውም አምና የመጣውን 120 ኤ ወደ 150፣ 210 ቢ ወደ 250 አሳድጋለሁ የሚል ግብ /ዕቅድ እንድንይዝ እየተደረግን ነው፡፡ ይህ ከበላይ አካል የሚመጣ ትዕዛዝ/መመሪያ ነው፡፡ እንዲህ ያለውን መመሪያ/ትዕዛዝ ከላይ የሚመጣ ጫና አይደለም ለማለት አይቻልም፣ የሚል የተለየ አቋም አንጸባርቀዋል፡፡ ለምሳሌ መምህርት[23] ስለዚሁ ጉዳይ ባነሱበት ክፍል፣ "ችሎታቸውን በማናውቃቸው ተማሪዎች ላይ በየዓመቱ ሁልጊዜ ግብ ጣሉ የሚባል ነገር አለ፡፡ ግብ እንጥላለን፡፡ የተማሪዎችን ችሎታ ሳናውቅ ከተለያየ ክፍል መጥተው ግብ እንጥላለን፡፡ ይኸን እንዴት ነው የማየው፣ አንደኛ በእኛ ላይ ተማሪዎቹ አነስተኛ ውጤት ሲያመጡ ይህን ያህል ግብ ጥለህ ነበር፤ ይህን ያህል ግብ ጥለሽ ነበር፤ ከዚያ አልደረሽም፤ ችግሩ ያንቺ ነው፡፡ ሁለተኛ፣ አማርኛን እንደቀላል ስለሚቆጥሩት አማርኛም እንደፊዚክስ ከጣላችሁበት..." ለሚሉ ዓይነት ትችቶች እንደሚዳረጉ ገልጸዋል፡፡ መምህር[11]ና[12]ም በእንዲህ ያለው አስተሳሰብ ከማይስማሙት ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ በእነሱ እምነት የተማሪ ውጤት በመምህራን ጥረት ብቻ ሊሻሻል የሚችል አይደለም፡፡ የብዙ ወገኖችን ለምሳሌ የራሳቸውን የተማሪዎችን፣ የወላጆችን ወዘተ ተሳትፎና ጥረት የሚጠይቅ ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ የተማሪዎች ውጤት አለመሻሻልን የመምህሩ ችግር አድርጎ መወሰዱ አግባብነት የሌለው ጫና ነው ብለው ያስባሉ፡፡

ከዚህ ግብ ያዙ፣ ከሚለው በተጨማሪ እንዲሁ (በአብዛኞች ዘንድ በአዎንታዊ ጫናነት የሚታይ ቢሆንም) የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል መምህራን የቱቶሪያል መርሐ ግብሮችን እያዘጋጁ ተማሪዎቻቸውን እንዲያግዙ፣ እንዲሁም ያለፉ ዓመታት የማጠናቂያ ፈተናዎችን እንዲሰሩላቸው በትምህርት ቤቶቻቸው ሀላፊዎች እንደሚታዘዙ ተናግረዋል፡፡ ለምሳሌ መምህር[15] ሰለእነዚህ ጉዳዮች ሲገልጹ "ትምህርት ቤቶቹም ቢሆኑ ፈተና ይሰራላቸው፤ ቅዳሜና ዕሁድ ወይም በትርፍ ሰዓት አግዟቸው የሚል በተደጋጋሚ ያዛሉ፣ ይከታተላሉ፣ በውጤት ተኮር ውል ላይም ማበረታቻ ወይም ቱቶሪያል የሰጠ/ያልሰጠ የሚለው ላይ የራሱ የሆነ ውጤት ይያዝበታል፤" ብለዋል፣

በአጠቃላይ በቀዳሚዎቹ ዐረፍተ ነገሮች እንደተወሳው የተማሪዎችን የክፍልም ሆነ የብሄራዊ ፈተና ውጤት ከፍ ለማድረግ ግብ 'እንዲጥሉ' እና ከግብ የሚያደርሱ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በትምህርት ቤቶቻቸው አስተዳደርና በሌሎች ከትምህርት ቤት ውጭ ባሉ የትምህርት መዋቅሮች በሚሰሩ ክፍሎች አዎንታዊም አሉታዊም ተጽዕኖዎች እንደሚደረጉባቸው ሲገልጹ፣ በወላጆች በኩል ግን በአማርኛ መምህራን ላይ የሚፈጠር የተለየ ጫና የለም የሚል ሃሳብ በተወያዮቹ ተንጸባርቋል። በአጠቃላይ ወላጆችን በሚመለከት በውይይቶቹ የተንጸባረቀው በከተማም ሆነ በገጠር የልጆቹ ትምህርት ጉዳይ ይመለከተኛል የሚልና ወደ ትምህርት ቤት እየመጣ የልጆቹን የትምህርት ሁኔታ የሚከታተል ወላጅ ቁጥር በጣም ጥቂት እንደሆነ ነው።

ሐ. ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን በቂ አለመሆን

ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ አነስተኝነት በሁሉም ውይይቶች የተሳተፉ መምህራን የተነሳ ሀሳብ /ችግር ነው። በተወያዮቹ እንደተገለጸው ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር የማያስችል ነው። ለምሳሌ ስለዚሁ ቋንቋውን ለማስተማር ስለተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ አለመሆን መምህር$_8$ ሲገልጹ "ያጨናንቀናል፤ ሁለታችንም፣ ተማሪዎችንም እኛንም። እንዲያውም ትረሰዋለህ፤ ሰኞ የሰጠኻቸውን ሀሙስ ትረሰዋለህ። ተከተታይ ምዘና ለመስጠት... የክፍለ ጊዜ ጥበቱ በትምህርቱ ሂደት ላይ በጣም ተጽዕኖ አለው፤"ብለዋል። መምህር$_{12}$ም ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፣

> ክፍለ ጊዜው ያንሳል ምንም ጥያቄ አያስፈልገውም። ወይ ክፍለ ጊዜው መጨመር አለበት ወይ ደግሞ ይዘቱ መሻሻል ወይ ማነስ አለበት። በዚያ ልክ እንዲሆን መደረግ አለበት። ወይም ደግሞ በደንብ እንትን ይባል ከተባለ ክፍለ ጊዜው መጨመር አለበት። ክፍለ ጊዜውና የሚሰጠው ይዘት ምንም አይጣጣምም። አራቱንም ክሂል ስሩ ተብሎ፣ እንደገና ደግሞ ሁለት/ ሰዋሰውና ሥነ-ጽሑፍ ተጨምሮ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ማይታሰብ ነው። በጣም አስቸጋሪ ነው። እና ይሽ እንዲያውም በጣም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው። ሲቪክስ ሲመጣ ተቆንጥሮ ተሰጠው፤ ድሮ ሦስት አይደል የነበረው! አማርኛ ድሮ ሦስት እኮ ነው የነበረው።

መምህር$_{25}$ ደግሞ በተለይ ከመልመጃዎቹ ጋር አያይዘው ስለዚሁ ስለጊዜው አነስተኛነት በገለጹበት ክፍል የሚከተለውን ተናግረዋል፤

መልመጃዎች አሁን ከዚህ ሁለት ሦስት ዓመት ውስጥ የተዘጋጁት መጻሕፍት ጥሩ ናቸው። እኔ እንደምገምተው፣ ሊያሰሩ የሚችሉ ናቸው። እንደተባለው ግን መልመጃዎችን በጥልቀት ከሰር ከሰሩ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲሰራና በእነዚያ ውስጥ አልፎ ክሂሉን አዳብሮ እንዲሄድ ጊዜው በጣም ውስን ነው፣ አጭር ነው። ሁለት ክፍለ ጊዜ ብቻ ነው በሳምንት የሚሰጠው። ስለዚህ ትምህርቱን በጥልቀት ሳይሆን ዝም ብለን ነካ አድርገን ነው የምናልፍ፣ አብዛኞቻችን ጥልቀት አንሰጠውም። ጥልቀት ካልተሰጠው ደግሞ የስርጸቱ ጉዳይ ትንሽ አጠራጣሪ ነው።

ከላይ የቀረቡት ጥቅሶች በሙሉ የቋንቋው መምህራን በቋንቋው ትምህርትነት የተካተቱትን ይዘቶች (መልመጃዎቹን ጨምሮ ማለት ነው) በአግባቡ ለማስተማር የተመደበው ክፍል ጊዜ ማነስ አንዱ ፈታኝ ምክንያት ነው፤ የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው የሚያሳዩ ናቸው። የጊዜው ማነስም መምህራኑ በማጠናቀቂያ ፈተናው ወደሚካተቱ ይዘቶች እንዲያተኩሩ እንዳስገደዳቸው በውይይቶቹ በተደጋጋሚ ተወስቷል።

በዚህም ምክንያት በእነዚህ የክፍል ደረጃዎች (ዘጠነኛና አስረኛ ክፍል) በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ በማስተማር ተማሪዎችን ጥሩ አድማጭ፣ ጥሩ ተናጋሪ፣ ጥሩ አንባቢና ጥሩ ጸሐፊ እንዲሆኑ ማስቻል እንደሚከብድ በውይይቶቹ ተንጸባርቋል። በቂ ጊዜ ለቋንቋው ትምህርት ባለመመደቡና በመሳሰሉት ምክንያቶች ለዓመት የታቀደውን ትምህርት ለመሸፈን ስለማይችሉ የተወሰኑትን የትምህርቱ ክፍሎች ለመዝለል፣ የተወሰኑትን ለማጠጋጋት፣ የተወሰኑትን ነካክቶ ለማለፍ፣ የተወሰኑትን ደግሞ (በፈተናው ትኩረት የሚሰጣቸውን) በዝርዝርና በጥልቀት ለማስተማር ግድ እንደሆነባቸው አብራርተዋል። በየዓመቱ ትምህርት ቤቶች የሚዘጉት በዓመቱ መጀመሪያ በወጣው የትምህርት ካላንደር መሰረት አለመሆኑ (ወደኃላ ወደፊት የሚል መሆኑ) በደራሽ ስብሰባዎችና በመሳሰሉት ምክንያቶች የትምህርት ጊዜ የሚባክን መሆኑ ደግሞ የተመደበችውን አነስተኛ ክፍለ ጊዜ ተጠቅመው የታቀደውን ለማስተማርና ተማሪዎቻቸውን ለፈተና እንኳን በአግባቡ ሳያዘጋጁ ጊዜው እንደሚያቋርጣቸው ተናግረዋል።

ከዚህም በመምህራኑ ዘንድ እንደመሰረታዊ ችግር እየታዩ ካሉ ጉዳዮች አንዱ ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ ከትምህርቱ ይዘት ጋር የማይመጣጠን መሆን እንደሆነና በዚህ ምክንያት የመማር ማስተማር ሂደቱ በማጠናቀቂያ ፈተናው በሚሸፈኑ ይዘቶች

ላይ ብቻ እንዲያተኮር እያደረጋቸው እንደሆነ ከውጤት ትንተናው መረዳት ይቻላል፡፡

መ. የክፍል-ተማሪ ጥምርታ

የክፍል-ተማሪ ጥምርታን በተመለከተ እንዲሁ በአብዛኛዎቹ ውይይቶች የተገኘው ውጤት ትንተና እንዳሳየው ከአምስቱ ትምህርት ቤቶች የአራቱ በአንድ ክፍል በአማካይ 60 እና ከ60 በላይ ተማሪ ይማራል፡፡ በመምህራኑ እምነት መሰረት በየትምህርት ቤቶቻቸው ያለው የክፍል-ተማሪ ጥምርታ በየመማሪያ ክፍሉ የተማሪው ቁጥር ከፍተኛ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ መምህራኑም ቋንቋውን በተለይም ክሂሎችን ለማስተማር እንዳይችሉ ካገዷቸው ምክንቶች አንዱ ይኸው የተማሪ-ክፍል ጥምርታ ነው ብለው እንደሚያምኑ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ ከዚሁ ጥምርታ ቋንቋውን ለማስተማር አመቺ ካለመሆን ጋር አያይዘው መምህራኑ ያነሱት ሌላው ጉዳይ የመምህር-ክፍል/ተማሪ ጥምርታን ነው፡፡ ተወያዮች በውይይቶቹ ሂደት እንዳንጸባረቁት አንድ መምህር ከ20-30 ክፍለ ጊዜ ሊይዝ ይችላል፡፡ በዚህ አስተሳሰብ መሰረት ለምሳሌ አንድ መምህር ሀያ ክፍለ ጊዜ እንዲይዝ ቢደረግ ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ መጠን በሳምንት ሁለት ስለሆነ 10 ክፍሎችን እንዲይዝ ይገደዳል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የተማሪ-ክፍል ጥምርታው በአማካይ 50 ቢሆን እንኳ (50*10) 500 ተማሪ ማስተማርና መመዘን ይጠበቅበታል ማለት ነው፡፡ በመምህራኑ የተጠቀሰው የክፍለ ጊዜ መጠን በመመሪያ የተደገፈ እንደሆነም ከየትምህርት ቤቶቹ ምክትል ርዕሳነ/ርዕሳነ መምህራን ጋር በተካሄዱት ውይይቶችም ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ የጥናቱ ውጤት ያሳየው አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች፣ ጥምርታዎቹ ከፈተና ተጽዕኖ ጋር ቀጥተኛ/ርቱዕ ሳይሆን ኢርቱዕ የሆነ ግንኙነት እንዳላቸው የሚያምኑ መሆናቸውን ነው፡፡ ይኸውም፣ ብዛት ያላቸውን ተማሪዎች ጊዜ ወስዶ በቋንቋው ያላቸውን የተግባቦት ችሎታ ለማዳበር ከመሞከር ይልቅ ለፈተና የሚጠቅሟቸው ክፍሎች ላይ በማተኮር በገለጻ እንዲያስተምሩ የሚያበረታታ መሆኑ ነው፡፡

የክፍል-ተማሪንና የመምህር-ተማሪ ጥምርታን በሚመለከት በተወያዮቹ ከተገለጹ ሀሳቦች መካከል አንድ ሁለቱን መመልከት ይቻላል፡፡ “የመምህር-ተማሪ ጥምርታ

ከዚህ የተለየ ነው፡፡... በአማካይ እስከ 80 ነው፡፡ እንደዚያም ሆኖ ደግሞ የመምህርና ተማሪ ጥምርታ ራሱ ሎድድ ነን እኛ፡፡ ዘንድሮ ብቻ 20 ምናምን ያዝን እንጂ፣ ትዝ ይለኛል አምና 30፣ 30 ይዘን ነበር...” (መምህር11)፣ እያሉ ባለፉት ዓመታት ይዘውት የነበረውን የክፍለ ጊዜ መጠን ይዘረዝራሉ፡፡ የሌላው ትምህርት ቤት ሌላ ተሳታፊ ደግሞ እንዲህ ይላሉ፡ “የተማሪዎች ቁጥር መብዛት...የምንሰራውን ስራ እንዳንሰራ ያግደናል፡፡ ለይዘቱም ለማስተማሪያ ዘዴያችንም፣ ልጆችንም እንደፈለግን አሰስ እንዳናደርጋቸውም [እንዳንመዝናቸውም) ያደርጋል፡፡ በተለይ በእኛ ትምህርት ቤት ከ75 በላይ ነው፡፡ እንደገና ሙቀቱ አለ፡፡ ከሰዓት በኋላ እንቅልፋቸውን እየተኙ፣ ምን እያሉ ጭምር ነው፤ እና ተጽዕኖ አለው፤”(መምህርት 18)፡፡

በሁለቱም ጥቅሶች የቀረቡት ሀሳቦች በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያለው የተማሪ-ክፍልና የመምህር-ሲክሽን/ተማሪ ጥምርታ ቋንቋውን ለማስተማር የሚያስቸግር አንድ ምክንያት እንደሆነና በተለይ የተማሪ-ክፍል ጥምርታው በክልሉ የትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ ሰነድ የተመለከተውን ጥምርት የሚጻረር እንደሆነ የሚያሳይም ነው፡፡

በአጠቃላይ የቡድን ተኮር ውይይት በተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች በተወያዮች እንደተንጸባረቀው በየትምህርት ቤቶቹ ያለው የተማሪ-ክፍል ጥምርታ ወይም በየክፍሉ የሚመደቡ ተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ እንደሆነና በየክፍሉ የተመደበው የተማሪ ቁጥር እንዲሁም የመምህር-ክፍል/ተማሪ ጥምርታው ከፍተኛ መሆንም መምህራኑ ቋንቋውን በተለይም የቋንቋውን ክሂሎች በአግባቡ ማስተማር እንዳይችሉ ካገዷቸው ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ የውጤት ትንተናው አሳይቷል፡፡

ሠ. የተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ዳራ/ችሎታ የሚያሳድረው ተጽዕኖ

የቡድን ተኮር ውይይቶቹ ተሳታፊዎች፣ ተማሪዎች ወደ ዘጠነኛ ክፍል ሲዛወሩ ለደረጃው የሚመጥን ችሎታ ይዘው የሚመጡ መሆን አለመሆናቸውንና ይዘውት የሚመጡት የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚያሳድረው አዎንታዊ/ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው እንዲገልጹ በውይይቶቹ ሂደት ተጠይቀው ነበር፡፡ ከዚህ ከተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ዳራ ጋር በተያያዘ ሁሉም በሚባል ደረጃ

ተወያዮቹ የሰጡት ምላሽ አሉታዊነቱን የሚያሳይ ነው። እንደመምህራኑ እምነት የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ከሚጠበቀው ደረጃ በታች ነው። ለዚህም ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ የተጠቀሰው አብዛኞቹ ተማሪዎች ከአንደኛ-ስምንተኛ ክፍል ባሉት የትምህርት ደረጃዎች ማዳበር ያለባቸውን የቋንቋ ችሎታ ሳያዳብሩ ወደ ዘጠነኛ ክፍል እንዲዛወሩ ስለሚደረግ ነው የሚለው ነው። ተወያዮቹ እንደገለጹት አብዛኞቹ ተማሪዎች በምርጫ ፈተና፣ በዝቅተኛ ፐርሰንት፣ መውደቅ የለም፤ ተማሪው ከወደቀ መምህሩም ወደቀ ማለት ነው፤ በሚል አመለካከት እየተገፉ ስማቸውን በወግ መጻፍና ፊደል እንኳን በትክክል መለየት ሳይችሉ ነው ዘጠነኛ ክፍል የሚደርሱት። ሀሳባቸውን የበለጠ መረዳት እንዲቻል መምህራኑ ይህንኑ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ዳራ በሚመለከት ከሰጧቸው አስተያየቶች መካከል የተወሰኑትን በአስረጅነት እንመልከት። ለምሳሌ፣ መምህር$_2$ "...ተማሪዎች መሰረታዊ የሆነ የችሎታ ማነስ ይታይባቸዋል። ማለት በዚህ በዘጠነኛ ክፍል በ10ኛ ክፍል የሚሰጠውን ትምህርት ለማስጨበጥ በምናስብበት ጊዜ ከታች ይዘዋቸው የሚመጧቸው ችሎታዎች አነስተኛ በመሆናቸው ከማንበብ ከመጻፍ ክሂላቸው አንጻርም በጣም የወረደ ስለሚሆን በምንፈልገው ጊዜ የምንፈልገውን አስተምረን ወደሚቀጥለው ክፍል ለመሄድ ችግር አለ፤" በማለት ጠቅለል አድርገው ተማሪዎች ከታች ባሉት የክፍል ደረጃዎች ማዳበር የሚገባቸውን የቋንቋ ችሎታ ሳያዳብሩ ወደ ዘጠነኛ ክፍል እንደሚሻገሩ ገልጸዋል። ይህም የ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን ለደረጃው የሚገባውን ትምህርት በሚፈለገው ፍጥነት ለማስተማር እንዳይችሉ እንዳገዳቸውና የተማሪዎች አቅም ከደረጃ በታች ሆኖ መገኘቱም የትምህርቱ አሰጣጥ ፈተና ተኮር እንዲሆን ካደረጉት ምክንቶች አንዱ እንደሆነ ተንጸባርቋል። መምህር$_{25}$ ደግሞ የሚከተለውን ተናግረዋል፤

> በእኛ ትምህርት ቤት ከፍተኛ ችግር አለ። እንዲያውም አንድ ነገር ላይ ወጥተህ ተናገር ብትለው ይፈራል፤ ይርበተበታል፤ ፊቱን ይዞራል፤ ይሸማቀቃል። ቁጭ ብሎ እንኳ ተናገር ብትለው ድምጹ ራሱ አይሰማም። የብዙ ተማሪ ድምጽ አይሰማም። እና እኔ ሳስተምር የማገኘው እንደዚህ አይነት ችግሮች ነው። ምክንያቱም ከታች ሲመጡ እንደዚህ አይነት Exposure [ተጋልጦ/ልምድ] የላቸውም። ስለዚህ...አንድ ዐረፍተ ነገር አስተካክለህ በቃል ተናገር ብትለው አይናገርም። ጻፍም ብትለው እንኳ መግቢያ፣ መደምደሚያ ያለው ድርሰት አስተካክሎ አይጽፍም። አንቀጽ እንኳ አስተካክሎ አደራጅቶ መጻፍ አይችልም፤

> አንቀጽ! አስተምረኸው፣ ነግረኸው! ነግረኸው! አምስት ጊዜ ምሳሌ ሰጥተኸው ጻፍ ብትለው፣ ሁለት ልጅ ልታገኝ ትችላለህ፣ ከክፍል ውስጥ።

የመምህር[25] ማብራሪያ ተማሪዎች በመናገርና በመጻፍ ክሂል ምን ያህል ድክመት እንዳለባቸው የሚያስረዳ ነው። በክፍል ምልከታዎቹ የተስተዋለውም የተባለውን ሀሳብ የሚደግፍ ነው።

መምህርት[23] ደግሞ ተማሪዎች በቋንቋው ክሂሎች ረገድ ያለባቸውን ችግር ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፤ "አብዛኛቹ ተማሪዎች በክሂሎች ላይ ከፍተኛ ድክመት አለባቸው። በተለይ ደግሞ ጽሕፈት ላይ አንድ ርዕስ ተሰጥቷቸው ጻፉ ቢባሉ ጭራሽ አንቀጽ፤ ድርሰት መጻፍ አይችሉም፤ ተማሪዎቹ። አንብቦ መረዳት ላይም ችግር አለባቸው፤ አብዛኞቹ። አንድ ነገር ተነቦላቸው ያዳመጡትን ጻፉ ቢባሉም... በፍጹም መስራት የማይችሉ ብዙ ተማሪዎች አሉ።"

በእኒህኛዋ መምህርት የተገለጸው ደግሞ ተማሪዎች በጽሕፈት፣ በንባብና በአዳምጦ መረዳት ክሂሎች የጎላ የችሎታ ማነስ ችግር ይዘው ወደ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪነት ይሻገራሉ የሚል ዕምነት መምህራኑ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ መምህርት[3]፣ "ተማሪዎች አቶ... እንደገለጸው የተለያየ ችግር አለባቸው።" ካሉ በኋላ በምሳሌ ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ፣ "የጽሕፈት ክሂል እኛ ማስተማር ያለብን ከመጻፍ ጋር ያለ ነው። አሁን ግን ፊደል ከማስቆጠር ጋር ሆኗል የኛ ስራ፣ ማንበብም ጋር ስትሄድ እንደዚያ ነው። እኛ ዓላማችን አራቱን ክሂሎች፣ ሥነ-ጽሑፍና ሰዋስውን ማጠናከር ነው። ግን ወደዚያ ተግባር የሚያስገባን ሁኔታ የለም። የተማሪዎች ችሎታ በጣም የወረደ ነው፤" ይላሉ።

በአጠቃላይ በአምስቱም ቦታዎች በተካሄዱት ውይይቶች ተወያዮቹ ያንጸባረቁት የተማሪዎቻቸው ችሎታ በተለይም በክሂሎች ረገድ ለደረጃው የቀረበውን ትምህርት ለመማር የሚያስችል ደረጃ ላይ የማይገኝ መሆኑን የሚያንጸባርቅ ነው። የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ለምን ዝቅተኛ ሊሆን እንደቻለም በውይይቶቹ የተለያዩ ምክንያቶች ተገልጸዋል። ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ በተወያዮች የተንጸባረቁት የሚከተሉት ናቸው፤

አንደኛው የሚያልፉበት የምዘና ሥርዓት ምርጫ መሆን የሚል ነው፡፡ በመምህራኑ እምነት መሰረት የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ከደረጃ በታች እንዲሆን ያደረገው አንዱና ዋነኛው ምክንያት እየተመዘኑ ወደሚቀጥለው ክፍል እንዲያልፉ የሚደረገው በምርጫ ፈተና መሆኑ ነው፡፡ ይህን በሚመለከት መምህርት8 ሲገልጹ “ቅባ ነው ለዚህ ያበቃቸው፡፡ ቢጽፉ፤ ለሌላም ሌላ ስራ ቢጽፉ እዚህ ደረጃ አይደርሱም ነበር፡፡ ግን ቅባ ስለሆነ ለዚህ አበቃቸው፤” ሲሉ፣ መምህር2ም እንዲሁ “ቀደም ያሉ ተማሪዎችን ስንመለከት እንደአሁኑ እያጠቆሩ አይደለም የመጡት እየጻፉ፣ እያነበቡ ነው የመጡት፡፡ ስለዚህ የተሻለ ነገር አላቸው፣ በአማርኛም በእንግሊዝኛም፡፡ እንደዚያው የአሁኖቹን ስናይ ደግሞ እያጠቆሩ ነው የመጡት ከሀ-መ ብቻ እየጻፉ ነው የመጡት ሌላ ፊደል አይጽፉም፡፡” በማለት የምርጫ ፈተና የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ከመጠን በላይ ደካማ እንዲሆን ምን ያህል ሚና እንደተጫወተ ተናግረዋል፡፡

በአጠቃላይ በሁሉቱም ጥቅሶች የቀረቡት ሀሳቦች ለተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ደካማ መሆን አንዱ መንስኤ /የችግር ምንጭ የቋንቋው ትምህርት የምዘና ሥርዓት መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ሁለተኛው፣ ለተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ድክመት በምክንያትነት የተገለጸው ከዚሁ ከምርጫ የምዘና ሥርዓት ጋር ተያያዥነት ያለው የኩረጃ ባህል እያደገ መምጣት ነው፡፡ ይህን በተመለከተም መምህርት3 እንዲህ ይላሉ፣ “ይኸ የመኮረጅ ነገር የተስፋፋው በዚህ የማጥቆር ነገር ነው፡፡...አነጣጣጥሮ ...እየገለበጠ መምጣት ሆነ፡፡ ቢጽፍ ኑሮ የራሱን ችሎታ ያዳብር ነበር፡፡” ሦስተኛው ምክንያት ሆኖ የቀረበው ተማሪ መውደቅ (መድገም) የለበትም ወይም በየዓመቱ ሁሉም ተማሪ ወደሚቀጥለው ክፍል/ የትምህርት ደረጃ መዛወር አለበት፤ የሚለው በትምህርት ሥርዓቱ የተዘረጋው መርህ/ መመሪያ/ አስተሳሰብ ነው፡፡ እንደመምህራኑ ግንዛቤ ይህ አስተሳሰብ በተለይ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከመምህርነት የስራ ብቃት ጋር እንዲያያዝም ተደርጓል፡፡ ከመምህርነት የስራ ብቃትና እድገት ጋር እንዲያያዝ መደረጉም፣ ማለትም ተማሪው ከወደቀ መምህሩም ይወድቃል የሚል አተያይ እንዲዳብር መደረጉ፣ መምህራኑ ተማሪዎች ሲወድቁ እኔም አብሬ የምወድቅ ከሆነ ለምን ገፋፍቼ አላሳልፋቸውም በማለት ደካማ ተማሪዎችን ሳይቀር ያለ ችሎታቸው ከክፍል ክፍል

እንዲዛወሩ እንዲያደርጉ አድርጓቸዋል። እንደመምህራኑ እምነት ይኸም ሌላው የችግሩ አንድ ምንጭ ነው። ስለዚህኛው ችግር መምህርት9 ሲያስረዱ ፣ "ትልቁ ነገር ምን መሰለህ ይህን ነገር ያመጣው ምንድነው መሰለህ መውደቅ የለም። መምህሩ ይህን ያህል ማድረስ አለበት የሚባለው ነገር ተጽዕኖ ይሆንና እኔ ለምን ብዩ ነው የምወድቀው የሚል አስተሳሰብ በመምህሩ ያድርና ተማሪውን የግድ እንዲያልፍ ያደርጋዋል፤" ብለዋል። መምህርት23ም፣ "በዚህ ደረጃ መምህራን ግብ ጥለው ከታችኛው ክፍልም አልደርስላቸው ሲሉ የመግፋት ሁኔታ ይኖራል። ከዚያ ግን መምህሩ ተጠያቂ እንዳይሆን ከግቡ አድርሻለሁ ለማለት ውጤት የመጨመር ሁኔታ ይታያል።" በማለት በቀዳሚዋ መምህርት የተገለጸውን ሀሳብ አጠናክረዋል። ይህም የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ደካማ እየሆነ ለመምጣቱ አንዱ መንስኤ ራሳቸው የቋንቋው መምህራን ያላመኑበትን መመሪያ ላለመቀበልና ከተጠያቂነት ለመሸሽ መመሪያውን አሉታዊ ውጤት በሚያስከትል ሁኔታ/መንገድ ተማሪዎቻቸውን ደጓጉሞ ወደ ቀጣዩ የክፍል ደረጃ በማሳለፍ እንዲተረጎም / ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረጋቸው እንደሆነ ያሳያል።

አራተኛው ምክንያት ተማሪዎች ከቋንቋው ችሎታ ድክመቶቻቸው ጋር ዘጠነኛና 10ኛ ክፍል ከደረሱ በኋላ አንደኛ በየክፍሉ ብዛት ያለው ተማሪ ስለሚመደብ፣ ሁለተኛ ለቋንቋው የተመደበው ክፍለ ጊዜ መጠን በጣም አነስተኛ በመሆኑ የቋንቋው መምህራን ብዙ ክፍሎችን (ሲክሸኖችን) እንዲይዙ ስለሚገደዱ፣ ሦስተኛ የመምህራን ጊዜ ከማስተማር ውጭ በሆኑ ሌሎች ልዩ ልዩ ተግባራት የተያዘ በመሆኑ ድክመቶቻቸውን እንዲያሻሽሉ ለመርዳት/ ለማገዝ ባለመቻሉ ከነችግሮቻቸው እንዲቀጥሉ እየተደረገ እንደሆነ በውይይቶቹ ከቀረቡት ሀሳቦች ለመረዳት ተችሏል። ለምሳሌ ከዚሁ ከአራተኛው ምክንያት ጋር በተያያዘ መምህርት7 ሲገልጹ የሚከተለውን ተናግረዋል፤

> ከዚህ መጥቶ ደግሞ ያለውን ክፍተት እንኳ በተወሰነ መልኩ እንደዚህ የመጻፍ፣ የምናምን ችግር ያለባቸውን በተወሰነ መልኩ እንኳ እኛ እናግዛቸውና ትንሽ ይሻሻሉ እንኳ እንዳንል አንድ መምህር ስምንት ክፍል ነው የያዘው። የስምንት ክፍል ተማሪን እያንዳንዱን ያለበትን የክሂል ደረጃ ዐውቄ ማሻሻል ባለው ክፍለ ጊዜ አልችልም። ስለዚህ ያ ችግር አሁንም ሳይሻሻል እያለፈ ይሄዳል ማለት ነው።

ረ. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ

የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ የሚፈጥረው የተለየ ተፅዕኖ እንዳለው ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ ሲሰጡ የተንጸባረቀው አስተያየት ሁለት አይነት ነው፡፡ አንደኛው 9ኛም ሆነ 10ኛ ክፍል ማስተማር ልዩነት የለውም፤ የሚል ሲሆን ሁለተኛው የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአንጻራዊነት ሲታይ ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ይልቅ የቀረበላቸውን ትምህርት ሳይመርጡ ለመማር የተሻለ ፈቃደኝነት ያሳያሉ የሚል ነው፡፡ የዚህም ምክንያት ናቸው ተብለው የተገለጹት፣ አንደኛ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው ዕውቅና አነስተኛ ስለሆነ፣ ሁለተኛ በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ በክፍል ፈተናዎች ውጤት መውደቅ ማለፍ ስላለና ወደቀጣዩ ክፍል ማለፍ ስለሚፈልጉ፣ ነው የሚሉት ናቸው፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የ10ኛ ክፍሎችን ያህል የማንፈልገውን አንማርም እስከማለት እንደማይደርሱ በውይይቶቹ ተንጸባርቋል፡፡

ሰ. ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ቦታ

ቀደም ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው በቡድን ተኮር ውይይቶቹ ከተማ፣ ከፊል ከተማና ገጠር በመባል በተመደቡበት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴን በመጠቀም እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ከዚህ አስተሳሰብ በመነሳት ከገጠር አንድ፣ ከከፊል ከተማ ሁለት እንዲሁም ከከተማ ሁለት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ 25 የአማርኛ መምህራን በቡድን ተኮር ውይይቶች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ከውይይቶቹ መረዳት እንደተቻለውም ተማሪዎቹ የሚመጡበትና ትምህርት ቤቶቹ የሚገኙባቸው ቦታዎች መለያየት የተነሳ በሙከራ ጥናቶቹ እንደታየው ሁሉ የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ጉልህ የሆነ አጋዥ ወይም ጎጅ ገጽታ መኖሩን የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በተወያዮቹ እንደተገለጸው በሁሉም ቦታዎች ቤተ መጻህፍት አለ፡፡ ሆኖም በሁሉም ቦታዎች የሚገኙት ቤተመጻሕፍት ቋንቋውን ለማሰተማር የሚረዱ/ የሚያስችሉ በቂ መጻሕፍትና ሌሎች አጋዥ መሳሪያዎች የሏቸውም፡፡ የሁሉም ትምህርት ቤቶች መምህራን(የገጠሮችም፣ የከፊል ከተማዎችም፣ የከተሞችም) ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ናቸው፡፡ የተማሪ-ክፍል ጥምርታን በተመለከተም የገጠር ትምህርት ቤቶች ወኪል የሆነው ትምህርት

ቤት የተሻለ ቢሆንም፣ የከፊል ከተማዎቹና የከተማዎቹ ከሚጠበቀው ደረጃ በጣም ከፍ ያለ ነው፡፡ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የመጫዎቻ ቦታዎች፣ የውሀና የመሳሰሉት ነገሮች/ ፋሲሊቲዎች አለመሟላት ችግር አለ፡፡ በመካከላቸው የታዩት ልዩነቶች አንደኛ ከገጠር ገበሬ ማህበር ቀበሌዎች የሚመጡ ተማሪዎች ከሰው ጠይቀው የሚሰሯቸው የቤት ስራዎች ሲሰጧቸው የተማረና ለጥያቄዎቻቸው ተገቢ መልስ ሊሰጣቸው የሚችል ሰው የሚቸገሩ ሲሆን የከተማዎቹና የከፊል ከተማዎቹ ለእንደዚህ ያሉ ችግሮች የተጋለጡ አይደሉም፡፡ ሁለተኛ የትምህርት ቤት አንድ መምህራን እንደገለጹት በከፊል ከተማ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ከገጠር የሚመጡ ተማሪዎች ፈረቃቸው ከሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ወደቤታችን ስንሄድ በመንገድ ችግር ያጋጥመናል እያሉ ሊሰጉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ እንደጅብ ያለ አውሬ ይተናኮለናል በሚል ስጋት የመጨረሻ ክፍለ ጊዜያትን ትምህርቶች ትኩረት ሰጥተው ለመከታተል የሚቸሩበት ሁኔታ ይከሰታል/ ሊከሰት ይችላል፡፡ በሌሎቹ ትምህርት ቤቶች በተለይም በከተማ እንዲህ ያለ ችግር የለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በሌሎች ተሳታፊዎች እንደተገለጸው የከተማ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ሊያማልሉ በሚችሉ ልዩ ልዩ የመዝናኛና ለሱስ የሚያጋልጡ አካባቢዎች የተከበቡ ሲሆኑ የገጠሮቹና የከፊል ከተማዎቹ ለእንደነዚህ ዓይነቶች ችግሮች የመጋለጥ ሁኔታቸው የከተሞችን ያህል የጎላ አይደለም፡፡

ከዚህ በላይ ከመምህራኑ ምላሽ ላይ ተመሰርቶ የቀረበው የመረጃ ትንተና ውጤት ሪፖርት፣ ትምህርት ቤቶቹ የሚገኙበትና ተማሪዎቹ የሚመጡበት ቦታ መለያየት በተለይ በአማርኛ ቋንቋ የመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ በተመለከተ የሚፈጥረው ልዩነት እንደሚኖር አያሳይም፡፡ የተወሰኑ ልዩነቶች ቢኖሩም ልዩነቶቹ በተለይ ከአንድ የትምህርት ዓይነት ጋር የሚያያዙ እንዳልሆኑ በዚህ ሪፖርት ተጨምቀው የቀረቡት ሀሳቦችም ሆኑ በአባሪ 14 የቀረቡት የተሳታፊዎች ዝርዝር ምላሾች አመላክተዋል፡፡

4.4.2..3 በመጠናዊና ዓይነታዊ ዘዴች የተተነተኑ የወሽባክ መከሰቻ ምክንያቶች ውህዳዊ ውጤትና ማብራሪያ

በአጠቃላይ በዚህ "በጥናቱ ዐውድ የወሽባክ መከሰቻ ምክንያቶች ምንድናቸው?" የሚለውን የምርምር ጥያቄ በሚመለከት እስካሁን በመጠናዊና ዓይነታዊ የመረጃ መሰበቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን የውጤት ትንተናና ትርጉም በተናጠል ሲቀርብ ቆይቷል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በእነዚህ መጠናዊና ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ መንገዶች የተተነተኑት ውጤትና ማብራሪያ ተቀናጅቶ ይቀርባል።

በዚህ ጥናት መምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራቸው ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ በሚያዳብሩት ግንዛቤና በሚያከናውኑት ተግባር ላይ ጫና ሊያሳድሩ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ከመምህራንና ከትምህርት ቤት አካባቢ ሁኔታዎች/ ዐውድ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች ተፈትሸዋል። ከእነዚህ መካከል ከመምህራን ባህርያት የመምህራን፣ አንደኛ ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ፣ ሁለተኛ የማስተማር ልምድ፣ ሦስተኛ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው ግንዛቤና አራተኛ የማጠናቀቂያ ፈተናው ለተማሪዎች ያለው ጠቀሜታ የሚሉት፣ ከዐውዳዊ ባህርያት መካከል ደግሞ የተማሪዎች ለመማር ያላቸው ዝንባሌ፣ ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠንና የተማሪዎች የቀደመ የቋንቋ ችሎታ/ዳራ ዋነኛ ተጽዕኖ ፈጣሪ ምክንያቶች መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። የተወሰኑት የመምህራንም ሆኑ ዐውዳዊ ባህርያት ደግሞ መጠነኛ ወይም ኢርተዕ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሆነው ተገኝተዋል። ከመምህራን ባህርያት ጸታ፣ ከዐውዳዊ ባህርያት ደግሞ ትምህርት ቤቶቹ የሚገኙበት ቦታ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ እንደሌለ የውጤት ትንተናው አሳይቷል።

በቀዳሚው አንቀጽ እንደተቆመው ከመምህራን ባህርያት መካከል መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ ጠንካራ በሚባል ደረጃ ለወሽባክ መከሰት መንስኤ እንደሚሆን ከመጠይቁ የተገኘው የጥናቱ ግኝት አመላክቷል። በቡድን ውይይቶቹም ተመሳሳይ ሀሳብ ተንጸባርቋል። ይህም የቋንቋው መምህራን ተማሪዎቻቸው በማጠናቀቂያ ፈተናው ጥሩ ውጤት ካላመጡ ቅር እንደሚሰኙ ወይም የመምህርነት

ግዴታቸውን/ ኃላፊነታቸውን እንዳልተወጡ፣ በአንጻሩም ጥሩ ውጤት ካመጡላቸው ደግሞ ግዴታቸውን በአግባቡ እንደተወጡ ወይም ማስተማር ያለባቸውን በትክክል ያስተማሩ ሆኖ እንደሚሰማቸውና እንደሚደሰቱ ያሳያል። የዚህ አንድምታም በጥናቱ ዐውድ የጥሩ መምህርነት መለኪያ ተማሪዎችን በብሄራዊ ፈተና ለስኬት /ለጥሩ ውጤት ማብቃት ነው የሚል ነው። ሁለተኛው አንድምታ ተማሪዎችን በሥርዓተ ትምህርቱ /በመርሐ ትምህርቶች የተካተቱ ጉዳዮችን በአግባቡ ማስተማር የጥሩ መምህርነት መገለጫ ወይም የመምህርነት ግዴታ አይደለም ማለት ነው። ይህም ከAlderson እና Wall (1993) ጥናት ጋር ሙሉ በሙሉ፣ ከGhorbani (2008) ጥናት ውጤት ጋር ደግሞ በከፊል ይደጋገፋል። በከፊል የተባለበት ምክንያትም በGhorbani ጥናት ሁለቱም ማለትም ተማሪዎችን በሁለቱም በኩል አልቆ መገኘት (ተግባቦታዊ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግና በፈተናም ለስኬት እንዲበቁ ማገዝ) የቋንቋ መምህርነት ግዴታ ወይም የጥሩ መምህርነት መገለጫ ተደርገው ነው የሚወሰዱት። በጥናቱ ዐውድ ግን መሰረታዊ ጉዳይ ተደርጎ የሚወሰደው የተማሪዎች የፈተና ውጤት እንዲሻሻል ማድረግ መቻል ብቻ ነው ማለት ነው። ከተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎች በመነሳት፣ የዚህ አንዱ ምክንያት የትምህርት ጥራትን ማዕከል ያላደረገ የትምህርት ተደረሻነት ትኩረት ውጤት ነው ብሎ መገመት ይቻላል።

ሁለተኛው ከመምህራን ጋር የተያያዘ ለወሸባክ መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ የተፈተሸው መምህራን በፈተናው ስለሚካተቱ ይዘቶች፣ ክሂሎችና በፈተናው ስለጥያቄዎቹ አቀራረብ ያላቸው እውቂያ ነው። ይህን ጉዳይ በሚመለከት የጽሑፍ መጠይቁ ትንተና ውጤት (ሰንጠረዥ 4.10) እንደሚያሳየው በ4.0337 አማካይ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ጠንካራ የሚባል እውቂያ እንዳላቸው አመላክቷል። በቡድን ውይይቶቹም እንኳን እኛ ተማሪዎቻችንም ያውቁታል የሚል ምላሽ ነው የተሰጠው። በየዓመቱ በተደጋጋሚ ትኩረት የሚሰጣቸው ክፍሎች ምን እንደሆኑ፣ ከመማሪያ መጽሐፎቹ በቀጥታ ተወስደው የሚጠየቁ የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍሎች የትኞቹ እንደሆኑ፣ ወዘተ. ሁሉ ካለፉ ዓመታት ፈተናዎች ምሳሌዎችን እየጠቀሱ ጭምር አስረድተዋል። ፈተናው በምርጫ የሚቀርብ መሆኑን ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ይዘት እንዴት እንደሚጠየቅና ሊጠየቅ እንደሚችል በጥልቀት እንደሚያውቁ ሁሉ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ይህም መምህራን

ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ጠንካራ በሚባል ደረጃ እውቂያ እንዳላቸው የሚያሳይ፣ በAlderson እና Wall (1993) ስራ የቀረበውን ሀሳብ የሚያጠናክርና ከCheng (2004) ጥናት ግኝት ጋር የሚደጋገፍ ነው።

ጉዳቱ Chen (2002ለ) Hughes (1988)ን በመጥቀስ እንደገለፁት ፈተናው በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ የተመሰረተ ስላልሆነ መምህራኑ ስለፈተናው ይበልጥ እያወቁ በሂዱ ቁጥር በፈተናው የማይካተቱ የትምህርቱን ክፍሎች ችላ እንዲሏቸው የሚያደርግ መሆኑ ነው። በዚህም ጥናት በተለይ ፈተናው በቀላሉ የሚተነበይ ሆኖ መገኘቱ የAlderson እና Hamp-lyon (1996) እና የChen (2002ሀ) እና (2002ለ) ጥናት ግኝቶችም እንዳሳዩቱ የመምህራኑ የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ይበልጥ ፈተና ላይ እንዲያተኩርና መሰረታዊ የሆኑት የቋንቋው ትምህርት ክፍሎች ማለትም ክሂሎቹ ችላ እንዲባሉ ማድረጉ ነው። ይህም በቡድን ውይይቶቹ፣ በክፍል ምልከታዎቹና ከክፍል ምልከታ በኋላ ከመምህራን ጋር በተካሄዱት ቃለመጠይቆች ጭምር ተረጋግጧል። ስለፈተናው ያላቸው ዕውቂያም Andrews እና ሌሎች (2002) እንዳሉት ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን በማየት የዳበረ ነው። ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን የሚያዩትም ክፍል ውስጥ እያመጡ ለተማሪዎቻቸው መስራትና ተማሪዎቻቸውን ማሰራት ስላለባቸው ነው። ይህን ማደረግም በትምህርት ቤቶቹ አስተዳደርም፣ በተማሪዎችም የሚያስመሰግን ተግባር እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል።

ሦስተኛው ከመምህራን ባህርያት ጋር ተያይዞ የተፈተሸው ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያመጡት ውጤትና ውጤቱ ለቀጣይ ሕይወታቸው በተለይም ለትምህርት እድል ያለው ጠቀሜታ ነው። ይህም በጽሑፍ መጠይቁ የተገኘው ውጤት አማካይ የጥንካሬ ደረጃ መካከለኛ ሆኖ ተገኝቷል። ከመምህራንና ከውጫዊ የትምህርት ባለሙያዎች ጋር የተካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች፣ ከርዕሳነ/ምክትል ርዕሳነ መምህራን ጋር የተካሄዱት ቃለመጠይቆች፣ እንዲሁም በምክትል ርዕሳነ መምህራን ቢሮ የሚገኙት የውጤት ስታትስቲኮች ያሳዩትም አንደኛ፣ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ሲነጻጸር አማርኛ የተሻለ ውጤት ከሚመጣባቸው የትምህርት ዓይነቶች አንዱ እንደሆነና በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ፣ ብዙ ተማሪዎች ወደ 11ኛ ክፍል ለማለፍ ከሚያስፈልጓቸው ሰባት የትምህርት ዓይነቶች አንዱ ሆኖ እንደሚያገለግላቸው ነው። ይህም አንደኛ የትምህርት ባለድርሻ አካላት የቋንቋው ትምህርት በትክክለኛው

መስመር እየተጓዘ ነው የሚል ግንዛቤ እንዲያዳብሩና የቋንቋውን ትምህርት አሰጣጥ ተገቢ አቅጣጫ የሚያሲይዝ እርምጃ እንዳይወስዱ/ ስራ እንዳይሰሩ የሚያደርግ አሉታዊ ሚና እንደሚጫወት አመላክቷል። ሁለተኛ፣ (Alderson እና Hamp-lyons 1996፣ Chen 2002ሀ፣) እንዳሉት መምህራኑ ተማሪዎች በቋንቀው ትምህርት የሚያስመዘግቡት ጥሩ ውጤት እየጠቀማቸው ነው የሚል ግንዛቤ በማዳበራቸው ትኩረታቸውን የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል ላይ እንዲያደርጉና ማስተማር ያለባቸውን ጠቃሚ ይዘት በተለይም የቋንቋውን ክሂሎች እንዳያስተምሩ እያደረጋቸው ነው።

የማስተማር ልምድን በተመለከተ በተለይ ከመምህራን ጋር የተካሄዱት የቡድን ውይይቶች ውጤት እንዳሳየው መምህራን በተሻለ ደረጃ ለማስተማርም ሆነ ተማሪዎችን ለፈተና ለማዘጋጀት ትልቅ ድርሻ አለው፤ የሚል እምነት አላቸው። ይህም የማስተማር ልምዳቸው እየጨመረ በሄደ ቁጥር ተማሪዎቻቸውን ለፈተና የማዘጋጀት አቅማቸው እያደገ እንደሚሄድ ያሳያል። ውጤቱም Chen (2002ሀ)፣ ብዙ ጥናቶች በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ለሚከሰት የፈተና ወሽባክ አንድ ምክንያት የማስተማር ልምድ ሆኖ ተገኝቷል ያሉትን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው። ከShohamy እና ሌሎች (1996) ጥናት ግኝት ጋርም የሚደጋገፍ ነው።

ከመምህራን ጋር ከተያያዙ ጉዳዮች መካከል ጾታ አንዱ ሲሆን በዚህ ጥናት የChen (2002) ጥናት እንዳሳየው ሁሉ፣ ወንድ ወይም ሴት መምህር መሆን ለፈተና ወሽባክ መከሰት ጉልህ ሚና እንደማይጫወት የጥናቱ ግኝት አመላክቷል። የጥናቱ ግኝት ያሳየው በሁለቱም ጾታዎች ላይ ፈተናው ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑን ነው።

በዚህ ጥናት ለወሽባክ መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ ከመምህራን ጋር በተያያዘ የተካተተው ሌላው ጉዳይ **የመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ ነው**። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቁም፣ ከአብዛኞቹ ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች የተገኘው መረጃ ያሳየው ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ብቻ ሳይሆን 10 እና ከዚያ በላይ ዓመት ያስተማሩትም በመምህርነት ቆይታቸው በተለይ ቋንቋውን ለማስተማር የሚያግዝ ስልጠና አግኝተው የማያውቁ መሆናቸውን ነው። በተለይ ከመምህራኑ ጋር የተካሄዱት የቡድን ውይይቶች እንዳሳዩት መምህራን

አንደኛ፣ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን የቋንቋ ማስተማሪያ መንገዶችም ተለዋዋጭ ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ ሁለተኛ፣ በዩኒቨርሲቲ የተማሪነት ቆይታ ወቅት የሚሰጡ ከቋንቋ ማስተማር ጋር የተያያዙ ኮርሶችን መውሰድ በራሱ ምሉዕ/ጥሩ የቋንቋ መምህር ለመሆን አያስችልም፤ የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ የዚህም አንድምታ ለመምህራን በየጊዜው የማስተማር ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያስችሉ የሥራ ላይ ስልጠናዎች ሊመቻቹላቸው ይገባል የሚል ነው፡፡

ሁለተኛዎቹ ለፈተና ወሽበካ መከሰት በምክንያትነት የተፈተሹት ከትምህርት ቤት ሁኔታ/ዐውድ ጋር የተያያዙት ጉዳዮች ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ስር ከተካተቱት ተላውጠዎች መካከልም አንደኛው የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ነው፡፡ በChen (2002ሀ) ጥናት እንደተረጋገጠው ሁሉ በዚህም ጥናት የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ መምህራን በፈተና ጉዳዮች ላይ አተኩረው እንዲያስተምሩና ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ እንዲሰሩላቸው ጠንካራ ጫና እንደሚያሳድር በጽሑፍ መጠይቁም ሆነ በተተኳሪ የቡድን ውይይቶቹ የተገኙት የጥናቱ ውጤቶች አሳይተዋል፡፡ ለዚህም የመምህራን የሥራ አፈጻጸም በተማሪዎች መሞላት ጫናውን ጠንካራ እንዳደረገው መገመት ይቻላል፡፡ በውይይቶቹ ተደጋግሞ እንደተወሳው ተማሪዎች መማር የሚፈልጉት በፈተና በቀጥታ የሚጠየቁ እንደሰዋስውና ሥነ-ጽሑፍ ያሉ ትምህርት ክፍሎችን ነው፡፡ ክሂሎችን መማር አይፈልጉም፡፡ ምክንያቱን ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ብቻ ለማያያዝ ቢከብድም በክፍል ምልከታዎችም እንዲጽፉ፣ ወጥተው ለክፍሉ ንግግር እንዲያደርጉ፣ ውይይት፣ ክርክር እንዲያካሂዱ፣ ወዘተ ሲጠየቁ/ ሲታዘዙ ፈቃደኛ እንደማይሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሁለተኛው በጥናቱ የተካተተው ዐውዳዊ የወሽባክ መከሰቻ ምክንያት፣ መምህራን በውጫዊ ሀይሎች (ለምሳሌ በርዕሰ መምህራን፣ በሌሎች የትምህርት ቤት አስተዳደር ክፍሎች፣ በወላጆችና ሌሎች የትምህርት ባለድርሻ አካላት) የተማሪዎቻቸውን የፈተና ውጤት እንዲያሻሽሉ የሚደረግባቸው ጫና መኖር አለመኖሩን የሚመለከተው ነው፡፡ ይህን በሚመለከት ደግሞ በጽሑፍ መጠይቁ በመካከለኛ የጥንካሬ ደረጃ በተለይ ከትምህርት ቤታቸው አስተዳደርና ሌሎች የትምህርት ዘርፍ መዋቅሮች የተማሪዎችን

የክፍልም ሆነ የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት እንድናሻሽል ጫና ይደርስብናል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። በበድን ውይይይቶቹም አብዛኞቹ እንደዚሁ ከ40% በታች የሆነ ውጤት እያመጡ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ያለፉ ተማሪዎችን ሳይቀር 50 እና ከዚያ በላይ ውጤት አስመጣለሁ የሚል ግብ እንዲይዙ የሚያስገድድ ጫና እያሳደሩብን ነው የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል። የተገኘው ውጤትም ከHerman እና Golen (1991 እና 1993)፣ Ghorbani 2008 እና Shih (2007) ጥናት ውጤቶች ጋር የሚደጋገፍ ነው። ከእነዚህ ጥናቶች ውጤት የዚህኛው የሚለየው፣ በሁሉም መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች የተማሪዎችን ውጤት እንዲያሻሽሉ ከወላጆች የሚመጣ ጫና አለመኖሩን ማሳየቱ ነው። ይህም ወላጆች ከሌላው የትምህርት ባለድርሻ አካላት በተለይ ስለልጆቻቸው የትምህርት ውጤት የማይጨነቁ ወይም ስለውጤት ሳይሆን ስለዕውቀት የሚጨነቁ ሆነው ሳይሆን በትምህርት ሥርዓቱ እንደዋነኛ ባለድርሻ አካላት የሚጫወቱት ሚና ባለመኖሩ ወይም የሚጫወቱት ሚና ዝቅተኛ በመሆኑ ነው ማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ክፍል የተገኘው የውጤት ትንተና በመምህራኑ ላይ ከትምህርት ቤታቸው አስተዳደር ጀምሮ በትምህርት ባለድርሻ አካላት የሚደርስባቸው ጫና የተማሪዎችን የተግባበት ችሎታ ማሻሻልን ስለማያካትት ከGhorbani (2008) ጥናት ግኝት ጋር በከፊል ይለያል።

በጽሑፍ መጠይቁም፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይቶችም ሌላው የመምህራኑ የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ፈተና ተኮር እንዲሆን ዋነኛ መንስኤ ሆኗል ተብሎ የተገለጸው ለትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን ነው። በተለይ በቡድን ውይይቶቹና ከክፍል ምልከታ በኋላ በተካሄዱት ቃለመጠይቆች መምህራኑ የቋንቋውን ክሂሎች እንዳያስተምሩ ካደረጓቸው ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን አነስተኛ መሆን ነው። እንደመምህራኑ እምነት በሳምንት ሁለት ጊዜ በሚኖር የ40፣ 40 ደቂቃ ግንኙነት የቋንቋውን ክሂሎች ማስተማር በፍጹም የማይቻል ነገር ነው። ይህም የትምህርት አሰጣጡ ፈተና ላይ እንዲያተኩር ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች አንዱ ለትምህርቱ የተፈቀደው ጊዜ

መጠን ሊሆን ይችላል የሚለውን Shohamy እና ሌሎች (1996)፣ Chen (2002) ሀሳብ የሚጋራ ነው።።

በጽሑፍ መጠይቁ ጠንካራ በሚል ደረጃ የተገለጸው፣ በቡድን ውይይቶችም ዋነኛ ችግርና የክፍል ትምህርቱ ፈተና ተኮር እንዲሆን ያደረገ ነው ተብሎ የተገለጸው ሌላው ምክንያት የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ዳራ ነው።። በውይይቶቹ ተሳታፊዎች እምነት ተማሪዎቻቸው አንደኛ፣ ከእንደኛ ክፍል ጀምሮ በምርጫ ፈተና እየተገመገሙ ዘጠነኛና 10ኛ ክፍል የደረሱ በመሆናቸው፣ ሁለተኛ በትምህርት ሥርዓቱ ከታች እስከ ላይ ያለው የምዘና ሥርዓት በምርጫ ፈተና ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የኩረጃ ባሕል እተስፋፋ እንዲመጣ በማድረጉና ለደረጃው የማይመጥኑ ተማሪዎች በኩረጃ ዘጠኛና 10ኛ ክፍል የሚደርሱ በመሆኑ፣ ሦስተኛ፣ በትምህርት ሥርዓቱ ማለፍ እንጂ መውደቅ የለም፣ ተማሪው ወደቀ ማለት መምህሩ ወደቀ ማለት ነው የሚል 'ፍልስፍና' ቦታ በማግኘቱ፣ አራተኛ ተማሪዎች ከስምንተኛ ክፍል ወደ ዘጠነኛ ክፍል የሚዛወሩበት ነጥብ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ፣ ዘጠነኛ ክፍል የሚደርሱት ለደረጃው የሚመጥን የቋንቋ ችሎታ ሳይኖራቸው ነው።። የዚህም አንድምታ እንዲህ ያለ የአቅም ማነስ ችግር መኖር ተማሪዎችን ለምርጫ ፈተና ከማዘጋጀት በተጨማሪ የመጻፍ፣ የማንበብ፣ የመናገርና የማዳመጥ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያስችል ትምህርት ለማስተማር እንዳንችል አድርጎናል የሚል ነው።። ምርጫቸውም የተማሪዎቻቸው መሰረታዊ ችግር የሆነውን በቋንቋው ክሂሎች የመገልገል አቅም ማነስ ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ በፈተና ስኬታማ ሊሆኑ የሚችሉባቸውን የዕውቀት ዘርፎች ማስተማር ሆኗል ማለት ነው።።

ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች ባይቀበሉትም፣ በጥናቱ የተሳተፉት መምህራን የተማሪ-ክፍልና የመምር-ክፍል ጥምርታ በተለይ በትምህርትነት የተካተቱትን የቋንቋውን ክሂሎች ለማስተማር እንዳይቻልና ኢርቱዕ በሆነ መንገድም ቢሆን መምህራን በፈተና የሚካተቱት ክፍሎች እየመረጡ ለማስተማር እንዲገደዱ ጫና ይፈጥራል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው በተለይ ከቡድን ውይይቶች የተገኘው የጥናቱ ውጤት አመላክቷል።።

የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃን በሚመለከት ደግሞ በመምህራን መካከል ሁለት ዓይነት አስተሳሰብ እንዳለ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። አንደኛው በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ላይ ፈተናው ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል ሲሆን ሁለተኛው የፈተናው ተጽዕኖ የሚጎላው 10ኛ ክፍል ላይ ነው የሚል ነው። በሁለተኛው ሀሳብ ባለቤቶች መሰረት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አንደኛ ለ፪ኛ ደረጃ ትምህርት አዲስ ስለሆኑ ሁለተኛ ገና ወደ10ኛ ክፍል ሊያልፉ ወይም ሊወድቁ የሚችሉት በመምህራቸው በሚካሄዱ ግምገማዎች ስለሆነ፣ ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በተሻለ ደረጃ መምህራቸው የሚያዟቸውን ተግባራት ለማከናውን ፈቃደኛ ይሆናሉ። ሁለቱም ለፈተና የሚማሩና የማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ያሳደረባቸው ናቸው በሚሉት ወገኖች ግንዛቤ መሰረት ደግሞ ተማሪዎች ስለፈተናው ማወቅ የሚጀምሩት ገና ዘጠነኛ ክፍል እያሉ ነው። ይህም ፈተናው ተማሪዎች ገና ዘጠነኛ ክፍል እያሉ የሚማሩትን እንዲመርጡ እያደረጋቸው ነው የሚል ግንዛቤ እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል ማለት ነው። ምክንያቱ በእርግጥ የፈተናው ተጽዕኖ ብቻ ነው ወይስ ሌላ ጉዳይ የሚለውን በትክክል ለማወቅ ቢያስቸግርም በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፎቻቸው የተካተቱትን የመጻፍና የመናገር ክሂሎች ተግባሮች በክፍል ስራነትም ሆነ በቤት ስራነት እንዲሰሩ በመምህሮቻቸው ሲጠየቁ/ ሲታዘዙ ተግባራዊ እንደማያደርጉ በተካሄዱት የክፍል ምልከታዎችም ማረጋገጥ ተችሏል። ከቀደምት ጥናቶች ጋር ለምሳሌ ከAlderson እና Wall (1993)፣ Shohamy እና ሌሎች (1996) ተደጋጋፊነት ያለው፣ የፈተናው ጫና 10ኛ ክፍል ላይ ይጎላል የሚለው ሀሳብ ነው። ምክንያቱም በእነዚህ ጥናቶች የተረጋገጠው ፈተናው ሊሰጥ የተቃረበበት የክፍል ደረጃ ላይ የሚማሩ ተማሪዎችና የሚያስተምሩ መምህራን ይበለጥ ለፈተና ተጽዕኖ የተጋለጡ እንደሆኑ ነው። በጥናቱ ዐውድም በአብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች በተለይ የመጨረሻው የትምህርት ወር/ ግንቦት ዋነኛ ተግባር ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ጥያቄዎች ለመስራት የሚውል መሆኑ ሲታሰብ የፈተናው ጫና 10ኛ ክፍል ላይ ይበረታል የሚለው ሀሳብ ሚዛን የሚደፋ ይመስላል።

ከዐውድ ጋር የተያያዘው ሌላው ለወሸባክ መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ በጥናቱ የተካተተው ትምህርት ቤቶቹ የሚገኙበት ቦታ(ከተማ፣ ከፊል ከተማና ገጠር የመሆን ጉዳይ) ነው። ይህን በተመለከተ የጥናቱ ውጤት ትምህርት ቤቶቹ

የሚገኙበት ቦታ (ከተማ፣ ከፊል ከተማና ገጠር መሆን) እና ተማሪዎቹ የሚመጡበት ቦታ መለያየት በተለይ በአማርኛ ቋንቋ የመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ ልዩነት እንዳለው አላሳየም፡፡ ይህም ከChen (2002ሀ) ጥናት ግኝት ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡ በዚህ ጥናት እንደተረጋገጠው ሁሉ Chen (2002ሀ) ታይዋን ውስጥ ከተማን፣ ከፊል ከተማንና ገጠርን መሰረት አድረገው ያካሄዱት ጥናት ውጤት ያሳየው ትምህርት ቤቶቹ የሚገኙበት ቦታ ወይም ተማሪዎቹ የሚመጡበት አካባቢ መለያየት ለወሸባክ መከሰት መንስኤ/ ምክንያት አለመሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ክፍል መምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራቸው ላይ ፈተናው ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ላዳበሩት ግንዛቤ ጫና ሊያሳድሩ ይችላሉ ተብለው ከሚታሰቡ የመምህራንና ዐውዳዊ ባህርያት መካከል የተለያዩ ተላውጠዎችን/ ምክንያቶችን ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ በምርመራውም ከመምህራን ባህርያት መካከል የመምህራን አንደኛ ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ፣ ሁለተኛ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው ግንዛቤ፣ ሦስተኛ የማስተማር ልምድ፣ አራተኛ የማጠናቀቂያ ፈተናው ለተማሪዎች ያለው ጠቀሜታ የሚሉት፣ ከዐውዳዊ ባህርያት መካከል ደግሞ የተማሪዎች ለመማር ያላቸው ዝንባሌ፣ ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠንና የተማሪዎች የቀደመ የቋንቋ ችሎታ/ዳራ ዋነኛ ተጽዕኖ ፈጣሪ/ የወሸባክ መከሰቻ ምክንያቶች ናቸው የሚል ግንዛቤ መምህራኑ እንዳላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የተወሰኑት የመምህራንም ሆኑ ዐውዳዊ ባህርያት መጠነኛ ወይም ኢርተዕ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ከመምህራን ባህርያት ጸታ፤ ከዐውዳዊ ባህርያት ደግሞ ትምህርት ቤቶቹ የሚገኙባቸው ቦታዎች የሚያሳድሩት የጎላ ተጽዕኖ እንደሌለ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

4.4.4 የተዛምዶ ትንተና (Correlation Analysis) ውጤትና ማብራሪያ

መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ (perceptions) /በጥገኛ ተላውጠውና በመምህራን ባህሪያት(በዐቢይ ተንባይ ተላውጠዎች)፣ እንዲሁም በጥገኛ ተላውጠውና

ዐውዳዊ ባህሪያት /በንዑሳን ተንባይ ተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር አንዱ የጥናቱ ዓላማ/ጉዳይ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በቀጣይ ተላውጦዎች (Continuous Vairables) መካከል ያለው ተዛምዶ በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት የተዛምዶ መለኪያ፣ በቀጣይና ደረጃዊ (Ordinal)ተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ ደግሞ በስፒርማን የተዛምዶ መለኪያ (Muijs 2004) ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ በተላውጦዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት የታየውም ‹‹SPSS 16›› የሚባለውን የመረጃ መተንተኛ ፕሮግራም በመጠቀም ነው፡፡

በተዛምዶዎች መካከል ያለውን የጥንካሬ ደረጃ ለመግለፅ የተሞከረው ደግሞ በMuijs (2004) እና Cohen እና ሌሎች (2007) የተገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ (Magnitude/ Effect Size) ወይም የ (“r”) መጠን መለኪያ አምስት ደረጃዎችን /መስፈርቶችን በመጠቀም ነው፡፡ መስፈርቶቹም የሚከተሉት ናቸው፤

1. < 0.+/- 1 ደካማ/ Weak
2. <0.+/-3 መጠነኛ/ Modest
3. <0.+/-5 መካከለኛ/ Moderate
4. <0.+/-8 ጠንካራ/ Strong
5. >+/-0.8 በጣም ጠንካራ/Very Strong የሚሉት ናቸው፡፡

በዚሁ መሠረት ሠንጠረዥ 4.18 በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት፣ ሠንጠረዥ 4.19 ደግሞ በስፒርማን የተዛምዶ መለኪያ ዘዴ የተካሄዱትን የትንተና ውጤቶት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ቀጥሎ በእነዚህ ሁለት የተዛምዶ መለኪያዎች የተካሄዱት የትንተና ውጤቶችና ማብራሪያዎች በቅደም ተከተል ሁለቱን የምርምር ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ይቀርባሉ፡፡

4.4.4.1 መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጦው) እና በመምህራን ባህርያት መካከል ያለው ተዛምዶ የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል የሚመለሰው ጥያቄ "መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጦው) እና በመምህራን ባህሪያት (በዐቢይ ተንባይ ተላውጠዎች) መካከል ያለው ተዛምዶ ምንድነው?" የሚለው ነው። በተላውጠዎች መካከል በተለይም በጥገኛና በዐቢይ ተንባይ ተላውጠዎች መካከል ያለውን ግንኙነትና የግንኙነት ደረጃ የሚመረመርበት ክፍል ነው። በዚህ ጥናት በጥገኛ ተላውጠው ክፍልነት/ አካልነት የተካተቱ ምድቦች ተግባራት/ጊዜ አደላደል፣ የማስተማር ዘዴ፣ የትምህርት ይዘት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የክፍል ምዘና የሚሉት ሲሆኑ፣ እነዚህ አምስት ምድቦች ቀደም ብሎ በሌላ ክፍል እንደተወሳው በመምህራኑ መጠይቅ በመጀመሪያዎቹ 27 ጥያቄዎች የቀረቡት ናቸው። ለተዛምዶና ለህብረ-ድህረት ትንተና በጥገኛ ተላውጠነት የተወሰደውም የእነዚህ 27 ጥያቄዎች ድምር አማካይ (mean) ነው። በዚህ ጥናት ከመምህራን ባህርያት ጋር የተያያዙትና በጥናቱ በዐቢይ ተንባይ ተላውጠነት የተካተቱት ጉዳዮችም የመምህራን ፆታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ ለሙያቸው ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ/ ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤና የሥራ ላይ ሥልጠና ተሳትፏቸው ናቸው።

የዚህን ክፍል የትንተና ውጤት አቀራረብ በጥገኛ ተላውጠው እና በመምህራን ባህርያት/ በዐቢይ ተንባይ ተላውጠዎቹ መካከል ካለው የተዛምዶ ጉልህነት(Level of Significance) ደረጃ ለመጀመር ያህል በሰንጠረዥ 4.18 ከቀረበው የተዛምዶ ትንተና ውጤት ማስተዋል እንደሚቻለው በጥገኛ ተላውጠውና በዐቢይ ተላውጠነት በተካተቱት ነጻ/ተንባይ ተላውጠ ነተ2(ነጻ ተላውጠ2)፣ ነተ3፣ ነተ4 እና ነተ5 መካከል ጉልህ (Significant) የሚባል ተዛምዶ አለ። በጥገኛ ተላውጠውና በእነዚህ አራት ነጻ/ተንባይ ተላውጠዎች መካከል ያለው ዝምድና የስህተት ይሁንታው (Level of significance/ P- Value) < 0.001 ነው። ይህም በዐቢይ ተንባይ ተላውጠነት የተካተቱት እነዚህ አራት ነጻ ተላውጠዎች ከጥገኛ ተላውጠው ጋር ጉልህ ዝምድና እንዳላቸው የሚያሳይ

ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጥገኛ ተላውጦው ከሌሎቹ የመምህራን ባሕርያት/ ዐቢይ ተንባይ ተላውጦዎች ጋር ጉልህ የሚባል ዝምድና እንደሌለው በዚህ ሰንጠረዥም ሆነ በስፒርማን የተዛምዶ መለኪያ በተተነተነው በቀጣዩ ሰንጠረዥ የቀረቡት የውጤት ትንተናዎች ያመለክታሉ፡፡

ሰንጠረዥ 4.18 መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ(በጥገኛ ተላውጦው)ና በመምህራን ባህርያት መካከል ያለው ተዛምዶ

		.1. (ጥ1	ነተ 2.	ነተ 3.	ነተ 4.	ነተ 5.	ነተ6.	ነተ 7.	ነተ 8.
.1. መምህራን ስለ ማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ያላቸው ግንዛቤ	Pearson Correlation	1	.523**	.363**	.474**	.394**	-.003	-.071	.026
	Sig. (2-tailed)		.000	.000	.000	.000	.980	.506	.808
	N	89	89	89	89	89	89	89	89
2. ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ	Pearson Correlation	.523**	1	.312**	.563**	.462**	.137	-.127	.131
	Sig. (2-tailed)	.000		.003	.000	.000	.202	.237	.221
	N (የመላሾች ብዛት)	89	89	89	89	89	89	89	89
3. ስለፈተናው ይዘት...ያላቸው አውቂያ	Pearson Correlation	.363**	.312**	1	.241*	.264*	.236*	-.082	-.264*
	Sig. (2-tailed)	.000	.003		.023	.013	.026	.447	.012
	N(የመላሾች ብዛት)	89	89	89	89	89	89	89	89
4. ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ	Pearson Correlation	.474**	.563**	.241*	1	.279**	.049	-.110	.072
	Sig. (2-tailed)	.000	.000	.023		.008	.651	.306	.505
	N (የመላሾች ብዛት)	89	89	89	89	89	89	89	89
5. መምህራን ስለተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ያላቸው ግንዛቤ	Pearson Correlation	.394**	.462**	.264*	.279**	1	.107	.069	.143
	Sig. (2-tailed)	.000	.000	.013	.008		.318	.520	.180
	N (የመላሾች ብዛት)	89	89	89	89	89	89	89	89
6. መምህራን ስለ ክፍለ ጊዜው መጠን ያላቸው ግንዛቤ	Pearson Correlation	-.003	.137	.236*	.049	.107	1	.060	-.054
	Sig. (2-tailed)	.980	.202	.026	.651	.318		.578	.612
	N (የመላሾች ብዛት)	89	89	89	89	89	89	89	89
7. መምህራን ስለተማሪዎች ችሎታ ያላቸው ግንዛቤ	Pearson Correlation	-.071	-.127	-.082	-.110	.069	.060	1	-.106
	Sig. (2-tailed)	.506	.237	.447	.306	.520	.578		.321
	N (የመላሾች ብዛት)	89	89	89	89	89	89	89	89
8. ውጫዊ ጫናዎች ላይ ያላቸው ግንዛቤ	Pearson Correlation	.026	.131	-.264*	.072	.143	-.054	-.106	1
	Sig. (2-tailed)	.808	.221	.012	.505	.180	.612	.321	
	N (የመላሾች ብዛት)	89	89	89	89	89	89	89	89

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

*. Correlation is significant at the 0.05 level (2-tailed).

(በዚህ ጥናት ነተ ማለት ነጻ ተላውጦ ማለት ሲሆን ቁጥሮቹ ደግሞ በዚህኛው ሰንጠረዥ በግራ በኩል ከ1-8 በሠንጠረዥ 4.19 ደግሞ ከ9-15 የተዘረዘሩትን ተላውጦች ይወክላሉ፡፡)

በተዛምዶ ጥናት በሁለተኛ ደረጃ የሚነሳው በተላውጠዎች መካከል ያለው የተዛምዶ አቅጣጫ ነው። በዚህ ረገድ ከሰንጠረገሮቹ መመልከት እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ ዐቢይ ተንባይ ተላውጠዎች ከጥገኛ ተላውጠው ጋር ያላቸው ግንኙነት ቀጥተኛ/ርቱዕ (Direct) ወይም የአንዱ መጠን ሲጨምር የሌላውም የሚጨምርበት ወይም የአንዱ ሲቀንስ የሌላውም የሚቀንስበት ዓይነት ተዛምዶ ያላቸው ናቸው። ከጥገኛ ተላውጠው ጋር ተገላብጧዊ (Inverse) የሚባል ዝምድና ያላቸው ዐቢይ ተንባይ ተላውጠዎች ነተ9፣ ነተ11 እና ነተ14 መሆናቸውን ሰንጠረዥ 4.19 ያመለክታል። የቀሩት በሙሉ ከጥገኛ ተላውጠው ጋር ቀጥተኛ (Direct) ተዛምዶ ያላቸው ናቸው።

በተዛምዶ ጥናት ዋነኛውና ሦስተኛው ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ በተላውጠዎች መካከል ያለው የግንኙነት መጠን (Magnitude/ Effect Size) ነው። በዚሁ መሰረት በሰንጠረዥ 4.18 እና 4.19 የቀረቡት ውጤቶች እንደሚያሳዩት በተውላጠዎች መካከል ያለው ግንኙነት በስሕተት ይሁንታ መለኪያ ዐይን ሲታይ የአብዛኛዎቹ ውጤት ከ0.05 በላይ ይሁን እንጂ ከዚህኛው የጥንካሬ ደረጃ መለኪያ አንጻር ሲታይ ግን የጥንካሬው ደረጃ ቢለያይም በጥገኛ ተላውጠውና በዐቢይ ተንባይ ተላውጠዎች መካከል ግንኙነት እንዳለ የሚያመለክት ነው።

በዚህ ረገድ በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ከተተነተነው ከመጀመሪያው ሰንጠረዥ ስንነሳ፣ አንደኛ፣ መምህራን ስለማስተማር ሙያ ባላቸው ግንዛቤና በጥገኛ ተላውጠው(ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባዳበሩት ግንዛቤ) መካከል አዎንታዊና ጉልህ ብቻ ሳይሆን ጠንካራ (strong) ተዛምዶ (r=0.523) ወይም (r^2) = 0.273529 እንዳላቸው ያሳያል። ይህም መምህራን ተማሪዎቻቸው በማጠናቀቂያ ፈተናው ደካማ (ዝቅተኛ) ውጤት ቢያመጡ ቅር እንደሚሰኙ ወይም መስራት የነበረባቸውን ተግባር በአግባቡ ያላከናወኑ ሆኖ እንደሚሰማቸው ወይም የጥፋተኝነት ስሜት እንደሚሰማቸው፣ በአንፃሩም ተማሪዎቻቸው ጥሩ ውጤት ካመጡ ደግሞ ሙያዊ ግዴታቸውን /ኀላፊነታቸውን በአግባቡ የተወጡ ሆኖ እንደሚሰማቸው ወይም ተገቢ የማስተማር ዝግጅት እያደረጉ የማስተማር ተግባራቸውን እያከናወኑ ያሉ ሆኖ እንደሚሰማቸው የሚያሳይ ነው። በፐርሰንት ሲሰላም 27.4% የሚሆነው በመምህራን ማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ

ያዳበሩት ግንዛቤና ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ የሚጋሩት የባህሪ መጠን ነው ማለት ነው፡፡

ሁለተኛው መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ጠቀሜታ ባላቸው ግንዛቤና የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጦው) መካከል ያለው ዝምድና ነው፡፡ በዚሁ በሰንጠረዥ4.18 እንደተመለከተው በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለው የተዛምዶ መጠን ደግሞ መካከለኛ (0.474) ነው፡፡ ይህም መምህራን ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያስመዘግቡት ውጤት ወደ መሰናዶ ለማለፍም ሆነ ለሌላ ትምህርትና ስልጠና ጥሩ አስተዋፅኦ አለው ብለው የማመናቸው ሂደት ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤም ከፍ እያለ እንደሚሄድ ያሳያል፡፡ 22.47% የሚሆነው መምህራን በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ያላቸው ግንዛቤ የተገለፀው በዚሁ ስለፈተናው ጠቀሜታ ባላቸው ግንዛቤ ነው፡፡ ሦስተኛው መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ባላቸው እውቅያና መምህራን ስለፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ /በጥገኛ ተላውጦው መካከል ያለው ግንኙነት ነው፡፡ በዚህም እንደቀዳሚዎቹ ሁሉ አዎንታዊ፣ ጉልህ (significance) እና በጥንካሬ ደረጃ መካከለኛ (r=0.363) የሚባል ተዛምዶ እንዳለ ሰንጠረዥ 4.18 ያሳያል::

መምህራን ስለፈተናው ይዘትና ቅርፅ ያላቸው እውቂያ በጨመረ ቁጥር የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤም ጉልህና መካከለኛ በሆነ የጥንካሬ ደረጃ እየጨመረ /እያደገ እንደሚሄድ ያመለክታል፡፡

የስፒርማን የተዛምዶ መለኪያን በመጠቀም የተካሄደው በሰንጠረዥ 4.19 የተመለከተው የትንተና ውጤት እንደሚያመለክተው ደግሞ በመምህራን ባህርያትነት ከተካተቱት ተላውጦዎች መካከል የትምህርት ደረጃ፣ ዕድ፣ የማስተማር ልምድና የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ካላቸው ግንዛቤ ጋር/ ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ጉልህ (P< 0.05) ዝምድና የሌላቸው ናቸው፡፡ በተዛምዶ ጥንካሬም እነዚህ ተላውጦዎች ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ያላቸው ተዛምዶ ሲታይ ዕድ

ከመምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ካላቸው ግንዛቤ /ከጥገኛ ተላውጦው ጋር መጠነኛ (r = 0.189) የሚባል ወይም 3.57% ተዛምዶ ሲኖረው በትምህርት ደረጃና በጥገኛ ተላውጦው፣ በማስተማር ልምድና በጥገኛ ተላውጦው እንዲሁም በስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎና በጥገኛ ተላውጦው መካከል ያለው ግንኙነት ደካማ የሚባል እንደሆነ በዚሁ ሰንጠረዥ የቀረበው ውጤት ያመለክታል፡፡

ሰንጠረዥ 4.19፣ መምህራን ስለፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጦውና በመምህራን ባህርት /በዐቢይ ነጻ ተላውጦዎች መካከል ያለው ተዛምዶ

			ጥተ 1	ነተ 9	ነተ 10	ነተ 11	ነተ12	ነተ 13	ነተ14	ነተ 15
Spearman's rho	1. መምህራን ስለ ማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖኖ ያላቸው ግንዛቤ (ጥተ1)	Correlation Coefficient	1.000	-.082	.189	-.066	.166	.054	-.100	.067
		Sig. (2-tailed)	.	.446	.078	.538	.122	.615	.353	.532
		N	89	89	88	89	88	89	88	89
	9. የትምህርት ደረጃ(ነተ9)	Correlation Coefficient	-.082	1.000	.023	.165	.044	.004	.275**	-.124
		Sig. (2-tailed)	.446	.	.834	.123	.681	.972	.010	.247
		N	89	89	88	89	88	89	88	89
	10. ጸታ(ነተ 10)	Correlation Coefficient	.189	.023	1.000	.169	-.129	.081	.165	-.076
		Sig. (2-tailed)	.078	.834	.	.116	.232	.451	.127	.482
		N	88	88	88	88	87	88	87	88
	11. በዿኛ ደረጃ ት/ት ቤቶች የማስተማር ልምድ (ነተ 11	Correlation Coefficient	-.066	.165	.169	1.000	.098	-.029	-.070	.155
		Sig. (2-tailed)	.538	.123	.116	.	.365	.790	.520	.148
		N	89	89	88	89	88	89	88	89
	12. የተማራ- ክፍለ ጥምርታ(ነተ 12	Correlation Coefficient	.166	.044	-.129	.098	1.000	.126	-.175	.064
		Sig. (2-tailed)	.122	.681	.232	.365	.	.243	.105	.551
		N	88	88	87	88	88	88	87	88
	13. የሚያሰተምሩት የክፍለ ጊዜ ብዛት (Teaching Load in Week()	Correlation Coefficient	.054	.004	.081	-.029	.126	1.000	.049	.159
		Sig. (2-tailed)	.615	.972	.451	.790	.243	.	.649	.136
		N	89	89	88	89	88	89	88	89
	14. የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ (ነተ14)	Correlation Coefficient	-.100	.275**	.165	-.070	-.175	.049	1.000	-.136
		Sig. (2-tailed)	.353	.010	.127	.520	.105	.649	.	.206
		N	88	88	87	88	87	88	88	88
	15. የቋንቋ ምዘናን የሚመለከት ኮርስ ስለመውሰዳቸው(ነተ15)	Correlation Coefficient	.067	-.124	-.076	.155	.064	.159	-.136	1.000
		Sig. (2-tailed)	.532	.247	.482	.148	.551	.136	.206	.
		N	89	89	88	89	88	89	88	89

ተዛምዶው/ Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed)

የትምህርት ደረጃ፣ የማስተማር ልምድና የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ካላቸው ግንዛቤ/ ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ያላቸው ዝምድናም ቀጥተኛ ሳይሆን ተገላብጧዊ (Inverse) ነው፡፡ ለምሳሌ የትምህርት ደረጃ እያደገ ሲመጣ መምህራን በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያሳድረው ተፅዕኖ እየጨመረ ሳይሆን እየቀነሰ እንደሚመጣ፣ እንዲሁም መምህራን በስራ ላይ ስልጠና ይበልጥ እየተሳተፉ በሄዱ ቁጥር የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እየቀነሰ እንደሚመጣ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም መምህራን የተሻለ ስልጠና እያገኙ በሄዱ ቁጥር ለፈተና ከማስተማር እየወጡ ማስተማር ያለባቸውን ተገቢ ትምህርት ወደማስተማር እንደሚሻገሩ የሚጠቁም ነው፡፡

ይህን ክፍል ለማጠቃለል፣ በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ የተካሄደው ትንተና (በሰንጠረዥ 4.18 የቀረበው) አንደኛ መምህራን ለማስተማር ሙያ ባላቸው ግንዛቤና የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጦው መካከል አዎንታዊ፣ ጉልህ ($P < 0.001$) እና ጠንካራ (strong) ተዛምዶ መኖሩን አሳይቷል፡፡ ሁለተኛ መምህራን ስለፈተናው ጠቀሜታ ባላቸው ግንዛቤና መምህራን በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጦው እንዲሁም መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ባላቸው እውቂያና መምህራን በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ መካከል አዎንታዊ፣ ጉልህ ($P< 0.001$) እና መካከለኛ ተዛምዶ መኖሩን እንዲሁ በሰንጠረዥ4.18 የቀረበው የውጤት ትንተና አመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሰንጠረዥ 4.19 የቀረበው የስፒርማን የተዛምዶ መለኪያ ውጤት ትንተና በፆታና መምህራን በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጦው መካከል መጠነኛ የሚባል ተዛምዶ፣ በትምህርት ደረጃና በጥገኛ ተላውጦው፣ በስራ ልምድና በጥገኛ ተላውጦው እንዲሁም በስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎና በጥገኛ ተላውጦው

መካከል ደካማ ተዛምዶ መኖሩን አሳይቷል። በእነዚህ አራት የመምህራን ባህርያት/ ነፃ ተላውጠዎችና በጥገኛ ተላውጠው መካከል ያለው ግንኙነት የጉልህነት ደረጃም ከ0.05 በላይ (P> 0.05) ሆኖ ተገኝቷል። ጥገኛ ተላውጠው ከጸታ፣ ከትምህርት ደረጃና ከስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ ጋር ያለው ግንኙነትም አሉታዊ (inverse) እንደሆነ የትንተና ውጤቶቹ አመላክተዋል።

4.4.4.2 መምህራን በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤና በዐውዳዊ ባህርያት መካከል ያለው ዝምድና ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ይኸኛው ደግሞ መምህራን በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጠውና በዐውዳዊ ባህርያት /በንዑሳን ተንባይ ተላውጠዎች መካከል ያለው ዝምድና ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ክፍል ነው። በዚህ ጥናት ከዐውድ ጋር የተያያዙ ንዑሳን ተንባይ ተላውጠነት የተካተቱትም መምህራን አንደኛ በተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ሁለተኛ በተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ/ዳራ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ሦስተኛ ለትምህርቱ የተመደበው ክፍለ ጊዜ መጠን ላይ ያላቸው አመለካከት፣ አራተኛ በተማሪ-ክፍል ጥምርታ ላይ ያላቸው አስተያት/ ግንዛቤ፣ አምስተኛ በውጫዊ ጫናዎች ላይ ያላቸው አመለካከት፣ ስድስተኛ፣ የሚያስተምሩት የክፍለ ጊዜ ብዛት ላይ ያላቸው አመለካከትና ሰባተኛ ምዘናን በሚመለከት ስለወሰዱት ኮርስ ያላቸው ግንዛቤ የሚሉት ናቸው።

በዚሁ መሰረት በሰንጠረዥ 4.19 በቀረበው፣ በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ከተለኩት አራት ዐውዳዊ ባህርያት /ንዑሳን ተላውጠዎች መካከል መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ካላቸው ግንዛቤ /ጥገኛ ተላውጠው ጋር ያለው የተዛምዶ መጠን (magnitude /effect size) ከፍ ያለ ሆኖ የተገኘው የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በመምህራን ላይ የሚያሳድረው ጫና ነው። በዚህ በተንባይ ተላውጠውና በጥገኛ ተላውጠው መካከል አዎንታዊና መካከለኛ ተዛምዶ (r = 0.394/ ወይም 15.5236%)

እንዳለ፣ የጉልህነት (Level of significance) ደረጃውም ከ0.001 በታች (P< 0.001) እንደሆነ በሰንጠረዥ 4.18 የቀረበው የትንተና ውጤት ያሳያል።

በሌሎቹ ማለትም መምህራን ስለክፍለ ጊዜው መጠን ባላቸው ግንዛቤና በጥገኛ ተላውጦው፣ እንዲሁም መምህራን ስለተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ (ዳራ) ባላቸው ግንዛቤና በጥገኛ ተላውጦው መካከል ያለው ተዛምዶ ደግሞ መጠኑ ደካማ፣ አቅጣጫው አሉታዊ፣ የጉልህነት ደረጃው ከ0.05 በላይ (P > 0.05) ሆኖ ተገኝቷል። ጥገኛ ተላውጦው መምህራን ውጫዊ ጫናዎች ላይ ካላቸው ግንዛቤ ጋር ያለው ግንኙነት ደግሞ የተዛምዶ መጠኑ ደረጃ ደካማ ሲሆን አቅጣጫው አዎንታዊ፣ የጉልህነት ደረጃው ከ0.05 በላይ (P> 0.05) ነው።

በስፒርማን የተዛምዶ መለኪያ የተሰሉት ዐውዳዊ ባሕርያት ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ያላቸው ግንኙነትም የሦስቱም ተዛምዶ መጠን ደካማ/ ዝቅተኛና የጉልህነት ደረጃቸው ከ0.05 በላይ (P> 0.05) እንደሆነ የሚያሳይ ነው። የተዛምዶ አቅጣጫቸው ሲታይ ደግሞ መምህራን በተማሪ-ክፍል ጥምርታ ላይ ባላቸው ግንዛቤና በጥገኛ ተላውጦው እንዲሁም የቋንቋ ምዘናን የሚመለከት ኮርስ ስለመውሰዳቸው ባላቸው ግንዛቤና በጥገኛ ተላውጦው መካከል ያለው ተዛምዶ አሉታዊ ሆኖ ተገኝቷል።

ባጠቃላይ ዐውዳዊ ተንባይ/ ነፃ ተላውጦነት ከተካተቱት ሰባት ተላውጦዎች መካከል ከጥገኛ ተላውጦው (መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ካላቸው ግንዛቤ) ጋር ጉልህ ዝምድና (P< 0.001) ያለው፣ አዎንታዊና የተዛምዶ መጠኑ ከፍ ያለ (መካከለኛ) ሆኖ የተገኘው መምህራን የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በማስተማር ስራቸው ላይ ስለሚያሳድረው ጫና ባላቸው ግንዛቤና በጥገኛ ተላውጦው መካከል ያለው ዝምድና ብቻ ነው። በሌሎቹ ንዑሳን ተንባይ ተላውጦዎችና በጥገኛ ተላውጦው መካከል ያለው ዝምድና ደካማና ጉልህ ያልሆነ (P>0.05) ሆኖ ተገኝቷል።

ARBA MINCH UNIVERSITY

4.4.5 የህብረ ድኅረት ትንተና (Multiple Regressions Analysis) እና ማብራሪያ

በምርምሩ ሦስተኛ ጥያቄ ስር የተካተቱት የመጨረሻዎቹ ሁለት ጥያቄዎች/መላምቶች የሚመለሱት ሁለት የተለያዩ የህብረ-ድህረት ማለትም ተዋረዳዊ (Sequential /Hierarchical) እና መደበኛ (Standard/ Simultaneous) የሚባሉትን ዘዴዎች በመጠቀም ነው። በመሆኑም "SPSS 16" የሚባለውን ፕሮግራም በመጠቀም የተለያዩ የህብረ ድህረት እሙኖችን (assumptions) (ለምሳሌ ቀጥተኝነት /Linierity ፣ ጽንፈኝነት / Outliers ፣ በነጻ ተላውጦዎች መካከል ጠንካራ ተዛምዶ አለመኖርን /Milticolinerity Muijs 2004, Larson- Hall 2010፣ Muijs 2004፣ Meyers et al 2005) ማሟላት የቻሉ ተላውጦዎችን መርጦ ግንኙነታቸውን በሁለቱ የጥናቱ ጥያቄዎች ቅደም ተከተል መሰረት በመፈተሽ በጥገኛና ተንባይ ተላውጦዎች መካከል ያለውን ግንኙነትና የግንኙነት ደረጃ ለመመርመር ተሞክሯል።

4.4.5.1 በጥገኛ ተላውጦው ላይ ተፅዕኖ በሚያደርስ ዐቢይ ተላውጦ ላይ ጣልቃ የሚገቡ ተላውጦዎች

በጥገኛ ተላውጦው ላይ ተፅዕኖ በሚያደርስ በእያንዳንዱ ዐቢይ ተላውጦ ላይ ጣልቃ የሚገቡ ተላውጦዎች ምንድናቸው? የሚለውን የምርምር ጥያቄ የሚመለከት ንዑስ ርዕስ ነው። ይህ ጥያቄ ሊመለስ የሚችለውም ከአንድ ነጻ/ ተንባይ ተላውጦ ጋር የትኛው ወይም የትኞቹ ጣልቃ እንደገቡ እንዲሁም እያንዳንዳቸው በምን ያህል መጠን በጥገኛ ተላውጦው ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደሩ በግልጽ ማሳየት የሚችለውን ተዋረዳዊ (sequential) የሚባለውን የኅብረ ድኅረት ዘዴ በመጠቀም ነው። በሌላ አባባል ይህ ዘዴ አንድ ተንባይ (ነፃ) ተላውጦ ከሌላ ነጻ ተላውጦ ጋር ጣልቃ ገብቶና ለብቻው በጥገኛ ተላውጦው ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳሳደረ ለይቶ ማሳየት የሚያስችል የኅብረ ድኅረት ዘዴ ነው (Larson Hall 2010፣ Cramer 2003)። ይህም ማጠቃለያ ሞዴል (Model Summary) በሚለው የኅብረ ድኅረት ውጤትን በሚያመለክተው ሰንጠረዥ የተጋርቶ መጠን (R^2)፣ ምጥን የተጋርቶ መጠን (Adjusted R square) እና እያንዳንዱ ተላውጦ በተናጠል በጥገኛ ተላውጦው ባህሪ

ላይ ያበረከተውን አስተዋጽኦ በሚያሳየው የተጋርቶ መጠን ለውጥ (R square change) የሚገለጽ ነው።።

በMuijs (2004፣165) እንደተገለጸውም በተለይ በጥናቱ የተካተቱ ተንባይ ተላውጠዎች ከጥናቱ አካላይ (Population) ጋር ያላቸውን ተስማሚነት (Fitness) ወይም ምጥን የተጋርቶ መጠን ለመተርጎም የሚከተሉትን አራት የተስማሚነት ደረጃዎች መሰረት ማድረግ ይገባል።። እነሱም፡-

1ኛ < 0.1 ደካማ (Poor)

2ኛ. 0.11 - 0.3 መጠነኛ (Modest)

3ኛ. 0.31 - 0.5 መካከለኛ (Moderate

4ኛ. > 0.5 ጠንካራ (Strong) የሚሉት ናቸው።።

በዚሁ መሰረት በተዋረዳዊም ሆነ በመደበኛ የሕብረ-ድኅረት ዘዴ የተገኙ ምጥን የተጋርቶ መጠን (Adjusted R square) ውጤቶችን የተስማሚነት ደረጃ ለመመርመር ተሞክሯል።።

ከላይ እንደተጠቆመው በዚህ በህብረ-ድህረት ክፍል መጀመሪያ ተዋረዳዊ ዘዴን በመጠቀም የተለያዩ የህብረ-ድህረት እሙኖችን (assumptions) አሟልተው የተገኙ ስምንት ተንባይ (ነፃ) ተላውጠዎች በጥገኛ ተላውጠው ባህርይ ላይ በአንድነትና በተናጠል ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ለመፈተሽ ተሞክሮ በሰንጠረዥ4.20 የተመለከተው ውጤት ተገኝቷል።። በዚህ ሰንጠረዥ ስምንት ሞዴሎች የተካተቱ ሲሆን የመጀመሪያው መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጠው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ በተናጠል ቀርቧል።። በዚህ ሞዴል የተለያዩ ክፍሎች እንደተገለጸው የሕብረ ተዛምዶው መጠን (multiple R) 0.535፣ የተጋርቶ መጠኑ (R^2) 0.287፣ ምጥን የተጋርቶ መጠኑ (adjusted R square) 0.278 ነው።። ይህም የሞዴሉ ተስማሚነት ወይም የምጥን ተጋርቶው መጠን መጠነኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው።። በተናጠል በጥገኛ ተላውጠው ባህሪ ላይ ያደረገው

አስተዋጽኦም (R square change) 0.287 ሲሆን ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ያለው የግንኙነት ደረጃም ጉልህ ወይም ከ0.001 በታች (P< 0.001) ነው።።

ሰንጠረዥ 4.20፣ የድህረት ውጤት ተዋረዳዊ ድኅረት ((Sequential Regression) ማጠቃለያ ሞዴል (Model Summary)

Model	R	R Square	Adjusted R Square	Std. Error of the Estimate	Change Statistics				
					R Square Change	F Change	df1	df2	Sig. F Change
1	.535[a]	.287	.278	.36238	.287	34.139	1	85	.000
2	.571[b]	.326	.310	.35424	.040	4.954	1	84	.029
3	.604[c]	.364	.341	.34617	.038	4.963	1	83	.029
4	.617[d]	.380	.350	.34385	.016	2.120	1	82	.149
5	.625[e]	.391	.353	.34298	.011	1.420	1	81	.237
6	.639[f]	.408	.364	.34013	.017	2.362	1	80	.128
7	.654[g]	.428	.377	.33667	.019	2.653	1	79	.107
8	.663[h]	.440	.382	.33520	.012	1.696	1	78	.197

ሀ. ተንባዮች Predictors: (Constant), መምህራን በማስስተማር ሙያ ላይ ያላቸው ግንዛቤ

ለ.ተንባዮች/ Predictors: (Constant), መምህራን በማስተማር ሙያ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ

ሐ. .ተንባዮች Predictors: (Constant), መምህራን በማስስተማር ሙያ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ, ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ

መ. .ተንባዮችPredictors: (Constant), መምህራን ስለማስተማር ሙያ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ, ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ የትምህርት ደረጃ ,

ሠ. .ተንባዮችPredictors: (Constant), መምህራን በማስስተማር ሙያ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ, ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ የትምህርት ደረጃ ,በስራ ላይ ስልጠና ተሳትፏቸው ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣

ረ. .ተንባዮች Predictors: (Constant), መምህራን በማስስተማር ሙያ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ, ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ የትምህርት ደረጃ ,በስራ ላይ ስልጠና ተሳትፏቸው ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ በተማሪዎች መማር ዝንባሌ ላ ያላቸው ግንዛቤ

ሰ. .ተንባዮችPredictors: (Constant), መምህራን በማስስተማር ሙያ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ, ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ የትምህርት ደረጃ ,በስራ ላይ ስልጠና ተሳትፏቸው ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ በተማሪዎች መማር ዝንባሌ ላ ያላቸው ግንዛቤ፣ የተማሪዎች ችሎታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ,

ሸ. .ተንባዮች Predictors: (Constant), መምህራን በማስስተማር ሙያ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ, ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ የትምህርት ደረጃ ,በስራ ላይ ስልጠና ተሳትፏቸው ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ በተማሪዎች መማር ዝንባሌ ላ ያላቸው ግንዛቤ፣ የተማሪዎች ችሎታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣የተማሪ-ክፍል ጥምርታ

ቀ. ጥገኛ ተላውጦ Dependent Variable: መምህራን ማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ቅድመ ዝግጅታቸውና የማስተማር ተግባራቸው ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ያላቸው ግንዛቤ(Perceptions)

ሞዴል ሁለት መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤና ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ በጋራ ለጥገኛ ተላውጦው ባህሪ ያበረከቱት አስተዋፅኦ እንዲሁ ከህብረ

ተዛምዶ፣ ከተጋርቶ መጠን፣ ከምጥን ተጋርቶ መጠንና በተለይ መምህራን ስለፈተናው ያላቸው እውቅያና በተናጠል በጥገኛ ተላውጦው ባህሪ ላይ ያበረከተውን አስተዋፅኦ መጠን በግልጽ ለይቶ ያሳያል። የምጥን ተጋርቶ መጠኑም መካከለኛ ነው። ሞዴል ሦስት ደግሞ መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያና ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ በጋራ በጥገኛ ተላውጦው ላይ ያሳደሩት ተፅዕኖ የህብረት ተዛምዶ መጠኑ 0.604፣ የተጋርቶ መጠኑ 0.364 እንደሆነና የጉልህነት ደረጃው ከ0.05 በታች (P<0.05) እንደሆነ የተገለፀበት ነው። የምጥን ተጋርቶ መጠኑ ደረጃም እንደቀዳሚው መካከለኛ (0.341) ነው። ሞዴል አራት አራቱ ዐቢይ ተላውጦዎች (መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ፣ ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤና የትምህርት ደረጃቸው) በጥገኛ ተላውጦው (መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ) ላይ ያሳደሩትን የተፅዕኖ መጠን የሚያሳይ ሲሆን የዚህም ምጥን የተጋርቶ መጠን መካከለኛ ነው።

ሞዴል አምስት፣ አምስቱ የመምህራን ባህርያትን የሚመለከቱ ዐቢይ ተላውጦዎች ማለትም መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለፈተናው ያላቸው እውቂያ፣ ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ፣ የትምህርት ደረጃቸውና በስራ ላይ ስልጠና ያላቸው ተሳትፎ በአንድነት በጥገኛ ተላውጦው ባህርይ ላይ 0.625 የሕብረ ተዛምዶ መጠን፣ 0.391 የተጋርቶ መጠን (R^2) አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን የሚያሳይ ነው። ምጥን የተጋርቶ መጠኑ ደግሞ መካከለኛ / 0.353 ነው።

ሞዴል ስድስት፣ ሰባትና ስምንት ደግሞ ንዑሳን (ዐውዳዊ) ተንባይ ተላውጦዎች ከአምስቱ ዐቢይ ተላውጦዎች ጋር በአንድነት ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ምን ያህል የልይይት መጠን እንደተጋሩ የሚያሳዩ ናቸው። በእነዚህ ሦስት ሞዴሎች (ሞዴል 6፣7 እና 8) እንደተገለፀው እነዚህ ሦስት ተንባይ ተላውጦዎች ማለትም መምህራን በተማሪዎች የመማር ዝንባሌ፣ የቋንቋ ችሎታና በተማሪ-ክፍል ጥምርታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ በጋራ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ /በጥገኛ ተላውጦው ላይ

ያሳደሩት ተፅዕኖ የሕብረ ተዛምዶ መጠን 0.038፣ ሲሆን የተጋርቶ መጠኑ (R^2) ደግሞ 0.049 ወይም 5% ነው። የሦስቱ ሞዴሎች (ሞዴል 6፣ 7 እና 8) ምጥን የተጋረቶ መጠንም (የእያንዳንዳቸው) እንደቀዳሚዎቹ ሁሉ መካከለኛ ነው።

ሞዴል ስምንት አምስቱ ዐቢይና ሦስቱ ንዑሳን ተንባይ ተላውጦዎች በአንድነት በጥገኛ ተላውጦው ላይ ያሳደሩት ተፅዕኖ የተገለፀበት ክፍል ነው። በዚሁ ሰንጠረዥ ሞዴል ስምንት እንደተገለፀው የስምንቱ ተንባይ ተላውጦዎች የህብረ ተዛምዶ መጠን 0.663 ሲሆን የተጋርቶ መጠኑ (R^2) ደግሞ 0.440 ነው። ስምንቱ ተንባይ ተላውጦዎች በጋራ ከጥገኛ ተላውጦው ጋር 44% የልይይት መጠን ይጋራሉ ማለት ነው።

ይህም መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው እውቅያ፣ ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ፣ የትምህርት ደረጃቸው፣ በስራ ላይ ስልጠና ያላቸው ተሳትፎ፣ በተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታና የተማሪ-ክፍል ጥምርታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ 44% ያህል መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ላዳበሩት ግንዛቤ (perceptions) በጣምራ ጫና እንዳሳደሩ ወይም ለወሸባክ መከሰት ምክንያት እንደሆኑ የሚያሳይ ነው። ተላውጦች ለወሸባክ መከሰት ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ የሚያሳይ ውጤት ነው። ቀሪው 56% ደግሞ በጥናቱ ያልተካተቱ ሌሎች ተላውጦዎች ተፅዕኖ ውጤት ነው ማለት ነው። የዚህ ሞዴል ምጥን የተጋርቶ መጠንም መካከለኛ /0.382 ነው።

በአጠቃላይ የሞዴሎቹ የተስማሚነት (Fitness) ደረጃ ሲታይም ከሞዴል አንድ በስተቀር የቀሩት ሰባት ሞዴሎች መካከለኛ የሚባል የስምምነት ደረጃ እንዳላቸው ምጥን የተጋርቶ መጠናቸው ውጤት አሳይቷል።

ሌላው የዚህ ተዋረዳዊ ህብረ-ድህረት ዘዴ ውጤት መሰረታዊ ክፍል እያንዳንዱ ተንባይ ተላውጦ በተናጠል በጥገኛ ተላውጦው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ የሚቀርብበት የ R ካሬ ለውጥ (R square change) የሚለው ነው። በዚህ ክፍል ስምንቱ ነፃ ተላውጦዎች በተናጠል ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳሳደሩ በግልፅ ተለይቶ ቀርቧል።

በዚሁ መሰረት ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው 0.287 ወይም 29% አስተዋፅኦ በማበርከት በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ ነው፡፡ መምህራን ስለፈተናው ያላቸው እውቅና እና ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ ደግሞ በጥገኛ ተላውጦው ላይ እያንዳንዳቸው አራት አራት ፐርሰንት ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡ የመምህራን የትምህርት ደረጃ፣ መምህራን በተማሪዎች የመማር ዝንባሌና የቋንቋ ችሎታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ደግሞ በተናጠል ሁለት፣ ሁለት ፐርሰንት በጥገኛ ተላውጦው (መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ) ላይ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡ የቀሩት ሁለቱ ተላውጦዎች (የመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎና መምህራን በተማሪ-ክፍል ጥምርታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ) አንድ አንድ ፐርሰንት በጥገኛ ተላውጦው ባህሪ ላይ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ናቸው፡፡

4.4.5.2 በእያንዳንዱ ነጻ ተላውጦ የተገለጸው የጥገኛ ተላውጦው ልዩነት ትንተናና ማብራሪያ

ሰንጠረዥ 4.21፣ የድህረት ውጤት ማጠቃለያ ሞዴል መደበኛ ድህረት (Regression Output: Model Summary (Standard Regression)

Model	R	R Square	Adjusted R Square	Std. Error of the Estimate	Change Statistics				
					R Square Change	F Change	df1	df2	Sig. F Change
1	.780[a]	.608	.404	8.87521	.608	2.975	12	23	.012

ሀ. ተንባዮች / Predictors: (Constant),፣ (መምህራን ለሙያቸ ያላቸው ከበሬታ፣ ሥለፈተናው ያላቸው ዕውቂያ ፣ የፈተናው ጠቀሜታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለተማሪዎች የመማር ዝንባሌና የቋንቋ ችሎታ ያላቸው ግንዛቤ፣ ፣ውጫዊ ጫናዎች ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣, በተመደበው ክፍለ ጊዜ መጠን ላይ ያላቸው ግንዛቤ ፣ የማስተማር ልምድ ,፣የተማሪ-ክፍል ጥምርታ፣, የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፏቸው.፣ የትምህርት ደረጃቸው (Qualification)፡፡

ሁለተኛው በህብረ ድኅረት ትንተና የሚመለስ የምርምር ጥያቄ (3.6) **"በእያንዳንዱ ነጻ ተላውጦ ሊገለጽ የሚችለው የጥገኛ ተላውጦው ልዩነት ምን ያህል ነው?"** የሚለው ነው፡፡ ይህን የምርምር ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችለው የህብረ-ድኅረት ዘዴ መደበኛ (standard /simultaneous) የሚባለው ነው፡፡ በብዙ የጥናት መስኮች

የሚዘወተርና ሰፊ ተቀባይነት ያገኘ የህብረ-ድኅረት ዘዴ ነው (Larson-Hall 2010, Meyers et al., 2005፣ Muijs 2004)። ሞዴሉ እንደ ተዋረዳዊ ዘዴ ተንባይ ተላውጠዎች በቅደም ተከተል ሳይሆን በአንድ ጊዜ አንድ ላይ ገብተው በጥገኛ ተላውጠው ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ የሚፈተሽበት ዘዴ ነው። በዚህ ዘዴ፣ ሞዴሉ፣ እያንዳንዱ ተላውጠ ያበረከተው አስተዋፅኦ ሳይሆን በጋራ ያበረከቱት ተፅዕኖ የሚገለጽበት ነው። የእያንዳንዱን ነጻ ተላውጠ አስተዋጽኦ የሚያሳየው የመደበኛ ድህረታዊ መጣኙ (standard regression coefficient_Beta) ውጤት ነው። ወደ መደበኛ ድህረታዊ መጣኙ/ ቤታ ውጤት ከመሻገራችን በፊት ግን ሞዴሉ የሚያሳየውን ውጤት በአጭሩም ቢሆን መመልከት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር ይህን መደበኛ፣ የሚባለውን የህብረ-ድኅረት ዘዴ በመጠቀም ስምንቱ ነፃ (ተንባይ) ተላውጠዎች በጥገኛ ተላውጠው ላይ ያሳደሩት ተፅዕኖ ተፈትሿል። ሰንጠረዥ 4.21 እንደሚያሳየውም ውጤቱ የህብረ ተዛምዶው መጠን (R)፣ የተጋርቶ መጠኑ ((R^2) 0.440 (44%)፣ ምጥን የተጋርቶ መጠኑ (adjusted R square) ደግሞ 0.382 ነው። እንዲሁም የጉልህነት ደረጃው (P value) ከ0.001 በታች (P < 001) ሆኖ ተገኝቷል። በአጠቃላይ 44% የሚሆነው የእነዚህ በጥናቱ የተካተቱት ተንባይ ተላውጠዎች ተጽዕኖ ውጤት ነው ማለት ነው። ይህም በመደበኛ የህብረ ድኅረት ዘዴ የተገኘው የምጥን ተጋርቶ መጠን በተዋረዳዊ ዘዴ ሞዴሎች ከተገኘው የምጥን ተጋርቶ መጠን ድምር ጋር የሚመሳሰል እንደሆነ የሚያመለክት ነው። ምክንያቱም በዚህኛውም የተገኘው የምጥን ተጋርቶ መጠን መካከለኛ በሚባል ደረጃ ከጥናቱ አካላይ ጋር የሚስማማ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

በዚህ መደበኛ በሚባለው የህብረ ድኅረት ዘዴ የእያንዳንዱን ነፃ ተላውጠ የጥንካሬ ደረጃ (strength /effect size) የሚያሳየው መደበኛ ድህረታዊ መጣኝ (standard regression coefficient) ወይም ቤታ/β ነው። በህብረ ድኅረት ትንተና የቤታ (የመደበኛ ድህረታዊ መጣኝ) ክብደት/ የጥንካሬ ደረጃ የሚተረጎመውም እንደኛ ከ0-0.1 ደካማ ውጤት፣ ሁለተኛ ከ 0.1-0.3 መጠነኛ ፣ ሦስተኛ ከ0.3 -0.5 መካከለኛ እና አራተኛ >0.5 ጠንካራ በመባል ነው (Muijs 2004)።

ሰንጠረዥ4.22፣ የመደበኛ ድህረታዊ መጣኝ (standard regression coefficient_Beta) ውጤት

ሞዴል/Model		Unstandardized Coefficients	Standardized Coefficients			Collinearity Statistics	
		B	Beta	t	Sig.	Tolerance	VIF
1	(Constant)	1.379		3.411	.001		
	የትምህርት ደረጃ	-.071	-.113	-1.251	.215	.879	1.138
	መምህራን ስለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ	.233	.302	2.645	.010	.552	1.810
	መምህራን ስለፈተናው ያላቸው ዕውቅና	.138	.195	2.112	.038	.841	1.189
	መምህራን ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ	.184	.246	2.350	.021	.656	1.525
	መምህራን ስለ ስራ ላይ ስልጠና ተሳትፏቸው ያላቸው ግንዛቤ	-.095	-.082	-.902	.370	.870	1.149
	መምህራን ስለተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ያላቸው ግንዛቤ	.126	.166	1.685	.096	.743	1.346
	መምህራን ስለተማሪዎች ችሎታ ያላቸው አመለካከት	-.071	-.150	-1.702	.093	.926	1.079
	የተማራክፍል ጥምርታ)	.057	.114	1.302	.197	.934	1.070

ሀ. ጥገኛ ተላውጣ/ (Dependent Variable :) መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ያላቸው ግንዛቤ

በመደበኛ የህብረ-ድህረት ዘዴ የተገኘው የቤታ ውጤት ከዚህ አንጻር ሲታይ አንደኛ የትምህርት ደረጃ (β=-113፤ P>0.05)፣ ሁለተኛ መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ (β=0.303፣ P < 0.01)፤ ሦስተኛ መምህራን ስለፈተናው ያላቸው እውቅና (β= 0.195፣ P < 0.05) ፣ አራተኛ መምህራን ስለፈተናው ጠቀሜታ

ያላቸው ግንዛቤ (β = 0.246፤ P < 0.05)፣ አምስተኛ መምህራን የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ላይ ያላቸው ግንዛቤ (β=0.166፣ P>0.05)፣ ስድስተኛ መምህራን የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ የሚፈጥረው ጫና ላይ ያላቸው ግንዛቤ (β= -0.150 P>0.05) እና ሰባተኛ የተማሪ-ክፍል ጥምርታ (β=0.114 P>0.05) የመደበኛ ድህረታዊ መጣኝ ክብደት/ የጥንካሬ ደረጃ መጠነኛ የሚባል ሆኖ ተግኝቷል፡፡ የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፏቸው ብቻ ደካማ የሚባል β=0.082፣ P > 0.05) የጥንካሬ ደረጃ እንዳለው ሰንጠረዥ 4.22 ያሳያል፡፡ ይህም ተንባይ ተላውጠዎቹ በጥገኛ ተላውጠው ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ በጥንካሬ ደረጃ ሲታይ አንደኛው፣ መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው አመለካከት፣ ሁለተኛው፣ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው ጠቀሜታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ሦስተኛው፣ መምህራን ስለፈተናው ያላቸው እውቅና፣ አራተኛው መምህራን የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በማስተማር ተግባራቸው ላይ ስለሚያሳድረው ጫና ያላቸው ግንዛቤ፣ አምስተኛው፣ መምህራን የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ የሚፈጥረው ጫና ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ መሆናቸውን፣ እንዲሁም የተማሪ-ክፍል ጥምርታ፣ የትምህርት ደረጃና የመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ ተፅዕኖ በስድስተኛ፣ በሰባተኛና በስምንተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ፣ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ካላቸው ግንዛቤ/ ከጥገኛው ተላውጠው ጋር ያላቸው ግንኙነት አቅጣጫም ከስምንቱ የአምስቱ አዎንታዊ፣ የሦስቱ አሉታዊ እንደሆነ በሰንጠረዥ 4.22 የቀረበው የመደበኛ ድህረታዊ መጣኝ ውጤት ያመለክታል፡፡ ከዚህም ስምንቱ ተንባይ (ነፃ) ተላውጠዎች በጥገኛ ተላውጠው ላይ የሚያሳድሩት የተፅዕኖ ጥንካሬ ደረጃ የተለያየ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የመደበኛ ድህረታዊ መጣኙ የጉልህነት ደረጃም ሰንጠረዡ እንደሚያሳየው ከስምንቱ ተንባይ ተላውጠዎች ጉልህ (P<0.05) ሆነው የተገኙት የመጀመሪያዎቹን ሦስት ደረጃዎች ናቸው፡፡ ሌሎቹ ከጥገኛ ተላውጠው ጋር ያላቸው ግንኙነት ጉልህ (significance) አይደለም ወይም ከ0.05 (P> 0.05) በላይ ነው፡፡

ARABA UNIV
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ARBA MINCH

4.5 ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ትንተናና ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ሌላው መሰረታዊ ጥያቄ "የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር መማር ሂደቶች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ተማሪዎች ያላቸው ግንዛቤ ምንድነው ?" የሚል ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎች ያላቸውን ግንዛቤ ማጥናት አንዱ የጥናቱ ዓላማ ነው፡፡ ለዚህም ዓላማ መረጃ በጽሑፍ መጠይቅ ከተማሪዎች ተሰብስቧል፡፡ በመሆኑም ይህ ክፍል በተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰው መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ የቀረበበት ነው፡፡ መረጃው የተሰበሰበው በአማራ ክልል በ2005 ዓ.ም የ10ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ተፈታኝ ከነበሩ ተማሪዎች ሲሆን የማጠናቀቂያ ፈተናውን ከመፈተናቸው አንድ ወር በፊት መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በጥናቱ ዘዴ ክፍል እንደተብራራው መረጃው ከተማሪዎች የተሰበሰበው በጥናቱ በተካተቱ ትምህርት ቤቶች በእድል ሰጭ ንሞና ዘዴ በተመረጡት የ10ኛ ክፍል ክፍሎች/ ሴክሽኖች ተመድበው ከሚማሩ ተማሪዎች ነው፡፡

የማጠናቀቂያ ፈተናው በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በተመለከተ የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማጥናት የተዘጋጀው ይህ የጽሑፍ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የተማሪዎችን ዳራ የሚመለከቱ ሁለት ጥያቄዎች እንዲሁም የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራቸውና በተማሪዎች ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጠው የሚጠይቁ ሁለት ዐውዳዊ ጥያቄች የተካተቱበት ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሦስት ምድቦችና በየምድቦቹ ስር የተለያዩ ጥያቄዎች የተካተቱበት ሲሆን ምድብ አንድ ተማሪዎች ሰለማስተማሪያና መማሪያ ተግባሮች ያላቸውን ግንዛቤ፣ ምድብ ሁለት ስለመማር ገጽታዎች (Aspects of Learing) ያላቸውን አመለካከት ለማጥናት የሚያስችሉ ንዑሳን ምድቦችና ጥያቄዎች የተካተቱባቸው ናቸው፡፡ የመጨረሻውና ሦስተኛው ምድብ ደግሞ ተማሪዎች ስለፈተናና በየዓመቱ ስለሚሰጠው የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ገጽታዎች ያላቸውን አመለካከት ለማጥናት የሚያስችሉ ሁለት ንዑሳን ምድቦችና 12 ጥያቄዎች የተካተቱበት ክፍል ነው፡፡ ጥያቄዎቹም በሊከርት ስኬል፣ መሠረት የቀረቡ ናቸው፡፡

4.5.1 የጥናቱ ተሳታፊዎች ዳራና የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራንና በተማሪዎች ስለሚሰጠው ትኩረት ያላቸው ግንዛቤ

ሀ.መጠይቅ በመሙላት የተሳተፉ ተማሪዎች ጸታና ዕድሜ

በምዕራፍ ሦስት በተገለጸው መሰረት ከስምንቱ ትምህርት ቤቶች 440 ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በመሙላት እንዲሳተፉ ተደርጎ 303ቱ (69%) መጠይቆችን በትክክል ሞልተው መልሰዋል። ከእነዚህ ውስጥ 148 (48.8%) ወንድ፣ 154 (50.8%) ሴት ናቸው። አንድ ተሳታፊ ጸታውን/ዋን አልገለጸም/ጸችም። መጠይቅ በመሙላት የተሳተፉት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች (88.8%) ዕድሜ ከ14-18 ዓመት ባለው ክልል ውስጥ የሚገኝ ነው። ይህም ተሳታፊዎቹ ከገጠር፣ ከከፊል ከተማና ከከተማ ትምህርት ቤቶች የተወከሉ መሆናቸው በዕድሜ ረገድ ልዩነት እንደሌለ የሚያሳይ ነው።

ለ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራንና በተማሪዎች የሚሰጠው ትኩረት ላይ የተማሪዎች ግንዛቤ

ሰንጠረዥ 4.23፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመማር-ማስተማር ሂደቶች ስለሚሰጠው ትኩረት የተማሪዎች ግንዛቤ

ተላውጠ	ምንም ጊዜ አያነሱም	መቶኛ	አልፎ አልፎ	መቶኛ	አንዳንድ ጊዜ	መቶኛ	በአብዛኛው ክፍለ ጊዜ	መቶኛ	በየክፍለጊዜው	መቶኛ
3. አማርኛ ቋንቋ ስትማሩ፣ መምህራችሁ የ10ኛ ክፍልን የአማርኛ ሀገር አቀፍ የማጠናቀቂያ ፈተና በተመለከተ ምን ያህል ጊዜ ያነሳሉ?	32	10.6	103	34.0	76	25.1	47	15.5	44	14.5
4 ያለፉ ዓመታት የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ለመስራት ምን ያህል ጊዜ ታውላላችሁ?	38	12.5	86	28.4	90	29.7	76	25.1	12	4.0

በዚህ ክፍል ተሳታፊዎች የማጠናቀቂያ ፈተናው በክፍል ምን ያህል እንደሚወሳና እነሱ ራሳቸው የፈtናውን ጥያቄዎች ለመስራት ምን ያህል ጊዜ እንደሚያውሉ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲገልጹ ተጠይቀው ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራቸው በክፍል ውስጥ ምን ያህል ጊዜ እንደሚነሳ ለተጠየቁት ጥያቄ አብዛኞቹ 179ኙ (59%) ተሳታፊዎች ፈተናው በመምህራኑ አልፎ አልፎ / አንዳንድ ጊዜ በክፍል ውስጥ እንደሚነሳ ሲገልጹ 15..5% በአብዛኛው ክፍለ ጊዜ፣ 14.5% ደግሞ በየክፍለ ጊዜው ይነሳል የሚሉትን አማራጮች መርጠዋል፡፡ 10.6% ምንም ጊዜ ስለፈተናው አያወሱም የሚለውን አማራጭ መርጠዋል፡፡ ይህም አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ይነስም ይብዛ የማጠናቀቂያ ፈተናው በሚማሩበት ዐውድ በአብዛኞቹ መምህራን የክፍል ትምህርት አቀራረብ ላይ ይወሳል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በክፍል ትምህርቱ የሚወሳ ከሆነ ደግሞ በመማር ማስተማር ሂደቶቹ ላይ ተጽዕኖ ሊሳድር እንደሚችል የሚጠቁም/ ፍንጭ የሚሰጥ ነው፡፡

ያለፉ ዓመታት የአማርኛ ማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ጥያቄዎች ለመስራት የሚያውሉት ጊዜ ካለ ምን ያህል እንደሆነ እንዲገልጹ ለተጠየቁት ጥያቄም አብዛኞቹ (58%) እንደቀዳሚው ሁሉ አልፎ አልፎ / አንዳንድ ጊዜ የሚሉትን መርጠዋል፡፡ ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽእኖ የሚያሳድረው በመምህራን ላይ ብቻ ሳይሆን በተማሪዎችም ላይ ጭምር እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡

በጥቅሉ ሲታይ የጥናቱ ተሳታፊዎች የማጠናቀቂያ ፈተናው በቋንቋው ትምህርት ሂደት በመምህራንም ሆነ በተማሪዎች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ትኩረት ይሰጠዋል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው ከላይ የቀረበው ማስረጃ ያሳያል፡፡ ስለፈተናው ተጽዕኖ ያላቸው ዝርዝር አተያይ /አመለካከት ደግሞ ወደኋላ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

4.5.2 ተማሪዎች ስለማስተማሪያና መማሪያ ተግባራት፣ ቋንቋውን ስለሚማሩባቸው እና ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ገጽታዎች (Aspects) ያላቸው ግንዛቤ

4.5.2.1 ተማሪዎች ስለማስተማሪያና መማሪያ ተግባራት (Classroom Teaching & Learning Activities) ያላቸው አመለካከት

ይህ ክፍል የተዘጋጀው ተማሪዎች መምህሮቻቸው ቋንቋውን ለማስተማር፣ እነሱ ለመማር በክፍልና ከክፍል ውጭ ስለሚጠቀሙባቸው የማስተማሪያና የመማሪያ ተግባራት ያላቸውን አመለካከት መሠረት በማድረግ የማጠናቀቂያ ፈተናው በእነዚህ ክፍሎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ (ካለ) ለመመርመር ነው። በጽሑፍ መጠይቁ በዚህ ክፍል ስድስት ንዑሳን ምድቦችና 39 ጥያቄዎች ተካተዋል። የትንተናው ውጤትና ማብራሪያም ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሀ. ተማሪዎች ለቋንቋው ማስተማሪያ ተግባራት ያላቸው አመለካከት

ተማሪዎች ስለመምህሩ የክፍል ውስጥ ንግግር ያላቸው ግንዛቤ

ይህ ምድብ ከተማሪዎች አመለካከት አንጻር የአማርኛ መምህራን በክፍል ውስጥ ምን ያህል እንደሚናገሩ ለመመርመር የሚያስችሉ ጥያቄዎችን የያዘ ነው። ይህም የማስተማሪያ መንገዳቸው ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ግንኙነት ያለው መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ያግዛል።

ሰንጠረዥ 4.24፣ ተማሪዎች ስለመምህሩ የክፍል ውስጥ ንግግር መጠን ያላቸው ግንዛቤ በመቶኛ ስሌት

ተላውጠዎች	በጭራሽ	መቶኛ	አልፎ አልፎ	መቶኛ	ብዙ ጊዜ	መቶኛ	በጣም ብዙ ጊዜ	መቶኛ
5.1 ለክፍሉ ተማሪ መናገር (talk to the Whole /Class)	9	3.0	98	32.3	115	38.0	78	25.7
5.2 ለየቡድኑ መናገር (talk to groups)	39	12.9	135	44.6	81	26.7	44	14.5
5.3 ለእያንዳንዱ ተማሪ መናገር (talk to individuals)	94	31.0	131	43.2	47	15.5	27	8.9
5.4 አለመናገር/ዝም ማለት (Keep Silent)	114	37.6	86	28.4	53	17.5	42	13.9

በዚሁ መሰረት በክፍል ውስጥ መምህሮቻቸው የሚናገሩበትን መጠን እንዲገልፁ ለተጠየቁት ጥያቄ በሰንጠረዥ 4.24 እንደሚታየው አብዛኞቹ ተሳታፊዎች (63.7%) መምህሮቻቸው ብዙ ጊዜና በጣም ብዙ ጊዜ በክፍል ውስጥ እንደሚናገሩ ገልጸዋል፡፡ ‹‹**አለመናገር**›› ለሚለው አማራጭ 37.6% **በጭራሽ ዝም አይሉምና** 28% **አልፎ አልፎ ዝም ይላሉ** ብለው መመለሳቸው ራሱ 68.6% የሚሆኑት ተሳታፊዎች በቋንቋው ትምህርት በክፍል ውስጥ ብዙ የሚናገሩት ተማሪዎች ሳይሆኑ መምህራኑ ናቸው ብለው እንደሚያምኑ የሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡ በመምህራኑ መጠይቅና በምልከታ ከተሰበሰበው መረጃ ትንተና ውጤት ጋር የሚዛመድ ግኝት ነው፡፡ ይህም የትምህርቱ አቀራረብ ከዘመናዊ ትምህርት ፍልስፍና፣ ከትምህርት ፖሊሲው ማስፈጸሚያ ማዕቀፍና ከተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርትና ከቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ጋር የሚጣላ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ይዘቶችን በተወሰነ ጊዜ ሸፍኖ ተማሪዎችን በምርጫ ለሚዘጋጅ/ ለሚቀርብ ፈተና ለማዘጋት የሚረዳ የአቀራረብ ስልት እንደሆነ ደግሞ ክርክር የሚያስነሳ አይደለም፡፡

ተማሪዎች ስለመምህራቸው የማስተማሪያ ተግባራት ያላቸው ግንዛቤ

በዚህ ምድብ ስር የተካተቱ ጥያቄዎች ደግሞ ተማሪዎች መምህሮቻቸው ቋንቋውን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸውን ተግባሮች በተመለከት ያላቸውን ግንዛቤ/ አመለካከት ለማወቅ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በሰንጠረዥ 4.25 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየውም በጥናቱ ከተሳተፉት ተማሪዎች መካከል 68% መምህሮቻቸው ብዙ ጊዜና በጣም ብዙ ጊዜ የትምህርቱን ዓላማ ለክፍሉ ተማሪ ያስተዋውቃሉ የሚል ግንዛቤ ሲኖራቸው 21.5% ደግሞ ለዚሁ ጥያቄ አልፎ አልፎ የሚለውን አማራጭ በመምረጥ መምህራኑ የትምህርቱን ዓላማ ማስተዋወቅን እንደ አንድ መሰረታዊ ተግባር እንደሚያከናውኑት አንጸባርቀዋል፡፡ ከማስተማር መርሆዎች አንዱ ዓላማን ማስተዋወቅ ቢሆንም በምልከታ የተገኘው መረጃ ግን የተባለውን አያንጸባርቅም፡ አብዛኞቹ ዓላማ ሲያስተዋውቁ አይስተዋሉም፡፡

ሰንጠረዥ 4.25፣ የክፍል ውስጥ የመምህሩ ተግባራትን በተመለከተ የተማሪዎች ግንዛቤ በመቶኛ ስሌት

ተላውጠዎች	በጭራሽ	መቶኛ	አልፎ አልፎ	መቶኛ	ብዙ ጊዜ	መቶኛ	በጣም ብዙ ጊዜ	መቶኛ
6.1 የትምህርቱን ዓላማ /ዓላማዎች ለተማሪዎች መንገር/ማስተዋወቅ፡፡	29	9.6	65	21.5	96	31.7	111	36.6
6.2 የምንባቡን ይዘት ማብራራት	18	5.9	55	18.2	112	37.0	113	37.3
6.3 የተለየ ቋንቋ ነክ ጉዳይ ሲያጋጥም (ለምሳሌ የቃላት ወይም የዐረፍተነገሮች አወቃቀር) ማብራራት	15	5.0	53	17.5	111	36.6	121	39.9
6.4 የመማሪያ መጽሐፉን መልመጃዎች አሰራር ማብራራት	17	5.6	52	17.2	86	28.4	140	46.2
6.5. ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን አሰራር ማብራራት	102	33.7	115	38.0	49	16.2	33	10.9
6.6 የቡድን ሰራ ወይም ውይይት ማደራጀት	31	10.2	100	33.0	97	32.0	67	22.1
6.7 የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት የምንማርባቸውን ተግባራት ማደራጀት	78	25.7	103	34.0	88	29.0	30	9.9
6.8 በተማሪዎች ፅሁፍ (ዐ.ነገር፣ አንቀፅ፣ ድርሰት...) የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ነጥብ በነጥብ ማብራራት	81	26.7	108	35.6	65	21.5	44	14.5

በሰንጠረዥ 4.25 በተራ ቁጥር 6.2፣ 6.3 እና 6.4 የተጠቀሱትን ተግባራት ደግሞ በአብዛኛዎቹ መላሾች በመምህራኑ ብዙ ጊዜና በጣም ብዙ ጊዜ የሚተገበሩ ናቸው ተብለው ተገልጸዋል፡፡ የቀሩትን ተግባራት በሚመለከት አብዛኛዎቹ መላሾች በጭራሽ የማይተገበሩና አልፎ አልፎ የሚተገበሩ የሚሉትን አማራጮች በመምረጥ የሚሰጣቸው ትኩረት አነስተኛ ወይም የማይተገበሩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ለ.ተማሪዎች ቋንቋውን ስለሚማሩባቸው ተግባሮች ያላቸው ግንዛቤ/አመለካከት

ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩባቸው ተግባሮች

ይህ ምድብ ተማሪዎች ቋንቋውን በሚማሩባቸው ተግባሮች ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያሳድረው ተጽዕኖ መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ የሚያስችል ነው፡

ሰንጠረዥ 4.26፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለሚማሯቸው የትምህርቱ ክፍሎች/ ተግባሮች ያላቸው ግንዛቤ በመቶኛ ስሌት

ተላውጠዎች	በጭራሽ	መቶኛ	አልፎ አልፎ	መቶኛ	ብዙ ጊዜ	መቶኛ	በጣም ብዙ ጊዜ	መቶኛ
7.1 የንባብ ክሂል	21	6.9	94	31.0	74	24.4	108	35.6
7.2 የጽሕፈት ክሂል	13	4.3	51	16.8	88	29.0	146	48.2
7.3 የመናገር ክሂል	12	4.0	56	18.5	92	30.4	135	44.6
7.4 የማዳመጥ ክሂል	9	3.0	38	12.5	65	21.5	186	61.4
7.5 ሰዋስው	28	9.2	82	27.1	103	34.0	86	28.4
7.6 ሥነ-ጽሑፍ	49	16.2	105	34.7	79	26.1	68	22.4

ተማሪዎቹ በዚህ ክፍል ከቀረቡላቸው ክሂሎችና የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች ውስጥ ብዙ ጊዜና በጣም ብዙ ጊዜ የሚማሯቸው/ የሚያከናወኗቸው እንደሆኑ አድርገው የገለጹት ድምር መሰረት ሲደረግ በክፍል ውስጥ በአንደኛ ደረጃ ልምምድ እናደርጋለን ብለው አብዛኛዎቹ (75%) የሚያምኑት የማዳመጥን ተግባር ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የመጻፍ ክሂል ነው (61.5%):: በ59.6% በቅርብ ርቀት የመጻፍ ክሂልን የሚከተለው የመናገር ክሂል ነው:: በሌላ ክፍል እንደተገለፀው ደግሞ መምህራኑ ተማሪዎቻቸው በቋንቋው ትምህርት ይበልጥ መማር የሚፈልጉት የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶችን ነው የሚል ግንዛቤ አላቸው:: የሚቀርበው ትምህርትም በዚህ አስተሳሰብ የተቃኘ ነው:: በዚህኛው መጠይቅ በተማሪዎች ምላሽ የተገኘው ውጤት ግን የዚህ ተቃራኒ ነው:: ብዙዎቹ መላሾች በመምህራን፣ በተማሪዎች የሚፈለጉ/ ትኩረት የሚሰጣቸው ትምህርቶች ናቸው፣ እየተባሉ የሚጠቀሱትን የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች ልምምድ እናደርግባቸዋለን ብለው የሚያስቡት ከክሂሎቹ በአነሰ ደረጃ ነው:: በክፍል ምልከታ የተስተዋለው እውነታ ግን መምህራኑ ያሉት ነው::

በተለይ የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶችን በተመለከተ ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ ከመምህራኑ ግንዛቤ ጋር የሚጣረስ የሆነው ለምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ አንስተን

ምክንያቶችን ለመገመት/ ለመመርመር ስንሞክር ምናልባትም አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለው በትምህርቱ ሂደት የተሻለ/ የበለጠ ጊዜ እንዲሰጣቸው የሚፈልጓቸው ትምህርቶች ስለሆኑ ሳይሆን አይቀርም የሚለው ነው። ከዚህ በመነሳት ለነዚህ ትኩረት ሰጥተው መማር ለሚፈልጓቸው ትምህርቶች በተሰጣቸው ጊዜ ስላልረኩ ሁለቱን የትምህርት ክፍሎች በተመለከተ የሚያደርጓቸው ልምምዶች በቂ አይደሉም ብለው ከማሰብ የሰጡት ሃሳብ እንደሆነ መገመት ይቻላል። በሌላ አገላለጽ በመምህራኑ እንደተወሳው ምናልባት በክሂሎች የሚያደርጉትን ውስን ልምምድ እንደ በቂ ጊዜ፣ የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶችን በተመለከተ የሚያደርጓቸውን /የሚያከናውኗቸውን ልምምዶች ደግሞ ብዙ ጊዜና ብዙ ልምምድ እንደሚያስፈልጋቸው ከማመን የመነጨ ሀሳብ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶቹ መላሾች ደግሞ የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች ውስጥ የሚካተቱት ይዘቶች ምን ምን እንደሆኑ ካለማወቅ/ ካለመለየት የሰጡት ምላሽ ይመስላል። ምክንያቱም በዚህኛው ክፍል አብዛኞቹ ተሳታፊዎች የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶችን ጭራሽ አንማርም ወይም አልፎ አልፎ የምናከናውናቸው ተግባሮች ናቸው ብለው፣ በሌላ ክፍል የቀረቡትን ዝርዝር የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ይዘቶችን በሚመለከት የሰጡት መልስ ደግሞ (ለምሳሌ ስለ ሐረግ አይነቶች፣ ስለ ሥነ-ጽሑፍ አይነቶችና የልብወለድ አላባውያን...ወዘተ) ብዙ ጊዜ ወይም በጣም ብዙ ጊዜ እንደሚማሯቸው የሚያንጸባርቅ/የሚያሳይ ነው።

በአንደኛ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት የምንማረው የማዳመጥ ክሂልን ነው፤ ያሉት ምላሽ የሚያንፀባርቀውም በትክክል ራሱን የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚያከናውኑትን ልምምድ ሳይሆን በመምህሮቻቸው ገለፃና ማብራሪያ የሚቀርቡላቸውን የሰዋስውና የሥነ-ጸሐፍ ይዘቶች እንዲሁም ስለእያንዳንዱ ክሂል የሚማሯቸውን የጽንሰ ሀሳብ ትምህርቶች (ለምሳሌ የአንቀጽ ምንነትና ባህርያት፣ የድርሰት አይነቶች፣ የውይይት /ክርክር መመሪያ...) የሚከታተሉባቸውን ሰዓታት ብዛት እንደሆነ ከመምህራን ጋር ከተካሄዱት የቡድን ውይይቶችና ከክፍል ምልከታዎች ከተገኘው መረጃ ጋር በማገናዘብ መረዳት/መገመት ይቻላል።

ተማሪዎች ቋንቋውን በክፍል ውስጥ ስለሚማሯቸው ንዑሳን የትምህርቱ ክፍሎች/ ተግባሮች ያላቸው ግንዛቤ

በአራቱ መሠረታዊ ክሂሎችና በሰዋስውና በሥነጽሑፍ ትምህርቶች ስር ከሚካተቱት ንዑሳን ክሂሎችና የዕውቀት ክፍሎች መካከል በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ መርሐ ትምህርቶች ሦስት ወይም ከሦስት በላይ ክፍለ ጊዜ የተመደበላቸውን ትምህርቶች በሚመለከት በመማር ማስተማሩ ሂደት ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጣቸው/ እንደሚተገበሩ ተማሪዎች ያላቸውን ግንዛቤ እንዲገለጹም ተጠይቀዋል፡፡ በአባሪ 17 የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያሳየውም በየክሂሎቹ እና በሰዋስውና በሥነጽሑፍ ትምህርቶች ስር ለተካተቱት ለነዚህ ትምህርቶች የጥናቱ ተሳታፊዎች ብዙ ጊዜና በጣም ብዙ ጊዜ የምንማራቸው ናቸው ብለው የመለሱት አማካይ ሲደመር ሰዋስው በ75% አንደኛ ደረጃ ላይ ሲገኝ ሥነጽሑፍ በ64.5% በሁለተኛነት ይከተላል፡፡ በ64% ሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ደግሞ የንባብ ክሂል ነው፡፡ የመጻፍ ክሂል በ41.6% በአራተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የማዳመጥና የመናገር ክሂል በጋራ በ23% በስድስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ለሁለቱ በጋራ የተሰጠው ውጤት ለሁለት ቢካፈል ለእያንዳንዳቸው 11.5 %፤ 11.5 % ይደርሳቸዋል እንደማለት ነው፡፡ ከዚህም በጥናቱ የተሳተፉት ተማሪዎች እነዚህ በመርሐ ትምህርቶቹ በማዳመጥና በመናገር ንዑሳን ክሂልነት የተካተቱትና በእነዚህ መሳሪያዎች ሦስትና ከሦስት ክፍለ ጊዜ በላይ የተመደበላቸው ውይይት፣ ክርክር፣ የዱብዳ ንግግር፣ የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር እና በተወሰነ ርዕስ ንግግር ማድረግ የሚሉት ትምህርቶች በክፍል ትምህርቱ ትኩረት የማይሰጣቸው ናቸው የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው እንረዳለን፡፡ እነዚህ የተማሪዎችን የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር በመርሐ ትምህርቶቹና በመማሪያ መጽሐፎቹ የተካተቱ ክፍሎች በማጠናቀቂያ ፈተናው በቀጥታ የማይመዘኑ መሆናቸው ደግሞ ግልጽ ነው፡፡

በፈተና የማይካተቱ ይዘቶች/ ክፍሎች ደግሞ በትምህርቱ ችላ ሊባሉ ይችላሉ (Alderson 2004፣ Howkey 2006)፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለዚህኛው ክፍል ተማሪዎቹ የሰጡት መልስ ቀደም ሲል በጥቅሉ (ስለክሂሎችና ስለ ሁለቱ የዕውቀት ዘርፍ ስለሚባሉት) ለተጠየቁት ጥያቄ ከሰጡት መልስ ጋር የሚጣረስ ነው፡፡ ከቀዳሚው

መልስ ጋር የሚጣረስ ይሁን እንጅ በሌላ በኩል ደግሞ አንደኛ በየክሂሉ እና በሰዋስውና በሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች ስር የሚካተቱትን ንዑሳን ይዘቶች ማስታወስ ባለመቻላው ሊሆን ይችላል፤ ሁለተኛ በመምህሮቻቸው የሚቀርብላቸውን ገለጻና ማብራሪያ የሚከታተሉበትን ሂደት ሁሉ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አድርገው በማሰብ የሰጡት መልስ ሳይሆን አይቀርም፤ የተባሉትን ግምቶች/ መላምቶች ትክክልነት በግልጽ የሚያሳይ ምላሽ ነው።።

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቋንቋውን ለመማር የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች /የሚያደርጓቸው ልምምዶች

ሰንጠረዥ 4.28፣ ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩባቸው ተግባሮች በመቶኛ ስሌት

ተላውጠዎች	በጭራሽ	መቶኛ	አልፎ አልፎ	መቶኛ	ብዙ ጊዜ	መቶኛ	በጣም ብዙ ጊዜ	መቶኛ
8.1 የጥንድ ሥራ መስራት፣	30	9.9	141	46.5	91	30.0	38	12.5
8.2 የቡድን ውይይት ማካሄድ፣	26	8.6	113	37.3	102	33.7	53	17.5
8.3 የራስን ሀሳብ በቃል ወይም በጽሑፍ መግለፅ ፣	28	9.2	111	36.6	100	33.0	63	20.8
8.4 ጥያቄ መጠየቅ፣	18	5.9	90	29.7	97	32.0	92	30.4
8.5 ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን መሥራት፣	104	34.3	83	27.4	83	27.4	83	27.4

በሰንጠረዥ 4.28 የቀረበው ውጤት እንደሚያሳየው፣ የቋንቋውን ክሂሎች፣ ሰዋስውና ሥነ-ጽሑፍን ለመማር የሚያከናውኗቸውን ተግባራት እንዲገልጹ ለተጠየቁት ተሳታፊዎቹ የሰጡት መልስ የሚያመለክተው አሳታፊ የሚባሉትንና በተለይም በተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት ከፍ ያለ ተቀባይነት ያላቸውን በጥንድ መስራትና በቡድን ውይይት ማካሄድ የሚሉትን በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባሮች እንደሆኑ ገልጸዋል።። ይሁን እንጂ፣ በተራ ቁጥር ስምንት ስር ከተዘረዘሩት አምስት ተግባራት አንጻር ሲታዩ ግን ብዙ ጊዜና በጣም ብዙ ጊዜ በመከናወን የቡድን

ውይይት በ51% በአራተኛ ደረጃ፤ የጥንድ ስራ መስራት በ42.5% በአምስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ በ62% በመወከል አንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ጥያቄ መጠየቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው (54.9%) ዋነኛ ተግባር ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን ጥያቄዎች መስራት ነው፡፡ ሦስተኛው ሀሳብን መግለጽ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ 56% በጥንድ፣ 45.9% በቡድን የተለያዩ ተግባራትን በጭራሽ እንደማያከናውኑ ወይም አልፎ አልፎ ብቻ እንደሚያከናውኑ ገልጸዋል፡፡ ይህም በተማሪዎች እነዚህ ሁለት አሳታፊ የተግባቦታዊ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች/ ስልቶች (Spada እና ሌሎች 1985) በመማር-ማስተማሩ ሂደቶች የተለየ ትኩረት አይሰጣቸውም ተብሎ እንደሚታመን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ፣ ከተማሪዎች ግንዛቤም በዘመናችን ዘመናዊ የትምህርት ፍልስፍናም ሆነ የመማር ትወራዎች (Stern 1983) እንዲሁም በተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አተያይ ተደጋፊ የሆኑት የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ላቅ ያለ ትኩረት እንደማያገኙ መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎችን ለፈተና ከማዘጋጀት ባለፈ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር በማገዝ ረገድ ይኸ ነው የሚባል ሚና እንዳለው የማይታወቀው ያለፉ ዓመታት ፈተና ጥያቄዎችን የመሥራት ተግባር ትኩረት በማግኘት በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ይህም የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ ከማዳበር የበለጠ ተማሪዎቹን ለፈተና የማዘጋጀቱ ተግባር የተሻለ ትኩረት እንደተሰጠው የሚጠቁም ነው፡፡ በክፍል ምልከታዎች የተስተዋለው ትምህርቱን በአብዛኛው በመምህራኑ ገለፃ የማቅረብ ሂደትና ተማሪ አሳታፊ የሚባሉ የትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን ችላ ማለትም የተማሪዎቹን ሀሳብ የሚያጠናክር/ የሚደግፍ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም የፈተናዎች ድርጅት ሀላፊ እንደገለጹት በሌሎች ሀገሮች እንደሚታየው ሁሉ በጥናቱም ዐውድ ውጫዊ/ ብሔራዊ ፈተናዎች በተለይም የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተናዎች የቋንቋው ትምህርት አሰጣጥ ላይ የቱን ያህል ጫና እየፈጠሩ እንደሆነ በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡

ከክፍል ውጪ የቋንቋ ችሎታቸውን የሚያሻሽሉባቸው ተግባሮች

ሰንጠረዥ 4.29፣ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳባር የሚያግዟቸው ከክፍል ውጭ የሚያከናውኗቸው ተግባራት

ተላውጠዎች	በጭራሽ	በመቶኛ ስሌት	አልፎ አልፎ	በመቶኛ ስሌት	ብዙ ጊዜ	በመቶኛ ስሌት	በጣም ብዙ ጊዜ	በመቶኛ ስሌት
10.1 ራዲዮ ማዳመጥ	94	31.0	111	36.6	50	16.5	38	12.5
.10.2 ቴሌቪዥን መመልከት	77	25.4	94	31.0	69	22.8	52	17.2
10.3 ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ማንበብ	93	30.7	114	37.6	52	17.2	31	10.2
10.4 ለፎኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና የሚያግዙ አጋዥ መጽሐፎችን ማንበብ	30	9.9	91	30.0	93	30.7	82	27.1
10.5 ያለፉ ዓመታት ፈተና ወረቀቶችን ለብቻና ከጓደኛ ጋር መሥራት	26	8.6	88	29.0	91	30.0	81	26.7

የጥናቱ ተሳታፊዎች ከክፍል ውጭ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያስችሉ የሬዲዮና የቴሌቪዥን መርሐ ግብሮችን ይከታተሉ፣ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን፣ እንዲሁም ለማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያግዟቸውን መጽሐፎችን ያነቡ እንደሆነና ያለፉ ዓመታት የፈተና ጥያቄዎችን እየሰሩ ይለማመዱ እንደሆነ ለተጠየቁት አብዛኛዎቹ (67.6%) "ብዙ ጊዜ" ወይም "በጣም ብዙ ጊዜ" ራዲዮ እንደማያዳምጡ፣ 56% የቴሌቪዥን መርሐ ግብሮችን እንደማይከታተሉ፣ 68% ጋዜጦችንና መጽሔቶችን እንደማያነቡ ገልጸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ 57.8% የሚሆኑት መላሾች ለፎኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና የሚያግዙ መጽሐፎችን "ብዙ ጊዜ" እና "በጣም ብዙ" ጊዜ እንደሚያነቡ፣ እንዲሁም 56.7% የሚሆኑት ተሳታፊዎች ለፈተና ራሳቸውን ለማዘጋጀት ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን እየሠሩ ለመለማመድ "ብዙ ጊዜ"ና "በጣም ብዙ ጊዜ" እንደሚያውሉ ገልፀዋል። ይህም ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያግዙ ተግባራትን እንደማያከናውኑ የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን

የዘመኑ ተማሪ ለፈተና የሚማር ነው ያሉትን አንዳንድ መምህራን ሀሳብ የሚያንጸባርቅም ይመስላል።

ይህን ክፍል ለማጠቃለል ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ብዙ የሚናገረው መምህሩ ነው ብለው ያምናሉ። ከመምህሮቻቸው የማስተማሪያ ተግባራት ትኩረት በማግኘት አንደኛው የተለየ ቋንቋ-ነክ ጉዳይ ሲያጋጥም (ለምሳሌ የቃላት ወይም የዐረፍተ ነገሮችን አወቃቀር) ማብራራት ሲሆን ሁለተኛው የምንባቦችንን ይዘት ማብራራት፣ ሦስተኛው ደግሞ የመማሪያ መጽሐፉን መልመጃዎች አሠራር ማብራራት ነው። ተማሪዎች ቋንቋውን በክፍል ውስጥ የሚማሩባቸውን ተግባራት በሚመለከትም በጥቅሉ ክሂሎችንና የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶችን በሚመለከት ለተጠየቁት በትምህርቱ ሂደት ትኩረት በማግኘት አንደኛው የማዳመጥ ክሂል፣ ሁለተኛው የመጻፍ ክሂል ሦስተኛው የመናገር ክሂል ነው፤ ብለው ቢመልሱም በእያንዳንዱ ዐቢይ ክሂል ስር የየተዘረዘሩትን ንዑሳን ክሂሎች ምን ያህል ጊዜ እንደሚማሯቸው እንዲገልጹ ለተጠየቁት ሌላ ጥያቄ የሰጡት መልስ ግን ለቀዳሚው ጥያቄ የሰጡትን መልስ የሚያፈርስ ነው። በመምህራኑ መጠይቅ፣ ከመምህራን ጋር በተካሄዱት ቡድን ተኮር ውይይቶችና በክፍል ምልከታዎች የተገኙት መረጃዎች ውጤት ትንተናዎች የሚያንጸባርቁትም ይኸኛውን /ሁለተኛውን ግኝት ነው። ቀደም ብሎ እንደተወሳው ለቀዳሚው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የተለየ የሆነው በማዳመጥ ክሂልና ገለጻን በማዳመጥ መማር መካከል ያለውን ልዩነት ባለመረዳታቸውና በእያንዳንዱ ክሂል/ የዕውቀት ዘርፍ ስር የሚካተቱትን ንዑሳን ትምህርቶች ማስታወስ ባለመቻላቸው እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል። በተለይም በምድብ 11 ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች በእያንዳንዱ ዐቢይ ክሂልና የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ይዘቶች ስር ለቀረቡት ንዑሳን ትምህርቶች የሰጡት ምላሽ ይህን በግልጽ አንጸባርቋል። በዚሁ መሰረት በእያንዳንዱ ዐቢይ ትምህርት ስር ለተካተቱት ንዑሳን ትምህርቶች ተማሪዎች የሰጡት መልስ ተደምሮ ለብዛታቸው ሲካፈል ብዙ ጊዜና በጣም ብዙ ጊዜ ትኩረት በማግኘት በ75..75% በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የሰዋስው ትምህርት ነው። ሁለተኛው የሥነ-ጽሁፍ፣ ሦስተኛው የንባብ ክሂል ትምህርት ነው። ከመምህራን ጋር በተካሄዱት የቡድን ውይይቶችና በምልከታ ከታየው የትምህርት አቀራረብ ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ የተገኘውም ይኸኛው ምላሽ ነው።

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቋንቋውን ለመማር የሚያደርጓቸውን የልምምድ መጠን ከአምስት ተግባራት አንጻር ደረጃ እንዲሰጡ የተጠየቁትን ጥያቄ በተመለከተ ደግሞ ብዙ ጊዜና በጣም ብዙ ጊዜ የሚሉትን አማራጮች የመለሱት ውጤት መቶኛ ስሌት ሲደመር አንደኛው ጥያቄ መጠየቅ የሚለው ነው፣ ሁለተኛው ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን ጥያቄዎች መስራት፣ ሦስተኛው ሀሳብን (በቃል ወይም በጽሑፍ) መግለጽ የሚሉት ናቸው።።

ባጠቃላይ በዚህ ክፍል ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ የሰጡት መልስ የማጠናቀቂያ ፈተናው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመማር-ማስተማር ሂደቶች ላይ በተለይም በትምህርቱ ይዘት፣ በማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና ለተግባራት በሚሰጣቸው ትኩረት ላይ ተጽዕኖ ያደርሳል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው።።

4.5.2.2 ተማሪዎች በመማር ገጽታዎች ላይ ያላቸው ግንዛቤ (Perceptions of Aspects of Learning)

ይኸኛው የመጠይቁ ክፍል በሊከርት የስምምነት ስኬል መሰረት የቀረበ ነው።። የተገኘው ውጤት የተተነተነውም በመቶኛ ስሌት(በፐርሰንት) ሳይሆን በአማካይና የአማካዩን ደረጃ በመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በተገለፁት አራት የጥንካሬ ደረጃ አመልካች ስያሜዎች (የማይለካ፣ ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ጠንካራ በሚሉት) በመግለጽ ነው።። በዚህኛው ክፍል የተካተቱት ጭብጦች አራት ሲሆኑ በአራቱ ስር 22 ጥያቄዎች ተጠይቀዋል።። ተማሪዎቹ ለእነዚህ 22 ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾችም ከዚህ በታች ተተንትነውና ተብራርተው ቀርበዋል።።

ሀ.ተሳታፊዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት

በዚህ ክፍል ስር ከቀረቡት አምስት ጥያቄዎች መካከል የቡድን ውይይት ማካሄድን ከሚመለከተው 12.3 በስተቀር ለቀሩት አራት ጥያቄዎች ተሳታፊዎቹ የሰጠት መልስ በአማካይ ደረጃ ጠንካራ ሆኖ ተገኝቷል።።

ሰንጠረዥ 4.30፣ ተሳታፊዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ /አተያይ

ተላውጠዎች	ብዛት/ N	አማካይ /Mean	መደደበኛ ልይይት.	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ /Item Effect
12. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ስታወዳድሩት እንዴት አገኛችሁት?				
12.1 ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ይልቅ ህይወታዊ ነው (ዘገባ፣ ደብዳቤ፣ ቃለጉባኤ፣... አጻጻፍን አዳምጠና አንብቦ መረዳት፣ ሀሳብን አሳክቶ መግለፅን የምንማርበት ነው) ።	300	3.6600	1.15854	ጠንካራ
12.2 የቋንቋው ትምህርት ተግባሮችን /መልመጃዎችን ሳቢ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።	299	3.5819	1.07557	ጠንካራ
12.3 አያሌ የቡድን ውይይቶችን የምናካሂድበት ትምህርት ነው።	289	3.190	1.1939	መካከለኛ
12.4 ከመምህራችንና ከክፍል ጓደኞቻችን ጋር ለመግባባት የተሻለ እድል የምናገኝበት ነው።	297	3.7811	1.17516	ጠንካራ
12.5 ትምህርታችንን ጨርሰን፣ በሥራ ዓለም ስንሰማራ ልናከናውናቸው ከምንችላቸው ተግባራት ጋር የሚዛመድ ነው።	298	3.6107	1.17615	ጠንካራ

ከዚህም በጥናቱ የተሳተፉት ተማሪዎች ጠንካራ በሚባል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንደኛ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ይልቅ ሕይወታዊ ነው፤ ሁለተኛ፣ ተግባሮቹ /መልመጃዎቹ ሳቢ ናቸው፤ ሦስተኛ፣ ከመምህሮቻቸውና ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ለመግባባት የተሻለ እድል የሚያገኙበት ነው፤ አራተኛ፣ ትምህርታቸውን ሲጨርሱና በሥራ ዓለም ሲሰማሩ ሊያከናውኗቸው ከሚችሏቸው ተግባራት ጋር ዝምድና ያላቸው ናቸው ብለው እንደሚያምኑ መገንዘብ ይቻላል።

ለ. ቋንቋውን ለመማር ባላቸው መነሳሳት (Motivation) ላይ የተማሪዎች ግንዛቤ

በዚህ ምድብ (ጭብጥ) ስር ሰባት ጥያቄዎች የተካተቱ ሲሆን ለሁሉም ጥያቄዎች ተሳታፊዎቹ የሰጡት ምላሽ አማካይ "ጠንካራ" በሚለው ምድብ ውስጥ የሚገኝ ነው። ይህም የተጋነነ ቢመስልም አብዛኛዎቹ መላሾች ቋንቋውን መማራቸው በተጠቀሱት ጉዳዮች ለስኬት ለመብቃት ያስችለናል ብለው እንደሚያምኑ ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 4.31፣ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ያላቸው መነሳሳት

ተላውጠዎች	ብዛት/ N	አማካይ /Mean	መደደበኛ ልይይት .	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ (/Item Effect)
13.1 ስለቋንቋ መሰረታዊ ባህርያትና የአወቃቀር ስርዓት ለመማር	300	3.9100	1.07350	ጠንካራ
13.2 ከትምህርት በኃላ የተሻለ ስራ ለማግኘትና በስራ ቦተ (ሪፖርት፣ ቃለጉባኤ፣ የስራ ደብዳቤ በመፃፍ፤ በማዳመጥና በመናገር... ክሂሎች) ውጤታማ ሆኖ ለመገኘት	299	4.0234	1.09427	ጠንካራ
13.3 በማህበራዊ ህይወት ንቁ ተሳታፊ ለመሆን፣	295	3.7729	1.20625	ጠንካራ
13.4 ወደ መሰናዶ ትምህርት ለማለፍ፣	293	3.8396	1.22957	ጠንካራ
13.5 ፈተና ለማለፍ	292	3.7842	1.26465	ጠንካራ
13.6 የትምህርት ቤቱን፣ የቤተሰብንና የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት፣	292	3.6781	1.13025	ጠንካራ
13.7 የአማርኛ ፊልሞችን፣ ድራማዎችን እንዲሁም የተለያዩ የሬዲዮና የቴሌቪዥን መርሀ ግብሮችን የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣	293	3.5154	1.26759	ጠንካራ

ሐ. የቋንቋ ችሎታቸውን ለማሻሻል የሚመርጧቸው የመማሪያ ስትራቴጂዎች

በዚህ ምድብ ስር ስድስት ጥያቄዎች ተካተዋል። ተማሪዎቹ ለነዚህ ጥያቄዎች ከሰጡት ምላሽ አማካያቸው "መካከለኛ" የሆነው ለ14.4 (በትምህርት ቤቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ክበባት /ድራማ፣ ክርክር ወዘተ.) መሳተፍ) እና 14.6 (የመማሪያ መጽሐፉን በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ይዞ መገኘት ለሚሉት) የሰጧቸው መልሶች ብቻ ናቸው። ለሌሎቹ አራት ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ በሙሉ "ጠንካራ" በሚባለው ምድብ ውስጥ የሚገኝ ነው። ይህም ተሳታፊዎቹ ቋንቋውን ለመማር እነዚህ አራት ስልቶች "ጠንካራ" በሚባል ደረጃ ተመራጭ ናቸው ብለው እንደሚያምኑ ያሳያል።

ሰንጠረዥ 4.32፣ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር የሚመርጧቸው ስልቶች/ስትራቴጂዎች

ተላውጠዎች	ብዛት /N	አማካይ /Mean	መደበኛ ልይይት	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
14.1 በክፍል የቡድን ስራዎች ሲሰጡ በንቃት መሳተፍ	294	3.8741	1.06182	ጠንካራ
14.2 በክፍል ውስጥ ሀሳብን ለክፍሉ መግለፅ	293	3.7645	1.13589	ጠንካራ
14.3 መልመጃዎችንና ሌሎች የቤት ስራዎችን በወቅቱ መስራት	291	3.7904	1.15402	ጠንካራ
4.4 በትምህርት ቤቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ክበባት (ድራማ፣ ክርክር...) መሳተፍ	290	3.3379	1.32174	መካከለኛ
.14.5 ለሰዋሰው ትምህርት የተለየ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል፣	293	3.7816	1.17336	ጠንካራ
14.6 የመማርያ መጽሐፉን በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ይዞ መገኘት	292	3.7603	1.20597	መካከለኛ

ይህን የመማር ገጽታዎች፣ የሚለውን ክፍል ለማጠቃለል የጥናቱ ተሳታፊዎች “ጠንካራ” በሚባል ደረጃ ለቋንቋው ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው፣ በትምህርቱም ስለቋንቋው መሰረታዊ ባህርያትና የአወቃቀር ሥርዓት/ ሰዋስው በተሻለ ደረጃ እንደሚማሩ፣ እንዲሁም የቋንቋው ትምህርት በማህበራዊ ሕይወታቸው ንቁ ተሳታፊ ለመሆንና ፈተና ለማለፍ (ወደ መሰናዶ ትምህርት ለመሸጋጋር) ይረዳናል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል። ቋንቋውን ለመማር የሚመርጧቸው የመማሪያ ስትራቴጂዎችም የቡድን ስራ ሲሰጥ በንቃት መሳተፍ፣ ሀሳብን መግለጽ፣ የቤት ሥራዎችን በወቅቱ መሥራትና ለሰዋስው ትምህርት የተለየ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል የሚሉት እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

4.5.2.3 ተማሪዎች ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ገጽታዎች (Aspects) ያላቸው አመለካከት

የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ሁለተኛ ክፍል ምድብ 9 እና ሦስተኛው ክፍል ምድብ 15 ስር የተካተቱት 12 ጥያቄዎች፣ ፈተና ነክ ስለሆኑ ጉዳዮች ተማሪዎች ያላቸውን አስተሳሰብ ለመመርመር የሚያግዙ መረጃዎችን ለማግኘት የተጠየቁ ናቸው። የመጀመሪያው በሊከርት የድግግሞሽ፣ ሁለተኛው በስምምነት ስኬል መሰረት የቀረቡ ናቸው። ቀጥሎ ተማሪዎቹ በሁለቱ ምድቦች ስር ለቀረቡት (መጀመሪያ በሊከርት

የድግግሞሽ ስኪል፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በስምምነት ስኬል እንዲመልሱ ለተጠየቁት) ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ የትንተና ውጤትና ማብራሪያ ይቀርባል፡፡

ሀ. ለፈተና ለመዘጋጀት የሚያከናውኗቸው ተግባራት

ሰንጠረዥ 4.33፣ ለፈተና ለመዘጋጀት የሚያደርጉት ልምምድ በመቶኛ ስሌት

ተላውጦዎች	በጭራሽ	መቶኛ	አልፎ አልፎ	መቶኛ	ብዙ ጊዜ	መቶኛ	በጣም ብዙ ጊዜ	መቶኛ
9.1 የንባብ ክሂል	22	7.3	59	19.5	94	31.0	128	42.2
9.2 የጽሕፈት ክሂል	16	5.3	74	24.4	96	31.7	110	36.3
9.3 የመናገር ክሂል	18	5.9	77	25.4	98	32.3	102	33.7
9.4 የማዳመጥ ክሂል	15	5.0	46	15.2	75	24.8	164	54.1
9.5 ሰዋስው	33	10.9	95	31.4	82	27.1	86	28.4
9.6 ሥነ-ጽሑፍ	55	18.2	99	32.7	69	22.8	62	20.5

ቀደም ብሎ ቋንቋውን ለመማር በእያንዳንዱ ክሂልና የዕውቀት ዘርፍ ምን ያህል ልምምድ እንደሚያካሂዱ/ እንደሚያከናውኑ እንደተጠየቁት ሁሉ እነዚህኑ የቋንቋው ክሂሎችና የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ክፍል ትምህርቶች በሚመለከት ራሳቸውን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ዝግጁ ለማድረግ ምን ያህል ጊዜ ልምምድ እንደሚያደርጉ እንዲገለጹ ተጠይቀውም ነበር፡፡ በሰንጠረዥ 4.33 እንደተመለከተው በዚሁ ምድብ ስር ለተካተቱት ስድስት ጥያቄዎች ተሳታፊዎቹ መልስ ሲሰጡ የማዳመጥ ክሂልን 78.9%፣ የንባብ ክሂልን 73%፣ የመጻፍ ክሂልን 68%፣ የመናገር ክሂልን 66%፣ የሰዋስው ትምህርትን 55.5% እና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርትን 43% የሚሆኑት መላሾች “ብዙ ጊዜ” እና “በጣም ብዙ ጊዜ” ልምምድ እናደርጋለን ብለዋል፡፡ በዚህኛውም ምላሽ የማዳመጥ ክሂል ከፍተኛ ትኩረት እንደሚያገኝ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጅ የማዳመጥ ክሂል በማጠናቀቂያ ፈተናው ስለሚካተት ከማዳመጥ ክሂል ጋር የተያይዙ ጥያቄዎችን ለመመለስ በክሂሉ በተጠቀሰው ደረጃ ልምምድ እንደሚያደርጉ እየገለፀ ነው ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ይልቁኑ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ከተሰበሰቡት መረጃዎችና ቀደም ብሎ አብዛኛውን ጊዜ የምንማረው የመምህራንን ንግግር

በማዳመጥ ነው ካሉት ጋር በማገናዘብ በመምህሮቻችን በክፍል ውስጥ በገለጻ የሚቀርብልንን ትምህርት እያዳመጥን ለፈተናው ራሳችንን እናዘጋጃለን እያሉ መሆናቸውን ነው መረዳት የሚቻለው።

ለ. በፈተና-ነክ ጉዳዮች ላይ የተማሪዎች ግንዛቤ

ሰንጠረዥ 4.34፣ በፈተና ነክ ጉዳዮች ላይ የተማሪዎች ግንዛቤ

ተላውጠዎች	ብዛት /N	አማካይ /Mean	መደደበኛ ልይይት.	የጥያቄው የመለካት ጥንካሬ ደረጃ
15.1 ተማሪዎች ፈተና ይጠላሉ፤	303	2.7822	1.35884	መካከለኛ
15.2 የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን በመስራት ይሻሻላል፣	292	3.6438	1.19126	ጠንካራ
15.3 ፈተና መፈተን(መውሰድ) በጣም ጠቃሚ የመማር ልምድ (የመማሪያ ስልት ነው።።	298	3.9329	1.17874	ጠንካራ
15.4 የፈተናዎች መኖር ተማሪዎች ጠንክረው እንዲያጠኑ ያደርጋል፣	294	4.1259	1.06503	ጠንካራ
15.5 ፈተናዎች ተማሪዎች ስለራሳቸው በሚኖራቸው ግንዛቤ (self - image) ላይ ጠቃሚ አስተዋፅኦ አላቸው፣	303	3.9637	1.07746	ጠንካራ
15.6 በፈተና የሚገኝ ውጤት ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆን ለመደሰት ወይም ለመከፋት ምክንያት ይሆናል።።	302	3.6093	1.33182	ጠንካራ

በሰንጠረዥ 4.34 እንደተመለከተው በዚህ ምድብ ፈተናን የሚመለከቱ ስድስት ጥያቄዎች ተካተዋል። ከእነዚህ ጥያቄዎች መካከል ተሳታፊዎቹ ለአምስቱ የሰጡት ምላሽ ደረጃ "ጠንካራ" ሆኖ ተገኝቷል። ለእነዚህ አምስት ጥያቄዎች መላሾች ከሰጡት ምላሽ መረዳት የተቻለውም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አንደኛ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን ጥያቄዎች በመሥራት የቋንቋ ችሎታን ማሻሻል ይቻላል ብለው እንደሚያምኑ፣ ሁለተኛ ፈተና ጠቃሚ የመማሪያ ስልት ነው ብለው እንደሚያስቡ፣ ሦስተኛ የፈተናዎች መኖር ተማሪዎችን ጠንክረው እንዲያጠኑ ያደርጋቸዋል ብለው እንደሚያምኑ፣ አራተኛ ፈተናዎች ተማሪዎች ስለራሳቸው በሚኖራቸው ግንዛቤ ላይ ጠቃሚ አስተዋፅኦ አላቸው ብለው እንደሚያስቡና አምስተኛ በፈተና ከፍተኛ ውጤት ማምጣት የሚያስደስት፣ ዝቅተኛ ውጤት ማምጣት ደግሞ በተቃራኒው የሚያስከፋ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው /ያላቸው መሆኑን ነው።

ከዚህ ከማጠናቀቂያ ፈተናው ገጽታዎች ጋር በተያያዘ የማጠናቀቂያ ፈተናው በተማሪዎች አመለካከት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ የሚመለከተውን ይህን ክፍል ለማጠቃለል ከሥነ-ሑፍ ትምህርት በስተቀር ሌሎቹን የቋንቋው ትምህርት ክፍሎች በሚመለከት አብዛኞቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች (ከ55% በላይ የሚሆኑት) "ብዙ ጊዜ" እና "በጣም ብዙ ጊዜ" ለፈተናው ለመዘጋጀት ልምምድ እናካሂዳለን የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል። ሌሎች ፈተና ነክ ጉዳዮችን በሚመለከተው ምድብ ስር ለቀረቡት ጥያቄች መልስ ሲሰጡም እንዲሁ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች "ጠንካራ" በሚባል ደረጃ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን በመስራት የቋንቋ ችሎታን ማሻሻል ይቻላል ብለው እንደሚያምኑ፣ ፈተና ጠቃሚ የቋንቋ መማሪያ ስልት ነው ብለው እንደሚያስቡ፣ የፈተና መኖር ተማሪዎችን ጠንክረው እንዲያጠኑ ያደርጋል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው፣ የፈተና ውጤት ተማሪዎች እንዲደስቱ ወይም እንዲከፉ ያደርጋል ብለው እንደሚያምኑ ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ በዚህ የተማሪዎችን ግንዛቤ በሚለከተው ክፍል፣ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በቋንቋው ትምህርት ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመመርመር ተሞክሯል። ክፍሉ ሁለት ንዑሳን ክፍሎች ያሉት ሲሆን በንዑስ ክፍል እንድ ስለተማሪዎች ዳራና ተማሪዎች በሚማሩበት የትምህርት ቤት ዐውድ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራቸውና በራሳቸው በተማሪዎቹ ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጠው ለመመርመር ተሞክሯል። በምርመራውም በመረጃ ምንጭነት የተሳተፉት ተማሪዎች ከከተማ፣ ከከፊል ከተማና ከገጠር ትምህርት ቤቶች የተወከሉ ቢሆኑም በጸታ ስብጥር ተቀራራቢነት ያላቸው፣ በዕድሜ እንዲሁ ከሁሉም ቦታዎች የተሳተፉት አብዛኞቹ ከ14-18 ዓመት ባለው ክልል ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል። የማጠናቀቂያ ፈተናውም በአብዛኞቹ መምህራን አልፎ አልፎ ወይም አንዳንዴ በትምህርቱ ሂደት መሃል እንደሚነሳና እነሱም በተመሳሳይ ደረጃ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን ለመስራት የምናውለው ጊዜ አለ ብለው እንደሚያምኑ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

ሁለተኛው ክፍል ሦስት ዋና ዋና ምድቦች የተካተቱበት ሲሆን ምድብ አንድ ተማሪዎች ስለማስተማሪያና መማሪያ ተግባራት ያላቸውን ግንዛቤ፣ ክፍል ሁለት

ተማሪዎች ሰለመማር ያላቸውን አመለካከት፣ ክፍል ሦስት ተማሪዎች ስለአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና ያላቸውን አመለካከት የሚመለከቱ ጭብጦች የተካተቱባቸው ናቸው፡፡ በዚሁ መሠረት ተሳታፊዎቹ፣ በምድብ አንድ ስር የተካተቱትን ንዑሳን ጭብጦች በሚመለከት አንደኛ የየክፍለ ጊዜው አብዛኛው ሰዓት በመምህራኑ ንግግር ነው የሚያዘው የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ ሁለተኛ የመምህሮቻቸውን የማስተማሪያ ተግባራት በሚመለከት ቋንቋ/ ሰዋስው ነክ የሆኑ ትምህርቶችን ማብራራት ዋነኛው የማስተማሪያ ተግባር ነው ብለው ያምናሉ፤ የመማሪያ መጽሐፎቹን ምንባቦች ይዘት ማብራራትና የመልመጃዎችን አሰራር ማስረዳት ደግሞ በሁለተኛና በሦስተኛ ደረጃ የሚገኙ የመምህሮቻቸው የማስተማሪያ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው፤ የሚል አመለካከት እንዳላቸው የውጤት ትንተናው አመላክቷል፡፡ ሦስተኛ፣ ተሳታፊዎቹ የተማሪዎችን የመማሪያ ተግባራት በተመለከተ በትምህርቱ ሂደት ትኩረት በማግኘት አንደኛው ሰዋስው፣ ሁለተኛው ሥነ-ጽሑፍ፣ ሦስተኛው የንባብ ክሂል ናቸው የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ አራተኛ፣ በክፍል ውስጥ የሚያደርጓቸውን ልምምዶች በተመለከተ በተግባቦታዊ ትምህርት ሰፊ ተቀባይነት ካላቸው የጥንድና የቡድን ስራ ይልቅ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን ለመስራት የተሻለ ጊዜ ይሰጣል/ ይመደባል የሚል ዕምነት አላቸው፡፡ አምስተኛ ከክፍል ውጭ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር ይበልጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ተግባሮች ናቸው ብለው የሚያምኑት አንደኛ፣ ለ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና የሚያግዙ መጽሐፎችን ማንበብ፣ ሁለተኛ፣ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን እየሰሩ መለማመድ የሚሉትን ነው፡፡

የሁለተኛው ክፍል ምድብ ሁለት የመማር ገጸታዎችን የሚመለከቱ ጭብጦች የተካተቱበት ሲሆን የተገኘው ውጤት ያሳየውም ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ይልቅ ሕይወታዊ፣ መልመጃዎቹን ሳቢ ሆነው እንዳገኟቸው፣ ከመምህሮቻቸውና ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ለመግባባት የተሻለ እድል የሚያገኙበት የትምህርት ዓይነት እንደሆነ፣ ከወደፊት የስራ ዓለም ሕይወት ጋር የሚዛመድ ዕውቀት የሚያገኙበትና ወደቀጣዩ የትምህርት ደረጃ ለመዛወር የሚረዳቸው የትምህርት ዓይነት ሆኖ እንዳገኙት ነው፡፡

የክፍል ሁለት ሦስተኛውና የመጨረሻው ምድብ ተማሪዎች ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ያላቸውን ግንዛቤ የሚመለከት ነው። ይህን ምድብ በሚመለከት ደግሞ አንደኛ የጥናቱ ተሳታፊዎች ለፈተና ለመዘጋጀት በተለይ ለአራቱ ክሂሎችና ለሰዋስው ትምህርቶች የተሻለ ትኩረት በመስጠት ራሳችንን እናዘጋጃለን የሚል አመለካከት እንዳላቸው፤ ሁለተኛ ፈተናና ለፈተና የሚደረግ ዝግጅት ጠቃሚ የቋንቋ መማሪያ ስልት ነው ብለው እንደሚያምኑ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

ከዚህም የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና በቋንቋው ትምህርት ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እያሳደረ እንዳለና የተጽዕኖው ደረጃ ክፍተኛ እንደሆነ አቅጣጫውም በአብዛኛው አሉታዊ እንደሆነ መረዳት ተችሏል።

4.6 የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ

ይህ ክፍል የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምንድን ነው/ ናቸው? ለሚለው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ከተለያየ አቅጣጫ የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት ትንተና የሚቀርብበት ነው። በዚሁ መሰረት፣ መጀመሪያ ስለመምህራኑ የማስተማር ባህርያት፣ በመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ፣ ቀጥሎ የማስተማር-መማር ሂደቶችን በሚመለከት በተደራጀ የክፍል ምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች፣ ከዚያም ምልከታ ከተካሄደባቸው መምህራን ጋር ምልከታ በተካሄደባቸው ትምህርቶች ላይ ተመስረተው በተካሄዱ ከፊል-ነጻ-ቃለመጠይቆች የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት ትንተናና ማብራሪያ በቅደም ተከተል ይቀርባሉ። በመጨረሻው ክፍል ደግሞ በእነዚህ ዓይነታዊና መጠናዊ ዘዴዎች የተተነተኑት መረጃዎች ውጤት እየተቀናጀና እየተብራራ ይቀርባል።

4.6.1 የመምህራን የማስተማር ባሕርያትን (Behaviours) በሚመለከት በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በመምህራን መጠይቅ ክፍል ሁለት ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ዋና ዓላማ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ተግባር ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ ነው። በዚህ ክፍል ስር ሁለት ምድቦች (categories) የተካተቱ ሲሆን

በመጀመሪያው ምድብ ስር ሁለት ጥያቄዎች፣ በሁለተኛው ምድብ ስር ደግሞ ሦስት ንዑሳን ክፍሎችና በንዑሳን ክፍሎች ስር 20 ጥያቄዎች ተካተዋል። ለእነዚህ ጥያቄዎች ተሳታፊዎቹ የሰጡት ምላሽ ውጤት በዚህ ክፍል በገላጭ ስታቲስቲክስ (በተለይም በብዛት/ድግግሞሽና በመቶኛ) ተተንትኖና ተብራርቶ ቀርቧል።

ሀ. የክፍል ትምህርት አደረጃጀት

በሰንጠረዥ 4.35 የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የክፍል ትምህርት አደረጃጀትን በሚመለከት ለተጠየቀው ጥያቄ 70.8% የሚሆኑት የሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት የሚደራጀው የአማርኛ መምህራን በጋራ ተወያይተው በሚወስኑት መሰረት እንደሆነ ሲገልጹ፣ 24.7% ደግሞ እያንዳንዱ መምህር አዋጭ ነው ባለው መንገድ የትምህርቱን ይዘት እንደሚያደራጅ አመልክተዋል። ሁለቱም የትምህርት ማደራጃ ስልቶች ጎላፊነቱን ለሙያው ባለቤት ለመምህሩ የሚሰጡ ናቸው። ወይም ጣልቃ የሚገባባቸው ውጫዊ ሀይል እንደሌለ የሚያመለክቱ ናቸው። ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ላለው ለሁለተኛው ጥያቄ የሰጡት ምላሽም ከቀዳሚው ጋር ተቀራራቢነት ያለው ነው። ይኸውም 66.3% የመለሱት የሚያስተምሩትን ትምህርት ቅደም ተከተል የሚያሲይዙት (በራሳቸው ምርጫ ማለት ነው) በመማሪያ መጽሐፎቹ መሰረት ነው። 11.2% የሚሆኑት ደግሞ የሚያስተምሩትን ትምህርት የሚያደራጁት በቋንቋው ክሂሎች መሰረት ነው ሲሉ 18% በመልመጃዎቹ መሰረት ነው ብለዋል። 3.4% የሚያስተምሩትን ትምህርት ቅደም ተከተል የሚያሲይዙት (የሚያደራጁት) በማጠናቀቂያ ፈተናው መሰረት እንደሆነ ገልፀዋል።

ሰንጠረዥ 4.35፣ የክፍል ትምህርት ይዘት አደረጃጀት በቁጥርና በመቶኛ

ጥያቄ (Item)	ተላውጠዎቹ(variables	ብዛት/ ድግግሞሽ Frequency)	በመቶኛ (ስሌት
1. የትምህርቱን ይዘት አደረጃጀት የሚወስነው ማነው?	ሀ. ርዕሰ መምህሩ	2	2.2
	ለ. የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ	1	1.1
	ሐ. የአማርኛ መምህራን በጋራ	63	70.8
	መ .እርስዎ ራስዎ	22	24.7
	መልስ የሰጡት ድምር	88	98.9
	ያልመለሱ	1	1.1
	ጠቅላላ ድምር	89	100.0
2. በትምህርት ቤታችሁ የምታስተምሩትን ትምህርት ቅደም ተከተል የምታሲዙት /የምታደራጁት እንዴት ነው?	ሀ.በመማሪያ መጽሐፉ መሰረት	59	66.3
	ለ. በትምህርት ቤቱ አሰራር መሰረት	1	1.1
	ሐ. በቋንቋው ክሂሎች መሰረት ለምሳሌ የንባባ፣የማዳመጥ...እያሉ በተናጠል በማደራጀት	10	11.2
	መ.በቋንቋው ትምህርት ተግባሮች/ መልመጃዎች መሰረት	16	18.0
	ሠ. ማጠናቀቂያ ፈተናው ለየትምህርቶቹ በሚሰጠው ትኩረት መሰረት	3	3.4
	ጠቅላላ ድምር	89	100.0

ለ. የትምህርት አዘገጃጀት (Lessons Preparation)

በዚህ ክፍል መምህራኑ የትምህርት እቅድ ሲያዘጋጁ ትኩረት ሊሰጧቸው ይችላሉ የተባሉ ሰባት ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡ መጠይቅ በመሙላት የተሳተፉት እነዚህ መምህራን ለእያንዳንዱ ጉዳይ ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጡ እንዲገልፁም "በጭራሽ"፣ "አልፎ አልፎ"፣ "ብዙ ጊዜ"ና "በጣም ብዙ ጊዜ" የሚሉ አማራጮች ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሰንጠረዥ 4.36፣ *የትምህርት አዘገጃጀት (Lesson Preparation) በሚመለከት የመምህራን ምላሽ በቁጥርና በመቶኛ ስሌት*

ጥያቄ	ተላውጠዎች	በጭራሽ	መቶኛ	አልፎ አልፎ	መቶኛ	ብዙ ጊዜ	መቶኛ	በጣም ብዙ ጊዜ	መቶኛ
3. የትምህርት ዕቅድ ሲያዘጋጁ ለሚከተሉት ጉዳዮች ምን ያህል ትኩረት ይሰጣሉ?	ለማስተማሪያ ዘዴዎች	1	1.1	17	19.1	52	58.4	19	21.3
	ለትምህርት ይዘቶች					37	41.6	50	56.2
	በትምህርቱ ሂደት ለሚከናወኑ ተግባራት	1	1.1	8	9.0	46	51.7	33	37.1
	ለቋንቋ ክሂሎች (ለማዳመጥ ፣መናገር፣ ማንበብና መጻፍ)	2	2.2	51	57.3	31	34.8	4	4.5
	ለአጋዥ ማቴሪያሎች ጽሑፎች እና/ መጻሕፍት			28	31.5	40	44.9	21	23.6
	የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሳሳት			24	27.0	42	47.2	22	24.7
	ለተማሪዎች የቤት ስራ ለመስጠት	1	1.1	20	22.5	43	48.3	22	24.7

በሰንጠረዥ 4.36 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየውም አብዛኞቹ "ለቋንቋው ክሂሎችና ለአጋዥ መጻሕፍትና ሌሎች ጽሑፎች›› ከሚለው በስተቀር ለቀሩት አምስት ጥያቄዎች :ብዙ ጊዜ" እና "በጣም ብዙ ጊዜ" ብለው የመለሱት ምላሽ ሲደመርና በመቶኛ ሲሰላ ውጤታቸው ከ70% በላይ ነው፡፡ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጧቸው ክፍሎች በደረጃ ሲቀመጡም አንደኛው የትምርት ይዘት ነው፡፡ ለዚህ ክፍል "ብዙ ጊዜ" እና "በጣም ብዙ ጊዜ" የሚለውን የመለሱት ድምር በመቶኛ ስሌት ሲቀመር 97.8% ነው፡፡ በ88.8% በሁለተኛ ደረጃነት የሚከተለው በትምህርቱ ሂደት ለሚከናወኑ ተግባራት የሚሰጠው ትኩረት ነው፡፡ ሦስተኛው የማስተማሪያ ዘዴዎች (79.7%) ነው፡፡ በ73% በአራተኛ ደረጃነት የሚከተለው ደግሞ ለተማሪዎች የቤት ሥራ ለመስጠት የሚሰጠው ትኩረት ነው፡፡ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ማነሳሳት

በመቶኛ ሲሰላ በ71.9% በአምስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በ68.5% በስድስተኛነት የሚከተለው ደግሞ ለአጋዥ ማቴሪያሎች/ ጽሑፎች እና መጻሕፍት የሚሰጠው ትኩረት ነው፡፡ ሰባተኛውና የመጨረሻ ደረጃ ላይ የሚገኘው ደግሞ መምህራኑ ለቋንቋው ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት ነው፡፡ ለቋንቋው ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደረጉ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም በጥቅሉ ሲታይ ግን የትምህርት ፖሊሲውን፣ የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፉንና የቋንቋውን ሥርዓት ትምህርት የሚቃረን እንደሆነ የሚጠቁም ነው፡፡

ሐ. የመምህራን ንግግር (Teachers`Talk)

ሰንጠረዥ 4.37፣ የመምህሩ ንግግር በቁጥርና በመቶኛ

ጥያቄ	ተላውጠዎች	በጭ ራሽ	በመቶ ኛ ስሌት	አልፎ አልፎ	በመቶ ኛ ስሌት	ብዙ ጊዜ	በመቶ ኛ ስሌት	በጣም ብዙ ጊዜ	በመቶ ኛ ስሌት
4.ሲያስተምሩ የሚከተሉትን ድርጊቶች በክፍል ውስጥ ምን ያህል ይፈጽሟቸውል?	4.1.ለክፍሉ ተማሪ መናገር (talk to the Whole /Class)	1	1.1	34	38.2	38	42.7	16	18.0
	4.2. ለየቡድኑ መናገር (talk to groups)	3	3.4	39	43.8	36	40.4	10	11.2
	4.3.ለእያንዳንዱ ተማሪ መናገር (talk to individuals)	17	19.1	51	57.3	16	18.0	5	5.6
	4.4. አለመናገር /ዝም ማለት (Keep Silent)	73	82.0	12	13.5	1	1.1	1	1.1

የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት አንደኛው መገለጫ ተማሪዎች ብዙ የሚናገሩበት፣ የመምህሩ ንግግር ደግሞ ውስን የሚሆንበት መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የጥናቱ ተሳታፊዎች ሐሳባቸውን እንዲገልፁ ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ከተጠቀሰው የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት መርህ ጋር የሚጣረስ ነው፡፡ አብዛኞቹ (60.7%) "ብዙ ጊዜ" ወይም "በጣም ብዙ ጊዜ" ለክፍሉ ተማሪ እንደሚናገሩ ነው የገለፁት፡፡ በክፍል ምልከታ ከታየው እውነታ ጋር የሚዛመድ ምላሽ ቢሆንም መምህራኑ በመጠይቁ

ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ግን በክፍል ምልከታ ከተገኘው መረጃ ትንተና ውጤት ዝቅ ያለ ነው። በምልከታ የተገኘው (የተሳታፊዎች አደረጃጀት ትንተና እንዳሳየው) ከ90% በላይ የሚሆነው ጊዜ የሚያዘው በመምህራኑ ንግግር ነው። በእርግጥ አለመናገር (keep silent) ለሚለው አራተኛው አማራጭ "ብዙ ጊዜ"ና "በጣም ብዙ ጊዜ" ብለው የመለሱት 2.2% ብቻ መሆናቸው እና 82% "በጭራሽ ዝም አልልም" የሚለውን አማራጭ መምረጣቸው በተዘዋዋሪ መምህራኑ በክፍል ትምህርቱ ሂደት ዋነኛ ተናጋሪ መሆናቸውን የሚያጠናክር ነው። የዚህም አንዱ ምክንያት የፈተናው ተጽዕኖ እንደሆነ የሚያሳዩ ተጨማሪ በጥናቱ ሌሎች ክፍሎች የታዩ ምልክቶች አሉ። የፈተናው አጠያየቅ ራሱ በመማር-ማስተማር ሂደቱ የተማሪዎችን የነቃ ተሳትፎ የሚያበረታታ አለመሆኑ ራሱ የተባለውን ለማሰብ የሚያስችል ነው ።

መ. የመምህራኑ የማስተማሪያ ተግባራት (Teaching Activities)

ሰንጠረዥ 4.38፣ የመምህሩ የማስተማር ተግባራት በቁጥርና በመቶኛ ስሌት

ጥያቄ	ተላውጠዎች	በጭ ራሽ	በመቶኛ ስሌት	አልፎ አልፎ	መቶ ኛ	ብዙ ጊዜ	በመቶ ኛ ስሌት	በጣም ብዙ ጊዜ	በመቶ ኛ ስሌት
5.የሚከተሉትን ተግባራት በክፍል ውስጥ ምን ያህል ያከናውኗቸዋል?	5.1 የየዕለቱን ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች መናገር	7	7.9	27	30.3	36	40.4	18	20.2
	5.2 ተማሪዎች እያንዳንዱን ትምህርት /ተግባር እንዴት መስራት እንዳለባቸው ማሳየት	1	1.1	14	15.7	45	50.6	28	31.5
	5.3 የምንባቦችን ይዘት ማብራራት	5	5.6	22	24.7	42	47.2		
	5.4 የመማሪያ መጽሀፉን መልመጃዎች ማብራራት			21	23.6	45	50.6	23	25.8
	5.5 የቤት ስራዎችን አሰራር ማብራራት			20	22.5	42	47.2	26	29.2
	5.6 ያለፉ ዓመታትን የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ወደ ክፍል እያመጡ ማሰራትና ፈተና እንዴት እንደሚሰራ ማብራራት	7	7.9	50	56.2	25	28.1	6	6.7
	5.7 የቡድን ስራዎችን እየሰጡ ማሰራት ወይም ውይይቶችን ማደረጀት			29	32.6	42	47.2	18	20.2
	5.8 የቋንቋ ክሂሎችን አዋህዶ/ አቀናጅቶ ማስተማር	1	1.1	25	28.1	47	52.8	16	18.0

ያለፉ ዓመታትን የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎች ወደ ክፍል እያመጡ መስራትና ማሰራትን በሚመለከት ደግሞ 56.2% "አልፎ አልፎ"፣ 28.1% "ብዙ ጊዜ"፣ 6.7% ደግሞ "በጣም ብዙ ጊዜ" እንደሚያከናውኑ ገልጸዋል። ስለዚህ ደረጃው ቢለያይም ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን በክፍል ውስጥ መስራትና ማሰራት እንዲሁም የፈተና አሰራርን ማስተማር የመምህራኑ አንድ መደበኛ የማስተማር ተግባር ተደርጎ መወሰዱን የጥናቱ ግኝት ያሳያል። ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው በክፍል ትምህርቱ የመማር ማስተማር ሂደቶች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ እያደረሰ እንዳለ የሚያመለክት ነው።

በአጠቃላይ በዚህ የመምህራንን የክፍል ውስጥ የማስተማር ባህርያት ለሚመለከቱ ጥያቄዎች ተሳታፊዎቹ የሰጡት ምላሽ ውጤት ትንተና መምህራኑ ለተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት የሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል። ያለፉ ዓመታትን የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ መስራትና ማሰራት እንዲሁም የፈተና አሰራር ብልሃትን ማስተማርም በአብዛኛዎቹ መምህራን እንደ አንድ የመምህርነት ተግባር ተደርጎ እየታየ እንደሆነም የውጤት ትንተናው አመላክቷል።

4.6.2 በተደራጀ የክፍል ምልከታ (Structured Observation) የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በምዕራፍ ሦስት እንደተገለጸው፣ ምልከታው የተካሄደው ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር መገለጫ (COLT) የሚባለውን የምልከታ ንድፍና በGreen (2007) የታከሉትን ክፍሎች በመጠቀም ነው። ተጨማሪ መረጃዎችም በመስክ ማስታወሻና በቪዲዮ ተቀርፀው ተሰብስበዋል። በዚሁ መሰረት በአባሪ 11 እንደተመለከተው በምልከታው የተካተቱት ዋነኛ ምድቦች የተሳታፊዎች አደረጃጀት፣ የትምህርት ይዘት፣ የይዘት ቁጥጥር፣ የተማሪዎች የመማር ዘዴ፣ ፈተና መጥቀስና ማቴሪያሎች የሚሉት ናቸው። በተሳታፊዎች ሦስት፣ በይዘት አራት፣ በይዘት ቁጥጥር ሦስት፣ በመማር ዘዴ አምስት፣ በማቴሪያሎች ስር ሁለት ዐቢይ ክፍሎች ተካተዋል። በእነዚህ በምልከታ ቅፁ በተካተቱ ክፍሎችና በመስክ ማስታወሻና በቪዲዮ የተሰበሰበው መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ከዚህ በታች ቀርቧል።

ሀ. የተሳታፊዎች አደረጃጀት

በሰንጠረዥ 4.39 እና 4.40 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በዘጠነኛ ክፍል በሦስቱም ምድቦች (በከተማ፣ በከፊል ከተማና በገጠር) በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከፍተኛውን ድርሻ ማለትም ከ70% በላይ የሚሆነውን ጊዜ የያዘው *መምህር-ተማሪ/ ክፍል* በመባል የሚታወቀው አደረጃጀት ነው። ይህ የመማር ማስተማር ሂደት አደረጃጀት ደግሞ የቋንቋን ተግባቦታዊ ገፅታ በማስተማር እንቅፋትነት የሚታወቅ/ የሚገለፅ ነው። ኢአሳታፊ ወይም መምህር-ተኮር (Teacher-center) የሚባል የተሳታፊዎች አደረጃጀት ነው። በሌላ አገላለፅ በሰንጠረዦቹ የቀረበው የውጤት ትንተና በገጠርም ሆነ በከተማ እንዲሁም በከፊል ከተማ ትምህርት ቤቶች ተመራጭ ተደርጎ የተወሰደው ወይም የሚወሰደው የትምህርት አቀራረብ መምህሩ የሚናገሩበት፣ ተማሪው የመምህሩን/ሯን ንግግር (ገለፃ፣ ማብራሪያ፣ መመሪያ፣ ወዘተ.) የሚያዳምጥበት መንገድ እንደሆነ በግልፅ ያሳያል። ከሰንጠረዦቹ ማስተዋል እንደሚቻለው በመምህሩ/ሯ በንግግር የሚቀርበው ትምህርትም በጥንድ ወይም በቡድን ለተቀመጡ ተማሪዎች ጭምር አይደለም፤ ሁሉም ለጠቅላላ /ለክፍሉ ተማሪ ብቻ የቀርበ ነው።

ሰንጠረዥ 4.39 ፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የከተማና የከፊል ከተማ ት/ቤቶች የ9ኛ ክፍል ትምህርቶች የተሳታ/አደረጃጀት

የተሳታፊዎች አደረጃጀት		ት/ቤት ፩			ት/ቤት ፪			የከተማ ት/ቤቶቹ አማካይ (Average)	ት/ቤት ፫	ት/ቤት ፬			የከፊል ከተማ የት/ቤቶቹ አማካይ (Average)
		መምህርት ሀ አማካይ (Average)	መምህርት ለ አማካይ	አማካይ (Average)	መምህርት ሐ አማካይ	መምህርት መ አማካይ	አማካይ / Average		መምህርት ሠ አማካይ	መምህር ረ አማካይ	መምህር ት ሰ አማካይ	የት/ቤት ፬ አማካይ (Average)	
ክፍላዊ	መ-ተ/ክ	54.56	98.61	76.59	77.17	97.22	87.19	81.89	77.18	44.00	86.48	65.24	71.21
	ተ-ተ/ክ	23.59	1.39	12.49	0.00	0.00	0.00	6.24	8.77	41.36	2.71	22.03	15.40
ቡድናዊ	የተለያየ ተግባር	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ተመሳሳይ ተግባር	9.32	0.00	4.66	16.77	0.00	8.39	6.53	3.03	14.64	2.71	8.67	5.85
ግላዊ	የተለያየ ተግባር	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ተመሳሳይ ተግባር	12.52	0.00	6.26	6.06	2.78	4.42	5.34	11.02	0.00	8.11	4.06	7.54
አጠቃላይ %		100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100

ሰንጠረዥ 4.40፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የገጠር 9ኛ ክፍል ት/ ቤቶች የተሳታፊዎች አደረጃጀት

የ9ኛ ክፍል ገጠር ት/ቤቶች ተሳታፊዎች አደረጃጀት						
የተሳታፊዎች አደረጃጀት		ት/ቤት ፭			የት/ቤት ፮ አማካይ (Average)	የገጠር ት/ቤቶቹ አማካይ (Average)
		መምህርት ሸ አማካይ (Average)	መምህርት ቀ አማካይ (Average)	የት/ቤት ፭ አማካይ (Average)		
ክፍላዊ	መ-ተ/ክ	85.32	73.37	79.35	67.19	73.27
	ተ-ተ/ክ	1.00	26.63	13.81	3.57	8.69
ቡድናዊ	የተለያየ ተግባር	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ተመሳሳይ ተግባር	10.00	0.00	5.00	14.65	9.83
ግላዊ	የተለያየ ተግባር	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ተመሳሳይ ተግባር	3.68	0.0	1.84	14.59	8.21
አጠቃላይ %		100	100	100	100	100

ሰንጠረዥ 4.41፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የከተማ፣ የከፊል ከተማና ገጠር ት/ቤቶች የ10ኛ ክፍል ትምህርቶች የተሳታፊዎች አደረጃጀት

በከተማ ት/ቤቶች የተሳታፊዎች አደረጃጀት							በከፊል ከተማ ት/ቤቶች ተሳታፊዎች አደረጃጀት			በገጠር ት/ቤቶች የተሳታፊዎች አደረጃጀት		
		ት/ቤት ፩			ት/ቤት ፪		ት/ቤት 3			ት/ቤት 5	ት/ቤት 6	
የተሳታፊዎች አደረጃጀት		መምህርት ተ አማካይ	መምህር ቸ አማካይ	የት/ቤት ፩ አማካይ	መምህር ነ አማካይ	የከተማ ት/ቤቶቹ አማካይ	መምህርት ኘ አማካይ	መምህርት አ አማካይ	የከፊል ከተማ ት/ቤቶቹ አማካይ	መምህርት ከ አማካይ	መምህርት ኸ አማካይ	የገጠር ት/ቤቶቹ አማካይ
ክፍላዊ	መ-ተ/ክ	76.05	84.00	80.02	100	90.00	86.15	100	93.08	46.46	59.36	52.91
	ተ-ተ/ክ	1.5	4.26	2.88	0.00	1.44	13.85	0.00	6.92	32.97	0.00	16.49
ቡድናዊ	የተለያየ ተግባር	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ተመሳሳይ ተግባር	13.98	2.65	8.32	0.00	4.16	0.00	0.00	0.00	0.00	40.64	20.32
ግላዊ	የተለያየ ተግባር	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ተመሳሳይ ተግባር	8.47	9.09	8.78	0.00	4.39	0.00	0.00	0.00	20.75	0.00	10.28
አጠቃላይ %		100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100

በሰንጠረዥ 4.41 የቀረበው የ10ኛ ክፍል ትምህርት የተሳታፊዎች አደረጃጀትም ከዘጠነኛ ክፍል ብዙም ልዩነት አይታይበትም፡፡ በዚህኛውም ቢሆን በገጠር ትምህርት ቤቶች ያለው እውነታ ለየት ያለ ቢመስልም በሁሉም ትምህርት ቤቶች ከ50% በላይ የሚሆነው ጊዜ በመምህራኑ ንግግር የተያዘ ነው፡፡ የገጠር ትምህርት ቤቶችን የተሳታፊዎች አደረጃጀት ለየት ያለ ያስመሰለውም በሌላኛው የዚሁ ክፍላዊና ኢአሳታፊ አደረጃጀት በተ-ተ/ክፍል የቀረቡ ትምህርቶች መኖራቸው ነው፡፡ በቡድን ወይም በግል ለሚሰሩ ተግባራት የተሻለ ጊዜ በመመደቡ የተፈጠረ ልዩነት አይደለም፡፡ ሁለቱ ክፍላዊ አደረጃጀቶች ሲደመሩ በገጠር ትምህርት ቤቶች ያለው ክፍላዊ አደረጃጀት ወደ 69% ከፍ እንዲል ያደርገዋል፡፡

ለተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ተመራጭነት ወዳላቸው ወደ ሁለተኛውና ሦስተኛው የተሳታፊዎች አደረጃጀት ስንሻገር በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በቡድን አደራጅቶም ሆነ በግል ተግባራትን ለማሰራት የተደረጉ ውስን ጥረቶች መኖራቸውን ሰንጠረዦቹ ያመለክታሉ፡፡ በሰንጠረዦቹ እንደቀረበው በዘጠነኛ ክፍል በአማካይ በከተማ 6.53% በከፊል ከተማ 5.85% እና በገጠር 9.83% የሚሆነው ጊዜ በቡድን ለሚሰራ ተመሳሳይ ተግባር ውሏል፡፡ በ10ኛ ክፍል ደረጃ ደግሞ እንዲሁ በአማካይ በከተማ 4.16% እና በገጠር 20.32% የሚሆነው የክፍለ ጊዜያቱ ጊዚያት (ደቂቃዎች) እንዲሁ በቡድን ለሚሰሩ ተግባራት መዋላቸውን የቀረቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ግላዊ ተግባርን በተመለከተም በእነዚሁ ሰንጠረዦች እንደቀረበው በዘጠነኛ ክፍል በአማካይ በከተማ 5.34% በከፊል ከተማ 7.54% እና በገጠር 8.21% የሚሆነው ጊዜ ተመሳሳይ ተግባራትን በግል ለማከናወን ውሏል፡፡ በ10ኛ ክፍል ደግሞ እንዲሁ በአማካይ በከተማ 4.39% እና በገጠር 10.28% የሚሆነው ጊዜ ለዚሁ በግል ለሚከናወን ተመሳሳይ ተግባር ውሏል፡፡

በሰንጠረዦቹ ከቀረበው መረጃ ማስተዋል እንደሚቻለው በየትኛው ቦታ/ ምድብ በቡድንም ሆነ በግል የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን የዋለ ጊዜ የለም፡፡

በፔዳጎጅ ሳይንስ በተለይም ተማሪ-ተኮር (student-centered) በሚባለው የትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በግልም ሆነ በቡድን እንዲሰሩ ማድረግ ተደጋፊ ስልት ቢሆንም ምልከታ በተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች አንድም ጊዜ በየትኛውም ቦታ (በከተማ ወይም በከፊል ከተማ ወይም በገጠር) ተግባራዊ ሲደረግ አልታየም፡፡

ከዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት አንደኛ፣ ዋነኛ የተሳታፊዎች አደረጃጀት መምህር-ተማሪ/ክፍል እንደሆነ፣ ሁለተኛ፣ በግልም ሆነ በቡድን ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በተደጋጋሚ እንደማያከናውኑ የተሳታፊዎች አደረጃጀት የትንተና ውጤት አሳይቷል፡፡ ለዚህም አንዱ ተፅዕኖ ፈጣሪ የማጠናቀቂያ ፈተናው እንደሆነ በቀዳሚዎቹ ክፍሎች ከቀረቡት የጥናቱ ውጤቶች ጋር በማገናዘብ መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በየዓመቱ የሚዘጋጁት የቋንቋው የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎች ተማሪዎች

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P.O. BOX 1176

አሳታፊ በሆኑ አደረጃጀቶች ቢማሩ በቀላሉ ሊሰሯቸው የሚችሏቸው፣ ኢ-አሳታፊ አደረጃጀቶችን በመጠቀም በመማራቸው ደግሞ ለመስራት የሚከብዷቸው ዓይነት አይደሉም፡፡ እውነታው እንዲያውም ተቃራኒው ነው ማለት ይቻላል፡፡ በእነዚህ ምልከታዎች ተማሪዎች በግልና በቡድን ዐረፍተ ነገር፣ አንቀፅ፣ ረቂቅ፣... ድርሰት ሲጽፉ፣ ጭውውት፣ ውይይት፣ ክርክር በተግባር ሲያካሂዱ፣ ንግግር ሲያደርጉ በተደጋጋሚ ሊታይ ያልቻለበት አንዱ ምክንት ይኸው ነው ማለት ይቻላል፡፡ የመማር-ማስተማር ሂደቱ አሳታፊና ክሂል ተኮር አለመሆኑ ፈተናውን ለመስራት እንደማያግድ ሁለቱም (መምህራኑም ተማሪዎችም) የተገነዘቡት ይመስላል፡፡ ያ ባይሆን ኑሮ መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎች እንዲህ ያሉ በመማሪያ መጽሐፎቹ የተካተቱ ተግባሮችን አይዘሏቸውም ነበር፡፡ እንዲህ ያሉ በግልና በቡድን የሚከናወኑ ተግባሮች የተማሪዎችን የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት ዝቅ ያደርጋሉ ተብሎ ቢታመን ኖሮ የትምህርቱ አቀራረብ የተለየ ይሆን እንደነበር መገመቱ አይከብደም፡፡ ሌላው ከላይ የተገለጸውን ሀሳብ የሚያጠናክረው በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ተግባራዊ የተደረጉት የግልና የቡድን ተግባራት በአብዛኛው የንባብ ክሂል፣ የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች መልመጃዎች መሆናቸው ነው፡፡ እነዚህ ትምህርቶች በዚህ መንገድ (በቡድንና በግል ተግባርነት ጭምር) እንዲቀርቡ የሚደረገውም ተማሪዎችን በፈተናው ውጤታማ ለማድረግ ታስቦ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

በዚህ በተሳታፊዎች አደረጃጀት በአንፃራዊ ሁኔታ ትንሽ ለየት ብሎ የሚታየው በ10ኛ ክፍል የገጠር ትምህርት ቤቶች ያለው ነገር ነው፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች መምህርት 'ሽ' በአማካይ 40.64% የሚሆነውን ጊዜ ለቡድን ስራ አውለውታል፡፡ መምህርት 'ከ'ም ቢሆኑ ቀላል የማይባል ጊዜ (በአማካይ 20.57%) ተማሪዎቻቸውን የግል ተግባር ለማሰራት አውለዋል፡፡ ይህም ከከተማዎቹና ከከፊል ከተማዎቹ ትምህርት ቤቶች ይልቅ በገጠር ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩት መምህራን በተሻለ ደረጃ ከመምህር ተኮር ዘዴ ጎን ለጎን ተማሪዎቻቸውን የሚያሳትፉ አደረጃጀቶችንም ለመሞከር መድፈራቸውን ያሳያል፡፡ ከምክንያቶቹ አንደኛው የትምህርት ቤቶቹ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከገጠር የመጡ/ የሚመጡ በመሆናቸው ጥሩ ውጤት ለማምጣት የሚያስችል የመማሪያ ዘዴ የመምህራኑን ገለፃ ማዳመጥ ነው ብለው

የማያምኑ በመሆናቸው በመምህሮቻቸው ላይ የሚያሳድሩት ጫና ስለሌለ ወይም ቢኖርም የጎላ ስላልሆነ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ምክንያት በእነዚህ የገጠር ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩት ሁለት መምህራን የማስተማር ልምድ ዝቅተኛ መሆን ይመስላል። በከተማና በከፊል ከተማ እያስተማሩ እንዳሉት መምህራን ብዙ ዓመት የማስተማር ልምድ ያካበቱ አይደሉም። ይህም ለፈተናው ያላቸው እውቂያ አነስተኛ እንዲሆንና ሲያስተምሩ በፈተና በሚካተቱ ይዘቶችና ገለጻ ላይ ብቻ እንዳያተኩሩ ያደረጋቸው ይመስላል። ይህም ከAlderson and Wall (1993) መላምት እና ከShohamy እና ሌሎች (1996) የጥናት ግኝት ጋር ይደጋገፋል።

በእነዚህ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል በሚያስተምሩ መምህራን ይህ ያልተከሰተው አንደኛ በትምህርት ቤት ስድስት የሚያስተምሩት መምህርት በቅርቡ ከሌላ ክልል ተዛውረው በመምጣታቸው ገጠር የተመደቡ እንጂ ልምድ ያላካበቱ ባለመሆናቸው ይመስላል። በትምህርት ቤት አምስት ያሉት ሁለቱ መምህራንም የትምህርት ደረጃቸውን ከዲፕሎማ ወደ ዲግሪ በክረምት ፕሮግራም ተከታትለው ከፍ ሲያደርጉ ከከተማ ወደ ገጠር በመዛወራቸው እንጂ ለብዙ ዓመታት ከተማ ውስጥ ያስተማሩ ስለሆኑ ስለፈተናው የተሻለ እውቂያ ያላቸው እንደሆኑ የተገኘው ውጤት የሚጠቁመው ነገር አለ። ጎላ ላይ የተካሄዱት የቡድን ውይይቶችም ይህንኑ የሚያጠናክሩ ሆነው ተገኝተዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በመምህራኑ የተሳታፊዎች አደረጃጀት ረገድ የተስተዋለውን ልዩነት ውጫዊ (ብሔራዊ) ፈተናዎች በመምህራን ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ከመምህር መምህር የተለያየ ነው፣ ከሚለው የAlderson እና Wall (1993) መላምት ጋርም ሊዛመድ ይችላል። ይህን ከመምህር-መምህር ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ የተወሰኑ ተጨማሪ ምሳሌዎችን ብንመለከት በትምህርት ቤት ፩ የመምህርት ‹ሀ› እና መምህር ‹ለ› የተሳታፊዎች አደረጃጀት በሁለቱም ዋነኛውን ስፍራ የያዘው መምህር-ተማሪ /ክፍል ቢሆንም የመምህርት ‹ሀ› ከመምህር ‹ለ› ከ30% በላይ ዝቅ ይላል። በእርግጥ ከዚሁ ከክፍላዊ አደረጃጀት ሁለተኛው ንዑስ ክፍል ማለትም ተማሪ-ተማሪ/ክፍል ጋር ተደምሮ ሲታይ ልዩነታቸው ጠባብ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መምህርት ‹ሀ› የተወሰኑ

ጊዜያትን በቡድንና በግል ለሚሰሩ ተግባራት ያዋሉ ሲሆን መምህር "ለ" ለነዚህ ተማሪ አሳታፊ ተግባሮች ያዋሉት ምንም ጊዜ የለም። ልዩነቱ ከያታ ጋር የተገናኘ ይሆን ተብሎ እንዳይታሰብ ደግሞ በዚያው ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ደረጃ በሚያስተምሩም ሆነ በሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዲህ ያለ ከያታ ጋር የተያያዘ ወጥነት ያለው ልዩነት አይታይም። ስለዚህ ከመምህር-መምህርም ሆነ በጸታ መለያየት ምክንያት በተሳታፊዎች አደረጃጀት ረገድ ልዩነት ይታያል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል መረጃ አልተገኘም። ሁሉም ማለት በሚያስችል ደረጃ ተመራጭ አድርገው የወሰዱት ክፍላዊ አደረጃጀትን ነው። ይህም የተሳታፊዎችን አደረጃጀት ለመወሰን አንዱ ምክንያት የማጠናቀቂያ ፈተናው ሊሆን ይችላል የሚለውን አተያይ በልጥ የሚያጠናክር ነው።

ለ. ይዘትና የይዘት አቀራረብ

ከሰንጠረዥ4.45- 4.49 የቀረቡት የተግባራቱ ይዘቶችና ለየይዘቶቹ የዋለው ጊዜ አማካይ እንደሚያሳየው በዘጠነኛና በ10ኛ ክፍል መካከል ተመሳሳይነትም ልዩነትም ይታያል። ለምሳሌ በዘጠነኛ ክፍል የተሻለ ትኩረት በማግኘት በከተማ አንደኛው አራቱን የቋንቋው ክሂሎች በጋራ የያዘው (የጽንሰ ሀሳብ ትምህርቶችን ይጨምራል) ተግባቦት (42.52%) ሲሆን ሁለተኛው ሰዋስው፣ (34.32%)፣ ሦስተኛው ሥነ-ጽሑፍ (16.24%) ነው። ክሂሎች ከ"ዕውቀት ዘርፎች" ጋር ሲነጻጸሩ ግን የዕውቀት ክፍሎችን (ሰዋስውንና ሥነጽሑፍን) ለማስተማር የዋለው ጊዜ ይበልጣል። በተጀመረው መንገድ በመቀጠል በከፊል ከተማ ያለውን ዕውነታ መመልከት ይቻላል። በከፊል ከተማ በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ከቀዳሚው በተቃራኒ ሥነ-ጽሑፍ (42.29%) ነው። ሁለተኛው ተግባቦት፣ ሦስተኛው ሰዋስው ነው። በገጠር ትምህርት ቤቶች ያለው ዕውነታ ከሁለቱ ይለያል። በዚህኛው ምድብ በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሰዋስው ሲሆን ሁለተኛው ሥነ-ጽሑፍ ነው። ተግባቦት በሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።

በ10ኛ ክፍል ያለው ሁኔታ ከዘጠነኛው ይለያል። በዚህኛው በከተማና በከፊል ከተማ ትምህርት ቤቶች ትኩረት በማግኘት የአንደኝነት ደረጃን የያዘው ሥነ-ጽሑፍ ነው።

ሰንጠረዥ 4.42፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የከተማ ት/ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት

	ይዘት	ት/ቤት ፩			ት/ቤት ፪			የከተማ ት/ቤቶቹ አማካይ
		መምህርት ሀ አማካይ	መምህርት ለ አማካይ	ት/ቤት ፩ አማካይ	መምህርት ሐ አማካይ	መምህርት መ አማካይ	የት/ቤት ፪ አማካይ	
1	አመራር ሥነ-ምግባር	0.5	0.69	0.59	0.00	2.78	1.39	0.99
	አሰራር procedure)	2.21	1.75	1.98	0.00	1.38	0.69	1.34
2	ተተኳሪ ቋንቋ							
2.1	ሰዋስው	36.79						34.32
	ምዕላድ (ምንነት፣ አይነት፣ ተግባር)	1.43	0.00	0.72	0.00	0.00	0.00	0.36
	ቃል (ምስረታ፣ አይነት ፣ ሙያ)	0.00	8.77	4.39	25.76	0.00	12.88	8.63
	ሀረግ (ምስረታ፣ መሪቃል ፣ አይነት)	13.41	49.52	31.46	0.00	0.00	0.00	15.73
	ዐ.ነገር (ክፍሎች፣ ስልቶች አይነት...)	21.95	16.45	19.2	0.00	0.00	0.00	9.60
2.2	ሥነ-ጽሑፍ (አጠቃቀም)	13.18						16.24
	ልቦለድ (አይነት፣ አላባውያን..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ግጥም (ሙያዊ ቃላት፣ አይነት..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ቅኔ (ህብረ ቃል፣ ሰምናወርቅ)	0.00	10.75	0.0.88	50.00	0.00	25.00	12.94
	ሥነ-ቃል (አይነት፣ ተግባር...)	2.82	0.00	1.41	0.00	0.00	0.00	0.71
	ዘይቤ (አይነት፣ ተግባር..)	10.36	0.00	5.18	0.00	0.00	0.00	2.59
	ፊሊጥ (ምንነት፣ ፍቺ፣ ተግባር..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
2.3	አጠቃቀም/ተግባቦት							42.51
	ማዳመጥ/ማስታወሻ መያዝ...)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ንግግር (ውይይት፣ ክርክር፣ ንግግር፣ ጭውውት..)	2.35	0.00	1.18	24.24	1.32	12.78	6.98
	ንባብ (ቅድመና የንባብ ጊዜ ተግባራት፣ መረዳት ፣ ዐውዳዊ ፍቺ...)	39.99	15.79	27.89	0.00	57.45	28.73	28.31
	መጻፍ (ዐ.ነገር፣ አንቀፅ፣ቢጋር፣ ረቂቅ... ድርሰት)	2.54	0.00	1.27	0.00	0.00	0.00	0.64
	መጻፍ (አያያዥና መሸጋገሪያ...)	0.00	0.00	0.00	0.00	26.39	13.19	6.59
	ፈተና	2.42	5.26	3.84	0.00	10.67	5.34	4.59
	ጠቅላላ የይዘት %	100	100	100	100	100	100	100

በእርግጥ በመጠን ቢለያዩም ከዘጠነኛ ክፍል ከፊል-ከተማ ጋር ይመሳሰላል፡፡ በሁለቱም ሁለተኛው ፈተና-ነክ ይዘት ነው፡፡ በከተማ ሰዋስው በሦስተኛነት ሲከተል

በከፊል ከተማ ከአራተኛው ከሰዋስው በ2% አካባቢ ከፍ ብሎ በ10.42% ተግባቦት በሦስተኛነት ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በገጠር ደግሞ ሰዋስው አንደኛ ሲሆን ሥነ-ጽሑፍ በቅርብ ርቀት (ከአንድ ነጥብ ባነሰ ጊዜ) በሁለተኛነት ይከተላል፡፡ ተግባቦት በሁለቱ ቦታዎች (በከተማና በገጠር) በሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ሰንጠረዥ 4.43 ፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የከፊል ከተማ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት

	ይዘት	ት/ቤት ፫	ት/ቤት ፬			የከፊል ከተማ ት/ቤቶቹ አማካይ
		መምህርት ሠ አማካይ	መምህርት ረ አማካይ	መምህርት ሰ አማካይ	የት/ቤት ፬ አማካይ	
1	አመራር ሥነ-ምግባር	0.00	0.00	4.13	2.06	1.03
	አሰራር (procedure)	0.00	0.00	24.59	12.29	6.15
2	ተተኳሪ ቋንቋ					
2.2	ሰዋስው					
	ምዕላድ (ምንነት፣ አይነት፣ ተግባር)	0.00	0.00	12.16	6.08	3.04
	ቃል (ምስረታ፣ አይነት፣ ሙ.ያ)	0.00	0.00	27.78	13.89	6.95
	ሐረግ (ምስረታ፣ መሪቃል፣ አይነት)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ዐ.ነገር (ክፍሎች፣አይነት፣ ስልት ...)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
2.2	ስነ-ጽሁፍ (አጠቃቀም)					
	ልቦለድ (አይነት፣ አላባውያን..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ግጥም (ሙ.ያዊ ቃላት፣ አይነት..)	18.75	0.00	0.00	0.00	9.38
	ቅኔ (ህብረ ቃል፣ ሰምናወርቅ)	0.00	100	1.35	50.67	25.34
	ስነ-ቃል (አይነት፣ ተግባር...)	0.00	0.00	6.76	3.38	1.69
	ዘይቤ (አይነት፣ ተግባር...)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ፊሊጥ (ምንነት፣ ፍቺ፣ ተግባር...)	0.00	0.00	5.15	2.57	1.29
	እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ	0.00	0.00	17.57	8.78	4.39
2.3	አጠቃቀም/ተግባቦት					
	ማዳመጥ/ማስታወሻ አያያዝ...)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ንግግር (ውይይት፣ ክርክር፣ ንግግር፣ ጭውውት..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ንባብ (የቅድመና የንባብ ጊዜ ተግባራት፣ መረዳት፣ ዐውዳዊ ፍቺ)	14.58	0.00	0.00	0.00	7.29
	መጻፍ(ዐ.ነገር፣ አንቀፅ፣ ረቂቅ ... ድርሰት)	66.67	0.00	0.00	0.00	33.34
	መጻፍ (አያያዥና መሸጋገሪያ..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
3	ፈተና (የማጠናቀቂያ፣ የክፍል..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ጠቅላላ የይዘት %	100	100	100	100	100

ለክሂሎችና በተለምዶ የዕውቀት ዘርፎች እየተባሉ ለሚጠሩት ለሥነ-ጽሑፍና ለሰዋስው የተሰጠው የትኩረት ደረጃ ሲነጻጸርም በዘጠነኛም ሆነ በ10ኛ ክፍል ከፍተኛ ልዩነት ይታያል። በሁሉም ቦታዎች በሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ክፍል ይዘት ነው። ወደ ኋላ እንደምንመለከተው ከሥነ-ጽሑፍና ከሰዋስው ትምህርቶች መካከልም ላቅ ያለ ትኩረት የተሰጠው የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታን ለማዳበር ለሚያግዙት ሳይሆን ዕውቀትን ለሚያስጨብጡት ክፍሎች ነው ማለት ይቻላል።

በክሂል ትምህርቶችም ቢሆን የተሻለ ጊዜ የሚሰጠው ለማመንጨት (የመናገርና የመጻፍ ክሂልን በተግባር እየተለማመዱ ለመማር) ሳይሆን እነዚህን የሚመለከቱ ፅንሰ ሃሳቦችን ለመማርና ለማስተማር ነው። በሌላ አባባል፣ በአብዛኛዎቹ መምህራን በሰዋስውና በሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ይዘቶች ብቻ ሳይሆን በክሂሎቹም ይበልጥ ትኩረት የሚሰጠው ለፅንሰ ሀሳብ ትምህርት ነው። ከፍተኛ ትኩረት በማግኘትም ሆነ የትምህርቱን ትኩረት ፅንሰ ሀሳብ ላይ ሳይሆን አንብቦ የመረዳት ክሂሎችን በማዳበር ላይ አተኩሮ የሚቀርበው የንባብ ክሂል ትምህርት ነው። በሰንጠረዦች ላይ በጥቅሉ ሲታይ የመጻፍ ክሂልም የተሻለ ትኩረት ያገኘባቸው ክፍሎች ያሉ ቢመስልም የየመምህሩ ትምህርት ይዘት ሲቀርብ መመልከት እንደሚቻለው ተማሪዎች በተግባር እየጻፉ የሚለማመዱበት አይደለም። ይህ ክፍል ስለመጻፍ ክሂል ፅንሰ ሀሳቦችን የተማሩበት ብቻም ሳይሆን ስለ ልቦለድ አላባውያንና የአተራረክ ዘዴዎች፤ ስለቅኔ ምንነት፣ ህብረ ቃል፣ ሰምና ወርቅ እንዲሁም የቅኔ አፈታት ዘዴ ወዘተ መምህራኑ በቃል ወይም ሰሌዳ ላይ በመጻፍ የሚያጽፏቸውን ማስታወሻዎች ለመጻፍ/ ለመገልበጥ ያዋሉት ጊዜ ሁሉ የተካተተበት ነው።

እነዚህ ሁሉ የተግባራት ይዘቶች ትኩረት እንዲያገኙ ሌሎቹ (በተለይም ደግሞ የቋንቋው ትምህርት ዋነኛ ጉዳይ የሆኑት ክሂሎቹ) ችላ እንዲባሉ፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ አልፈጠረም ብሎ ለማሰብ አያስችልም። ይልቁኑ በፈተናዎቹ ሀሳብን በተግባር በጽሑፍም ሆነ በቃል የመግለፅ ችሎታን የሚመዝኑ ጥያቄዎች የማይካተቱ መሆናቸው ቀላል የማይባሉ የክሂሎች፣ የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ቴክኒካል(የፅንሰ

ሃሳብ) ይዘቶች በፈተናዎቹ የሚካተቱ መሆናቸው የፈጠረው ተፅዕኖ ውጤት ነው ብሎ ለመደምደም የሚያበረታታ ነው።

የየመምህሮቹን የተግባራት ይዘቶችና አቀራረብ ማየቱ ከላይ የተነሱ ሀሳቦችን በግልፅ ለመረዳትና በመምህራን መካከል ያለውን ለየይዘቶቹ የሚሰጡትን ትኩረት፣ የትኩረት ዓይነቶችና አቀራረብ በተሻለ ደረጃ ለማጤን ያግዛል። ስለዚህ ወደዚያው መሻገር ይሻላል።

ከዘጠነኛ ክፍል መምህራን ከመምህርት 'ሀ' መነሳት ይቻላል። በሰንጠረዥ4.42 እንደተመለከተው የትምህርት ቤት አንድ የመምህርት 'ሀ' የስምንት ሳምንታት ትምህርቶች የክፍል ውስጥ ተግባራት ዋና ዋና ይዘቶች ሰዋስው፣ ሥነ-ጽሑፍና ንባብ ናቸው። የክፍል አመራር፣ ፈተና፣ ንግግርና ጽሕፈትም በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን የመወከል እድል አግኝተዋል። ላቅ ያለ ሽፋን ካገኙት አንዱ የሆነው ሰዋስው በ36.79% ሲወከል ከሰዋስው ደግሞ በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ዐረፍተ ነገር ነው። ሁለተኛው ሐረግ ነው። በእኒህ መምህርት ዐረፍተ ነገርን በተመለከተ የዐረፍተ ነገር ምንነትና ክፍሎች፣ በተለያዩ የሐረግ ዓይነቶች ዐረፍተ ነገሮችን መመስረትና ተራና ውስብስብ ዐረፍተ ነገር የሚሉት ይዘቶች ተካተዋል። በሐረግ ረገድ ደግሞ አምስቱ የሐረግ ዓይነቶች፣ መሪ ቃልና የተለያዩ የሐረግ ዓይነቶችን መመስረት ተካተዋል። በሥነ-ጽሐፍ ትምህርትነት የቀረቡት ይዘቶች ደግሞ ዘይቤዎች (ከግጥም ውስጥ የተለያዩ ዘይቤዎችን ማውጣትን ይጨምራል) እና ሥነ-ቃል ናቸው። የሁለቱም ትምህርቶች (የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ) ይዘቶች የቀረቡት በአብዛኛው በመምህርቷ ገለፃና በጥያቄና መልስ ነው።

በሰንጠረዥ 4.42፣ እንደተመለከተው በእኒህ በመምህርት "ሀ" ከቋንቋ ክሂሎች ደግሞ ከፍተኛ ሽፋን በማግኘት በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ይዘት የንባብ ክሂል ነው። በትምህርቱ አቀራረብም የቅድመ ንባብና የድኅረ ንባብ ተግባራት፣ ከድኅረ ንባብ ተግባራት ደግሞ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችና ለቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት በተደጋጋሚ የቀረቡ ክፍሎች ናቸው። የንባብ ጊዜ ተግባራት አልፎ አልፎ ተካተዋል። የመምህርቷ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በአብዛኛው በመስኩ ምሁራን የሚመከሩ ዘመናዊ የንባብ ትምህርት ማቅረቢያ ስልቶችን በተለይም በጋራ

መማማር (Cooperative Learning) የተከተለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የቅድመ ንባብ ተግባራትን መጀመሪያ በግል ቀጥሎ በጥንድ/ በቡድን እንዲሞክሩ ማድረግ፣ ቀጥሎ ምንባቦቹን በግልና በለሆሳስ (ድምጽ ሳያሰሙ) ማስነበብ፣ ከዚያ የድኅረ ንባብ ተግባራት ላይ በጥንድ ወይም በቡድን ወይም በጋራ ማወያየት፣ መምህርቷ በተደጋጋሚ የሚከተሉት የንባብ ትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ በአንፃሩ ሌሎቹ መምህራን ብዙ ጊዜ ምንባባቱን ራሳቸው የሚያነቡ ወይም ተማሪዎቹ እጅ እያወጡ እድል ሲያገኙ አንዳንድ አንቀፅ ተራ በተራ የሚያስነብቡ፤ ቀጥሎም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በጥያቄና መልስ ዘዴ የሚያሰሩ ናቸው፡፡

ከመጻፍ ክሂል አስረጂ/ ገላጭ ድርሰት በእኒህ መምህርት የቀረበ ይዘት ነው፡፡ አስረጅ ድርሰት እንዴት እንደሚጻፍ ካስረዱና ምሳሌ ካሳዩ በኋላ እያንዳንዱ ተማሪ በምሳሌው መሰረት ጽፎ እንዲመጣ የቤት ስራ ሰጥተው ነበር፤ በተባለው ቀንም ተማሪዎቹ እየተነሱ የጻፉትን ድርሰት እንዲያነቡ እድል መስጠት ቢጀምሩም ጽፈው የመጡት ሦስት ተማሪዎች ብቻ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም ሦስቱ ተማሪዎች ካነበቡና በተነበቡት ድርሰቶች ጠንካራና ደካማ ጎን ላይ በመምህርቷ አስተያየት ከተሰጠ በኋላ ቀሪው ሰዓት በቅጽሎችና ስሞች ዓረፍተ ነገር መጻፊያነት እንዲውል ተደርጓል፡፡ የስምንተኛው ክፍለ ጊዜ ዋነኛ ይዘት ንግግር የነበረ ሲሆን አብዛኛው ደቂቃ በመማሪያ መጽሐፉ ገጽ 192 የቀረበውን <u>የንግግር መመሪያ</u> ዝርዝር ነጥቦች ለመግለጽ/ ለማስረዳት እንዲውል ተደርጓል፡፡ ቀጥሎ የይድነቃቸው ተሰማን ታሪክ መነሻ በማድረግ ባለፈው ክፍለ ጊዜ በተነገራቸው መሰረት መመሪያውን ተከትለው ያዘጋጁትን የቃል ንግግር ለጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ዕድል ቢሰጥም እያንዳንዳቸው ከአንድ ደቂቃ ላልበለጠ ጊዜ ያህል አራት ተማሪዎች ንግግር እንዳደረጉ ሌላ ፈቃደኛና ዝግጅት ያደረገ ተማሪ በመጥፋቱ እንደ ድርሰቱ ንባብ ሁሉ ይኸኛውም በታሰበው መንገድ ሳይቀጥል ቀርቷል፡፡ ይህም ተማሪዎች እንዲጽፉና እንዲናገሩ እድል የሚፈጥርላቸው መምህር ቢያገኙም የመጻፍና የመናገር ክሂላቸውን ለማዳበር እንደ ማይፈልጉ ያሳየ አንድ ማስረጃ ነው ሊባል ይችላል፡፡ በዚሁ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍሉ መምህር የማስተማር ሂደት ላይም ተመሳሳይ ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ እንዲህ ያሉ ጠቃሚ ክሂሎችን ተማሪዎች ለመማር አለመፈለጋቸው ምናልባትም

እንዲህ ያሉ ክሂሎች በማጠናቀቂያ ፈተናው በተግባር ስለማይጠየቁ/ ስለማይካቱት ሊሆን ይችላል፡፡

የዚሁ ትምህርት ቤት ሌላው መምህር (መምህር 'ለ') የክፍል ትምህርት ተግባራት ይዘቶች በአብዛኛው ከመምህርት 'ሀ' ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ከመምህር 'ለ' ጋር ከተካሄዱት ውይይቶች ማረጋገጥ የተቻለውም መምህራኑ (ዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩት ሁሉ ማለት ነው) የሚያስተምሩትን የሚያቅዱት በጋራ እየተመካከሩ ነው፡፡ በሁለቱ መምህራን ይዘት መረጣና ትኩረት ጉልህ ልዩነት ያልታየው በዚሁ ምክንያት ይመስላል፡፡ ጉልህ ሊባል የሚችል ልዩነት ከታየባቸው ክፍሎች አንዱ እኒህኛው መምህር በንባብ ክሂል ትምህርት መነሻነት ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ መፈለግን ሲያስተምሩ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ የሚለውን ክፍል መዝገበ ቃላቱን በክፍል ውስጥ ይዘው በመግባት የቃላቱን መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ከመዝገበ ቃላቱ እየፈለጉና እያነበቡ ለማስተማር ያደረጉት ጥረት ነው፡፡

የትምህርት ቤት፪ መምህራን የክፍል ትምህርት ተግባራትን ይዘቶች በተመለከተ የመምህርት'ሐ' ቅኔ (ህብረ ቃል፣ ሰምና ወርቅ)፣ ቃላት (ለቃላት ተመሳሳይና ለተሰመረባቸው ቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት)፣ የክፍል አመራር፣ ንግግር/ የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ የሚሉት ናቸው፡ በመጨረሻው ርዕስ ስርም መምህርቷ ሰሌዳ ላይ እየፃፉ የገለጿቸው የሚከተሉት ነጥቦች ተካተዋል፡፡ ዋነኛው ንዑስ ርዕስ <u>ከክርክር በፊትና በክርክር ጊዜ</u> የሚል ሲሆን ከክርክር በፊት በሚለው ይዘት 1. መጻሕፍትን በማንበብና ሰዎችን በመጠየቅ መረጃዎችን መሰብሰብ 2. ሀሳቦችን በቅደም ተከተል ማደራጀት 3. ልምምድ ማድረግ (ራስን በመስታወት እያዩ፣ ሌሎች ሰዎች አስተያየት እንዲሰጡን በማድረግ) 4. አለባበስን ማስተካከል የሚሉት፣ በክርክር ጊዜ በሚለው ስር ደግሞ 1.ሰላምታ መስጠት 2. ርዕስን ለአድማጭ ማስተዋወቅ 3. አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን አለማድረግ 4. ሰዓትን ማክበር 5. እይታን ወደ አድማጭ ማድረግ 6. የሀሳቡን ፍሰት መጠበቅ 7. ከአድማጭ የሚመጣ ጥያቄ መቀበልና 8. የተቀናቃኞችን ሞራል አለመንካት፣ የሚሉት ነጥቦች ተካተዋል፡፡

የዚሁ ትምህርት ቤት የመምህር "መ" ትምህርቶች ተግባራት ይዘቶች የክፍል አመራር (ሥነ-ምግባር)፣ ዐውዳዊ አገባብ፣ ፈተና (ተከታታይ ምዘናና የውጤት

አሰጣጥና የ፪ኛ ሴሚስተር ማጠቃለያ ፈተና)፣ የሙግትና ክርክር ሥርዓትና ንባብ (አንብቦ መረዳት) ናቸው።።

የከፊል ከተማ ትምህርት ቤቶች ትምህርቶች (ተግባራት) ዋና ዋና ይዘቶች ስንመለከትም የመምህርት‹ሡ› የቅድመ ጽሕፈት ተግባራት (ርዕስ መምረጥና ማጥበብ፣ አስተዋፅኦ መንደፍና ረቂቅ መጻፍ_በገለፃ የቀረቡ ይዘቶች)፣ ደብዳቤ (የደብዳቤ ምንነት፣ ዓይነት /የግል፣ የመስሪያ ቤት፣ የደብዳቤ ዓይነቶች በቅርፅና በይዘት የሚመሳሰሉባቸውና የሚለያዩባቸው ባህርያት)፣ ግጥምና የንባብ ክሂል_ አንብቦ መረዳት ናቸው።። በዚሁ በከፊል ከተማነት ከተካተቱ ትምህርት ቤቶች አንዱ በሆነው የትምህርት ቤት፬ መምህራን የክፍል ትምህርቶች ተግባራት ይዘቶችን ስንመለከትም የመምህር‹ረ› ቅኔ (ጎብረ ቃል፣ ሰምና ወርቅ እና የቅኔ መፍቻ ዘዴዎች)፣ የመምህርት ‹ሰ› የምዕላድ ተግባራት፣ የቃል ሙያ (ባለቤት፣ ተሳቢ....)፣ ቅኔ፣ ሥነ-ቃል፣ ፈተናና የዐረፍተ ነገር ክፍሎች (ባለቤት፣ ተሳቢ፣ ማሰሪያ አንቀፅ)፣ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ፣ ፈሊጦችና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ናቸው።። የሁለቱም መምህራን ትምህርቶች ለሥነ-ጽሑፍ ዘርፍ ይዘቶች የላቀ ትኩረት ሰጥተዋል።። የሁለተኛዋ መምህርት ደግሞ ከሥነ-ጽሑፍ በተጨማሪ የተለያዩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አካተዋል።። አንዳቸውም የክሂል ትምህርት ይዘት አላካተቱም።።

በገጠር ትምህርት ቤቶች በመምህርት ‹ሽ› ትምህርቶች የተካተቱት ይዘቶች የክፍል አመራር (ሁለቱም ማለትም አሰራርና ሥነ-ምግባር) ከሰዋስው ምዕላድ፣ ቃልና ዓረፍተ ነገር ናቸው።። ከዐረፍተ ነገር ደግሞ ጅምር ዐረፍተ ነገሮችን በተገቢ ግሶች ማሟላትና በተሰጡ ቃላት ዐረፍተ ነገር መመስረት ናቸው።። በሥነ-ጽሑፍ ዋነኛ ትምህርት ሆኖ የቀረበው ግጥም ሲሆን በግጥም ትምህርትነትም የግጥምና የዝርው ልዩነት፣ የግጥም ባህርያት፣ ከግጥም ውስጥ ለወጡ ቃላት አገባባዊና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ መስጠት (ተመሳሳይ እና ተቃራኒ)፣ ግጥምን አንብቦ መረዳትና ጅምር ስንኞችን መጨረስ የሚሉት ተካተዋል።። ዘይቤ ሌላው በእኒህ መምህርት ትኩረት ያገኘ የትምህርት ይዘት ነው።። በመማሪያ መፅሐፉ የቀረቡ ሦስት ዘይቤዎች ላይ ሌሎች አምስት ዘይቤዎች በእኒህ መምህርት ዋነኛ የዘይቤ ትምህርት ሆነው ቀርበዋል።። ከመጻፍ

ክሂል ደግሞ በራስ አባባል መጻፍ፣ የቃላት መጥበቅና መላላት ሦስት ህጎች፣ ርዕስ መምረጥና ማጥበብ፣ አስተዋፀኦ መንደፍና ረቂቅ መጻፍ የሚሉት ተካተዋል።

ሰንጠረዥ 4.44፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የገጠር ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት

	ይዘት	ት/ቤት ፩			ት/ቤት ፪	የት/ቤቶቹ አማካይ /Average
		መምህርት ሸ አማካይ	መምህርት ቀ አማካይ)	መምህርት ሰ አማካይ	መምህርት በ አማካይ	
1	አመራር ሥነ-ምግባር	1.76	1.63	1.95	1.43	1.69
	አሰራር (procedure)	2.75	0.00	1.37	0.00	0.68
2	ተተኳሪ ቋንቋ					
2.2	ሰዋስው					47.23
	ምዕላድ (ምንነት፣ አይነት፣ ተግባር)	12.5	0.00	6.25	0.00	3.13
	ቃል (ምስረታ፣ አይነት፣ ሙ.ያ)	4.14	0.00	2.07	0.00	1.04
	ሀረግ /ምስረታ፣ መሪቃል፣ አይነት)	0.00	0.00	0.00	28.93	14.47
	ዐ.ነገር (ክፍሎች፣አይነት፣ ስልት	22.23	0.00	11.11	46.07	28.59
2.2	ሥነ-ጽሑፍ (አጠቃቀም)					27.59
	ልቦለድ (አይነት፣ አላባውያን...)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ግጥም (ሙ.ያዊ ቃላት፣ አይነት...)	12.5	86.79	49.64	0.00	24.82
	ቅኔ (ህብረ ቃል፣ ሰምናወርቅ..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ስነ-ቃል (አይነት፣ ተግባር...)	3.5	0.00	1.75	0.00	0.87
	ዘይቤ (አይነት፣ ተግባር...)	5.0	2.63	3.82	0.00	1.90
	ፊሊጥ (ምንነት፣ ፍቺ፣ ተግባር...)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
2.3	አጠቃቀም/ተግባቦት					22.91
	ማዳመጥ/ማስታወሻ አያያዝ...)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ንግግር (ውይይት፣ ክርክር፣ ንግግር፣ ጭውውት..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ንባብ (የቅድመና የንባብ ጊዜ ተግባራት፣ መረዳት፣ ዐውዳዊ ፍቺ)	5.65	0.00	2.82	1.43	2.13
	ጽሕፈት (ዐ.ነገር፣ አንቀፅ፣ ረቂቅ ድርሰት)	29.94	8.94	19.44	18.57	19.00
	ጽሕፈት (አያያዥና መሸጋገሪ...ያ)	0.00	0.00	0.00	3.57	1.78
3	ፊተና (የማጠናቀቂያ፣ የክፍል..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ጠቅላላ የይዘት %	100	100	100	100	100

መግለጫ፤

ለየተግባሩ የዋለው ደቂቃ ብዛት ሲካፈል ምልከታ ለተካሄደበት ጠቅላላ ደቂቃ ሲባዛ በመቶኛ ስሌት

የትምህርቶቹ አቀራረብም የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶቹ ሳይቀር ፅንሰ ሃሳብን ማሳወቅ ላይ ያተኮረና በመምህርቷ ገለፃና በጥያቄና መልስ የተከናወነ ነው።

የዚሁ ትምህርት ቤት ፪ኛዋ የዘጠነኛ ክፍል መምህርት የትምህርት ይዘቶች ደግሞ በአብዛኛው በሥነ-ግጥም ላይ ያተኮሩ ናቸው። የተወሰኑ ጊዜያት ለዘይቤ ትምህርትና ተማሪዎችን ግጥም ለማጻፍና ለማስነበብ ውለዋል። የግጥምም ሆነ የዘይቤ ትምህርት ይዘቶች ከቀዳሚዋ መምህርት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ለየት ያለና በቀዳሚዋ መምህርት ያልተካተተው ደብዳቤ (የደብዳቤ ምንነት፣ ዓላማ፣ ተግባራት፤ የስራ ደብዳቤ ቅርፅ_ አድራሻ፣ ጸሐፊ፣ የተጻፈበት ቀን...) የሚለው ነው።

በትምህርት ቤት ፮ ከቀዳሚው ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ትምህርት ለየት ያለ ነገር የተስተዋለው አብዛኛው ጊዜ ለሰዋስው ትምህርት ይዘት ማስተማሪያነት እንዲውል መደረጉ ነው። ከመምህርቷ ትምህርቶች ተግባራት ይዘቶች ማስተዋል እንደሚቻለው የበለጠ ትኩረት የተሰጠው ለሰዋስው ነው። ከሰዋስውም ተማሪዎችን ጥሩ አድማጭ፣ ጥሩ ተናጋሪ፣ ጥሩ አንባቢና ጥሩ ፀሐፊ ለማድረግ ለሚያግዙት ክፍሎች አይደለም። በ10ኛ ክፍል ደረጃ ያለው እውነታም ከዘጠነኛው የተለየ አይደለም። ከዘጠነኛ ለየት የሚያደርገው ነገር በዚህኛው ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎች ዋነኛ የትምህርት ይዘት ሆነው መካተታቸው ነው። ስለዚህ የ10ኛ ክፍል ተግባራት ይዘቶችን ለመመልከት የተሞከረው ዝርዝር ውስጥ ሳይገባ /በደምሳሳው ነው።

ቀደም ብሎ እንደተወሳው የ10ኛ ክፍል የተግባራት ይዘቶች ከዘጠነኛው ትምህርት ይዘቶች በብዙ መልኩ መመሳሰል የሚታይባቸው ናቸው። ለማንኛውም ሀሳቡ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን ቀጥሎ ከከተማ ትምህርት ቤቶች መምህራን ተግባራት ይዘቶች በመጀመር በአጭር በአጭሩ ለመቃኘት ተሞክሯል።

በሰንጠረዥ4.45 እንደተመለከተው በትምህርት ቤት፮ በመምህርት ‹ተ› ከፍተኛ ሽፋን ያገኘው (65.06%) የሥነ-ጽሑፍ ይዘት ነው። ከሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ይዘት ውስጥም ቅኔ፣ ሥነ-ቃልና ፈሊጦች የተወከሉበት ትምህርት ነው። በቅኔ ትምህርት የቅኔ ምንነት፣ ጎብረ ቃል፣ ሰምና ወርቅና የቅኔ መፍቻ ዘዴዎች ተካተዋል። ከሥነ-ቃል ዓይነቶች ደግሞ የቃላዊ ግጥም ዓይነቶችና ቃላዊ ግጥሞችን በዓይነታቸው መመደብ እንዲሁም የምሳሌያዊ አነጋገሮችን ፍቺና ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በተገቢ አባባል ማሟላት ዋነኛ የትምህርት ይዘት ሆነው ቀርበዋል።

ሰንጠረዥ 4.45፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የከተማ እና የከፊል ከተማ ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት

		ከተማ					ከፊል ከተማ		
	ይዘት	ት/ቤት ፩			ት/ቤት ፪	የከተማ ት/ቤቶች አማካይ	ት/ቤት 3		የከፊል ከተማ ት/ቤቶች አማካይ
		መምህርት ተ አማካይ	መምህርቸ አማካይ	የት/ቤት ፩ አማካይ	መምህርነ አማካይ		መምህርኘ አማካይ	መምህርአ አማካይ	
1	አመራር ሥነ-ምግባር	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	አሰራር (procedure)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
2	ተተኳሪ ቋንቋ								
2.2	ሰዋስው	15.78	34.51	25.14	0.00	12.57	17.44	0.00	8.72
	ምዕላድ (ምንነት፣ አይነት፣ ተግባር...)	1.5	3.08	2.29	0.00	1.15	0.00	0.00	0.00
	ቃል (ምስረታ፣ አይነት፣ ሙያ...)	1.0	2.16	1.58	0.00	0.79	7.86	0.00	3.93
	ሐረግ (ምስረታ፣ መሪቃል፣ አይነት..)	5.16	21.48	13.32	0.00	6.66	0.00	0.00	0.00
	ዐ.ነገር (ክፍሎች፣ አይነት፣ስልት ...)	8.12	7.79	7.95	0.00	0.00	9.58	0.00	4.79
2.2	ሥነ-ጽሑፍ (አጠቃቀም)	65.06	36.89	50.98	0.00	25.49	22.59	0.00	41.47
	ልቦለድ (አይነት፣ አላባውያን...)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ግጥም (ሙያዊ ቃላት፣ አይነት ...)	0.00	0.54	0.27	0.00	0.00	12.88	30.11	21.49
	ቅኔ (ጎብረ ቃል፣ ሰምናወርቅ..)	36.05	19.12	27.58	0.00	0.00	8.59	0.00	4.29
	ስነ-ቃል (አይነት፣ ተግባር...)	23.39	7.58	15.49	0.00	0.00	0.00	3.23	1.62
	ዘይቤ (አይነት፣ ተግባር)	0.00	1.08	0.54	0.00	0.00	0.00	25.42	12.71
	ፊሊጥ (ምንነት፣ ፍቺ፣ ተግባር)	5.62	4.25	4.94	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ	0.00	4.32	2.16	0.00	0.00	3.12	0.00	1.56
2.3	አጠቃቀም/ተግባቦት	19.16	26.42	22.79		11.39	0.00	0.00	10.42
	ማዳመጥ/ማስታወሻ መያዝ...)	0.58	0.00	0.29	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ንግግር (ውይይት፣ ክርክር፣ ንግግር፣ ሞውውት..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
	ንባብ (የቅድመና የንባብ ጊዜ ተግባራት፣ መረዳት፣ ዐውዳዊ ፍቺ)	16.23	20..47	18.35	0.00	0.00	10.00	0.00	5.00
	ጽሕፈት (ዐ.ነገር፣ቢ.ጋር፣ አንቀፅ፣ ረቂቅ ድርሰት)	2.35	5.95	4.15	0.00	0.00	10.83	0.00	5.42
	ጽሕፈት (አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት..)	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
3	ፈተና (የማጠናቀቂያ፣ የክፍል..)	0.00	2.16	1.08	100	50.54	37.12	41.24	39.18
	ጠቅላላ የይዘት %	100	100	100	100	100	100	100	100

ሰንጠረዥ 4.46፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው የገጠር ት/ቤቶች የ10ኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት

	ይዘት	ት/ቤት ፩ መምህርት ከ አማካይ	የት/ቤት ፪ መምህርት ኸ አማካይ	የት/ቤቶቹ አማካይ
1	አመራር ሥነ-ምግባር	1.15	0.00	0.58
	አሰራር (procedure)	2.29	3.50	2.89
2	ተተኳሪ ቋንቋ			
2.2	ሰዋሰው			29.38
	ምዕላድ (ምንነት፣ አይነት፣ ተግባር...)	0.00	0.00	0.00
	ቃል (ምስረታ፣ አይነት፣ ሙ.ያ...)	0.00	0.00	0.00
	ሐረግ (ምስረታ፣ መሪቃል፣ አይነት...)	0.00	0.00	0.00
	ዐ.ነገር (ክፍሎች፣አይነት፣ ስልት ...)	0.00	58.77	29.38
2.2	ሥነ-ጽሑፍ (አጠቃቀም)			28.19
	ልቦለድ (አይነት፣ አላባውያን...)	16.67	0.00	8.34
	ግጥም (ሙ.ያዊ ቃላት፣ አይነት...)	0.00	0.00	0.00
	ቅኔ (ጎብረ ቃል፣ ሰምናወርቅ...)	29.59	0.00	14.79
	ሥነ-ቃል (አይነት፣ ተግባር)	1.33	0.00	0.67
	ዘይቤ (አይነት፣ ተግባር)	0.00	0.00	0.00
	ፊሊጥ (ምንነት፣ ፍቺ፣ ተግባር)	1.33	0.00	0.67
	እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ	7.44	0.00	3.72
2.3	አጠቃቀም/ተግባቦት			22.57
	ማዳመጥ/ማስታወሻ መያዝ...)	0.00	0.00	0.00
	ንግግር (ውይይት፣ ክርክር፣ ንግግር፣ ጭውውት..)	33.33	0.00	16.66
	ንባብ (የቅድመና የንባብ ጊዜ ተግባራት፣ መረዳት፣ ዐውዳዊ ፍቺ)	6.86	0.00	3.72
	ጽሕፈት (ዐ.ነገር፣ አንቀፅ፣ቢ.ጋር፣ ረቂቅ.. ድርሰት)	0.00	4.39	2.19
	ጽሕፈት (አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት)	0.00	0.00	0.00
3	ፈተና (የማጠናቀቂያ፣ የክፍል..)	0.00	33.33	16.66
	ጠቅላላ የይዘት %	100	100	100

መግለጫ፤

ለየተግባሩ የዋለው ደቂቃ ብዛት ሲካፈል ምልከታ ለተካሄደበት ጠቅላላ ደቂቃ ሲባዛ በመቶኛ ስሌት

በሰዋስው ዘርፍ ደግሞ የምዕላድ ምንነትና ዓይነት፣ ከምዕላዶች ቃላትን መመስረት፣ በሐረግ ትምህርት የሐረግ ምንነት፣ መሪ ቃልና የሐረግ ዓይነቶች፣ በዐረፍተ ነገር ትምህርትነት የዐረፍተ ነገር ዓይነቶች (ሀተታዊ፣ ጥያቄያዊ፣ ትዕዛዛዊና አጋናኝ) ቀርበዋል። ከአራቱ ክሂሎች ንባብ በ16.23%፣ ጽሕፈት በ2.35% እና ማዳመጥ 0.58% ተወክለዋል። ይህም በዘጠነኛ ክፍል እንደታየው ሁሉ ከንባብ ውጭ ያሉት ሦስቱ ክሂሎች በ10ኛ ክፍልም ምን ያህል ችላ የተባሉ የክሂል ዘርፎች እንደሆኑ የሚያሳይ ነው። በጥናቱ ቀዳሚ ክፍሎች ከጽሑፍ መጠይቆችና ከቡድን ተኮር ውይይቶች የተገኙ የጥናቱን ውጤቶች ትክክለኛነት የሚያረጋግጥም ነው።

የዚሁ ትምህርት ቤት ሁለተኛ መምህር፣ መምህር "ቸ" ትምህርትም ትኩረት በማግኘት በአንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ይዘት ሥነ-ጽሑፍ (36.89%)፣ ሁለተኛው ሰዋስው ነው። ከክሂሎች ደግሞ በሁለቱም መምህራን የተሻለ ሽፋን ያገኘው (በ16.23% እና 20.47%) የንባብ ክሂል ነው። ቀደም ብሎ ለሌላ ዓላማ በሌላ ክፍል እንደተገለጸው፣ በእኒህኛው መምህር ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ገጽ 112 ‹‹ሴቶች በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ስላላቸው ሚና›› በሚል ርዕስ አጠር ያለ ጽሑፍ አዘጋጅተው ለክፍሉ በንባብ እንዲያሰሙ የታዘዘውን፣ በመመሪያው መሰረት ጽፈው እንዲመጡ የሳምንት ጊዜ ቢሰጣቸውም በተባለው ቀን የቤት ስራውን ሰርቶ የመጣው አንድ ተማሪ ብቻ ነው። በመሆኑም የእሱን ብቻ ጽሑፍ ተማሪዎች እንዲያዳምጡ በማድረግ ሌሎቹ ሳይጽፉና ሳያነቡ ወደ ሌላ ርዕስ ሲሻገሩ በምልከታው ተስተውሏል። በእኒሁ መምህር በዚሁ በመጻፍ ክሂል ትምህርት በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ የንግድ ስራ ደብዳቤ ባህርይ፣ ቅርፅና ይዘትም በገለፃ ቀርቧል። ተማሪዎች በተግባር በክፍል ውስጥ እንዲጽፉ ወይም በቤት ስራነት ጽፈው እንዲያመጡ የተሰጠ ተግባር ግን አልነበረም። የትምህርት ቤት ፭ ይዘት መቶ በመቶ በሚባል ደረጃ ፈተና ላይ ያተኮረ ነበር። በትምህርት ቤት አንድም እንደዚህኛው ባይበዛም ለፈተና ጉዳይ የዋለ ጊዜ አለ።

በከፊል ከተማ ትምህርት ቤትም ዋነኛ ይዘት ሆነው የቀረቡት እንደ ትምህርት ቤት፭ ሁሉ የፈተና ጥያቄዎች ናቸው። በዚህ ትምህርት ቤት በሁለቱም መምህራን (በመምህር 'ኘ' በአማካይ 37.12፣ በመምህር 'አ' 41.24%) አብዛኛው ጊዜ የዋለው ለዚህ ዓላማ ነው። በእርግጥ ከዚህ በተጨማሪ ከፈተናው ጥያቄዎች ጋር በማያያዝ ቢሆንም እንኳ መምህር 'ኘ' ከሥነ-ጽሑፍ ግጥምን፣ ቅኔንና እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችን ለማስተማር በአማካይ 22.59% ያህል ጊዜ አውለዋል። ለሰዋስው ደግሞ በተለይም የቃላትንና ዐረፍተ ነገር ይዘቶችን ለማስተማር በአማካይ 17.44% የሚሆነውን ጊዜ ተጠቅመዋል። ከክሂሎች ደግሞ ንባብና ጽሕፈት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የመወከል አጋጣሚ አግኝተዋል። የጽሕፈት ትምህርቱም በቃላት የቀረበን መረጃ ወደ ሰንጠረዥና ቁጥር የመቀየር ተግባር ነበር።

በመምህር 'አ' የፈተና ጥያቄዎችን ከመስራት ቀጥሎ የተሻለ ሽፋን ያገኘው (30.11%) የግጥም ትምህርት ይዘት ነው። በግጥም ትምህርትም የግጥም ባህርያት (ሰዋስዋዊ ሕግጋትን አለመጠበቅ፣ ዕምቅነት፣ በዘይቤዎች ያሸበረቀ መሆን)፣ የግጥም ሙያዊ ቃላት (ሐረግ፣ ስንኝ፣ ቤት፣ ቤት መድፊያ፣ አርኬ ወይም አንጓ) የግጥም ዓይነቶች (የወል፣ ሰንሰ፣ ቡሄ በሉ) የሚሉት ይዘቶች ተካተዋል። ሁለተኛው (25.42%) ዘይቤ ነው። በዘይቤ አይነትነት በእኒህ መምህር ትኩረት ተሰጥቷቸው የቀረቡትም ተነፃፃሪ፣ ተለዋጭ፣ ሰውኛ፣ እንቶኔ፣ ግነት፣ ኩሸት፣ ተምሳሌትና አያዎ ናቸው። እያንዳንዱ ዘይቤ በተለያዩ ምሳሌዎች እየተደገፈ በዝርዝርና በስፋት በትምህርት ይዘትነት ቀርቧል። የእኒህ የመምህር 'አ' የክፍል ትምህርት ይዘት አቀራረብ ከሌሎቹ ለየት ይላል። ለየት ከሚያደርጋቸው ነገሮች አንዱ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ በተለያዩ ገጾች የቀረበን የትምህርት ይዘት ወደ አንድ በማምጣት የሚያቀርቡ መሆናቸውና ከትምህርቱ በኋላ በዚያ ትምህርት ዙሪያ የቀረቡ ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተና ጥያቄዎችን እያመጡ ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚሰሩ መሆናቸው ነው። ለምሳሌ የሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ በተለያዩ ገጾች ተለያይቶ የቀረበ ሲሆን እሳቸው ግን በአንድ ላይ አቀናጅተው ያቀርቡታል። በዚሁ መሰረት ግጥም ነክ ትምህርቶችን በተከታታይ ያስተምሩና ግጥምን በማንበብና በቀደመ ዕውቀት የሚመለሱ ግጥም ነክ ጥያቄዎችን፣ ከማጠናቀቂያ ፈተናው አሰባስበው ተማሪዎቻቸውን ያሰራሉ። ዘይቤን፣ ፈሊጦችን፣ ወዘተ. በተመለከተም እንዲሁ ያደርጋሉ። ተማሪዎቹ ለማጠናቀቂያ ፈተና ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡም ቀደም ብለው ከተማሩት ትምህርት ጋር እያገናዘቡ ምክንያት መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ሌላው የእኒህን መምህር የትምህርት ይዘት አቀራረብ ለየት የሚያደርገው በጥያቄና መልስ ቴክኒክ በሰፊው የሚጠቀሙ መሆናቸውና ተማሪዎች መልስ የሚሰጡትም በጋራ /በአንድ ላይ መሆኑ ነው። በትምህርት አቀራረብ ዘዴያቸው በመማረክ ይሁን በሌላ ምክንያት፣ በግልፅ ማረጋገጥ ባይቻልም፣ ከሌሎች መምህራን ይልቅ የእኒህ መምህር ክፍል ሁል ጊዜ በተማሪ ብዛት የተጨናነቀ ነው። በሌላ ክፍል በሌላ መምህር የሚማሩ ተማሪዎች ሁሉ ወደ እኒህ መምህር ክፍል እየገቡ ይማራሉ። ፈተናዎቹን ከትምህርቱ ጋር አያይዞ ማቅረብ በሌሎች ትምህርት ቤቶችም የተለመደ እንደሆነ ከተተኳሪ የቡድን ውይይቶቹ ለመረዳት ተችሏል።

ሐ. ይዘት ቁጥጥር

ይዘት ቁጥጥር የመማር ማስተማር ሂደቱን ይዘቶች የሚመርጠውና የሚቆጣጠረው ማነው? የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ በተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት መገለጫ (COLT) ንድፍ መሰረት ይዘት ቁጥጥር ሦስት አማራጮች ያሉት ነው፡፡ አንደኛው የትምህርቱን ይዘት የሚመርጠውና የሚቆጣጠረው ሙሉ በሙሉ መምህሩ የሚሆንበት ሁኔታ ነው፡፡ ሁለተኛው ይዘቱን መምህሩና ተማሪው የሚመርጡበትና/ የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ/ አጋጣሚ ሲሆን ሦስተኛው የተግባራቱ ይዘት በተማሪው የሚመረጥበት አማራጭ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በሰንጠረዥ 4.47 የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ በአማካይ **በከተማ** 96.83% **በከፊል ከተማ** 96.89% **በገጠር** 92.03%፤ በ10ኛ ክፍል እንዲሁ በአማካይ በከተማ 95.97 በከፊል ከተማ 100% እና በገጠር 83.34% ይዘቶች የሚመረጡትና ቁጥጥር የሚደረግባቸው በመምህራኑ ነው፡፡ ይህም ይዘት መረጣውና ቁጥጥሩ በሁሉም ቦታዎች በአብዛኛው በመምህራኑ ብቻ እንደሚከናወንና ተማሪዎችን አሳታፊ አለመሆኑን ወይም በመምህራኑ ብቻ የሚወሰን መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በተግባራቱ ይዘት መረጣ አብረው ባልተሳተፉበት ትምህርት ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ ባይሆኑ ደግሞ የሚገርም አይሆንም፡፡

ሰንጠረዥ 4.47፣ የክፍል ምልከታ የተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት ቁጥጥር

የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት ቁጥጥር							የአስረኛ ክፍል ትምህርቶች ይዘት ቁጥጥር					
ት/ቤቱ የሚገኝበት ቦታ	ትምህርት ቤት	መምህሩ/ሯ	ይዘት ቁጥጥር			ጠቅላላ የይዘት ቁጥጥር %	ትምህርት ቤት	መምህሩ/ሯ	ይዘት ቁጥጥር			ጠቅላላ የይዘት ቁጥጥር %
			መምህር-ቴክስት	መምህር-ተማሪ ቴክስት	ተማሪ-ቴክስት				መምህር-ቴክስት	መምህር-ተማሪ ቴክስት	ተማሪ - ቴክስት	
ከተማ	ት/ቤት ፩	መምህርት ሀ	87.31	12..69	0.00	100	ት/ቤት ፩	መምህርት ተ	100.00	0.00	0.00	100
		መምህር ለ	100.00	0.00	0.00	100		መምህር ቸ	98.18	1.82	0.00	100
	የት/ቤት ፩ አማካይ		93.66	6.34	0.00	100	የት/ቤት ፩ አማካይ		99.09	0.91	0.00	100
	ት/ቤት ፪	መምህርት ሐ	100.00	0.00	0.00	100	ት/ቤት ፯	መምህር ነ	92.85	7.15	0.00	100
		መምህር መ	100.00	0.00	0.00	100						
	የት/ቤት፪ አማካይ		100.00	0.00	0.00	100						
	የከተማ አማካይ		96.83	3.17	0.00	100						
ከፊል ከተማ	ት/ቤት ፫	መምህርት ሠ	100.00	0.00	0.00	100			95.97	4.03	0.00	100
	ት/ቤት ፬	መምህር ረ	86.77	0.00	13.23	100	ት/ቤት ፫	መምህር ኘ	100.00	0.00	0.00	100
		መምህርት ሰ	100.00	0.00	0.00	100		መምህር አ	100.00	0.00	0.00	100
	የት/ቤት ፬ አማካይ		93.38	0.00	6.62	100	የት/ቤት ፫ አማካይ		100.00	0.00	0.00	100
	ከፊል ከተማ አማካይ		96.69	0.00	3.31	100			100.00	0.00	0.00	100
ገጠር	ት/ቤት ፭	መምህርት ሸ	93.12	2.76	4.12	100	ት/ቤት ፭	መምህርት ከ	66.67	33.33	0.00	100
		መምህርት ቀ	75.00	0.00	25.00	100	ት/ቤት ፯	መምህርት ኸ	100.00	0.00	0.00	100
	የት/ቤት ፭ አማካይ		84.06	1.38	14.56	100						
	ት/ቤት ፯	መምህርት በ	100.00	0.00	0.00	100						
	የገጠር ት/ቤቶች አማካይ		92.03	0.69	7.28	100			83.34	16.67	0.00	100

መግለጫ፤

ለየተግባሩ የዋለው ደቂቃ ብዛት ሲካፈል ምልከታ ለተካሄደበት ጠቅላላ ደቂቃ ሲባዛ በመቶኛ ስሌት

መ. የተማሪው የመማሪያ ዘዴ

ሰንጠረዥ 4.48፣ የከተማና ከፊል ከተማ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመማሪያ ዘዴ

	ከተማ							ከፊል ከተማ				
	ትምህርት ቤት ፩			ትምህርት ቤት ፪			የት/ቤቶቹ አማካይ	ት/ ቤት ፫	ት/ ቤት ፬		የት/ቤት፬ አማካይ	የት/ቤቶቹ አማካይ
የቋንቋው ክሂል	መምህርት ሀ አማካይ	መምህር ለ አማካይ	የት/ቤት ፩ አማካይ	መምህርት ሐ አማካይ	መምህር መ አማካይ	የት/ቤት፪ አማካይ		መምህርት ሠ አማካይ	መምህር ረ አማካይ	መምህርት ሰ አማካይ		
ማዳመጥ %	78.16	100	89.08	72.25	97.22	84.73	78.49	85.95	85.37	92.79	89.08	
መናገር %	0.00	0.00		0.00	0.00		0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	87.52
ማንበብ %	8.86	0.00	4.43	0.00	2.78	1.39	2.91	3.13	0.00	0.00	0.00	0.00
መጻፍ %	3.66	0.00	1.83	6.06	0.00	3.03	2.43	7.89	0.00	5.41	2.70	1.57
ማዳመጥና መናገር	6.47	0.00	3.23	21.69	0.00	10.85	7.04	0.00	14.63	1.80	8.22	5.29
ማዳመጥና መጻፍ	0.00	0.00		0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	4.11
ማንበብና መናገር	2.85	0.00	1.43	0.00	0.00	0.00	0.715	3.03	0.00	0.00	0.00	
መጻፍና ማንበብ	0.00	0.00		0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	1.51
ጠቅላላ የመማሪያ ዘዴ %	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100

መግለጫ፤

ለየተግባሩ የዋለው ደቂቃ ብዛት ሲካፈል ምልከታ ለተካሄደበት ጠቅላላ ደቂቃ ሲባዛ በመቶኛ ስሌት

ሰንጠረዥ 4.49፣ የገጠር ት/ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመማሪያ ዘዴ

የተማሪዎች የመማሪያ ዘዴ	ትምህርት ቤት ፭			የት/ቤት ፮ መምህርት በ አማካይ	የት/ቤቶቹ አማካይ
	መምህርት ሸ አማካይ	መምህርት ቀ አማካይ	የት/ቤት ፭ አማካይ		
ማዳመጥ %	90.43	100.00	95.21	70.75	82.98
መናገር %	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
ማንበብ %	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
መፃፍ %	6.44	0.00	3.22	15.42	9.32
ማዳመጥና መናገር	0.00	0.00	0.00	14.64	7.32
ማዳመጥና መፃፍ	3.13	0.00	1.57	0.00	0.78
ማንበብና መናገር	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
መፃፍና ማንበብ	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
ጠቅላላ የመማር ዘዴ %	100	100	100	100	100

ሰንጠረዥ 4.50፣ የከተማ፣የከፊል ከተማና የገጠር ት/ቤቶች የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የመማሪያ ዘዴ

የተማሪዎች የመማር ዘዴ	የከተማ ትምህርት ቤት ፩			የት/ቤት ፮ (መምህርነ) አማካይ	የከተማ ት/ቤቶቹ አማካይ	የከፊል ከተማ ትምህርት ቤቶች			የገጠር ትምህርት ቤቶች		
	ት/ ቤት፩ መምህርትተ አማካይ	ት/ ቤት፩ መምህርቸ አማካይ	የት/ቤት ፩ አማካይ			ት/ ቤት ፫ መምህር'ኘ አማካይ	መምህርአ አማካይ	የከፊል ከተማ አማካይ	ት.ቤት ፭ መምህርትከ አማካይ	ት/ቤት ፮ መምህርትኸ አማካይ	የገጠር ት/ቤቶች አማካይ
ማዳመጥ %	65.14	88.06	76.60	100.00	88.30	100.00	100.00	100.00	72.37	58.45	65.41
መናገር %	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
ማንበብ %	6.47	7.09	6.78	0.00	3.39	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
መፃፍ %	2.00	0.00	1.00	0.00	0.50	0.00	0.00	0.00	27.63	0.00	13.81
ማዳመጥና መናገር	9.86	0.00	4.93	0.00	2.46	0.00	0.00	0.00	0.00	41.55	20.78
ማዳመጥና መፃፍ	16.53	4.65	10.59	0.00	5.29	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
ማንበብና መናገር	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
መፃፍና ማንበብ	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
ጠቅላላ የመማር ዘዴ %	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100	100

መግለጫ፤

ለየተግባሩ የዋለው ደቂቃ ብዛት ሲካፈል ምልከታ ለተካሄደበት ጠቅላላ ደቂቃ ሲባዛ በመቶኛ ስሌት

ሰንጠረዥ 4.51 ፣የከፊል ከተማና የገጠር ት/ቤቶች የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የመማሪያ ዘዴ

የተማሪዎች የመማሪያ ዘዴ	የከፊል ከተማት/ቤት			የገጠር ት/ቤት		
	ት/ ቤት ፫ መምህርን አማካይ	መምህር አ አማካይ	የከፊል ከተማ አማካይ	ት.ቤት ፩ መምህርት ከ አማካይ	ት/ቤት ፪ መምህርት ኸ አማካይ	የገጠር ት/ቤቶቹ አማካይ
ማዳመጥ %	100.00	100.00	100.00	72.37	58.45	65.41
መናገር %	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
ማንበብ %	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
መፃፍ %	0.00	0.00	0.00	27.63	0.00	13.81
ማዳመጥና መናገር	0.00	0.00	0.00	0.00	41.55	20.78
ማዳመጥና መፃፍ	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
ማንበብና መናገር	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
መፃፍና ማንበብ	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00	0.00
ጠቅላላ የመማር ዘዴ %	100	100	100	100	100	100

መግለጫ፣

ለየተግባሩ የዋለው ደቂቃ ብዛት ሲካፈል ምልከታ ለተካሄደበት ጠቅላላ ደቂቃ ሲባዛ በመቶ የተሰላ

በተግባቦታዊ ቋንቋ ማስተማር ምልከታ ንድፍ መሰረት የተማሪው የመማሪያ መንገድ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣ ማጻፍና ውህድ እንዲሁም ሌላ የሚሉ ክፍሎች የተካተቱበት ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ አራቱ በእያንዳንዱ የቋንቋ ክሂል የተለማመዱት ለምን ያህል ጊዜ ነው? የሚለውን በሚመለከት መረጃ የተሰበሰበበት ነው፡፡ አምስተኛው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የቋንቋ ክሂሎችን በማዋሃድ የተለማመዱባቸውን ደቂቃዎች መጠን የሚመለከት ነው፡፡ ሌላ የሚለው ከተጠቀሱት ውጭ የሆነ የመማሪያ መንገድ ቢከሰት ለዚያ መመዝገቢያ ተዘጋጅቶ የነበረ ክፍል ነው፡፡

ከላይ በተለያዩ ሰንጠረገሮች (ከሰንጠረዥ 4.48 እስከ 4.51) የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በሁሉም ምድቦች (በከተማ፣ በከፊል ከተማና በገጠር) አብዛኛው የመማር መንገድ በማዳመጥ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በየምድቡ ያለውን እውነታ በተናጠል ስንመለከትም በዘጠነኛ ክፍል በአማካይ በከተማ 89.08%፣ በከፊል ከተማ 85.37% በገጠር 82.98% የሚሆነውን ድርሻ የያዘው ተማሪዎች የቀረበላቸውን ትምህርት እያዳመጡ የሚማሩበት ሂደት ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚናገረው መምህሩ ነው፤ እና አብዛኛውን ጊዜ የምንማረው በማዳመጥ ነው፤ ያሉትን የሚያጠናክር ነው፡፡

በ10ኛ ክፍል ያለው እውነታም ከዚህ ብዙም ልዩነት የለውም፡፡ በሰንጠረዥ 4.50 እንደተመለከተው በአማካይ በከተማና በከፊል ከተማ 100%፣ በገጠር 65.41% የሚሆነውን ጊዜ ተማሪዎች ለማዳመጥ ተግባር አውለውታል፡፡ ከሁለቱ የክፍል ደረጃዎች በገጠር በ10ኛ ክፍል ያለው የመማሪያ መንገዶች በመጠኑ ለየት ይላሉ፡፡ በዚህኛው ምድብ ከሌሎቹ በተሻለ በአማካይ በማዳመጥና በመናገር 20.78%፣ በመጻፍ 13.81% ተማሪዎች መማር ችለዋል፡፡ ሆኖም ቀደም ብሎ በይዘት ክፍል እንደተገለጸው ለመጻፍ ያዋሉት አብዛኛው ጊዜ በተለይ በመምህርት 'ከ' ስለልቦለድ አላባውያንና የልቦለድ ዘዴዎች የሚያጽፏቸውን ማስታወሻ ለመጻፍ የተገለገሉበት መሆኑ ሲጤን ሀሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታን ለማዳበር እንዳልተጠቀሙበት መረዳት ይቻላል፡፡

ሠ. ፈተና መጥቀስ (Test References)

ምልከታ በተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች፣ በቋንቋው ትምህርት መሀል የክፍል ወይም የብሔራዊ ፈተናን የሚመለከቱ ጉዳዮች ማንሳት በአንደኛው መንፈቀ ዓመት ምልከታ በተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች እንደታየው ሁሉ በእነዚህኛዎቹም ተደጋግሞ የተስተዋለ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም በ10ኛ ክፍል ትምህርት ያለው እውነታ በአንደኛው መንፈቀ ዓመት ከታየው የላቀም ነው፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ በትምህርቱ መሀል እንዲህ ያለ ጥያቄ ብትጠየቁ እንዴት ትመልሳላቸው? በብሔራዊ ፈተናው እንዲህ፣ እንዲህ ተብላችሁ ልትጠቁ ትችላላችሁ! እነዚህ፣ እነዚህ በክፍልም በብሄራዊ ፈተናውም ሊመጡ ይችላሉ፣ ወዘተ. ከሚሉ አገላለጾች በተጨማሪ ቀደም ብሎ ለሌላ ዓላማ ሲገለጽ እንደተወሳው፣ ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ራሳቸው ክፍለ ጊዜ ተመድቦላቸው ሲቀርቡ የታዩባቸው ክፍለ ጊዜዎች ብዙ ናቸው፡፡ በዘጠነኛ ክፍልም ቢሆን በትምህርት ቤት አንድ/ ፋሲለደስ፣ በሁለቱም መምህራን፣ በህዳሴ ጠዳ፣ መሸንቲና ሆጤ በሁሉም መምህራን የቴስት ወረቀቶችን መልስ በመስራት፣ በሚቀጥለው ሳምንት ስለሚፈተኑት ቴስት ወይም የማጠቃለያ ፈተና አመጣጥ በማስረዳትና እንዴት መመለስ እንዳለባቸው የአሰራር ስትራቴጂዎችን በማስተማር መልክ የፈተና ጉዳይ ተደጋግሞ ሲነሳ ተስተውሏል፡፡ ይህም በተለይ አርመው ከሚመልሱላቸው የቴስት ወረቀቶችና በቀጣዩ ሳምንት ስለመሚፈተኑት ፈተና ከሚሰጠው ማብራሪያ ጋር ተገናዝቦ ሲታይታመምህራኑ ተማሪዎቻቸውን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ለማዘጋጀት የሚያደርጉት ጥረት አካል ነው ማለት ይቻላል፡፡

ረ. የትምህርት መሳሪያዎች (Materials)

በዚህ ጥናት በተካሄዱት የክፍል ምልከታዎች በተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት መገለጫነት ከሚታወቁት የትምህርት መሳሪያ ዓይነቶች መካከል መምህራኑና ተማሪዎቹ የተለያዩ ፕዳጎጂዊና ከፊል ፕዳጎጅካል የሚባሉ ማቴሪያሎችን እንደሚጠቀሙ ማረጋገጥ ተችሏል። በሌላ በኩል ደግሞ መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎቹ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ማዳበር የሚያስችሉ ሌሎች ተፈጥሯዊ/ ፕዳጎጂዊ ያልሆኑ የጽሑፍም ሆነ ሌላ ዓይነት መሳሪያዎችን እንደማይጠቀሙ ለመረዳት ተችሏል። መሳሪያዎችን የሚጠቀሙበት ዋነኛው ዓላማም ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት ነው። ይህም በቀጣዩ ክፍል በቀረበው ከክፍል ምልከታ በኋላ ከመምህራኑ ጋር በተካሄዱት ቃለ መጠይቆች በተገኙ መረጃዎች ይበልጥ ተዘርዝሮና ተብራርቶ ቀርቧል።

4.6.3 ከክፍል ምልከታዎች በኋላ ከመምህራን ጋር በተካሄዱ ቃለ መጠይቆች የተሰበሰበ መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ከክፍል ትምህርት ምልከታ በኋላ ምልከታ ከተካሄደባቸው መምህራን ጋር ቃለ መጠይቅ በማካሄድ ስለማስተማር-መማር ሂደቶች ተጨማሪ መረጃ መሰብሰብ በጥናቱ ታቅዶ የነበረ ጉዳይ ነው። በዚሁ መሰረት የታሰበውን ያህል ባይሳካም በዘጠነኛ ክፍል 10፣ በ10ኛ ክፍል 17 የክፍል ምልከታዎች ላይ የተመሰረቱ ቃለ መጠይቆች ምልከታ ከተካሄደባቸው ዘጠኝ መምህራን ጋር ቃለመጠይቆችን ማካሄድ ተችሏል። በቃለመጠይቆቹ የተሳተፉት መምህራንም ከቅዳሜ ገበያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ ወንድና አንድ ሴት፣ ከመሸንቲ ሁለት ሴቶች፣ ከፋሲለደስ ሁለት ወንድና ሁለት ሴት፣ ከህዳሴ ጠዳ አንድ ሴት እና ከአዘዞ አንድ ወንድና አንድ ሴት ናቸው። አራቱ ዘጠነኛ፣ አምስቱ ደግሞ 10ኛ ክፍል ሲያስተምሩ ምልከታ የተካሄደባቸው መምህራን ናቸው። ከመካከላቸው ሁለቱ (አንድ ወንድና አንድ ሴት) ዐይነ-ስውራን ናቸው።

በእነዚህ መምህራን ለቃለ መጠይቆቹ መሰረት በሆኑት ምልከታ በተካሄደባቸው 27 ክፍለ ጊዜያት በዘጠነኛም ሆነ በ10ኛ ክፍል ትምህርቶች የተሸፈኑት ይዘቶች በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው። ለምሳሌ የሚከተሉት የሰዋስው፣ የሥነ-ጽሑፍና የክሂል ትምህርት

ይዘቶች ምልከታ በተካሄደባቸው ክፍለ ጊዜያት፣ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የቀረቡ ናቸው።።

አንደኛ፣ ሰዋስውን በሚመለከት ከምዕላድ (የምዕላድ ምንነትና አገልግሎት፣ ከቃላት (እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ)፣ ከሐረግ (የሐረግ ምንነት፣ መሪ ቃልና የሐረግ አይነቶች)፣ ከዐረፍተ ነገር (የዐረፍተ ነገር ክፍሎችና ዓይነት)፣ ሁለተኛ፣ ሥነ-ጽሑፍን በተመለከተ፤ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ዘይቤ፣ ፈሊጦች፣ ቅኔ (የቅኔ ምንነት፣ ሰምና ወርቅና የቅኔ መፍቻ ዘዴዎች)፣ ሦስተኛ፣ የንባብ ክሂልን በተመለከተ፣ አንብቦ መረዳት (ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ ተግባራት) እና ዐውዳዊ ፍቺ፣ አራተኛ፣ ከመጻፍ ክሂል የሥራ ደብዳቤ፣ የሚሉት በሁለቱም ክፍሎች ምልከታዎች ሲካሄዱ መምህራኑ ያስተማሯቸው ይዘቶች ናቸው።።

በዘጠነኛ ክፍል ብቻ የተሸፈኑ ርዕሶች/ ይዘቶች ከሰዋስው የቃላት መጥበቅና መላላት፣ አያያዦችና መሸጋገሪያዎች፣ ከሥነ-ጽሑፍ፣ ሥነ-ግጥም (የግጥምና ዝርው ጽሑፍ ልዩነት፣ ጅምር ስንኞችን ማሟላት)፣ ከመጻፍ ክሂል ገላጭ ድርሰት የሚሉት ሲሆኑ በ10ኛ ክፍል ብቻ የቀረቡት ደግሞ ከሰዋስው፤ ነፃና ጥገኛ ምዕላዶች፣ ቃላት መመስረት፣ በቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ዐረፍተ ነገር መመስረት፣ ከሥነ-ጽሑፍ፤ ቃላዊ ግጥሞች፣ ከንግግር፤ መመሪያን ተከትሎ መከራከር፣ ከመጻፍ ክሂል፤ ሥዕላዊ ድርሰት፣ ማስታወሻ አያያዝና ሥርዓተ ነጥብ የሚሉት ናቸው።።

ከመምህራኑ ጋር የተካሄዱት ቃለ መጠይቆች የመጀመሪያው ጥያቄ ስለየዕለቱ ትምህርት ዓላማዎች የሚጠይቅ ነው።። በቃለመጠይቆች የተሳተፉት መምህራን ለዚህ ጥያቄ የሰጡት ምላሽም የየዕለቱ ትምህርቶች ዓላማዎች ከተዘረዘሩት የትምህርት ይዘቶች ጋር የተያያዙ መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው።። ምላሻቸው በይዘቶቹ አማካኝነት የሚቀርብላቸውን ትምህርት ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ ተፈላጊውን የባህርይ ለውጥ እንዲያመጡ ለማድረግ ነው የሚል ነው።። ለምሳሌ የሐረግ ዓይነቶች የሚለውን ያስተማሩ መምህራን የትምህርቱ ዓላማ ነው ብለው የገለፁት፣ ተማሪዎች ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ የሐረግ ዓይነቶችን ይለያሉ /መለየት ይችላሉ የሚለውን ነው።።

ለሁለተኛውና ለሦስተኛው ጥያቄ ማለትም የየዕለቱን ትምህርት እንዴት ማቅረብ/ ምን ምን ዘዴዎችን ተጠቅመው ትምህርቱን ለማቅረብ አስበው እንደነበረና ባሰቡት መሰረት ትምህርቱን ማቅረብ ችለናል ብለው ያምኑ እንደሆነ ለተጠየቁት ጥያቄ ከንባብ ክሂል በስተቀር ሌሎች ትምህርቶችን በተመለከተ የሰጡት ምላሽ ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁሉም ዋነኛ የማስተማሪያ ዘዴያቸው ገለፃና አልፎ አልፎ በገለፃ መሀል ጥያቄና መልስን በመጠቀም እንደሚያስተምሩ ነው ያረጋገጡት፡፡ በምልከታዎቹ የታየውም በመምህራኑ የተገለፀውን የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ የንባብ ክሂል ትምህርትን በተመለከተ ግን አንዳንዶቹ ተማሪዎችን በለሆሳስ በማስነበብ፣ አንዳንዶቹ የመጽሐፍ እጥረት ስላለ በሚል ምክንያት ተማሪዎችን ተራ በተራ እያስነሱ ለክፍሉ ተማሪ በማስነበብ ለማቅረብ አቅደው እንደነበረና እቅዳቸውን ባለመ.ት መሰረት ተግባራዊ ማድረግ መቻላቸውን አስረድተዋል፡፡ በክፍል ምልከታዎቹ የታየውም ይኸው የተለመደ የንባብ ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴያቸው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ አንድ መምህር ደግሞ ተማሪዎችን ለማስነበብ ጊዜው ስለማይበቃ ራሳቸው አንብበው ወደ መልመጃዎቹ ሊሻገሩ መቻላቸውን ተናግረዋል፡፡

ሌሎች ትምህርቶችን በተመለከተ (የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ሳይቀር) ለምን ይበልጥ ገለፃን በመጠቀም ለማስተማር እንደመረጡ ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስም የተማሪው ብዛትና ፍላጎት እንዲሁም የጊዜ እጥረት እንዲህ ያለውን አቀራረብ እንዲመርጡ እንዳስገደዳቸው ገልፀዋል፡፡

ምልከታ በተካሄደባቸው ዕለታት ያስተማሯቸው ትምህርቶች ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ውጤታማ እንዲሆኑ ወይም የፈተናውን ጥያቄዎች በቀላሉ መመለስ እንዲችሉ የሚያግዛቸው ነገር ይኖር ይሆን? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ደግሞ አብዛኞቹ (ከ90%) በላይ የሚሆኑት ትምህርቶቹ ተማሪዎችን የማጠናቀቂያ ፈተናውን ለመስራት እንዲችሉ በደንብ ያግዟቸዋል የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዘጠኙ መካከል አንዷ ብቻ ‹‹የቋንቋው ትምህርት አንድ አካል ሆኖ እስከ ቀረበ ድረስ እኔን የሚመለከተኝ እዚያ ያለውን መግለፅ ነው፡፡›› ሲሉ፤ አንድ ሌላ መምህር ደግሞ በእለቱ ካስተማሯቸው ሁለት ጉዳዮች አንዱ ማለትም ስለጽህፈት ያስተማሩት ተማሪዎችን ለሕይወታቸው እንጂ ለፈተናው አይጠቅማቸውም፤ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የቀሩት የዘጠነኛም ሆኑ የ10ኛ ክፍል መምህራን በሙሉ (ቃለ መጠይቆቹ በተናጠልና በየዕለቱ ትምህርት ላይ ተመስርተው

የተካሄዱ ቢሆኑም) ሁሉም ትምህርቶች ተማሪዎቻቸውን ለማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያዘጋጇቸው መሆናቸውን ተናግረዋል። ሌላው ቀርቶ መመሪያን ተከትሎ መከራከር በሚል ርዕስ ተማሪዎቻቸውን እንዲከራከሩ ሲያደርጉ ምልከታ የተካሄደባቸው መምህርት እንኳ በቃለ መጠይቁ የሰጡት መልስ የክርክር ሥርዓትን ተከትለው እንዲከራከሩ ሲደረግ በፈተናው የሚካተቱትን ክርክር-ነክ ጥያቄዎች ለመመለስ ያስችላቸዋል የሚል ነው። ከዚሁ ጋር አያይዘውም በትምህርቱ መግቢያና ማጠቃለያ የክርክር ሥርዓትን/ መመሪያን ትኩረት ሰጥተው ያስተማሩትም ተማሪዎች መመሪያውያን በደንብ እንዲረዱትና በፈተናው ስለክርክር የሚጠየቁትን ጥያቄዎች መመለስ እንዲችሉ ለማገዝ እንደሆነ ገልፀዋል። እንደ እኒህ መምህርት እምነትም ተማሪዎቻቸውን ከሀገሪቱ ተማሪዎች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ የሚቻለውም በዚህ መንገድ በማስተማር ነው።

በአጠቃላይ በቃለ መጠይቆቹ የተሳተፉት መምህራን የየዕለቱን ትምህርት በተመለከተ ለማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎችን በማዘጋጀት ረገድ ለምንና እንዴት እንደሚረዳቸው የገለጿቸው ሀሳቦችና ማስረጃዎች ደግሞ እንደሚከተለው ተጨምቀው ቀርበዋል፤

አንደኛ የመፃፍ ክሂልን በተመለከተ፤ሥርዓተ ነጥቦች በፈተናው ይጠየቃሉ፤ አንደኛ ትክክለኛ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም እንዲለዩ፣ ሁለተኛ፣ ክፍት ቦታ ያደርግና እዚህ ቦታ ምን ዓይነት ሥርዓተ ነጥብ ብንጠቀም ተገቢ ይሆናል? የሚል ይጠየቃል። ማስታወሻ ስለመያዝ ደግሞ፤ ለምሳሌ ማስታወሻ ስትይዙ አንደኛ የሚከናወኑ ተግባራት፣ ሁለተኛ የሚያስፈልገው ነገር፣ ሦስተኛ ቅደም ተከተሉ ትክክል የሆነው በየትኛው አማራጭ የቀረበው ነው? እየተባለ ይጠየቃል። ስለድርሰት ደግሞ፣ ምን ዓይነት ድርሰት ነው የቀረበው? ምንባቡ በምን የድርሰት ዓይነት የተፃፈ ነው? እያለ ይጠይቃል።

ሁለተኛ የንባብ (የአንብቦ መረዳት) ክሂልን በተመለከተ፤

- በፈተናው ምንባብ ይቀርባል፤ በዝርውም በግጥምም ያቀርባል፤ ዛሬ የተማሩት ለዚያ መለማመጃ ይሆናቸዋል።
- በማጠናቀቂያ ፈተናው ምንባብ ይቀርብና ይህ ሀሳብ በየትኛው አንቀፅ ነው ያለው? ምንባቡ የትኛውን የድርሰት ዓይነት ይወክላል? የሚሉ ዓይነት ጥያቄዎች

ይጠየቃሉ:: በእለቱ የተማሩት ትምህርት እንዲህ ያሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችላቸዋል::

- በማጠናቀቂያ ፈተናው የምንባቡን ዐውድ ተከትለው የሚፈቷቸው ቃላት ይቀርባሉ:: ቃላቱን በዐረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባትም ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ይጠየቃሉ:: የዕለቱ ትምህርት እንዲህ ያሉ ጥያቄዎችን ለመስራት ያስችላቸዋል::

ሦስተኛ ሰዋስውን በተመለከተ፣

- በፈተናው የምዕላዱ ዓይነት (ነፃ፣ ጥገኛ) ይጠየቃል፣ የተጨመሩትን ቅጥያዎች እንዲለዩ ይጠየቃል:: የምዕላድ ተግባር ይጠየቃል፣ እንዲህ ያሉ ጥያቄዎችን ለመስራት የዛሬው ትምህርት ተማሪዎችን ያግዛቸዋል::
- በማጠናቀቂያ ፈተናው ዐረፍተ ነገር ሰጥቶ የቃል ክፍሉን (ስም፣ ግስ፣ ወዘተ.) እያሉ እንዲለዩ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ይካተታሉ፤ የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ለምሳሌ የዚህ ቃል ተመሳሳይ፣ የዚህ ቃል ተቃራኒ የትኛው ነው? እየተባለ ይጠየቃል፤ ልዩ የሆነው ቃል የቱ ነው? እየተባለም ይጠየቃል፤ የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ እየተባለ ይጠየቃል፤ የተማሩት ትምህርት እንዲህ ያሉ ጥያቄዎችን ለመስራት የሚያስችላቸው ነው::
- በማጠናቀቂያ ፈተናው ለምሳሌ ሐረግ ተሰጥቷቸው ዓይነቱን ሊጠይቅ ይችላል፤ ዐረፍተ ነገር ሰጥቶ በዐረፍተ ነገሩ ውስጥ ሐረጉን ሊጠይቅ ይችላል፤ የቃል ክፍል ሰጥቶ ይህን መሪ አድርጎ ምን ዓይነት ሐረግ ሊመሰረት ይችላል ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል:: ስለዚህ እንዲህ ያሉ ጥያቄዎችን ለመስራት የእለቱ ትምህርት ያግዛቸዋል::
- በፈተናው የዐረፍተ ነገር ዓይነት በቅርፅ ተራና ውስብስብነት፣ በአገልግሎት ሐተታዊነት፣ ጥያቄያዊነት፣ ትዕዛዛዊነት ይጠየቃል:: ለምሳሌ ዐረፍተ ነገሮችን ይሰጥና የትኛው ተራ ነው? የትኛው ውስብስብ ነው? የትኛው ትዕዛዛዊ ነው? ብሎ ይጠይቃል:: ወይም ከሚከተሉት ትዕዛዛዊ ወይም ተራ ወይም ውስብስብ የሆነው የትኛው ዐረፍተ ነገር ነው? በሚል መንገድ ይጠይቃል:: የዐረፍተ ነገር ክፍሎችን የሚመለከቱ ጥያቄዎችም ይጠየቃሉ:: ለምሳሌ ሙሉ ዓረፍተ ነገር ይሰጥና የተሰመረበትን ሐረግ ዓይነት ለዩ ተብሎ ይጠየቃል:: እንዲህ ያሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተማሪዎች ስለሐረግና ዐረፍተ ነገር መማር አለባቸው::

አራተኛ ሥነ-ጽሑፍን በተመለከተ፣

- ሥነ-ቃሎችና ምሳሌያዊ አነጋገሮች በፈተናው ስለሚጠየቁ እንዲህ ያለ ትምህርት መማራቸው ፈተናውን ለመስራት ያግዛቸዋል። ሥነ-ቃሎችን በሚመለከት ከሥነ-ቃል ባህሪያት አንፃር፣ ከመልዕክቱ አንፃር፣ ከምደባው አንፃር ይጠየቃል። ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በተመለከተ ደግሞ አንደኛ በፍቺ የተለዩ የሆኑትን እንዲለዩ ይጠይቃል፤ ሁለተኛ ጅምር ሰጥቶ የሚጨርሰውን ይጠይቃል፤ ሦስተኛ በፍቺ የሚመስላቸውን/ የሚቃረናቸውን ይጠይቃል፤ አራተኛ፣ ሐተታ ይሰጥና በምሳሌያዊ አነጋገር በአጭሩ የሚገልፀው የትኛው ነው? እያለ ይጠይቃል፣ አምስተኛ፣ ከወቅቱ ጋር ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን በሚመለከት ይጠይቃል። ስለዚህ ሥነ-ቃልና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን መማራቸው አስፈላጊ ነው።
- ፈሊጦችም እንዲሁ በፈተናው ይጠየቃሉ። ባለፈው ራሱ ባህር-ወለድ የሚለው ከመማሪያ መጽሐፍ ተወስዶ በፈተናው ተጠይቋል። ስለዚህ ፈሊጦችን መማራቸው ፈተና ለመስራት ይጠቅማቸዋል(ይረዳቸዋል)። ከዚህ በተጨማሪ የፈሊጥ ፍቺ በዐውድ ይጠየቃል። ቀጥተኛ ፍቺ ይጠየቃል፣ ፈሊጥ ያልሆነውን ለዩ ብሎ ይጠይቃል።
- ስለ ዘይቤ ይጠየቃል፣ የዘይቤ ዓይነት ይጠየቃል፣ አንዳንድ ጊዜ በዘይቤ የተገለፀውን መልዕክት ይጠየቃል። ስለዚህ ስለዘይቤ መማራቸው ተማሪዎችን ፈተና ለመስራት ያግዛቸዋል።
- ስለልቦለድ በደንብ ይጠየቃል። ማስታወሻ ባጻፍኳቸው በልቦለድ አላባውያንና ዘዴዎች ዙሪያ በፈተናው ጥያቄዎች ይጠየቃሉ፣ በቀጥታ ይጠየቃሉ። በተደጋጋሚ መጥተዋል። ለምሳሌ ከአላባውያን ገጸ-ባህርያት የሚንቀሳቀሱበት ቦታና ጊዜ ተጠይቆ ያውቃል። አንቀፅ ሰጥቶ በየትኛው የአተራረክ ዘዴ ነው የቀረበው? የሚል ጥያቄ መጥቷል። የልቦለድ ጭብጥ ይጠየቃል። ባለታሪኮች ምን ይባላሉ ወዘተ እየተባለ ይጠየቃል።

እነዚህ በመምህራኑ የተገለፁት ማስረጃዎች መምህራኑ በፈተናው የሚጠየቁትን/ ሊጠየቁ የሚችሉ ክፍሎችን እንዴት በጥልቀት እንደሚያውቋቸው የሚያሳዩ ብቻ ሳይሆኑ የሚያስተምሩት በፈተና የሚመጡ ጉዳዮችን ብቻ እንደሆነም ፍንጭ የሚሰጡ ናቸው። ፈተና አስቤ አላስተምርም ያሉት መምህርት ራሳቸው ያስተማሩት ትምህርት ለፈተና

እንዴት እንደሚያግዝ ሲገልፁ መታየታቸው ሁሉም በሚባል ደረጃ በፊተናው ተፅዕኖ ስር እንደወደቁ የሚያመለክት ነው ማለት ይችላል፡፡ መምህራኑ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው ግንዛቤና በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባሮችም ምን ያህል ትይዩ/ ተደጋጋፊ እንደሆኑ በክፍል ምልከታም ሆነ ከምልከታ በኋላ ከመምህራኑ ጋር በተካሄዱት በእነዚህ ቃለ መጠይቆች የተገኙት የጥናቱ ውጤቶች በግልጽ አሳይተዋል፡፡ በመምህራኑ ግንዛቤና ተግባራት መካከል የሚጣረስ ነገር እንደሌለ በሁሉም መንገድ የተካሄዱት የውጤት ትንተናዎች አሳይተዋል፡፡

በየዕለቱ ምን ምን አጋዥ የትምህርት መሣሪያዎች እንደተጠቀሙ ለተጠየቁት ጥያቄ ደግሞ ሰዋስውን ለማስተማር፤ የጌታሁን አማረን <u>የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ</u> የባዩ ይማምን <u>የአማርኛ ሰዋስው፤</u> ለቃላት የየሻው ተሰማን <u>ልሳነ ሰብዕ ከመልሳነ ብዕር</u>፡ የተለያዩ መዝገበ ቃላትን፣ ለሥነ-ጽሑፍ፤ የዘሪሁን አስፋውን <u>የሥነ ጽሑፍ መሰረታውያን</u>፡ የምሳሌያዊ አነጋገር መጽሐፎችን፣ የዳኛቸውና አምሳሉ <u>የአማርኛ ፊሊጣዊ አነጋሮችን፣</u> ለመጻፍ ክሂል በተለይም ለሥርዓተ ነጥብ <u>የቀለም ጠብታን፣</u> ለሁሉም ይዘቶች ደግሞ ከ7-10 እና ከ9-10 የሚሉና የፈተና ጥያቄዎችን የሚሰሩ መጽሐፎችን እንደተጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ ለክሂል ትምህርት (ያውም ለሥርዓተ ነጥብ ብቻ ነው) አጋዥ መጽሐፍ እንደተጠቀሙ የተጠቆመው፡፡ ያውም አንድ መጽሐፍ ብቻ ነው፡፡

በአብዛኛዎቹ ምልከታ በተካሄደባቸው ክፍሎች (በሙከራ ጥናቱ ጭምር) ብዙ ጊዜ በመጻፎቹ የተካተቱ መልመጃዎች ሲዘለሉ ታይቷል፡፡ በተለይ በዋናው ጥናት ለምልከታ ሲገባ መማሪያ መጽሐፎችን ይዞ የመግባት ነገር ስለነበር የሚዘለሉ ክፍሎችን በቀላሉ ለመለየት ተችሏል፡፡ በክፍል ምልከታዎቹ ማስተዋል እንደተቻለው አንድን መልመጃ እንዳለ ወይም ከመልመጃዎቹ ውስጥ የተወሰኑ ጥያቄዎችን መዝለል የተለመደ ክስተት ነበር፡፡ በተለይ ተማሪዎች እንዲወያዩ፣ በሆነ ርዕስ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ፣ ረቂቅ፣ ቢጋር፣ አንቀፅ፣ ዘገባ፣ ደብዳቤ፣ ድርሰት ወዘተ እንዲጽፉ የሚያዙ ጥያቄዎች/ መልመጃዎች በተደጋጋሚ ይዘለላሉ፡፡ በመሆኑም ከክፍል ምልከታዎች በኋላ በተካሄዱት ቃለ መጠይቆች እነዚህ፣ እነዚህ መልመጃዎች/ ጥያቄዎች ለምን ተዘለሉ? የሚል ስድስተኛ ጥያቄ እንዲጠየቅ ተደርጓል፡፡ ለዚህ ጥያቄ የተሰጡ ዋና ዋና ምላሾችም የሚከተሉት ናቸው፤

- ከክሂል ጋር የተያያዙ ተግባራዊ ትምህርቶችን ለመማር/ለመስራት ብዙ ጊዜ ተማሪዎች ፈቃደኛ አይሆኑም፡፡ ለምሳሌ መጻፍ ቁጭ ማለትን፣ ሀሳብ ማፍለቅን ይጠይቃል፡፡ ይህን ማድረግ አይፈልጉም፡፡ ሰዋስው ግን የክሂሎችን ያህል ጊዜ አይፈልግም፡፡
- የጽሑፍና የንግግር ይዘት የተዘለሉት በጊዜ እጥረት ነው፤ በፈተናው የሚካተቱትን ቅድሚያ ሰጥቶ ለመሸፈን ነው፡፡
- ጊዜው በደራሽ ስራዎችና ስብሰባዎች ስለሚታወክ በቅድሚያ በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚካተቱን ለመሸፈን ነው፡፡
- መናገር፣ መጻፍ፣ ለመማር ተማሪዎች ፍላጎት የላቸውም፡፡
- ክሂሎችን ለመመዘንም አስቸጋሪ ነው፡፡ የማንመዝነውን ደግሞ ማስተማር የለብንም፡፡
- የመናገር፣ የማዳመጥና የመጻፍ ክሂሎችን 1ኛ በየክፍሉ ብዙ ተማሪ ስላለ፣ 2ኛ የተመደበው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ ስለሆነ አናስተምራቸውም፡፡
- ክሂል-ነክ ትምህርቶች ጊዜ የሚፈልጉ ወይም ጊዜ የሚወስዱ ስለሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ክርክር የመለማመጃ ጊዜ ይፈልጋል፤ ለማቅረብም ሰፋ ያለ ጊዜ ይወስዳል፡፡
- ሰዋስው፣ ቃላት፣ ሥነ-ጽሑፍ በፈተና የሚካተቱ ናቸው፡፡ እነዚህን ካልተማሩ የፈተና ውጤታቸው ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ክሂሎቹ በፈተና የሚካተቱ አይደሉም፡፡

4.6.4 በጽሑፍ መጠይቅ፣ በተደራጀ የክፍል ምልከታና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ውህዳዊ የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ጥናት ስለመምህራን የማስተማር ባህርያት በጽሑፍ መጠይቅ፣ አጠቃላይ የማስተማር-መማር ሂደቶችን በተመለከተ ደግሞ የተደራጀ የክፍል ምልከታንና ከምልከታ በኋላ ስለእየዕለቱ ትምህርት የተወሰኑ ጉዳዮችን በሚጠይቅ ከፊል-ነጻ-ቃለ መጠይቅ ከአራት የዘጠነኛና ከአምስት የ10ኛ ክፍል መምህራን መረጃ ተሰብስቧል፡፡ መረጃው ከተሰበሰበ በኋላም በጽሑፍ መጠይቅና በክፍል ምልከታ የተሰበሰሰው መረጃ በመጠናዊ በተለይም አማካይን በመጠቀም፣ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰበው ደግሞ በዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልቶች ተተንትነዋል፣ የውጤት ትንተናዎቹም ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

ተተንትነውና ተብራርተው የቀረቡት መረጃዎች በጋራ እንዳሳዩትም ጠንካራ የሚባሉ በማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ ምክንያት የተከሰቱ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ የማስተማር-መማር ባህርያት እየተከሰቱ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ እነዚህ፣ በጥናቱ የተገኙ በፈተናው ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰቱ የማስተማርና የመማር ባህርያት ምን ምን እንደሆኑ ተጨምቀው ከመጠነኛ ማብራሪያ ጋር እንዲቀርቡ ተደርገዋል፡፡

- መምህራኑ ሲያስተምሩ ተማሪዎቹ ሲማሩ በአጠቃላይ በሀገሪቱ ትምህርት ፓሊሲ የሥርዐተ ትምህርት ማዕቀፍና በቋንቋው ሥርዓት ትምህርት መሰረት ለቋንቋው ክሂሎች ትኩረት አይሰጡም፡፡ በተግባቦታዊ ቋንቋ ማስተማር መርህ መሰረት ተማሪዎቹ በቋንቋ ክሂሎች ሰፊ ልምምድ እንዲያደርጉ ሲደርግ አልተስተዋለም፡፡ ይህም በተዛማጅ ጽሑፎች ክፍል በ2.1 እንደተገለጸው ፈተናዎቹ በሌላው ዓለም ከ1940ዎቹ እስከ 1960ዎቹ ይዘጋጁ እንደነበሩት ፈተናዎች ተግባቦትን ሳይሆን ዕውቀትን በመመዘን ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው እየተፈጠረ ያለ ችግር ነው ብሎ ለመደምደም ያስችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ይመስላል፣ በመማር ማስተማር ሂደቶቹ በአብዛኛው ክፍለ ጊዜያት ረጅሙን ድርሻ የሚይዙት ተማሪዎች ሳይሆኑ መምህራኑ ናቸው፡፡
- የግልና የቡድን ስራዎች (የጥንድ ስራን ጨምሮ) ብዙም አይበረታቱም፡፡ አልፎ አልፎ ሲሰጡም ተማሪዎቹ በትክክል ምን መስራት እእንዳለባቸው ግልፅ መመሪያ አይሰጣቸውም፡፡ የሚሰሩትን በግልፅ ባለማወቃቸው ይሁን በሌላ ምክንያት ተማሪዎችም በቡድን የመስራት ዝንባሌ አያሳዩም፡፡
- ከተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት መርህ በተቃራኒ ብዙ የሚናገሩት ተማሪዎች ሳይሆኑ መምህራኑ ናቸው፡፡ የዚህም አንዱ መንሰኤ የማጠናቀቂያ ፈተናው እንደሆነ ከተማሪዎችና ከመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቆች፣ ከክፍል ምልከታዎችና ከክፍል ምልከታ በኋላ ከመምህራን ጋር የተካሄዱት ቃለ መጠይቆች የተገኙት መረጃዎች ውጤት ትንተናዎች አሳይተዋል፡፡
- የጥናቱ ውጤት እንዳመላከተው፣ ክመማሪያ መጽሐፎቹ የሚዘለሉ ክፍሎች አሉ፡፡ መምህራን በመማሪያ መጽሐፎቹ ውስጥ ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎች ተጨማሪ መልመጃዎችን ለተማሪዎቻቸው እያዘጋጁ የሚሰጡባቸው አጋጣሚዎችም አሉ፤ ተማሪዎች ተጨማሪ መጽሐፎቹን እንዲያነቡ መጻሕፍት የሚጠቆሙባቸው ይዘቶችም አሉ፡፡ የማይጠቆሙባቸውም አሉ፡፡ የዚህ ዋና ምክንያት የማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ እንደሆነ የዓይነተዊና መጠናዊ የመረጃ ትንተና ውጤቶች አሳይተዋል፡፡

- የጥናቱ ውጤት እንዳሳየው በማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ምክንያት፣ ከመማሪያ መጽሐፉቹ ውስጥ በሳጥን በሳጥን ከተቀመጡት ማስታወሻዎች በተጨማሪ መምህራኑ፣ ራሳቸው አዘጋጅተው ማስታወሻ የሚያጽፏቸው ርዕሰ ጉዳዮች አሉ። በመማሪያ መጽሐፎቹ ከቀረቡት መካከልም የሚያልፏቸው/ የማያስተምሯቸው ክፍሎች አሉ።
- ተማሪዎቹ የቤት ስራ ሲሰጣቸው በታዘዙት መሰረት የማይሰሯቸው መልመጃዎች አሉ። የዚህም አንዱ ምክንያት ስለሚከብዳቸው ሊሆን ቢችልም ሌላው ምክንያት ግን በማጠናቀቂያ ፈተናው ስለማይካተቱ እንደሆነ መምህራኑ በቃለመይቆቹና በቡድን ውይይቶቹ አረጋግጠዋል።ታ

እነዚህ የማስተማርና መማር ባህርያት በሙከራ ጥናቱ ወቅትም ሆነ በዚህ በዋናው ጥናት የታዩ ክስተቶች ናቸው። ክስተቶቹም በሁለቱም መንፈቀ ዓመቶች የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራኑና በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ባህርያት/ የማስተማር መማር ተግባራት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር የሚያሳዩ ናቸው። የወሸባክ ባህርያቱ በመጀመሪያው መንፈቀ ዓመትም ሆነ በሁለተኛው መንፈቀ ዓመት መከሰታቸውም በቋንቋው ትምህርት ወሸባክ መከሰት የሚጀምረው ገና ትምህርቱ ሲጀመር ጀምሮ እንደሆነ የሚያመላክት ነው። ተፅዕኖውም በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችና መምህራን ላይ ሳይቀር የሚንፀባረቅ ነው። በተለይ በዓመቱ ማብቂያ ወራቶች ደግሞ የተፅዕኖው ደረጃ ከፍ እያለ ይሄዳል።

በአጠቃላይ በፈተናው የሚከሰተው ተፅዕኖ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጉዳዮችን መለየት በፈተናው ትኩረት የማይሰጣቸውንና ትኩረት እያጡ የመጡትን እንዲሁም ትኩረት እያገኙ የመጡትን አዳዲስ ጉዳዮች/ ክፍሎች መለየት፣ በልየታዎቹ መሰረትም በየዓመቱ በሚዘጋጁ ፈተናዎች ትኩረት እያገኙ የመጡትን ትኩረት እየሰጡ ማስተማር፣ በክፍል ውስጥ በፈተናዎች ላይ ዝርዝር ውይይት ማካሄድ፣ ትምህርቱ በፈተናው በሚካተቱ ጉዳዮች ላይ እነዲያተኩር በተማሪዎች ተደጋጋሚ ግፊትና ጫና መደረግ፣ በፈተናው የሚካተቱ ትምህርቶችን በተመለከተ ከመማሪያ መጽሐፎቹ በተጨማሪ ሌሎች ማጣቀሻ መጻሕፍትን መምህራኑ እየተጠቀሙ እንዲያስተምሩ ጫና መፍጠር፣ በቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸውን የቋንቋው ክሂሎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ተገቢ ቦታ እንዳያገኙ ማድረግ፣ በማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅእኖ ምክንያት የተከሰቱ ክስተቶች እንደሆኑ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች (በቡድን ውይይቶቹ ጭምር) የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት ትንተና አሳይቷል። ግኝቶቹም ወላዊነት

የሚታይባቸው ናቸው፣ ከቦታ ቦታ ወይም ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ልዩነት የሚታይባቸው አይደሉም፡፡

4.7 በውጫዊ (macro) የትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ስለሚያሳድሩት ተፅዕኖ በቡድን ከተካሄዱ ወይይቶችና ከሰነድ የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በምዕራፍ ሦስት እንደተጠቀሰው የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ውጫዊ (macro) ወሽባክ ለመፈተሽ በጥናቱ ከታቀፉት ዞኖችና የዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤቶች መካከል ሁለት የዞን ከተማ አስተዳደርና (ባህር ዳርና ደሴ) ሁለት የዞን ትምህርት መምሪያዎች (ደቡብ ወሎና ሰሜን ጎንደር) በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በእነዚህ መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ የሥርዓተ ትምህርት፤ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተና ክፍል ኃላፊዎች በቡድን ውይይቶች እንዲሳተፉ ተደርገዋል፡፡ እነዚህ ክፍሎች የተመረጡትም ከመማር-ማስተማርና ከፈተና ምዘና ጋር ባላቸው ቀጥተኛ ግንኙነት መስፈርትነት ነው፡፡ ከአራቱ የአንዱ የፈተና ክፍል ተጠሪ በውይይት ለመሳተፍ ባለመቻላቸው የመምሪያው የዕቅድ ክፍል የፈተና ክፍሉን ስራና አሰራሩን ያውቁታል ተብለው የፈተና ክፍሉን ወክለው በውይይቱ ተሳትፈዋል፡፡ ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችም በሚከተሉት ንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍለው ተተንትነዋል፤ የተገኙት ውጤቶችም ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

የትምህርት ጥራትን ማሻሻል

ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ተሳታፊዎች እንዳስረዱት ከዚህ ቀደም ከፍተኛ ትኩረት ይሰጥ የነበረው ለትምህርት ተደራሽነት ነበር፡፡ አሁን ግን ጥራት ላይ በማተኮር እየተሰራ ነው፡፡ ለምሳሌ ባለሙያ፩ “በዞንም እንደ ሀገርም እየተሰራ ባለው ሁኔታ የትምህርት ጥራት የወቅቱ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው” ይላሉ:: በዚህ ሐሳብ በአራቱም ውይይቶች የተሳተፉ ተወያዮች ይስማማሉ፡፡ በተወያዮቹ እንደ ተንፀባረቀው በዞናቸው ብሎም በክልልና በሀገር ደረጃ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ከክልል ትምህርት ቢሮ በተሰጣቸው አቅጣጫ መሰረት በእቅድ እየተመሩ የሚከተሉትን ተግባራት እያከናወኑ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ እየተሰራ ያለ ተግባር ነው ተብሎ በውይይቶቹ የተጠቀሰው ስድስት መርሐ ግብሮች በሀገር ደረጃ ተቀርፀው እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ወርደው እንዲተገበሩ የማድረግ ጉዳይ ነው። ከስድስቱ የትምህርት ጥራት መርሐ ግብሮች መካከል ደግሞ የትምህርት ቤት መሻሻል መርሐ ግብር (SIP) ላይ የተማሪ ውጤት ግብ ተጥሎ ልዩ ልዩ ውጤታማ ስራዎች እየተሰሩ ነው የሚለው በቀዳሚነት ተጠቅሷል። ባለሙያዩ ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልፁ እንዲህ ይላሉ፣

> "የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ስድስት ፓኬጆች ተቀርፀው ተግባራዊ እየተደረጉ ሲሆን በተለይም ሲፕ (SIP) ላይ የተማሪ ውጤት ግብ ተጥሎ ከግብ ለማድረስ ልዩ ልዩ ተግባራት እየተከናወኑ ነው። በሥርዓተ ትምህርት ብልፀጋም የፈተና ሥርዓት የራሱ አካሄድ አለው። አሁን የምዘና ሥርዓት ስታንዳርዱን ለማስጠበቅ እየተሰራ ያለው ነገር በጉድኝትና በወረዳ ደረጃ መለኪያ ፈተና እያዘጋጁ ነው። እንደ ዞንም የ፪ኛ ደረጃ ፈተና አዘጋጅተዋል። ልዩ ልዩ የብቃት መለኪያ ፈተናዎች እየተዘጋጁ በክፍል ፈተናና በብሔራዊ ፈተና መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ ስራዎች ተጀምረዋል። እና ይህን ስራ ዓልመን እየሰራን ነው።"

ከባለሙያዩ ንግግር መረዳት የሚቻለው የትምህርት ጥራት ለማረጋገጥ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ነው። የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ መለኪያ ሆኖ እያገለገለ/ እንዲያገለግል እየተደረገ ያለው ደግሞ ፈተና ነው። በዚህ ሂደትም በክፍልና በብሔራዊ ፈተናዎች መካከል ያለውን ክፍተት መሙላት አንድ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ተግባር ተደርጎ ተወስዷል። በባለሙያዩ እንደተገለፀው ሁሉ በሌሎች ተወያዮችም ተደጋግሞ የተጠቀሰው ክፍተት በትምህርት ቤት ደረጃ የሚዘጋጁት ፈተናዎች የብሔራዊ ፈተናዎችን ያህል ጥራት ያላቸውና ተማሪዎችን ለብሔራዊ ፈተናዎች የሚያዘጋጁ ሆነው አለመገኘታቸው ነው። በአባሪነት ከተያያዙት የክፍል ፈተናዎች ማስተዋል እንደሚቻለውም ለዚህ ችግር ዋነኛ መፍትሄ ተደርጎ እየተወሰደ ያለው ፈተናዎቹ በትምህርት ቤት ሳይሆን በዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤቶችና በዞን ትምህርት መምሪያዎች እንዲዘጋጁ ማድረግን ነው። በእርግጥ እነዚህኛዎቹም ፈተናዎች እንዲዘጋጁ እየተደረገ ያለው ከየትምህርት ቤቶች በየትምህርት ዓይነቶቹ በማስተማር ችሎታቸው፣ በሥራ ልምዳቸው፣ በስራ አፈጻጸማቸውና በመሳሰሉት መስፈርቶች በሚመለመሉ/ በሚመረጡ መምህራን ነው። ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ ውስጥ በጉድኝት፣ በወረዳ፣ በዞን ፈተናዎች እንዲዘጋጁ እየተደረገ ነው ሲሉ ይህንኑ አሰራር እያመለከቱ ነው።

በየወሰነ ትምህርቱ/ በየመንፈቀ ዓመቱ ከሚዘጋጁት እነዚህ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በተጨማሪም በየደረጃው ማለትም በየወረዳው፣ በየክፍለ ከተማው፣ በየዞን ትምህርት መምሪያው፣ በክልል ትምህርት ቢሮ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዘርፎች የብቃት መለኪያ ፈተናዎች (proficiency tests) እየተዘጋጁ ለዘጠነኛና ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሰጡ እየተደረገ እንደሆነም የውይይቶቹ ተሳታፊዎቹ ተናግረዋል፡፡ በአባሪነት ከተካተቱት የክፍል ፈተናዎች መካከል የመጨረሻው ለምሳሌ የብቃት መለኪያ ፈተና ናሙና ነው፡፡ እነዚህ የክፍልም ሆነ የብቃት መለኪያ ፈተናዎች በትምህርት ቤት ደረጃ ይዘጋጁ ከነበሩት/ ከሚዘጋጁት የሚለዩት በእነዚህኛዎቹ አንደኛ በየትምህርት ዓይነቱ ብዙ ጥያቄዎች (በአብዛኛው ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጋር እኩል ወይም ተቀራራቢ የሆኑ ጥያቄዎች) የሚዘጋጁባቸው መሆናቸው ነው፡፡ ሁለተኛ ሁሉም ጥያቄዎች በምርጫ ብቻ የሚዘጋጁ ናቸው፤ በትምህርት ቤት ደረጃ እንደሚዘጋጁት የክፍል ፈተናዎች የተወሰኑም ቢሆን እንደ እውነት/ሀሰት በሉ፤ አዛምዱ የሚሉ ዓይነት ጥያቄዎች አይካተቱባቸውም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ እውነትም ከትምህርት ቤት በላይ ባሉ መዋቅሮች ተቆጣጣሪነት እየተዘጋጁ ያሉ ፈተናዎች ይበልጥ የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን የሚመስሉና እንደተባለው በክፍል ፈተናዎች ይታይ ነበር የተባለውን ክፍተት የሚሞሉ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የውይይቶቹ ተሳታፊዎች፣ የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ተገቢና ሞዴል ተደርገው ሊወሰዱ እንደሚገባቸው የሚያሳይ የጥናት ውጤት ስለመኖሩ የሚያውቁት ነገር አለመኖሩን ወይም ስለዚህ ጉዳይ የደረሳቸው ምንም ዓይነት መረጃ እንደሌለ አልሸሸጉም፡፡ ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ምን ዓይነት ወሸባክ እንዳላቸው በጥናት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በክልሉ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ሆነው እየተወሰዱ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ እስካሁን የቀረቡት ነጥቦች የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ (ወሸባካቸው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆኑ ባልታወቀበት ሁኔታ) በትምህርት ቤት ደረጃ (micro level) ብቻ ሳይሆን በውጫዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት(Macro Level) ላይ ሳይቀር ተፅዕኖ እያሳደሩ እንደሆነ ያሳያሉ፡፡

በእርግጥ፣ በሁሉም ቦታዎች በተካሄዱት የቡድን ውይይቶች እንደተገለጸው፣ የሚዘጋጁት ፈተናዎች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ፈተና አዘጋጆች አንደኛ የፈተና ልየታ ሰንጠረዦችን (Table of Specifications) እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡ ሁለተኛ ጥያቄ ለማውጣትም ሆነ የፈተና ልየታ ሰንጠረዦችን ለማዘጋጀት ዝቅተኛ የመማር ብቃቶችን

/Minimum Learning Competencies/ ዋነኛ መነሻ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡ በአባሪ 18 የቀረቡት ፈተናዎች ግን ጥያቄዎቹ በተገለፀው መንገድ እየተዘጋጁ መሆናቸውን አያሳዩም፡፡ ምክንያቱም በተባለው መሰረት የሚዘጋጁ ቢሆኑ ኑሮ በፈተናዎቹ ጥያቄዎችና በቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ ይኖር ነበር፡፡ ሆኖም ለሌላ ዓላማ የተካሄደው ምርመራ ያሳየው እነዚህ ፈተናዎች አንደኛ የአእምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎችን ዝቅተኛ ችሎታ እንጂ እንደ ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ ያሉ ችሎታዎችን በአግባቡ የሚመዝኑ ጥያቄዎች የተካተቱባቸው ሆነው አልተገኙም፡፡ ሁለተኛ በመርሐ ትምህርቶቹ የተካተቱ የማዳመጥ፣ የመናገርና የመጻፍ ዝቅተኛ ብቃቶች በፈተናዎቹ ጥያቄዎች እንዲወከሉ እየተደረጉ አይደለም፡፡ በእርግጥ እውነት/ ሀሰት በሉ፣ አዛምዱና አልፎ አልፎ ክፍት ቦታ ሙሉ የሚሉ አጠያየቆችን ጭምር በሚጠቀሙት በትምህርት ቤት ደረጃ በሚዘጋጁ ፈተናዎች ላይም እነዚህ ሁለት ችግሮች ይንፀባረቃሉ፡፡ ይህም አበበ (1990)፣ Madaus (1988) እንዳሉት የኢትዮጵያ ትምህርት የሚመራው በህጋዊ ሥርዓተ ትምህርቶች (Official Stated Curriculum) ሳይሆን በብሔራዊ ፈተናዎቹ እንደሆነ የሚያሳይ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡ ከዚህም በኢትዮጵያ ሁኔታ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ባሉ አካላት ማለትም በመምህራን፣ በተማሪዎችና በትምህርት ቤቶቹ ርዕሳነ መምህራን/ አስተዳደር ላይ ብቻ ሳይሆን በውጫዊ /macro የትምህርት ባለ ድርሻ አካላት ግንዛቤና ተግባራት ላይ ጭምር ተፅዕኖ እያሳደሩ እንደሆነና የተፅዕኖው ዓይነትም በአብዛኛው በውስጣዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ እያሳደሩት እንዳለው ያለ አሉታዊነቱ የበዛ እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡ በዚህም የትምህርት ጥራት መለኪያ እየሆነ ያለው በአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎችና በሥርዓተ ትምህርቶቹ በቀረቡት ትምህርቶች ረገድ ተማሪዎች ያሳዩት ለውጥና እድገት ሳይሆን ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ጋር ትይዩ በሆኑት በክፍል/ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችና በብቃት ፈተናዎች የሚያስመዘግቡት ውጤት ነው፡፡

እስካሁን የቀረቡት ነጥቦችን መሰረት በማድረግ የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ በውጫዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ እያሳደሩት ያሉት ተፅዕኖ ከወሸባክ መለኪያዎች (dimensions) አንፃር ሲፈተሽም አሉታዊነቱ የሚያመዝን፣ ጉልህ፣ ጠንካራ፣ ጥቅልና ንጥል የወሸባክ ባህርያት የሚታዩበትና የጊዜ ውስንነት የማይታይበት ወይም ወቅታዊ ያልሆነ /ሁልጊዜ የሚከሰት ነው፡፡

የተማሪዎችን አቅም ማጎልበት

የተማሪዎችን አቅም ለማጎልበት ቀደም ሲል ከትምህርት ቤት መሻሻል መርሐግብር ጋር ተያይዞ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ እየተሰራ ካለው ተግባር በተጨማሪ ከክልል ትምህርት ቢሮ ጀምሮ በየደረጃው ባሉት የትምህርት መዋቅሮች የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ እንደሆነ ተወያዮቹ ገልጸዋል። በአብዛኛዎቹ ተወያዮች ዋና ዋና ተግባራት ናቸው ተብለው የተገለፁትም የሚከተሉት ናቸው፤

አንደኛ የተሻሉ ተማሪዎችን ለማፍራት የዝውውር (Promotion) ፖሊሲ በክልል ደረጃ እንዲወሰን ተደርጓል። ቀደም ባሉት ጊዜያት የተማሪዎች ከክፍል ክፍል ዝውውር በትምህርት ቤት ደረጃ ሳይቀር ይወሰን እንደነበርና አሁን ግን ወረዳዎችም ሆኑ ዞኖች የዝውውር ፖሊሲ እንደሌላቸው ወይም ይህ ስልጣን ለክልል ትምህርት ቢሮ ብቻ የተሰጠ እንደሆነ ተገልጿል። ይህም አሰራር፣ በክልል ደረጃ ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸው ልጆች የሚዛወሩበትን እድል የሚያመቻችና ተማሪዎች እንዳይዘናጉና በክልል ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ የሚያግዝ ነው ተብሎ ይታመናል።

ሁለተኛ፣ ተማሪዎችን ለማብቃት የሚያስችሉ የተለያዩ የማጠናከሪያ ትምህርት ሥርዓቶች ተዘርግተዋል። ሦስተኛ፣ ተማሪዎች አንድ ለአምስት እንዲደራጁ በማድረግ እርስ በርሳቸው እንዲደጋገፉና በመምህሮቻቸው ወርክሸቶች እየተዘጋጁ እንዲሰጧቸው እየተደረገ ነው። አራተኛ፣ በየወሰነ ትምህርቱ ማብቂያ ላይ የሚዘጋጁ ፈተናዎች በትምህርት ቤት ደረጃ መዘጋጀታቸው እንዲቀርና በወረዳ ወይም በዞን ደረጃ እንዲዘጋጁ እየተደረገ ነው። የተከታታይ ምዘና ውጤት ከ60% ወደ 40% ዝቅ እንዲልና በወረዳ ወይም በዞን የሚዘጋጁ የማጠቃለያ ፈተናዎች ከ60% እንዲያዙ እየተደረገ ነው። ይህም ተማሪዎች የሚወዳደሩት በትምህርት ቤታቸው ካሉት ተማሪዎች ጋር ብቻ እንዳልሆነ አውቀው ጠንክረው እንዲያጠኑና እንዲማሩ ያበረታታል ተብሎ ይታሰባል። መምህራንና የየትምህርት ቤቶቹ አስተዳደርም የበለጠ ተግተው እንዲሰሩ ያነቃቃል ተብሎ ይገመታል።

አራተኛውና ከመጀመሪያው ነጥብ ጋር ግንኙነት ያለው፣ ዋነኛው የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የተማሪዎችን አቅም ማጎልበቻ ዘዴ ነው ተብሎ የተገለፀው ደግሞ ግብ

ጥሎ ግብን ለማሳካት መስራት የተባለው ስትራቴጂ ነው፡፡ ተወያዮቹ እንዳስረዱት የተማሪ ውጤት ግብ ምን መሆን አለበት የሚለው ከክልል እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ታልሞ እየተተገበረ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም ተማሪ በሁሉም የትምህርት ዓይነት 50 እና በላይ ያመጣል፤ ከዚያ ቀጥሎ 30% የሚሆነው ተማሪ 75 እና በላይ ያመጣል፤ ቀሪው 15% ደግሞ 85 እና በላይ ያመጣል፤ ተብሎ ታቅዶ እየተሰራ ነው፡፡ ይህን ለማረጋገጥም በየወሰነ ትምህርቱ ማብቂያ ላይ የመጀመሪያው የካቲት ላይ ሁለተኛው ከሰኔ ጀምሮ በትምህርት ቤት፣ በወረዳ፣ በዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ በዞን ትምህርት መምሪያና በክልል ትምህርት ቢሮ የጥያቄ/ የውጤት ትንተና ይሰራል፤ እንዴት እየተሰራ እንዳለም እ.ኤ.አ. የ2004 ዓ.ም ፈተና ውጤት ትንተና ሰነዶችን ለአጥኝው በማሳየት አረጋግጠዋል፡፡ በምልከታው ጊዜ ከሰነዶቹና በሰነዶቹ ውስጥ ከተካተቱት ሰንጠረዦች ማረጋገጥ እንደተቻለው የፈተና ውጤት ትንተናው ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንዱ የብሔራዊ/ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ውጤት ትንተና ሲሆን ሁለተኛው የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የየወሰነ ትምህርቶቹ ፈተና ውጤቶች ትንተና ነው፡፡ ከብሔራዊ ፈተናዎቹ ለምሳሌ በክልሉ ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ የተላከላቸው በስታቲስቲክስ በተለይም በገላጭ ስታቲስቲክስ በሰንጠረዦች ተደግፎ የቀረበ ባለ ብዙ ገጽ ሰነድ ነው፡፡ ሰንጠረዦቹ በተለያዩ አምዶች (Column) የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በዚህ ሰነድ የተካተተው፣ ሠንጠረዥ 3 በክልል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተፈተኑት ጠቅላላ ተማሪዎች በአገር አቀፍ ከተፈተኑት ከሌሎች ክልሎች ጋር በቁጥር፣ በያታና በድምር ሲነፃፀር የሚኖረውን የተሳትፎ ደረጃ የሚያመለክት ትንተና የሚል ርዕስ ያለው ነው፡፡ በሰንጠረዡ የተካተቱት አምዶችም 1ኛ.ክልል 2ኛ. ንፅፅር (በቁጥርና በ%)፣ 3ኛ. በየክልሉ ጠቅላላ የተፈተኑ (ወ ሴ ድ ደረጃ)፣ አራተኛ በየክልሉ ከ A - C ያስመዘገቡ (ወ ሴ ድ ደረጃ) የሚሉት ናቸው፡፡

ውይይት በተካሄደባቸው ቦታዎች ከዚህ ሰንጠረዥ ጋር ተመሳሳይነት ባላቸው ቅፆች የብሔራዊና የክፍል ፈተናዎች ውጤት ትንተና በየትምህርት ዓይነቱ የትምህርት ቤቶቹን ደረጃ የሚያሳዩ ትንተናዎች እንደሚሰሩም ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚያም እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፣ ወረዳና ዞን የሚገኝበትን ደረጃ እንዲያውቅ የትንተና ውጤቶቹ እንደሚላኩለትና እንዳስፈላጊነቱ የመጀመሪያዎቹን ደረጃዎች ላገኙ ትምህርት ቤቶች፣

መምህራንና ተማሪዎች፣ የሽልማት ሥነ-ሥርዓት ሊዘጋጅ እንደሚችል በውይይቶቹ ተገልጿል፡፡

ይህም አሰራር ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የሀገሪቱ ትምህርት የፈተና ተዕዕኖ ጥገኛ መሆኑን የሚያመለክት ሌላ አስረጅ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

ሌላው የተማሪዎችን ውጤት ከፍ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ስራ በየዓመቱ በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ከፍተኛ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎችና ትምህርት ቤቶች ስፖንሰር በማፈላለግና የሽልማት ሥነ-ሥርዓት በማዘጋጀት የሚሸለሙበት ባህል እንዲዘረጋ እየተደረገ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ሌሎች ትምህርት ቤቶችና ተማሪዎች በሚቀጥሉት ዓመታት ከፍተኛ ውጤት ለማምጣት ጠንክረው እንዲሰሩ እንደሚያነሳሳና የፉክክር መንፈስ ለመፍጠር እንደሚያስችል ይታመናል፡፡

እስካሁን የቀረቡት ነጥቦች በሙሉ ውጫዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ራሳቸው በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ተጽዕኖ ስር እንደወደቁ የሚያሳዩ ብቻ ሳይሆኑ፣ በየትምህርት ቤቶቹ የሚካሄዱት የመማር-ማስተማር ሂደቶች ፈተና በተለይም የማጠናቀቂያ ፈተና ተኮር እንዲሆኑ ጠንካራ ተጽዕኖ ለማሳደር ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ የሚያሳዩ ጭምርም ናቸው፡፡

የቋንቋ መምህራን አቅም ጉልበታና ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው ጊዜ

ከባለሙያዎቹ ጋር በተካሄዱት ውይይቶች የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ቁልፉ ግብአት ሳይሆን መምህሩ ነው፤ የሚል ሀሳብ ተንጸባርቋል፡፡ ለምሳሌ ባለሙያ ስለዚሁ ጉዳይ ሲያስረዱ የሚከተለውን ተናግረዋል፤

> ለትምህርት ጥራት ቁልፉ መምህሩ ነው፡፡ ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ ትልቁ ነገር ግብዓት ሳይሆን መምህሩ ነው፡፡ ምክንያቱም እዛ ላይ ተጨባጭ የሚያደርገው ምንድነው መምህሩ አክቲቭ ከሆነ፣ መምህሩ ተግባሩን የሚፈፅም ከሆነ ያለ መጽሐፍ ተማሪዎችን ማብቃት ይችላል፡፡ ይህን በአባቶች አይተናል፡፡ በቤተክህነት አይተናል.. መርጃ መሳሪያ ሳይጠቀሙ ማንበብ መጻፍን የሚያስችሉበት ሁኔታ አለ፡፡...ቁልፉ ያለው መምህሩ ላይ ነው፡፡

ከዚህ ሐሳብ ጋር በማያያዝም መምህራን ለትምህርት ጥራት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፤ የሚል ግንዛቤ ካለ የነሱ አቅም እንዲጎለብት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የስራ ላይ ስልጠና እንዲያገኙ የሚደረግበት ሥርዓት አለ? የሚል ጥያቄ ተጠይቀው ነበር፡፡ ለዚህ ጥያቄ በአብዛኛዎቹ ቦታዎች (በሦስቱ) የተሰጠው መልስ ከቋንቋ ትምህርት ጋር በተያያዘ በተለይ ለአማርኛ መምህራን የተሰጠ የስራ ላይ ስልጠና የለም የሚል ነው፡፡ ለእንግሊዝኛ መምህራን በየጊዜው ይዘረጉ በነበሩት የእንግሊዘኛ ማሻሻያ መርሐ ግብሮች መሰረት ስልጠናዎች ይሰጡ ነበረ፡፡ እሱም አሁን አሁን እየቀረ ነው የሚል ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዘውም እንደ ርዕሳነ/ ምክትል ርዕሳነ መምህራን ሁሉ እነዚህኛዎቹም (የአማርኛ መምህራን) ስልጠና ባያገኙም በቋንቋው ትምህርት አሰጣጥ ላይ የፈጠረው ችግር እንደሌለና ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በንጽጽር ሲታይ፣ ተማሪዎች በብሔራዊ ሆነ በክፍል ፈተናዎች ጥሩ ውጤት እያመጡበት ያለ የትምህርት ዓይነት እንደሆነ በውይይቶቹ አንጸባርቀዋል፡፡

በምታደርጉት ክትትል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት የሚመጣበት ብቻ ነው ወይስ መምህራኑ በቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት መሰረት የቋንቋውን ክሂሎች እያስተማሩና ተማሪዎቻቸውን ጥሩ ተናጋሪ፣ ጥሩ ፀሐፊ፣ ጥሩ አንባቢና ጥሩ አድማጭ እንዲሆኑ እያገዟቸው ነው የሚል እምነት አላችሁ? የሚል ጥያቄም ተጠይቀዋል፡፡ ለዚህ ጥያቄ የሰጡት መልስ የላይኛውን የሚያረር ይመስላል፡፡ ሁሉም በሚባል ደረጃ በየትምህርት ቤታቸው እየተሰጠ ባለው የቋንቋው ትምህርት የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ በተለይም ክሂሎችን በሚመለከት እየተሻሻለ ነው የሚል እምነት እንደሌላቸው ተወያዮቹ ተናግረዋል፡፡ ለምሳሌ ባለሙያ፱ ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልፁ የሚከተለውን ተናግረዋል፡፡ ‹‹...በትክክል የተጠና ባይሆንም እኔ ቋንቋው እንዲያውም ‘ዲክላይን’ እያደረገ (እየሞተ) ነው እላለሁ፤ ማመልከቻ እንኳን መጻፍ አይችሉም [በትምህርት ሥርዓቱ ያለፉትን ተማሪዎች ማለታቸው ነው]፡፡ በዲግሪ ‘ግራጁዌት’ አድርገው [ተመርቀው] መጥተው እንኳን እዚህ ለመቀጠር ፈልገው የሚጽፉት ማመልከቻ በጣም የሚያስቅ ነው!›› ከዚህ በተጨማሪ የወይይቶቹ ተሳታፊዎች፣ ለሱፐርቪዥን ወደ እየትምህርት ቤቶች እየሄዱ፣ አንደኛ በየክፍሉ ሲገቡ የሚያዩትና የሚሰሙት፣ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ድክመት የሚያሳይ እንደሆነ፣ ሁለተኛ የተለያዩ ፎርሞችን ሲያስሞሉ ለምሳሌ ብዙ ተማሪ ስሙን እንኳን በትክክል ለመጻፍ ሲቸገር/ ሲያቅተው እንደሚመለከቱ፣ እየጠቀሱ በተለይ በመጻፍና

በመናገር በኩል ተማሪዎቹ ከፍተኛ ችግር እንደሚታይባቸው የሚታወቅ ነገር መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የገለጹት ሀሳብም፣ ከመምህራኑ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡ አንዳንዶቹ የውይይቶቹ ተሳታፊዎች የዚህ ሁሉ ችግር መንስኤ በቋንቋው ትምህርት እንደጹሮው አንደኛ ድርሰት፣ ሁለተኛ የእጅ ጽህፈት፣ ሦስተኛ የቃል ጽሕፈት የሚባሉት ትምህርቶች ክፍለ ጊዜ ተመድቦላቸው ስለማይሰጡ ነው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

ተወያዮቹ ከሂሎችን በተመለከተ ተማሪዎቹ ድክመት እንደሚታይባቸውና በአግባቡ እየተማሩ እንዳልሆነ ቢያምኑም ይህን ችግር ለመፍታት የሚያስችል ምን ምን እርምጃ እየተወሰደ ነው? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ተጠየቃዊ የሆነ ምላሽ ሰጥተዋል፣ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም ዋነኛ መፍትሄ ተደርገው የተገለጹት፣ አንደኛው ይህ ችግር ሊፈታ የሚችለው በራሳቸው በቋንቋው መምህራን ነው፤ የሚል ሲሆን ሁለተኛው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ በኢግራ (EGRA) ጥናት ውጤት መሰረት የተጠናከረ ትምህርት እንዲሰጥ እየተደረገ ነው የሚል ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት እንዳመላከተው በ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት ረገድ የሚታይባቸውን ድክመት ለማሻሻል የተደረገም ሆነ ሊደረግ የታሰበ ነገር የለም፡፡ ይህም ችግሩ ተባብሶ መቀጠሉ እንደማይቀር የሚጠቁም ነው፡፡ በተወያዮቹ ተደጋግሞ እንደተንፀባረቀው በትምህርት ሥርዓቱ በመሰረታዊ ችግርነት ታይቶ መፍትሄ እየተፈለገለት ያለው የሳይንስና የሂሳብ ትምህርቶች ጉዳይ ነው፡፡ በቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ላይ ያለው ትኩረት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ የሚያበቃ ነው፤ የሚል አንድምታ ያለው ምላሽ ነው የተሰጠው፡፡

ከዚሁ ጋር በማያያዝ ለብሔረሰብ ቋንቋ የተመደበው ሁለት ክፍለ ጊዜ የብሔረሰብ ቋንቋ ተመርጦ መሰጠት እስኪጀምር ለምን ለእንግሊዝኛና አማርኛ ቋንቋ እንዲከፋፈል አልተደረገም? ለቋንቋ ትምህርት የተመደበ ክፍለ ጊዜ ለቋንቋ ትምህርቶች ቢሰጥ አይመረጥም ነበር? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄም የሰጡት መልስ ከክልሉ ትምህርት ቢሮ የተሰጠው አቅጣጫ ያን ማድረግ የሚጋብዝ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በተወያዮቹ እንደተንጸባረቀው ስለእነዚህ ክፍለ ጊዜያት ጉዳይ በክልሉ የተሰጠው አቅጣጫ በቋንቋ ትምህርት ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት/ ለማጥበብ እንዲጠቀሙባቸው ሳይሆን ችግር ለሚታይባቸው የትምህርት ዓይነቶች ትምህርት ቤቶቹ እንዲጠቀሙባቸው የሚያበረታታ ነው፡፡ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ችግር የሚታይባቸው ዋነኛ የትምህርት ዓይነቶች

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA

ሆነው የተገኙት ደግሞ የሳይንስና የሂሳብ ትምህርቶች ስለሆኑ ለብሔረሰብ ቋንቋ የተመደቡት ክፍለ ጊዜያት ለነዚህ ትምህርቶች እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

የመጨረሻው ጥያቄ በሥርዓተ ትምህርት ማስፈጸሚያ ማዕቀፉ በሳምንት 35 ክፈል ጊዜ/ የሙሉ ቀን ትምህርት በሚሠጥባቸው ትምህርት ቤቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ በሳምንት አራት ክፍል ጊዜ እንዲሰጥ የተደነገገው በእናንተ ዞን በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተግባራዊ ሊደረግ ያልቻለው ለምንድነው? የሚል ነበር፡፡ ለዚህም ጥያቄ በአብዛኞቹ የተሰጠው ምላሽ በክልሉ የወጣው የክፍለ ጊዜ ድልድል ይህን የሚያንጸባርቅ አይደለም የሚል ዓይነት ነው፡፡ ይህም መምህራኑ የማስተማር-መማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች አንዱና ዋናው ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ መጠን ማነስ ነው ያሉትን ችግር ለማቃለል የሚያስችል መፍትሄ እየተፈለገ አለመሆኑን ያሳያል፡፡

4.8 በማጠናቀቂያ ፈተናው መርሐ ግብር ምክንያት የተበረታቱ አዎንታዊና አሉታዊ የወሽባክ ገፅታዎች

በተለያዩ ዓይነታዊና መጠናዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ውጤት ትንተናዎች እንዳሳዩት በማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት አዎንታዊም አሉታዊም የወሽባክ ዓይነቶች ተከስተዋል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረት ቀጥሎ ከአዎንታዊዎቹ በመነሳት በእያንዳንዱ የወሽባክ ዓይነት የተበረታቱ የወሽባክ ገፅታዎች ቀርበዋል፡፡

4.8.1 በማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት የተበረታቱ አዎንታዊ የወሽባክ ገጽታዎች

የአማርኛ ቋንቋ በብሔራዊ ፈተናነት ተካቶ መሰጠቱ የሚከተሉት አዎንታዊ የወሽባክ ገጽታዎች እንዲታዩ እንዳደረገ በመምህራንና በተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቆች፣ በክፍል ምልከታና በተለይም ከመምህራን ጋር በተካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶችና ቃለ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ትንተና ውጤቶች አመላክተዋል፡፡

አንደኛ ተማሪዎች የቋንቋውን ትምህርት በአዎንታዊነት እንዲያዩትና ትምህርቱን በፍላጎት እንዲከታተሉት አበረታቷል፡፡ ለዚህ ሀሳብ አስረጅነት በተለያዩ ቦታዎች በተካሄዱት የቡድን ውይይቶች መምህራኑ ደጋግመው ሲያነሱት የነበረው የ11ኛና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ለማስተማር እጅግ በጣም መቸገራቸውን ነው፡፡ የዚህም ዋነኛ

ምክንያት አድርገው የተረዱት የቋንቋው ትምህርት በ12ኛ ክፍል ፈተናነት የማይሰጥ መሆኑን ነው፡፡ እንደ መምህራኑ እምነት እንዲህ ያለ ችግር መከሰት የጀመረው ቀደም ሲል 12ኛ ክፍል ላይ ይሰጡ የነበሩ የቀለም ትምህርቶች በሙሉ እንደገና በ12ኛ ክፍል ፈተናነት ሲካተቱ የአማርኛ ቋንቋ ብቻ ተነጥሎ ከቀረ ወዲህ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በማነፃፀርም የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ቋንቋው በብሔራዊ ፈተናነት ስለሚሰጥና ጥሩ ውጤት እናመጣበታለን በሚል ግምት ለቋንቋው ትምህርት አዎንታዊ አስተያየት እንዲኖራቸውና የሚሰጠውን ትምህርት በፍላጎት እንዲከታተሉ አድርጓቸዋል፤ የሚል ግንዛቤ በተለይ መምህራኑ እንዳላቸው በውይይቶቹ አንፀባርቀዋል፡፡ ተማሪዎቹም ከፈተና ጋር ለተያያዙት በጽሑፍ መጠይቁ በዘጠነኛውና በ15ኛው ጥያቄ ስር ለተካተቱት ፈተና ነክ ንዑሳን ጥያቄዎች የሰጡት መልስም በመምህራኑ የተገለፀውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

ሁለተኛው የማጠናቀቂያ ፈተናው ያበረታታው አዎንታዊ ወሽባክ በፈተና የሚካተቱ የትምህርቱ ይዘቶች በተለይም በማጠናቀቂያ ፈተናው በየዓመቱ ትኩረት የሚሰጣቸው የሰዋስው፣ የሥነ-ጽሑፍና የአንብቦ መረዳት ክፍሎች በትምህርቱ (በመማር- ማስተማር ሂደቶቹ) መምህራኑና ተማሪዎቹ ሰፊ ትኩረት እንዲሰጧቸው ማድረጉ ነው፡፡ በክፍል ምልከታዎች ማስተዋል እንደተቻለውም እነዚህን ክፍሎች መምህራን ለማስተማር፣ አብዛኞቹ ተማሪዎች ለማማር ፍላጎትና ተነሳሽነት አላቸው፡፡ በፈተናው ሰፊ ሽፋን የሚሰጣቸው ተግባራትና ይዘቶች በትምህርቱም ትኩረት እንደሚያገኙ በምልከታው ከመረጋገጡ በተጨማሪ በመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅም ‹‹ጠንካራ›› በሚባል ደረጃ የተገለጸ ጉዳይ ነው፡፡ በቡድን ውይይቶቹም ተመሳሳይ ሀሳብ ተንፀባርቋል፡፡ በተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው መረጃም የተባለውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

ሦስተኛ የማጠናቀቂያ ፈተና በማስተማር-መማር ሂደቶቹ ላይ ከፈተናው ጋር በተያያዘ መልኩ ቢሆንም መምህራኑም ተማሪዎችም ተጨማሪ አጋዥ የትምህርት መሳሪያዎችን እንዲያነቡ፤ መምህራኑ ተጨማሪ መልመጃዎችን እያዘጋጁ ወይም ከሌሎች አጋዥ መሳሪያዎች እየወሰዱ እንዲያሰሩ፣ ተማሪዎች ደግሞ የሚሰጧቸውን መልመጃዎች በፍላጎት እንዲሰሩ አበረታቷል፡፡

ለፈተና በመዘጋጀት ስም አንድን የትምህርት ይዘት ከተለያየ አቅጣጫ በስፋት ተማሪዎች እንዲረዱት/ እነዲገነዘቡት የማድረግ ጥረት እንደሚደረግም በተጨባጭ በክፍል

ምልከታዎችም ተስተውሏል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች ስለምዕላድ፣ የሐረግ ዓይነቶች፣ የልቦለድ አላባውያንና ተራና ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮች፣ ዘይቤ፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ግጥምና የግጥም ባህርያትና ሙያዊ ቃላት በተማሩባቸው ክፈለ ጊዜያት፣ በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚካተቱ ጥያቄዎችን መስራት እንዲችሉ ለመርዳት በማሰብ እንደሆነ መገመት ቢቻልም እግረ መንገዱን ተማሪዎች ስለእነዚህ ጉዳዮች ጠለቅ ያለ ዕውቀት እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ትምህርቶች በክፍል ውስጥ ሲቀርቡ፣ ተማሪዎችም በትኩረት ሲከታተሉ በምልከታዎቹ ተስተውሏል፡፡ ከምልከታዎች በኋላ ምልከታ ከተካሄደባቸው መምህራን ጋር የተካሄዱት ቃለመጠይቆችም ይህንኑ በግልጽ አንጸባርቀዋል፡፡ ይህም የፈተናው አንድ አዎንታዊ ገፅታ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ሌላው በWall (2005) ስራ የብሔራዊ/ ውጫዊ ፈተና ጥቅም ተብሎ የተገለጸው በሁሉም ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ ትምህርት እንዲሰጠ ለማድረግ ያስችላል የተባለው (አሉታዊነቱ የበዛ ቢሆንም) በተግባር ታይቷል፤ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ ትምህርት እንደሚሰጥ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

4.8.2 በማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት የተበረታቱ አሉታዊ የወሽባክ ገጽታዎች

በማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት የተከሰቱ አሉታዊ የወሽባክ ገፅታዎችን በተመለከተ አንደኛ በፈተናው የማይካተቱ ይዘቶች በተለይ የቋንቋው ትምህርት መሰረታዊ ጉዳዮች የሆኑትን የቋንቋውን ክሂሎች ተማሪዎች ለመማር ፍላጎት እንዳይኖራቸውና በመማሪያ መጽሐፎቻቸው የተካተቱ ክሂል ነክ መልመጃዎችን እየሰሩ የመለማመድ ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡ በሌላ አገላለጽ የማጠናቀቂያ ፈተናው የቋንቋው ትምህርት በመርሐ ትምህርቶች በቀረቡት ዓላማዎችና ይዘቶች ላይ ሳይሆን በፈተናው ትኩረት በሚሰጣቸው ክፍሎች ላይ በተለይም በሰዋስው፣ በሥነ-ጽሑፍ፣ በተወሰነ ደረጃ በንባብና በሌሎች ክሂሎች የጽንሰ ሃሳብ ትምህርት ላይ እንዲያተኩር የሚያደርግ አሉታዊ ጫና እየፈጠረ ነው፡፡ ሁለተኛ በትምህርት ፖሊሲው፣ በሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፉና በቋንቋው ሥርዓት ትምህርት ትኩረት የተሰጣቸው የቋንቋው ክሂሎች በተለይም የመናገር፣ የማዳመጥና የመጻፍ ክፍሎች በመማር ማስተማር ሂደቶቹ ችላ እንዲባሉ እያደረገ ነው፡፡ ይህም የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሑፍና በቃል ለመግለፅ የሚችሉ ወይም

ማመልከቻ፣ ዘገባ፣ ቃለጉባኤ፣ ወዘተ. የሚጽፉ፣ ተናግረው የሚያሳምኑ ተከራክረው የሚረቱ... እንዲሆኑ የሚያግዝ እንዳይሆን አድርጎታል። ሦስተኛ የማጠናቀቂያ ፈተናው ባህርይ አሳታፊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚያበረታታ ባለመሆኑ የትምህርቱ አብዛኛው ጊዜ በመምህራኑ የሚያዝና የተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብን የማያንፀባረቅ እንዲሆን እያደረገው ነው።

አራተኛ፣ ተማሪዎች በመምህሮቻቸው አልፎ አልፎ የሚሰጧቸውን በመማሪያ መጽሐፎቻቸው የተካተቱ፣ ፈተና ለመስራት ግን ላያግዙ የሚችሉ፣ ተግባሮችን/ መልመጃዎችን የመስራት ፍላጎት እንዳይኖራቸው እያደረገ መሆኑ ሌላው የፈተናው አሉታዊ ወሽባክ ውጤት ነው። ለዚህም በትምህርት ቤት‹፩› ለዘጠነኛና ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፎቻቸው ከቀረቡ የመጻፍ ክሂል ተግባሮች መካከል አንድ አንድ ጥያቄ በመመሪያቸው መሰረት ጽፈው እንዲመጡ ከሳምንት ያላነሰ ጊዜ ተሰጥቷቸው በታዘዙት መሰረት ሰርተው የተገኙት ከዘጠነኛ ክፍል ሦስት፣ ከ10ኛ ክፍል አንድ ተማሪ ብቻ መሆናቸውን ማስታወስ ይቻላል። በንግግር ክሂል ረገድም እንዲሁ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው የቀረበላቸውን የዝነኛውን የስፖርት ሰው፣ የይድነቃቸው ተሰማን የሕይወት ታሪክ ካነበቡ በኋላ ለአንድ ሳምንት ዝግጅት አድርገው በቃል/ በንግግር እንዲያቀርቡ የቤት ስራ ተሰጥቷቸው ቀኑ ሲደርስ ተዘጋጅተው የመጡትና ወጥተው ለማቅረብ ፈቃደኛ ሆነው የተገኙት ሦስት ተማሪዎች ብቻ መሆንም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው። ከሦስቱ አንዳቸውም ከአንድ ደቂቃ የበለጠ ጊዜ የተጠቀመ ተማሪ አለመኖርም ወይ የመናገር ክሂላቸው እጅግ በጣም ደካማ ነው ወይም ዝግጅት ሳያደርጉ ነው የሚመጡት፣ የሚለውን የሚያሳይም ነው። አለበለዚያም በፈተና የማይካተትን ትምህርት ለመማር በፍጹም አይፈልጉም ማለት ነው።

ቀላል የማይባል የትምህርት ጊዜ ያለፉ ዓመታትን የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎች ለመስሪያነትና የፈተና አሰራር ስትራቴጂን ለማስተማሪያነት እንዲውል ተጽዕኖ ያሳደረው ይኸው የማጠናቀቂ ፈተናው እንደሆነም የጥናቱ ግኝት አመላክቷል ።

የክፍል ትምህርት ምዘና ሥርዓቱም የቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ሳይሆን የማጠናቀቂያ ፈተናው ነጸብራቅ እንዲሆን የሚያደርግ አሉታዊ ጫና እየፈጠረ እንደሆነም የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ይህም ጫና የክፍል ፈተናዎች የክፍል ትምህርቱን በትምህርቱ

መሳሪያዎች አቀራረብ አንፃር ለመገምገሚያነት ከማገልገል ይልቅ ከማጠናቀቂያ ፈተናው አቀራረብ ጋር ለማስተዋወቂያነት እንዲውሉ እያደረገ ነው፡፡ የዚህም አንድምታ የቋንቋው ትምህርት በሕጋዊው የቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ሳይሆን በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚመራ ነው የሚል ነው፡፡

በአጠቃላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው የቋንቋው ትምህርት በትምህርት ፖሊሲው፣ በሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፉና የቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ከተመሰረተበት የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ እንዲያፈነግጥና ዕውቀትን ማስገንቢያ ትምህርት እያደረገው ነው፡፡

ከሌሎች የወሽባክ ገጽታዎች/ መለኪያዎች/ (Dimensions) አንጻር ሲታይም የፈተናው ወሽባክ አንደኛ ንጥልም፣ ጥቅልም የወሽባክ ገጽታዎች እንደሚከሰቱ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በንጥልነት የሰዋስው፣ የሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች ትኩረት እንዲያገኙና የመጻፍ፣ የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎች ችላ እንዲባሉ ማድረጉ በተለይ ከቋንቋ ትምህርት ጋር ብቻ የተያያዘ ክስተት ነው፡፡ ከጥቅልነት አንፃር ደግሞ በማንኛውም ትምህርት ዓይነት ሊታይ የሚችለው ሥርዓተ ትምህርትን ማጥበብ፣ በፈተና ለሚካተቱ ክፍሎች ትኩረት መስጠትና የማያካትቱን ችላ ማለት ተስተውሏል (Alderson እና Wall1993፣ Watanabe 2004)፡፡ ከጥንካሬ (Intensity) አኳያ ደግሞ በተለይ አሉታዊ የወሽባክ ገፅታዎች በAlderson እና Wall (1993) Watanabe (2004) ስራዎች እንደተገለጸው ጠንካራ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ አሉታዊዎቹ የቋንቋው ትምህርት የሥርዓተ ትምህርቱ ሳይሆን የፈተናው ተገዥ/ ነጸብራቅ እንዲሆን እስከማድረግ የደረሰ ተፅዕኖ ማሳደር የቻሉ ናቸው፡፡ የታለመ (Intended) እና ያልታለመ የወሽባክ ውጤቶችን በተመለከተ ደግሞ ከፈተናዎች ኤጀንሲ የተገኙ መረጃዎች ከታለመት የወሽባክ ገፅታዎች አንዱና ዋና የመማር ማስተማር ሂደቱ በሥርዓተ ትምህርቱ መሰረታዊ ክፍሎች ላይ እንዲያተኩር መገፋፋት ቢሆንም በተግባር ያለው እውነታ ግን የተባለውን የሚያሳይ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በተግባር የታየው እውነታ ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራኑ በቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት በተካተቱት ጠቃሚና መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን በፈተናው በሚካተቱት ክፍሎች ላይ ብቻ ትኩረት እንደሚያደርጉ አመላክቷል፡፡ ስለዚህ በWatanabe 2004 ከተገለጹት መካከል የሚጎላው ያልታለመው የወሽባክ ገፅታ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሄ

5.1. መግቢያ

በዚህ የጥናቱ የመጨረሻ ምዕራፍ፣ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሄ የሚቀርቡበት ነው። በመሆኑም፣ መጀመሪያ የጥናቱ ዋና ዓላማ፣ መሰረታዊ ጥያቄዎች፣ ተሳታፊዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ መረጃ የተተነተነባቸው መንገዶች፣ የመረጃ ትንተናውና የትንተናው ዋና ዋና ግኝቶች ተጨምቀው ይቀርባሉ። ከዚያም በጥናቱ ግኝቶች ላይ የተመሰረቱ መደምደሚያዎች ይከተላሉ። በመጨረሻም ችግሮችን ለመፍታት ያስችላሉ/ ያግዛሉ የተባሉ መፍትሄዎች ይቀርባሉ።

5.2. ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ የማጠናቀቂያ ፈተናውን ወሽባክ ለማጥናት ነው። የማጠናቀቂያ ፈተናውን ወሽባክ በተለይ በአማራ ክልል ሁኔታ/ ዐውድ (context) መነሻነት ለማጥናት የታለመውን ዓላማ ለማሳካትም ቅይጥ (mixed) የምርምር ዘዴ ንድፍ ተመርጧል። የተነሱት የምርምሩ መሰረታዊ ጥያቄዎችም የሚከተሉት ናቸው፤

1. የፈተናዎች ኤጀንሲ የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን አዎንታዊ ወሽባክ ከፍ ለማድረግ ምን ምን ስትራቴጂ ይጠቀማል /የሚጠቀምባቸው ስትራቴጂዎች ምንድን ናቸው?
2. የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና፣
   2.1 ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ጋር ይዛመዳል?
   2.2 ከቋንቋው ትምህርት ዓላማዎች ጋር ይዛመዳል?
3. የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው የሚፈጥረውን ተጽዕኖ እንዴት ይገነዘቡታል?

ለዚህ ሰፊ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ለሚከተሉት ዝርዝር ጥያቄዎች ትኩረት ተሰጥቷል፤

3.1 የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው (በክፍል ውስጥ ተግባራት/፣ በማስተማር ዘዴ፣ በትምህርት ይዘቶች፣ በትምህርት ማቴሪያሎችና በክፍል ትምህርት ምዘና) ላይ ስለሚያደርሰው ተፅዕኖ ያላቸው ግንዛቤ (Perceptions) ምንድነው?

3.2. በጥናቱ ዐውድ የወሽባክ መከሰቻ (መምህራን ማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግባራቸው ላይ በሚያሳድረው ተጽዕኖ ላይ ላዳበሩት ግንዛቤ) ምክንያቶች (Factors) ምንድን ናቸው?

3.3 በመምህራን ባሕርያት (የመምህራን የትምህርት ደረጃ፣ ጾታ፣ የሥራ ልምድ፣ ለማስተማር ሙያ ያላቸው ከበሬታ፣ ከፈተናው ጋር ያላቸው ትውውቅ፣ በፈተናው ጠቀሜታ ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ በሥራ ላይ ሥልጠና መርሐ ግብሮች ያላቸው ተሳትፎ) እና መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጦው (Variable) መካከል ያሉት ተዛምዶዎች ምንድናቸው?

3.4 በትምህርት ቤቶቹ ዐውድ (context characterstics) _መምህራን በተማሪዎች የመማር ዝንባሌ ላይ ባላቸው ግንዛቤ፣ በውጫዊ ተጽዕኖዎች ላይ ባላቸው አመለካከት፣ ለቋንቋው ትምህርት በተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠንና የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ/ ዳራን በተመለከተ ባላቸው ግንዛቤ፣ በተማሪ-ክፍል ጥምርታ) እና መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጦው) መካከል ያሉት ተዛምዶዎች ምንድናቸው?

3.5 በጥገኛ ተላውጦው ላይ ተጽዕኖ በሚያደርስ በእያንዳንዱ የመምህራን ባህርያት (ዐቢይ ተላውጦ) ላይ ጣልቃ የሚገቡ ተላውጦዎች ምንድን ናቸው?

3.6 በእያንዳንዱ ነጻ ተላውጦ (የወሽባክ መከሰቻ ምክንያት) ሊገለጽ የሚችለው የጥገኛ ተላውጦው ልዩነት ምን ያህል ነው?

4 የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር መማር ሂደቶች ላይ ስለሚያሳድራቸው ተጽዕኖዎች ተማሪዎች ያላቸው ግንዛቤ ምንድነው?

5 የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድራቸው ተጽዕኖዎች ምንድን ናቸው?

6 የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ውጫዊ (Macro) ወሽባክ (በውጫዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ የሚያሳድሯቸው ተጽዕኖዎች) ምንድን ናቸው?

7 በማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት ምን ምን አዎንታዊ የወሽባክ አላባዎች (elements) ይበረታታሉ (encouraged)?

8 በማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት ምን ምን አሉታዊ የወሽባክ አላባዎች ይበረታታሉ?

እነዚህን የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስ፣ በቅይጥ የምርምር ዘዴ ንድፍ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተለያዩ ዓይነታዊና መጠናዊ መረጃዎችን መሰብሰብ የሚያስችሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና የመተንተኛ ቴክኒኮች ተመርጠዋል። በጥናቱ በመረጃ ምንጭነትም፤ አንደኛ፣ በጥናቱ ከታቀፉት አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የአምስት ትምህርት ቤቶች ርዕሰ/ምክትል ርዕሰ መምህራን፣ ሁለተኛ፣ በጥናቱ ከታቀፉት ዞኖች፣ የዞን ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤቶችና የዞን ትምህርት መምሪያዎች የሥርዓተ ትምህርት፣ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተና ክፍሎች ኃላፊዎች፣ ሦስተኛ፣ ከትምህርት ሚኒስቴር የፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች፣ ከሰነዶች ደግሞ የአምስት ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች (እ.ኢ.አ. ከ2000-2004 ዓ.ም ያሉት)፣ የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መርሐ ትምህርቶች፣ እ.ኢ.አ. የ2004 እና የ2005 ዓ.ም በጥናቱ የታቀፉት ትምህርት ቤቶች የ፩ኛና የ፪ኛ መንፈቀ ዓመት ፈተናዎች፣ የፈተናዎች ኤጀንሲ ሰነድ (ራዕይ፣ ተልእኮና እሴቶችን የያዘ)፣ የትምህርት ፖሊሲ ሰነዶች በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል።

ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች መረጃዎችን ለመሰብሰብ ደግሞ፤ አንደኛ፣ ሁለት የጽሑፍ መጠይቆች፣ አንድ የተደራጀ የክፍል ምልከታ የሚካሄድበት ንድፍ/ ቅፅና የተለያዩ ሰነዶች መጠናዊ መረጃዎችን፣ ሁለተኛ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች፣ ቃለ መጠይቆችና የፖሊሲ ሰነዶች ደግሞ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት አገልግለዋል።

ጥናቱን ለማካሄድ ከ89 መምህራን በጽሑፍ መጠይቅ፣ ከ25 መምህራን በቡድን ተኮር ውይይት፣ ከ17 መምህራን በክፍል ምልከታ፣ ከዘጠኝ መምህራን ከክፍል ምልከታ በኋላ በከፊል-የተደረጀ ቃለ መጠይቅ፣ ከ303 ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ፣ ከአምስት ርዕሰ/ምክትል ርዕሰ መምህራን በቃለ መጠይቅ፣ ከ12 የዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤቶችና የዞን ትምህርት መምሪያ ኃላፊዎች በቡድን ተኮር ውይይት፣ ከሁለት የፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና ሁለት የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በከፊል-የተደረጀ ቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በሰነድ ትንተና ደግሞ የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርቶች፣ እ.ኤ.አ. ከ2000-2004 ዓ.ም የተዘጋጁት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች፣ እ.አ.አ. ከ2004 - የ2005 ዓ.ም. የተዘጋጁት በጥናቱ የተካተቱ የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ፭ኛና የ፪ኛ መንፈቀ ዓመት የዘጠነኛና የ10 ክፍል ፈተናዎች፣ እንዲሁም የፖሊሲ ሰነዶች ተመርምረዋል።

በዚህ ሁኔታ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላም መጠናዊ የሆኑት በስታትስቲካዊ (በመቶኛ፣ በአማካይ፣ በተዛምዶና በጎብረ-ድኅረት) ዘዴዎች፣ ዓይነታዊ የሆኑት ደግሞ በጭብጠቻቸው መሰረት በዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ መንገዶች ተተንትነዋል።

በዚህ መልክ በመጠናዊም ሆነ በዓይነታዊ መንገዶች በተካሄዱ የመረጃ ትንተናዎች የተገኙት ውጤቶች በምርምሩ ጥያቄዎች ቅደም ተከተል መሰረት እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል።

በየዓመቱ የሚዘጋጁ ብሔራዊ/ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች፣ ታላሚ ተፈታኞችን የመመዘን ደረጃና አዎንታዊ ወሽባክ ከፍ ለማድረግ፣ በፈተናዎች ኤጀንሲ የተለያዩ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ እየተደረጉ እንደሆነ የጥናቱ ግኝቶች አመላክቷል። ሆኖም እነዚህ ስትራቴጅዎች፣ አንደኛ Wall (2005) እንደገለጹት የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ በየትምህርት ቤቶቹ ወጥ (ተመሳሳይ) ትምህርት እንዲሰጥ፣ ሁለተኛ ሁሉም ጥያቄዎች በቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ላይ ተመስርተው እንዲዘጋጁ፣ ሦስተኛ በማስተማር-መማር ሂደቶቹ ወቅት በፈተናው ትኩረት የሚሰጣቸው የሰዋስው፣ የሥነ-ጽሑፍ፣ የአንብቦ መረዳትና የሌሎቹ ክሂሎች የጽንሰ ሀሳብ ትምህርት ክፍሎች ይዘቶች ትኩረት እንዲሰጣቸው ለማድረግ ቢያስችሉም በትምህርት ፖሊሲ ሰነዶችና በቋንቋው ትምህርት ላቅ ያለ ትኩረት

የተሰጣቸው አብዛኞቹ የቋንቋው ክሂሎች ችላ እንዲባሉ የሚያደርግ አሉተዊ ሚና እየተጫወቱ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። አዎንታዊ ወሽባክን ከፍ ለማድረግ ደግሞ ፈተናዎቹ የችሎታ መለኪያ (achievement) ፈተና ባህሪያትን እንዲያሟሉ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

‹‹የፈተና ጥያቄ አዘጋጆች ዓላማ በትምህርትነት የተካተቱ በጣም ጠቃሚ ክሂሎችንና እውቀቶችን መመዘን ነው፤" (Siddiek 2010)። ይህም አዎንታዊ ወሽባክን ያበረታታል (Siddiek 2010፣ Green 2007)። በዚህ ረገድ የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የአዕምሯዊ ምድብ ስድስት ችሎታዎች (የትምህርት ዓላማዎች) የሚሸፈኑባቸውና በተመጣጣኝ ናሙና የሚወከሉባቸው አለመሆናቸውን የጥናቱ ግኝት አረጋግጧል። ሰንጠረዥ 4.1. እንደሚያሳየው ከስድስቱ ዓላማዎች ከ90% በላይ የሚሆነውን ውክልና ያገኙት በዝቅተኛ የአዕምሯዊ ችሎታነት የሚታወቁት ዕውቀትና ግንዛቤ ናቸው። ሁለቱም ችሎታዎች ከማስታወስ ጋር የተያያዘ ዝቅተኛ ደረጃ የአእምሯዊ ምድብ ክፍሎች ናቸው። ሌላው መሰረታዊ ችግር እነዚህ ሁለት ችሎታዎች በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ፣ የሥርዓተ ትምህርት ማስፈፀሚያ ማዕቀፍና በቋንቋው ትምህርት የሥርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች ትኩረት ያልተሰጣቸው መሆናቸው ነው። በእነዚህ ሰነዶች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸውና የተማሪዎችን ጥልቅ አስተሳሰብ (Critical Thinking) የሚመለከቱ አዕምሯዊ ችሎታዎች ማለትም ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ በፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎችም በፈተናዎቹ ትኩረት እንደሚሰጣቸው ተገልፆ የነበረ ቢሆንም በተግባር የፈተናዎቹ ጥያቄዎች ሲፈተሹ ግን በተባለው መሰረት እንዳልተወከሉ ለማረጋገጥ ተችሏል። የጥናቱ ውጤት ያሳየው፣ እነዚህ አራት አዕምሯዊ ውስብስብ ችሎታዎች በፈተናዎቹ ችላ የተባሉ ክፍሎች መሆናቸውን ነው። ይህ ደግሞ (Siddiek (2010) እንዳሉት፣ እነዚህ በጣም አስፈላጊ/ ጠቃሚ ችሎታዎች በትምህርቱም ችላ እንዲባሉ የሚያደርግ ወይም አሉታዊ ወሽባክን የሚያበረታታ ተግባር ነው።

የፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በፈተናዎቹና በመርሐ ትምህርቶቹ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ አለ የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል። በሌላ በኩል ደግሞ የፈተናዎቹ አቀራረብ በምርጫ ጥያቄ መገደብ በቋንቋ ትምህርት የክሂሎች ትምህርት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ወሽባክ ሊፈጠር ይችላል የሚል

ግንዛቤ በድርጅቱ ኃላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች እንዳለ የጥናቱ ግኝት አመላክቷል። ሆኖም ችግሩን ከመገንዘብ ባለፈ የምርጫ ፈተና መሆኑ የቋንቋውን ክሂሎች ለመመዘን አለማስቻሉ እየፈጠረው ያለውን ችግር ለመፍታት የሚያስችል መፍትሄ በኤጀንሲው ገና እንዳልተገኘለት ለመረዳት ተችሏል። ለጊዜው መፍትሄው በራሳቸው በቋንቋው መምህራን እጅ ያለ ነው፤ የሚል እምነት ነው ያላቸው። መምህራኑ ክሂሎችን ትኩረት ሰጥተው ካስተማሯቸውና በክፍል ምዘናዎቻቸው እንዲካተቱ ካደረጓቸው ችግሩ የጎላ ላይሆን ይችላል የሚል እምነት በድርጅቱ ኃላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች እንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል።

ከዚህ ቀደም፣ በየትምህርት ዓይነቶቹ ከየትምህርት ቤቶቹ ይላክና ከማጠናቀቂያ ፈተናው ውጤት ጋር ይደመር የነበረው 30%፣ ትምህርት ቤቶቹ እየላኩ ያሉት ትክክለኛ የተማሪዎችን ችሎታ የሚያሳይ የምዘና ውጤት አይደለም በሚል ምክንያት ተቋርጦ እንደቀረ ለማወቅ ተችሏል። የተማሪዎችን ችሎታ በሚያሳይ መልኩ እንደገና እንዲጀመር የሚደረግበትን አሰራር ለማፈላለግ እየተደረገ ያለ ጥረት እንደሌለም የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ይህም አብዛኞቹ በምርጫ ላይሆን በተግባር የሚመዘኑ የቋንቋው ክሂሎች በክፍል ምዘናዎች እንዲካተቱ እየተደረጉ ከማጠናቀቂያ ፈተናዎች ውጤት ጋር እንዲደመሩ ሊደረግ የሚችልበትን አሰራር ለመፍጠር ፍላጎቱ እንደሌለ ያሳያል።

የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርት ምድቦች ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው በተለያዩ ሰንጠረዦች የቀረቡት መረጃዎችና የትንተና ውጤቶች አሳይተዋል። በጥናቱ ከተካተቱ አምስት የትምህርት ምድቦች መካከልም በተለይ በአራቱ ላይ ማለትም በማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ በክፍል ትምህርት ግምገማ፣ በተግባራት/ ጊዜ አመዳደብና በትምህርት ይዘቶች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ አማካይ ጠንካራ ሆኖ ተገኝቷል። በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የጥንካሬ ደረጃ ደግሞ መካከለኛ እንደሆነ የትንተና ውጤቱ አሳይቷል። ይህም መምህራኑ የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በአብዛኛው የትምህርት ምድቦች (በተግባራት፣ በትምህርት መሳሪያዎች፣ በይዘቶችና በክፍል ትምህርት ምዘናቸው) ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ ያሳድራል የሚል ግንዛቤ እንዳላቸው ያመላክታል። በማስተማሪያ ዘዴዎቻቸው ምርጫ ላይም ቢሆን ጠንካራ

በሚባል ደረጃ አይሁን እንጂ ፈተናው ተዕዕኖ እንደሚያሳድር የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ይህም ግኝት በክፍል ምልከታ፣ ከመምህራኑ ጋር በተካሄዱት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶችና ከክፍል ምልከታ በኋላ በተካሄዱት ቃለ መጠይቆች ከተገኘው ውጤት ጋር ተደጋጋፊ/ ተመሳሳይ ነው።

በቀደምት ተመራማሪዎች ለወሽባክ መከሰት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ እየተባሉ ከሚጠቀሱት ጉዳዮች/ ተላውጠዎች መካከል ከመምህራንና ከዐውድ ጋር የሚያያዙት በዚህ ጥናት ዐውድ ተመርምረዋል። በተደረገው ምርመራም ከመምህራን ባህሪያትም ሆነ ከዐውድ ጋር የተያያዙት ተላውጠዎች ለወሽባክ መከሰት ጠንካራ ወይም መካከለኛ በሚባል ደረጃ ምክንያት እንደሚሆኑ ማረጋገጥ ተችሏል። በዚሁ መሰረት ከመምህራን ጋር ከሚያያዙት መካከል አንደኛ ለማስተማር ሙያ የሚሰጡት ክብር ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ ሁለተኛ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው እውቂያ፤ ከዐውድ ጋር ከሚያያዙት መካከል ደግሞ አንደኛ፣ የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በማስተማር ላይ የሚፈጥረው ጫና፣ ሁለተኛ ለቋንቋው ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠንና ሦስተኛ የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ /ዳራ የመምህራኑ የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ፈተና ተኮር እንዲሆን ጠንካራ ጫና የሚፈጥሩ ምክንያቶች ሆነው ተገኝተዋል። ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤና ውጫዊ ጫናዎች ደግሞ መካከለኛ በሚባል የጥንካሬ ደረጃ ለወሽባክ መከሰት ምክንያቶች እንደሆኑ የትንተና ውጤቱ አሳይቷል። በሌሎች መረጃ መሰብሰቢያዎች ተሰብስበው የተተነተኑት መረጃዎች ውጤቶችም ይህንኑ ያንጸባረቁ ናቸው። ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ የተለያዩ መንስኤዎች እንዳሉት ያመላክታል።

መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተዕዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ /perceptions) (በጥገኛ ተላውጠው) እና በመምህራን ባህርያት (በዐቢይ ተንባይ ተላውጠዎች)፣ እንዲሁም መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተዕዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤና በዐውዳዊ ባህርያት መካከል ያለውን ተዛምዶ በተመለከተ አንደኛ፣ መምህራን ፈተናው በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ስለሚያሳድረው ተዕዕኖ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጠውና መምህራን ስለማስተማር ሙያ ባላቸው ግንዛቤ መካከል አዎንታዊ

(direct)፣ ጉልህ (P < 0.05) እና ጠንካራ (strong_r = 0.523) ተዛምዶ እንዳለ የትንተና ውጤቱ አሳይቷል። ይህም መምህራን ተማሪዎቻቸው በማጠናቀቂያ ፈተናው ጥሩ ውጤት ካመጡ ሙያዊ ኃላፊነታቸውን/ ግዴታቸውን በአግባቡ የተወጡ ሆኖ እንደሚሰማቸው፤ በአንፃሩም ዝቅተኛ ውጤት ካመጡ ደግሞ መስራት የነበረባቸውን ተግባር/ ሙያዊ ኃላፊነት በአግባቡ ያልሰሩ/ ያልተወጡ ወይም ተገቢ ዝግጅት እያደረጉ የማስተማር ስራቸውን ያላከናወኑ ሆኖ እንደሚሰማቸው የሚያሳይ ነው። ሁለተኛ፣ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጦው) እና መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ጠቀሜታ ባላቸው ግንዛቤ መካከል አዎንታዊ፣ ጉልህና መካከለኛ ተዛምዶ መኖሩን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። ይህም መምህራን ተማሪዎች በቋንቋው ፈተና የሚያስመዘግቡት ውጤት ለቀጣይ የትምህርትም ሆነ የሥልጠና እድል የሚጠቅማቸው ሆኖ ባገኙት ቁጥር የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖም ከፍ እያለ እንደሚሄድ የሚያሳይ ነው። ሦስተኛ፣ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጦውና መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው እውቅያ መካከልም እንዲሁ አዎንታዊ፣ ጉልህና መካከለኛ ተዛምዶ መኖሩን የትንተና ውጤቱ አሳይቷል። ከዚህም መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ይዘትና ቅርጽ ያላቸው እውቂያ እየጨመረ ሲሄድ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ዝግጅትና ትግባራ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖም ጉልህና መካከለኛ በሚባል ደረጃ እየጨመረ እንደሚሄድ መረዳት ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ጾታ፣ የማስተማር ልምድና የስራ ላይ ሥልጠና ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ጉልህ ያልሆነና በጥንካሬም ጾታ መጠነኛ፣ ሌሎቹ ዝቅተኛ ዝምድና እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። በተለይ የትምህርት ደረጃ፣ የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ ላይ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ካላቸው ግንዛቤ/ ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ያላቸው ዝምድና አቅጣጫም ተገላብጧዊ (Inverse) ነው። ይህም የመምህራን የትምህርት ደረጃ እያደገ ሲሄድና በስራ ላይ ስልጠና የሚኖራቸው ተሳትፎ እየጨመረ ሲሄድ የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ እየቀነሰ እንደሚሄድ ያሳያል።

መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤና በዐውዳዊ ባህርያት መካከል ያለው ተዛምዶ የውጤት ትንተና እንዳሳየው ደግሞ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጦው) እና መምህራን የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በማስተማር ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ባላቸው ግንዛቤ መካከል ብቻ አዎንታዊ፣ ጉልህ ($P < 0.001$) እና በጥንካሬ ደረጃ መካከለኛ ተዛምዶ መኖሩን አሳይቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ መምህራን ስለክፍለ ጊዜ መጠን ባላቸው ግንዛቤና ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጦው)፣ መምህራን ስለተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ/ዳራ ባለቸው ግንዛቤና በጥገኛ ተላውጦው፣ በተማሪ-ክፍል ጥምርታና በጥገኛ ተላውጠው፣ መምህራን የቋንቋ ምዘናን በሚመለከት ስለወሰዱት ኮርስ ባላቸው ግንዛቤና በጥገኛ ተላውጦው መካከል ያለው ተዛምዶ አቅጣጫ አሉታዊ፣ ጉልህ ያልሆነና የጥንካሬ ደረጃው ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ይህም በጥናቱ ዐውድ ከዐውዳዊዎቹ ይልቅ ከመምህራን ጋር የተያያዙት ምክንያቶች ይበልጥ ለወሽባክ መከሰት መንስኤ እንደሚሆኑ የሚያመላክት ነው።

ተዋረዳዊ (sequential) በመባል የሚታወቀውን የጎብረ-ድጎረት ዘዴ በመጠቀም በተካሄደው ትንተና ደግሞ መምህራን ስለማስተማር ሙያ፣ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ጠቀሜታ፣ ስለስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ፣ ስለየተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በማስተማር ላይ ስለሚፈጥረው ጫና፣ ስለተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ/ዳራ፣ ስለተማሪ-ክፍል ጥምርታ ያላቸው ግንዛቤና የትምህርት ደረጃ፣ የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ዝግጅታቸውና ትግበራቸው ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ ላዳበሩት ግንዛቤ በጣምራ 44% ያህል ተፅዕኖ እንደሚፈጥሩ የትንተና ውጤቱ አመልክቷል። ይህም በጥናቱ የተካተቱት እነዚህ ነፃ ተላውጠዎች መምህራኑ ስለፈተናው ተፅዕኖ ላዳበሩት ግንዛቤ ከፍተኛ ጫና የመፍጠር ሃይል ያላቸው መሆኑን ያሳያል።

ሌላው በዚሁ በተዋረዳዊ ዘዴ የተካሄደው ትንተና R ካሬ ለውጥ (R square change) ውጤት እንዳሳየው ከእነዚህ ስምንት ነፃ/ተንባይ ተላውጠዎች መካከል 0.278 ወይም 28% አስተዋፅኦ በማበርከት አንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው መምህራን ስለማስተማር ሙያ ያላቸው

ግንዛቤ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ነው፡፡ እያንዳንዳቸው አራት አራት ፐርሰንት ተፅዕኖ በማሳደር በሁለተኛ ደረጃነት የሚከተሉት ደግሞ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው እውቂያና ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ የሚሉት ናቸው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት የመምህራን የትምህርት ደረጃ፣ መምህራን የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በማስተማር ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖና የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ/ዳራ ላይ ያላቸው ግንዛቤ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ሦስት የወሸባክ መከሰቻ ምክንያቶች (ነጻ ተላውጠዎች) እያንዳንዳቸው ሁለት፣ ሁለት ፐርሰንት መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ (በጥገኛ ተላውጠው) ላይ ጫና እንዳሳደሩ የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡ የቀሩት ሁለቱ ማለትም መምህራን ስለስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎና ተማሪ-ክፍል ጥምርታ ያላቸው ግንዛቤ ደግሞ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ /ወይም በጥገኛ ተላውጠው ባህሪ ላይ አንድ አንድ ፐርሰንት አስተዋፅኦ ያበረከቱ ናቸው፡፡

መደበኛ የህብረ-ድኅረት ዘዴን በመጠቀም የተካሄደው የመደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ (standard regression coefficient - Beta) ትንተና ውጤት እንዳሳየው ደግሞ እያንዳንዱ የወሸባክ መከሰቻ ምክንያት (ነፃ/ ተንባይ ተላውጠ)፣ መምህራን ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተጽዕኖ ባላቸው ግንዛቤ/ በጥገኛ ተላውጠው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የተለያየ ነው፡፡ በጥንካሬ ደረጃ ግን ከአንዱ (የስራ ላይ ስልጠና ተሳትፎ) በስተቀር የቀሩት ሰባቱ መጠነኛ (0.1-0.3) በሚባለው ምድብ ውስጥ የሚገኙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ከስምንቱ፣ የስራ ላይ ሥልጠና ተሳትፎ ላይ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ የሚለው ተላውጠ ብቻ ለጥገኛ ተላውጠው ባህርይ ያበረከተው አስተዋጽኦ ጥንካሬ ደረጃ ዝቅተኛ/ ደካማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በጸታ ስብጥር ተቀራራቢነት ያላቸው፣ ከከተማ፣ ከከፊል ከተማና ከገጠር ትምህርት ቤቶች በእድል ሰጭ ንሞና ዘዴ ተመርጠው በመረጃ ምንጭነት ከተሳተፉት ተማሪዎች የተገኘው የመረጃ ትንተና ውጤት እንዳሳየው፤ ተማሪዎች የማጠናቀቂያ ፈተናው በአብዛኞቹ መምህራን በትምህርቱ ሂደት አልፎ አልፎ ይነሳል፤ መምህራኑና ተማሪዎቹ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን በክፍል ውስጥ ለመስራት የሚያውሉት ጊዜ አለ የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ የመምህራኑን የማስተማሪያ ተግባራት በተመለከተም የየክፍለ ጊዜው አብዛኛው ሰዓት በመምህራኑ ንግግር ይያዛል፤ ቋንቋ/ ሰዋስው ነክ የሆኑ ትምህርቶችን ማብራራት

ዋነኛው የማስተማሪያ ተግባር ነው ብለው ያምናሉ፡፡ የመማሪያ መጽሐፎቹን ምንባቦች ይዘት ማብራራትና የመልመጃዎችን አሰራር ማስረዳት ደግሞ በሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃነት የሚገኙ የመምህሮቻቸው የማስተማሪያ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው የሚል አመለካከት አላቸው፡፡

የተማሪዎችን የመማሪያ ተግባራት በሚመለከት በትምህርቱ ሂደት ትኩረት በማግኘት አንደኛው ሰዋስው፣ ሁለተኛው ሥነ-ጽሑፍ ፣ሦስተኛው የንባብ ክሂል ናቸው የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚያደርጓቸውን ልምምዶች በተመለከተም በተግባቦታዊ ትምህርት ሰፊ ተቀባይነት ካላቸው የጥንድ፣ የቡድንና የግል ስራዎች ይልቅ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን ለመስራት የተሻለ ጊዜ ይሰጣል የሚል ዕምነት አላቸው፡፡ ከክፍል ውጭ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር ይበልጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ተግባሮች ናቸው ብለው ✍የሚያምኑትም አንደኛ ለ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና የሚያግዙ መጽሐፎችን ማንበብ፣ ሁለተኛ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን እየሰሩ መለማመድ የሚሉትን ነው፡፡

የመማር ግጽታዎችን በሚመለከት ደግሞ ተማሪዎች የቋንቋውን ትምህርት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ይልቅ ሕይወታዊ፣ መልመጃዎቹ ሳቢ፣ ከመምህሮቻቸውና ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ለመግባባት የተሻለ እድል የሚሰጥ፣ ከወደፊት የስራ ዓለም ሕይወት ጋር የሚዛመድ ዕውቀት የሚያስገኝ ወደቀጣዩ የትምህርት ደረጃ ለመዛወር የሚረዳ የትምህርት ዓይነት ሆኖ እንዳገኙት የትንተና ውጤቱ አሳይቷል፡፡ ይህም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ከሚማሯቸው ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማነጻጸር የተሰጠ አስተያየት ነው፡፡

ከፈተና ጋር ተያይዘው ለተጠየቁት ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ ትንተና ውጤት እንዳሳየው ደግሞ አብዛኞቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ራሳቸውን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት ጠንካራ በሚባል ደረጃ ልምምድ ያካሂዳሉ፡፡ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን በመስራት የቋንቋ ችሎታን ማሻሻል ይቻላል ብለው ያምናሉ፡፡ ፈተና ጠቃሚ የቋንቋ መማሪያ ስልት ነው ብለው ያስባሉ፡፡ የፈተና መኖር ተማሪዎችን ጠንክረው እንዲያጠኑ ያደርጋቸዋል የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ የፈተና ውጤት ተማሪዎች እንዲደስቱ ወይም እንዲከፉ ያደርጋል ብለው ያምናሉ፡፡

ከዚህም የፈተና ጉዳይ በተማሪዎች ዘንድ ምን ይህል ክብደትና ትኩረት እንደሚሰጠውና የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና በቋንቋው ትምህርት ላይ ምን ያህል ተጽእኖ እያሳደረ እንዳለ፣ የተጽዕኖ ደረጃውም ክፍተኛ እንደሆነ፣ አቅጣጫውም በአብዛኛው አሉታዊ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

በተማሪዎች የተገኙት የጥናቱ ግኝቶችም ከመምህራኑ በተለያዩ መንገዶች ተሰብስበው ከተተነተኑት መረጃዎች ውጤት ጋር በአብዛኛው የሚደጋገፉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደቶችን በተመለከተ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተሰብስቦ የተነተነው መረጃ ውጤት እንዳሳየው፤ የቋንቋው ትምህርት በተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ መንገድ እየቀረበ አይደለም፡፡ የቋንቋው ትምህርት በተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ መንገድ እየቀረበ አለመሆኑን ካመላከቱ ማስረጃዎች መካከልም አንዱ በክፍል ውስጥ ብዙ የሚናገሩት ተማሪዎች ሳይሆኑ መምህራኑ መሆናቸው ነው፡፡ ሁለተኛው በማስተማር-መማር ሂደቶች ትኩረት የሚሰጣቸው የትምህርቱ ዓላማዎች/ ይዘቶች አንደኛ የሰዋሰው፣ ሁለተኛ የሥነ-ጽሑፍ፣ ሦስተኛ የንባብ ክሂልና አራተኛ ሌሎች ክሂሎችን የሚመለከቱ የጽንሰ ሀሳብ ትምህርቶች እንዲሁም ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች መሆናቸው ነው፡፡ በመርሐ ትምህርቶቹና በመማሪያ መጽሐፎቹ ሰፊ ትኩረት የተሰጣቸው የክሂሎቹ ተግባራዊ ትምህርቶች ችላ ተብለው የሚታለፉ ናቸው፡፡ የትምህርት ይዘቶቹ በአብዛኛው የሚመረጡት በመምህራኑ ነው፤ የተማሪዎቹ ተሳትፎ አይጨመርበትም፡፡ የሚመረጠው የመማሪያ ዘዴ ማዳመጥ ነው፡፡ ሌሎቹ በተግባቦታዊ ትምህርት ትኩረት የሚሰጣቸው የመማሪያ ዘዴዎች ቦታ ተነፍጓቸዋል፡፡

5.3. መደምደሚያ

የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን፣ በተማሪዎችና ሌሎች የትምህርት ባለድርሻ አካላት ግንዛቤና ተግባራት ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ እንደሆነ፣ እንዲሁም በማጠናቀቂያ ፈተናውና በአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች፣ በማጠናቀቂያ ፈተናውና በቋንቋው መርሐ ትምህርቶች ዓላማዎች መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ (Overlapping) እንደሌለ የጥናቱ

ግኝቶች አሳይተዋል፡፡ በቋንቋ መርሐ ትምህርቶችና በክፍል ፈተናዎች መካከል ያለው ግንኙነትም አሉታዊ እንደሆነ የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡ ከእነዚህ ከጥናቱ ግኝቶች ላይ በመመስረትም የሚከተሉት መደምደሚያዎች ቀርበዋል፡፡

የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው በትምህርት ሚኒስቴር በፈተናዎች ኤጀንሲ የሚዘጋጁ የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን የጥራት ደረጃና አዎንታዊ ወሽባክ ከፍ ለማድረግ የተለያዩ ስትራቴጂዎች ተነድፈው ተግባራዊ እየተደረጉ ነው፡፡ አዎንታዊ ወሽባክን ለማበረታታትም ፈተናዎቹ የችሎታ መለኪያ ፈተናን ባህርያት የሚያሟሉ፣ በተለይም ደግሞ የሥርዓተ ትምህርቶቹ ነፀብራቅ፣ የአዕምሯዊ ምድብ ትምህርት ዓላማዎችን ያገናዘቡ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው የሚል እምነት በድርጅቱ ኃላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች እንዳለ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፈተናው በምርጫ ጥያቄ ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆኑ በተለይ በቋንቋ ትምህርት፣ የቋንቋው ክሂሎችን (ከንባብ በስተቀር) በቀጥታ ለመመዘን እንዳልተቻለና በዚህ ረገድ ፈተናው በክሂል ትምህርቶች አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል በኤጀንሲው እንደሚታመን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ ሆኖም አንደኛ የማጠናቀቂያ ፈተናው በሌሎች አገሮች ካለው ዘመናዊ የቋንቋ ፈተና ዝግጅትና አሰጣጥ ልምድ ጋርም ሆነ ከሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲና ከሥርዓተ ትምህርቶቹ ጋር የሚጣጣም እንዲሆን በማድረግ ወይም ክሂሎቹ በተግባር የሚመዘኑበትን መንገድ በማፈላለግ በኩል ያለው ዝግጁነት ደካማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ገና ወደፊት ሶፍት ዌር ከተገኘ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል ከሚል የዘለለ ሃሳብ አልዳበረም፡፡ እንዲህ ያለውን ችግር በተወሰነ ደረጃ ሊያቃልል ይችል የነበረው፣ በሌሎች አገሮችም የተለመደው አሰራር የክፍል ምዘና ውጤቶች ከማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጋር የሚደመሩበትን ስልት ማመቻቸትና ተግባራዊ ማድረግ ነበር፡፡ ሆኖም በዚህ በኩል ያለው ተነሳሽነት ደካማ ነው ተብሎ የሚደመደም ነው፡፡

የጥናቱ ውጤት እንዳሳየው በማጠናቀቂያ ፈተናውና በአዕምሯዊ የትምህርት ምድብ ዓላማዎች/ ችሎታዎች፣ በማጠናቀቂያ ፈተናውና በቋንቋ ትምህርት መርሐ ትምህርቶች ዓላማዎች እንዲሁም በቋንቋው መርሐ ትምህርቶችና በክፍል ፈተናዎች መካከል ተጣጥሞሽ (overlapping) ወይም አዎንታዊ ተዛምዶ የለም፡፡ በተለይ በአዕምሯዊ ምድብ ስድስት የትምህርት ዓላማዎችና በፈተናዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት አሉታዊ ብቻ

ሳይሆን በጣም ጠንካራና ጉልህ የሆነ አሉታዊነት የሚታይበት ነው፡፡ ለምሳሌ በፈተናዎቹ የተሻለ ውክልና እንዲያገኙ የሚጠበቁት ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ በፈተናዎቹ ያገኙት ውክልና ከ10% በታች ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቋንቋው ሥርዓተ ትምህርትም ሆነ በትምህርት ፖሊሲውና ሌሎች ሰነዶች ብዙም ቦታ ያልተሰጣቸው፣ እውቀትና ግንዛቤ ከ90% በላይ በሆኑ ጥያቄዎች እንዲወክሉ ተደርገዋል፡፡ የክፍል ፈተናዎች የትምህርቱ ዓላማዎች ሳይሆን የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ነፀብራቅ ሆነው መገኘታቸውም እንዲሁ የፈተናዎቹን ወሸባክ አሉታዊነት የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህም የማጠናቀቂያ ፈተናው የአዕምሯዊ ምድብና የቋንቋው ትምህርት ዓላማዎች በማስተማር-መማር ሂደቶች በአግባቡ ተግባራዊ እንዳይደረጉና የክፍል ፈተናዎች የትምህርቱ ነፀብራቅ እንዳይሆኑ እንቅፋት እየሆነ ወይም አሉታዊ ሚና እየተጫወተ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደተቻለው መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የማጠናቀቂያ ፈተናው በቋንቋው ትምህርት አሰጣጥ ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ ሁለቱም የማጠናቀቂያ ፈተናው የማስተማር-መማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንዲሆን እያደረገ ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ በመምህራኑና በተማሪዎች እምነት፣ በምልከታም እንደተረጋገጠው ፈተናው ተፅዕኖ እያሳደረ ያለውም በመሰረታዊ የትምህርት ምድቦች ላይ ነው፡፡ በፈተናው ጫና የሚደርስባቸው የትምህርት ምድቦችም የትምህርቱ ተግባራት፣ የትምህርቱ ይዘቶች፣ የትምህርት መሣሪያዎች፣ የክፍል ምዘናዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ይህም የቋንቋው ትምህርት ሥርዓተ ትምህርቱ በተመሰረተበት በተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት ፍልስፍናና መርሆዎች እንዳይመራና ክሂሎቹ በትምህርቱ አሰጣጥ ችላ እንዲባሉ አድርጓል የሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሳል፡፡

ከመምህራን ባህርያትና ከዐውድ ጋር ከተያያዙት ተላውጦዎች መካከል አብዛኞቹ በዚህ ጥናት ዐውድም ለወሸባክ መከሰት ምክንያት እንደሚሆኑ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ በጥናቱ ከተካተቱት እነዚህ ተላውጦዎች መካከልም ለወሸባክ መከሰት ዋነኛ ሆነው የተገኙት መምህራን ለማስተማር ሙያ ያላቸው ግንዛቤ፣ ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላቸው ዕውቂያ፣ ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያመጡት ውጤት ስላለው ጠቀሜታና የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በማስተማር ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይ ያላቸው ግንዛቤ የሚሉት ምክንያቶች (factors) ናቸው፡፡

ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደተቻለው የማጠናቀቂያ ፈተናው በቋንቋው ትምህርት ላይ እያሳደረ ያለው ተፅዕኖ ከወሽባክ ገፅታዎች (መለኪያዎች/ dimensions) አንፃር ሲመረመር ደግሞ አቅጣጫው አዎንታዊም አሉታዊም ሆኖ ተገኝቷል። ሆኖም ከአዎንታዊዎቹ ይልቅ አሉታዊዎቹ ይበዛሉ። አሉታዊዎቹን ጉልህና የመማር-ማስተማር ሂደቱን ጠንካራ በሚባል ደረጃ የሚያደናቅፉ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል። ከንጥልነትና ጥቅልነት የወሽባክ ገፅታ/መለኪያ አንፃር ሲታይም ሁለቱም ባህሪያት እንደሚከሰቱ የጥናቱ ግኝት አሳይቷል።

የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው ውጫዊ (macro) የትምህርት ባለድርሻ አካላት በብሔራዊ ደረጃ የሚዘጋጁ የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን የሚመለከቷቸው እንደትልቅ ነገርና እንደተገቢ የሆነ የትምህርት አሰጣጥና የትምህርት ጥራት መለኪያ አድርገው ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። ለዚህም መደምደሚያ ብዙ አስረጅዎች አሉ። ከእነዚህ አንዱ በየዓመቱ በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥሩ ውጤት ለሚያስመዘገቡ ትምህርት ቤቶችና ተማሪዎች በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ የሚከናወኑ የሽልማት ሥነ-ሥርዓቶች ይበልጥ ተቀባይነት እያገኙ እየመጡ መሆናቸው ነው። ሁለተኛው እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፣ ወረዳ፣ የዞን ከተማ አስተዳደርና የዞን ትምህርት መምሪያ በየትምህርት ዓይነቱ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የተሻለ ውጤት በማስመዝገብ (በማስመጣት) የሚገኙበትን ደረጃ (ስንተኛ እንደወጡ) የሚያሳይ ስታቲስቲክስና ማብራሪያ በክልል ትምህርት ቢሮ ሳይቀር እየተዘጋጀ በየዓመቱ እንዲደርሳቸው የሚደረግበት ሥርዓት መዘርጋቱ ነው። የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ደካማ እንደሆነ እየታወቀ ተማሪዎች በምርጫ ፈተና የሚያመጡትን የተሻለ ውጤት መለኪያ በማድረግ ለቋንቋው ትምህርት አሰጣጥ ድጋፍ መንፈግና በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ዝቅተኛ ውጤት ለሚመጣባቸው የሳይንስና የሂሳብ ትምህርቶች ልዩ ልዩ ድጋፍ ማድረግም ሌላው ውጫዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተፅዕኖ ሌላ አስረጅ ነው።

የጥናቱ ውጤት እንዳሳየው በትምህርት ቤት ደረጃ ይዘጋጁ የነበሩት የዘጠነኛና የ10ኛ ክፍል የክፍል ፈተናዎች ከትምህርት ቤት እየወጡና በዞን ከተማ አስተዳደርና በዞን ትምህርት መምሪያዎች እንዲዘጋጁ እየተደረገ ነው። የመንፈቀ ዓመት የማጠቃለያ ፈተናዎችም ከ40% ወደ 60% እንዲያድጉ እየተደረገ ነው። 20% ደግሞ በቴስት እንዲሸፈን እየተደረገ ነው። ይህም፣ የትምህርት ሥርዓቱ በመርህ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት

የነበረውን የተከታታይ ምዘና አስተሳሰብ ችላ እያለ ወደ ፈተና እየተመለሰ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናው አሉታዊ ተፅዕኖ አንድ ውጤት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ በዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤቶችና በዞን ትምህርት መምሪያዎች የሚዘጋጁ ፈተናዎች በሙሉ የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ሞዴል የሚያደርጉና በምርጫ ብቻ የሚዘጋጁ ናቸው። የሥርዓተ ትምህርቶቹ ነፀብራቅ እንዲሆኑ የሚደረግ ብዙም ጥረት የለም። ሌላው ቀርቶ በትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ክፍል የሚዘጋጁ የብቃት ፈተናዎች እንኳ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ግልባጭ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው። ከዚህ ተነስቶ በፈተናዎቹ ኤጀንሲ የሚዘጋጁ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች የትክክለኛ ችሎታ መለኪያ፣ የትምህርት አሰጣጥ አቅጣጫ አመላካችና የትምህርት ጥራት ማሳያ እስከመሆን የዘለቀ ጫና እያሳደሩ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል። ይህም አበበ (1990) እንዳሉት የክልሉ (ምናልባትም የሀገሪቱ) ትምህርት እየተመራ ያለው በትምህርት ፖሊሲውና በሥርዓተ ትምህርቶች ሳይሆን በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ እንደሆነ የሚያመላክት ነው። የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጫና በትምህርት ቤት ደረጃ የተገደበ እንዳልሆነና በሌሎች ውጫዊ የትምህርት ባለድርሻ አካላት/ ክፍሎች ላይም ጉልበቱን እያሳየ እንደሆነ ያመላክታል።

5.3. መፍትሄ

የጥናቱ ውጤቶች በየዓመቱ የሚዘጋጁትና የሚሰጡት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች በቋንቋው ትምህርት ግልፅ፣ ጠንካራና ይበልጥም አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደሩ እንደሆነ አመላክተዋል። የመምህራንና የተማሪዎችን ግንዛቤና ተግባር ፈተና ላይ ያተኮረ (የተመሰረተ) እንዲሆን አድርጎታል። የቋንቋውን ትምህርት ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ከመስራት ይልቅ መምህራኑ ተማሪዎችን ለፈተና ማዘጋጀት ላይ፣ ተማሪዎቹ ለፈተና መዘጋጀት ላይ እንዲያተኩሩ እያደረገ ነው። ይህም የተለያዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት (educational parties/ stake holders) የፈተናውን አወንታዊ ወሸባክ ከፍ የሚያደርጉ/ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ እርምጃዎችን ሊወሰዱ እንደሚገባቸው የሚያመላክት ነው። ስለዚህ የሚፈለጉትን የመማር ውጤቶች ማሳካት ይቻል ዘንድ ከጥናቱ ግኝቶች ላይ በመመስረት የሚከተሉት መፍትሄዎች ቀርበዋል።

አንደኛ፡ የመማር ማስተማሩ ሂደት በተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት መንገድ እንዲሰጥና የቋንቋውን ትምህርት ዓላማዎች በማሳካት ላይ እንዲያተኩር በሌሎች አገሮች እንደሚደረገው ሁሉ በፈተናዎች ኤጀንሲ የቋንቋው ክሂሎች በተግባር የሚመዘኑባቸው መንገዶች ቢፈለጉ፤ ከዚህ በተጨማሪ ለጊዜው በኤጀንሲው ሊመዘኑ የማይችሉ የቋንቋው ክሂሎች ተለይተው በዞን ትምህርት መምሪያዎችና ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤቶች የፈተና ክፍል አስተባባሪነት እነዚህ ክሂሎች በትምህርት ቤት ደረጃ በትክክል የሚመዘኑበት ሥርዓት ተዘርግቶ የሚገኘው ውጤት እንደቀድሞው ከማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ውጤት ጋር የሚደመርበት አሰራር እንደገና እንዲጀመር ቢደረግ፡፡

ሁለተኛ፡ ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ የአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች በተለይም ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ በፈተናዎቹ ጥያቄዎች እንዲሸፈኑና ተገቢ ውክልና እንዲያገኙ በምዘና (measurement) ባለሙያዎች እንዲታዩ ወይም የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ይህን የተመለከተ ሥልጠና እንዲያገኙ ቢደረግ፡፡ እንዲሁም የድርጅቱ የፈተና ሥርዓት ከምርጫ እስኪወጣ ድረስ በምርጫ ፈተና መወከል የሚችሉ ክፍሎች በመርሐ ትምህርቶቹ በተሰጣቸው ትኩረት መሰረት ተመጣጣኝ ውክልና እንዲያገኙ ቢደረግ፡፡

ሦስተኛ፣ የክፍል ፈተናዎች የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ሳይሆን የቋንቋው ትምህርት ነፀብራቅ የሚሆኑበት አሰራር ቢቀየስ፡፡ በወረዳ፣ በዞን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤቶችና በዞን ትምህርት መምሪያዎች የተጀመሩትን የዘጠነኛና የ10ኛ የክፍል ፈተናዎች የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ለማስመሰል እየተደረገ ያለው ጥረት የሚታረምበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል፡፡ የትምህርት ጥራቱን ደረጃ ለማረጋገጥ እየተባሉ የሚዘጋጁት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን የሚመስሉ በወረዳ፣ በዞን...የሚዘጋጁ ፈተናዎች የትምህርት ጥራት መምጣት አለመምጣቱን የሚያረጋግጡ ሳይሆኑ፣ ስለትምህርት ጥራት የተሳሳተ መረጃ የሚሰጡ ዓይነት ስለሆኑ በሌሎች በትክክል የትምህርቶቹ ዓላማዎች መሳካት አለማሳካታቸውንና የትምህርቱ ጥራት እየተሻሻለ መምጣት አለመምጣቱን መመዘን በሚያስችሉ ፈተናዎች ሊተኩ ይገባቸዋል፡፡

አራተኛ፣ መምህራንን ከዘመናዊ የቋንቋ ማስተማሪያ መንገዶች ጋር ለማስተዋወቅ የሚያስችሉ ተከታታይ የሥራ ላይ ስልጠና ዕድሎች ቢፈጠሩ፡፡ ከቡድን ውይይቶችና ከክፍል ምልከታዎች የተገኙት መረጃዎች እንዳሳዩት የብዙ መምህራን ምርጫና ችሎታ አንድን የትምህርት ይዘት በገለፃ ማቅረብ ነው፡፡ ሌሎች አሳታፊ የሚባሉ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለምሳሌ በቡድን ለማወያየት፣ በጥንድና በግል ለማሰራት አልፎ አልፎ ሲሞክሩም አይሳካላቸውም፡፡ ይህም በአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች እየተጠቀሙ የማስተማር ክሂሉና ልምዱ ስለሌላቸው የተከሰተ ችግር ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ሌላው ቀርቶ በቡድን ወይም በጥንድ ወይም በግል ምን፣ እንዴት፣ ለምን ያህል ጊዜ፣ ወዘተ. እንደሚሰሩ እንኳ ግልፅ መመሪያ ሲሰጡ አይታዩም፡፡ እነሱም ከሙያቸው ጋር የተያያዙ የሥራ ላይ ስልጠናዎች የማያገኙ በመሆናቸውም ተከፍተዋል፡፡ ስለዚህ (በዩኒቨርሲቲዎች ወይም በሌላ ቦታ ያሉ ባለሙያዎችን በመጠቀም ሊሆን ይችላል)፣ መምህራኑ የሥራ ላይ ስልጠናዎች እንዲያገኙ ቢደረግ አንድ የችግር ማቃለያ መንገድ ነው፤ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በሌላው ዓለምም ባህል የሆነ ጉዳይ ነው፡፡

አምስተኛ፣ የቋንቋው ክፍለ-ጊዜ በክልሉ ትምህርት ቢሮ ሳይሆን ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው የክፍለ ጊዜ ድልድል ቢመራ፡፡ በጥናቱ ሂደት ማረጋገጥ እንደታቻለው በሥርዓተ ትምህርት ማስፈጸሚያ ሰነዱ ላይ በቀን ሰባት ክፍለ ጊዜ በሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች ለአፍ-መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ መጠን በሳምንት አራት ነው፡፡ ሆኖም ጥናቱ በተካሄደበት ክልል ይህ መመሪያ ተግባራዊ እየተደረገ አይደለም፤ተግባራዊ የማድረግ ፍላጎት መኖሩን የሚያሳይ ምልክትም የለም፡፡ መምህራኑ ደግሞ መሰረታዊ ችግር አድርገው የሚያቀርቡት የክፍለ ጊዜውን ማነስ ነው፡፡ ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው ደግሞ ይኸ ጉዳይ የክልሎች ሳይሆን የትምህርት ሚኒስቴር ስልጣን ነው፡፡ ስለዚህ ክልሉ አንድም አማርኛ ቋንቋን እንደ አፍ-መፍቻ ቋንቋ የማይታይበትን ተጠየቅ ማሳየት አለበት፤ ወይም በማዕከላዊ መንግሥት የተደለደለውን የክፍለ ጊዜ መጠን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ስድስተኛ፣ የመምህራን ቁጥጥር፣ ግምገማ፣ የሥራ አፈፃፀምና የድግፍ አሰጣጥ ሥርዓትን መቀየር/ ማሻሻል ቢቻል፡፡ አሰሪ መስሪያ ቤታቸው በመምህራን ላይ የሚያደረገው ቁጥጥር ክትትልና ግምገማ ከማስተማር ተግባራቸው ላይ የተመሰረተ አይደለም የሚል የመምህራን

እምነት አለ፡፡ መምህራኑ በተለይ በቡድን ውይይቶች እንዳንፀባረቁት በመምህራን ላይ የሚካሄደው ቁጥጥር፣ ክትትልና ግምገማ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ በማዳበር ላይ ሳይሆን ክሂሎችን እንደማያካትቱ የሚታወቁትን የብሄራዊና የክፍል ፈተናዎች ውጤት በማሻሻል ላይ ያተኮረ ግብን በማሳካት አለማሳካት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህም ዋነኛ ተግባራቸው የሆነው የትምህርቱን ዓላማዎች የማሳካት ጉዳይ እንዲዘነጋ ወይም ችላ እንዲባል እያደረገው ነው፡፡ በቋንቋው ትምህርት ዓላማ መሰረት ተማሪዎቻቸውን ጥሩ ፀሐፊ፣ ጥሩ አንባቢ፣ ጥሩ ተናጋሪና ጥሩ አድማጭ ስለማድረግ አለማድረጋቸው የሚነሳ ነገር የለም፡፡ ይህም የቁጥጥር፣ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓቱ በትክክለኛው መስመር ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለዚህ ከትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራን ጀምሮ፣ ባለድርሻ አካላት ይህን ጉዳይ ሊያስቡበት/ ሊያጤኑት ይገባል፡፡

ሰባተኛ ወላጆች በልጆቻቸው ተምህርት ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበትንና በመምህሮቻቸው የሚሰጧቸውን ተግባራት እንዲሰሩ እንዲከታተሉ የሚደረገበት መንግድ ቢፈለግ፡፡ በጥናቱ ዐውድ በአብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ትምህርት ቤት የሚውሉት ለግማሽ ቀን ወይም ከአምስት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህ ወላጆች ተማሪዎች ወደፊት በስራ ዓለም ሲሰማሩ በሚገለገሉበት ቋንቋቸውም ሆነ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች የሚኖራቸውን አቅም በትምህርት ገበታ ቆታቸው ከፍ በማድረግ ሂደት ድርሻቸውን በአግባቡ ሊወጡ የሚችሉበት መንገድ ሊፈለግ ይገባዋል፡፡
ስምንተኛ፣ ተማሪዎች መብታቸውን ብቻ ሳይሆን የተማሪነት ግዴታቸውን ዐውቀው በመምህሮቻቸው የሚሰጧቸውን ከፈተና ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ተግባራት/መልመጃዎች ጭምር በአግባቡ መስራት የሚችሉበት መንገድ ቢፈለግ፡፡

ዋቢዎች (References)

ትምህርት ሚኒስቴር:: 1996:: የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት፤ዘጠነኛና አስርኛ ክፍል:: የቋንቋዎች ት/ሥ/ት/ቢድን/ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ኢንስቲቲዩት፤ አዲስ አበባ::

አምሳሉ አክሊሉ:: 1976:: *አጭር የኢትዮጲያ ሥነ-ፅሑፍ ታሪክ* :: አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፣ (ያልታተመ)::

አበባ ሁሴን:: 2000:: *የ10ኛ ክፍል አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በመማር-ማስተማር ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ*:: ባህር ዳር ዩንቨርሲቲ፤ የ፪ኛ ዲግሪ መሚያ፣ ያልታተመ::

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ:: 2002:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መለኪያ (ስታንዳርድ)::ባህር ዳር፤ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ሥራ ሂደት::

የትምህርት እና ስነ-ጥበብ ሚኒስቴር::1940:: *የአንደኛ ደረጃ ሰርዓተ ትምህርት*፣ (ያልታተመ)::

_____ ::1944:: *የሁለተኛ ደረጃ ሰርዓተ ትምህርት*፣ ያልታተመ) ::

_____:: 1950:: *የሁለተኛ ደረጃ ሰርዓተ ትምህርት ለመከራ የወጣ*፣ (ያልታተመ)::

_____::1951:: *የአንደኛ ደረጃ የአጥቢያ ሰርዓተ ትምህርት*፣ (ያልታተመ) ::

_____::1956::*የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ሰርዓተ ትምህርት*፣(ያልታተመ) ::

የኢትዮጲያ የሽግግር መንግስት አጠቃላይ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ:: 1986::አዲስ አበባ፣ (ያልታተመ)::

የኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፕብሊክ ሕገ መንግስት:: 1995:: አዲስ አበባ::

ዮናስ አድማሱ፣ ሀብተማርያም ማርቆስ፣ ዮሀንስ አድማሱና ጎይሉ ፋላስ::1966:: *አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ*:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣(ያልታተመ)::

ዮናስ አድማሱ:: 1999:: *ሥነ-ፅሑፍ በቋንቋ ጥናትና ትምህርት ሊኖረው የሚችለው ሚና/ችግሩ ምንድነው?* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ከገፅ 119-124::

ፈቃደ አዘዘ። 1999።አንዳንድ ነጥቦች ስለሁለተና ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ስነሥርዓተ ትምህርቶች፣ ስለመማሪያ መጻሕፍት አና ስለሥነ - ፅሑፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ከገፅ 102-118።

Abebe Bekele. 1990. *Principles of Curriculum*. Addis Ababa University (Unpulished Teaching Material)

Adane Taye. 1993. *A Historical Survey of state Education in Ethiopia.* Addis Ababa: (unpublished Teching Material).

Aldeson, J. C. 1999. Testing is too important to be Left to Testers. Lancaster Univirsity

Alderson, J. C .2000. *Assessing Reading*. Urited Kingdom: CUP.

_____ .2004. *Foreward.* In L, Cheng, Y. Watanabe, & A. Curtis (Eds.), Washback *in language testing: research contexts and methods*. Mahwah, New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates, Inc. (pp. xix-xxi).

Alderson, J. C. Clapham, C. and Wall, D. 1995. *Language Test Construction and Evaluation.* Great Britain: CUP.

Alderson, J. C. and Hamp-Lyons, L. 1996. *TOEFL preparation courses: a study of washback.* Language Testing, 13(3), 280-297.

Alderson, J.C and Wall, D. 1993. *Does washhack Exist*? Aplied Lngisrics. 14(2) 115-129.

AL-Jamal, D. and Ghadi, N. 2008. *English Language General Secondary Certificate Examination Washback in Jordan.* Asian EFL Journal. 10 /3

Andrews, S., Fullilove, J., & Wong, Y. 2002. *Targeting washback: A case study. System, 30,* 207-223.

Bachman, L.F 1990 *Fundamental Consideration in Language Testing*. Oxford: OUP.

_____ 2002. *Some reflections on task-based language performance. assessment.* Retrieved on Nov, 20, 2010 fromhttp://140.119.186.100/2007 Testing /Bachman2002

Bachman L.F and Cohen, A.D. 1998. *Interfaces between Second Languages Testing Research.* Cambridge: CUP.

Bachman, L.F. and Palmer, A.S.1996. *Language Testing in Practice*. Oxford: OUP.

Balcer, D. 1989. *Language Testing. A crirical survey and praclical guide*. London: Edward Arnold.

Bailey, K. 1999. *Washback in language testing*. TOEFL Monograph Series. MS –15. Princeton: Educational Testing Service.

Bailey, K.M. 1996. *Working for Washback a Review of the Washhack concept in Language Testing*. Language Testing. 13(3),257-279.

Brown,H,D. 2004. *Language Assessmet Principlles and Clasroom Practices*, Longman: California,

_____.2007. *Principles of Language Learing and Teaching*.U.S.A: Longman.

Brown,J.D.1996.*Tesfing in Language Programs*. New Jersey: Prentice Hall Regents.

Brown, J. .D and Hudson T. 2002.*Criteion Referenced Language Testing*. Camridge: CUP.

Canale, M. & Swain, M. 1980. *Theoretical bases to communicative approaches to communicative teaching and testing*. Applied Linguistics, *1*, 1-47

Chen, L, D. 2002. *Taiwanese Junior HighSchool Engilish Teachers` Perceptions of the Washback Effect of the Basic Copetence Tessting in English*. Ohio State University. (Unpublished Ph.D Thesis).

Chen, L. 2002. *Washback of a public exam on English teaching*. (ERIC Document Reproduction Service No. ED472167).

Cheng, L. 1997. *How Does Washback Influence Teaching? Implications for Hong Kong*.. Language and Education 11, 1: 38 – 54.

_____.2000. W*ashback or Backwash: A review of the impact of testing on teaching and learing,* Queen University: Canada.

_____. 2004. *The Washback Effect of a Ppublic Examination Change on Teacher's Perceptions toward their Classroom Teaching*. In L. Cheng, Y. Watanabe, & A. Curtis (Eds.),*Washback in language testing: Research contexts and methods*

_____.2005, *Chenging Language Teaching Through Language Testing: A Washback Study* . Cambrige: CUP.

Cheng, L. Curtis , A.2004. *Washback or Backwash: A review of the impact of testing on teaching and learing*. In L. Cheng, Y. Watanabe,& A. Curtis (Eds.). Washback in language testing: Research contexts and methods.. Malwah, New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates..

Creswell,J. W. 2007. *Research Design: Qualitative, Quantitative, and Mixed Methods Approches*. (3rd. Ed). London: SAGE Publications.

Creswell, J.W. 2014.Research Design. London: SAGE Publications.

Cumming, A and Berwick, R. (Eds).1996. *Validation in Language Testing*. Clevedon: Multilingual Matters LTD. Curriculum Development and Implementation Core-Process (CDCP).

Ministry of Education.2010. *Curriculum Framework for Ethiopian Education* (KG- Grade 12).

Davidson, F. and Lynch, K. 2002. *Testcraft. A Teacher's Guide to Writing and using Language Test Specifications* . London: Yale Universtiy Press.

Davies, A Brawn, A Elder, C. hill,k Lamlex, T. and MCNamara, T. 2002 . *Dictionary of Languagge Testing*. Cambridge: CUP.

Dejene Leta. 1990. *Achievement, Washback and Proficiency in School Leaving Examination: A Case of Innovation in an Ethiopian Setting*. Lancaster University of Lancaster, Department of Linguistics and Modern English Language. (Unpublished Ph.D. Thesis.)

Dereje Negede. 2002. *An Investigation of the Washback Effect of the Ethiopian School Leaving Certificate (ESLEC) English Language Examination*. Addis Ababa: Addis Ababa University. (Unpublished MA Thesis).

Desalegn Chalchisa.2005. *Comparative Study of Students` Achievement in English and Mathematics in Addis Ababa,* Amhara and Oromo Reginal States of Ethiopia: (Unpublished Ph.D. Thesis.)

Dornyei,Zoltan. 2007. *Research methods in Applied LIngustics: Quantitative, Qualitative And Mixed methodologies*. Oxford : OUP.

Douglas, D. 2010. Understanding Language Testing. Hodder Education; UK

Ebel, R.L. 1979. *Essentials of Educational Mesurement*. (3rd edition.) New Jersey: Prentice Hall.

Fournier-Kowaleski,L. 2005. *Depicting Washback in the Intermediate Spanish Language Classroom; A Descriptive Study of Teacher`s Instructional Behavioous AS They Relate to Tests.* Ohio State University. (Unpublished Ph.D Thesis).

Fulcher, G. 2002. *Assessment in English for Academic Purposes: Putting Content Validity in Its Place*. Applied Lingusihic 221-236.

_____ 2010. *Practical Language Testing*. London: Hodder Education.

Fulcher, G and Davidson, F . 2007. *Language Testing and Assessment An Advanced Resource Book* .London: Routledge.

Getachew, A and Derib , A. 2006. *Language policy in Ethiopia: History and Current Trends. Ethiop.* J Educ and Se. 2 (1), 37-61.

Ghorbani, M,R.2008. *The washback effects of the universityEnterance Examinationon on Iranian English Teachers`Curiculum Planing and Instruction.* Iranian EFL Journal.2. 60-75.

Green,A. 2007. *IELTS Washback in Context Preparation for Academic Writing in Higher Education.* Cambrige: CUP.

Grouland, N.E 1986. *Measurement and Evaluation in Teaching.* New York: Macmillan.

Hawkey, R . 2006. *Impact theory and practice: studies of the IELTS test and Progetto Lingue 2000*, Cambridge: Cambridge University Press.

Harison, A. 1983. *A Language Testing Handbook.* London: Macmillan Publishers Ltd.

Hayes, B., & Read, J. (2004). *IELTS test preparation in New Zealand: Preparing students for the IELTS academic module*. In L. Cheng, Y. Watanabe, & A. Curtis (Eds.), Washback in language testing: Research contexts and methods (pp. 97-112). Mahwah, NJ: Lawrence Erlbaum Associates.

Heaton, J.B. 1988. *Writing English language Tests.* Londen : Longman.

Hemming, G. 1987. A Guide to Language Testing . Heinle & Heinle Publishers: Boston.

Herman, J. L., & Golan, S. (1993). *The effects of standardized testing on teaching and schools.* Educational Measurement: Issues and Practice, *12*, 20-25,

Hughes, A. 2003.*Testing for Language Teachers.* Second editon.Cambridge: CUP.

ICDR. 2004. *Minimum Learing Copetencies in Amharic for Grades 9-10.*

Kassa Mihretie .2007. *An Exploration of the Washback Effect of the Ethiopian Higher Education Entrance Certificate Examination (EHEECE) of English Language.* MA Thesis. Addis Ababa : Addis Ababa University.

Kruger, R.A. 1994. *Focus groups.* (2nd ed.). California: Sage Publications, Inc.

Krueger, R. 2002. *Designing and conducting focus group interviews.* University of Minnesota. Retrieved July 10, 2012, from http://www.shadac.umn.edu/img/assets/18528/FocGrp_Krueger._Oct02.pdf.

Larson-Hall, J. (2010. *A Guide to Doing Statistics in Second Language Research Using SPSS.* New York: Rout ledge.

Madson, H .S. 1976. *Language Examination in Ethiopian.* In M.L Bender,. J .D. Bowen, C.A. Cooper, and C.A. Ferguson.(Eds.). *Language in Ethiopia.* Oxford: OUP.

_____. 1983.*Techniques in Language Testing.* Oxford: OUP.

Madaus, G. F. (1988). The influence of testing on the curriculum. In L. Travers (Ed.), *Critical issues in curriculum (87th yearbook of the Society for the Study of Education), Part 1* (pp.83-121). Chicago, IL: Chicago University Press

McNamara, T. 2004. *Language Testing.* In Davies, A. and Elder, C (eds.). *The Handbook of Applied Linguistics.* Australia: Blackwell publishing.

_____. 2000. *Language Testing.* Offord: OUP.

Melkamu Abate. 2007. *The Washback Effect of Grade Ten English Language (EGSEC) Examination.* MA Thesis. Addis Ababa: Addis Ababa University.

Messick, S. 1996. *Validity and Washback in Language Testing.* Language Testing.13(2),241-256.

Miyata-Boody, N, and Langham, C.S. 2000. *Communicative Lnguage Testing_ an Attainable goal ?* The British council, TolyG. Retrived on December 1, 2010, from http:// faculty. Ksu. edu. Salaljarr /Research % 20library /Testing/ 20 References.

Morrow.K. 1979 *Coummunicative Language Testing: Revolution or Evolution*? In C.J Brumfit, and K Johnson. (Eds). The Communicative Approach to Language Teashing. Oxford : OUP.

Muijs,D. 2004.*Doing Quantitative Research in Education.*London: sage Pulications.

Mulu, Nega and Daniel Tefera. 2005. *Introduction to Measurement and Evalution.* Addis Ababa University : Addis Ababa. (Unpublished Materil).

Munzenmaier ,Ms, and Rubin, N. *Perspectives: Bloom`s Taxonomy :What`s Old is New Again.*

Oller, J, 1979. *Language Tests at School.* Londen: Longman.

Qi, L. 2004. *Has a high-stakes test produced the intended changes*?. In L. Cheng, Y. Watanabe & A. Curtis (Eds.), Washback in language testing: research contexts and methods (pp. 147-170). Mahwah,NJ:Lawrence Erlbaum Associates.

Rani,T.S. Priyadrsaini, J. R. and Bhaskara, D.R. 2004. *Educational Measurment and Evalution.* Darya Ganij; Arronk Offeset Press.

Richards, J.C. 1996. *Classroom-Based Evaluation in Second Language Education.* Cambridge: CUP.

Robson, C. 2002. *Real world research.* Oxford: Blackwell.

Sax. G. 1974. *Principles of Educational Measurment and Evalution.*Califonia: Washington Publishing Company.

Schmidt, C. 2004. *The Analysis of Semi-Structured Interviews.* In U. Flick, E. v. Kardorff, & I. Steinke (Eds.), A Companion to Qualitative Research (pp. 253–258). London: Sage.

Shih, C. 2009. *How tests change teaching: A model for reference*. English Teaching: Practice and Critique. *8/2,* 188-206

Shohamy, E .1993. The *Power of Tests: The Impact of Language Tests on Teaching and Learning.* Johons Hopkins University: Washington, D C.

Shohamy, E. Demitsa-Schmidt, S. and Ferman . I. 1996. *Test impact revisted: Washhack Effect over Time*. Language Testing. 13(3), 298-317.

Siddiek, A.G. 2010. *The Impact of Test Content Validity on Language Teaching and Learing.* Asian Social Science. vo l6, No. 12 December.

Simachew, Gashaye. 2012. *Washback of the University Entrance English Exam (UEEE) on Teachers' and Students' Practices: The Case of Preparatory Schoolsin Amhara National Regional State*. Addis Ababa Univerisity: Addis Ababa. (Unpublished Ph.D Thesis).

Spada, N., & Fröhlich, M. 1995. *The Communicative Orientation of Language Teaching Observation Scheme (COLT).* Sydney, Australia: Macquarie University, The National Centre for English Language Teaching and Research (NCELTR).

Spratt,M. 2005, *Washback and the Classroom:The implications for teaching and learing of studies of washback from exams*, Languade Teaching Research _9(1). 5- 29.

Taylor, L. 2005. *Washback and impact.* ELT Journal, 59(2), 154-155.

Taylor ,S. J. and Bogdan. 1998. *Introduction to Qualitative Research Methods*. New York: John Wiley & Sons Inc.

Teshome, Demissie. 1995 . T*he Construction and Validation of a Test in English for Tertiaty Education with Reference to AAU.* (Unpublished Ph.D Thesis).

Tesfaye Shewaye and Taylor, C.V. 1976 *Language Curriculum.* In M.L Bender, J .D. Bowen, C.A. Cooper, and C.A. Ferguson.(Eds.). Language in Ethiopia. Oxford: OUP.

Tilahun Mengesha. 19945. *National Examinations in Ethiopia and South Ausralia : A Comparative Study.* Flinders University of South Ausralia (Unpublished Ph.D Thesis).

Wall, D. 2005. *The impact of high-stakes examinations on classroom teaching: A case study using insights from testing and innovation theory.* Cambridge: Cambridge University Press.

Wall, D. and Alderson, J.C .1993. *Examiing Washback, the Sr Lankan Impact Study.* Language Testing _10(1).

Wall, D., & Alderson, J. C. 1993. Examining washback: the Sri Lankan impact study.*Language Testing*, 10, 41-70.

Watanabe, Y. 1997. *The Washback effects of the Japanese University Entrance Examinations of English-Classroom- based Research..* University of Lancaster. Lancaster. (Unpublished PhD thesis)

Weir, C.1990. *Commuicative Language Testing.* Englllewood Cliffs, NJ: prentice-Hall Regent.

___. 2005. *Language Testing and Validation. An Evidence-based Approch.* New York: Pilgrave Macmillan.

Weir, C.J, A. Hughes and D. Porter. 1990. *Reading Skills: Hierarchies, Imlicational Relationships and Identiiablity.* In Reading in a Foreigh Language, vol 7 Nub1 Autumn.

አባሪ አንድ፤ በሙከራ ጥናትኽ በመምህራን የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

ክፍል ፩ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በመምህራን የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና የክፍል ትምህርት አቀራረብ ላይ የሚፈጥረው ተዕዕኖ /Washback

መመሪያ ፡- ከዚህ በታች የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና የክፍል ትምህርት አቀራረብ ላይ ያለውን **አዎንታዊና አሉታዊ** ተዕዕኖ በሚመለከት ያለዎትን አጠኖት ለማወቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች በዝርዝር ቀርበዋል ፡፡ በመሆኑም በቀረቡት ሃሳቦች ላይ መስማማት አለመስማማትዎን ከበጭራሽ አልስማማም እሰከ በጣም እስማማለሁ የሚሉ አራት አማራጮች መካከል ምርጫዎ ከሆነው ክፍል(አማራጭ) ስር የ/X/ ምልክት በማድረግ ይመልሱ ፡፡

ተ ቁ	ጥያቄዎች	በጭራሽ አልስማማም	አልስማማም	እስማማለሁ	በጣም እስማማለሁ
1	የማጠናቀቂያ ፈተናው የተማሪዎችን የፈተና አሰራር ችሎታ ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትን እንዳከናውን ያነሳሳኛል የሚል ስሜት ይሰማኛል፡፡				
2	ለማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎችን ለማዘጋጀት በሚል ዓላማ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች እንዲዳብሩ የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራትን /መልመጃዎችን አልፎ አልፎ አሰራለሁ				
3	የማጠናቀቂያ ፈተናው መሰጠቱ ቢቋረጥ ወይም የሚያተኩርባቸው ይዘቶች ቢቀየሩ/ አጠያየቁ ምርጫ ብቻ መሆኑ ቢቀር ለየትምህርቱ (ለእያንዳንዱ ክሂል፣ ለሰዋሰውና ለሥነጽሁፍ ክፍሎች) የምመድበው ጊዜ ከበፊቱ የተለየ ይሆናል ፡፡				
4	የክፍል ውስጥ ተግባራትን/መልመጃዎችን የማዘጋጀው /የማሰራው የማጠናቀቂያ ፈተናውን መሰረት በማድረግ ነው ፡፡				
5	በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የበለጠ ሽፋን የሚሰጠው ለሰዋሰውና ለስነጽሑፍ ትምህርት ነው ብዬ ስለማሰብ ተግባቦታዊ (የማዳመጥን፣ የመናገርን፣ የማንበብንና የመፃፍ ...) ክሂሎችን ለማስተማር ከማውለው የበለጠ ጊዜ ለሁለቱ እሰጣለሁ ፡፡				
6	የተወሰኑ ክፍለ ጊዜያትን በተለይም የፈናው ጊዜ እየተቀረበ ሲመጣ የፈተና አሰራር ስልቶችን /ስትራቴጅዎችን ለማስተማሪያነት አውላለሁ ፡፡				
7	አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ውስጥ ትምህርት ተግባራትን የማቅደውና የማዘጋጀው የማጠናቀቂያ ፈተናውን ሳይሆን ሌሎች ምክንያቶችን ለምሳሌ የመማሪያ መጽሐፉን፣ የማስተማር ልምዴን ወይም የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ መሰረት አድርጌ ነው፡፡				
8	የማስተማሪያ ዘዴዎችን የምመርጠው ተማሪዎቹን በማጠናቀቂያ ፈተናው ለስኬት የሚያበቁልኝ መሆናቸውን ግምት ውስጥ አስገብቼ ነው፡፡				
9	ተማሪዎቹን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት የማያስችሉ አንዳንድ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለማስተማሪያነት አልገለገልባቸውም ፡፡				
10	በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚካተቱ ክሂሎችንና የሰዋስውና የስነ-ጽሑፍ ክፍሎችን ለማስተማር የሚረዱኝን የማስተማሪያ ዘዴዎች መርጨ እጠቀማለሁ ፡፡				
11	አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ውስጥ ትምህርት ተግባራትን የማቅደውና የማዘጋጀው የማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያተኩርባቸው ይዘቶች ላይ ተመርኩዤ አይደለም ፡፡				

12	ከመማሪያ መፅሐፉ በተጨማሪ ተማሪዎቹ በማጠናቀቂያ ፈተናው ስኬታማ እንዲሆኑ የሚረዱ ናቸው የምላቸውን አጋዥ መፃሕፍትና ጽሑፎች እጠቀማለሁ ፡፡				
13	ተማሪዎቹ ለማጠናቀቂያ ፈተናው ዝግጁ እንዲሆኑልኝ በማሰብ በፈተናው ሊካተቱ ይችላሉ ከምላቸው ምንጮች(መጽሐፎች...)ጥያቄዎችን እያዘጋጀሁ አለማምዳቸዋለሁ፡፡				
14	ተማሪዎቹ ከማጠናቀቂያ ፈተናው አቀራረብ ጋር እንዲተዋወቁ ለማገዝ ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን እየሰሩ እንዲለማመዱ አደርጋለሁ ፡፡				
15	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛውን የቋንቋ ትምህርት ክፍል (ክሂል፣ ሰዋስው፣ ሥነጽሑፍ) ነው የበለጠ ትኩረት ሰጥቼ ማስተማር ያለብኝ? የሚለውን ለመወሰን ተፅዕኖ ያሳድርብኛል ፡፡				
16	አንዳንድ የመማሪያ መጽሐፉ ክፍሎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ስለማይሸፍኑ ሳስተምር እዘላቸዋለሁ ወይም እንደነገሩ ነካክቼ አልፋቸዋለሁ ፡፡				
17	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎችን ደጋፊ ዕሁፎች /መጽሐፎች መጠቀም እንዳለብኝ ተፅዕኖ ያሳድርብኛል፡፡				
18	በመማሪያ መጽሐፉ የተካተቱትን ይዘቶችና ተግባሮችን በሙሉ በትምህርት ዓመቱ ለቋንቋው ትምህርት በተመደበው ክፍለ ጊዜ ለመሸፈን እንኳ አስቸጋሪ ቢሆንም ጊዜውን አብቃቅቼ ለማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያግዙ ሌሎች መፃሕፍትን በአጋዥነት እጠቀማለሁ ፡፡				
19	በማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረት የሚሰጠው ለአራቱ የቋንቋው ክሂሎች ንዑሳን ክሂሎች ነው፣ የሰዋስውና የስነጽሑፍ ትምህርቶች ችላ የተባሉ ናቸው፡፡				
20	ቋንቋውን ሳስተምር በማጠናቀቂያ ፈተናው የመካተት አጋጣሚያቸው ክፍተኛ ነው ብዬ በማስባቸው የመማሪያ መጽሐፉ ክፍሎች ላይ አተኩራለሁ፡፡				
21	የማጠናቀቂያ ፈተናው ጥያቄዎች በአብዛኛው የአጠቃላይ □ኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መፅሐፎች ውስጥ የተካተቱ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የመጻፍና የማንበብ ክሂሎችና የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ይዘቶችና ተግባሮች በተመጣጠነ ደረጃ የተወከሉባቸው ናቸው፡፡				
22	ምንም እንኳ አንዳንድ ርዕሰ ጉዳዮች /የትምህርቱ ይዘቶች በማጠናቀቂያ ፈተናው ላይጠየቁ እንደሚችሉ ባውቅም ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ በቂ ስለሆነ በመማሪያ መጽሀፉ የተካቱትን ሁሉ እሸፍናለሁ፡፡				
23	የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርቱ ይዘቶች ምርጫ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡				
24	የተማሪዎችን የቤትና የክፍል ስራ እንዲሁም ፈተናዎች ለመገምገም የምጠቀምባቸው መስፈርቶች ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት የሚያግዙ ናቸው፡፡				
25	ለተማሪዎቹ ሙከራ(quiz)፣ ቴስትና ፈተና ሳዘጋጅ ጥያቄዎቹ ባለፉት ዓመታት በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ውስጥ ከተነሱ ጉዳዮች ጋር የሚዛመዱ እንዲሆኑልኝ ጥረት አደርጋለሁ፡፡				
26	አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቹን የምገመግመው የምርጫ ጥያቄዎችን ሳይሆን እንደ ጻፉ (□ረፍተነገር፣ አንቀጽ፣ ድርሰት፣ ዘገባ...)፣ግለጹ፣ አብራሩ፣ ተንትኑ፣ አስረዱ...የሚሉ አጠያየቆችን በመጠቀም ነው፡፡				
27	በክፍል ፈተናዎች የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክሂል እፈትናለሁ፡፡				
28	በክፍል ፈተናዎች የተማሪዎቹን የንግግር ክሂል እፈትናለሁ፡፡				
29	በማዘጋጃቸው የክፍል ፈተናዎች ውስጥ ተማሪዎቹ ልዩ ልዩ ድርሰቶችን (አንቀጽ፣ ዘገባ፣ ደብዳቤ፣ ድርሰት...) በተግባር እንዲፅፉ በማድረግ የመፃፍ ክሂልን እመዝናለሁ፡፡				
30	በማዘጋጃቸው የክፍል ፈተናዎች ውስጥ የተማሪዎቹን የተለያዩ ንዑሳን አንብቦ የመረዳት ክሂሎች(ሀቅን ከግል አስተየየት፣ ምክንያትን ከውጤት፣ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን				

	መለየትን ፣ እንድምታ፣ ማጠቃለል፣መደምደም...)ለመግመገም የሚያስችሉ ክንውኖችን አላካትትም፡፡				
31	ተማሪዎቼን የምመዝንበትን ስልት በአብዛኛው ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ይመሳሰላል፡፡				
32	ተማሪዎች የቤትና የክፍል ስራዎቻቸውን እርስ በርስ የመገማገም ልምድ አላዳበሩም፡፡				

ክፍል ፪ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራኑ ላይ በሚፈጥረው ተፅዕኖ ላዳበሩት ግንዛቤ፣ በምክንያትነት ሊታዩ ከሚችሉ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች

መመሪያ ፡- ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አራት አማራጮች መካከል ተገቢ የሚሉትን በመምረጥ ይመልሱ፡፡

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	በጭራሽ	አልስማ	እስማማለ	በጣም
33	ተማሪዎቼ ወደዱትም ጠሉትም ጠቃሚ ነው ብዬ የማስበውን ሁሉ አስተምራለሁ፡፡				
34	ተማሪዎቼ መማር የማይፈልጓቸውን በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ያሉ ይዘቶች ለማስተማር የማውለው ጊዜ አነስተኛ ነው፡፡				
35	በተማሪዎች ፍላጐት መሰረት አብዛኛውን ጊዜ የማስተምረው በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚካተቱን የትምህርቱ ክፍሎች ነው፡፡				
36	የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ (Attitudes) በማስተማር ተግባሬ ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡				
37	ተማሪዎቼ የክፍል ትምህርቱ ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ተዛማጅነት ያለው እንዲሆን ይፈልጋሉ፡፡				
38	ብዙውን ጊዜ ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው ጥሩ ውጤት ያመጣሉ ብዬ እጠብቃለሁ፡፡				
39	ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው በሌላ መምህር ከተማሩ ሌሎች ተማሪዎች ያነሰ ውጤት ቢያመጡ ቅር ይለኛል፡፡				
40	ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው ስኬታማ ባይሆኑ /ጥሩ ውጤት ባያመጡ መስራት የነበረብኝን ተግባር ያልሰራሁ /guilty/ ሆኖ ይሰማኛል፡፡				
41	የተማሪዎቼ የፈተና ውጤቶች ሰዎች በእኔ ላይ ለሚኖራቸው አመለካከት(አዎንታዊ ወይም አሉታዊ) ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡				
42	የማጠናቀቂያ ፈተናው እንዴት ማስተማር እንዳለብኝ ጠቃሚ ግብረ - መልስ (feedback) ወይም መረጃ ይሰጠኛል፡፡				
43	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎቹን ክሂሎችና የሰዋሰውና የስነጽሑፍ ትምህርቶች ትኩረት ሰጥቼ ማስተማር እንዳለብኝ ጠቃሚ ግብረ- መልስ ይሰጠኛል፡፡				
44	የተማሪዎችን የፈተና ውጤት ለማሻሻል በቋንቋ መምህራን ዘንድ ፉክክር ስለሌለ ተጨማሪ ነገሮችን ለመስራት ጥረት አላደርግም፡፡				
45	የተማሪዎቼን ፈተና ውጤት እንዳሻሽል ከተማሪዎቼ ወላጆች/ ቤተሰቦች ጫና የሚደረግብኝ መስሎ ይሰማኛል፡፡				
46	የትምህርት ቤታችን ርዕሳነ-መምህራን /አስተዳዳሪዎች የተማሪዎችን የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት ከመማር አንጻር ስለሚያወዳድሩ፣ የራሴን ተማሪዎች የፈተና ውጤት እንዳሻሽል ተጽዕኖ የሚያሳድርብኝ ይመስለኛል፡፡				

47	የማስተምረው ተማሪዎቼ የቋንቋ ዕውቀትና ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ነው፡ በማጠቃለያ ፈተናው የተሻለ ውጤት ማምጣት አለማምጣታቸው አያሳስበኝም፡፡				
48	የማጠናቀቂያ ፈተናው በምን በምን የትምህርቱ ክፍሎች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግና የአጠያቅ ስልቱ እንዴት እንደሆነ የማውቀው ነገር ባለመኖሩ በፈተናው ምክንያት በማስተማር ሂደቱ ላይ ለውጥ ለማምጣት ብዬ የማደርገው የተለየ ጥረት የለም፡፡				
49	ማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎቹ የትምህርቱ ክፍሎች ላይ ትኩረት እንደሚያደረግ አውቃለሁ				
50	የማጠናቀቂያ ፈተናውን ደረጃ የምረዳው በተማሪዎች የወደፊት የስራ ዕድል ላይ ጫና ፈጣሪ እንደሆነ አድርጌ ነው ፡፡				
51	ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያስመዘግቡት ውጤት ለአብዛኛዎቹ መምህራን የመምህርነት ብቃት ጠቃሚ የማረጋገጫ መንገድ ነው ብየ አምናለሁ ፡፡				
52	ለአብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያገኙት ውጤት ጠቃሚ ማበረታቻ ነው ፡፡				
53	ተማሪዎች በአማርኛ የማጠናቀቂያ ፈተና የሚያመጡት ውጤት ወደ መሰናዶ ትምህርት ለማለፍ ተፅዕኖ እንዳለው/ የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት እረዳለሁ ፡፡				
54	የማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎች ስለቀሰሙት የቋንቋ ዕውቀት (ሰዋስው፣ቃላት...) የሚሰጠው ግብረ- መልስ በጣም አነስተኛ ነው፡፡				
55	የማጠናቀቂያ ፈተናው የተማሪዎቼን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ብቃት ለመመዘን /ለመለካት የሚያስችል ነው ብየ አምናለሁ ፡፡				
56	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትምህርት ቤታችንን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት በአብዛኛው ቀይሮታል ብዬ አምናለሁ ፡፡				
57	የግል ባህሪዬ (ሰብዕናዬ) በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀቴና በክፍልትምህርት አቀራረቤ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል የሚል እምነት አለኝ፡፡				
58	ቋንቋውን ለማስተማር የተመደበው ጊዜ በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀቴና በክፍል ትምህርት አቀራረቤ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል ፡፡				

ክፍል ፫ የመምህራንን የማስተማር ባህርያት/የማስተማር ተግባር(Behaviors) በተመለከተ

መመሪያ አንድ፡- እባክዎ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ተገቢ ነው የሚሉትን መልስ በያዘው አማራጭ ትይዩ ባለው ሳጥን ውስጥ የ 'X' ምልክት በማድረግ ይመልሱ፡፡

1. የትምህርቱን አደረጃጀት የሚወስነው ማነው?

ሀ. ርዕሰ መምህሩ ☐ ሐ. የአማርኛ መምህራን በጋራ ☐

ለ. የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ ☐ መ. እርስዎ ራስዎ ☐

2. በትምህርት ቤታችሁ የምታስተምሩትን ትምህርት ቅደም ተከተል የምታሲዙት /የምታደራጁት እንደት ነው?

ሀ. በመማሪያ መጽሐፉ መሰረት ☐

ለ.በትምህርት ቤቱ አሰራር መሰረት ☐

ሐ. በቋንቋው ክሂሎች መሰረት ለምሳሌ የንባባ፣የማዳመጥ...እያሉ በተናጠል በማደራጀት ☐

መ. በቋንቋው ትምህርት ተግባሮች/መልመጃዎች መሰረት ☐

ሠ. ማጠናቀቂያ ፈተናው ለየትምህርቶቹ በሚሰጠው ትኩረት መሰረት ☐

መመሪያ ሁለት፡- እባክዎ '1. በጭራሽ 2. አልፎ አልፎ 3.. ብዙ ጊዜ 4. ሁልጊዜ ' የሚሉትን ሰሌሎች በመጠቀም ለሚከተሉት ጉዳዮች ተገቢ የሚሉትን ደረጃ ይስጡ፡፡

3	ሀር የትምህርት ዕቅድ ሲያዘጋጁ ለሚከተሉት ጉዳዮች ምን ያህል ትኩረት ይሰጣሉ?	በጭራሽ	አልፎ አልፎ	ብዙጊዜ	ሁልጊዜ
3.1	ለማስተማር ዘዴዎች				
3.2	ለትምህርት ይዘቶች				
3.3	በትምህርቱ ሂደት ለሚከናወኑ ተግባራት/መልመጃዎች				
3.4	ለቋንቋ ክሂሎች(ለማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍ)				
35	ለአጋዥ ማቴሪያሎች(ጽሁፎች እና/መጻሕፍት				
3.6	የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሳሳት				
3.7	ለተማሪዎች የቤት ስራ ለመስጠት				
4	**ሲያስተምሩ የሚከተሉትን ድርጊቶች በክፍል ውስጥ ምን ያህል ይፈጽሟቸዋል?**				
4.1	ለክፍሉ ተማሪ መናገር (talk to the Whole /Class)				
4.2	ለየቡድኑ መናገር (talk to groups)				
4.3	ለእያንዳንዱ ተማሪ መናገር (talk to individuals)				
4.4	አለመናገር /ዝም ማለት (Keep Silent)				
5	**የሚከተሉትን ተግባራት በክፍል ውስጥ ምን ያህል ያከናውኗቸዋል?**				
5.1	የየዕለቱን ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች መናገር				
5.2	ተማሪዎች እያንዳንዱን ትምህርት/ተግባር እንዴት መስራት እንዳለባቸው ማሳየት				
5.3	የምንባቦችን ይዘት ማብራራት				
5.4	የመማሪያ መጽሀፉን መልመጃዎች ማብራራት				
5.5	የቤት ስራዎችን አሰራር ማብራራት				
5.6	ያለፉ ዓመታትን የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ወደ ክፍል እያመጡ ማሰራትና ፈተና እንዴት እንደሚሰራ ማብራራት				
5.7	የቡድን ስራዎችን እየሰጡ ማሰራት ወይም ውይይቶችን ማደረጀት				
5.8	የቋንቋ ክሂሎችን አዋህዶ/አቀናጅቶ ማስተማር				

ክፍል ፬ አጠቃላይ መረጃ

መመሪያ ፡- ከተራ ቁጥር 1 — 9 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ከእርሰዎ ዳራ (Background) ጋር የሚስማማውን አማራጭ የያዘው ክፍል ሳጥን ውስጥ X *ምልክት በማድረግ ይመልሱ ፡፡*

1. ፆታ 1 ሴት ☐ 2 ወንድ ☐
2. በዚህ ዓመት እያስተማሩ ያሉት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን ነው?
   1 አዎ ☐ 2 አይደለም ☐
3. ካለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ (የያዝነውን ዓመት ጨምሮ) የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን ስንት ዓመት አስተምረዋል ?
   1 አንድ ☐ 2 ሁለት ☐ 3 ሶስት ☐ 4 አራት ☐ 5 አምስት ☐
4. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ያለዎትን የትምህርት ደረጃ የሚያመለክተው ክፍል ላይ የተለመደውን የ 'X' ምልክት ያስቀምጡ፡፡
   1 የመጀመሪያ ዲግሪ (ቢ.ኤ) በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ (በአማርኛ) ☐
   2 የመጀመሪያ ዲግሪ አማርኛን በማስተማር (ቢ.ኢ.ዲ.) ☐
   3 ሁለተኛ ዲግሪ .አማርኛን በማስተማር ኤም ኤ ☐
5. ጠቅላላ የማስተማር ልምድዎ ስንት ዓመት ነው? ☐ ዓመት አስተምሬአለሁ፡፡
6. በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያለዎት የማስተማር ልምድ (የያዝነውን ዓመት ጨምሮ) ስንት ዓመት ነው ? ☐ ዓመት አስተምሬአለሁ፡፡
7. በአንድ ክፍል የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ብዛት በአማካኝ ስንት ነው?
   1 ከ30-40 ☐ 2 41-50 ☐ 3 51-60 ☐ 4 ከ60 በላይ ☐
8. ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ (የያዝነውን ዓመት ጨምሮ) ስንት የስራ ላይ ስልጠና /ትምህርት አግኝተዋል?

   1. ከሁለት በታች ☐ 2. ከ3-5 ☐ 3. ከ6-10 ☐ 4. ከ10 በላይ ☐

9. እባክዎ በየዓመቱ ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ስለሚዘጋጀው የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ያለዎትን አስተያየት (ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን ጨምሮ) ይግለጹልኝ፡፡

አባሪ ሁለት፡- በመከራ ጥናት ፩ የተካሄደ የቡድን ተኮር ውይይት መምሪያ

1. የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርት አስተቃቀዳችሁ ላይ የሚያደርሰውን /የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በሚመለከት ያላችሁን ግንዛቤ ብትገልጹልኝ?

2. በትምህርት አስተቃቀዳችሁና በክፍል ትምህርት አቀራረባችሁ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ምክንያቶች /ምንጮች /Factors/ አሉ የሚል ግንዛቤ አላችሁ? እንዴት?
3. የግል ባህሪያችሁ /ሰብዕናችሁ በትምህርት አስተቃቀዳችሁና የክፍል ትምህርት አቀራረባችሁ ላይ ስለሚያደርሰው ተፅዕኖ (ያላችሁ ግንዛቤ ምንድን ነው?

4. በትምህርት አስተቃቀዳችሁና በክፍል ትምህርት አቀራርባችሁ ላይ የምታስተምሩበት ዐውድ የሚኖረውን ተፅዕኖ በተመለከተ ያላችሁ ግንዛቤ ምንድን ነው?

5. ፈተናውና እንድታስተምሩ በሚጠበቅባችሁ ትምህርት መካከል ተገቢ ዝምድና አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?

አባሪ ሦስት: በመ/ራ ጥናት ፪ በመምህራን የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

በአዲስ አበባ ዩንቪርስቲ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የዶክትሪት ዲግሪ ትምህርት የጥናት ፕሮጀክት

የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና በቋንቋው መምህራን የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና የክፍል ትምህርት አቀራረብ ሂደት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለማጥናት የአማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ መጠይቅ

ውድ መምህራን!

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ ከዚህ በኋላ ***የማጠናቀቂያ ፈተና(ው)*** በመባል የሚገለጸው **የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና** በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀታችሁና በክፍል ትምህርት አቀራረባችሁ ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖና መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ ለሚካሄደው ጥናት ጠቃሚ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ጥናቱም የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ ረገድ ከፍ ያለ ድርሻ እንዳለው በሚታመንበት ውጫዊ(ሀገር አቀፍ) ፈተና አዘገጃጀትና የማጠቃለያ ፈተናው **የአማርኛ ቋንቋን** በመማር ማስተማር ሂደት ላይ እየፈጠረ ያለውን ተጽዕኖ/ወሽባክ በተመለከተ ጠቃሚ ግብአት ለማግኘት ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

መጠይቁ አራት ክፍሎች አሉት፡ የመጀመሪያው የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና በክፍል ትምህርት አቀራረባችሁ ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ ሁለተኛው ክፍል በፈተናዎቹ የሚፈጠሩ ተጽዕኖዎችን ምንጮች (መነሻዎች/ ምክንያቶች (factors) የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበውበታል፡፡ ሶስተኛው የመምህራን የማስተማር ባህርያት የሚመለከቱ ጥያቄዎች የቀረቡበት ነው፡፡ አራተኛው ክፍል ደግሞ ከግለ-ባህሪያችሁና ከትምህርት ቤቶቻችሁ ዐውድ/ባህርያት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች የቀረቡበት ነው፡፡

ውድ መምህራን!

ጥናቱ ወደ ታለመለት ዓላማ የሚደርሰው እናንተ በምትሰጡት እውነተኛና ትክክለኛ መረጃ ነው፡፡ በመሆኑም ለሁሉም ጥያቄዎች የተሟላ መልስ በመስጠት ትተባበሩኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

የሚሰበሰው መረጃም ከታለመው ጥናትና ምርምር ውጭ ለሌላ ዓላማ እንደማይውል ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

ለሚደረግልኝ ትብብር ሁሉ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

(በዚህ መጠይቅ ክሂል(ክሂሎች) የሚለው የሚወክለው ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍ በመባል የሚታወቁትን የቋንቋው ክሂሎች መሆኑን ማስታወስ እወዳለሁ፡፡)

ክፍል አንድ፡- የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በመምህራን የማስተማር ቅድመ ዝግጅት(የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት) ና የክፍል ትምህርት አቀራረብ ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ /Washback ላይ የመምህራን ግንዛቤ

መመሪያ አንድ **፡- እባክዎ ከተግባር/ጊዜ አመዳደብ፣ ከሚያስተምሩበት ዘዴ፣ ለማስተማር ከሚጠቀሙባቸው ማቴሪያሎች፣ ሲያስተምሩ ከሚሸፍኑባቸው የትምህርት ይዘቶች ጥልቀት (Depth) እና የክፍል ትምህርት ምዘና አንጻር ያለዎትን የስምምነት ደረጃ በተመለከተ ግንዛቤዎን (Perceptions) ከዐረፍተ ነገሮቹ/ ጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ከቀረቡልዎት አምስት ምድቦች መካከል ይበልጥ በሚስማሙበት አማራጭ ስር ይህን ‹‹√›› ምልክት በማስቀመጥ ይመልሱ፡፡**

ቁጥሮቹ የሚወክሉት የሚከተለውን ነው፤

1. **ጭራሽ አልስማማም፤** 2. **አልስማም፤** 3. **ለመወሰን እቸገራለሁ ፤**
4. **እስማማለሁ ፤** 5. **በጣም እስማማለሁ፤**

ተቁ	ተግባሮች / ጥያቄዎች	1	2	3	4	5
1	የማጠናቀቂያ ፈተናው የተማሪዎችን የፈተና አሰራር ችሎታ ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትን እንዳከናውን ያነሳሳኛል የሚል እምነት አለኝ፡፡					
2	ለማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎችን ለማዘጋጀት አራቱንም የቋንቋው ክሂሎች በመርሀ ትምህርቶቹ በተሰጣቸው ትኩረት መሰረት የተለያዩ ተግባራትን በማሰራት አስተምራለሁ ፡፡					
3	የማጠናቀቂያ ፈተናው መሰጠቱ ቢቋረጥ ወይም የሚያተኩርባቸው ይዘቶች ቢቀየሩ/ አጠያየቁ ምርጫ ብቻ መሆኑ ቢቀር ለየትምህርቱ (ለእያንዳንዱ ክሂል፣ ለሰዋሰውና ለሥነጽሁፍ ክፍሎች) የምመድበው ጊዜ ከበፊቱ የተለየ ይሆናል ፡፡					
4	የክፍል ውስጥ ተግባራትን/መልመጃዎችን ሳዘጋጅና ተማሪዎቼን ሳሰራ የማጠናቀቂያ ፈተናውን መሰረት አደርጋለሁ ፡፡					
5	በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የበለጠ ሽፋን የሚሰጠው ለሰዋሰውና ለስነጽሑፍ ትምህርት ነው ብዬ ስለማሰብ ተግባቦታዊ (የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ...) ክሂሎችን ለማስተማር ከማውለው የበለጠ ጊዜ ለሁለቱ እሰጣለሁ ፡፡					
6	የተወሰኑ ክፍለ ጊዜያትን በተለይም የፈተናው ጊዜ እየቀረበ ሲመጣ የፈተና አሰራር ስልቶችን /ስትራቴጅዎችን ለማስተማሪያነት አውላለሁ ፡፡					
7	አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ውስጥ ትምህርት ተግባራትን የማቅደውና የማዘጋጀው የማጠናቀቂያ ፈተናውን ሳይሆን ሌሎች ምክንያቶችን ለምሳሌ የመማሪያ መጽሐፉን ፣ የማስተማር ልምዴን ወይም የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ መሰረት አድርጌ ነው፡፡					
	የማስተማሪያ ዘዴዎችን የምመርጠው ተማሪዎቼን በማጠናቀቂያ ፈተናው ለስኬት የሚያበቁልኝ መሆናቸውን ግምት ውስጥ አስገብቼ ነው፡፡					

9	ተማሪዎቼን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት የማያስችሉ አንዳንድ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለማስተማሪያነት አልገለገልባቸውም ።						
10	ከመማሪያ መፅሐፉ ቡተጨማሪ ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው ስኬታማ እንዲሆኑ የሚረዱ ናቸው የምላቸውን አጋዥ መፃሕፍትና ጽሑፎች እጠቀማለሁ ።						
11	ተማሪዎቼ ለማጠናቀቂያ ፈተናው ዝግጁ እንዲሆኑልኝ በማሰብ በፈተናው ሊካተቱ ይችላሉ ከምላቸው ምንጮች(መጽሐፎች...) ጥያቄዎችን እያዘጋጀሁ አለማምዳቸዋለሁ ።						
12	ተማሪዎቼ ከማጠናቀቂያ ፈተናው አቀራረብ ጋር እንዲተዋወቁ ለማገዝ ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን እየሰሩ እንዲለማመዱ አደርጋለሁ ።						
13	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛውን የቋንቋ ትምህርት ክፍል (ክሂል፣ ሰዋስው፣ ሥነጽሑፍ) ነው የበለጠ ትኩረት ሰጥቼ ማስተማር ያለብኝ? የሚለውን ለመወሰን ተዕዕኖ ያሳድርብኛል።						
14	አንዳንድ የመማሪያ መጽሐፉ ክፍሎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ስለማይሸፍኑ ሳስተምር እዘላቸዋለሁ ወይም እንደነገሩ ነካክቼ አልፋቸዋለሁ ።						
15	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎችን ደጋፊ ዕሁፎች /መጽሐፎች መጠቀም እንዳለብኝ ተዕዕኖ ያሳድርብኛል።						
16	በመማሪያ መጽሐፉ የተካተቱትን ይዘቶችና ተግባሮችን በሙሉ በትምህርት ዓመቱ ለቋንቋው ትምህርት በተመደበው ክፍለ ጊዜ ለመሸፈን እንኳ አስቸጋሪ ቢሆንም ጊዜውን አብቃቅቼ ለማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያግዙ ሌሎች መፃሕፍትን በአጋዥነት እጠቀማለሁ።						
17	በማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረት የሚሰጠው ለአራቱ የቋንቋው ክሂሎች ነው፤ የሰዋስውና የስነጽሑፍ ትምህርቶች ችላ የተባሉ ናቸው።						
18	ቋንቋውን ሳስተምር በማጠናቀቂያ ፈተናው የመካተት አጋጣሚያቸው ክፍተኛ ነው ብዬ በማስባቸው የመማሪያ መጽሐፉ ክፍሎች ላይ አተኩራለሁ።						
19	የማጠናቀቂያ ፈተናው ጥያቄዎች በአብዛኛው የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መፅሐፎች ውስጥ የተካተቱ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የመጻፍና የማንበብ ክሂሎችና የሰዋስውና የሥነ-ጽሑፍ ይዘቶችና ተግባሮች በተመጣጠነ ደረጃ የተወከሉባቸው ናቸው።						
20	ምንም እንኳ አንዳንድ ርዕሰ ጉዳዮች /ይዘቶች በማጠናቀቂያ ፈተናው ላይጠየቁ እንደሚችሉ ባውቅም ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ በቂ ስለሆነ በመማሪያ መጽሀፉ የተካቱትን ሁሉ እሸፍናለሁ።						
21	የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርቱ ይዘቶች ምርጫ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።						
22	የተማሪዎችን የቤትና የክፍል ስራ እንዲሁም ፈተናዎች ለመገምገም የምጠቀምባቸው መስፈርቶች ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት የሚያግዙ ናቸው።						
23	ለተማሪዎቼ ሙከራ(quiz)፣ ቴስትና ፈተና ሳዘጋጅ ጥያቄዎቼ ባለፉት ዓመታት በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ውስጥ ከተነሱ ጉዳዮች ጋር የሚዛመዱ እንዲሆኑልኝ ጥረት አደርጋለሁ።						
24	አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቼን የምገመግመው በምርጫ ሳይሆን እንደ ጻፉ (□ረፍተነገር፣ አንቀጽ፣ ድርሰት፣ ዘገባ...)፣ግለጹ፣ አብራሩ፣ ተንትኑ፣ አስረዱ...የሚሉ አጠያየቆችን በመጠቀም ነው።						
25	በክፍል ፈተናዎች የተማሪዎቼን የማዳመጥ ክሂል እፈትናለሁ።						
26	በክፍል ፈተናዎች የተማሪዎቼን የንግግር ክሂል እፈትናለሁ።						
27	በማዘጋጃቸው የክፍል ፈተናዎች ውስጥ ተማሪዎቼ ልዩ ልዩ ድርሰቶችን(አንቀጽ፣ ዘገባ፣ ደብዳቤ፣ ድርሰት...) በተግባር እንዲፅፉ በማድረግ የመፃፍ ክሂልን እመዝናለሁ።						
28	በማዘጋጃቸው የክፍል ፈተናዎች ውስጥ የተማሪዎቼን የተለያዩ ንዑሳን አንብቦ የመረዳት ክሂሎች(ሀቅን ከግል አስተየየት፣ ምክንያትን ከውጤት፣ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን መለየትን ፣ እንድምታ፣ ማጠቃለል፣መደምደም...)ለመገምገም የሚያስችሉ ክንውኖችን አላካትትም።						
29	ተማሪዎቼን የምመዝንበት ስልት በአብዛኛው ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ይመሳሰላል።						

መመሪያ ሁለት፡- የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የትምህርት አስተቃቀድና የክፍል ትምህርት አቀራረብ ላይ በሚፈጥረው ተፅዕኖ ላዳበሩት ግንዛቤ፣ ምክንያት(Factors) ሊሆኑ ከሚችሉ ተላውጠዎች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ እባክዎ ከፊት ለፊታቸው ከቀረቡት አምስት ምድቦች ውስጥ በምትስማሙበት አማራጭ ስር የ ‹‹✓›› ምልክት በማስቀመጥ ይመልሱ፡፡

ቁጥሮቹ የሚወክሉት የሚከተለውን ነው፤

1. ጭራሽ አልስማማም፤ 2. አልስማም፤ 3. ለመወሰን እቸገራለሁ
4. እስማማለሁ፤ 5. በጣም እስማማለሁ፤

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	1	2	3	4	5
30	ተማሪዎቹ ወደዱትም ጠሉትም ጠቃሚ ነው ብዬ የማስበውን ሁሉ አስተምራለሁ፡፡					
31	ተማሪዎቹ መማር የማይፈልጓቸውን በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ያሉ ይዘቶች ለማስተማር የማውለው ጊዜ አነስተኛ ነው፡፡					
32	በተማሪዎች ፍላጐት መሰረት አብዛኛውን ጊዜ የማስተምረው በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚካተቱን ክፍሎች ነው፡፡					
33	የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ (Attitudes) በማስተማር ተግባሬ ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡					
34	ተማሪዎቹ የክፍል ትምህርቱ ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ተዛማጅነት ያለው እንዲሆን ይፈልጋሉ፡፡					
35	ብዙውን ጊዜ ተማሪዎቹ በማጠናቀቂያ ፈተናው ጥሩ ውጤት ያመጣሉ ብዬ እጠብቃለሁ፡፡					
36	ተማሪዎቹ በማጠናቀቂያ ፈተናው በሌላ መምህር ከተማሩ ሌሎች ተማሪዎች ያነሰ ውጤት ቢያመጡ ቅር ይለኛል፡፡					
37	ተማሪዎቹ በማጠናቀቂያ ፈተናው ስኬታማ ባይሆኑ /ጥሩ ውጤት ባያመጡ መስራት የነበረብኝን ተግባር ያልሰራሁ /guilty/ ሆኖ ይሰማኛል፡፡					
38	የተማሪዎቹ የፈተና ውጤቶች ሰዎች በእኔ ላይ ለሚኖራቸው አመለካከት(አዎንታዊ ወይም አሉታዊ) ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡					
39	የማጠናቀቂያ ፈተናው እንዴት ማስተማር እንዳለብኝ ጠቃሚ ግብረ - መልስ (feedback) ወይም መረጃ ይሰጠኛል፡፡					
40	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎቹን ክሂሎችና የሰዋሰውና የስነጽሑፍ ትምህርቶች ትኩረት ሰጥቼ ማስተማር እንዳለብኝ ጠቃሚ ግብረ- መልስ ይሰጠኛል፡፡					

41	የተማሪዎችን የፈተና ውጤት ለማሻሻል በቋንቋ መምህራን ዘንድ ፉክክር ስለሌለ ተጨማሪ ነገሮችን ለመስራት ጥረት አላደርግም፡፡					
42	የተማሪዎቼን ፈተና ውጤት እንዳሻሽል ከተማሪዎቼ ወላጆች/ ቤተሰቦች ጫና የሚደረግብኝ መስሎ ይሰማኛል፡፡					
43	የትምህርት ቤታችን ርዕሳነ-መምህራን /አስተዳዳሪዎች የተማሪዎችን የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት ከመማር አንጻር ስለሚያወዳድሩ፣ የራሴን ተማሪዎች የፈተና ውጤት እንዳሻሽል ተጽዕኖ የሚያሳድርብኝ ይመስለኛል፡፡					
44	ማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎቹ የትምህርቱ ክፍሎች ላይ ትኩረት እንደሚያደረግ አውቃለሁ					
45	የማስተምረው ተማሪዎቼ የቋንቋ ዕውቀትና ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ነው፤ በማጠቃለያ ፈተናው የተሻለ ውጤት ማምጣት አለማምጣታቸው አያሳስበኝም፡፡					
46	የማጠናቀቂያ ፈተናው በምን በምን የትምህርቱ ክፍሎች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ስለማላውቅ በፈተናው ምክንያት በማስተማር ሂደቱ ላይ ለውጥ ለማምጣት ብዬ የማደርገው የተለየ ጥረት የለም፡፡					
47	የማጠናቀቂያ ፈተናውን ደረጃ የምረዳው በተማሪዎች የወደፊት የስራ ዕድል ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንደሆነ አድርጌ ነው ፡፡					
48	ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያስመዘግቡት ውጤት ለአብዛኛዎቹ መምህራን የመምህርነት ብቃት ጠቃሚ የማረጋገጫ መንገድ ነው ብየ አምናለሁ ፡፡					
49	ለአብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያገኙት ውጤት ጠቃሚ ማበረታቻ ነው ፡፡					
50	ተማሪዎች በአማርኛ የማጠናቀቂያ ፈተና የሚያመጡት ውጤት ወደ መሰናዶ ትምህርት ለማለፍ ተፅዕኖ እንዳለው/ የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት እረዳለሁ ፡፡					
51	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትምህርት ቤታችንን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት በአብዛኛው ቀይሮታል ብዬ አምናለሁ ፡፡					
52	የግል ባህሪዬ (ሰብዕናዬ) በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀቴና በክፍልትምህርት አቀራረቤ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል የሚል እምነት አለኝ፡፡					
53	ቋንቋውን ለማስተማር የተመደበው ጊዜ በማስተማር ቅድመ ዝግጅት (በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀቴ)ና በክፍል ትምህርት አቀራረቤ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል ፡፡					

ክፍል ሁለት፡- የመምህራንን የማስተማር ባህርያት/የማስተማር ተግባር(Behaviors) በተመለከተ

መመሪያ አንድ፡- እባክዎ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ተገቢ ነው የሚሉትን መልስ በያዘው አማራጭ ትይዩ ባለው ሳጥን ውስጥ ይህን ‹‹√›› ምልክት በማድረግ ይመልሱ፡፡

1. የትምህርቱን ይዘት አደረጃጀት የሚወስነው ማነው?
   - ሀ. ርዕሰ መምህሩ ☐
   - ሐ. የአማርኛ በጋራ መምህራን ☐
   - ለ. የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ ☐
   - መ. እርስዎ ራስዎ ☐
2. በትምህርት ቤታችሁ የምታስተምሩትን ትምህርት ቅደም ተከተል የምታሲዙት /የምታደራጁት እንዴት ነው?
   - ሀ. በመማሪያ መጽሐፉ መሰረት ☐
   - ለ. በትምህርት ቤቱ አሰራር መሰረት ☐
   - ሐ. በቋንቋው ክሂሎች መሰረት ለምሳሌ የንባባ፣የማዳመጥ...እያሉ በተናጠል በማደራጀት ☐
   - መ. በቋንቋው ትምህርት ተግባሮች/መልመጃዎች መሰረት ☐
   - ሠ. ማጠናቀቂያ ፈተናው ለየትምህርቶቹ በሚሰጠው ትኩረት መሰረት ☐

መመሪያ ሁለት፡- እባክዎ ‘1. በጭራሽ 2. አልፎ አልፎ 3.. ብዙ ጊዜ 4. በጣም ብዙ ጊዜ ‘ ከሚሉት ሰኬሎች መካከል ይበልጥ በሚስማሙበት አማራጭ ስር ይህን ‹‹√›› ምልክት ያድርጉ ፡፡

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	1	2	3	4
3	**የትምህርት ዕቅድ ሲያዘጋጁ ለሚከተሉት ጉዳዮች ምን ያህል ትኩረት ይሰጣሉ?**				
3.1	ለማስተማር ዘዴዎች				
3.2	ለትምህርት ይዘቶች				
3.3	በትምህርቱ ሂደት ለሚከናወኑ ተግባራት/መልመጃዎች				
3.4	ለቋንቋ ክሂሎች(ለማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍ)				
3.5	ለአጋዥ ማቴሪያሎች(ጽሁፎች እና/መጻሕፍት				
3.6	የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሳሳት				
3.7	ለተማሪዎች የቤት ስራ ለመስጠት				
4	**ሲያስተምሩ የሚከተሉትን ድርጊቶች በክፍል ውስጥ ምን ያህል ይፈጽሟቸዋል?**				
4.1	ለክፍሉ ተማሪ መናገር (talk to the Whole /Class)				
.2	ለየቡድኑ መናገር (talk to groups)				
.3	ለእያንዳንዱ ተማሪ መናገር (talk to individuals)				
.4	አለመናገር /ዝም ማለት (Keep Silent)				
	የሚከተሉትን ተግባራት በክፍል ውስጥ ምን ያህል ያከናውኗቸዋል?				
.1	የየዕለቱን ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች መናገር				
.2	ተማሪዎች እያንዳንዱን ትምህርት/ተግባር እንዴት መስራት እንዳለባቸው ማሳየት				
.3	የምንባቦችን ይዘት ማብራራት				
.4	የመማሪያ መጽሀፉን መልመጃዎች ማብራራት				
5	የቤት ስራዎችን አሰራር ማብራራት				
6	ያለፉ ዓመታትን የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ወደ ክፍል እያመጡ ማሰራትና ፈተና እንዴት እንደሚሰራ ማብራራት				
7	የቡድን ስራዎችን እየሰጡ ማሰራት ወይም ውይይቶችን ማደረጀት				
8	የቋንቋ ክሂሎችን አዋህዶ/አቀናጅቶ ማስተማር				

ክፍል አራት፡- ዳራዊ መረጃ

መመሪያ አንድ፡- ከተራ ቁጥር 1 — 4 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ከእርሰዎ ዳራ (Background) ጋር የሚስማማውን አማራጭ የያዘው ክፍል ሳጥን ውስጥ ይህን ‹‹√›› ምልክት በማድረግ ይመልሱ ፡፡

1. ፆታ 1 ሴት ☐ 2 ወንድ ☐
2. ካለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ (የያዝነውን ዓመት ጨምሮ)

ሀ. የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ስንት ዓመት አስተምረዋል ?

1 አንድ ☐ 2 ሁለት ☐ 3 ሶስት ☐ 4 አራት ☐ 5 አምስት ☐

ለ. የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን ስንት ዓመት አስተምረዋል ?

1 አንድ ☐ 2 ሁለት ☐ 3 ሶስት ☐ 4 አራት ☐ 5 አምስት ☐

3. ያለዎት የትምህርት ደረጃ ፡-

1 የመጀመሪያ ዲግሪ (ቢ.ኤ) በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ (በአማርኛ) ☐

2 የመጀመሪያ ዲግሪ አማርኛን በማስተማር (ቢ.ኢ.ዲ.)☐

3 ሁለተኛ ዲግሪ አማርኛን በማስተማር ኤም ኤ ☐

መመሪያ ሁለት፡- እባክዎ የሚከተሉት ጥያቄች ደግሞ መልስዎትን በክፍት ቦታዎች ላይ በመጻፍ ይመልሱልን፡፡

4. በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያለዎት የማስተማር ልምድ (የያዝነውን ዓመት ጨምሮ) ስንት ዓመት ነው ? _____ ዓመት አስተምሬአለሁ፡፡
5. በአንድ ክፍል የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ብዛት በአማካኝ ስንት ነው? _____
6. ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ ከቋንቋ ማስተማር ፈተና አወጣጥ/ አዘገጃጀት ጋር ግንኙነት ያላቸው ስንት የስራ ላይ ስልጠና /ትምህርት አግኝተዋል ? _____
7. በመደበኛ የዩኒቨርስቲ ትምህርትዎ የቋንቋ ፈተናን(ምዘናን) የሚመለከት ኮርስ ወስደዋል? _____
8. ተማሪዎችዎን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት ከመማሪያ መፅሀፉ ውጭ የሚጠቀሙባቸው ሌሎች አጋዥ መሳሪያዎች (ማጣቀሻ መጽሐፎችና ሌሎች ማቴሪያሎች) ካሉ ይዘርዝሪቸው፡፡
9. እባክዎ በየዓመቱ ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ስለሚዘጋጀው የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ያለዎትን አስተያየት (ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን፣ ወደፊት እንዴት ባለ ሁኔታ ሊዘጋጅ እንደሚገባው የሚሰጡትን ምክር...) ይግለጹልኝ፡፡

አባሪ አራት፤ በመከራ ጥናት፤ በተማሪዎች የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

በተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና በቋንቋው መማርና ማስተማር ሂደት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ያላቸው ግንዛቤ (perceptions)

ውድ ተማሪዎች!
የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ አማርኛ ፈተናን ከመማር ማስተማሩ ጋር አዛምዶ ለማጥናት ለታሰበ ምርምር መረጃ ማሰባሰብ ነው።።
(በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥና የ10ኛ ክፍል ትምህርታችሁን ስታጠናቅቁ በምትፈተኑት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና ላይ ምን አይነት ግንዛቤ (perceptions) እንዳላችሁ ለማጥናት ይህ መጠይቅ ተዘጋጅቷል።።)
ለጥናቱም ስኬት የእናንተ እውነተኛና ትክክለኛ ምላሽ ወሳኝ በመሆኑ ሁሉንም ጥያቄዎች በትክክል በመመለስ እንደትተባበሩ በአክብሮት ትጠየቃላችሁ።። በመጠይቁ የምትሰጡት ማንኛውም መረጃ ከምርምሩ ስራ ውጭ ለሌላ ተግባር አይውልም፤ በመጠይቁ ስም አይፃፍም።።
ጊዜ ሰጥታችሁ መጠይቁን በጥንቃቄ በመመላት ስለተባበራችሁኝ፣ በጣም አመሰግናለሁ።።

ክፍል አንድ፡ ዳራዊ መረጃ

ትክክለኛ መልስ ከያዘው ሳጥን ውስጥ የ‹‹√›› ምልክት አስቀምጡ፡

1. ፆታ 1. ወንድ ☐ 2. ሴት ☐
2. ዕድሜ 1. ከ14-18 ☐ 2. ከ19-22 ☐ 3. ከ 22 በላይ ☐
3. የወላጆችህ/ሽ የቤተሰቦችህ/ሽ ዋነኛ መተዳደሪያ ምንድነው?
   1. ግብርና ☐ 2. የመንግስት ስራ ☐ 3. ንግድ ☐ 4. ሌላ ☐
4. አማርኛ ቋንቋ ስትማሩ፣ መምህራችሁ ፣ የ10ኛ ክፍልን የአማርኛ ሀገር አቀፍ የማጠናቀቂያ ፈተና በተመለከተ ምን ያህል ጊዜ ያነሳሉ?
   1. ምንም ጊዜ አያነሱም ☐ 2. አልፎ አልፎ ☐
   3. አንዳንድ ጊዜ ☐ 4. በአብዛኛው ክፍለ ጊዜ ☐ 5. በየክፍለ ጊዜው ☐
5. ያለፉ ዓመታት የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ከክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ መስራት ምን ያህል ጊዜ ታውላላችሁ?
   1. ምንም ጊዜ አላውልም ☐ 2. አልፎ አልፎ ☐
   3. አንዳንድ ጊዜ ☐ 4. ብዙ ጊዜ ☐ 5. ሁልጊዜ ☐

ክፍል ሁለት፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብቡና ከፊት ለፊታቸው ከቀረቡት አራት ምድቦች /አማራጮች ውስጥ በምትስማሙበት አማራጭ ስር የ ‹‹✓›› ምልክት በማስቀመጥ መልሱ፡፡ ቁጥሮቹ የሚወክሉት የሚከተለውን ነው፤

1. በጭራሽ ፤ 2. አልፎ አልፎ ፤ 3. ብዙ ጊዜ ፤ 4. በጣም ብዙ ጊዜ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	1	2	3	4
7	**የአማርኛ መምህራችሁ የሚከተሉትን ምን ያህል ጊዜ ያከናውናሉ?**				
7.1	ለአጠቃላይ የክፍሉ ተማሪዎች መናገር (talk to the whole class)				
.7.2	በቡድን ለተቀመጡ ተማሪዎች መናገር (talk to groups of students)				
7.3	ለእያንዳንዱ ተማሪ በተናጠል መናገር (talk to individual students)				
7.4	ምንም ሳይናገሩ ተማሪዎች የሚናገሩትን (የሚሰሩትን) መከታተል				
7.5	የቤት ወይም የክፍል ስራዎችን ማረም				
7.6	ከክፍል ውጭ ያረሙትን ድርሰት/ ሌላ የቤት ስራ ለተማሪዎች መመለስ				
8	**በአማርኛ ክፍለ ጊዜ መምህራችሁ የሚከተሉትን ተግባራት (activities) ምን ያህል ተግባራዊ ያደርጋሉ?**				
8.1	የትምህርቱን ዓላማ /ዓላማዎች ለተማሪዎች መንገር/ማስተዋወቅ፡፡				
8/2	የምንባቡን ይዘት ማብራራት				
8.3	የተለየ ቋንቋ ነክ ጉዳይ ሲያጋጥም (ለምሳሌ የቃላት ወይም የዐረፍተነገሮች አወቃቀር) ማብራራት				
8.4	የመማሪያ መጽሐፉን መልመጃዎች አሰራር ማብራራት				
8.5	ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን አሰራር ማብራራት				
8.6	የቡድን ሰራ ወይም ውይይት ማደራጀት				
8/7	የቋንቋ ክሂሎች በቅንጅት የምንማርባቸውን ተግባራት ማደራጀት				
8/9	በተማሪዎች ፅሁፍ (ዐ.ነገር፣ አንቀፅ፣ ድርሰት...) የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ነጥብ በነጥብ ማብራራት				
9	**በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚከተሉትን የቋንቋ ክሂሎችና የሰዋሰውና የሥነ-ፅሁፍ ክፍሎች ምን ያህል ትማራላችሁ /ታከናውናላችሁ?**				
9.1	***1. የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን በተመለከተ***				
9.1.1	በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ጭውውቶችን ማካሄድ፣				
9.1.2	በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ውይይቶችን ማካሄድ፣				
9.1.3	አካባቢያዊ፣ ወቅታዊና አገራዊ ጉዳዮች ላይ በቂ መረጃዎችን ከልዩ ልዩ ምንጮች አሰባስቦ ክርክር ማካሄድ፣				
9.1.4	በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች መልዕክትን ግልፅ የሚያደርጉ የድምፅና የአካል እንቅስቃሴዎችን... በመጠቀም የዳብዳ ንግግር ማድረግ፣				
9.1.5	በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዝግጅት በማድረግና መልዕክትን ግልፅ የሚያደርጉ የድምፅ እና የአካል እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር ማድረግ፣				
9.2	***የንባብ ክሂልን (የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችን) በሚመለከት***				
9.2.1	በፅሁፍ የቀረቡ ሀሳቦችን ሀቅና የግል አስተያየት እያሉ መለየት፣				
	በፅሁፍ የቀረቡ ሀሳቦችን መንስኤ(ምክንያት) እና ውጤት እያሉ መለየት፣				
9.2.2	በሚነበብ ፅሁፍ ዋና ዋናና ጠቃሚ ዝርዝር ሀሳቦች መለየት፣				
9.2.3	በሚነበቡ ፅሁፎች ውስጥ ለሚገኙ አዳዲስ ቃላት፣ በአገባባቸው መሰረት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን መስጠት፣				

9.2.4 9.2.5	በዳሰሳ ንባብ(Scanning) በፅሁፍ ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር መረጃዎችን መፈለግ፣				
	በግርፍ ንባብ (Skimming) የአንድን ፅሁፍ አጠቃላይ ሀሳብ መረዳት፣				
9.2.6	መተንበይ ማለትም ቀጣይ ሀሳብን /ይዘትን ከንባብ በፊትና በንባብ ጊዜ መገመት				
9.2..7	ከልዩ ልዩ መግለጫዎች (ከስዕል፣ ከሰንጠረዥ...) መረጃዎችን ማግኘት፣				
9.2.8	ነባር ዕውቀትን ከሚነበበው ጋር ማስተሳሰር፣				
9.2.9	በአንድ ፅሁፍ ውስጥ በግልፅና በውስጠ ታዋቂነት የቀረቡ ሀሳቦችን መረዳት፣				
9.2.10	እንድምታ ንባብ፤ ማለትም በግልፅ ያልሰፈሩ ሀሳቦችንና መረጃዎችን መረዳት፣				
9.2.11	ከጽሑፉ ሀሳብና ከግል ልምድ በመነሳት ድምዳሜ ላይ መድረስ፣				
9.2.1.2	ማጠቃለያ / በፅሁፉ ዋና ዋና ሀሳቦች ላይ በመመርኮዝ ማጠቃለል፣				
9.2.13	ያነበቡትን ፅሁፍ አስተዋፅኦ አሚልቶ ማቅረብ፣				
9.3	***የመፃፍ ክሂልን በተመለከተ***				
9.3.1	ስርዓተ ነጥቦችን (በፅሁፍ ውስጥ) በተገቢ ቦታቸው ማስገባት/መጠቀም				
9.3.2	ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን በመገልገልና የአንቀጽ አጻጻፍ መርህን በመከተል የተለያዩ (ተራኪ፣ አወዳዳሪ፣ ገላጭ ...) አንቀፆችን መፃፍ				
9.3.3	የተለያዩ የስራና ንግድ ነክ ደብዳቤዎችን መፃፍ ፣				
9.3.4	በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ዘገባ መፃፍ ፣				
9.3.5	ማርቀቅ.፣ ረቂቁን ማረም ፣መከለስና የድርሰቱን ዋና ፅሁፍ መፃፍ ፣				
9.3.6	ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ተገልግሎ መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ ያላቸው የተለያዩ (ተራኪ፣ ስዕላዊ፣ ገላጭና አመዛዛኝ) ድርሰቶች መፃፍ፣				
9.3.7	የአንድን ፅሑፍ ወይም ንግግር መልዕክት ሳያዛቡ አሳጥሮና አስፋፍቶ በራስ አባባል መፃፍ፣				
9.3.8	ግለ ታሪክ መፃፍ (የራስን ወይም የሌላን ሰው)፣				
9.3.10	ከተለያዩ ንግግሮችና ፅሑፎች የሚገኙ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ፣				
9.3.11	ቃለ ጉባኤ መያዝ / መጻፍ(በስብሰባዎች)፣				
9.4	***የሰዋሰው ዕውቀትን ለማጎልበት ከሚረዱ መሰረታዊ ሀሳቦች ጋር መተዋወቅ***				
9.4.1	የቋንቋ ምንነትን፣ አጀማመርንና ባህሪያትን መግለጽ ፣				
9.4.2	ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን (ቅጥያዎችን) ማውጣት፣				
9.4.3	የሚጠብቁና የሚላሉ ድምፆችን መለየት፣				
9.4.4	የቃላት ቅርፅን በመደብ፣ በፆታና በቁጥር መለየት፣				
9.4.5	ገላጮች (የስምና የግስ) መለየት፣				
9.4.6	የአማርኛ ቃላት ክፍሎችን (ስም፣ ቅጽል፣ ግስ...) መለየት፣				
9.4.7	የሀረግ አይነቶችን (ቅፅላዊ፣ ስማዊ፣ መስተዋድዳዊ፣ ተውሳከ ግሳዊ፣ ግሳዊ) መለየት፣				
9.4.8	ተራና ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን መለየትና መጻፍ፣				
9.4.9	በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ ያሉ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጎችን መለየትና ተግባራቸውን መግለፅ፣				
9.4.10	ለቃላትና ሀረጎች ተመሳሳይና ተቃራኒያቸውን መስጠት፣				
9.5	***ሀሳብን ስነ-ፅሁፋዊ በሆነ መልክ የመግለፅ ችሎታን በተመለከተ***				
9.5.1	የፈጠራ ስነ-ፅሁፍ ዘርፎችን (ስነ-ቃል፣ ግጥም፣ ልቦለድ፣ ድራማ) መለየት፣				
9.5.2	የሥነ-ቃል አይነቶችንና ባህሪያትን መለየት				
9.5.3	በምሳሌያዊ ንግግሮች የሚቀርቡ አስተያየቶችንና ልምዶችን መረዳትና የራስን ንግግርና ፅሁፍ በምሳሌያዊ ንግግሮች አጉልቶ ማቅረብ፣				
9.5.4	በአካባቢያችሁ የሚነገሩ የፍቅርና የስራ ቃል ግጥሞች አሰባስቦ ማቅረብ፣				

9.5.5	የግጥም ባህርያትን መግለፅ፣				
9.5.6	የግጥም ስልቶችን ከምጣኔና ከምት አንፃር መለየት፣				
9.5.7	ግጥምን ወደዝርው ፅሁፍ መለወጥ፣				
9.5.8	ግጥሞችን ከይዘትና ከቅርጽ አንጻር መገምገም፣				
9.5.9	ግጥም መግጠም/መጻፍ፣				
9.5.10	የፊሊጣዊ ንግግሮችን መልዕክት መረዳት፣				
9.5.11	በተለያዩ ዘይቤዎች (በአነፃፃሪ፣ ተለዋጭ፣ ሰውኛ፣ ተምሳሌት፣ ግነት...) የቀረቡ አባባሎችን/ሀሳቦችን መረዳትና ማብራራት፣				
9.5.12	የተለያዩ ዘይቤዎችን በመጠቀም ሀሳብን በንግግርና በፅሁፍ አጉልቶ ማቅረብ፣				
9.5.13	የልቦለድ አይነቶችን፣ አላባውያንና ቴክኒኮችን መለየት፣				
9..5.14	ረጅምና አጭር ልቦለዶችንና ድራማዎችን በማንበብ ባህሪያቸውን መግለፅ፣				
8.5.15	የኢትዮጵያን ታዋቂና ቀዳሚ የስነ-ፅሁፍ ሰዎችና ስራዎቻቸውን መለየት፣				
10	**በአማርኛ ክፍለ ጊዜያት የሚከተሉትን ተግባራት ምን ያህል ታከናውናላችሁ?**				
10.1	የጥንድ ስራ መስራት፣				
10.2	የቡድን ውይይት ማካሄድ፣				
10.3	የራስን ሀሳብ በቃል ወይም በፅሑፍ መግለፅ ፣				
10.4	ጥያቄ መጠየቅ፣				
10.5	ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን መስራት፣				
11	**ለአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ዝግጅት፣ የሚከተሉትን ክሂሎችና የፅውቀት ዘርፎች ለማዳበር ምን ያህል ልምምድ ታደርጋላችሁ?**				
11.1	ማንበብ				
11.2	መፃፍ				
11.3	መናገር				
11.4	ማዳመጥ				
11.5	ሰዋሰው				
11.6	ሥነ-ፅሁፍ				
12	**የሚከተሉትን ተግባራት ከክፍል ውጭ ምን ያህል ታከናውናላችሁ?**				
12.1	ራዲዮ ማዳመጥ				
12.2	. ቴሌቪዥን መመልከት				
12.3	ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ማንበብ				
12.4	ለ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና የሚያግዙ አጋዥ መጽሐፎችን ማንበብ				
12.5	ያለፉ ዓመታት ፈተና ወረቀቶችን ለብቻና ከጓደኛ ጋር መስራት				

ክፍል 3፡ የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች በያዙት ሀሳብ መስማማት/ አለመስማማታችሁን ከቀረቡላችሁ አምስት ምድቦች (1. ጭራሽ አልስማማም 2. አልስማማም 3. ለመወሰን እቸገራለሁ 4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ) መካከል ከምትስማሙበት አማራጭ ስር የ ‹‹✓›› ምልክት አስቀምጡ፡፡

ተ.ቁ	ጥያቄ	1	2	3	4	5
13	**የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ስታወዳድሩት እንዴት አገኛችሁት?**					
13.1	ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ይልቅ ሀይወታዊ ነው (ዘገባ፣ ደብዳቤ፣ ቃለጉባኤ፣... አጻጻፍን አዳምጦና አንብቦ መረዳት፣ ሀሳብን አሳክቶ መግለፅን የምንማርበት ነው) ፡፡					
13.2	የቋንቋው ትምህርት ተግባሮችን /መልመጃዎችን ሳቢ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡					
13.3	አያሌ የጥንድ ስራዎችንና የቡድን ውይይቶች የምናካሂድበት ትምህርት ነው፡፡					
13.4	ከመምህራችንና ከክፍል ጓደኞቻችን ጋር ለመግባባት የተሻለ እድል የምናገኝበት ነው፡፡					
13.5	ትምህርታችንን ጨርሰን፣ በሥራ ዓለም ስንሰማራ ልናከናውናቸው ከምንችላቸው ተግባራት ጋር የሚዛመድ ነው፡፡					
14	**አማርኛ ቋንቋ የምትማሩበትን ምክንያት በሚመለከት ቀጥሎ በቀረቡት ሀሳቦች ምን ያህል ትስማማላችሁ?**					
14.1	ስለቋንቋ መሰረታዊ ባህርያትና የአወቃቀር ስርዓት ለመማር					
14.2	ከትምህርት በኃላ የተሻለ ስራ ለማግኘትና በስራ ቦታ (ሪፖርት ፣ ቃለጉባኤ፣ የስራ ደብዳቤ በመፃፍ፣ በማዳመጥና በመናገር... ክሂሎች) ውጤታማ ሆኖ ለመገኘት					
14.3	በማህበራዊ ህይወት ንቁ ተሳታፊ ለመሆን፣					
14.4	ወደ መሰናዶ ትምህርት ለማለፍ፣					
14.5	ፈተና ለማለፍ					
14.6	የትምህርት ቤቱን፣ የቤተሰብንና የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት፣					
14.7	የአማርኛ ፊልሞችን፣ ድራማዎችን እንዲሁም የተለያዩ የሬዲዮና የቴሌቪዥን መርሀ ግብሮችን የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣					
15	**ቋንቋ ለመማር የምትመርጧቸው ስልቶች /ስትራቴጅዎች የትኞቹ ናቸው?**					
15.1	በአማርኛ የተፃፉ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ማንበብ					
15.2	በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፉ የተለያዩ የራዲዮ መርሀ ግብሮችን መከታተል					
15.3	በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፉ የቴሌቪዥን መርሀ ግብሮችን መመልከት					
15.4	በክፍል የቡድን ስራዎች ሲሰጡ በንቃት መሳተፍ					
15.5	በክፍል ውስጥ ሀሳብን ለክፍሉ መግለፅ					
15.6	መልመጃዎችንና ሌሎች የቤት ስራዎችን በወቅቱ መስራት					
15.7	በትምህርት ቤቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ክበባት (ድራማ፣ ክርክር...) መሳተፍ					
15.8	. ለሰዋሰው ትምህርት የተለየ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል፣					
15.9	የመማርያ መጽሐፉን በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ይዞ መገኘት					
16	**በሚከተሉት አስተሳሰቦች ምን ያህል ትስማማላችሁ?**					
16.1	ተማሪዎች ፈተና ይጠላሉ፣					
16.2	የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን በመስራት ይሻሻላል፣					
16.3	ፈተና መፈተን(መውሰድ) በጣም ጠቃሚ የመማር ልምድ (የመማሪያ ስልት) ነው፣					
16.4	የፈተናዎች መኖር ተማሪዎች ጠንክረው እንዲያጠኑ ያደርጋል፣					
16.5	ፈተናዎች ተማሪዎች ስለራሳቸው በሚኖራቸው ግንዛቤ (self -image) ላይ ጠቃሚ አስተዋፅኦ አላቸው፣					
16.6	በፈተና የሚገኝ ውጤት ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆን ለመደሰት ወይም ለመከፋት ምክንያት ይሆናል፡፡					

አባሪ አምስት፤

ለፈተናዎች ኤጀንሲ ሀላፊዎች የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ

የተሳታፊው ስም_____

ቃለመጠይቁ የተካሄደበት ቀን _____

ቃለ መጠይቁ የተጀመረበት ሰዓት_____

ቃለመጠይቁ የተካሄደበት ቦታ_____

ያበቃበት ሰዓት _____

መግቢያ ትውውቅ ፣ ፈቃደኛ ስለመሆናቸው ማመስገን(በቃለ መጠይቁ ለመሳተፍ በመመስማመዎት በቅድሚያ በጣም አመሰግናለሁ!

የጥናቱ ዓላማ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና በቋንቋው ትምህርት አሰጣጥ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለማጥናት ነው፡፡ ለዚህም እርስዎ የሚሰጡኝ መረጃ በጣም ያስፈልገኛል፡፡በውይይታችን የምንለዋወጣቸው ሀሳቦች ምስጢራዊነት የተጠበቀና ለዚህ ጥናት ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

ጥያቄዎች (Questions)

1. በየዓመቱ ፈተና አዘጋጅ/አውጭ ባለሙያዎች በየትምህርት አይነቱ እንዲመረጡ የሚደረገው እንዴት ነው?
   የመምረጫ መስፈርቶች የሚዘጋጁት በማን ነው በድርጅቱ በየትምርት ክፍሎቹ በጥምርት በፈተናዎች ኤጅንሲ በሀገር አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎች በየትምህርት ዐይነቶቹ የሚዘጋጁበት(ባቸው) ምክንያት(ቶች) ምንድነው /ምንድን ናቸው? (የፈተናዎቹ ዓላማ(ዎች)
2. በኤጀንሲው የሚዘጋጁ ፈተናዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንዲኖራቸው ነው የሚጠበቀው /;የሚታለመው?
3. ስርዓተ ትምህርቶቹ(በመርሀ ትምህርቶቹ የተካተቱት ዓላማዎችና ይዘቶች) እና የፈተናዎቹ ጥያቄዎች እንዲጣጣሙ /እንዲዛመዱ (overlap እንዲያደርጉ) የሚደረጉ ጥረቶች ካሉ ቢገልጹልኝ?
4. በየትምህርት አይነቶቹ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች በመማር ማስተማሩ ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት ወይም አዎንታዊና አሉታዊነት የሚታወቁባቸው /የሚረጋገጡባቸው መንገዶች ካሉ ቢያስረዱኝ?
   ለምሳሌ በጉዳዩ ላይ በየጊዜው የሚካሄዱ ጥናቶች አሉ? ወይስ ሌላ ግብረ- መልስ የሚገኝባው ስልቶች ተቀይሰዋል?
6 የቋንቋ ትምህርት መሰረታዊ ትኩረት ክሂሎች ናቸው ፤በተማሪዎች አቅም ረገደም ገልቶ እየታየ ያለው ችግር ይኸው ነው ፤ ለዚህ ችግር መባባስ በምክንያትነት ከሚጠቀሱ ጉዳዮች

የማጠናቀቂያ ፈተናዎች አጠያየቅ ምርጫ ብቻ በመሆኑና እንደ ቀድሞው በሌላ አጠያየቅ ስልት ስለማይፈተኑ ነው በዚህ ረገድ የፈተናዎችን ደረጃ ከፍ ለማድረግና የአጠያየቅ ዘዴውን ምርጫ ብቻ ከመሆን እንዲወጣ (በጽሑፍ የሚመለሱ ጥያቄች የተካተቱበት እንዲሆን) እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ካሉ ቢያስረዱኝ?

7 የፈተናውን ደረጃ ከፍ ለማድረግና የአጠያየቅ ዘዴው ምርጫ ብቻ ከመሆን እንዲወጣ (በጽሑፍ የሚመለሱ ጥያቄች የተካተቱበት እንዲሆን) እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ካሉ ቢያስረዱኝ?

8. ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ በኤጀንሲው የሚዘጋጁ ፈተናዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚያሳድሯቸውን ተጽዕኖዎች አዎንታዊነት ከፍ ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶችና በጥረቶቹ በተግባር የታዩ መሻሻሎች ካሉ ቢገልጹልኝ?

ቆስቋሽ ጥያቄች በፈተና ጥያቄዎች አዘጋጆች አመራረጥና ስልጠና፣

በጥያቄዎች አወጣጥ (Item Writing) ፣
የፈተናዎችን አስተማማኝነት(Reliabilty) አግባብነት (Vailidity) በማሳደግ ረገድ፣

9. የቋንቋ ፈተናዎች አዘገጃጀት የተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርስ በኤጀንሲው የሚደረግላቸውን ድጋፍ ፣ክትትልና ቁጥጥር ቢያስረዱኝ

10. ማጠቃለያና መደምደሚያ

1. እስካሁን ከተነጋገርንባቸው የተለየ /ተጨማሪ ሀሣብ ይኖራችኋል?
2. ተጨማሪ /ሌላ አስተያየት ካላችሁ?

11.ስንብት (አድናቆት) /appreciating/

በኤጀንሲው የሚዘጋጀው ፈተና በቋንቋው ትምህርት አሰጣጥ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በተመለከተ ስላከፈሉኝ ሀሳብ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ወደፊት በአካልና በስልክ ከዚሁ ከፈተናው ጋር በተገናኙ ጉዳዮች እንደገና እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ

እጅግ በጣም አመሰግናለሁ!

አባሪ ስድስት፤ ለፈተናዎች ኤጀንሲ የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች የተዘጋጀ ቃለመጠይቅ

ለፈተናዎች ኤጀንሲ በአማርኛው ክፍል የሰሩና እየሰሩ ላሉ ባለሙያዎችና ፈተና አዘጋጆች የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ

የተሳታፊው ስም_____ቃለመጠይቁ የተካሄደበት ቀን _____ ቃለ መጠይቁ የተጀመረበት ሰዓት_____ ቃለመጠይቁ የተካሄደበት ቦታ_____

ያበቃበት ሰዓት _____

መግቢያ ትውውቅ ፣ ፈቃደኛ ስለመሆናቸው ማመስገን(በቃለ መጠይቁ ለመሳተፍ በመመስማመዎት በቅድሚያ በጣም አመሰግናለሁ!

የጥናቱ ዓላማ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና በቋንቋው ትምህርት አሰጣጥ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለማጥናት ነው፡፡ ለዚህም እርስዎ የሚሰጡኝ መረጃ በጣም ያስፈልገኛል፡፡በውይይታችን የምንለዋወጣቸው ሀሳቦች ምስጢራዊነት የተጠበቀና ለዚህ ጥናት ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

ጥያቄዎች (Questions)

1. የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የሚያካትታቸውን ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ቢዘረዝሩልኝ?
2. እነዚህን የዘረዘሩልኝ ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች በፈተናው በመሸፈንና በመወከል ረገድ ከሚሰጣቸው ክብደት /ትኩረት አንጻር እባክዎ በቅደም ተከተላቸው መሰረት ይግለጹልኝ፡፡ **ቆስቋሽ ጥያቄዎች፤-**

   በመሸፈን 1ኛ 2ኛ...

   /ባለ መሸፈን፣

   የተሻለ ትኩረት /ውክልና በማግኘት፣ ዝቅተኛ ትኩረት በማግኘት

   ተመጣጣኝ ውክልና በማግኘት...
3. በማጠናቀቂያ ፈተናው ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ለሥነ-ልሳናው ዕውቀት (ለሰዋስውና ቃላት) ነው? ወይስ ለአጠቃቀም (ለማዳመጥ፣ ለመናገር፣ ለማንበብና ለመጻፍ ክሂሎች) ነው? ወይስ ከዚህ የተለየ ገጽታ ያለው ነው? ለምን?
4. የማጠናቀቂያ ፈተናው ሲዘጋጅ የሚከተለው የትኛውን የቋንቋ ትምህርትና ፈተና ዝግጅት አተያይ ነው?

   ቆስቋሽ ጥያቄ ከመዋቀራዊያንና ከባህርያዊያን የሚመነጨውን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት; ወይስ ከማህበራዊ ሥነ-ልሳንና ከስነ-ልቦናዊ ስነ-ልሳን የሚመነጨውን ተግባቦታዊ ቋንቋ ማስተማርና መፈተን አተያይ?

   ወይስ ከነዚህ የተለየ የሚከተለው ሌላ አተያይ አለው? ለምን?
5. በየዓመቱ የሚዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ የማጠናቀቂያ ፈተና ቋንቋውን በማስተማርና መማር ሂደቱ ላይ (የክፍል ፈተናዎችን አዘገጃጀት ጨምሮ) ምን ዐይነት ተጽዕኖ እንዲኖረው ነው የሚጠበቀው(የሚታለመው) ? (ስነ-ልሳንና ስነጽሑፍ ላይ ፣ እንዲያተኩር ወይስ ክሂሎች ላይ? እንዴት? (Intended Washback)

6. ስርዓተ ትምህርቱ(በመርሀ ትምህርቱ የተካተቱት ዓላማዎችና ይዘቶች) እና የፈተናው ጥያቄዎች እንዲጣጣሙ /እንዲዛመዱ (overlap እንዲያደርጉ) የሚደረጉ ጥረቶች ካሉ ቢገልጹልኝ?
7. ፈተናዎቹ በነማን ነው የሚዘጋጁት አዘጋጆችን ለመምረጥ የምትጠቀሙባቸውን መስፈርቶች ሊገልጹልኝ ይችላሉ? ለአዘጋጆች የሚሰጥ የተለየ ስልጠና አለ? አዘጋጆቹ ይቀያየራሉ? ወይስ ቋሚ ናቸው ? ለምን ?
8. ጥያቄ አውጭዎች(Item Writters) የሚጠቀሙበት ልየታ(Specifications) ምን ምን ይዘቶችና ጉዳዮች የተካተቱበት ነው? ምክንያቱ ምንድነው ?
9. ፈተናው የሚሰጥበት /ዓላማ /የሚሰጥባቸው ዓላማዎች ምንድነው/ ምድንናቸው? ችሎታ /ብቃት... ለመመዘን...
10. የማጠናቀቂያ ፈተናው በመማር ማስተማሩ ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት ወይም አዎንታዊና አሉታዊነት የሚታወቁባቸው /የሚረጋገጡባቸው መንገዶች ካሉ ቢያስረዱኝ?
ለምሳሌ በጉዳዩ ላይ በየጊዜው የሚካሄዱ ጥናቶች አሉ? ወይስ ሌላ የተቀየሱ ግብረ-መልስ የሚገኝባው ስልቶች አሉ?
11. ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ በኤጀንሲው የሚዘጋጁ ፈተናዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚያሳድሯቸውን ተጽዕኖዎች አዎንታዊነት ከፍ ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶችና በጥረቶቹ በተግባር የታዩ መሻሻሎች ካሉ ቢገልጹልኝ?
ቆስቋሽ ጥያቄች በፈተና ጥያቄዎች አዘጋጆች አመራረጥና ስልጠና፣
በጥያቄዎች አወጣጥ (Item Writing) ፣
የፈተናዎችን አስተማማኝነት(Reliabilty) አግባብነት (Vailidity) በማሳደግ ረገድ፣
12. የፈተናውን ደረጃ ከፍ ለማድረግና የአጠያየቅ ዘዴው ምርጫ ብቻ ከመሆን እንዲወጣ (በጽሑፍ የሚመለሱ ጥያቄች የተካተቱበት እንዲሆን) እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ካሉ ቢያስረዱኝ?
13. እየታማ በጥናትም እየተደገፈ ያለውን የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ደካማነት በተለይም በክሂሎች ረገድ ያለውን የጎላ ሊባል የሚችል ችግር ለማቃለል የማጠናቀቂያ ፈተናው አዘገጃጀትና አፈታተን ሂደት ምን ምን ሚና እየተጫወተ ነው ተብሎ ይታሰባል?
14. የማጠናቀቂያ ፈተናውን ዋና ዋና ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ሊባሉ የሚችሉትን እባክዎ ይዘርዘሩልኝ?
15. ማጠቃለያና መደምደሚያ
    3. እስካሁን ከተነጋገርንባቸው የተለየ /ተጨማሪ ሀሣብ ይኖራችኋል?
    4. ተጨማሪ /ሌላ አስተያየት ካላችሁ?

16.ስንብት (አድናቆት) /appreciating/

በኤጀንሲው የሚዘጋጀው ፈተና በቋንቋው ትምህርት አሰጣጥ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በተመለከተ ስላከፈሉኝ ሀሳብ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ወደፊት በአካልና በስልክ ከዚሁ ከፈተናው ጋር በተገናኙ ጉዳዮች እንደገና እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ
እጅግ በጣም አመሰግናለሁ!

አባሪ ሰባት፤ ለሙከራ ጥናትፀ እና ለዋናው ጥናት ከመምህራን ጋር ለተካሄደ የቡድን ውይይት የተዘጋጀ መምሪያ

የቡድን ተኮር ውይይት መምሪያ (Focus group Discussion Guide)

I. መግቢያ አንኳን ደህና መጣችሁና ስም ትውውቅ፣ የቡድን ተኮር ውይይቱን ዓላማ መግለፅ ቀጥሎ ተሳታፊ መምህንኑ የትምህርት ዳራቸውንና የስራ ልምዳቸውን የሚጠይቀውን ቅፅ እንዲሞሉ ማደል፡፡

II. *መምህራን ስለየኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና ተፅዕኖ /ወሸባክ ያላቸው አጠኖቶች/ ግንዛቤ / perceptions/*

መምህራን ስለየኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና ተፅዕኖ ያሏቸውን አጠኖቶች የሚከተሉትን ዋና ዋናና ንዑሳን ጥያቄዎች እየጠየቁ መረጃ መሰብሰብ፡

1. በአጠቃላይ፣ በትምህርት አስተቃቀዳችሁ(የማስተማር ቅድመ ዝግጅት) እና የክፍል ውስጥ የማስተማር ክንውናችሁ (Instruction) ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩባችሁ/ የሚያደርሱባችሁ ምንድን ናቸው?
2. የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርት አስተቃቀዳችሁ ላይ የሚያደርሰውን /የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ምን ያህል/ እንዴት ትገነዘቡታላችሁ?

   ቆስቋሽ ጥያቄዎች /Probing questing/

   1. ዓመታዊና ዕለታዊ እቅድ አዘገጃጀት ላይ
   2. የማስተማሪያ ማቴሪያሎች አመራረጥ_ ከመማሪያ መፅሐፎቹ በተጨማሪ (choice of teaching materials other than textbooks)
   3. የክፍል ውስጥ ተግባራት/ መልመጃዎች (classroom activities)
   4. የማስተማሪያ ዘዴዎቻቸሁ(your teaching method)
   5. የምታስተምሩት ይዘት(the content you would teach) እና
   6. ተማሪዎቻችሁን የምትገመግሙበት መንገድ (the way you would assess your students).
3. በትምህርት አስተቃቀዳችሁ(የማስተማር ቅድመ ዝግጅት) እና የክፍል ውስጥ የማስተማር ክንውናችሁ (በክፍል ትምህርት አቀራረባችሁ) ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ምክንያቶች /Factors/ አሉ (ይኖራሉ) የሚል አጠኖት/ ግንዛቤ አላችሁ? እንዴት?

   ሊነሱ የሚገባቸው ቆስቋሽ ጥያቄዎች

   1. የተማሪዎች የመማር ዝንባሌዎች(students' learning attitudes,)
   2. እናንተ ለሙያችሁ ያላችሁ ክበሬታ (your professional dignity)
   3. ከውጭ የሚመጡባችሁ ጫናዎች (pressure from external forces) (ከቢጤ፣ ከወላጅ
   4. ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ያላችሁ ዕውቂያ ደረጃ (the level of your awareness)
   5. የማጠናቀቂያ ፈተናው ያለው ጠቀሜታ/ ደረጃ /status
   6. የተማሪዎች የቋንቋ ዳራ/ችሎታ (በሥነ-ልሳን፣ በሥነ-ጽሑፍ፣ በክሂሎች)
   7. ለትምህርቱ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት
4. የግል ማንነታችሁ /ሰብዕናችሁ (personal characteristic) በተለይም ዕታችሁ፣ የማስተማር ልምዳችሁና የትምህርት ዳራችሁ (Educational Background) በትምህርት አስተቃቀዳችሁና የክፍል ትምህርት አቀራረባችሁ ላይ ስለሚያደርሰው ተፅዕኖ ያላችሁ ግንዛቤ ምንድን ነው

(To what extent do you perceive your personal characteristic impacts your erceptions...)?

5. በትምህርት አስተቃቀዳችሁና በክፍል ትምህርት አቀራርባችሁ ላይ የምታስተምሩበት (የትምህርት ቤታችሁ ዐውድ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ እንዴት ትገነዘቡታላችሁ?

ቆስቋሽ ጥያቄዎች

1. ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ቦታ/location፣
2. ትምህርት ቤቱ የመንግስት መሆኑ፣
3. የምታስተምሩበት የክፍል ደረጃ /the grade/s that you are teaching?
4. ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር የሚመጣ ጫና /stress from your school administration/፣
5. የተማሪዎች ብዛት በክፍል /size of the class/ ፣
6. ተማሪዎችን፣ መምህራንና ሌሎች ወገኖችን የሚመለከቱ ደንቦች፣ መመሪያዎች...

6. ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በስንት የስራ ላይ ስልጠናዎች /ትምህርቶች/ ተሳትፋችኋል?
ስልጠና/ ትምህርት አግኝታችሁ የምታውቁ ከሆነ የተሳተፋችሁባቸው ስልጠናዎች ቋንቋን በተለይ ደግሞ የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር እና ወይም ለመመዘን የሚያግዙ ሆነው አገኛችኋቸው? ለምን?

III. የሥርዓተ ትምህርቱና የፈተናው መዛመድ/መጣጣም (Overlapping)

7. የማጠናቀቂያ ፈተናውን ተገቢነት እንዴት ትገነዘቡታላችሁ?

ቆስቋሽ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎችን ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ (መሰናዶ ትምህርት) ከማሸጋገር አንፃር፣
2. ተማሪዎችን ለወደፊቱ የስራ ሕይወት መዘጋጀታቸውን ከመለካት/በቋንቋው ክሂሎች መገልገል መቻል አለመቻላቸውን ከማረጋገጥ አኳያ፣
3. ከቋንቋው ስርዓተ ትምህርት ጋር በመጣጣም /overlap በማድረግ ረገድ
4. ከመማሪያ መፅሐፎቹ ተግባሮች /መልመጃዎች ጋር ካለው ተዛምዶ አንፃር

8. . ተማሪዎቻችሁ ቋንቋውን ሲማሩ ትኩረት የሚሰጡት ለየትኞቹ የትምህርቱ ዓላማዎች/ይዘቶች ነው? ለምን ይመስላችኋል?

9. የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና ጥያቄዎች ከአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ይዘቶች ጋር አግባብ ያለው (ቀጥተኛ) ተዛምዶ አላቸው የሚል እምነት አላችሁ? ለምን?

iV. የመምህራን የማስተማር ባህርያት (Behaviors)

10. የትምህርት ዕቅድ ስታዘጋጁ ትኩረት የምትሰጧቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

11. ስታስተምሩ የምትጠቀሙባቸውን ዋና ዋና የማስተማሪያ ዘዴዎች/ስልቶች (ገለጻ፣ ቡድን ስራ፣ ጥንድ ስራ ...) ከሚሰጣቸው ትኩረት አንጻር በቅደም ተከተላቸው መሰረት ዘርዝሩልኝ።

አንዱን ካንዱ ለማበላለጥ ምክንያቶቻችሁ ምን ምን እንደሆኑ ብታሰረዱኝ ?

12. ስታስተምሩ በምትሰጧቸው ትኩረት ቅደም ተከተል መሰረት የትምህርቱን ይዘቶች ዘርዘሩልኝ::
    የትኛዎቹን በይበልጥ በክፍል ውስጥ የትኛዎችን ደግሞ ከክፍል ውጭ እንዲለማመዱ እንደምታደርጉና ምክንያታችሁን ግለጹልኝ::

IV. አዎንታዊና አሉታዊ ወሽባክ (Positive & Negative Washback)

13. የተማሪዎችን የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት /scores/ የተሻለ ለማድረግ በትምህርት ቤት ደረጃ እና በግል ምን ምን ጥረቶች ይደረጋሉ?
14. ፈተናው የቋንቋው ትምህርት አሰጣጥ ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ አለ?
    ካለ ትምህርቱ በምን በምን ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር የሚገፋፋ ነው?
    የገሀዱ ዓለም የቋንቋ አጠቃቀም(መናገር፣ መጻፍ...)ላይ ወይስ ዕውቀት (ሰዋስውና ሥነ-ጽሑፍ) ላይ ?
15. ተማሪዎችን ከማጠናቀቂያ ፈተናው ይዘትና ቅርጽ(Format) ጋር ለማስተዋወቅ (Familiarize ለማድረግ) እና ፈተና የመስራት ክሂላቸውን ለማሻሻል የምታከናውኗቸው ተግባራት ካሉ ግለጹልኝ::

16. የማጠናቀቂያ ፈተናው በተማሪዎች መማር ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ አለ? ካለ ተጽዕኖ መፍጠር የሚጀምረው መቼ ነው?
    ገና ዘጠነኛ ክፍል እያሉ? ወይስ 10ኛ ክፍል ላይ ነው? በሁለተኛ ሴሚስተር? /ከዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ?
17. በእናንተ እምነት ፈተናው ምን ምን የቋንቋ ችሎታን ለመመዘን ያስችላል?
18. ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎች ምን ምን ያውቃሉ/ያላቸው ግንዛቤ ምንድን ነው?
19. የማጠናቀቂያ ፈተናው ዋና ዋና ጠንካራና ደካማ ጎኖች ናቸው የምትሏቸውን ዘርዝሩልኝ::

vi. ማጠቃለያና መደምደሚያ

5. እስካሁን ከተነጋገርንባቸው የተለየ /ተጨማሪ ሀሣብ ይኖራችኋል?
6. ተጨማሪ /ሌላ አስተያየት ካላችሁ?

V. አድናቆት /appreciating/

አባሪ ስምንት፣ በዋናው ጥናት በመምህራን የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

በአዲስ አበባ ዩንቪርስቲ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የዶክትሪት ዲግሪ ትምህርት የጥናት ፕሮጀክት
የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና በቋንቋው መምህራን የማስተማር ቅድመ ዝግጅትና የማስተማር ተግባር ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለማጥናት
የአማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ መጠይቅ

ውድ መምህራን!

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ ከዚህ በኋላ ***የማጠናቀቂያ ፈተና(ው)*** በመባል የሚገለጸው **የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና** መምህራን የማስተማር ቅድመ ዝግጅትና የማስተማር ተግባር ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖና መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ ለሚካሄደው ጥናት ጠቃሚ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ የሚሰበሰበው መረጃም የማጠናቀቂያ ፈተናው በቋንቋው ትምህርት ሂደት ላይ እየፈጠረ ያለውን ተጽዕኖ/ ወሽባክ በተመለከተ ጠቃሚ ግብአት ለማግኘት ያስችላል፡፡
መጠይቁ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ቅድመ ዝግጅትና የማስተማር ተግባር ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ በሚመለከት መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ሁለተኛው ክፍል በፈተናዎቹ የሚፈጠሩ ተጽዕኖዎችን ምንጮች/ ምክንያቶች (factors) የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበውበታል፡፡ሶስተኛው የመምህራንን የማስተማር ባህርያት የሚመለከቱ ጥያቄዎች የቀረቡበት ነው፡፡ አራተኛው ክፍል ደግሞ ከመምህራን ግለ-ባህሪያትና ከትምህርት ቤቶቹ ዐውድ/ባህርያት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች የቀረቡበት ነው፡፡

ውድ መምህራን!

ጥናቱ ወደ ታለመለት ዓላማ የሚደርሰው እናንተ በምትሰጡት እውነተኛና ትክክለኛ መረጃ ነው፡፡ በመሆኑም ለሁሉም ጥያቄዎች የተሟላ መልስ በመስጠት ትተባበሩኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡
የሚሰበሰው መረጃም ከታለመው ጥናትና ምርምር ውጭ ለሌላ ዓላማ እንደማይውል ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡ ለሚደረግልኝ ትብብር ሁሉ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡
ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

(በዚህ መጠይቅ ክሂል(ክሂሎች) የሚለው የሚወክለው ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍ በመባል የሚታወቁትን የቋንቋው ክሂሎች መሆኑን ማስታወስ እወዳለሁ፡፡)
መጠይቁን በምትሞሉበት ጊዜ ግልጽ ያልሆነላቸው ጉዳይ ካለ በስልክ ቁ 0918775775 ወይም 0913224747 ምልክት ማድረግ /መደወል ይቻላል፡፡

ክፍል አንድ፡- የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በመምህራን የማስተማር ቅድመ ዝግጅት(የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት) እና የማስተማር ተግባር ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ /Washback effect ላይ የመምህራን ግንዛቤ (Perceptions)

መመሪያ አንድ **፡- እባክዎ ከተግባር/ጊዜ አመዳደብ፣ ከሚያስተምሩበት ዘዴ፣ ለማስተማር ከሚጠቀሙባቸው ማቴሪያሎች፣ ሲያስተምሩ ከሚሸፍኑዋቸው የትምህርት ይዘቶች ጥልቀት (Depth) እና የክፍል ትምህርት ምዘና አንጻር ያለዎትን የስምምነት ደረጃ በተመለከተ ግንዛቤዎን ከዐረፍተ ነገሮቹ/ ጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ከቀረቡልዎት አምስት ምድቦች መካከል ይበልጥ በሚስማሙበት አማራጭ ስር ይህን ‹‹√›› ምልክት በማስቀመጥ ይመልሱ፡፡**

ቁጥሮቹ የሚወክሉት የሚከተለውን ነው፤

1.ጭራሽ አልስማማም፤ 2. አልስማም፤ 3. ለመወሰን እቸገራለሁ ፤

4.እስማማለሁ ፤ 5. በጣም እስማማለሁ ፤

ተቁ	ተግባሮች / ጥያቄዎች	1	2	3	4	5
1	የማጠናቀቂያ ፈተናው የተማሪዎችን የፈተና አሰራር ችሎታ ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትን እንዳከናውን ያነሳሳኛል የሚል እምነት አለኝ፡፡					
2	የማጠናቀቂያ ፈተናው መሰጠቱ ቢቋረጥ ወይም የሚያተኩርባቸው ይዘቶች ቢቀየሩ፣ አጠያየቁም ምርጫ ብቻ መሆኑ ቢቀር ለየትምህርቱ (ለእያንዳንዱ ክሂል፣ ለሰዋሰውና ለሥነጽሁፍ ክፍሎች) የምመድበው ጊዜ፣ የማስተማር ዘዴዬና የክፍል ፈተና አዘገጃጀቴ ከበፊቱ የተለየ ይሆናል ፡፡					
3	የክፍል ውስጥ ተግባራትን/መልመጃዎችን ሳዘጋጅና ተማሪዎቼን ሳሰራ የማጠናቀቂያ ፈተናውን መሰረት አደርጋለሁ ፡፡					
4	በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የበለጠ ሽፋን የሚሰጠው ለሰዋሰውና ለስነጽሑፍ ትምህርቶች ነው ብዬ ስለማሰብ ተግባቦታዊ (የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ...)ክሂሎችን ለማስተማር ከማውለው የበለጠ ጊዜ ለሁለቱ እሰጣለሁ፡፡					
5	የተወሰኑ ክፍለ ጊዜያትን (በተለይም የፈተናው ጊዜ እየቀረበ ሲመጣ) የፈተና አሰራር ስልቶችን /ስትራቴጅዎችን ለማስተማሪያነት አውላለሁ ፡፡					
6	አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ውስጥ ትምህርት ተግባራትን የማቅደውና የማዘጋጀው የማጠናቀቂያ ፈተናውን ሳይሆን ሌሎች ምክንያቶችን መሰረት አድርጌ ነው፡፡					
7	የማስተማሪያ ዘዴዎችን የምመርጠው ተማሪዎቼን በማጠናቀቂያ ፈተናው ለስኬት የሚያበቁልኝ መሆናቸውን ግምት ውስጥ አስገብቼ ነው፡፡					
8	ተማሪዎቼን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት የማያስችሉ አንዳንድ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለማስተማሪያነት አልገለገልባቸውም ፡፡					
9	ከመማሪያ መፅሐፉ በተጨማሪ ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው ስኬታማ እንዲሆኑ የሚረዱ ናቸው የምላቸውን አጋዥ መፃሕፍትና ጽሑፎች እጠቀማለሁ ፡፡					
10	ተማሪዎቼ ለማጠናቀቂያ ፈተናው ዝግጁ እንዲሆኑልኝ በማሰብ በፈተናው ሊካተቱ ይችላሉ ከምላቸው ምንጮች(መጽሐፎች...) ጥያቄዎችን እያዘጋጀሁ አለማምዳቸዋለሁ ፡፡					
11	ተማሪዎቼ ከማጠናቀቂያ ፈተናው አቀራረብ ጋር እንዲተዋወቁ ለማገዝ ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን እየሰሩ እንዲለማመዱ አደርጋለሁ፡፡					
12	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛውን የቋንቋ ትምህርት ክፍል (ክሂል፣ ሰዋስው፣ ሥነጽሑፍ) ነው የበለጠ ትኩረት ሰጥቼ ማስተማር ያለብኝ? የሚለውን ለመወሰን ተፅዕኖ ያሳድርብኛል ፡፡					
13	አንዳንድ የመማሪያ መጽሐፉ ክፍሎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ስለማይሸፍኑ ሳስተምር እንደነገሩ ነካክቼ አልፋቸዋለሁ ወይም እዘላቸዋለሁ ፡፡					
14	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎቹን ደጋፊ ዕሁፎች /መጽሐፎች መጠቀም እንዳለብኝ ተፅዕኖ ያሳድርብኛል፡፡					
15	በመማሪያ መጽሐፉ የተካተቱትን ይዘቶችና ተግባሮች በሙሉ በትምህርት ዓመቱ ለቋንቋው					

	ትምህርት በተመደበው ክፍለ ጊዜ ለመሸፈን እንኳ አስቸጋሪ ቢሆንም ጊዜውን አብቃቅቼ ለማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያግዙ ሌሎች መፃሕፍትን በአጋዥነት እጠቀማለሁ ፡፡					
16	በማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረት የሚሰጠው ለአራቱ የየቋንቋው ክሂሎች ነው፣ የሰዋስውና የስነጽሑፍ ትምህርቶች ችላ የተባሉ ናቸው፡፡					
17	ቋንቋውን ሳስተምር በማጠናቀቂያ ፈተናው የመካተት አጋጣሚያቸው ከፍተኛ ነው ብዬ በማስባቸው የመማሪያ መጽሐፉ ክፍሎች ላይ አተኩራለሁ፡፡					
18	ምንም እንኳ አንዳንድ ርዕሰ ጉዳዮች /ይዘቶች በማጠናቀቂያ ፈተናው ላይጠየቁ እንደሚችሉ ባውቅም ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ በቂ ስለሆነ በመማሪያ መጽሀፉ የተካተትን ሁሉ አሸፍናለሁ፡፡					
19	የማጠናቀቂያ ፈተናው በትምህርቱ ይዘቶች ምርጫ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡					
20	የተማሪዎችን የቤትና የክፍል ስራ እንዲሁም ፈተናዎች ለመገምገም የምጠቀምባቸው መስፈርቶች ተማሪዎቼን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት የሚያግዙ ናቸው፡፡					
21	ለተማሪዎቼ ሙከራ(quiz)፣ ቴስትና ፈተና ሳዘጋጅ ጥያቄዎቹ ባለፉት ዓመታት በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ውስጥ ከተነሱ ጉዳዮች ጋር የሚዛመዱ እንዲሆኑልኝ ጥረት አደርጋለሁ፡፡					
22	አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቼን የምገመግመው በምርጫ ሳይሆን እንደ ጻፉ (□ረፍተነገር፣ አንቀጽ፣ ድርሰት፣ ዘገባ...)፣ግለጹ፣ አብራሩ፣ ተንትኑ፣ አስረዱ...የሚሉ አጠያየቆችን በመጠቀም ነው፡፡					
23	በክፍል ፈተናዎች የተማሪዎቼን የማዳመጥ ክሂል እፈትናለሁ፡፡					
24	በክፍል ፈተናዎች የተማሪዎቼን የንግግር ክሂል እፈትናለሁ፡፡					
25	በማዘጋጃቸው የክፍል ፈተናዎች ውስጥ ተማሪዎቼ ልዩ ልዩ ድርሰቶችን (አንቀጽ ፣ ዘገባ፣ ደብዳቤ፣ ማመልከቻ...) በተግባር እንዲፅፉ በማድረግ የመፃፍ ክሂልን እመዝናለሁ፡፡					
26	በማዘጋጃቸው የክፍል ፈተናዎች ውስጥ የተማሪዎቼን የተለያዩ ንዑሳን አንብቦ የመረዳት ክሂሎች(ሀቅን ከግል አስተየየት፣ ምክንያትን ከውጤት፣ ዋና ሀሳብን ከዝርዝር ሀሳቦች መለየትን ፣ ማጠቃለልን፣መደምደምን...) ለመገምገም የሚያስችሉ ክንውኖችን አላካትትም፡፡					
27	ተማሪዎቼን የምመዝንበት ስልት በአብዛኛው ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ይመሳሰላል፡፡					

መመሪያ ሁለት፡- የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ቅድመ ዝግጅታና የማስተማር ተግባር ላይ በሚፈጥረው ተፅዕኖ ላይ ላዳበሩት ግንዛቤ፣ ምክንያቶች(Factors) ሊሆኑ የሚችሉ ተላውጠዎች ናቸው፡፡ እባክዎ ከፊት ለፊታቸው ከቀረቡት አምስት ምድቦች ውስጥ በሚስማሙበት አማራጭ ስር የ ‹‹√›› ምልክት በማስቀመጥ ይመልሱ፡፡

ቁጥሮቹ የሚወክሉት የሚከተለውን ነው፤

1. ጭራሽ አልስማማም፤ 2. አልስማም ፤ 3. ለመወሰን እቸገራለሁ ፤
4. እስማማለሁ ፤ 5. በጣም እስማማለሁ ፤

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	1	2	3	4	5
28	ተማሪዎቼ ወደዱትም ጠሉትም ጠቃሚ ነው ብዬ የማስበውን ሁሉ አስተምራለሁ፡፡					
29	በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ያሉ ፣ ተማሪዎቼ መማር የማይፈልጓቸውን ይዘቶች ለማስተማር የማውለው ጊዜ አነስተኛ ነው፡፡					
30	በተማሪዎች ፍላጐት መሰረት አብዛኛውን ጊዜ የማስተምረው በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚካተቱን ክፍሎች ነው፡፡					
31	የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ (Attitudes) በማስተማር ተግባሬ ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡					
32	ተማሪዎቼ የክፍል ትምህርቱ ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ተዛማጅነት ያለው እንዲሆን ይፈልጋሉ፡፡					
33	ብዙውን ጊዜ ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው ጥሩ ውጤት ያመጣሉ ብዬ እጠብቃለሁ፡፡					

34	ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው በሌላ መምህር ከተማሩ ሌሎች ተማሪዎች ያነሰ ውጤት ቢያመጡ ቅር ይለኛል።					
35	ተማሪዎቼ በማጠናቀቂያ ፈተናው ስኬታማ ባይሆኑ /ጥሩ ውጤት ባያመጡ መስራት የነበረብኝን ተግባር ያልሰራሁ /guilty/ ሆኖ ይሰማኛል።					
36	የተማሪዎቼ የፈተና ውጤቶች ሰዎች በእኔ ላይ ለሚኖራቸው አመለካከት (አዎንታዊ ወይም አሉታዊ) ተፅዕኖ ያሳድራሉ።					
37	የተማሪዎችን የፈተና ውጤት ለማሻሻል በቋንቋ መምህራን ዘንድ ፉክክር ስለሌለ ተጨማሪ ነገሮችን ለመስራት ጥረት አላደርግም።					
38	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎቹን ክሂሎችና የሰዋስውና የስነጽሑፍ ትምህር ቶች ትኩረት ሰጥቼ ማስተማር እንዳለብኝ ጠቃሚ ግብረ- መልስ ይሰጠኛል።					
39	የተማሪዎቼን ፈተና ውጤት እንዳሻሽል በየደረጃው ያሉ የትምህርት ዘርፍ መዋቅሮች ለምሳሌ ወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች፣ የዞን ትምህርት መምሪያዎችና የክልሉ ትምህርት ቢሮ ተጽዕኖ የሚያሳድሩብኝ ይመስለኛል።					
40	የተማሪዎቼን ፈተና ውጤት እንዳሻሽል ከተማሪዎቼ ወላጆች/ ቤተሰቦች ጫና የሚደረግብኝ መስሎ ይሰማኛል።					
41	የትምህርት ቤታችን ርዕሳነ-መምህራን /አስተዳዳሪዎች የተማሪዎችን የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት ከመማር ጋር ስለሚያወዳድሩ፣ የራሴን ተማሪዎች የፈተና ውጤት እንዳሻሽል ተጽዕኖ የሚያሳድሩብኝ ይመስለኛል።					
42	ማጠናቀቂያ ፈተናው የትኛዎቹ የትምህርቱ ክፍሎች ላይ ትኩረት እንደሚያደረግ አውቃለሁ					
43	የማስተምረው ተማሪዎቼ የቋንቋ ዕውቀታቸውንና ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ነው፤ በማጠቃለያ ፈተናው የተሻለ ውጤት ማምጣት አለማምጣታቸው አያሳስበኝም፡					
44	የማጠናቀቂያ ፈተናው በምን በምን የትምህርቱ ክፍሎች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ስለማላውቅ በፈተናው ምክንያት በማስተማር ሂደቱ ላይ ለውጥ ለማምጣት ብዬ የማደርገው የተለየ ጥረት የለም።					
45	የማጠናቀቂያ ፈተናውን ደረጃ የምረዳው በተማሪዎች የወደፊት የስራ ዕድል ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንደሆነ አድርጌ ነው ።					
46	ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያስመዘግቡት ውጤት ለአብዛኛዎቹ መምህራን የመምህርነት ብቃት ጠቃሚ የማረጋገጫ መንገድ ነው ብየ አምናለሁ።					
47	ለአብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያገኙት ውጤት ጠቃሚ ማበረታቻ ነው ።					
48	ተማሪዎች በአማርኛ የማጠናቀቂያ ፈተና የሚያመጡት ውጤት ወደ መሰናዶ ትምህርት ለማለፍ ተዕዕኖ እንዳለው/ የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት እረዳለሁ ።					
49	የማጠናቀቂያ ፈተናው የትምህርት ቤታችንን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት በአብዛኛው ቀይሮታል ብዬ አምናለሁ ።					
50	የግል ባህሪዬ (ሰብዕናዬ) በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀቴና በክፍልትምህርት አቀራረቤ ላይ ተዕዕኖ ያሳድራል የሚል እምነት አለኝ።					
51	ቋንቋውን ለማስተማር የተመደበው ጊዜ በማስተማር ቅድመ ዝግጅት (በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀቴ)ና በማስተማር ተግባሬ ላይ ተዕዕኖ ያሳድራል ።					
52	ተማሪዎች ወደ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ሲሸጋገሩ ለደረጃው የሚመጥን የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ይዘው ነው።					
53	ለአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት ለደረጃው የተመደበውን ትምህርት በወቅቱ ለማጠናቀቅ በቂ/ ተመጣጣኝ ነው።					

ሁለት፡- የመምህራንን የማስተማር ተግባራት / የማስተማር ባህርያት(Behaviors) የሚመለከቱ ጥያቄዎች

መመሪያ አንድ፡- እባክዎ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ተገቢ ነው የሚሉትን መልስ በያዘው አማራጭ ትይዩ ባለው ሳጥን ውስጥ ይህን ‹‹√›› ምልክት በማድረግ ይመልሱ፡፡

1 .የትምህርቱን ይዘት አደረጃጀት የሚወስነው ማነው?

ሀ. ርዕሰ መምህሩ ☐ ሐ. የአማርኛ መምህራን በጋራ ☐

ለ. የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ ☐ መ. እርስዎ ራስዎ ☐

2. በትምህርት ቤታችሁ የምታስተምሩትን ትምህርት ቅደም ተከተል የምታሲዙት /የምታደራጁት እንዴት ነው?

ሀ. በመማሪያ መጽሐፉ መሰረት ☐

ለ. በትምህርት ቤቱ አሰራር መሰረት ☐

ሐ. በቋንቋው ክሂሎች መሰረት ለምሳሌ የንባባ፣የማዳመጥ...እያሉ በተናጠል በማደራጀት ☐

መ. በቋንቋው ትምህርት ተግባሮች/ መልመጃዎች መሰረት ☐

ሠ. ማጠናቀቂያ ፈተናው ለየትምህርቶቹ በሚሰጠው ትኩረት መሰረት ☐

መመሪያ ሁለት፡- እባክዎ ‘1. በጭራሽ 2. አልፎ አልፎ 3.. ብዙ ጊዜ 4. በጣም ብዙ ጊዜ ‘ ከሚሉት ሰኬሎች መካከል ይበልጥ በሚስማሙበት አማራጭ ስር ይህን ‹‹√›› ምልክት ያድርጉ ፡፡

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	1	2	3	4
3	**የትምህርት ዕቅድ ሲያዘጋጁ ለሚከተሉት ጉዳዮች ምን ያህል ትኩረት ይሰጣሉ?**				
3.1	ለማስተማር ዘዴዎች				
3.2	ለትምህርት ይዘቶች				
3.3	በትምህርቱ ሂደት ለሚከናወኑ ተግባራት/መልመጃዎች				
3.4	ለቋንቋ ክሂሎች(ለማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍ)				
3.5	ለአጋዥ ማቴሪያሎች(ጽሁፎች እና/መጻሕፍት				
3.6	የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሳሳት				
3.7	ለተማሪዎች የቤት ስራ ለመስጠት				
4	**ሲያስተምሩ የሚከተሉትን ድርጊቶች በክፍል ውስጥ ምን ያህል ይፈጽሟቸዋል?**				
4.1	ለክፍሉ ተማሪ መናገር (talk to the Whole /Class)				
4.2	ለየቡድኑ መናገር (talk to groups)				
4.3	ለእያንዳንዱ ተማሪ መናገር (talk to individuals)				
4.4	አለመናገር /ዝም ማለት (Keep Silent)				
5	**የሚከተሉትን ተግባራት በክፍል ውስጥ ምን ያህል ያከናውኗቸዋል?**				
5.1	የየዕለቱን ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች መናገር				
5.2	ተማሪዎች እያንዳንዱን ትምህርት/ተግባር እንዴት መስራት እንዳለባቸው ማሳየት				
5.3	የምንባቦችን ይዘት ማብራራት				
5.4	የመማሪያ መጽሀፉን መልመጃዎች ማብራራት				
5.5	የቤት ስራዎችን አሰራር ማብራራት				
5.6	ያለፉ ዓመታትን የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ወደ ክፍል እያመጡ ማሰራትና፡ ፈተና እንዴት እንደሚሰራ ማብራራት				
5.7	የቡድን ስራዎችን እየሰጡ ማሰራት ወይም ውይይቶችን ማደረጀት				
5.8	የቋንቋ ክሂሎችን አዋህዶ/አቀናጅቶ ማስተማር				
5.9	የቤት /የክፍል ስራዎችን ማረም				

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176

ክፍል አራት፡- ዳራዊ መረጃ

መመሪያ አንድ፡- ከተራ ቁጥር 1 — 4 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ከእርሰዎ ዳራ (Background) ጋር የሚስማማውን አማራጭ የያዘው ክፍል ሳጥን ውስጥ ይህን ‹‹√›› ምልክት በማድረግ ይመልሱ ፡፡

1. ፆታ 1 ሴት ☐ 2 ወንድ ☐
2. ካለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ (የያዝነውን ዓመት ጨምሮ)
   ሀ. የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ስንት ዓመት አስተምረዋል ?
   1 አንድ ☐ 2 ሁለት ☐ 3 ሶስት ☐ 4 አራት ☐ 5 አምስት ☐
   ለ. የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን ስንት ዓመት አስተምረዋል ?
   1 አንድ ☐ 2 ሁለት ☐ 3 ሶስት ☐ 4 አራት ☐ 5 አምስት ☐
3. ያለዎት የትምህርት ደረጃ ፡-
   1 የመጀመሪያ ዲግሪ (ቢ.ኤ) በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ (በአማርኛ) ☐
   2 የመጀመሪያ ዲግሪ አማርኛን በማስተማር (ቢ.ኢ.ዲ.)☐
   3. የመጀመሪያ ዲግሪዎ ሌላ ከሆነ ይጠቀስ _____
   4 ሁለተኛ ዲግሪ አማርኛን በማስተማር ኤም ኤ ☐
   1. ሁለተኛ ዲግሪዎ ሌላ ከሆነ ይጠቀስ _____

መመሪያ ሁለት፡- እባክዎ የሚከተሉት ጥያቄች ደግሞ መልስዎትን በክፍት ቦታዎች ላይ በመጻፍ ይመልሱልን፡፡

4.. በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያለዎት የማስተማር ልምድ (የያዝነውን ዓመት ጨምሮ) ስንት ዓመት ነው ? _____ ዓመት አስተምሬአለሁ፡፡
5. በአንድ ክፍል የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ብዛት በአማካኝ ስንት ነው?_____
6. በሳምንት የሚያስተምሩት ክፍለ ጊዜ ብዛት ስንት ነው? _____
7. ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ ከቋንቋ ማስተማር ፈተና አወጣጥ/ አዘገጃጀት ጋር ግንኙነት ያላቸው ስንት የስራ ላይ ስልጠና /ትምህርት አግኝተዋል? _____
8. በመደበኛ የዩኒቨርስቲ ትምህርትዎ የቋንቋ ፈተናን(ምዘናን) የሚመለከት ኮርስ ወስደዋል?_
9. ተማሪዎችዎን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት ከመማሪያ መፅሀፉ ውጭ የሚጠቀሙባቸው ሌሎች ማጣቀሻ መጽሐፎችና ሌሎች ማቴሪያሎች ካሉ ይዘርዝሪቸው፡፡
10. እባክዎ በየዓመቱ ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ስለሚዘጋጀው የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ያለዎትን አስተያየት (ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን፣ ወደፊት እንዴት ባለ ሁኔታ ሊዘጋጅ እንደሚገባው የሚሰጡትን ምክር...) ይግለጹልኝ፡፡(ቦታ ካነሰዎት በጀርባ ያለውን ገጽ ይጠቀሙ)፡፡

አባሪ ዘጠኝ፣ በዋናው ጥናት በተማሪዎች የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና በቋንቋው መማርና ማስተማር ሂደት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ያላቸው ግንዛቤ (perceptions)

ውድ ተማሪዎች!

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ አማርኛ ፈተናን ከመማር ማስተማሩ ጋር አዛምዶ ለማጥናት ለታሰበ ምርምር መረጃ ማሰባሰብ ነው፡፡በተለይም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥና የ10ኛ ክፍል ትምህርታችሁን ስታጠናቅቁ በምትፈተኑት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የአማርኛ ፈተና ላይ ምን አይነት ግንዛቤ (perceptions) እንዳላችሁ ለማጥናት ይህ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡

ለጥናቱ ስኬት የእናንተ እውነተኛና ትክክለኛ ምላሽ ወሳኝ በመሆኑ ሁሉንም ጥያቄዎች በትክክል በመመለስ እንደትተባበሩ በአክብሮት ትጠየቃላችሁ፡፡ በመጠይቁ የምትሰጡት ማንኛውም መረጃ ከምርምሩ ስራ ውጭ ለሌላ ተግባር አይውልም፡፡

በመጠይቁ ስም አይፃፍም፡፡

ጊዜ ሰጥታችሁ መጠይቁን በጥንቃቄ በመመላት ስለተባበራችሁኝ፣ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ክፍል አንድ፣ ዳራዊ መረጃ

ትክክለኛ መልስ ከያዘው ሳጥን ውስጥ የ‹‹√›› ምልክት አስቀምጡ፣

1. ፆታ 1. ወንድ ☐ 2. ሴት ☐
2. ዕድሜ 1. ከ14-18 ☐ 2. ከ19-22 ☐ 3. ከ 22 በላይ ☐
3. አማርኛ ቋንቋ ስትማሩ፣ መምህራችሁ የ10ኛ ክፍልን የአማርኛ ሀገር አቀፍ የማጠናቀቂያ ፈተና በተመለከተ ምን ያህል ጊዜ ያነሳሉ?
   1. ምንም ጊዜ አያነሱም ☐ 2. አልፎ አልፎ ☐
   3. አንዳንድ ጊዜ ☐ 4. በአብዛኛው ክፍለ ጊዜ ☐ 5. በየክፍለ ጊዜው ☐
4. ያለፉ ዓመታት የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ለመስራት ምን ያህል ጊዜ ታውላላችሁ?
   1. ምንም ጊዜ አላውልም ☐ 2. አልፎ አልፎ ☐
   3. አንዳንድ ጊዜ ☐ 4. ብዙ ጊዜ ☐ 5. ሁልጊዜ ☐

ክፍል ሁለት፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብቡና ከፊት ለፊታቸው ከቀረቡት አራት ምድቦች /አማራጮች ውስጥ በምትስማሙበት አማራጭ ስር የ ‹‹√›› ምልክት በማስቀመጥ መልሱ፡፡ ቁጥሮቹ የሚወክሉት የሚከተሉትን ነው፤

1. በጭራሽ ፤ 2. አልፎ አልፎ ፤ 3. ብዙ ጊዜ ፤ 4. በጣም ብዙ ጊዜ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	1	2	3	4
5	**የአማርኛ መምህራችሁ የሚከተሉትን በክፍል ምን ያህል ጊዜ ያከናውናሉ?**				
5.1	ለአጠቃላይ የክፍሉ ተማሪዎች መናገር (talk to the whole class)				
5.2	በቡድን ለተቀመጡ ተማሪዎች መናገር (talk to groups of students)				
5.3	ለእያንዳንዱ ተማሪ በተናጠል መናገር (talk to individual students)				
5.4	ምንም ሳይናገሩ ተማሪዎች የሚናገሩትን (የሚሰሩትን) መከታተል				

6	**በአማርኛ ክፍለ ጊዜ መምህራችሁ የሚከተሉትን ተግባራት (activities) ምን ያህል ተግባራዊ ያደርጋሉ?**				
6.1	የትምህርቱን ዓላማ /ዓላማዎች ለተማሪዎች መንገር/ማስተዋወቅ፣				
6.2	የምንባቡን ይዘት ማብራራት፣				
6.3	የተለየ ቋንቋ ነክ ጉዳይ ሲያጋጥም (ለምሳሌ የቃላት ወይም የዐረፍተነገሮች አወቃቀር) ማብራራት፣				
6.4	የመማሪያ መጽሐፉን መልመጃዎች አሰራር ማብራራት፣				
6.5	ያለፉ ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን አሰራር ማብራራት፣				
6.6	የቡድን ሰራ ወይም ውይይት ማደራጀት፣				
6.7	የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት የምንማርባቸውን ተግባራት ማደራጀት፣				
6.8	በተማሪዎች ዕሁፍ (ዐ.ነገር፣ አንቀፅ፣ ድርሰት...) የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ነጥብ በነጥብ ማብራራት፣				
7	**በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚከተሉትን የቋንቋ ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ምን ያህል ትማራላችሁ?**				
7.1	ማንበብ				
7.2	መፃፍ				
7.3	መናገር				
7.4	ማዳመጥ				
7.5	ሰዋስው				
7.6	ሥነ-ዕሁፍ				
8	**በአማርኛ ክፍለ ጊዜያት የሚከተሉትን ተግባራት ምን ያህል ታከናውናላችሁ?**				
8.1	የጥንድ ስራ መስራት፣				
8.2	የቡድን ውይይት ማካሄድ፣				
8.3	የራስን ሀሳብ በቃል ወይም በዕሑፍ መግለፅ ፣				
8.4	ጥያቄ መጠየቅ፣				
8.5	ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን መስራት፣				
9	**ለአጠቃላይ ፱ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ዝግጅት፣ የሚከተሉትን ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ለማዳበር ምን ያህል ልምምድ ታደርጋላችሁ?**				
9.1	ማንበብ				
9.2	መፃፍ				
9.3	መናገር				
9.4	ማዳመጥ				
9.5	ሰዋሰው				
9.6	ሥነ-ዕሁፍ				
10	**የሚከተሉትን ተግባራት ከክፍል ውጭ ምን ያህል ታከናውናላችሁ?**				
10.1	ራዲዮ ማዳመጥ				
10.2	. ቴሌቪዥን መመልከት				
10.3	ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ማንበብ				
10.4	ለ፱ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና የሚያግዙ አጋዥ መጽሐፎችን ማንበብ				
10.5	ያለፉ ዓመታት ፈተና ወረቀቶችን ለብቻ ወይም ከጓደኛ ጋር መስራት				
11	**በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚከተሉትን የቋንቋ ክሂሎችና የሰዋሰውና የሥነ-ዕሁፍ ክፍሎች ምን ያህል ትማራላችሁ /ታከናውናላችሁ?**				
11.1	*1. የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን በተመለከተ*				
1.1.1	በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ውይይቶችን ማካሄድ፣				
11.1.2	አካባቢያዊ፣ ወቅታዊና አገራዊ ጉዳዮች ላይ በቂ መረጃዎችን ከልዩ ልዩ ምንጮች አሰባስቦ ክርክር ማካሄድ፣				
11.1.3	በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች መልዕክትን ግልፅ የሚያደርጉ የድምፅና የአካል እንቅስቃሴዎችን... በመጠቀም የዳብዳ ንግግር ማድረግ፣				

11.1.4	በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዝግጅት በማድረግና መልዕክትን ግልፅ የሚያደርጉ የድምፅ እና የአካል እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር ማድረግ፣				
11.1.5	በተወሰነ ርዕስ ንግግር ማድረግ				
11.2	***የንባብ ክሂልን (የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችን) በሚመለከት***				
11.2.1	በሚነበብ ፅሁፍ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋናና ጠቃሚ ዝርዝር ሀሳቦችን መለየት፣				
11.2.2	በሚነበቡ ፅሁፎች ውስጥ ለሚገኙ አዳዲስ ቃላት፣ በአገባባቸው መሰረት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን መስጠት፣				
11.2..3	ከልዩ ልዩ መግለጫዎች (ከስዕል፣ ከሰንጠረዥ...) መረጃዎችን ማግኘት፣				
11.3.	***የመፃፍ ክሂልን በተመለከተ***				
11..3. 1	ስርዓተ ነጥቦችን (በፅሁፍ ውስጥ) በተገቢ ቦታቸው ማስገባት/መጠቀም				
11. 3..2	ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን በመገልገልና የአንቀጽ አጻጻፍ መርህን በመከተል የተለያዩ (ተራኪ፣ አወዳዳሪ፣ ገላጭ ...) አንቀፆችን መፃፍ				
11.3..3	የተለያዩ የስራና ንግድ ነክ ደብዳቤዎችን መፃፍ ፣				
11.3.4	በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ዘገባ መፃፍ ፣				
11.3.5	ማርቀቅ፣ ረቂቁን ማረም ፣መከለስና የድርሰቱን ዋና ፅሁፍ መፃፍ ፣				
11.3.6	ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ተገልግሎ መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ ያላቸው የተለያዩ (ተራኪ፣ ስዕላዊ፣ ገላጭና አመዛዛኝ) ድርሰቶች መፃፍ፣				
11.3.7	ከተለያዩ ንግግሮችና ፅሑፎች የሚገኙ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ፣				
11.4	***የሰዋሰው ፅውቀትን ለማጎልበት ከሚረዱ መሰረታዊ ሀሳቦች ጋር መተዋወቅ***				
11..4.1	የቋንቋ ምንነትን፣ አጀማመርንና ባህሪያትን መግለጽ ፣				
11.4.2	የሀረግ አይነቶችን (ቅፅላዊ፣ ስማዊ፣ መስተዋድዳዊ፣ ተውሳከ ግሳዊ፣ ግሳዊ) መለየት፣				
11.5.	***ሀሳብን ስነ-ፅሁፋዊ በሆነ መልክ የመግለፅ ችሎታን በተመለከተ***				
11.5.1	የፊጠራ ስነ-ፅሁፍ ዘርፎችን (ስነ-ቃል፣ ግጥም፣ ልቦለድ፣ ድራማ) መለየት፣				
11.5.2	የፊሊጣዊ ንግግሮችን መልዕክት መረዳት፣				
11.5.3	በተለያዩ ዘይቤዎች (በአነፃፃሪ፣ ተለዋጭ፣ ሰውኛ፣ ተምሳሌት፣ ግነት...) የቀረቡ አባባሎችን/ ሀሳቦችን መረዳትና ማብራራት፣				
11.5.4	የልቦለድ አይነቶችን፣ አላባውያንና ቴክኒኮችን መለየት፣				

ክፍል 3፡ የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች በያዙት ሀሳብ መስማማት/ አለመስማማታችሁን ከቀረቡላችሁ አምስት ምድቦች (1. ጭራሽ አልስማማም 2. አልስማማም 3. ለመወሰን እቸገራለሁ 4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ) መካከል ከምትስማሙበት አማራጭ ስር የ ‹‹√›› ምልክት አስቀምጡ፡፡

ተ.ቁ	ጥያቄ	1	2	3	4	5
12	**የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ስታወዳድሩት እንዴት አገኛችሁት?**					
12.1	ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ይልቅ ህይወታዊ ነው (ዘገባ፣ ደብዳቤ፣ ቃለጉባኤ፣... አጻጻፍን አዳምጦና አንብቦ መረዳት፣ ሀሳብን አሳክቶ መግለፅን የምንማርበት ነው) ፡፡					
12.2	የቋንቋው ትምህርት ተግባሮችን /መልመጃዎችን ሳቢ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡					
12.3	አያሌ የቡድን ውይይቶችን የምናካሂድበት ትምህርት ነው፡፡					
12.4	ከመምህራችንና ከክፍል ጓደኞቻችን ጋር ለመግባባት የተሻለ እድል የምናገኝበት ነው፡፡					
12.5	ትምህርታችንን ጨርሰን፣ በሥራ ዓለም ስንሰማራ ልናከናውናቸው ከምንችላቸው ተግባራት ጋር የሚዛመድ ነው፡፡					
13	**አማርኛ ቋንቋ የምትማሩበትን ምክንያት በሚመለከት ቀጥሎ በቀረቡት ሀሳቦች ምን ያህል ትስማማላችሁ?**					
13.1	ስለቋንቋ መሰረታዊ ባህርያትና የአወቃቀር ስርዓት ለመማር					
13.2	በማህበራዊ ህይወት ንቁ ተሳታፊ ለመሆን፣					

13.3	ከትምህርት በኃላ የተሻለ ስራ ለማግኘትና በስራ ቦታ (ሪፖርት ፣ ቃለጉባኤ፣ የስራ ደብዳቤ በመፃፍ፤ በማዳመጥና በመናገር... ክሂሎች) ውጤታማ ሆኖ ለመገኘት					
13.4	ወደ መሰናዶ ትምህርት ለማለፍ፣					
13.5	ፈተና ለማለፍ					
13.6	የትምህርት ቤቱን፣ የቤተሰብንና የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት፣					
13.7	የአማርኛ ፊልሞችን፣ ድራማዎችን እንዲሁም የተለያዩ የሬዲዮና የቴሌቪዥን መርሀ ግብሮችን የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣					
14	**ቋንቋ ለመማር የምትመርጧቸው ስልቶች /ስትራቴጅዎች የትኞቹ ናቸው?**					
14.1	በአማርኛ የተፃፉ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ማንበብ፣					
14.2	በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፉ የተለያዩ የራዲዮ መርሀ ግብሮችን መከታተል፣					
14.3	በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፉ የቴሌቪዥን መርሀ ግብሮችን መመልከት፣					
14.4	በክፍል የቡድን ስራዎች ሲሰጡ በንቃት መሳተፍ፣					
14.5	በክፍል ውስጥ ሀሳብን ለክፍሉ መግለፅ፣					
14.6	መልመጃዎችንና ሌሎች የቤት ስራዎችን በወቅቱ መስራት፣					
14.7	በትምህርት ቤቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ክበባት (ድራማ፣ ክርክር...) መሳተፍ፣					
14.8	. ለሰዋሰው ትምህርት የተለየ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል፣					
14.9	የመማሪያ መጽሐፉን በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ይዞ መገኘት፣					
15	**በሚከተሉት አስተሳሰቦች ምን ያህል ትስማማላችሁ?**					
15.1	ተማሪዎች ፈተና ይጠላሉ፣					
15.2	የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ያለፉ ዓመታት ፈተናዎችን በመስራት ይሻሻላል፣					
15.3	ፈተና መፈተን በጣም ጠቃሚ የመማር ልምድ (የመማሪያ ስልት) ነው፣					
15.4	የፈተናዎች መኖር ተማሪዎች ጠንክረው እንዲያጠኑ ያደርጋል፤					
15.5	ፈተናዎች ተማሪዎች ስለራሳቸው በሚኖራቸው ግንዛቤ (self -image) ላይ ጠቃሚ አስተዋፅኦ አላቸው፤					
15.6	በፈተና የሚገኝ ውጤት ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆን ለመደሰት ወይም ለመከፋት ምክንያት ይሆናል፡፡					

አባሪ አስር፣ ለምክትል/ ርዕሳነ መምህራን የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ

ለአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህት ቤቶች ርዕሳነ መምህራንና /ምክትል ርዕሳነ መምህራን የሚቀርቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

የትምህርት ቤቱ ስም ውይይቱ የተካሄደበት ቀን የተጀመረበት ሰዓት
የተጠናቀቀበት ሰዓት

፩ የጥናቱን ዓላማ መግለጽ

፪ ጥያቄዎች

1. መምህራን መያዝ ያለባቸው የክፍለ ጊዜና የክፍል/ ሴክሽን ብዛት የሚወሰነው እንዴት ነው? በመነሻነት የሚያገለግል መመሪያ አለ?
2. የተከተታይ ምዘና ውጤት የሚሰጠው እንዴት ነው ? መስፈርቶች ምንድን ናቸው ? መስፈርቶቹ እንደየትምህርቱ አይነት ባህሪ የሚለያዩ ናቸው ወይስ ወጥ ናቸው?
3. የተማሪዎችን የክፍልና የማጠናቀቂያ ፈተና ለማሻሻል (ተማሪዎች ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ እንዲዛወሩ ወይም በማጠናቀቂያ ብሄራዊ ፈተናዎች ውጤታማ እንዲሆኑ) በባለድርሻ አካላት (በትምህርት ቤቱ፣በወረዳው ት/ጽ/ቤት፣በዞን ፣በክልል ት/ት ቢሮ ታቅደው የሚሰሩ ስራዎች ካሉ ቢያስረዱኝ? የፈተናው ***መኖር ጠቀሜታስ*** ምንድነው ?
4. ትምህርት ቤቱ ባለፉት አመታት የተማሪዎችን ውጤት በማሻሻል ረገድ በባለድርሻ አካላት (ለምሳሌ በዞኑ ትምህርት መምሪያና በክልሉ ትምህርት ቢሮ) የተሰጠውን ደረጃና አስተያየት እባክዎ ያስረዱኝ፡፡
   የተጠቀሱት አካላት የትምህርት ቤቶቹን ደረጃ ለመመዘን የሚጠቀሙባቸው ሰነዶች ምን ምን እንደሆኑ ቢገልጹልኝ?
5. የትምህርት ቤታችሁ የቋንቋ መምህራን ባለፉት አምስት ተከታታይ አመታት ውስጥ ቋንቋን ለማስተማርና ለመገምገም የሚያግዙ ስልጠናዎች አግኝተው ያውቃሉ?
6. የትምህርት ቤታችሁ የቋንቋ መምህራን የቋንቋ ክሂሎችን (የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን) ትኩረት ሰጥተው እንዲያስተምሩና ምዘናዎቻቸው እነዚህን ክሂሎች ያካተቱ እንዲሆኑ የምታደርጉት ክትትልና ድጋፍ ካለ ቢያስረዱኝ?
7. ተማሪዎቻቸውን በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ለጥሩ ውጤት ለሚያበቁ መምህራን የሚሰጥ ማበረታቻ ወይም ሌላ የማትጊያ ስርዓት አለ? ለምን?
8. ባለፉት ተከታታይ አምስት አመታት(2004ን ጨምሮ) በትምህርት ቤታችሁ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማጠናቀቂያ ብሄራዊ ፈተና ውጤት ከሌሎች የትምህርት ዐይነቶች ጋር ሲነጻጸር ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ቢያስረዱኝ?
9. በትምህርት ቤቱ የሥነ-ጽሑፍና የድራማ ክበባት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ምን ምን ጥረቶች ይደረጋሉ?
10. ተማሪዎችን በማጠናቀቂያ ፈተናዎች ውጤታማ ለማድረግ በትምህርት ቤቱ ፣ በወረዳው፣በዞኑ ትምህርት መምሪያና በክልሉ ትምህርት ቢሮ የሚደረጉ (እስከአሁን ያልተጠቀሱ)ጥረቶች ካሉ ቢገልጹልኝ?
11. ተማሪዎች ለመማር ያላቸውን ፍላጎትና በፈተና ውጤታማ ለመሆን የሚያደርጉትን ጥረት ቢገልጹልኝ፡፡
12. ሌላ ያልተጠቀሰ አስተያየት ካለዎት?

፫ ምስጋና

አባሪ 11፤ ከዞን የትምህርት ባለሙያዎች ጋር ለተካሄድ ቡድን ውይይት የተዘጋጀ መምሪያ

ለዞን ትምህርት መምሪያ/ለከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት ሀላፊዎች የሚቀርቡ የቡድን ተኮር ውይይት መምሪያ/ መነሻ ጥያቄዎች

1. በዞኑ ትምህርት መምሪያ ስር ባሉ ወረዳዎች /በከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ስር በሚገኙ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ጥራትን ከፍ ለማድረግ /ለማሻሻል ምን ምን ተግባራት እየተከናወኑ እንዳሉ ብታስረዱኝ ?
2. የተማሪዎችን የክፍልና የማጠናቀቂያ ፈተና ለማሻሻል (ተማሪዎች ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ እንዲዛወሩ ወይም በማጠናቀቂያ ብሄራዊ ፈተናዎች ውጤታማ እንዲሆኑ) በባለድርሻ አካላት (ትምህርት ቤቶች፣ ወረዳው ት/ጽ/ቤቶች፣ዞኑ/ከተማ አስተዳደሩ ፣ክልል ት/ት ቢሮው አቅደው የሚሰሯቸው ስራዎች ካሉ ብታስረዱኝ? የማጠናቀቂያ ፈተናው *መኖር ጠቀሜታስ* ምንድነው ?
3. ትምህርት ቤቶች በየሴሚስተሩ /በየዓመቱ ደረጃ የሚሰጣቸው ከሆነ፣ ዋና ዋና መስፈርቶችን ብትገልጹልኝ ?
4. በዞኑ/ በከተማ አስተዳደሩ ስር በሚገኙ የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን በትምህርት ፖሊሲውና በስርዓተ ትምህርቱ ማዕቀፉ መሰረት ትኩረታቸውን የቋንቋ ክሂሎች ላይ አድርገው እንዲያስተምሩ ምን ምን ድጋፍ ይደረግላቸዋል ?
5. በዞኑ/በከተማ አስተዳደሩ ስር ባሉ የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ ቋንቋን ለማስተማርና ለመገምገም የሚያግዙ ስልጠናዎች አግኝተው ያውቃሉ? ለምን ?
6. ያለፉት ዓመታት የ10ኛ ክፍል የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት ትንተና ዞኑ/ከተማ አስተዳደሩ በቋንቋ ትምህርቶች(በአማርኛና በእንግሊዘኛ) ተማሪዎችን ወደ መሰናዶ በማሳለፍ ረገድ በክልሉ የሚገንበትን ደረጃ ብታስረዱኝ?
7. በዞኖ/በከተማ አስተዳደሩ ባሉ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥሩ ውጤት የሚመጣባቸው የትምህርት አይነቶች ምን ምን ናቸው? ምክንያቶቹ ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
8. ከ7-12 በሚደርሱ ክፍሎች (Sections) እየተመደቡ የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራን የቋንቋውን ክሂሎች በአግባቡ ለማስተማርና ለመገምገም ይችላሉ ተብሎ ይታመናል? እንዴት?
9. ሌላ ያልተጠቀሰ አስተያየት ካላችሁ?

አባሪ 12፤ የተግባቦታዊ ቋንቋ ትምህርት መገለጫ የምልከታ ንድፍ/ቅጽ

የምልከታ ቁጥር ማዕከል ቀን

ጊዜ/Time	ተግባራት (Activity		የተሳታፊዎች አደረጃጀት (participant Organization)							ይዘት (Content)						የተማሪዎች የመማር ዘዴ	ፈተና ነክ /test Refer.			ማቴሪያሎች(Materials)					
	የመምራን	የተማሪዎች	ክፍላዊ(WHho le Class)			ቡድን		ግል		አመራር	ተተኪሪ ቋንቋ	የይዘት ቁጥጥር				ማ/መ/ማን/መጻ/ሌላ				አይነት/Time			ምንጭ/ Souce		
			መ-ተ/ክ	ተ-ተ/ክ	በጋራ/Chor	የተለያየ	ተመሳሳይ	የተለያየ	ተመሳሳይ		ስነ-ልሳን	ስነ-ጽሁፍ	አጠቃቀም	መ-ቴክስት	መ-ተ-ቴክስት	ተ-ግባ		ማጠናቀቂያ	ልኅ	ስነ-ራ-ቴክ	ጽሁፍ W	ማለማ /A	ማታይ /V	ፒዲኤፍ P	ካሬል ፕ S	ተፈጥሯዊ/N

አባሪ 13፤ የፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ምላሾች ናሙና

ከፈተናዎች ኤጀንሲ የአማርኛው ክፍል የፈተና ዝግጅት ባለሙያ ጋር የተካሄደ ቃለመጠይቅ ከቴፕ ካሴት ወደጽሑፍ የተቀየረ

ለጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች ቃል በቃል

1.የትምህርት ደረጃቸውና የስራ ልምዳቸው

የትምህርት ደረጃ ቢ.ኤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ፣ ኤም.ኤ አማርኛን በማስተማር፡፡ በስራ ልምድና ረገድ አስራ ሁለት አመት ያህል በሁለተኛ ደረጃ ከ9-12 በአማርኛ መምህርነት ከዚያ ቀጥሎ በትምህርት ሚኒስቴር በተለያዩ ሙያዎች በስርዓተ ትምህርት ዝግጅትና አሁን ባለሁበት ፈተና ዝግጅት ባለሙያነት አገልግሎት ሰጥቻለሁ፡፡

2. የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የሚያካትታቸውን ዋና ዋና ይዘቶች (ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች) ምንድን ናቸው?

ምላሽ፡ አዎ እነዚህ እንግዲህ በስርዓተ ትምህርቱ ስርዓተ ትምህርቱ አራቱን የክሂል ዘርፎችና ሁለት የዕውቀት ዘርፎችን ነው የሚያካትተው፡፡ አካቶ የተዘጋጀው ማለት ማዳመጥ፣ ንግግር ፅህፈትና ማንበብ በክሂል ዘርፍ በእውቀት ዘርፍ ደግሞ ስነ-ልሳንና ስነ-ጽሁፍ ናቸው፡፡ እና እነዚህን የስርዓተ ትምህርት ይዘቶች መሰረት በማድረግ ነው ያው ፈተናው የሚዘጋጀው፡፡

3. እነዚህን የዘረዘሩልኝ ይዘቶች በፈተናው በመሸፈንና በመወከል ረገድ ከሚሰጣቸውክብደት/ትኩረት አንፃር እባክዎ በቅደም ተከተላቸው መሰረት ይግለፁልኝ?

እንግዲህ እንትኑ ነው የሚወስነው የስርዓተ ትምህርቱ ሽፋን ነው፡፡ ከሞላ ጎደል ስነ-ልሳንና ስነ-ጽሁፍ ሰፊ ሽፋን አላቸው፡፡ ሌሎቹም እንደዚያው ነው ተቀራራቢ ነው ምናልባት የንግግርና የማዳመጥ ክሂሎች ናቸው፡፡ ለመለካትም አስቸጋሪ ስለሆኑ ነው እነዚህ ካልሆኑ በስተቀር ሌሎቹ ተቀራራቢ እንትን ነው ያላቸው እና በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የተሰጣቸው የክፍለ ጊዜ መጠን ነው የሚወስነው፡፡ እና ከዚያ አንፃር እና በተለይ ለመለካት ያላቸው አመቺነት ምክንያቱም እኛ የምንሰጠው ፈተና ምርጫ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ አንጻር ንግግርና ማዳመጥ ያው በተግባር ካልሆነ በስተቀር ለመመዘን አስቸጋሪ ነው፡፡ ፅህፈትም እንደዚሁ እና ከሞላ ጎደል ግን ብዙም ይህን ያህል የጎላ ልዩነት አላቸው ለማለት አንችልም፡፡ ወሳኙ ግን በእንትኑ ውስጥ በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የተሰጣቸው የክፍለ ጊዜ መጠን ነው፡፡

4. ፈተናውን ለማዘጋጀትና በውስጡ የሚካተቱትን ይዘቶች ለመወሰን መነሻ የሚደረጉት ምንጮች (ሰነዶች) ምንድናቸው? በምንጮቹ (በሰነዶች) ትኩረት የሚሰጠው ለምንድነው?

የስርዓተ ትምህርት ማቴሪያሎች ማለት ሲለበሱ አለ መርህ ትምህርቱ ማለት ነው፡፡ ከዚያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተግባራዊ እየሆነ የመጣው አጥጋቢ የእውቀት ደረጃ መለኪያ (MLC/minimum learning competency) የሚለው እሱ አለ፡፡ ከዚያ መጽሐፍቶች ናቸው መማሪያ ማስተማሪያ (teacher guide) ቲቸር ጋይድ የተማሪው ቴክስት ናቸው፡፡

5. የማጠናቀቂያ ፈተናው ሲዘጋጅ የሚከተለው የትኛውን የቋንቋ ትምህርትና ፈተና ዝግጅት አቀራረብ (approach) ነው?

አይ ከዚያ ላይ እንኳ ብዙም እንትን የለም ይህን ነው የምንከተለው የምንለው፡፡ ለምን ራሱ እንትኑ የተገደበ ነው፡፡ ለምሳሌ በምርጫ ጥያቄ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እና ስለዚህ የተለያዩ እንትኖች ያካተተ open ended ጥያቄዎችን የተካተቱበት ቢሆን ኖሮ ምንአልባት እነዚህን ጉዳዮች አንስቶ እንትን ለማለት ይቻል ይሆናል፡፡ ስለዚህ ከዚህ አንፃር ብዙም እንትን የለም፡፡

6. በየዓመቱ የሚዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ የማጠናቀቂያ ፈተና ቋንቋውን በማስተማርና መማር ሂደቱ ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ እንዲኖረው ነው የሚጠበቀው (የሚታለመው) (intended washback)?

አዎ ምንድነው ሁሉንም እንትኖች አካቶ ነው የሚቀርበው ፈተናው ሁሉንም የክሂል ዘርፎች እንደገና ደግሞ ሁለቱን የእውቀት ዘርፎች ማለት ነው በዚህ ላይ ደግሞ በተቻለ አቅም በየክፍል ደረጃው ያሉ ወይም በስርዓተ ትምህርቱ የተዘረዘሩ ይዘቶች ማለት ነው፡፡ ዓላማዎች እነዚህ እንዲሸፈኑ ነው ጥረት የሚደረገው ስለዚህ የግድ መምህራን ሁሉንም ይዘቶች በዓመቱ ውስጥ እንዲሸፍኑ አስተዋፅየ ያደርጋል፡፡ እንደዚህ ሆኖ መዘጋጀቱ ለተማሪውም እንደዚሁ ነው፡፡ ድሮ ከዚህ በፊት ይቀርቡ የነበሩ ፈተናዎች ይዞታቸው በተወሰኑ ክሂሎች ወይም በእውቀት ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ምናልባትም ደግሞ ከስርዓተ ትምህርቱ ውጪ የሚሆኑበት አይነት ነገር ማለት ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ነገር ስለነበረ በቃ አማርኛ ምን ችግር አለው ሳንዘጋጅ ምን ሳንል ልንፈተነው የምንችለው ነው የሚል አይነት ግንዛቤ በተማሪዎች ዘንድ ነበር፡፡ ወይም አንድ ሁለት ቀን ምናምን ወይም ሶስት ቀን ሲቀረው ነው አሁን ግን የግድ በአማርኛ ውጤት ማምጣት የሚፈልግ ተማሪ የግድ መጻህፍቶችን እንትን ማለት አለበት፤ መጽሀፍቶችንም ትምህርቱንም በሚገባ መከታተል አለበት ይህን እንዲያደርግ ያስገድደዋል የሚዘጋጁትን እንትኖች ማለት ነው፡፡ እና ያላጠና ወይም ያልተዘጋጀ ተማሪ በነሲብ የሚያገኘው አይደለም፡፡ እና ከዚህ አንፃር የሆነ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ለመምህራንም ለተማሪዎችም በአጠቃላይ ለመማር ማስተማሩ ሂደት::

7. በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርተ ስርዓተ ትምህርቶችና በፈተናው መካከል ምን አይነት ግንኙነት እንዲኖር ይጠበቃል? ለምን?

አዎ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ያው ፈተናው የሚመሰረተው በስርዓተ ትምህርቱ ላይ ነው፡፡ እና ስርዓተ ትምህርቱ ላይ የተጠቀሱ የተዘረዘሩ ዓላማዎች እነዚያን ዓላማዎች መለካት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ናቸው እንዲቀርቡ የሚደረገው፤ እንዲካተቱ የሚደረገው እና ሁሉም በተቻለ አቅም ሊለኩ የሚችሉ ዓላማዎች በፈተናዎች ይሸፈናሉ፡፡ ስለዚህ በሁለቱ መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለ ማለት ነው፡፡ በስርዓተ ትምህርቱና በፈተናው መካከል እና ስለዚህ ሙሉ በሙሉ መሰረት የሚያደርገው እንትኑን ነው የምናዘጋጀው ብሉ ፕሪንት (blueprint) ነው ያንን መሰረት አድርጎ ነው ከዚያ ውጪ እንዳይሆን ነው ጥረት የምናደርገው ከስርዓተ ትምህርቱ ውጪ እንዳይሆን ስለዚህ በሁለቱ መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለ ማለት ነው፡፡

8. ፈተናውን የሚያዘጋጁት ባለሙያዎች የሚመረጡባቸው መስፈርቶች ምንድን ናቸው? ለአዘጋጆቹ የሚሰጥ የተለየ ስልጠና አለ? አዘጋጆቹ በየዓመቱ ይቀያየራሉ? ወይስ ቋሚ ናቸው? ለምን?

አዎ እንግዲህ ይህኛው ምናልባት እንትን ነው፡፡ በፈተና ዝግጅት ልምድ ያላቸው በመምህርነት ሙያ ላይ ያሉ እነዚህ ናቸው እንዲሳተፉ የሚደረገው እና ሁልጊዜ ከዝግጅት በፊት አጠቃላይ ስልጠና ይሰጣል፡፡ ወደ ዝግጅት ከመግባታቸው በፊት አረንቴሽን (orientation) በሚገባ ይሰጣል፡፡ ምን ምን እንትን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው የጥያቄዎችን አዘገጃጀት በተመለከተ ስለምርጫው ስለጥያቄው ስለራሱ ስለ ስቲሞቹ እንደዚህ አዘገጃጀት ብዙ ብዙ ነገሮችን አይተው ማዘጋጀት እንዳለባቸው የተለያዩ biased አይነት ሁኔታዎች እንዳይከሰቱ ማድርግ ስላለባቸው አሬንቴሽን ይሰጣቸዋል፡፡

9. ፈተናው የሚሰጥበት ዓላማ/ዓላማዎች ምንድነው? ምንድን ናቸው? ችሎታ/ ብቃት ለመመዘን?

ተማሪዎች በስርዓተ ትምህርቱ አማካኝነት የተሰጣቸው ትምህርት አለ እና ያንን ምን ያህል አውቀዋል የሚለውን ለመመዘን ነው፡፡ እንጂ ተማሪዎችን እርስበርስ ለማወዳደር እከሌ ጎበዝ ነው እከሌ ሰነፍ ነው እንደዚህ የሚለውን ነገር አይደለም፡፡ በሚገባ ተከታትለው ጨብጠዋል ወይም አልጨበጡም ነው እርስ በእርስ ማወዳደር አይደለም እና እከሌ ጎበዝ፣ እከሌ ሰነፍ እከሌ ደግሞ መካከለኛ እውቀት ነው ያለው ከሚል አንፃር አይደለም እና በዙሪያ በቀረበው ለምሳሌ በአንድ ጥያቄ ላይ ሁሉም ተማሪ እንትን ሊመልሰው ይችላል፡፡ ያ ማለት እነዚያ ተማሪዎች ሊመልሰው ይችላል ያማለት በሚገባ እነዚያ ተማሪዎች ያን ይዘት ተረድተውታል ማለት ነው፡፡

10. የማጠናቀቂያ ፈተናው በመማር ማስተማሩ ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት የሚታወቁባቸው / የሚረጋገጡባቸው መንገዶች ካሉ ቢያስረዱኝ?

የለም፣ እንደዚያ የተደረገ እንትን የለም ምናልባት የምናገኘው ምን ያህል ጥያቄዎች እንትን ፈተናው ከተማሪው አንፃር ፈተናው ምን እንትኖች አሉበት/ ችግሮች አሉበት የሚል አይነት እንደሁ በእንትን ምንድነው የሚደረገው አንድ እንትናችን ፈተናው ESLCE ሲካሄድ ማለት በዚያ ጊዜ የሚበተን ወረቀት አለ አብሮ ከፈታኞቹ ጋር የሚላክ እሱ ብዙ ነገሮችን ያካተተ ነው ፩ኛው ፈተናዎችን በተመለከተ ያላቸውን አስተያየት በዚያ በፈተና ስራ ላይ የሚሰማሩ ሱፐርቫይዘሮች ፈታኞች እንትን እንዲያደርጉ አስተያየት እንዲሰጡበት ማለት ነው እና በዚያ አጋጣሚ የአማርኛ ፈተናውን ያዩ ምክንያቱም የተለያዩ ሰዎች ናቸው በየፈተና ጣቢያው የሚገኙት እና እነሱ የየራሳቸው አስተያየት ምልከታ ይሰጣሉ፡፡ እንትን አይደለም የሆነ ጊዜ ሰጥተው አይደለም፣ በወፍ በረር አይነት ነገር ነው፡፡ እንትን የሚያደርጉት አስተያየት የሚሰጡት እና አልፎአልፎ የምናገኘው እንትን አለ፡፡ ለምሳሌ ፓሴጁ/ ክብዱል ምንባቡ ማለት ነው አጥሯል፣ ረዝሟል የሚል አይነት ነገር አስተያየቶች ይመጣሉ እና ይህ ለእኛ ትንሽ የሆነ የሚሰጠን እንትን አለ፡፡

ከዚያ በተረፈ አግሬሲቭሊ (aggressively) ይህን በተመለከተ የሄድንበት ነገር የለም፡፡ ወደፊት ግን የሚታሰብ ነገር አለ ይህን በተመለከተ ምናልባት ተማሪውን በማሳተፍ ሊሆን ይችላል፡፡ የተፈተነውን ማለት ነው ደግሞ መምህራን ጠለቅ ባለ ሁኔታ ስለፈተናው አስተያየት እንዲሰጡ እንዲህ እንዲህ አይነት የሚታሰብ ነገር አለ ምናልባት ጥናትም ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚያ በተረፈ እኛ በየጊዜው የምናካሂደው የitem analysis በእያንዳንዱ ፈተና ላይ የጥያቄውን የክብደት ደረጃ ወይም በተመሪዎች መካከል ያለውን የመለየት አቅም በተመለከተ በየጊዜው እንትን ይደረጋል እና ለእኛ እንትን ሰጠናል፡፡ ሂንት ይሰጠናል ለቀጣይ እንትኖች ፈተናዎች እንጂ በተለይ እነዚህ መምህራንና ተማሪዎች ዋና እነሱ ናቸው እና እነሱን ባካተተ ወደፊት ካልሆነ በስተቀር ይህን ያህል ቅድም ከጠቀስኩት አስተያየት የማግኛ መንገድ ውጭ ሌላ እንትን የለም፡፡ በዚያች ተመስርተን አልፎ አልፎ የምናካሂዳቸው እንትኖች አሉ፡፡ በተለያየ አካባቢ ተመሳሳይ ነገር አይነት አስተያየት ሲመጣ በሪፖርቱ ማጠቃለያ የፈተና አካሄድ መሰረት ከዚያ ተነስተን የምናሻሽላቸው ነገሮች አሉ፡፡

11. ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ በኤጀንሲው የሚዘጋጁ ፈተናዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚያሳድሯቸውን ተፅዕኖዎች አዎንታዊነት ከፍ ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶችና በጥረቶቹ በተግባር የታዩ መሻሻሎች ካሉ ቢገልፁልኝ?

እሱን በተመለከተ እንግዲህ ያለውን የእኛ ከባለሙያነት አንፃር ምክንያቱም እኛ ነን ለፈተና አዘጋጆች ኦረንቴሽን የምንሰጠው ተገቢውን ወደ ፈተና ዝግጅት ከመሄዳቸው በፊት መጀመሪያ ሲመረጡ ቅድም እንደተባለው የትምህርት ደረጃቸው የፈተና አዘገጃጀት ችሎታቸው ታይቶ ነው የሚመረጡት ከዚያ በተጨማሪ ግን ኦረንቴሽን እንሰጣቸዋለን፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ማለት ነው፡፡ ለአንድ ቀን ወይም ለግማሽ ቀን ከማዘጋጀት አንፃር ማለት ነው እና እኛም በየጊዜው የራሳችን አቅም ለማሻሻል ጥረት እናደርጋለን፡፡ እና ከዚህ አንፃር በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የባለሙያውን አቅም ለማሻሻል የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ነው፡፡ ስልጠናዎች እንደዚህ እና የፈተናው አዘገጃጀት በመልካም ሁኔታ እንዲሄድ ለማድረግ ማለት ነው፡፡ እና በዚሁ መሰረት ስልጠናዎች እየተሰጡ ነው ስልጠናዎች እየወሰድን ነው፡፡ In General በሆነ ሁኔታ ስነግርህ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በአብዛኛው መምህራን የነበርን ነን ከፈተና አዘገጃጀት አንጻር ያለን እንትን በተወሰኑ ኮርሶች የተገደበና ያው በልምድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከዚያ በተጨማሪ እና ይህን ክፍተት በማየት መስሪያ ቤቱ የተለያዩ ስልጠናዎች እያዘጋጀ እየሰጠ ነው፡፡ እና በዚያ መሰረት የተሻለ አቅም እየተፈጠረ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የረጅም ጊዜ እንትንም እንደዚሁ እየተሰጠ ነው፡፡

ባለሙያዎች እና የእኛ አቅም በዚህ መልኩ የሚዳብር ከሆነ ለፈተና አዘገጃጀቱ ከፈተና አዘጋጆች ጋር ለሚኖረን ግንኙነት የተሻለ አቅም ይፈጥራል፡፡ እና የተሻለ ፈተና እንዲዘጋጅ አስተዋፅኦ

ያደርጋል፡፡ እና ይህንን እያየን ነው፡፡ እና ስለዚህ ቅድም እንደተባለው ደግሞ ያው በየጊዜው የፈተና ትንተና ይካሄዳል፡፡ Item analysis የየአመቱ ፈተና ምን እንደሚመስል የጥያቄዎቹ ድክመትና ጥንካሬ የምንፈትሽበት የItem analysis ይካሄዳል፡፡ እና ያ የItem analysis የሚጠቁመው ነገር ፈተናዎቹ በአብዛኛው ተፈታኞችን በሚገባ የሚለዩ መሆናቸውን በተከታታይ የሚካሄዱ የ Item analysis ውጤቶች ያሳያሉ፡፡ እራሱ ውጤቱ ለምሳሌ የዛሬ ሁለት አመት ወይም የዛሬ ሶስት አመት የተሰጠው ፈተና እና የዛሬ አመት የተሰጠው ፈተና ውጤት በጣም ተቀራራቢ ነው፡፡ እንትኑ ሲታይ እና ይህ ሲታይ ፈተናው ሪሊያብሊቲው ከፍተኛ መሆኑን የሚያሳየው አስተማማኝ ነው፡፡ አስተማማኝ ፈተና እንደሚወጡ ይጠቁመናል፡፡ በተለያየ መልኩ የምናገኘው እንትን የሚያሳየን ውጤት የፈተናዎቹን አስተማማኝነትና አግባብነት ነው፡፡ ነገር ግን የበለጠ ደግሞ የፈተናችን አስተማማኝነትና አግባብነት የበለጠ የተሻሻለ እንዲሆን ደግሞ ቅድም እንዳልኩት በተለያዩ ስልጠናዎች እየታገዘ፣ የተለያዩ ስልጠናዎች እየተሰጡን ነው፡፡ አቅማችን እየዳበረ ነው የምንገኘው፡፡

12. **የፈተናውን ደረጃ ከፍ ለማድረግና የአጠያየቅ ዘዴው ምርጫ ብቻ ከመሆን እንዲወጣ (በጽሑፍ የሚመለሱ ጥያቄዎች የተካተቱበት እንዲሆን እየተዳረጉ ያሉ ጥረቶች ካሉ ቢያስረዱኝ?**

በሀሳብ ደረጃ ነው በሌላ አካባቢ ያለው ኮንሰርን Cncern ከዚህም አካባቢ አለ ይህን በተመለከተ ለምድንነው የጽኑፍ ጥያቄዎች የማይካተቱት የሚለው ከዚህም የሚንሸራሸር ሃሳብ ነው፡ ከላይ አካባቢም የሚንሸራሸር ሃሳብ ነው፡፡ ነገር ግን እንዴት ወደዚያ ይገባ የሚለው ነው Challenging እየሆነ ያለው:: የተማሪው ቁጥር ብዙ ነው፡፡ እና ይህን ለማድረግ ለማረም ከእርማት አንፃር ራሱን የቻለ እንትን(Problem) ነው፡፡ እና ስለዚህ ረጋ ተብሎ የሚታዩ ብዙ ነገሮችን ያካተተ ጉዳይ ነው፡፡ እና ስለዚህ ይህ ነገር ካልታየ በስተቀር ልክ ነው፡፡ ሃሳቡ እንደዚያ መሆን አለበት፡፡ እንደዚያ ካልሆነ አንድ ተማሪ በተለይ በቋንቋ ረገድ በተግባር ያንን ነገር እንትን ካላደረገ የሚገልጸውን ነገር ካልገለጸ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው:: ስለዚህ ከዚህ አንጻር ሃሳቡ እየተንሸራሸረ ነው እንግዲህ ወደፊት ጊዜ የሚያመጣው ነገር ነው የሚሆነው ወደዚያ የሚኬድበት ነገር ሊፈጠር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሃሳቡ አለ፡፡ እና ሃሳቡ በየጊዜው እየተንሸራሸረ፣ እየጎለበተ፣ እየጎለበተ ሲሄድ እና ወደፊት ተግባራዊ የሚሆን ይመስለኛል፡፡

በትምህርት ቤቶች ምዘናዎች ላይ ህግ ቢሆን ክትትል የሚደረግበት የሆነ ለንግግር፣ ለጽሑፍ ይህን ያህል ፐርሰንት የሚል ሥርዓት እንዲዘረጋ ቢደረግስ?

ከታችም ያለው ችግር የተማሪዎች ብዛት፣ የክፍለ ጊዜው ማነስ ለመተግበር ያስቸግራቸዋል፡፡ አርሞ ግብረ-መልስ ለመስጠት ስለሚቸገሩም ነው፡፡ የግድ የክፍለ ጊዜ መጨመር ብቻ አይደለም የሚገባባቸው ክፍሎች ቢቀነሱለት 10 ክፍል ክሂልና ብቻ የሚገባ ቢሆን የተሻለ ጊዜ ሊያገኝና እየጻፈ ነበር መልስ ለመስጠት ጊዜ ሊያገኝ ይችላል፡፡

13. **የቋንቋ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ችግር እንዴት ነው ሊፈታ የሚችለው?**

ምክንያቱ ከላይ የተገለፀው ነው፡፡ ከተማሪው ቁጥር አንፃር ከመሳሰሉት ነው፡፡ ፕሮብሌሙ ምርጫ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ እንግዲህ ወደፊት ቀስ በቀስ ወደዚያ ሊገባ ይችላል፡፡ ምክንያቱም እየተነሳ ነው፡፡ በበላይ አካባቢም ግንዛቤ እያገኘ ነው ለምንድነው ፈተናዎቻችን እነዚህን ነገሮች የማያካትቱት የሚል ነገር እየተነሳ ነው፡፡ ለምን መሰለህ ከተማሪው ቁጥር አንፃር ሌሎችንም ግምት ውስጥ አስገብቶ ነው ወደዚህ መግባት የሚቻለው በአንዴ ዝም ብለህ የምትገባበት አይደለም ብዙ የምታስተካክላቸው ነገሮች አሉ፡፡ ወደዚህ ውስጥ ለመግባት ከተማሪው ቁጥር አንፃር እንጂ ሀሳቡ በጣም እንትን እያለ እየመጣ ነው በተለይ ከላይ አካባቢ ለምንድነው እንደዚህ አይነት ያሉ ጥያቄዎች የማይካተቱት የሚል ማለት ነው፡፡ እና ሁላችንም ጋር ያለ ግንዛቤ ይህ ነው፡፡ አሁን ቋንቋ ላይ የግድ እነዚህ በተለይ ንግግርና ማዳመጥ still አሁን እነሱም አሁን እነዚህ open ended የሆኑ ጥያቄዎች ይግቡ ብትል መጀመሪያ አሁን ልታደርግ የምትችለው ምንድነው ጽህፈት

ነው፡፡እንጂ የንግግርና የእንትንን እሱ ራሱን የቻለ የሚጠይቀው ነገሮች አሉ፡፡ ያን ለማድረግ ደግሞ ይይዘናል አሁን ያለንበት ደረጃ በጣም እንትን ያደርጋል፤ ይይዘናል ምናልባት ከፅኑፍ ጋር የተያያዙት ናቸው፡፡ እና ግን ሀሰቡ በጣም እንትን እያለ ስለሆነ ወደዚያ የሚካሄድበት ሁኔታ በጣም የሚቀርብ ይመስለኛል፡፡ ተስፋ ያለው ነው፡፡

14. ፈተናው ሲዘጋጅ ተማሪዎች የተማሩት ሁሉ መካተቱ እንዴት ይረጋገጣል?

ያው ቅድም እንደጠቀስነው ነው፡፡ ዋና እንትናችን ስርዓተ ትምህርቱ ነው፡፡ Blue print ሲዘጋጅ በዚያ መሰረት ነው የሚዘጋጀው እና እያንዳንዱ እንትን ይዘት ክፍለ ጊዜ period allotment የተሰጠው ክፍለ ጊዜ period allotment አለው እና ከዚያ አንፃር ያን መሰረት አድርገን ነው ጥያቄውን የምናወጣው/ የምናዘጋጀው እና በተቻለ አቅም ሊለኩ የሚችሉ ይዘቶች ወይም ሊለኩ የሚችሉ የትምህርት አይነቱ ዓላማዎች በፈተናው ውስጥ እንዲካተቱ ነው የምናደርገው እና ስለዚህ ሰፊ እንትን ነው ያለው፡፡

15. ተማሪዎች በፈተናው ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ምን ይጠበቅባቸዋል?

አዎ ቅድም ተጠቅሷል፡፡ ቅድም እንደተጠቀሰው ምንድነው ብዙው ተማሪ ዘንድ ያለው ግንዛቤ አማርኛ ስለሚናገሩት ቋንቋውን ማለት እንችለዋለን ምንም አያቅተንም የሚል ነገር ነው ያለው ከዚህ አንፃር ብዙም ትኩረት አይሰጡትም፡፡ የነበረው ትሬንድ እንደዚያ ነው፡፡ እና ያንን የሚሰብር ይመስለኛል የአሁኑ የጥያቄ አዘገጃጀቱ የግድ አንድ ተማሪ በአማርኛ ጥሩ ውጤት ማምጣት ከፈለገ ክፍል ውስጥ ገብቶ በደንብ መከታተል አለበት፡፡ የስርዓተ ትምህርቱን መጻጎፍት በሚከባ መከታተል አለበት እና እንደዚህ እና ይህን ያላደረገ ተማሪ ጥሩ ውጤት ማምጣት አይችልም፡፡ እነዚህን ነገሮች ማድረግ የቻለ በደንብ የተከታተለ መጻህፍቱን በሚገባ የሚከታተል የሚያነብ ከሆነ ኤክሰርሳይሶችን የተለያዩ መለማመጃዎችን የሚሰሩ ተማሪ ከሆነ ጥሩ ውጤት ያመጣል፡፡

16. የማጠናቀቂያ ፈተናውን ዋና ዋና ጠንካራና ደካማ ጎኖች ሊባሉ የሚችሉ ገጽታዎች ካሉት እባክዎ ይዘርዝሩልኝ?

ጠንካራ ጎኑ ምንድነው በሥርዓተ ትምህርቱ የተሸፈኑ ይዘቶች አካቶ መቅረቡ ዓላማዎችን ለመለካት መሞከሩ እና ተማሪዎችም በሚገባ ትምህርቱን በሚገባ ከተከታተሉ ውጤት ማምጣት እንደሚችሉ የሚያስገነዝብ ሆኖ መዘጋጀቱ ይህ እንደ ጠንካራ ጎን ሊወሰድ ይችላል፡፡ መምህራንም እንደዚሁ፣ መምህራንም በሚገባ ካስተማሩ በሚገባ ባስተምር በተማሪው ዘንድ ከውጤት አንፃር ለውጥ ሊመጣ ይችላል ብለው በሚገባ እንዲያስተምሩ ያስገድዳቸዋል ምክንያቱም ፈተናው ከተለያየ እንትን ነው የሚመጣው ሁሉንም የክሂል ዘርፎች በተቻለ አቅም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እያንዳንዱ ክሂልና የእውቀት ዘርፍ እንዲሸፈን ነው የሚደረገው ስለዚህ በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በየዓመቱ እንዲሸፈኑ የሚጠበቁ የትምህርት ይዘቶች እንዲሸፍኑ ያስገድዳቸዋል እና ይህ ጠንካራ ጎኑ ነው ማለት ነው፡፡ ደካማ ጎኑ ቅድም ያልነው ሁሉንም ይዘቶች ሁሉንም የክሂል ዘርፎች በሚገባ መልኩ የሚለካ ፈተና አይደለም የሚለኩ ጥያቄዎችን ፈተናው አካቷል ለማለት አንችልም ለምሳሌ የማዳመጥ የንግግርና የፅኁፈት ክሂሎችን ማለት ነው እና እነዚህ እንግዲህ ክፍት የሆኑ ጥያቄዎች ተማሪው እንዲፅፍ ወይም እንዲናገር ወይም ያዳመጠውን መረዳቱን የሚጠይቁ ጥያቄዎች አለመካተታቸው የፈተናውን አሉታዊነት/ወይም ደካማ ጎን የሚያሳይ ነው፡፡

በተዘዋዋሪ እንደሚፈተኑ ሲያስረዱ ደግሞ እንዲህ ብለዋል፡፡ በተቻለ አቅም ስለድርሰት ካነሳን ከፅኁፈት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚያ ውስጥ የእውቀት ዶሜኑ እንትን ሊያደርግ ይችላል፡፡ ትግበራ ነው? Comprehension ነው፤ እውቀት ነው? ወዘተ የሚለው እንትን ሊል ይችላል ግን ጽህፈት ነው፡፡ ከጽህፈት ጋር የምታነሳው ጽህፈት ውስጥ የሚጠቃለል ነው፡፡ ስለዚህ ጽኁፈትን በቀጥታ አይፈተኑም ግን በተዘዋዋሪ መንገድ ይጠየቃሉ፡፡ ለምሳሌ አሁን ደብዳቤ መፃፉ ነው ዋናው እንትን የሚደረገው ግን ያንን ማድረግ ስለማይቻል በተዘዋዋሪ ቅርጹን ምናምን ሲባል ያን ያህል ተማሪ የሚጽፍ ቢሆን እነዚህን ነገሮች ያካተተ መሆኑን ይረዳል፡፡ ስለህይወት ታሪክ ብንጠይቀው እንደዚያ ነው፤ ስለ ቃለ ጉባኤ ከሌሎች ፅኁፎች ጋር እያነፃፀረ አይነት ጥያቄዎች ወይም ቃለጉባኤ

ምንድንነው የሚያካትታቸው ነገሮች? አይነት ጥያቄ ቢቀርቡ ያው ስለ ቃለጉባኤ ግንባቤ ይኖረዋል ማለት ነው እና የሚጽፍ ቢሆን ቅርፁን ጠብቆ ሊፅፍ ይችላል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ንግግር፣ ማዳመጥና ጽህፈት በቀጥታ አይኖሩም እንጂ በተዘዋዋሪ አሉ፡፡ እና እንደዚያ ስለሆነ የፅህፈት እንትኖች ወይም የንግግር እንትኖች ተሸፍነዋል ማለት ይቻላል፡፡ አሁን ለምሳሌ ስለክርክር ብታነሳ አንድ ተከራካሪ ለክርክር የሚሳተፍ ወይም የክርክር አዳማጭ/ ተከራካሪ ምንድነው ማድረግ ያለበት? የሚል አይነት ከዚያ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ቢቀርቡ እነዚህን ነገሮች ተማሪው ተገንዝቧል ማለት ነው፡፡ እና ወደፊት ተከራካሪ ቢሆን እነዚያን ነገሮች ጠብቆ ነው ተራ መጠበቅ እንዳለበት insult ማድረግ እንደሌለበት እንዲህ እንዲህ አይነት ነገሮችን የሚያውቅ ከሆነ ከሞላ ጎደል ተከራካሪ መሆን ይችላል፡፡ እና እንዲህ እንዲህ አድርገን ለመሸፈን ነው እየተደረገ ያለው፡፡ እንደ ድክመት የተነሳበት ምክንያት በተግባር ካላሳየ በስተቀር ደብዳቤ ፅፎ ካላሳየ አንድ ሪዛልቱን ድርሰትም እንደዚሁ ፅፎ ግን ከሞላ ጎደል ስዕላዊ፣ አመዛዛኝ ወዘተ የድርሰት አይነቶችን መለየት መቻሉ ራሱ አንድ እንትን ነው አንድ ደረጃ ነው፡፡

17. ማጠቃለያና መደምደሚያ

እስካሁን ከተነጋገርንባቸው የተለየ/ተጨማሪ ሀሳብ ይኖርዎታል?

ይህ እንግዲህ ዋና እንትኑ ምንድነው ቅድም እንደተጠቀሰው ከታች ጀምሮ ፈተናው ብቻ ሳይሆን ታች ያለው የምዘና እንትን በየክፍል ደረጃው በክፍል ውስጥ መምህራን ከምዘና ጋር ያላቸው ቁርኝት ስለምዘና ያላቸው እውቀት ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡ እና ከዚያ ላይም ሰፊ ስራ ሊሰራ ይገባዋል፡፡ በተለይ አሁን ያለው የብሔራዊ ፈተናው እንዲዚያ አይነት ችግሮች አሉበት open ended ጥያቄዎችን አለማውጣቱ ማለት ነው ይህ ደግሞ የተማሪውን በነዚያ እንትኖች አንፃር ምን ያህል እንትን ለመለካት ያስቸግራል፡፡ ግን ይህን መምህራኑ በሚያደርጉት ነገር ማስተካከል ይቻላል፡፡ ለጊዜው ፈተናው ወደዚያ እስከሚሄድ ድረስ እና በተቻለ አቅም መምህራን ምዘናዎቻቸውን እነዚህን ነገሮች እያካተቱ እንደሆኑ እንዲጽፉ ወይም እንዲናገሩ በተለያዩ አክቲቪቲዎችም ሊሆን ይችላል፡፡

በየጊዜው በሚሰጧቸው ኮንቲኒየስ አሰስመንቶች ሊሆን ይችላል፡፡ እንደዚያ እንደዚያ እያደረጉ በማጠቃለያ ፈተናዎቻቸው ሊሆን ይችላል እና ከዚያ እንደዚህ የሚደረግ ከሆነ ምናልባት ይህን ችግር የፈተናውን ድክመት በዚህ መልኩ ፈተናው ወደዚያ እስከሚሄድ ድረስ እንደዚህ አድርጎ ማቃለል የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ ከዚያ አካባቢ እንዲህ ያለ ስራ መሰራት አለበት፡፡ ከእኛ እንደዚሁ በተገኘው አጋጣሚ የሚመለከታቸው እንትኖች አካላት መምህራን እንደዚያ እንዲሄዱ የሚደረጉ ጥረቶች ያሉ ይመስለኛል፡፡ በተለያየ ደረጃ ከታችኛው ክፍል ጀምሮ ከcontinous assessment ጋር ከምን ጋር እንደዚህ በተያያዘ የሚሰጡ ስልጠናዎች አሉ፡፡ የተለያዩ ሞጁሎች ምንም እንደዚህ ድክመቶችም ይሰራጫሉ፡፡ የመምህራንን ብቃት እንትን ለማለት ማለት ነው፡፡ ለመለካት ከምዘና አንፃር ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶች አሉ፡፡ እና እነዚህ ጥረቶች ይበልጥ ተጠናክረው መቀጠላቸው በተለይ ከቋንቋ ትምህርት አንጻር፣ በተለይ ደግሞ ከአማርኛ፣ እንግሊዝኛና አማርኛን ስታወዳድር ለእንግሊዝኛ የሚሰጠው ትኩረት ራሱ የሚመደብለት period ማለት ነው እርግጥ የራሱ የሆነ እንትን ሊኖረው ይችላል መነሻ ምክንያት ሊኖረው ይችላል፡፡ እና ከዚያ ከዚያ አንፃር ትልቁን ሚና መምህራን መጫወት የሚችሉ ይመስለኛል፡፡ እና ወደዚያ ነው በተለይ መኬድ ያለበት የመምህራንን ብቃት ከማሳደግ አንጻር ፈተናዎቻቸው እንዲህ እንዲሆኑ የተለያዩ የጥያቄ አይነቶችን በማካተት ማለት ነው የሚያቀርቡ ስልጠናዎች፣ ማኑዋሎች እንደዚህ በክልል ደረጃም በማእከል ደረጃም እየተዘጋጁ እንዲደርሱ በተለያየ ጊዜ ስልጠናዎች እንዲሰጡ ቢደረግ ያለውን ክፍተት የፈተናውን ማለት ነው በዚህ መሸፈን ይችላል፡፡

አባሪ 14፤ በቡድን ተኮር ውይይቶች የተሳተፉ መምህራን ምላሾች ናሙና

ከትምህርት ቤት አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከአምስት የአማርኛ መምህራን ጋር የተካሄደ የቡድን ተኮር ውይይት

ጥያቄ 1ን፤ በማስተማር ቅድመ ዝግጅትና በማስተማር ተግባራቸው ላይ የሚያጋጥማቸው አጠቃላይ ችግሮች በተመለከተ በተወያዮቹ የተሰጡ አስተያየቶች

መምህር$_{21}$፡ እኔ ችግር ነው ብዬ የማስበው አንድ ተማሪ የመማር ፍላጎት የለውም የሚል ነው፡፡ የሆነ ክፍል ውስጥ ገብተህ አንተ ተዘጋጅተህ ምን ብለህ እንትን ስትል ተማሪው ቋንቋዬ ነው እ-አውቀዋለሁ ቀላል ነው ከሚል አንፃር ይሁን እንትን የለም፤ የተማሪው የመማር ፍላጎት የለም፡፡ እና አንተ ተዘጋጅተህ ገብተህ በሞራል እንትን እያልክ ተማሪው ፍላጎት ሲያጣ ያንተ የማስተማር ፍላጎትህ ይወርዳል ያ አንድ ችግር ነው ብዬ ነው የማስበው፡፡

ሌላው አሁን አሁን በተለይ ለቋንቋ ትምህርት እንትን የለውም ቫሊው እየተሰጠው አይመስለኝም አሁን ለሳይንስ ትምህርቶች የሚል ነገር ነው እንትን ያለው ለቋንቋው ብዙም ይህ ቱቶሪያል፣ እ ... የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ ከላይም ይመስለኛል ፕሮግራም እንኳ ቢውጣ ለሳይንስ ትምህርቶች ነው ቅድሚያ እየተሰጠ ያለው ያም አንድ ችግር እ... ተፅዕኖ ያለው ይመስለኛል፡፡ ልክ እንደለላው ትምህርት በእኩል ደረጃ ተማሪም እኩል ግንዛቤ ኖሮት ቢያልፍ ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ በእኔ ያለው ችግር

አንዳንዴ ደግሞ መጽሐፎች ላይ ግልፅ ያልሆኑ ነገሮች የመምጣት መጽሐፍን ብንይዘው ኑሮ ጋሽ አባይ ልታግዘኝ ትችላለህ የሆነ ... በምናስተምርበት ጊዜ ግልፅ ያልሆኑ ከድሮው ሰዋሰው ጋር የተያያዙ አሁን 10ኛ ክፍል ላይ ከድሮው የተያያዙ ነገሮች ያጋጠሙን ነገሮች አሉ፡፡ የቃላት ርባታ፤ ሳቢ ዘር፣ ጥሬ ዘር፣ ምናምን የሚሉት ነገሮች አሁን እነሱ በምናስተምርበትም፣ በምናዘጋጅበትም ጊዜ እንትን የለም፣ አጋዥ ነገር የለም፡፡ አሁን ሳቢ ዘር ምንድነው፣ ጥሬ ዘር ምንድነው ይህን ርባታውን ተከትለን የምንሄድበት አሁን ዘመናዊ የሆኑ ነገሮች አጋዥ ነገሮች የለም፡፡ እኛ በራሳችን ተነጋግረን እንዴት እንትን እንበለው ብለን መሄድ ነው እነዚህ ነገሮች ያጋጥሙናል፡፡

መምህር$_{22}$፡ እንግዲህ እንደተባለው ከዝግጅት ስንጀምር ተማሪው የመጣበት / የኋላ ታሪኩን ስናየው በቋንቋው ብዙም በሰል ብሎ አይመጣም የሚጠበቅበት ደረጃ ላይ ሆኖ አናገኘውም ዘጠነኛ ክፍል ሲመጣ፡፡ በአንዳንድ ጽንሰ ሃሳቦች ላይ የተዛባ ሃሳብ ይዞ የመምጣት ሁኔታ አለ፡፡

ከዚያም በተጨማሪ ቅድም እንደተነገረው የማጣቀሻ መጻሕፍት እጥረት ለሁለታችንም ለእኛም ለተማሪውም ነው ችግሩ፡፡

ተማሪውም በቂ እንዳይዘጋጅ ያደርገዋል፡፡ እኛም በቂ ዘግጅት አድርገን እንዳንመጣ እንቅፋት ይሆናል፡፡ ስለዚህ የማጣቀሻ መጻሕፍት በተለይም መጽሐፍ ላይ የተጠቀሱት ነገሮች በየትምህርት ቤቶች ቢገኙ... በእያንዳንዱ በእኛ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ያለ ችግር ይመስለኛል ቢኖሩ የተሻለ ይሆናል፡፡

ሌላው በማስተማር ሂደት የሚገጥሙን ችግር የክፍለ ጊዜ ድልድሉ ነው፡፡ የጊዜ ድልድሉ በሳምንት ሁለት ነው የሚለው ግን መጽ□□ □□□□□ ሁለት ክፍለ ጊዜ የሚያውቅ አይደለም፡፡ የሩጫ ሁኔታ ይኖራል፡፡ ስንቋጭ ደግሞ ያው መሸፈን የሚል ግዴታ በሌለ ከእኛ ፍጥነት ጋር እኩል ላይሄዱ ይችላሉ ብዙዎቹ እነዚህ እነዚህ ችግሮች ይገጥማሉ፡፡

አሁን አሁን እንኳን እየተሻሻለ ነው እንጂ በማስተማር ሂደት የምናተኩርባቸው ነጥቦች ብሔራዊ ፈተናዎች ላይ ያለማግኘት ሁኔታ ነበር፡፡ አሁን አሁን በእርግጥ ይህ ችግር እየተቀረፈ ነው፡፡ መማሪያ መጻሕፍቱ ላይ እያተኮሩ ነው አሁን ቀደም ሲል ግን መምህሩም እንደፈለገ ያገኘውን ዋቢ ተጠቅሞ ያስተምራል ተማሪውም ተከተለም አልተከተለም እንደየአቅሙ የፈለገውን ይዘጋጃል፡፡ ዞሮ

ዞሮ ጥያቄና ተጠያቂ ሳይገናኙ ይቀራሉ የሚል ስጋት እንደነበር ነው። በእርግጥ በዚህ ሁለት ሶስት ዓመት ውስጥ አዳዲሶቹ መጻሕፍት ከተዘጋጁ ወዲህ ጥሩ ነው። የዘንድሮውም አሁን እንዳየነው ጥሩ ነው። ስለዚህ እነዚህ እነዚህ ሁኔታዎች ሲስተካከሉ ነው።

ሌላው የተማሪው ዝንባሌ እንደተባለው even 12ኛ ክፍል ላይ ብሔራዊ ፈተና ላይ የለም። ሌሎች ትምህርቶች አሉ። ይህኛው ነን እስከ 12ኛ ክፍል እየተማሩት ነው ብሔራዊ ፈተና ላይ ግን የለም ይህ ትኩረት ደግሞ ተማሪው ወደፊት ምን ያህል በዚህ እጠቀምበታለሁ ከሚል አንጻር የክትትል፣ የፍላጎት ማነስ አንዱ ምክንያት ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። ስለዚህ የሚመለከተው ክፍሎች ትኩረት አድርገው ቢያንስ ቋንቋው ከተሰጠ የሚሰጠው እንደሌሎች ትምህርቶች እስከ 12ኛ ክፍል ነው ከዚያ በኋላ እንደየምርጫው ሊመርጡትም ላይመርጡትም ይችላል። ያ ከሆነ ደግሞ ትኩረት ተሰጥቶት ከክፍለ ጊዜ ድልድል አንፃር ቢሰራ ነው።
በተረፈ ሌሎቹ ደግሞ ይጨምሩበታል።
መምህርት24፡ ዝግጅቱ ላይ እኔ የሚታየኝ እነሱ ከገለፁት እንትን ክሂሎች ላይ እ .. ማዳመጥ፣ መናገር የሚባሉ ነገሮች ብዙ ጊዜ ለማስተማር ለማቀድም ራሱ አስቸጋሪ ነገር ነው። እነሱን ለማስተማርና እቅዱን ለማውጣት ብዙ አጋዥ ነገሮችም አያገኙም አስቸጋሪ ነው።
ብዙ ጊዜ ደግሞ ተማሪዎቻቸውን ማዳመጡን፣ መናገሩን ለምደውታል እንደ ሌሎቹ የምናስይዛቸው አዲስ ነገር የለም። እነዚህን በማስተማር ላይ በትኩረት ብዙም የሚቀጥል ነገር አይደለም። ናሙና የሚሆኑ ነገሮችም አናገኝም። ናሙና ለምሳሌ የተቀዱ ድምፆች፣ ጥሩ ንግግሮች እነዚህ እነዚህ አሁን ተቀርፀው ብናገኝ እነዚህ አጋዥ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ እነዚህ ላይ ችግር አለ።
ክፍለ ጊዜ ላይ የተባለው ነገር ብዙም ባልደግመውም ብዙ ጊዜ ምንድነው የእኛ እንትን ማሚያ ነው እንጂ ታስቦበት የሚደለደል ፕሮግራም አይደለም ፕላዝማ አለ ፕላዝማው በሌለበት ጊዜ ነው የእኛን እንትን የሚሉት ስለዚህ ወደ መጨረሻው ክፍለ ጊዜ ነው የሚመድቡን ወደ መጨረሻው ስለሚመድቡን ተማሪዎች ከተዳከሙ በኋላ ተማሪዎች ክትትላቸው ብዙም አጥጋቢ አይደለም።

መምህርት25፡ እሺ ጥሩ እንግዲህ ዋናው የቋንቋው መሰረታዊ ዓላማ በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መነሻ ነው ተማሪው ጥሩ አድማጭ እንዲሆን አድማጭ ብቻ ሳይሆን ጥሩ አድማጭ እንዲሆን ጥሩ አድማጭ ሆኖ ያዳመጠውን ነገር አመዛዛኝ ቢሆን አስተሳሰብ ወይም ክሪቲክስ በሆነ አገላለፅ ትክክል ነው ትክክል አይደለም እንዲል፣ ሲናገርም ያዳመጠውን ነገር መሰረት አድርጎ እንዲናገር፣ ከዚያም የስነ-ልሳን እውቀቶችን በአግባቡ ለመስራት እንዲችል አሁን እዚህ ላይ እኛ በዚህ መሰረት ለማስተማር ስናስብ ተማሪው ቋንቋውን ከቤተሰብ ስለሚናገረው፣ ተናግሮት ስለሚመጣ እ... የሚያውቀው አርጎ ይገምታል። ወደ ትምህርት ቤት ሲመጣ ቋንቋውን አውቀዋለሁ ብሎ እ አዲስ .. እ የስነ-ልሳን እውቀቶች ካልሆኑ በስተቀር አዳዲስ ነገሮችን ብዙም አያገኝም ያው ማዳመጡንም፣ መናገሩንም ይህን የመሳሰለውን ነገር ከቤተሰብ አውቆት ስለሚመጣ ለምዶት ስለሚመጣ ቀደም ባሉት ክፍሎች አገናዝቦ ስለሚመጣ እዚህ ደረጃ ላይ ብዙም ትኩረት ያለመስጠት ነገር ይታያል። በክፍል ውስጥ እኔ በማስተምርበት ማለት ነው። አንድ ይህ ነው ሁለት የሚሰጡ መልመጃዎች አሉ። መልመጃዎች አሁን ከዚህ ሁለት ሶስት ዓመት ውስጥ የተዘጋጁት መጻሕፍት ጥሩ ናቸው እኔ እንደምገምተው ሊያሰሩ የሚችሉ ናቸው። እንደተባለው ግን መልመጃዎች በጥልቀት እያሰሩ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲሰራና በእነዚያ ውስጥ አልፎ ክሂሉን አዳብሮ እንዲሄድ ጊዜው በጣም ውስን ነው። አጭር ነው። ሁለት ክፍለ ጊዜ ብቻ ነው በሳምንት የሚሰጠው ስለዚህ ትምህርቱን ራስ በኖነ መንገድ ወይም በጥልቀት ሳይሆን ወይም በላዩ ዝም ብለን ነካ አድርገነው ነው የምናልፍ አብዛኛዎቻችን ጥልቀት አንሰጠውም። ጥልቀት ካልተሰጠው ደግሞ የስርዓቱ ጉዳይ ትንሽ እ... አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል። አሁን ተማሪዎች በዚህ ችግር ውስጥ ነው ያሉት እንጂ በመጽሐፉ ላይ አሁን ያለው ዝግጅት ጥሩ ይመስለኛል። መምህራንም ዝግጅታቸውን መሰረት አድርገው ነው የሚያስተምሩት ።።የምናስተምር በእቅድ መሰረት ነው የምናስተምረው።። እናቅዳለን የምናቅደ በእነዚህ በአራቱ

የቋንቋ ክሂሎትና በስነ-ልሳን ክሂሎትም ጭምር ነው። እነሱን መሰረት አድርገንም የምናስተምረው ነገር ግን ቅድም እንዳልኩት አንዳንድ ቦታ ላይ የተወሰኑ የስነ-ልሳን ክበድ የሚሉ ነገሮች አሉ። ተማሪዎች ከታች ክፍል ያልተማሯቸው አዳዲስ ነገሮችም ሊያጋጥሟቸው ይችላል፣ እነዚያን በጥልቀት ለማስተማር የጊዜው ትንሽ ሁኔታ እጥረት ይታያል፣ እንጂ ጥሩ ይመስለኛል በመጽሐፉ ደረጃ ማለት ነው።

ሌላው እኛ መምህራንም ብንሆን በአሰለጣጠንም ቢሆን በሜትዶሎጂም ቢሆን በሳይንሱ፣ በቋንቋው ሳይንሶች እውቀትም ቢሆን የተለያየ አለ የተለያየ ልዩነት እንዳለ አያሌው ልዩነት ይታየኛል። ማለት እያንዳንዱ መምህር በዩኒቨርሲቲም ደረጃም ቢሆን የሚያስተምረው ነገር ከሌላው ለየት የሚል ነገርም አለ። ስለዚህ እኔ የተማርኩት ሌላው ከተማሪው በመጠኑ ቢሆን ክፍተት ያለ ይመስለኛል። ስለዚህ መምህራን እኩል የችሎታ ደረጃ የለንም ብዬ አስባለሁ። በእርግጥም እኩል መሆን አስቸጋሪ ነው። አይመጣም። ግን ይህ ልዩነት አለ በ ሜትዶሎጂም እንለያያለን፣ በስነ-ልሳን እውቀታችንም እንለያያለን ያ ራሱ በተማሪዎች መማር ላይ የተወሰነ ልዩነትና ተፅዕኖ ያመጣ ብዬ አስባለሁ።
ሌላው አሁን የተዘጋጀው መጽሐፍ ከጊዜ እጥረት አንፃር ካልሆነ በደንብ ቢሰራበት በበኩሌ የተሻለ ነው ብዬ ነው የማስበው ፈተናም ላይ ያንኑ ነው የሚያመጡት አሁን... እንደ በፊቱ ሌላ ቦታ እንትን አይሉም። ያንኑ በጥልቀት ቢማሩት ያው ራሱ ጥሩ ነው ቅድም አባይ ያለው ነገር አለ ፈተና ወደ ላይም ዘልቆ ስለማይሄድ ትምህርቱ የመሰልቸት ሁኔታ አለ እነዚህ በበኩሌ የሚታዩ ነገሮች ናቸው ብዬ አስባለሁ።
መምህርት[23]፡ በተለይ ጽሕፈትን ግብረ መልስ ለመስጠት ለማስተማር ከተማሪው ቁጥር አንፃር በጣም አስቸጋሪ ነው። ድርሰት መጻፉ፣ አንቀፅ ሲፅፉ፣ ለልጆቹ ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው ነገር ግን የተማሪዎች ቁጥር ከክፍል ውስጥ በርከት ያለ በመሆኑ የተወሰኑ ተማሪዎችን አይተን የሌሎችን ማረም እንቸገራለን። ስለዚህ ክሂል ለማዳበር ላይ ችግር አለ።

2. የማጠናቀቂያ ፈተናው በማስተማር ቅድመ ዝግጅታቸው እና በማስተማር ተግባራቸው ላይ የሚያሳድረውን የተፅዕኖ ደረጃ ምን ያህል እንደሚገነዘቡት ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ (አዎንታዊ ተፅዕኖ) አሉታዊ ተፅዕኖ ወይስ ምንም ተፅዕኖ የለውም?
2.1. የዓመታዊና ዕለታዊ እቅድ አዘገጃጀት ላይ

መምህርት[21]፡ ዓመታዊና ዕለታዊ ትምህርት ዝግጅት በተመለከተ አንድ መምህር ሲያቅድ ፈተናውን እያሰበ ነው። ጊዜ ያስፈልጋቸዋል፣ እቅድ በምናቅድበት ጊዜ ይህ ጊዜ ያስፈልገዋል የምንለውን ሰፊ ጊዜ እንሰጠዋለን፣ ለማስተማር የሚወስደው ጊዜ አለ። በዚያ ስር ይኖራሉ የሚባሉ ይዘቶች አሉ። እና እነዚያ ይዘቶች ደግሞ ምን ያህል አስፈላጊነት አላቸው። እኔ አሁን ስናስተምር ብዙ ጊዜ ለማትሪክ እና 10ኛ ክፍል ላይ ከሆነ፣ ሳስተምር ይህ ማዳመጥን እና የሚጽፉት ነገር ላይ ትኩረት አላደርግም። 10ኛ ክፍል ላይ ከሆነ ምክንያቱም ይህን አዳምጡ፣ ይህን ይህን ፃፉ ተብሎ ፈተና ላይ ይመጣል ብዬ ስለማላስብ አይ በቃ ይህ እንደዚህ ነውና በማቅድበት ጊዜ ፈተና ይሆናል ተብሎ የሚታሰበውን በዚያ መሰረት አንድ መጽሐፍን መሰረት አድርገህ ነው። መፅሐፍን እሱን መሰረት አድርገን ግን ሰፊ ጊዜ የሚፈልገውን ሰፊ ጊዜ እንሰጠዋለን፣ አይ እዚህ ላይ እንኳ እንትን ባልል/ም ብዙም ነገር የለውም የምንለውን ጠባብ ጊዜ እየተሰጠው ይሄዳል በዛ መልኩ ነው የምናቅደው፣ ያው ተፅዕኖ አለው ብዬ ነው የማስበው።

እለታዊ እቅዳችሁስ ላይ?
ዕለታዊም ቢሆን የምናስተምረው ያው ፈተና ጋር የተያያዘ ነው ብለህ የምታስበውን ነው ይጠቅማቸዋል ብለህ የምታስበው ነው ጊዜም ስለሌለው አሁን እኔ ሳስተምር ጊዜም ስለሌለኝ ሁለት ክፍለ ጊዜ ነው የተሰጠው ይህን ይህን እ- እዚህ ላይ ጊዜ ባጠፋ አንድ ላልሸፍነው እችላለሁ የሚለው

ነገር አለ ሁለት ላይጠቅማቸው እ ለፈተናው አጋዥ ላይሆን ይችላል የሚለው ነገር አለ በዚያ መልኩ ነው፡፡

የነሱ ፍላጎትስ ምንድነው? የተማሪዎች?

መምህርት$_{21}$፡ አዎ! አይ ይህን እንለፈው ይላሉ፣ ስናስተምር ይህን ይህን ለምን አታልፈውም እንዲያውም አንዴ መልመጃውን በኋላ እንስራ ዝም ብለሽ የሚጠቅመውን ብቻ ዝም ብለሽ አስተምሪን አይ መልመጃ መስራት አለበት መልመጃ ካልሰራችሁ ምንም አልተለማመዳችሁም፡፡ መጀመሪያ 10ኛ ክፍል ስገባ ታህሳስ ላይ ነው የጀመርኩት ያጋጠመኝ ነገር መልመጃ አታሰሪን ነው ዝም ብለሽ እያስተማርሽን፣ የሆነ ነገሩን እንትን እያልሽ አጫጭር ማስታወሻ እየሰጠሽን ሂጂ በዚያ መልኩ አይ እንደዚያማ አላደርግም መልመጃ መሰራት አለበት ብለን ከተማሪዎች ጋር ተነጋግረናል፣ መልመጃ መሰራት አለበት... የተማሪው ይመርጣል ነገ ደግሞ ተፅዕኖ ታደርጋለህ አንተ የምታምንበት ነው መስራት ያለብህ ብዬ ነው የማስበው የማምንበትም፡፡

መምህርት$_{22}$፡ እሺ በዚህ በተነሳው ጥያቄ ላይ በመጀመሪያ እንደ እኔ መጽሐፉን ለማስተማር ሲነሳ ሳቅድ □ የመጽሐፍ ምን ያህል ጊዜ ይጨርሳል 10 ወራት አሉን 10ን ተነጋግረናል በጋራ ነው የሚዘጋጀው፣ እንሸነሽነዋለን፣ ከሸነሸንኩ በኋላ እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ምን መሸፈን አለብኝ የሚለውን አውጥቼ ነው የማስተምረው እግረ መንገዱን በማስተምርበት ሰዓት ካለፉት ተሞክሮዎች የሚነሱ አንዳንድ ፅንሰ ሃሳቦች በዚህ ጊዜ እኮ እንደዚህ ነበር የሚለውን እያወሳሁ አፅንኦት እንዲያደርጉበት እንዲከታተሉ አደርጋለሁ ከዚያ ውጪ ግን ፈተናውን አስቤ እኔ አይደለም የማስተምረው፡፡ የወቅቱን ርዕሰ ይዘት አይና በዚያ ርዕስ ላይ ማድረግ የሚገባቸውን ነገር ማወቅ የሚገባቸውን ለማስገንዘብ ነው የምሞክረው፡፡ እንደተባለው በተለይ በንግግርና በማዳመጥ ክሂሎች ላይ ሳምፕል አሳይቶ፣ ናሙና አሳይቶ ከማለፍ ውጪ እነሱም የተወሰነ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ከማድረው ውጪ ጊዜ ብዙ አልወስድም፡፡ ለምን የተሰጠው ክፍለ ጊዜና መፅሐፍ ተመጣጣኝ አይደለም፡፡መፅሐፉ ሰፊ ነው የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በሳምንት ሁለት ነው፡፡

ያ ስንል አሁን እኔ በበኩሌ ዝም ብሎ ፈፅሞ ተፅዕኖ አያደርግም ለማለት አይደለም፡፡ ተፅዕኖውን እያሰብኩ አይደለም የማስተምረው ይዘቱን በማስጨበጥ ሂደት ላይ አተኩራለሁ ከዚያ በኋላ ከዚህ ቀደም በተነሱት ብሔራዊ ፈተናዎች፣ በተነሱት ጥያቄዎች ላይ ለምሳሌ ስርዓተ ነጥብን በተመለከተ በምናስተምርበት ሰዓት በዚህ ወቅት እኮ እንደዚህ ያለ ስርዓተ ነጥብ ተሰጥቶ ተጠይቆ ነበር፡፡ ስለዚህ እናንተም እንደዚህ አይነቶችን ብታተኩሩባቸው ጊዜ ሰጥታችሁ ልታጠኗቸው ይገባል የሚል እንላቸዋለን፡፡ ስነ ቃል በሌሎችም እንጂ ፈተናውን በቀጥታ እያሰብኩ የሚለው እንደ እውነቱ እኔ እንደዚያ አላደርግም፡፡

መምህርት$_{24}$፡ ምናልባት እ ብሔራዊ ፈተናው ቀጥተኛ ተጽዕኖ አለው ከሚለው ላይ እንደጊዜው ይለያያል ብዬ እገምታለሁ፡፡ ለምሳሌ 9ኛ ክፍል የሚያስተምር የ10ኛ ክፍል አስቦ አይሰራውም ዘጠነኛ ክፍል ስታስተምር 10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ይህ ይመጣላችኋል ብለህ አታስተምር፡፡ ግን አላማ ምዘና ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ አንተ አላማህን አሳካህ ማለት ምዘና ላይ ያንን ነገር ተማሪው አሳክቷል ሰራው ማለት ነው፡፡ እና ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ ግን ዘጠነኛ ክፍል እያለህ ይህ እኮ 10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ይመጣል ብለህ ይህ ነገር ታሳቢ አይደረግም እኔ አላደርግም በበኩሌ ሳቅድም ጭምር፣ ሳቅድም ጭምር ለዓመቱ ያለን ነገር minimum learning requirement አለ፡፡ በየጊዜው ከአንድ ተማሪ በዚህ እንትን ላይ ሲደርስ ምን ይጠበቃል የሚል ነገር አለ፣ ያንን ነገር ታሳቢ አድርገን ነው እቅዱን የምናወጣው፡፡ 10ኛ ክፍል ላይ ስንደርስ ግን ትክክል ነው፡፡ 10ኛ ክፍል ስንደርስ ተወዳዳሪ እንዲሆኑልን እንፈልጋለን፣ ተማሪዎቻችን ስለዚህ እዚህ ላይ አትኩሩ፡፡ እዚህ ላይ እንትን በሉ ያንን ተሳቢ ያደርጋል እንጂ እኔ ዘጠነኛ ክፍል ላይ እያለሁ እኔ ይህን እንትን አልለውም፣ አላስበውም፡፡

መምህርት$_{25}$፡ እሺ ጥሩ ነው አሁን እኔ ቅድም ካልኩት ላይ ነው የምነሳው በዚህ ሁለት ሶስት ዓመት ፈተናዎች በመፅሐፉ ላይ መሰረት አድርገው ነው የሚዘጋጁት፡፡ 95፣ 96፣% መቼም በለካው እስከዚያ የሚደርስ ነገር መፅሐፉን መሰረት ያደረገ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ መፅሐፉን ማስተማር ማለት ለፈተና አልሞ ማስተማር ነው ብዬ እገምታለሁ፡፡

ዕቅዱም በዚያ መሰረት ነው የሚታቀደው በመፅሐፉ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ መፅሐፉን በአግባቡ ማስተማር /መተርጎም ማለት ብሔራዊ ፈተናው የሚመጣውም ያው ስለሆነ በደንብ ካወቁት በውጤታቸውም የተሻለ ነገር ሊያገኙ ይችላሉ ብለን ነው የምናስበው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ብሔራዊ ፈተና መቼም ተወዳዳሪነት ነው፡፡ ያስተማርኳቸው ልጆችም በፊትም ጥሩ ውጤት እንዲያመጡልኝ ስለምፈልግ፣ ከእኔ በዚህ ክፍል የተማሩ ልጆች ይህን ያህል A ይህን ያህል B አመጡ የሚባልም የእኔ በተወሰነ ደረጃም ሊሳካ ስለሚችል ትኩረት ሰጥቼም አስተምራለሁ፡፡ በጣም ፈተናን ትኩረት ሰጥቼ ማለት ነው፡፡ መሰረት አድርጌ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ማጣቀሻ መጻሕፍችንም በተጨማሪነት ፈተና ሊያተኩርባቸው ይችላል የምላቸውን አገናዝቤ አስተምራለሁ፡፡ ሰፋ ያለ ምሳሌያዊ ንግግር ሰፋ ያለ ቅኔ፣ ሰፋ ያለ ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ሰፋ ያለ ዘይቤ፣ ከሌሎችም መፅሐፎች ከውጪም በማጣቀስ አስተምራለሁ፡፡ ስለዚህ እኔ በ10ኛ ክፍል ላይ መምህሩ አውቆትም፣ ሳያውቀውም ፈተናው ይገዛዋል ብዬ ነው የማስበው ፈተናው ይገዛዋል፡፡ አውቆትም ሆነ ሳያውቀው ምክንያቱም ፈተናው በመጽሐፉ ላይ ነው መሰረት የሚያደርገው እሱም ያንን መፅሐፍ በደንብ ካስተማረ ዞሮ ዞሮ ያው በፈተናው govern ወይም በፈተናው መስመር በፈተናው ጥሩ ውጤት ያመጡልናል ብሎ ስለሚያስብ ነው ከዚያ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ነጥቦችን መሰረታዊ ነው እቅዱና ፈተናው ተመጣጣኝ ናቸው፣ አብረው የሚሄዱ ናቸው፡፡ ገላጭና ተገላጭ ናቸው፤ መነሻና መድረሻ ናቸው ማለት ነው በእኔ አስተሳሰብ ጨርሻለሁ፡፡

2.2. የማጠናቀቂያ ፈተና በማስተማሪያ ማቴሪያሎች አመራርና (ከመማሪያ መጽሐፎቹ በተጨማሪ ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በተመለከተ ስላላላቸው ግንዛቤ ተወያዮቹ የሰጡት አስተያየት

መምህርት$_{24}$፡ የአማርኛ ሰዋሰው ባዬ ይማም፣ የጌታሁንን የአማርኛ ሰዋሰው የቀዳሚው ትውልድ የአማርኛ ሰዋሰው ቦዝ አንቀፅና የመሳሰሉትን ለማስተማር የመርስኤ ሀዘንንና የተክለማርያም ሩንታዬን ጨምቆ የያዘ ነው፡፡

መምህርት$_{25}$፡ ጥሩ የአማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው? ሰዋሰው አላት ደምሴና አምሳሉ

መምህርት$_{24}$፡ ከ7-10 እና ከ9-10 የሚሉትን መፅሐፎች ለሽያጭ የሚቀርቡ አሉ አይደለ እነሱ ናቸው፡፡

መምህርት$_{21}$፡ ቅድመ ኮሌጅ ከ9-12 የተዘጋጀ ለስነ-ፅሁፍ

መምህር$_{24}$፡ የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን

መምህር$_{25}$፡ ዳኛቸው የስነ-ፅሁፍ መ...

መምህር$_{23}$፡ የብርሃኑ ገበየሁ የአማርኛ ግጥም

መምህር$_{25}$፡ የቀለም ጠብታ ሲል ሁሉም ይህን ለስነ-ፅሁፍ ሳይሆን ለሌላ ዓላማ የሚጠቀሙበት እንደሆነ በመግለፅ ተቃወሙት፡፡

መምህርት$_{24}$፡መኩሪያ ወርቁ፡ የአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የምሳሌያዊ ንግግር ስብስብ ነው፡፡

መምህርት$_{24}$፡ እሳት ወይ አበባ የተለያዩ ልቦለዶችና ግጥሞች አጭር ልቦለዶችን ጨምሮ

ክሂል ላይ

መምህርት$_{22}$፡ የዳኛቸው ወርቁ የፅሁፍ መመሪያ

መምህርት$_{24}$፡ የየሻው ተሰማ ልሳነ ብዕር ከመልሳነ ሰብዕ

መምህርት$_{21}$፡ የሰለሞን አለፎም በሳል ድርሰት

መምህርት$_{23}$፡ ዘይቤ እና የቅኔ አፈታት ዘዴዎች መፅሐፉ ላይ ስለሌሉ ሌሎች ምንጮችን ተጠቅሞ ማስተማር ግድ ነው፡፡ የተለያዩ መጻሕፍትን እንጠቀማለን ዘይቤና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ላይ

መፅሐፍቹም ያዛሉ፡፡ እነዚህን መጽሀፍች ተጠቅመን መልመጃዎችን በማሰራት ተማሪዎችን ለፈተናው ዝግጁ እንዲሆኑ እናደርጋለን፡፡

መምህርት24፡ 1ኛ የመማሪያ መፅሐፉ ጀርባ ላይ አለ፡፡ ምን ምን መጠቀም እንዳለብን የሚገልፅ አለ፡፡ እነዚህ በአብዛኛው ልንጠቀምባቸው የሚገባ ናቸው፡፡ ቃል በቃል አይምጣ እንጂ ስነ-ጽሁፍና ሰዋሰው ያለው በዚያው ነው የሚመጣው ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ያ ስትራክቸር እንዳለ ነው የሚመጣው ያ ከዚያ ላይ ያለው አይምጣ እንጂ ተውሳክ ግሳዊ ሀረግ፣ ቅፅላዊ ሀረግ፣ እነሱ እንዳሉ ነው የሚመጡ፡፡

ስነ-ፅሁፍ ላይም ስንሄድ ዘይቤዎች እነዚያ ጠቅላላ እ... ያሉት ነገሮች ከዚያ ላይ ያገኛቸው ነገሮች ናቸው ተግባራዊ የሚሆኑት ግጥም ላይም ስንሄድ እንደዚያ ያሉ ነገሮች ናቸው ያሉት፡፡

ስለዚህ ስነ-ፅሁፍና እንትን ላይ በትክክለኛ... እንትን አጋዥ ናቸው፡፡ እነዚያን ባናገኝ ኑሮ እኛም እንትናችን ማስፋት አንችልም፡፡ ጥሩ እውቀትም ሰጥተን ያንን ፈተና ውጤታማ አይሆንም ነበር ብዬ ነው የምገምተው፡፡

መምህርት22፡ እ... መጻሕፍት መጠቀሙ እኛን ሙሉ ያደርገናል የምንሰጠው አማራጭ ምሳሌ እናገኛለን፡፡ እ እዚያ ላይ የተነሱት ይዘቶች ጥሩ ጥሩ ምሳሌዎች እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የመጽሐፍ ጥቅም ቀጥተኛ ነው ለማለት አይደለም፡፡ ከመጽሐፉ የተሰጡት የተጀመሩት እ የተሰጡት ምሳሌዎች ወይም አጫጭር ማስታወሻዎች ወይም short notes ተብለው የተሰጡት ነገሮች ይጠባሉ እኛ ግን ያንን አስፍተን ስንገባ ጨምቀንም ለማቅረብ እንችላለን፡ብዙም አንቸገርም ምክንቱም ብዙ እውቀት እናገኛለን ለነሱም ደግሞ ተጨማሪ እነዚህን አንብቡ ለማለት ያስችለናል፡፡ ስለዚህ ዞሮ ዞሮ ያስተማርነው ነገር በተጨባጭ ሲጠየቁ ይመልሳሉ ማለት ነው፤ ከዕውቀት ባሻገር

መምህርት21፡ ብዙም የምጨምረው ነገር የለኝም፡፡ ግን ያው የተለያዩ መጻሕፍትን ማየት እ ከዚያ ከፈተናው ጋር ተያያዥነት አላቸው እነዚህ መጻሕፍት ለምሳሌ የዘሪሁን አስፋው ላይ የወሰድነው/ያቀረብነው ግጥም እንዳለ ተናገር አንተ ሀውልት የሚለው ሞዴል ፈተና ላይ አውጥተነው ነበር እኛ ያው መሰረት አድርገን እናስተምራለን፡፡ ማትሪክ ላይ ያ ግጥም እንዳለ በፈተናነት መጣ፡፡ አይ ሁኔ የተደሰትኩት መደሰት በጣም ነው ደስ ያለኝ ሞዴል ፈተናችን ነበር፤ ማትሪክ ፈተና ላይ ያ ግጥም መጣ፡፡ እና ተያያዥነት አለው ይህ ፈተና የሚያወጣውም አካልም እኮ የትም አያመጣውም፡፡ እነዚህን መጻሕፍት ሰብስቦ ተጠቅሞ ነው እና እነዚያን ማየቱ በጣም ተገቢ ነው አጋዥነትም አለው፡፡

2.3. የክፍል ውስጥ ተግባራት/መልመጃዎች ላይ የማጠናቀቂያ ፈተናው የሚያሳድራቸውን ተፅዕኖ በተመለከተ በተወያዩቹ የተሰጡ አስተያየቶች/ ስለማስጨመር ማስቀነስ አቅሙ፡፡

መምህርት24፡ ብዙ ጊዜ እንትን የምንለው መጽሐፍን መሰረት አድርገን ነው መልመጃ የምንሰራው ቅድም መምህር 25 የተናገረው አንድ ነገር አለ፡፡ ይህ አፍ መፍቻ ቋንቋን ማስተማር በጣም ከባድ ነው መናገርን፣ ማዳመጥን ተምረውት ይመጣሉ፡፡ ከዚህ አሁን መጽሐፉ ላይ እንትን የሚለው ነገር መመሪያውን እንጂ እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉት አይደለም የሚያስተምረው ብዙ ጊዜ አሁን ለምሳሌ ንግግር ቢያስተምር የንግግር ቅድመ ዝግጅት የንግግር አቀራረብ እንደዚህ እንደዚህ አድርጉ እንጂ ያንን ነገር እንደዚህ አድርጎ የሚል ግን ከፈተና አይመጣም፡፡ አሁን ከንግግር ቅድመ ዝግጅት ምንድነው? በንግግር ጊዜ የማያካትተው የትኛው ነው ብሎ ነው የሚያቀርበው እንጂ ንግግር በቀጥታ እንዳያደርጉ/እንዲለማመዱ የሚያበረታታ ፈተናም የለም፡፡ እና ቅድም እንደተባለው በመጽሐፉ ከሚጠበቀው የተሻለ እውቀት አላቸው፡፡ በእርግጥ ስርዓት ጠብቀው ይናገራሉ፣ አዝረክርከው ይናገራሉ፡፡ ያ ሌላ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ግን ቢያንስ ቢያንስ ሃሳባቸውን ይገልፁበታል፡፡ እና አንዳንድ ጊዜ ከጊዜ ጥበት አንጻር እኔ ለራሴ የማደርገው የንግግር ክሂሎች ምናምን ነገሮች ላይ አንዳንድ ጊዜ የprocedure ነገር መስሎ ይታየኛል ያንን የምዘልበት አንዳንድ ነገር አለ፡፡ ሌሎች ነገሮችን ግን መጽሐፍን መሰረት አድርጌ መልመጃዎችን እያሰራሁ ነው የምሄደው ምናልባት እኔ

አላርም ይሆናል እንጂ ደብተራቸውን ተለዋውጠው ያንን ነገር አርማለው መልስ ሰርቼ ያንን ነገር በጋራ እየተወያየንበት እንሰራለን፡፡

መልመጃዎቹን የምንሰራቸው እንደዚህ ነው፡፡ ምናልባት ተጨማሪ መልመጃ ሳይሆን መጽሐፉ ላይ ካሉ መግለጫዎች በጣም ተቀንጭበው የወጡ ናቸው መግለጫዎቹ፣ እነዚያን ነው የምናሰፋቸው እንጂ እኔ በበኩሌ መልመጃ ላይ ከመጽሀፉ ካለው ውጪ የተለየ መልመጃ ብዙ አልሰጥም ድርሰት ለምሳሌ ቢኖር አንዳንድ ጊዜ ላለመገደብ ስል በራሳቸው መንደርደሪያ ዓ. ነገር እንትን ብላችሁ ፃፉ ልል እችላለሁ፡፡ ካልሆነ በስተቀር ብዙ ጊዜ መልመጃ የማሰራቸው መፅሐፉ ላይ ያለው ነው፡፡
ማጠቃለያ ስለዚህ ለማስተማር ሰፋ ያሉ ነገሮች ውስጥ እገባለሁ መልመጃ ለማሰራት ግን በመጽሐፉ ብቻ ነው የምወሰነው በሚሉ የጠያቂው ማጠቃለያ ተስማምተዋል፡፡
መዝለልን በተመለከተ ደግሞ የሚከተለውን ተናግረዋል፡፡
መምህር$_{23}$ በተለይ ክሂል ላይ ዘልያለሁ አንደኛ የጊዜ ችግር ነው ጨርሱ ስንባል፡፡
ጊዜ እጥረትን በተመለከተ መደበኛ ጊዜ የሚሻሙ ሌሎች ምክንያቶችም እንዳሉ ለተጠየቁት .. በጋራና የማስተማሪያ ጊዜ የሚሻማ ሌላ ምክንያት እንዳለ ተናግረዋል ፡፡ በግል ደግሞ፤
መምህርት$_{25}$፡ አለ እንጂ እረ ከባድ ነው እንጂ/ ደራሽ ስብሰባዎች በመኖር ማለት ነው፡፡
መምህርት$_{24}$፡ አዎ ይሄ ብሔር ብሔረሰብ ተብሎ በተለይ የጥዋት ፈረቃ በነበርንበት ጊዜ ይህን ነገርም ማንሳትም አንችልም፡፡
መምህርት$_{25}$፡ ከባድ ነው እንጂ!
መምህርት$_{24}$፡ ምክንያቱም የእኛን ትንሽ ስህተት ነው የሚፈልጉት እኔ አሁን ባጠፋ ይጎላል የነሱ ግን እንትን ቢል ወደ ሌላ ነው የሚቀሩት አሁን ይህን ነገር ባነሳ ቃሉን ራሱ ሀሳቡን ብሰነዝር አንተ ራስህን ይህን ቀዳዳ መቼ ሞልተህ ነው የሚለኝ እንጂ ይህን ነገር ለተማሪዎቹ አስቤ እንደማቀርበው አያስበውም ሰውዬው በእርግጠኝነት፡፡ እና ይህን ተስማምቼ ለመኖር ስል አላነሳውም ማንሳትም አይገባኝም፡፡
ግልጽ እንዲያደርጉ ለተጠየቁት መልስ ሲሰጡ በእቅድ ስለማይያዙ ደራሽ ስብሰባዎች የሰጡት አስተያየት
መምህርት$_{24}$፡ አሁን ዘንድሮ የጥዋት ፈረቃ ላይ የብሔረሰቦች እንትን ተብሎ ጥዋት ጥዋት ብዙ ክፍለ ጊዜ miss ይሆናል፡፡
መምህርት$_{25}$፡ ቢያንስ በ15 ቀን አንድ ቀን ስብሰባ አለ
ጥያቄ በትምህርት ሰዓት?
መምህርት$_{25}$፡ አዎ! በትምህርት ሰዓት የዚህ ትምህርት ቤት ደግሞ ይብሳል::
መምህርት$_{23}$፡ በስድስት ሰኔ የሚጀመረው እኮ (ፈተናው ማለት ነው) ለግምገማ ነው፡፡ ለግምገማ እኛ ልንገመገም!
አወያይ ስለዚህ ባልታሰቡ ምክንያቶች የሚባክኑ ጊዜያት አሉ በሚለው ትስማማላችሁ፡፡
አዎ! በጋራ
መምህርት$_{22}$፡ እንኳን ያልታሰበውና የታሰበውም ክፍለ ጊዜውና መጽሐፉ ተመጣጣኝ አይደለም፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ ተባብሶ በስብሰባዎችና በአንዳንድ የተለዩ አጋጣሚዎች ይባክናሉ፡ አይደለም የእኛ ትምህርት ቤት ቀርቶ በአገር አቀፍ ደረጃም እኮ የሚወርዱ አንዳንድ እንትኖች አሉ፡፡ ሰሞኑን ተረጋግታችሁ ኮርሱን ሸፍኑ ምናምን ሲባል ነበር ቀደም ሲል ሰሞኑን ደግሞ ሌላ መመሪያ መጣ፣ ቶሎ ጨርሱና ስብሰባ ልትገቡ ነው፡፡ ተማሪው ወላጅ ስብሰባ ነው፡፡ ይህ ከላይ የመጣ ነው፡፡
አወያይ ስለዚህ የትምህርት ቤቱ ብቻ ሳይሆን ከላይ የሚመጣም ነው፡፡
አዎ! በጋራ፡፡
መምህርት$_{22}$፡ ያን ግን እንደብክነት አይታይም፡፡ እነሱ አያዩትም
መምህርት$_{24}$፡ ትምህርት ቤቱ ለወቅታዊ ጉዳይ ነው ትኩረት የሚሰጥ፡፡

መምህርት22፡ ስለዚህ ቅድም ያነሳነው ክፍለ ጊዜያትን በአንዳንድ ይዘቶች ላይ ሰፋ ያለ ጊዜ መውሰድና አንዳንድ ጊዜ ጨፍልቆ የማለፍ ሁኔታ የሚኖረው እነዚህም ይገራሃል ወደዚያ... ተረጋግተን... እ

አወያይ አንደኛ የክፍለ ጊዜው ማነስ አለ ሁለተኛ በራሱ በአካባቢ የሚፈጠሩ የጊዜ ብክነቶች አሉ ማለት ነው?

አዎ በጋራ

መምህርት22፡ ሌላው ተደጋግመው የሚመጡ ወይም የሚደገሙ ይዘቶች አሉ፡፡ ቅድም እንደተባለው ተደጋግመው የሚመጡ ከሆኑ እና አንተ በምታስተምርበት ጊዜ የተማሪው ምላሽ የማያረካ ከሆነ የግድ ወጣ እያልክ መልመጃ የማሰራት ሁኔታ ይኖራል፡፡

ለምሳሌ ሰዋሰው ጥሬ ቃል ክፍሎች ላይ የኛም 10ኛም በተደጋጋሚ ይመጣል፡፡

አሁን በዚያ ላይ መልመጃ መጽሐፉ ላይ ያለውን ስትጠይቃቸው በአብዛኛው በእኩል ደረጃ ላይ አታገኛቸውም ወጣ ገባ ነው፡፡ የተወሰኑ አብረውም ይሄዳሉ አብዛኛው ደግሞ ይቀርብሃል በዚህን ጊዜ ተጨማሪ መልመጃ የማሰራት አጋጣሚ ይኖርሃል፡፡ ምክንያቱም በክፍልም ፈተናም ሆነ በብሔራዊ ፈተና ይህ የቋንቋው ዋነኛ ይዘት ስለሆነ የቃል ክፍሎችን ያላወቀ ተማሪ ሰዋሰውን፣ ስነ-ፅሁፍን በአግባቡ ይጠቀማል ማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ እና ተጨማሪ መልመጃዎች በዚያ በዚያ ምክንያት ሊጨመሩ ይችላሉ ነው እንጂ ጊዜ እያለን አይደለም አሁን ከሌላው ጊዜ ቀንሰን ነው፡፡

መምህርት21፡ ተብሏል፡፡ እኔ መፅሀፍ ላይ ብዙ ጊዜ ምን አለ መሰለህ በቃ የጊዜ እጥረት አለ፡፡ አሁን እኔ ተጨማሪ መልመጃ ላሰራ/ለማሰራት ብፈልግ ጊዜ የለኝም፡፡ እና □ መምህር 24 እንዳለው በምሳሌ የሚቀርቡ ነገሮችን አቀርባለሁ፡፡ መፅሀፉ ላይ ያለውን አስተምራለሁ፡፡ ወደ መጨረሻ እንዲያውም ሲቀሩብኝ በጣም እያፈጠንኩ፣ በቃልም ይህን እየሰራን እንሂዳለን መልመጃዎችን፣ እንጂ እኔ ተጨማሪ መልመጃ ሰጥቼም አላውቅ፡፡

2.4. የማስተማሪያ ዘዴዎቻቸው ላይ የማጠናቀቂያ ፈተና ተጽዕኖ በተመለከተ ተወያዮቹ ያላቸው ግንዛቤ

መምህርት21፡ እኔ ብዙ ጊዜ በመጀመሪያ ጥያቄና መልስን እመርጣለሁ፡፡ ተማሪዎችን አንድን ርዕስ ሳቀርብ በመጀመሪያ እጠይቃቸዋለሁ ጥያቄ ከዚያ ከሚሉት ነገር ተነስቼ ገለጻ ያለው ነገር ካለ በገለፃ ነገር አደርገዋለሁ፣ እገልጸዋለሁ እ... የቡድን ስራ እጠቀማለሁ በግል ስራ የሚሰሩትን ነገር እጠቀማለሁ፡፡

መምህርት22፡ እ... እንግዲህ የምናስተምራቸው ርዕሶች ነው የሚወስኑት ይህንን፡፡ ገለፃ በአብዛኛው የምትሸፍንበት ርዕስ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ስለ ድርሰት አይነቶች ለማስተማር ድርሰት ምንድነው? የድርሰት አይነቶች ምንድናቸው? ጥያቄና መልስ እያደረግክ በአብዛኛው እኔ መምህሩ ገለፃውን እያካሄድኩ ምሳሌዎችን እየጻፍኩ እተገብራለሁ፡፡ በሌላ መልክ ለምሳሌ ክርክርን በተመለከተ የሚማሩ ከሆነ ተማሪው ነው አብዛኛውን ጊዜ የሚሸፍነው፡፡ መመሪያዎችን ታሳያቸዋለህ፣ በቡድን ትከፋፍላቸዋለህ፤ ከዚያ በኋላ ራሳቸው እንትን ይላሉ ስለዚህ እንደየርዕሱ በአንድ ክፍለ ጊዜ ሁለትም ሶስትም የምንጠቀምበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ የሚወስነው ያው የትምህርቱ ርዕስ ነው፡፡

አወያይ የዘዴ ምርጫዎቻቸው ከፈተናው ጋር ግንኙነት □ኖረው ይሆን? ,የትምህርቱ ርዕስ አንዱ መሆኑ ተገልፃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሌላ ምን ምክንያት አለ?

መምህርት24፡ ጊዜው ቢጨመር ጥሩ ነው ጊዜውም ራሱ አንዳንድ ጊዜ አጭር ሲሆን በቡድን ከማሰራት ይልቅ በገለጻ ቶሎ ለመጨረስ የሚደረግ ነገር እኔ እንትን አለኝ ከይዙቱ ጋር አብሮ ጊዜውም በአማራጭነት ይጨመር፡፡

መምህርት23፡ በቤት ስራነት ሰጥተን በማሰራት እንዲያቀርቡም እናደርጋለን አንዳንድ ጊዜ ጥያቄ በቤት ስራነት ብዙ ጊዜ የምትሰጧቸው ምን አይነት ስራዎችን ነው?

መምህርት25፡ መልመጃዎችን ነው የምንሰጣቸው፡፡

አወያይ ምን አይነት መልመጃዎችን?
መምህርት$_{25}$፡ ከሁሉም ዓይነት
መምህርት$_{23}$፡ ከቤት ስራም ውጪ አንዳንድ ጊዜ አንብበውት የሚመጡት ካለ አንብበው እንዲመጡ ይደረጋል፡፡
መምህርት$_{25}$፡ ሌላው ደግሞ cooperative learning የሚባል አይተን እኔ እንደዚያ ያለ ስራ እያሰራዋቸው ነው አሁን እኔ cooperative learning ምንድነው? ርዕሱ አንድ ነው፡፡ ለሁሉም እሰጣቸዋለሁ ያንን ርዕስ እያንዳንዱ የየራሱን ሰርቶ ይመጣና በጋራ አንድ አርጎ ያመጣል፡፡ ይህ cooperative learning ነው፡፡ በአንድ ርዕስ ላይ ከፋፍዬ እሰጣቸዋለሁ፡፡ በቡድን ስራ ላይ እኔ ይህን ተጠቅሚያለሁ፡፡
መምህርት$_{23}$፡ ይህን ሁላችንም የምናከናውነው ነው፡፡
ጥያቄ በዘዴዎቻችሁ ላይ ፈተናው የሚፈጥረው ተፅዕኖ አለ ወይ መጥፎ ወይም ጥሩ ተጽዕኖ ሳናስበው ወይም ሆን ብለን
መምህርት$_{25}$፡ positive እ አዎንታዊም አሉታዊም ተፅዕኖ አለው በተለይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው
መምህርት$_{21}$፡ - እያንዳንዱ የማስተማር ዘዴ የራሱ የሆነ አሉታዊም አዎንታዊም እንትን ይኖረዋል፡፡ ገለፃን ጊዜ ለመቆጠብ ትጠቀምበታለህ በቡድን ማሰራት ደግሞ ተማሪዎች ሊጠቀሙበት ሊረዳዱበት ነው ነገር ግን እኔ ብዙ ጊዜ በቡድን ሲሰራቸው ሌላ ወሬ እያወሩ አገኛቸዋለሁ፡ ስትሄድ እየሰራን ነው ምናምን ይሉሃል ወደዚያው ስትዞር ወሬ እያወሩ ታገኛቸዋለህ ይህ ተማሪዎች የግንዛቤ እጥረት ስላለ እኔ የቡድን ስራውን እንግዲያው ክፍል ውስጥ ስሩ ብለን እንትን ከምንላቸው መምህር 25 እንዳለው በቡድን እንዲያሰባስቡ እንዲነጋገሩበት ማድረግ የተሻለ ነገር ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ የቡድን ስራን እኔ በበኩሌ ለወሬ ይገፋፋቸዋል፡፡

ተማሪዎችንም ብዙ ጊዜ በቡድን ስሩ ስትላቸው ይህ አንድ ለአምስት የሚባል አደረጃጀት አለ፡፡ አሁን ያን ደስተኞች አይደሉም፡፡ ምክንያቱም ጫና የተወሰኑ በሚሰሩት ተማሪዎች ላይ ጫና አለ፡፡ እነዚያ እንዲሰሩት ይደረጋል፡፡ በቡድን ሲሰሩ ገልብጠው ነው የሚመጡት ብዙዎች ምንድነው ቢያንስ ሲፅፉ እንኳ የሆነ ነገር እንዲያውቁ ለማድረግ እንጂ የቡድን ስራ ቢጠቀሙበት ያው ሳያንስ እንደማለፍ እንደሚታወቀው ጠቃሚ ነበር፡፡ ግን ክፍል ውስጥ የተማሪው ግንዛቤ የለውም፡፡ አሉታዊ ተፅዕኖው የበለጠ ነው እንደኔ በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ ጫና የሚፈጥር ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ ይህ የማስተማር ዘዴን ከጊዜ አንጻር ብዙ ጊዜ በተለይ ከእነዚህ እንትኖች ላይ ወደገለጻቸው እናመራለን ተማሪዎችን እንጠይቃቸዋለን የተወሰነ ነገር ከዚያ ወደ ገለጻ እንትን እላለሁ ያ ሚትድ ትክክል እንዳልሆነ አውቃለሁ ግን ደግሞ በዚያ መልኩ እጠቀማለሁ፡፡

አወያይ፡ ስለዚህ እናጠቃለው! ለማስተማሪያ ዘዴ ምርጫችን አንደኛ ርዕሰ ጉዳይ 2ኛ ጊዜው 3ኛ እያንዳንዱ የማስተማር ዘዴ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ጎን መሰረት አድርጎ ነው እንጂ ፈተናው በዘዴ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የለውም ብለን እንለፈው ?
መምህርት$_{21}$፡ እዚህ ላይ ምን አለ መለሰህ ፓርሽኑን መሸፈን አለበት ብለህ የምትሄደው እኮ እኔ 10ኛ ክፍል ላይ ሲሆን ነው ዘጠነኛ ክፍል ላይ ይህን አላስብም፡፡ ዘጠነኛ ክፍል ላይ ተማሪዎች ምን ያውቁ የሚለው ነው ዘንድሮ ግን 10ን ስላስተማርኩ በተወሰነ ጊዜ አንዳችን 10 እንይዛለን አንዳችን ዘጠነኛ ወይ ቀላቅለን የምንይዝበት አጋጣሚ አለ እና እንደዚያ ስለሆነ ነው ዘጠነኛ ክፍል ላይ ከሆነ አላስበውም በምን መልኩ እየሸፈንኩት ልሂድ ምን ያወቀ ነው፡፡ 10 ከሆነ ግን እዚህ ላይ ይህን እንደዚህ ባደርገው ይህ ከፈተናው ጋር ይገናኛል ሁሌም ይህ ከፈተናው ጋር እንዲህ እነረዲህ ያለ ግንኙነት አለው እንዲህ እንዲህ ያለ ነገር አለ አንዴ ፈተና ሳላስተምራቸው ማለት አይመጣም ብዬ አይ ይህ አይመጣም ሰንጠረዥ ነገር ነው እና ስታቲስቲክስ መመላት አሁን ልክ ማትሪክ ፈተና ላይ እንትን ቀረበና ስታቲስቲክሱ የዚህ ምን ያክል ነው፣ ምን ያክል ነው፡፡ እኔ አሁን ይህ የሂሳብ ትምህርት ነው፣ ይህ ደግሞ እንደዚህ ይህ ጊዜ ማጥፋት ነው ዘለልኩ በእኔ ግምት ነው ማትሪክ ላይ የጥያቄ መጥቶ አገኘሁት እኔ በጣም ነው የገረመኝ እና በጣም ነው የገረመኝ እና በጣም ቆጨኝ ያን

ባለመስራቴ ይህን ለካ እንዲህ ባደርገው ኑሮ እና 10ኛ ክፍል ላይ ከሆነ የምታስተምር ታስባለህ ፈተናውን የተወሰነ ነገር እያሰብክ ነው፡፡
ጥያቄ ዘዴ ምርጫሽ ላይ?
መምህርት21፡ ያው መግለጽ ካለብኝ እገልፀዋለሁ ያኮ ይጠቅማቸዋል ከሚለው አንጻር ነው፡፡ ገለጻ ላይ ማተኮር ለመሸፈን ነው፡፡ ስለዚህ በዘዴ ላይ የተወሰነ ነገር አለው፡፡
መምህርት23፡ ትምህርቱን የምንሸፍነው በዘዴ ነው የምንሸፍነው ለአጠቃላይ እውቀትና ለፈተና ነው፡፡ ፈተናን ማሰብ የግድ ነው ብያለሁ ቅድም በመጀመሪያ ደረጃ ዓላማውን ተግባራዊ ስናደርግ ዘዴውን እያሰብን ነው፡፡ ዘዴው ደግሞ በቀጥታ ነው እንጂ ለፈተና የሚሆነው በተዘዋዋሪ አይደለም፡፡ በገለጻ ስንገልፅላቸው ሀሳቡን ስናስተላልፍላቸው ተማሪዎቹ ይረዳሉ የተረዱት ነገር በፈተና ይመጣል፡፡ በገለፃ ብንገልፀው ኑሮ ባይረዱት ኖሮ ባይገባቸው ኖሮ ፈተናውን ሊሰሩት አይችሉም፡፡ በቡድን ስራ አሰራራቸው ለሰሩት ነገር ምላሽ ባንሰጣቸው ኖሮ ባያውቁት ኖሮ ፈተናውን መመለስ አይችሉም ነበር፡፡ ስለዚህ ዋና ሊታይ የሚችል ካላማ ጋር ዘዴው ነው፡፡ ዓላማውን ተግባራዊ የምናደርገው ከዘዴው ጋር ስናገኘው ነው እና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዘዴው ከፈተናው ተያያዥነት አለው፡፡

አወያይ፡ ስለዚህ ሁለት አይነት ሃሳብ ነው ያለው ማለት ነው፡፡ አንዱ ፈተናው በዘዴ ምርጫችን ላይ ተፅዕኖ አለው፡፡ ሌላው የለውም የሚል ማለት ነው፡፡
መምህርት24፡ በነገራችን ላይ አሁን ለምሳሌ ያህል ከምናደምጠው ወደ 11% ከምንመለከተው ወደ20% የሚል የፔዳጎጂ አባባል አለ፡፡ ይህን ታሳቢ አድርገን ለፈተናው እንሰራለን ነው፡፡ ገለፃን የምንጠቀምበት ምክንያት ምንድነው ጊዜን ለመሻማት ከቨር ለማድረግ ነው፡፡ ከቨር አድርገን ይዘቱን ሸፈንን ማለት ልጆቹ ለፈተና ተዘጋጁ ማለት ነው ይህን ታሳቢ እናደርጋለን፡፡
መምህርት22፡ መመሪያዎች አሉ ለምሳሌ ስለ ንግግር ያቀራረበና የዝግጅት መመሪያዎች አሉ፡፡ እነዚያን ነገሮች እናሳያቸዋለን ማስታወሻውንም ደብተራቸው ላይ ፅፈው ጊዜ ወስደው ስለሚያነቡ እንዲያተኩሩበት እናደርጋለን፡፡ ግን በዚያ ላይ እያንዳንዱ ተማሪ በቡድን ንግግር እስከሚያቀርብ በዚያ ላይ እስከሚሳተፉ ጊዜ አታግኝም፡፡ ርዕስ ሰጥተህ እያንዳንዱን ማናገር አለበት ለመናገር፡፡ እኔ ንግግርን የምመዝነው ተሳትፎ የምንለው የምንሰጣቸው ነጥብ አለ፡፡ ስለዚህ በዚያ ተሳትፎ የፅሀፈት ክሂል ሰጥተው ፅሁፉን በሚያነብበት ሰዓት ሌላው ስላዳመጠው ነገር ስለተነበበለት ነገር ስለሚጠየቅ የንግግር መልስ መስጠቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ እነዚህን ክሂሎች እንደማስተማሪያ ዘዴያችን እንመዝናቸዋለን፡፡ እና የግዴታ በንግግርና በማዳመጥ ክሂል ላይ ጊዜ እናጥፋ ካልን ከተሰጠው የመጽሐፉ ሽፋን አንፃር ጊዜ ይበላብናል፡፡

አወያይ ከቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በሚሰጣቸው ትኩረት ደረጃቸው ምን ይመስላል?
መምህርት22፡ አንደኛው ሰዋሰው ነው፡፡ ቀጥሎ ስነ-ጽሁፍ ነው፡፡
አወያይ ከክሂሎች ማን የበለጠ ትኩረት ያገኛል?
መምህርት21 ንባብ ይቀድማል ስናስተምር ነው አይደል?
አወያይ ‹አዎ›
መምህርት25፡ ጥያቄ ይሰራሉ ምንባቡን ያነባሉ የቤት ስራ ይሰራሉ በምንባቡ፡፡ መፅሐፉ ራሱ ለማዳመጥ ትኩረት አልሰጠውም ዘጠነኛ ክፍል፡፡
አወያይ ስለዚህ ማዳመጥ መጨረሻ ላይ ይመጣል ማለት ነው? አዎ! በጋራ፡፡
በ2ኛ ደረጃ ላይ የሚመጣው ምንድነው?
መምህርት22፡ ፅሀፈት፡፡ **አወያይ** ትስማማላችሁ? መለያየት ትችላላችሁ፡፡
አይ ነው፡ ሁሉም ተስማሙ፡፡
መምህርት23፡ ከዚያ መናገር ቀጥሎ ማዳመጥ ነው፡፡
አወያይ የተለየ ሃሳብ አለ? ሁሉም በተጠቀሰው ቅደም ተከተል ተስማሙ፡፡
በማጠናቀቂያ ፈተናው ብዙ ጥያቄ የሚጠይቀው በየትኛው ነው?

አንደኛው ሰዋሰው፣ ሁለተኛ ስነ-ጽሁፍ ሶስተኛው ንባብ ነው ሁሉም በዚህ ተስማምተዋል፡፡

3.3.1. የተማሪዎችን ችሎታ በተለይም የማመንጨት ችሎታን በተመለከተ

መምህርት$_{24}$፡ ሃሳብ አመንጭቶ መገለፅን ይህን አልሞከርኩትም አንድን የተዘጋጁ ፅሁፍ ተለማምደው ይመጣሉ ከ5 ፐርሰንት አለው በደንብ አድርገው ሲያቀርቡት አይቻለሁ፡፡

መምህርት$_{25}$፡ አንድ ቲዎሪ የማውቀው አለኝ ቋንቋ ሰው አወቀ የሚባለው ስርዓቱንና ደንቡን ህጉን አውቆ በዚያ መሰረት የተለያዩ ዐረፍተ ነገሮችን አመንጭቶ መናገር ሲችል ነው፡፡ ወጥቶ መናገር መቻል ነው ያጠናውን ሽምድዶ ቢናገር ችሎታው አድጓል ልንለው አንችልም በግሌ ስለዚህ ተማሪው በእኛ ትምህርት ቤት ከፍተኛ ችግር አለ እንዲያውም አሁን አንድ ነገር ላይ ወጥተህ ተናገር ብትለው ይፈራል፣ ይርበተበታል ፊቱን ያዞራል፣ ይሸማቅቃል፣እ ድምጽ አይሰማም ቁጭ ብሎ እንኳ ተናገር ብትለው ድምፁ ራሱ አይሰማም የብዙ ተማሪ ድምፁ አይሰማም እና እኔ ሳስተምር የማገኘው እንደዚህ አይነት ችግሮች ነው፡፡ ምክንያቱም ከታች ሲመጡ እንደዚህ አይነት ኤክስፖዣር የላቸውም፡፡ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ቋንቋውን አሁን አንድ ዐረፍተ ነገር አስተካክለህ በቃልህ ተናገር ብትለው አይናገርም፡፡ እንኳን አንቀፅ፣ እንኳን ድርሰት፣ እንኳን መደምደሚያ፣ እንኳን መነሻ፣ መግቢያ፣ መጨረሻ ሊያቀርብ ይቅርና በቃሉ ማለት ነው፡፡ ጻፍም ብትለው እንኳ መግቢያ፣ መደምደሚያ ያለው ድርሰት በትክክል አስተካክሎ አይፅፍም፡፡ አንቀፅ እንኳን አስተካክሎ አደረጅቶ መፃፍ አይችልም፡፡ አንቀፅ፡፡ አስተምረህው፣ ነገርኸው! ነገርኸው! አስተማርኸው አምስት ጊዜ ምሳሌ ሰጥተኸው ጻፍ ብትለው ሁለት ልጅ ልታገኝ ትችላለህ ከክፍል ውስጥ እና ከፍተኛ የሆነ የቋንቋ ችግር እ ክሂሉ አልዳበረም፡፡ እኔ በልጆቹ ውስጥ ክሂሉ አልዳበረም ከብዙ እንትን አንጻር ከባህል፣ ከቤተሰብ ከመጡበት የትምህርት እርከን ደረጃ - ከታች፣ ከዚያ ከዚያ አንፃር ማለት ይቻላል አላጠናሁትም የትኛው እንደሆነ ግን ብዙ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ ክሂሉን በአግባቡ እየተጠቀመበት አይደለም፣ ተማሪዎቹ፡፡

እወያይ፡ እያንዳንዳችሁ የራሳችሁን አቋም መያዝ ትችላላችሁ፡፡አሁን ምንድነው ከዚህ ጋ ዝንባሌ ቅድም የተነጋገርነው ነገር አለ የተማሪዎች ዝንባሌ የላቸውም ምናልባትም እናውቀዋለን ከሚለው የተነሳ ሊሆን ይችላል በሚለው ሃሳብ ተስማምተናል፡፡ ግን ተግባራዊነቱ ላይ ሁለት አይነት ሃሳብ አለ ችግር የለውም በተግባር ሲታይ ጎበዝ የሆኑ አሉ የሚል አለ፡፡ ችግሩ የበዛ ነው የሚል አለ፡፡

መምህርት$_{24}$፡ ይህን እኔ እቀበለዋለሁ፡፡ የለም ተብሎ ሊደመደም አይችልም ስብሰባ ላይ መ.ልጭ አድርገው የተናገሩት ከመምህሩ በበለጠ አስታውሳለሁ፣ ስብሰባ ላይ መምህራን ላይ እንዲህ እንዲህ ብለው ሃሳባቸውን በደንብ ነው የገለፁት፡፡

መምህርት$_{25}$፡ few in numbers ሁሉም ተማሪ እንደዚህ አይደለም ከሌላ ክልል ካሉ ተማሪዎች ይልቅ እነዚህ ከነዚያ በተሻለ ይናገራሉ፣ ያዳምጣሉ፣

መምህርት$_{23}$፡ እኔ ግን አብዛኞቹ ተማሪዎች በክሂሎች ላይ ከፍተኛ ድክመት አለባቸው በተለይ ደግሞ ፅሀፈት ላይ አንድ ርዕስ ተሰጥቷቸው ፃፍ ቢባሉ ጭራሽ አንቀፅ፣ ድርሰት መጻፍ አይችሉም ተማሪዎቹ አንብቦ መረዳት ላይም ችግር አለባቸው አብዛኞቹ፡፡

አንድ ነገር ተነቦላቸው ያዳመጣችሁትን ፃፍ ቢባሉ ወይም ደግሞ ስሩ ቢባሉ በፍፁም መስራት የማይችሉ በፍፁም ብዙ ተማሪዎች አሉ፡፡ የነሱ ችሎታቸው ሲታይ የት ላይ ነው በተወሰነ በሚያውቁት ርዕስ ላይ ነው፡፡ ሀሳብ ተናገሩ ከተባሉ ግን የተወሰኑት ተነስተው ይናገራሉ ያውም የተወሰኑት ናቸው የሚናገሩት ወደ ሴቶች ስንመጣ ደግሞ ስናያቸው እፍረት አለ፣ መሸማቀቅ አለ ወጥቶ መናገር የለም አንዳንድ የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ ቋንቋውን ቅድም እንደተባለው ተናገርነው ከሚለው አንፃር ተናገሩ ስንላቸው ተነስተው እንዲያውም ክፍሉን ያናጉታል ያልሆነ ነገር እየተናገሩ፡፡ ስለዚህ ሁሉም ተማሪዎች ጥሩ ናቸው ክሂሉን ተቀብለውታል ማለት ያስቸግራል ውስን ናቸው የተቀበሉት፡፡ አብዛኞቹ የመጻፍ፣ አንብቦ ተረድቶ፣ የመሰረት አዳምጦ የመመለስ ችግር አለባቸው፡፡

3.2. ከውጭ የሚመጡባቸውን ጫናዎች በተመለከተ

እኔ ከዚህ ላይ ጋሽ አገኘሁ የተረዳህበት መንገድ እኛ ያልነው ስናስተምርም ሆነ ስናቅድ መጀመሪያ ያለው ችግር ተማሪዎች እናውቀዋለን ስለሚናገሩት፡፡ ስለሚናገሩት እናውቀዋለን አማርኛ ትምህርት ቀላል ነው ብለው ነው የሚመጡት ነው... እንጂ ተማሪዎች እንደኔ/እንደኛ አገላለፅ መናገር ይችላሉ፣ ማዳመጥ ይችላሉ የሚለውን ነገር አይደለም፡፡ አሁን አንተ የተረዳኸው ከዚያ አንፃር ይመስለኛል፡፡ እና ማዳመጥና መናገር ችግር የለባቸውም ያልከው እኛ የወሰድነው ተማሪው ቋንቋዬ ነው ብሎ ስለሚያስብ የተማረው እይታ ነው፡፡ ቋንቋዬ ነው ብለው የሚያስቡት እንደ ቀላል ነው የሚያስቡት ነው፡፡ ከዚያ አንዴ የሆነ እንትን ያልኩት የአማርኛ ፊዚክስ ፈተንሽ ያሉኝ ቦታ አለ፡፡ እንደዚህ እንትን ብለው፣ በአማርኛ እንዴት እወድቃለሁ እያሉ ይመጣሉ ወደቁ ተማሪዎች እንዴ በአማርኛ የምወድቀው ለምንድነው በአማርኛ እንደሚወደቅ እወቁት እስከዚህ ድረስ ምክንያቱም እነሱ አማርኛ ማለት ቀላል ነው ይሰሩታል ከዚያ አንፃር ነው እንጂ ተማሪው ይናገራል፣ ተማሪው ማዳመጥ ይችላል ማለት አይደለም በዚህ መልኩ ቢስተካከል

3.2. ከውጪ የሚመጡባቸውን ጫናዎች፣ ዕውቅና በሚመለከት የተሰጡ አስተያየቶች

መምህርት$_{21}$፡ ስለፈተናው አንድ ምርጫ መሆኑን ነው የሚታሰበው በምርጫ ማዳመጥ፣ መናገር እነዚህ አሁን ጻፍ የሚሉት ነገሮች በዚያ ላይ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንደማይመጡ እንትን ትላለህ፡፡ የሚጠየቁት በቲዎሪ ደረጃ ይጠየቃሉ ለምሳሌ ማዳመጥ እንዴት አወቅሽው

እ. ከ ከፈተናው ታየዋለህ፡፡ ለምሳሌ እ - ማዳመጥ አሁን የማዳመጥ ቅድመ ዝግጅት ማዳመጥ ላይ እ- የማዳመጥ *መመሪያ* የሆነ ያልሆነ፣ በምታዳምጥበት ጊዜ እ - ያለህን እውቀት የመጀመሪያህን እውቀት ማያያዝ የሚሉ *መመሪያዎች* አሉ፡፡ የዚያ አካል ያልሆነ *መመሪያ* የቱ ነው እንደዚህ ያሉ ነገሮችን በፅሀፈት ክሂልም የፅሀፈት ክሂል ባህርያትን ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡ እነዚያን ነገሮች እንደሚማሩ ታውቃለህ፡፡ በቃ *መመሪያዎችን*፣ ባህርያቱን፣ ምናምን ለማትሪክ ስታዘጋጅ ያን ታደርጋለህ፡፡

እንዴት አወቅሽ? *መምህርት*$_{23}$ ያው ነዋ ከፈተናው እያየሁ ነዋ!

3.5. የማጠናቀቂያ ፈተናውን ደረጃ /ጠቀሜታ በተመለከተ

መምህርት$_{21}$፡ ማለት በተወሰነ ደረጃ የዘንድሮውና የባለፈውን አመት አላውቅም እንጂ ብዙ ጊዜ አማርኛ በቅድሚያ በኤ እንትን ይቀመጣል፡፡ ያ ደግሞ ያው እንደ አንድ ሳብጀክት ተይዞ ለፕሪፓራቶሪ ለምንም እንትን ይላል፡፡

3.6. የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ/ዳራ ዘጠነኛ ሲደርሱ በቂ አቅም ይይዛሉ?

መምህርት$_{21}$፡ በተለይ በተለይ ዘመት እንዳለችው መጻፍ የሚባለው ነገር ስማቸውን እንኳ አስተካክለው የማይፅፉ ተማሪዎች ያጋጥመናል፡፡

ከደረጃው በታች ናቸው ብላ ታምናለች በአወንታ እንዳረጋገጠችው፡፡

3.2. ከውጪ የሚመጡባቸውን ጫናዎች በሚመለከት የተሰጡ አስተያየቶች

መምህርት$_{22}$፡ የውጪ ጫና እንዲህ ላይዘወተር ይችላል፡፡ በብዙዎቻችን ላይ ላይደርስ ይችላል እንጂ የውጪ ጫና አለ፡፡ እ- ምናልባት እንዲያው ምስክር የሚሆንም ሰው ከመካከላችን አለ፡፡ ምንባብ ስታወጣ አንተ ጀኒውንሊ ለቋንቋ ማስተማሪያ ብለህ የምትመርጠውን ነገር ሌላ ትርጉም የሚሰጡት ነገር ይኖራል፡፡ የውጭ ጫና የምትሰጣቸው ተማሪዎችም ሆኑ አንተ የምትሰራቸው ዐ. ነገሮች ፖለቲካዊ ትርጉም ሊሰጥብህ ይችላል፡፡ ወዳላሰብከው ጽንፍ ውስጥ ይወስዱሃል--- እና አንዳንድ ጊዜ ደከም ያለ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አንተን ለማጥመድ የሚፈልጉ ክፍሎች ካሉ ይህን በጣም ይጠቀሙበታል፡፡ ገላህን ሰደህ እንዳትናገር የሚያደርግህ ነገር አለ የምትለውን ነገር ተጠንቅቀህ እንድታወጣ ያደርጋሉ፡፡

ሌላ የውጭ ጫና ያልኩህ የክፍለ ጊዜ ብክነቱ የውጭ ጫና ነው፡፡ ያላሰብከው ይመጣል አሁን ባለፈው እኔና አንተ ስንገናኝ ሁለት ሳምንት እኔ አራት ክፍለ ጊዜ አለኝ ብዬ ተዝናንቼ በአመታዊ እቅዴ መሰረት ለማስተማር ተዘጋጅቼ ስመጣ ባልታሰበ ደራሽ ስብሰባና ደራሽ ስራ ሳንገናኝ ቀረን

መጨረሻ ላይ አብቃቅቼ አንድ ክፍለ ጊዜ አገኘሁ ሁለት ክፍል ኮምባይን አድርጌ ሁለት ክፍሎችን አመጣሁ እኔ ባሰብኩት ባቀድኩት ሳይሆን ቢያንስ ይሆናል በምለው መልክ ለመሸፈን ሞከርኩ እና ጫናዎች አብዛኛውን አሉ፡፡

ሌላው ጫና ጥያቄ አንተ ለማዘጋጀት በምትፈልግበት በጥያቄ ቁጥር ትገደባለህ፡፡ ይህን ያህል ገጽ ከዚህ በላይ አትሄድም የምትባልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ አንተ እንትን ያልካቸውን ተማሪዎች የምትፈትነው በራስህ ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህ ትምህርቱን አንተ ባየህበት ሁኔታ ሌላው አካል ላያይ ይችላል፡፡

ሌላው የውጭ ጫናው የወላጆች ተፅዕኖ ያለበት ይሁን ወይም ተማሪዎች የፈጠሩት ነው ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ በምንጠራበት ሰዓት ተማሪው አይመጣልህም፡፡ ይህ ምናልባት እንግዲህ ከእኔ ውጪ ነው፡፡ ተማሪው ለምን አልመጣም ይህ ራሱ አንድ እንትን ነው ወላጆች እምቢ ብለውት ነው፤ እንደዚያ እንዳትል ደግሞ በወላጆች ስብሰባ ጊዜ የሚገኙ ወላጆች ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ ሲባል ቢያንስ ግንዘብ እንኳን አዋጥተን ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ ለሚሰራው ስራ እንሸፍናለን የሚል የሳይንስ ትምህርቶች ፕሮግራም ሲሰራ ወላጆች በደስታ ነው የተቀበሉት፡፡ እኛ ግን በነጻ እናስተምራለን ብለን የምንጠራቸው ተማሪዎች ቃል ገብተው፣ ሁኔታውን አይተው ሲቀሩ ታያለህ ደግሞ፡፡ ስለዚህ ያም ከውጪ ጫናዎች የሚመደብ ይመስለኛል ምክንያቱም በእኛ ከኖርማል ፕሮግራሙ የምንሸፍነው የምናስገድደው ስለማይሆን፡፡

ያልተጠቀሱ ካሉ/የሚጻረሯቸውም?

መምህር$_{25}$፡ እኔ ያልተጠቀሱትን ስናገር ከውጪ ጫና አለ፡፡ አንዳንዴ በቋንቋው ውስጥ ሌሎች ቃላትም ታገኛለህ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ያልሆኑ ሁለተኛ ተማሪዎች ከማህበረሰቡ ይዘውት የሚመጡት አማርኛን እንደ ቀላል ነገር ስለሚቆጥሩት አንዳንዴ ደብተር እንኳ የማይገዙበት ሁኔታ አለ፡፡ ሁለተኛ ትምህርት ቤቱ ራሱ ለተወሰኑ የትምህርት አይነቶች ቱቶሪያል ግንዘብ ሲመድብ አማርኛ አልተመደበለትም፡፡ ይህ ጫና ነው ይህ ነገር አለመመደቡ አይደለም፡፡ በተማሪውና በህብረተሰቡ ዘንድ አማርኛ ምንም ትኩረት ያልተሰጠው አይነት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሌሎቹ አሁን በግንዘብ እየተማሩ ነው ለአማርኛ ግን አልተመደበም ይህ የውጭ ጫና ነው፡፡

ሁለተኛ ስታስተምር በጣም ትፈራለህ፡፡ ክፍል ውስጥ ብዙ አሉ፣ ያንተን አፍ የሚቆጥሩ ነገርን ያመጡብኛል ብለህ ፈርተህ ነው፡፡ የምትሰጣቸው ምሳሌዎች ሁሉ የተገደቡ ነው የሚሆኑት፣ እኔ በዚህ አጋጣሚ የሆነ ችግር ደርሶብኛል ቀደም ያለ ስለሆነ ነው እሱን ማንሳት አልፈልግም ያን የቅርቡን ነው የምናገረው አሁን ለምሳሌ አንድ ቀን እኔ የሆነ ስለሀረግ አስተምራለሁ፡፡ ክፍል ውስጥ ስለሀረግ እና እንዲህ ብሎ ያየኛል፡፡ እንግዲህ አየህ ተልእኮ እየያዙ የሚመጡ አሉ፡፡ በአንድ ግጥም ውስጥ ሶስት ሀረግ ሊኖር እንደሚችል እንደምሳሌ እያደረግኩ ነው የምነግራቸው፡፡ አሁን አንድ የማውቀው ሀረግ ትዝ አለኝ እንትን ግጥም ትዝ አለኝና ያን ስናገር ‹‹እህ›› አለኝ፡፡ አፈዘብኝ በጣም፡፡ እንትኑን ልንገርህ ግጥሙን እንደ ቅኔ ያለ ረጅም ነው፡፡ “እግዜር በጨለማ፣አምላክ በጨለማ እንዳይሄድ አውቃለሁ፤ ቀን ያልፋል ብለውኝ እጠብቀዋለሁ›› ነው የሚለው አሁን ገብቶሃል በኋላ ነው ትዝ ያለኝ እኔ ያ ሰው አይኑን ገልበጥ አድርጎ እንዲህ ሲያየኝ ይህ ነገር በሌላ ተርጉሞብኛል ብዬ በጣም ደነገጥኩ ገብቶሃል እና ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ አለ በአማርኛ ብቻ አይደለም በማንኛውም የመማር ማስተማር እንትን ውስጥ ክፍል ውስጥ አፍ ቆጣሪዎች አሉ፡፡ ያንን ተፅዕኖ መምህሩ የሚፈልገውን ምሳሌ ሰጥቶ እንዳያስተምር የሚያደርጉ በስፋት አሉ፡፡ ይህን ለመጨመር ፈልጌ ነው፡፡

መምህርት$_{23}$፡ ሌላው ችሎታቸውን በማናውቃቸው ተማሪዎች ላይ በየዓመቱ ሁልጊዜ ግብ ጣሉ የሚባል ነገር አለ፡፡ ግብ እንጥላለን የተማሪዎችን ችሎታ ሳናውቀው ከተለያየ ክፍል መጥተው ግብ እንጥላለን፡፡ ይህን እንዴት ነው የማየው አንደኛ በእኛ ላይ ተማሪዎች አነስተኛ ውጤት ሲያመጡ ይህን ያህል ግብ ጥለህ ነበር፣ ይህን ያህል ግብ ጥለሽ ነበር፣ ከዚያ አልደረሽም ችግሩ ያንቺ ነው

ይባላል፡፡ ሁለተኛው አማርኛን እንደ ቀላል ስለሚቆጥሩት አማርኛም እንደፊዚክስ ከጣላችሁበት እየተባልን እንወቀሳለን፡፡

አወያይ፡ ተማሪዎች ናቸው?

መምህርት$_{23}$፡ ተማሪዎች አይደሉም፤ ከላይ ነው ግብ የሚያስጥልህም የላይኛው ነው፡፡ ውጤቱ ሳይሳካ ሲቀርም የሚጠይቅህ የላይኛው ነው፡፡ የማስተማር ስነ-ዘዴህ የተማሪዎች የደረጃ መጠንም አይታይም፡፡ ልክ ያንተ ስህተት እንደሆነ ነው የሚቆጠረው ሌላው በዚህ ትምህርት ለምሳሌ ዘጠነኛ ክፍል የማያነብ የማይፅፍ ተማሪ አለ ስንል በዚህ ደረጃ መምህራን ግብ ጥለው ከታችኛው ክፍልም አልደርስላቸው ሲሉ የመማሩት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ከዚያ ግን መምህሩ ተጠያቂ እንዳይሆን ከግቡ አድርሻለሁ ለማለት ውጤት የመጨመር ሁኔታ ይታያል፡፡ ይህ አንድ ችግር ነው፡፡

ሌላው የውጭ ጫና ምንድነው ቅድም ተነስቶ ነበር የአማርኛ ትምህርት 12ኛ ክፍል በማጠቃለያው ፈተና አይሰጥም፡፡ እንዲያውም ተማሪዎች በውጭ የሚሉት ምንድነው ደግሞ ለአማርኛ 12ኛ ክፍል ለማይሰጠው ታሪኩ ለጎደለው ትምህርት እኮ ነው የሚባለው አማርኛ እኮ ታሪኩ የጎደለ ትምህርት ነው፡፡ ለምን እናነበዋለን ለምን እንዘጋጃለን ብለው ተማሪዎች ይተውታል፤ ይህ ከውጪ የሚመጣ ጫና ነው፡፤

ሌላው ይህ የስብሰባ ጉዳይ ነው፡፡ ክፍል ውስጥ እያስተማረ እያለን ማሳሰቢያ ልሰጥ ነው፤ ይህን ልፈጽም ነው ይባሉ፣ ማሳሰቢያ ይሰጣል መብት ይባላል፡፡ የወላጅ ወተመ የሚባል ነገር አለ፣ ስብሰባ ይባላል፡፡ ክፍለ ጊዜህን ተጠቅመህ አላሰራህም፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ ክፍለ ጊዜ የእኛ ብቻ ሳይሆን የሌላውም ክፍለ ጊዜ ፖርሽኑ ሳይሸፈን ተማሪዎች ለፈተና ይቀመጣሉ፡፡

መምህር$_{25}$፡ በጣም ክብር የተነፈገው ቋንቋ ነው፡፡

መምህር$_{24}$፡ ይህን ለማጠናከር ቅድም ከተባለው በተጨማሪ መጽሐፍት የሚቀየሩት በየአምስት ዓመቱ ነው፡፡ አማርኛ የተቀየረው በሰባት አመቱ ነው፡፡ በሰባት ዓመቱ ተቀይሮ እንኳን ሌሎቹ የመጽሐፍ ትውውቅ አካሂደዋል መምህራን፣ የመጻህፍት ትውውቅ እየተጠሩ አካሂደዋል፡፡ እኔ ለአማርኛ በፍጹም አንድ መምህር ባህርዳር ሂደ እንትን ብሏል፡፡ ካሉት ሌሎቹ መምህራን እንድንነጋገርበት እድል አልተሰጠም፡፡ የመጽሐፍ ትውውቅ እንኳ እንድናካሂድ እድሉ ራሱ አልተመቻቸልንም፡፡ ሌሎች መምህራን ግን አዘዞ እየተጠሩ እንግሊዝኛ፣ ሲቪክስ፣ የሳይንስ መምህራን ምናምን እየተጠሩ ተዋውቀዋል፡፡

መምህር$_{25}$፡ ጠይቀን ነበር በጀት የለም ለአማርኛ ተባለ ቀረ፡፡

መምህር$_{24}$፡ እና ይህ እኩል የማይታይ መሆኑን ያሳያል፡፡

መምህርት$_{23}$፡ ትኩረት የሚሰጠው ለሳይንስ ትምህርቶች ነው፡፡

3.4. በማጠናቀቂያ ፈተናው ላይ ያላቸው እውቅና

መምህር$_{22}$፡ የማጠናቀቂያ ፈተናው በፊት የነበረውና አሁን ያለው በጣም በጣም ይለያያል፡፡ አንደኛ መጽሐፉ አሁን ለማስተማሪያ እ ለማስተማር በሚያመች መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ የዘጠኝም የ10ም የአምናውም ፈተና የዘንድሮውም ፈተና በትኩረት አይቼዋለሁ፡፡ በመጻህፍቱ ይዘቶች ላይ ነው የሚያተኩረው፡፡ ፈተናው ያው የምታስተምረውን ነገር አሁን ዘንድሮ የወጣው ፈተና ለሚቀጥለው በምን ላይ ማተኮር እንዳለብህ ይነግርሃል፡፡ እኛ ስለምናየው የተማሪው ወጣ ብላችሁ አስተምሩን የሚለው ዝንባሌ ከድሮው አሁን ቀንሷል፡፡ በበኩሌ እንደማየው በፊት ብዙ የሰዋሰው መጻህፍትን ከዚያም ከዚህም ቀራርመህ የምታስተምረው ነበር፡፡ አሁን ሁሉንም ይዘቶች እዛው መጽሐፉ ላይ አሉ፡፡ ምናልባት የመግለጫ የማነስ፣ የመስፋት ሁኔታ ይኖራል እንጂ የምሳሌዎቹ የመጥበብ፣ የማነስ፣ የመስፋት ሁኔታ ይኖራል እንጂ ከዚያ ውጪ ፈተናው አዘገጃጀቱ ከምናስተምረው እንትን ጋር ያው ተመሳሳይ ነው፡፡

ክሂሎችም ቢሆኑ እኮ እምልህ በፈተና ተናግር ብለህ እንደማትለው ይታወቃል ግን እነዚያን የሚጠይቅበት አለው፡፡ የትኛው ነው ከንግግር ዝግጅት የሚካተተው፣ የማይካተተው፣ የትኛው ነው ከንግግር አቀራረብ የሚካተተው፣ የማይካተተው የሚለው አለ እዚያ ውስጥ፡፡

መፃፍን በተመለከተ ለምሳሌ ቅደም ተከተል ይሰጥሃል ወይ የጊዜ ወይ የድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክልና እስቲ መልክ አስይዘህ አንድ ተራኪ ድርሰት ጻፍባቸው ይልሃል ወይም ለመጻፍ የሚያመቸው የትኛው ነው ይልሃል፡፡ ስለዚህ የፅሁፍ ክሂል በዚያው ውስጥ እኮ አለ፡፡ ግን አጠያየቁ እኛ ክፍል ውስጥ የምናደርገው ልምምድ አይደለም፡፡ ስናስተምራቸውም እኮ እኛ በዚህ መልክ ብትጠየቁ ብለን አያይዘን ነው በምናስተምራቸው ለጥያቄ የሚያመች የድሮው እኛ ያልደረስንበት ጻ የሚል ነበር የሚል አለ፡፡ አሁን ያንን እንጠብቅ ብንል ከተማሪው ቁጥር ከጊዜ አወሳሰዱ ከበጀት ከምኑ አንፃር በሰው የማይታረም ስለሆነ ያንን አንጠብቅም መቼም አሁን

አወያይ፡ በተባለው ትስማማላችሁ?

ተወያዮቹ፡ አዎ! በጋራ

መምህርት$_{23}$፡ ደረጃው ጥሩ የሚሆነው እኮ እንደድሮው ቢሆን ነው፡፡ እነዚህ የሚጠሉና የማይጠሉ የሚባሉ ሳብጀክቶች አሉ፡፡ አሁን እንግሊዝኛና ሂሳብ ጭራሽ የሚቀሩ ትምህርቶች አይደሉም በዚያ ደረጃ እንኳ እኔ የሚጣል ትምህርት ስለሆነ ጥሩ ነው አልልም፡፡

መምህር$_{22}$፡ አሁን ቅድም የተነገረው ምን መሰለህ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት ስለማይገፉ፣ ርቆ ለማየት ብዙም አይገፉቸውም የሳይንስ ትምህርት ፍላጎት ያለው ተማሪ በብሔራዊ ፈተና ቢመጣም ባይመጣም ያው የሚመርጠው ያው ሳይንሱን ስለሆነ ግዴለም፡፡ ግን የቋንቋ ሙከራቸው ጥሩ የሆነ ፈጥረው የመጻፍ፣ የምትሰጣቸውን ቶሎ የመቀበል አቅም ያላቸው ልጆች ምናልባትም በዚሁ ይቀጥላሉ ብለህ የምትገምታቸው ተማሪዎች 10ኛ ክፍል ካለፉ በኋ በቃ እነሱ ተስፋ ያጡና ይተዋሉ፡፡ ለሌላው ትምህርት ነው ጊዜ የሚሰጡት ለምን መንግስት ራሱ ትኩረት ያልሰጠውን ነገር እኔ ምን ብዬ ወንዝ የሚያሻግር ምናም- ቅድም የተባለው፡፡ ስለዚህ የእኛ ተማሪዎች በዚህ ላይ ችግር የለም ቢያንስ እኛ ስንመክራቸው እኮ ቢያንስ እኮ ይህችን ድልድይ ያሻግራችኋል ነው የምንላቸው፡፡ ፊዚክስን፣ ማትስን የሚደፍረው ተማሪ የተወሰነ ነው፡፡ ቁጥሩ ከግማሽ በታች ነው፡፡ በቋንቋ በኩል ቢያንስ አንብበው የተወሰነ ጥያቄ ይመልሳሉ፡፡ ለምን ትኩረት ሰጥተው እኛ የምንሰጣቸውን ምክር ተቀብለው ከሄዱ ማለት ነው፡፡ ካልተቀበሉ ዞሮ ዞሮ በእኛም እኮ በቋንቋው ሳይንስ ስለሆነ አሁን የሚማሩት እ- ያልተከታተለ ተማሪ አይደለም ለወደፊቱ አርቆ ሊያይበት ለአሁኑም ቢሆን እንትን ሊሆን አይችልም፡፡ ፕሮባብሊቲው ሰፊ ነው፡፡

3.6. ለትምህርቱ የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን ላይ ቀደም ብሎ በተገለፀው ነው የምትስማሙት ወይም የምትጨምሩት ወይም የተለየ ሃሳብ አላችሁ በቂ አቅም ሳይፈጥሩ ይመጣሉ በሚለው ነው የምትስማሙት?

መልስ እ - አዎ በጋራ

መምህርት$_{23}$- አንዱ እሱ ነው ሌላው ደግሞ 6ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከወሰዱ በኋላ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ተሻግረው የሚመጡት በጣም በአነስተኛ ፐርሰንት ነው 30 ፐርሰንት ነው፡፡ በቃ ለኮታ መሸፈኛ ነው የሚመጡት በእኛም ብቻ ሳይሆን በሌላው የትምህርት አይነት ለኮታ መሸፈኛ ይመጣሉ፡፡ ዘጠነኛ ክፍል ከደረሱ በኋላ የዘጠነኛ ክፍል አቅም የላቸውም፡፡ በ30 ፐርሰንት የመጣውን ተማሪ በ70 ግብ ያዙ እንባላለን፡፡ በጣም ከፍተኛ ችግር ነው፡፡

መምህር$_{22}$፡ እዚህ ቅድም የተነሳው አማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ማነሱን በተመለከተ ያለውን ችግር ለማሳወቅ የተደረገ ጥረት ስለመኖር አለመኖሩ ስለተነሳው ጉዳይ ‹‹ይህ የፅኛ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በእነሱ በእርስ በርሳቸው ጥያቄው ቢነሳም የፖለቲካ አቋም የተያዘበት ነው የሚመስለው፡፡ ከዚህ ቀደም አስታውሳለሁ የ2ኛ ደረጃ መምህራን ከ10፣ 15 ዓመት በፊት ነው በዞን ደረጃ ስብሰባ ተጠርተን ሄደን ነበር፡፡ እነሱ የፈለጉት ማለት የፖለቲካ ክንፉን የያዘው የሚመራው አካል የሚፈልገው የተለያየ የብሔረሰብ ቋንቋ እንዲሰጥ ነው እንጂ አማርኛ ቋንቋ የክልሉ ቋንቋ ነው፡፡ እንደብሔረሰብ ቋንቋ የተሻለ ክፍለ ጊዜ ሊጠቀም ይገባል የሚል አቋም የለም፡፡ የሚፈለገው ወይ ኦሮምኛ ወይ ትግርኛ ወይ ሌላ እንዲጠና ነው፡፡ አሁን ይህ ጥያቄ በእኛ ብናነሳው አይደለም ወደ ላይ ሊሄድ እንጂ ርዕሰ መምህሩም በቀና የሚያየው አይመስለኝም፤ ስርዓተ ትምህርቱን የሚመራው፡፡

መምህርት$_{23}$፡ በተለይ መምህርት$_{22}$ እንደሚለው ለቋንቋው ትምህርት ትኩረት አልተሰጠውም፡፡ በዚህ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ወደታችኛው አሁን ተሻሽሎ ካልሆነ በስተቀር አንደኛ ክፍል ላይ እኮ በሳምንት ይማሩ የነበረው ለብዙ አመታት አማርኛ አንድ ክፍለ ጊዜ ነው፡፡ ይህንን እንዲያውም ከዚህ ኮሌጅ የክልሉና የኮሌጁ ስብሰባ ላይ አንስተነው የተሰጠን ምላሽ ምንድነው ሌሎችን የትምህርት አይነቶች በአማርኛ ስለሚማሩ አማርኛንም እግረመንገዳቸውን ይማሩት የሚል ምላሽ ነው የሰጡን፡፡ አልሰማንም ሳይሆን ትኩረት አልተሰጠበትም ለቋንቋው ይህም በየጊዜው ሳይነሳ ቀርቶ አይደለም፡፡ ያውቁታል፡፡ ነገር ግን በቋንቋ ችሎታ የሚባለው ነገር ምንድነው ሥነ-ፅሁፍ የሚፅፍ፣ ግጥም የሚደረድር አይደለም ያጣነው የሳይንስ ተማሪ እየተባለ እኮ በየመድረኩ የሚናገረው ፡፡ እሁን እኮ በእኛ ስብሰባ ላይ ይነገራል፣ የሳይንስ ተማሪ ነው ያጣነው፡፡ እነዚህ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርቶች ችግር የለብንም፡፡ ችግር የለብንም ተብሎ ዩኒቨርሲቲ የሚገባው እኮ 70 በ 30 የሚባል ነገር ተሰጥቷል፡፡

ስብሰባ ላይ እኮ እኛ ይነገረናል፡፡ አሁን ሰኔ ግምገማ ላይ ትኩረት የሚደረገው ሳይንስ መምህራን ከግባችሁ ላይ ደርሳችኋል (ሌሎቹ የሚጠየቁት ዘግይቶ መሆኑን አብረው ገልፀዋል)፡፡ መጀመሪያ የሳይንስ ትምህርቶች፣ ከዚያ ደግሞ ማህበራዊ ሳይንስ ላይ ጂኦግራፊና ሂስትሪ ሲቪክስ፣ ከዚያ በኋላ አማርኛ በሶስተኛ ደረጃ በአራተኛ የሰውነት ማጎልመሻ እና ትኩረት አንሶታል፡፡ ከሌላኛው፡፡

4. ጾታና የስራ ልምድ በትምህርት አስተቃቅዳችሁና የክፍል ትምህርት አቀራረባችሁ ላይ ስለሚያሳድሩት ተፅዕኖ ያላችሁ ግንዛቤ ምንድነው?

መምህርት$_{22}$፡ ፆታን በተመለከተ እኔ ችግር ያለበት አይመስለኝም፡፡ እስካሁን ባየሁት ምናልባት ያሉት መምህራን ዝግጅት አቅም ይመስለኛል፡፡ እና እስካሁን ልዩነት ያለ ሆኖ አላየሁትም፡፡

ነገር ግን የማስተማር ልምድ ከሚለው ላይ የማስተማር ልምድ በጣም በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ቅድም ያልናቸውን መጽሀፍ ሪፈር ማድረግ የሚያዘወትረው ልምዱ ጅማሪ የሆነው ነው፡፡ ሌላው አይጠቀምባቸውም ማለት አይደለም፡፡ ግን ቢያንስ አንድ አመት ሁለት ዓመት ካየው በኋላ ያንን ለማስተማር ብዙም ችግር አይኖርበትም ፡፡ ስለዚህ የማስተማር ልምድ የጥያቄ አውጣጡችን ያለማምዳል፣ ከተማሪው እኩ የምትማረው ትምህርት እኩ ቀላል አይደለም፡፡ ከታች ይዘውት የሚመጡት አንዳንድ የተዛነፉ ለምሳሌ ምዕላድ ምንድነው የሚለውን ዘጠነኛ ክፍል ሲመጡ ምእላድ ማለት ቅጥያ ማለት ነው የሚለውን ነው ይዘውት የሚመጡት፡፡ ግን ምዕላድ ማለት ቅጥያ አይደለም ቃል ወይም የቃል ክፍል ሆኖ ነው የምታገኘው እና የማስተማር ልምድ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ለቋንቋው ብቻ አይደለም ለሌሎችም የምናየው ነገር ነው፡፡

አወያይ፡ በዚህ ትስማማላችሁ ? በማስተማር ልምድ አስተወጽኦ?

አዎ በጋራ

መምህርት$_{21}$ ሴት ወንድ መሆን አንዳንዴ በቋንቋ ብቻ ሳይሆን ምናልባት በሌሎች ነገሮች ለይ ልዩነት የለውምብዩ አምናለው ግን ይሄ ሁሉም ያምንበታል ማለት ግን አደለም መክንያቱም አንዳንዴ የተማሪዎች አመለካከት ስታይ ሊረብሽህ ይችላል ፡፡ አንዱ ፈተና ስንፈትን ሴት ሆኜ ነው እንዴ እንደዚህ ያፋጠጠብኝ ወይስ ምንድነው የሚለው ነገር እኔን እንትን ብሎኛል፡፡ እኔ በራሴ ያሰብኩትን ነው፡፡ እና የተወሰነ ሴት ወንድም ሳይሆን አካላዊምም ሁኔታም የሚወስነው ይመስለኛል፡፡ የተወሰነ ሊፈሩህ ይችላሉ ብዩ አስባለሁ፡፡

አወያይ ስለዚህ የማስተማር ልምድ ብዙ ሚና አለው የሚል እምነት አላቸው ማለት ነው?

መምህርት$_{21}$፡ አዎ! ጀማሪ ስትሆን አንድ ያው መጀመሪያ ፈተናዎቹ ምን ላይ እንዳሉ እንትን ላትል ትችላለህ፡፡ ግን እያየኸው በሂደክ ቁጥር ይህ ነገር አለ ለካ ይህን ነገር እንትን ብለው እያልክ አሁን ባለው ቅድም ከገለፅኩልህ አንፃር ይህን ሰንጠረዥ ማሰራት አይጠቅምም ብዩ በመጀመሪያ አለፍኩት፡፡ መጣ ጥያቄው አይደልን ከዚያ በኋላ እነዚህን ነገሮች ልክ እንዲህ እንዲህ ነበረ አንድ ወቅት እንዲህ ነበረ አንድ ወቅት እንዲህ አጋጥሞኛል፡፡ ስለዚህ በታች ይህን እዩት እያልኩ

እሄዳለሁ፡፡ ይህ ምንድነው ልምድህ እየጨመረ የማስተማር ልምድህ ሲጨምር ምን ነገር መስራት እንዳለብህ እያወቅህ የምትሄድ ይመስለኛል፡፡

5. የሚያስተምሩበትን/የትምህርት ቤት ዐውድ እንዴት እንደሚገነዘቡት (በማስተማር ዝግጅታቸው የማስተማር ተግባራቸው ላይ የሚያስተምሩበት አውድ የሚኖረውን ተፅዕኖ በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ) የሰጡት አስተያየት

5.1. ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ቦታ

መምህርት$_{25}$ ፡ጥሩ ትምህርት ቤት ፔዳጎጂካሊና ሳይኮሎጂካሊ አንድ ትምህርት ቤት ለመማር ማስተማር ሂደት ወሳኝ ነው፡፡ ግቢው ማራኪ ሲሆን ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ለመምጣት ይናፍቃል፡፡ ግቢው ምቹ ሲሆን ውሃ ሲኖር ሌሎችም ፋሲሊቲዎች ሲኖሩት ትምህርት ቤት ለመምጣት ይናፍቃል፡፡ የእኛ ግቢ በዚህ ሁኔታ ብዙም የተሟላ አይደለም፡፡ ተማሪ እንዲያውም ሩጠ ወጥቶ መሄድ ነው የሚፈልገው፡፡ ምክንያቱም ብዙ የተደራጀ ነገር የለም፡፡ ላይብራሪ በአቅም መጠን ገብቶ መስተናገድ አይቻልም፡፡ እንደምታየው ግቢው የተልከሰከሰ ነው፡፡ የመጫወቻ ሜዳ የለውም፡፡ የመማሪያ ክፍሎቹ ምቹ አይደሉም፡፡ እዚህ አካባቢ መኪና አለ ጥሩንባ እየነፋ አንዳንድ ተማሪዎችን ይበጠብጣቸዋል፡፡ በር ላይ ቆሞ ራሱ የማይለው ነገር የለም አንዳንድ ቀን አለው፡፡ ስለዚህ ይህ ግቢ እኔ በአጠቃላይ ወደፊት እንጃ እንጂ አሁን በቆየንበት አምስት ዓመት ውስጥ ለመማር ማስተማሩ ምቹ የሆነ ግቢ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በግሌ አጥር የለም ሜዳ የለም መንገድ ዳር መሆኑ፣ የክፍሎቹ ምቹ አለመሆን፣ ሲወጡ ሲገቡ የተሰነካከለ ነው የተስተካከለ አይደለም ድንጋዩ፣ ምናምኑ፡፡

መምህርት$_{22}$፡ በቂ ብርሃን የሌላቸው የመማሪያ ክፍሎችም አሉ፡፡

መምህርት$_{23}$፡ በአካባቢው አሸሽ ቤቶች ፊልም ቤቶች መኖራቸው ስታንዳርዱ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት አይደለም እስካሁን ያለው፡፡ ገና ወደፊት ካልሆነ በስተቀር፡፡

5.2 የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ ተፅዕኖን በተመለከተ

መምህርት$_{25}$፡ አንድ ነው፡፡ የእኛ ትምህርት ቤት በእኛ ዲፓርትመንት እንዴት መሰለህ የምንጠቀመው፡፡ ለምሳሌ ዘንድሮ ዘጠነኛ ክፍል አስተምሬ ከሆነ በሚቀጥለው አመት እነዚያን ልጆቼን ይገር 10ኛ ነው የምገባው ገብቶሃል፡፡ ዘጠነኛ ክፍል አስተማርኩኝ ልጆቼን ይገር 10ኛ እገባለሁ፡፡ በዚሁ በዘጠነኛና በ10 እንደ አሃዳዊ ስርዓት ነው የምንጠቀመው በዚህ ኮንሰፕት ነው ያለነው፡፡ ምናልባት አንዳንዴ አንድ ሰው ይተርፋል እንጂ ወይ ሊተርፍ ወይ ይበዛል እንጂ ዘጠነኛ ክፍል የያዝናቸው ተማሪዎች 10ኛ ክፍል ይዘን እንሄዳለን እናስፈትናለን ከዚያ በኋላ ተመልሰን ወደ ዘጠኝ ትመለሳለህ፡፡ ስለዚህ ዘጠነኛ ክፍል ማስተማር 10ኛ ክፍል ማስተማር በግሌ ለእኔ እኩል ነው፡፡

መምህርት$_{22}$፡ ሌላው የቋንቋው ይዘቶች እኮ ራሱ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ዘጠነኛ ክፍል ያሉ ይዘቶች ምዕራፍ አንድ የሁለቱም ተመሳሳይ ነው፡፡ ርዕሱ ራሱ አፅንኦት የመስጫ ነው 10ኛ ክፍል ላይ ማጠናከሪያ እንጂ ይዘቶቹ ተመሳሳይ ናቸው፡፡

አወያዩ፡ እናንተ ጋር 10 ስለሆኑ ለመማር ቸልተኛ የሚሆኑበት ነገር ዘጠኝ ላይ ለመማር ጥሩ የሚሆኑበትን ነገር የለም፡፡

መምህርት$_{25}$፡ ዘጠኝ ላይ ትንሽ የስነ-ምግባር ችግር ይታያል አንደኛ ኢንቫይሮመንቱን ገና አልተላመደም፡፡ አዲስ ናቸው ከ8ኛ ክፍል ነው የመጡት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ገና መግባታቸው ነው፡፡ እዚህ ላይ የተወሰነ የስነ-ምግባር ችግር ያጋጥምህል፣ 10 አንዳንዴ ወደ መጨረሻው ወደ ሞዴል ፈተናው አካባቢ ካልሆነ ስነ-ምግባራቸውም ጥሩ ይመስለኛል የተሻለ ነው፡፡

መምህርት$_{22}$፡ለይዘቶች እንግዳ ይሆናሉ ዘጠነኛ ክፍል 10ኛ ክፍል ላይ ችግር የለብንም ማልፋት ነው፡፡

5.3. የተማሪዎች ብዛት በክፍል እንደ አንድ ችግር የሚታይ ነው ? የናንተ በአማካይ በክፍል ስንት ነው?

መምህርት$_{25}$፡ 68፡፡ *መምህርት$_{24}$፡* አሉ 69 አሉ ከ65-69 በአማካይ፡፡

ጥያቄ፡ ለማስተማር ምቹ ነው ወይስ አይደለም

በጋራ፡ ምቹ አይደለም!

መምህርት$_{22}$፡ በተለይ አንድ ለአምስት የሚለው አደረጃጀት በቃ የይስሙላ ነው፡፡

6 ስልጠናን በተመለከተ

መምህር$_{25}$፡ ቋንቋን በተመለከተ አግኝተንም አናውቅ፡፡ እንትን ነው የምንወያይ ሀምሌ ላይ የፖለቲካ የምናምን ነገሮች

አወያይ ቋንቋ ለማስተማር ያግዛል?

መምህርት$_{25}$፡ ምንም አያግዙም ወይ ጉድ ለእኛ ስልጠና?

7 የማጠናቀቂያ ፈተናው ተገቢነት ላይ ያላቸው ግንዛቤ

7.1. ተማሪዎችን ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ ከማሸጋገር አንፃር

መምህርት$_{25}$፡ በእኛ ትምህርት የተሻለ ውጤት ነው የሚያመጡት፡፡ እኛም በጣም ነው የምንሰራ፡፡ በእኛ ትምህርት ኤዎች ሲቆጠሩ ሁልጊዜ አንደኛ ነን፡፡ አይደል አባይ ስለዚህ እነዚህ ለልጆቹ እየጠቀሟቸው ነው በጣም ወደ መሰናዶ ለመግባት አምናም ቆጥሬያለሁ ወደ 90 ኤ ነው፡፡ ወደ 150 ቢ ነው ያገኙት፡፡ ስለዚህ በእኛ ትምህርት የሚያገኙት ውጤት ልጆቹን ወደ መሰናዶ እየገፋቸው ነው ጥሩ ነው፡፡

7.2. ለስራ ዓለም መዘጋጀታቸውን ከመለካት አንፃር ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ

መምህር$_{22}$፡ አዎ ቁጥራቸው አነስተኛ ነው እንጂ ፈተናው በእርግጥ ለሁሉም ለሰነፉም፣ ለመካከለኛውም፣ ለጎበዙም የሚቀርብ ስለሆነ ፈተናው ግን ለማስተማር ሂደት ያንን ከግብ ያደርሳል ወይ እኛ የምንገምተው እንደ እኔ ቁጥራቸው ያንስብሃል፡፡ ስብሰባ ይመራል ብለህ የምትገምተው አፍልቆ ይጽፋል የምትለው የተጻፈውን በትክክል በተሰጠው መመዘኛ አንፃር ይገመግማል ይተቻል የምትለው ያንስብሃል ቁጥሩ እንጂ አለ እኮ ብዙዎቹ፣ እና ፈተናው ለዚህ
የበቁትንና ያልበቁትን ያሳያል፡፡

መምህር$_{22}$፡ በዚያ ደረጃ ለምትላቸው ልጆች ያወጣቸዋል፡፡ ፈተናው እነዚያን ይለያቸዋል

መምህር$_{25}$፡ አናሳ ናቸው፡፡

መምህር$_{24}$፡ እስቲ አንድ ነገር አሁን እነዚህ እኮ ምንድናቸው ፕሮዳክቲቭ ስኪልስ የሚባሉት አይደሉም፡፡ አዎ! ይለካል ለማለት አይሰደፍርም፡፡ ምክንያቱም አሁን ቃለ ጉባዔና በቃለ ጉባዔ የማይካትተው የቱ ነው? እንደዚህ ነው እንጅ ቃለ ጉባኤ ይዞ መጀመሪያ የስብሰባ ርዕስ የስብሰባ ጊዜ ሁለት ምናምን እንደዚህ እንጂ እንዲፅፉ አያደርግም፡፡ ስለዚህ መቻላቸው በምን ይታወቃል?

አወያይ፡ እነሱ/ ፈተና አዘጋጆች ይህን ያወቀ ሰው ነው የሚመልሰው የሚል ሃሳብ ቢኖራቸውስ?

መምህር$_{24}$፡ አሁን የግድ ጥሩ ነገር አነሳህ! ባልከው መንገድ ሊያስኬድ የሚችለው የትኛው ነው? ይህ ጀምብል ሴንቴንስ ይሰጣል፡፡ የተዛቡ ዐ.ነገሮች ተሰጥቶ አንቀፁን እስቲ የተሟላ አንቀፅ አድርገው ያንን ቅደም ተከተሉን ጥሩ ነው ያን ሊመዝን ይችላል፡፡ እንጂ አሁን ከአንድ የቃለ ጉባኤ ውስጥ የትኛው ነው ቀረ የትኛው ገባ ብሎ እንትን ማለት እኔ ትክክለኛ ይመዝናል ብዬ አልገምትም፡፡

አወያይ፡ በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ እንጂ በማመንጨት ደረጃ የመመዘን አቅሙን ትጠራጠራላችሁ? ይለካል ብላችሁ አታምኑም?

መምህር$_{24}$፡ አዎ እኔ እንደዚያ ነው የማስበው፡፡

*መምህርት$_{23}$፡*ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ማምጣት የማይገባቸው ተማሪዎች ኤ አምጥተው እናገኛቸዋለን፡፡ ቢ ማምጣት የሌለባቸው ቢ ያመጣሉ በማጠቃለያ ፈተናው፡፡

መምህር$_{25}$፡ ሙሉ በሙሉ አይለካም፡፡ የተወሰነ ግን የሚያሳየው ነገር አለ ጎበዙን ምንጊዜም ታየዋለህ በዚያ ሙሉ በሙሉ ግን እ... ተማሪው በዚያ ደረጃ ይገለጻል ማለት ይከብዳል

7.3 ከቋንቋው ስርዓተ ትምህርት ጋር ፈተናው ይጣጣማል ?

መልስ ይጣጣማል በጋራ፡፡

መምህርት$_{24}$፡ *የመግለፅ ችሎታቸውን የማይመዝን መሆኑ ነው እንጂ ልዩነቱ ይጣጣማል፡፡ አወያይ ከመልመጃዎቹ ጋር ፈተናው ይያዛል ብላችሁ ታምናላቻሁ?*

መልስ (አዎ በጋራ

መምህር$_{24}$፡ *ቃል በቃል አይምጣ እንጂ ያው ነው፡፡*

8 የተማሪዎችን የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት (score) የተሻለ ለማድረግ በትምህርት ቤቱ ደረጃና በግላቸው ምን ምን ጥረት እንደሚደረግ እንዲያስረዱ ለተጠየቁት የሰጡት ምላሽ፡፡

መምህር$_{25}$፡ አዎ! ትምህርት ቤቱ፣ ወረዳው፣ ክልሉ የሚያደርገው ነገር የለም ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ ምንም የሚያደርገው ነገር የለም፡፡ ዲፓርትመንታችን ግን ሌት ተቀን ነው የሚሰራው ለዚህ ውጤት ምን እናደርጋለን አንደኛ በየቀኑ የምናስተምራቸው መልመጃዎች በየቀኑም ባይሆን በየሳምንት ቅድም መምህር 22 እንደገለጸው እንወያያለን፡፡ እንዴት በምን ዓይነት ዘዴ እናስተምር በምን ዓይነት እናስተምር ብለን እንወያያለን፡፡

ሁለት እኔ *መምህር*$_{22}$ ገብቼ ሱፐርቫይዝ አደርገዋለሁ፡፡ *መምህር*$_{22}$ እኔን ሳስተምር ሱፐርቫይዝ ያደርገኛል፡፡ እ! ሱፐርቪዥን አለን፤ የውስጥ ሱፐርቪዥን በዚያ እንመካከራለን፡፡ ሶስት ለማብቃት/ተማሪዎችን ለማብቃት ተጨማሪ ክፍለ ጊዜያትን በሰፋት እንሰጣለን፡፡አራት የሥነ-ፅሁፍ ክበብ አለ፡፡ በሥነ-ጽሁፍ ክበባችን ተማሪዎቻችን የተሻለ ተናጋሪ፣ የተሻለ አንባቢ፣ የተሻለ አቅራቢ እንዲሆኑ በስፋት እንሰራለን፡፡ አምስት እቅዳችንና ያቀድነው ጥላናችን በአግባቡ በአግባቡ ምንም ሳይቀር በየዓመቱ እንፈፅማለን፡፡ ስለዚህ ከዚህ ከዚህ አንጻር አሁን የእኛ ትምህርት ቤት በተደረገው የስነ-ጽኑፍ የምናምን ውድድር ባለፈው ሽልማትን የተወሰነ ነገር አግኝተናል፡፡ ብዙ ነገሮችን እንፈፅማለን፡፡ እንጥራለን፣ እንወያያለን፡፡ በየሳምንቱ ስብሰባ አለን፡፡ በየ15 ቀኑ ስብሰባ እናደርጋለን፡፡ ስለትምህርቱ መሻሻል ስለሜትዶሎጂያችን፣ በምን አይነት አቀራረብ ብናቀርበው የተሻለ እንደሚሆን እየተነጋገርን ስለምንሰራ በእኛ ዲፓርትመንት የተሻለ አፈፃፃም አለ:: አስባለሁ፡፡

መምህር$_{24}$፡ ይችን እንትኗን ለማጠናከር ያክል የመረዳዳቱን ነገር አናፍርም በቃ ልሳሳት እችላለሁ ሰው ነኝ፡፡ ይህ እንዴት ነው አይ ዛሬ ሳስተምር እኔ ተሳስቻለሁ፡፡ ነገ ከእሷ ጋር ተነጋግሬ ላርም እችላለሁ፡፡ የእኛን መከባበር ሳይሆን የልጆቻችን ውጤት ነው የምንመለከተው እነሱ የተሳሳተ ግንዛቤ ይዘው መሄድ የለባቸውም የሚለው ነገር ትኩረት የምንሰጠው ነው፡፡ እ! ይብዛም ይነስም በተለይ ማየት ለተሳናቸው ተማሪዎች እንደዚህ እንደዚህ አትኩሩ በማለት ለእኔ ማየት ለተሳናቸው የተለየ እንትን እናደርጋለን፡፡

እ በዚህ ዓመት በሴቶች ፕሮግራም ታቅዶ ሀሙስ ሀሙስ ቀን ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ እንሰጥ ነበር፡፡ ከትምህርት ሰዓታችን ውጪ፡፡ ሌላው አሁን እኮ ቅድም ያልነው ነገር እነዚያን ነገሮች እንኳ መስራት ሳንችል ክፍለጊዜው አነስተኛ ስለሚሆን ተጨማሪ ነገር የምናሰራው በትርፍ ጊዜያች ነው፡፡ የቡድን ስራም ቢሆን ምናምን ቢሆን ያንን የምናሰራው በትርፍ ጊዜያችን ነው፡፡ እነሱን ቀጥረን፡፡ እንዲያው የነሱ ፈቃደኛ አለመሆን ለምሳሌ *መምህር* 22 አንድ ጊዜ ጠርቶ ሁለት ተማሪ መጣለት፡፡ እና እንደዚህ ለምን እንደክማለን ብለን ነው እንጂ ውጤታችሁ ለማሻሻል በእኛ በኩል ፍላጎት አለን፡፡ ልጆቹ እንደተባለው ቅድም አቶ ተስፋዬ ገሰሰ ናቸው አዝረክርከው እንደሚናገሩት አዝርክርከው ይፅፉሉ እንደሚሉት ያን በማድረጋቸው እንትን የሚሉትት ነገር አላቸው፡፡ ትንሽ ቀለል ያለ ትኩረት ስለሚሰጡት እንጂ በዚህ በኩል ጥረት እናደርጋለን፡፡

መምህር$_{25}$፡ ሌላ የረሳኋት አለች የቋንቋ እና የመማር ሂደትን ለማሻሻል እ የጥናት ምርምሮችም እናደርጋለን፡፡

መምህርት$_{23}$፡ውጤታቸውን ለማሻሻል የመለማመጃ ጥያቄዎች እንሰጣቸዋለን፡፡ የ10ኛ ክፍል የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ይሰራላቸዋል፡፡ ከሌላ ትምህርት ቤት የተሰጡ የሞዴል ፈተናዎች ይሰሩላቸዋል፡፡ ራሳቸውም እንዲሰራላቸው ይጠይቃሉ፡፡

አባሪ 15፤ ናሙና የዞን ትምህርት ባለሙያዎች ምላሾች

ከዞን ት/መምሪያ የስርዓተ-ትምህርት ክፍል ኃላፊ/የትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ ኃላፊና የፈተና ክፍል ተወካይ (የዕቅድ ክፍል) ተጠሪ ጋር የተደረገ የቡድን ውይይት

1. የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የሚሰሩ ስራዎችን በሚመለከት የሰጧቸው አስተያየቶች

ባለሙያ ፩ - በትምህርት ጥራት ዙሪያ በዞንም እንደ ሀገርም እየተሰራ ባለው ሁኔታ ትምህርት ጥራት የወቅቱ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያግዙ 6 መርሃ ግብሮች በሀገር ደረጃ ተቀርፀው እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ወርደው እየተተገበሩ ነው፡፡ እነሱም፡ የትምህርት ቤት መሻሻል፣ የመምህራን ልማት፣ የICT፣ የስርዓተ ትምህርት መርሀ ግብር ናቸው፡፡ የእነዚህ መርሀ ግብሮች የእያንዳንዳቸው ተልዕኮ ትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ብሎም የተማረውን ውጤት ማሻሻል ነው፡፡ ከዚህ በፊት ትኩረት ተደርጎ የሚሰራው የትምህርት ተደራሽነት ላይ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ግን ጥራት ላይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በርካታ ተማሪዎች ጎልተው እየወጡ (outshine) ነው፡፡

ባለሙያ ፪- የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ 6 package ተቀርፀው ተግባራዊ እየተደረጉ ሲሆን በተለይም ሲፕ (SIP) ላይ የተማሪ ውጤት ግብ ተጥሎ ልዩ ልዩ ተግባራት እየተከናወኑ ነው፡፡ በስርዓተ ትምህርት ብልጸጋም የፈተና ስርዓት የራሱ አካሄድ አለው፡፡ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ሶስት መለኪያዎች (standard) ወጥተዋል፡፡ ፈተና እና ምዘና ከሆነ በሂደትና በውጤት የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡ አሁን የምዘና ስርዓት ስታንዳርዱን ለማስጠበቅ እየሰራ ያለው ነገር በጉድኝትና በወረዳ ደረጃ መለኪያ ፈተና እያዘጋጁ ነው፡፡ እንደ ዞንም የ2ኛ ደረጃ የ9ነኛ ክፍል ፈተና አዘጋጅተናል፡፡ ልዩ ልዩ የብቃት መለኪያ ፈተናዎች እየተዘጋጁ በክፍል ፈተና እና በብሔራዊ ፈተና መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ ስራዎች ተጀምረዋል፡፡ እና ይህንን ስራ አልመን እየሰራን ነው፡፡

ጥያቄ 2. የተሻሉ ተማሪዎችን ለማፍራት የሚሰሩ ስራዎች ምንድን ናቸው?

ባለሙያ ፩፡ የተሻሉ ተማሪዎችን ለማፍራት ፕሮሞሽን ፖሊሲ በክልል ደረጃ የተወሰነ ነው፡፡ ሰሜን ጎንደርም ሆነ ደቡብ ጎንደር የራሱ የሆነ የፕሮሞሽን ፖሊሲ የለውም፡፡ በአፈፃፀም ደረጃ ግን የተሻለ አፈፃፀም ያለው የኛ (ሰሜን ጎንደር) ነው፡፡ ሌላው ተማሪዎችን ለማብቃት የሚሰራ ነገር ማጠናከሪያ ትምህርትን በመስጠት ዙሪያ ተማሪዎችን በተለየ መንገድ ለማብቃት የሚያስችሉ የተለያዩ ፕሮግራሞች የሚዘረጉበት ሁኔታ አለ፡፡ እና ፉክክርም አለ፣ የሽልማት ሥነ-ስርዓትም አለ፣ ሽልማትን በተመለከተ በየዓመቱ የምናደርገው ነገር ስፖንሰር እያፈላለግን በናሽናል ኤግዛም ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን ወደ ዞን እየሳብን ሽልማት የምንሰጥበት አሰራር አለ፡፡ እና በዛ መንገድ ተነሳሽ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ የተማሪዎች ውጤት የተሻለ እንዲሆን ስራ እየተሰራ ነው ያለው፡፡

ባለሙያ ፪፡ በተጨማሪም ክፍተቱን ለመሙላት ሞዴል የብቃት ፈተና እየተሰጠ ነው፡፡ የማጠናከሪያ ትምህርት ስርዓት ተዘርግቷል፡፡ የማበረታቻ ስርዓት ገባ ወጣ ቢልም አለ፡፡ የመምህራንን የማስተማር ብቃት ለማጎልበት በጥናትና ምርምር እንዲሳተፉ መደረጉ በዚህ ዓመት የቀረቡ ጥናቶችች በርካታ ናቸው፡፡ ሌላው ደግሞ ስታንዳርዱ ወጥቷል፡፡ የተማሪ ውጤት ግብ ምን መሆን አለበት የሚለው ላይ አልመን ነበር የምንሰራው፡፡ 50 ፐርሰንት ተማሪ ወይም ሁሉም ተማሪ በሁሉም የትምህርት አይነት 50 እና በላይ ያመጣሉ፡፡ ከዛ በመቀጠል ደግሞ 30 ፐርሰንት ተማሪ 75 ፐርሰንት እና በላይ ያመጣል ተብሎ ነው የሚጠበቀው፡፡ ቀሪው 15 ፐርሰንት ደግሞ 85 ፐርሰንት እና በላይ ያመጣል ተብሎ ታቅዶ ነው እየተሯሯጥን ያለነው፡፡ ስለዚህ ይሄ ሬንጅ ለስራ የሚያነሳሳና የትምህርት ጥራት ለማረጋገጥ የተማሪ ውጤት ለማሻሻል አልመን እየሰራን ነው፡፡

ባለሙያ ፩፡ የትምህርት ጥራትን ከፍ ለማድረግ ለምሳሌ continous assessment በፊት የነበረው 60 በ40 ነበር 60ው መምህሩ ውጤት እየሰራ የሚሄድበት 40 ደግሞ ፈተና እየተሰጠ የሚገመገምበት ነበር፡፡ አሁን ግን the reverse እንዲሆን የማድረግ ነገር አለ ማለት እዛ ጋር ያለውን biased የሆነውን የውጤት አሰጣጥ at least minimize ያደርገዋል ከሚል አንጻር ነው፡፡ ለትምህርት ጥራት ቁልፉ መምህር ነው፡፡ ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ ትልቁ ነገር ግብዓት ሳይሆን መምህሩ ነው፡፡ ምክንያቱም እዛ ላይ ተጨባጭ የሚያደርገው ምንድነው መምህሩ active ከሆነ፣ መምህሩ ተግባሩን የሚፈፅም ከሆነ፣ ያለመፅሀፍ ተማሪዎችን ማብቃት ይቻላል፡፡ ይህን በአባቶች አይተናል፡፡ በቤተክህነት አይተናል፡፡ መርጃ መሳሪያ ሳይጠቀሙ ማንበብ መጻፍን የሚያስችሉበት ሁኔታ አለ፡፡ እና ለምንድነው የማን ችግር ነው? የግብዓት ችግር ነወይ? ግብዓት ሊሟላ ይገባዋል ግን መሰረታዊ ነገር አይደለም፡፡ ቁልፉ ያለው መምህሩ ላይ ነው፡፡

ጥያቄ፡ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ መስጫ መስፈርቶች በተመለከተ

ባለሙያ ፪፡ አንዱ ክራይቴሪያ የተማሪ ውጤት ትንተና፣ ሌላው ከሪፖርት አላላክ፣ የህብረተሰብ ትምህርት ቤት ግንኙነት ናቸው አሁን ግን ከግብዓት ከሂደትና ከውጤት ጋር የተያያዙ መለኪያዎች (standard) ወጥተዋል፡፡

ጥያቄ፡ የቋንቋ መምህራን በትምህርት ፖሊሲውና በስርዓተ ትምህርቱ ማዕቀፍ መሰረት ትኩረታቸውን የቋንቋ ክሂሎች ላይ አድርገው እንዲያስተምሩ ምን ምን ድጋፍ ይደረግላቸዋል?

ባለሙያ ፫፤ መጽሐፉ ላይ ለስኪሎች ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ንባብ፣ ፅሁፍ ፈተና አወጣጡንም ስናይ እነዚህን ይይዛል practically ግን listening እና የመሳሰሉትን exercise ልምምድ የሚያደርጉበት አለ ለማለት አይቻልም፡፡ ሌላ የኮሙኒኬሽን ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ብዙ አይደለም፡፡ ግን ሂደቱ ላይ ታያለህ፡፡ አሁን ፈተናም ላይ ስታይ የኮሙኒኬሽን ክፍል ይኖራል፡፡ ግን ያ በተግባር አሁን በእንትን የሚያሳዩት አይደለም፡፡ ጥያቄውን ሊመልሱት ይችላሉ፡፡ ግን practically መሰረቱ ላይ የሚቀር ይመስለኛል፡፡ ቲዎረቲካል የሆነውን ነገር እንትን ከማድረግ ባለፈ practically ይህ ነገር ወደታች አለ የሚል እምነት የለኝም፡፡

ባለሙያ ፭፡ ወደ አፈፃፀም ስንገባ ግን በየጊዜው የበቁ እና ያልበቁ ተማሪዎችን ላኩ ስንል የሚላክልን መረጃ የሚያነቡ፣ የሚፅፉ፣ የሚያስሉ ተብሎ ነው የሚላከው፡፡ይሄ ማለት 4ቱን ስኪሎች ተግባራዊ ማድረጋቸውን እየተከታተልን ነው፡፡ የ EGRA ጥናት አሁን እሱ የኛ ክልል፣ ዞን ያለበትን ችግር እና የማንበብና የመፃፍ ችግር እንዳለባቸው ልጆቻችን ያሳያል፡፡ ከዛ ከችግራችን እንዴት እንውጣ ብለን የተለያዩ ስልጠናዎችን እየሰጠን ነው፡፡

ባለሙያ ፫፡ አሁን ስርዓቱ መዘርጋቱና አቴንሽኑ ከትምህርት ፖሊሲው ነው የሚጀምረው፡፡ ለቋንቋ የተሰጠው እንትን ፖሊሲውም ላይ አለ፡፡ ነገር ግን አሁን በትክክል የተጠና ባይሆንም እኔ ቋንቋው እንደውም decline እያደረገ ነው፡፡ አሁን በአብዛኛው እንትን ላይ የምናየው ምንድነው ማመልከቻ እንኳን መፃፍ አይችሉም፡፡ Even graduate አድርገው መጥተው እንኳን እዚህ ለመቀጠር apply አድርጉ ስትል እንኳ ማመልከቻ ፅፈው የሚመጡት በጣም የሚያስቅ ነው፡፡ ክላስ ሱፐርቪዥን ገብተን እንትን ስንል ያሳፍራ ኮሚዩኒኬሽኑ፡፡ ተማሪዎችም ራሱ ፎርም ሲሞሉ እናያለን 12ኛ ክፍሎች ፎርም ሲሞሉ ስማቸውን እንኳን በትክክል አይሞሉም፡፡ ስለዚህ አሁን ይህ የመጻፍ፣ የመናገር ስኪላችን አሁን ምን ላይ ነው የሚገኘው የሚለው ነገር አሳሳቢ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ትኩረቶቹ መዘርጋታቸው አንድ ነገር ሆኖ ለውጡ ግን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ ድሮ የነበረው ተማሪ እና የአሁኑ ስናነፃፅረው እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ ትንሽ አስቸጋሪ ነው በጣም ብዙ መስራት የሚጠበቅ ነው፡፡

ባለሙያ ፩፡ ችግሩ የተማሪው ብቻ ሳይሆን የመምህሩም ነው፡፡ ይህ ችግሩ የሚመጣው ተማሪው ላይ ብቻ ሳይሆን ከላይ እስከ ታች ያለና የቆየ ነው፡፡ የመምህሩን አቅም ገንብቶ የተማሪውን አቅም መገንባት ከተቻለ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡ ባለሙያ ፫ ያነሳው ነገር እኮ በየቦታው ሄደን የማያነብ፣ የማይፅፉ ልጆች እናገኛለን፡፡ በቃ ዝም ብሎ ቁልጭ ቁልጭ የሚሉ ለdropout አንዱ ትልቁ ችግር academic እንትናቸው ዝቅተኛ ስለሆነ ለምን እዛ ሰፈር አረጋለሁ ከዛ ከዛ ተመልሼ ለምን አልሄድም ካስገባችሁኝ ተመልሼ 1ኛ ክፍል ልግባ አለበለዚያ ለስም ለምንድነው 4ኛ ክፍል ተብዬ እቀመጣለሁ፡፡ አራተኛ ክፍል ሲደርሱ ለ4ኛ ክፍል profile ያላሟሉ እንትኖች 1ኛ ክፍል የሚገቡበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

ጥያቄ፡ የቋንቋ መምህራን ቋንቋ ለማስተማር የሚያስችል ስልጠና አግኝተው ያውቃሉ ወይ?

ባለሙያ ፩፡ አማርኛ ላይ የለም፡፡ ለዚህ ተብሎ የተለየ ኦቴንሽን አልተሰጠም፡፡

ጥያቄ 7፡ በዞኑ ጥሩ ውጤት የሚመጣበት ትምህርት የቱ ነው

ባለሙያ ፩፡ ዝቅተኛ ውጤት የሚመጣበት አንዱ ሂሳብ ነው ቀጥሎ ፊዚክስ ነው፡፡ ቀጥሎ እንግሊዝኛ ነው፡፡ በ3ኛ ደረጃ እና እየተሻለ ስትመጣ ደግሞ ስነዜጋ ነው የተሻለ የምታገኘው ስነዜጋ ትምህርት ላይ እንዴት እንደሆነ አላውቅም ጥሩ act ያደርጋሉ፡፡ ባዮሎጂ ላይ፣ አማርኛ ላይ እነዚህ እነዚህ ትምህርቶች ላይ አለ አሁን አሳይሃለሁ ሰነዱን፡፡ የመጨረሻዎቹን ውጤት የሌላቸው እንትን ግን ሂሳብ ነው ቀጥሎ የከፋው ትምህርት ፊዚክስ ቀጥሎ እንግሊዝኛ ነው፡፡

ጥያቄ 8፡ የመምህራን section ብዛትን በተመለከተ

ባለሙያ ፫፡ ለብሄረሰብ ቋንቋ የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በሚመለከት የክልሉ መንግስት ትምህርት ቤቶች አስፈላጊ ለሆኑት ትምህርቶች ያውሉት ነው የሚለው፡፡ አንድ Specifically ለቋንቋ ያውሉት አይልም፡፡ የአማራ ክልል ይህን አይልም፡፡ ስለዚህ እኛ አስፈላጊ የምንላቸው ሂሳብና ሳይንስ የትምህርት ዓይነቶች ስለሆነ እነዚህ ክፍለ ጊዜ አብዛኞቹ ት/ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ለሂሳብና ሳይንስ እንጂ ወደ ቋንቋ አይደለም፡፡

ስታንዳርዱ ምንድነው አንድ መምህር በሳምንት 30 ፔሬድ ማስተማር አለበት ይላል፡፡ ግን አሁን በተጨባጭ 30 ፔሬድ በሳምንት የሚያስተምር የለም፡፡ በተለይ 2ኛ ደረጃ ስንመጣ 30 ፔሬድ በሳምንት የሚያስተምር የለም፡፡አብዛኞቹ 12 እና 18 ነው የሚይዙት፡፡ አንዳንድ ወረዳ 30 ነው የሚለውና በዚህ አግባብ እንሂድ ይላል፡፡ ይሄኛው አያስኬድም ተከታታይ ምዘና በራሱ ችግር ስለሆነ ይህንን የፔሬድ ድልድል ግምት እናስገባለን፡፡ ከዛ ጋራ እያስተያየን ነው የመምህራን ምደባ የምናካሂደው፡፡ያው ችግር ሲያጋጥም 30 ክ/ጊዜ አልያዝክም ብሎ ሊጭነው ይችላል፡፡ የተባለው ትክክል ሆና አንድ section ሁለት section የያዙ መምህራን አሉ፡፡ ሩቅ ትምህርት ቤቶች አካባቢ ስንሄድ 2 section ብቻ የያዘ ታገኛለህ እዚያ ላይም አይሰራም፡፡ አሁን መጀመሪያ በአስተሳሰብ እንጂ የፔሬድ ጫናው ብቻ አይደለም፡፡ በአስተሳሰብ መጀመሪያ ይህን እንሰራዋለን፡፡ ስራችን ነው ብሎ የማምጣቱ ነገር ችግር አለ፡፡ ሁለት ፔሬድ ይዞ ቁጭ ብሎ ታገኘዋለህ፡፡ ምንም አይሰራም፡፡ እና አስተሳሰቡ ላይ መስራት የሚሻል ይመስለኛል፡፡

ባለሙያ ፪፡ ተጨማሪ የምሰጠው እዛ ላይ ያለው ነገር ብዙ ት/ቤቶች አሉ መያዝ ካለባቸው ሎድ በታች የያዙ፡፡ ግን ሲሰሩ እያየን አይደለም፡፡ በመሰረቱ አንድ መምህር በሳምንት መስራት የሚገባው 40 ሰዓት ነው፡፡ 22.5 ሰዓቱን ክፍል ውስጥ ይገባል 12.5ቱ ደግሞ ከክፍል ውጪ የሚሰሩ ናቸው፡፡ ከክፍል ውጪ የሚሰሯቸው ተግባራቱ ማለት የተማሪ ደብተር ማረምን፣ በክበባት መሳተፍን የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውንባቸው ናቸው፡፡ ይሄ 40 ሰዓት ከሳይንሳዊ እንትን ጋር ተያይዞ በቀን 8 ሰዓት በሳምንት 5 ቀን 5 x 8 = 40 ሰዓት መሰራት አለበት የሚለው መምህሩ ተመድቦለታል፡፡

አባሪ16፤ በመምህራን የተሞላው የጽሑፍ መጠይቅ ክሮቫሽ አልፋ

Cronbach's Alpha	Cronbach's Alpha Based on Standardized Items	N of Items
.802	.812	29

Reliability Statistics

Cronbach's Alpha	Cronbach's Alpha Based on Standardized Items	N of Items
.802	.812	29

አባሪ 17

ተማሪዎች ቋንቋውን በክፍል ውስጥ ስለሚማሯቸው ንዑሳን የትምህርቱ ክፍሎች/ ያላቸው ግንዛቤ በመቶኛ ስሌት ሲታይ

ተላውጠዎች	በጭራሽ	መቶኛ	አልፎ አልፎ	መቶኛ	ብዙ ጊዜ	መቶኛ	በጣም ብዙ ጊዜ	መቶኛ
11.በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚከተሉትን የቋንቋ ክሂሎችና የሰዋሰውና የሥነ-ፅሁፍ ክፍሎች ምን ያህል ትማራላችሁ /ታከናውናላችሁ?								
11.1የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን በተመለከተ	574	37.9	112	36.9	55	18	15	5
11.1.1 በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ውይይቶችን ማካሄድ፣	111	36.6	118	38.9	54	17.8	14	4.6
11.1.2 አካባቢያዊ፣ ወቅታዊና አገራዊ ጉዳዮች ላይ በቂ መረጃዎችን ከልዩ ልዩ ምንጮች አሰባስቦ ክርክር ማካሄድ፣	159	52.5	103	34.0	26	8.6	11	3.6
11.1.3 በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች መልዕክትን ግልፅ የሚያደርጉ የድምፅና የአካል እንቅስቃሴዎችን... በመጠቀም የዱብዳ ንግግር ማድረግ፣	135	44.6	108	35.6	37	12.2	15	5.0
11.1.4 በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዝግጅት በማድረግና መልዕክትን ግልፅ የሚያደርጉ የድምፅ እና የአካል እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም የቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር ማድረግ፣	128	42.2	98	32.3	59	19.5	15	5.0
11.1.5 በተወሰነ ርዕስ ንግግር ማድረግ	41	13.5	132	43.6	97	32.0	21	6.9
11.2 የንባብ ክሂልን በተመለከተ	75/3	8.3	241/ 3	26.5	348/3	38.3	234/ 3	25.7
11.2.1 በሚነበብ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋናና ጠቃሚ ዝርዝር ሀሳቦችን መለየት፣	15	5.0	69	22.8	130	42.9	82	27.1
11.2.2 በሚነበቡ ጽሑፎች ውስጥ ለሚገኙ አዳዲስ ቃላት፣ በአገባባቸው መሰረት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን መስጠት፣	15	5.0	62	20.5	118	38.9	105	34.7
11.2..3 ከልዩ ልዩ መግለጫዎች (ከሥዕል፣ ከሰንጠረዥ...)መረጃዎችን ማግኘት፣	45	14.9	110	36.3	98	32.3	47	15.5
የመጻፍ ክሂል	**483/7**	**22.8**	**705/7**	**33.2**	**560/ 7**	**26.4**	**323/7**	**15.2**
11.3.1 ሥርዓተ ነጥቦችን (በጽሑፍ ውስጥ) በተገቢ ቦታቸው ማስገባት/መጠቀም	22	7.3	75	24.8	95	31.4	95	31.4
11.3.2 ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን በመገልገልና የአንቀጽ አጻጻፍ መርህን በመከተል የተለያዩ (ተራኪ፣ አወዳዳሪ፣ ገላጭ...) አንቀፆችን መጻፍ	34	11.2	83	27.4	117	38.6	68	22.4
11.3.3 የተለያዩ የሥራና ንግድ ነክ ደብዳቤዎችን መፃፍ ፣	149	49.2	106	35.0	33	10.9	13	4.3

ተላውጠ	በጭራሽ	መቶኛ	አልፎ አልፎ	መቶኛ	ብዙ ጊዜ	መቶኛ	በጣም ብዙ ጊዜ	መቶኛ
11.3.4 በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ዘገባ መጻፍ ፣	112	37.0	135	44.6	42	13.9	11	3.6
11.3.5 ማርቀቅ፣ ረቂቁን ማረም ፣መከለስና የድርሰቱን ዋና ጽሑፍ መጻፍ ፣	94	31.0	111	36.6	60	19.8	23	7.6
11.3.6 ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን ተገልግሎ መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ ያላቸው የተለያዩ (ተራኪ፣ ሥዕላዊ፣ ገላጭና አመዛዛኝ) ድርሰቶች መፃፍ፣	55	18.2	102	33.7	96	31.7	46	15.2
11.3.7 ከተለያዩ ንግግሮችና ዕሑፎች የሚገኙ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ፣	17	5.6	93	30.7	117	38.6	67	22.1
11.4 የሰዋሰው ዕውቀትን ለማጎልበት ከሚረዱ መሰረታዊ ሀሳቦች ጋር መተዋወቅ	28/2	4.6	103/2	17	220/2	36.3	236/2	38.9
11.4.1 የቋንቋ ምንነትን፣ አጀማመርንና ባህሪያትን መግለጽ ፣	18	5.9	60	19.8	121	39.9	93	30.7
11.4.2 የሀረግ አይነቶችን (ቅፅላዊ፣ ስማዊ፣ መስተዋድዳዊ፣ ተውሳክ ግሳዊ፣ ግሳዊ) መለየት፣	10	3.3	43	14.2	99	32.7	143	47.2
11.5ሀሳብንሥነጽሑፋዊ በሆነ መልክ የመግለፅ ችሎታን በተመለከተ	101/4	8.3	308/4	25.4	453/4	37.4	329/4	27.1
11.5.1 የፈጠራ ሥነ-ጽሑፍ ዘርፎችን (ሥነ-ቃል፣ ግጥም፣ ልቦለድ፣ ድራማ) መለየት፣	42	13.9	87	28.7	97	32.0	71	23.4
11.5.2 የፊሊጣዊ ንግግሮችን መልዕክት መረዳት፣	21	6.9	80	26.4	127	41.9	69	22.8
11.5.3 በተለያዩ ዘይቤዎች (በአነፃፃሪ፣ ተለዋጭ፣ ሰውኛ፣ ተምሳሌት፣ ግነት...) የቀረቡ አባባሎችን/ ሀሳቦችን መረዳትና ማብራራት፣	22	7.3	70	23.1	111	36.6	96	31.7
11.5.4 የልቦለድ አይነቶችን፣ አላባውያንና ቴክኒኮችን መለየት፣	16	5.3	71	23.4	118	38.9	93	30.7

አባሪ 18፡ በጥናቱ የተካተቱ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ናሙና

የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና ግንቦት ፳፻፬/2004 ዓ.ም.

የትምህርት አይነት መለያ:- 01 **የዚህ ጥራዝ መለያ:- 83**
የጥያቄ ብዛት:- 90 **የተፈቀደው ጊዜ:- 90 ደቂቃ**

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 1 እስከ ጥያቄ 6 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ከተሰጡት አማራጮች መካከል ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ምረጥ።

1. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መካከል በሀቅ ላይ ለተመሰረተ ሀሳብ የትኛው ምሳሌ ሊሆን ይችላል?

   A. ልቦለድ የግጥምን ያህል አንባቢን አይስብም ብል አልተሳሳትኩም።
   B. አጭር ልቦለድ እንደ ረጅሙ ሁሉ የልቦለድ አላባውያንን ይጠቀማል።
   C. አጭር ልቦለድ በሬዲዮ ሲተረክ የበለጠ ይማርካል።
   D. ከተውኔት ይልቅ ፊልም ማየት ያስደተኛል።

2. "እንዲህ እንደሱ አይነት አፍንጫ ያለው ሰው አላየሁም...እሰው ጉዳይ እየገባ የሚያሸት። " የሚለው አባባል አንድምታ ምንድን ነው?

   A. ሰውየው የማንንም ምስጢር ፈልፍሎ የሚያወቅ ነው።
   B. ሰውየው በመረጃ የተደገፈ ሀሳብ አቅርቦ ለማሳመን የሚጥር ነው።
   C. ሰውየው "የራሷ እያረረባት ያሰው ታማስላለች" የሚሉት አይነት ነው።
   D. ሰውየው በማያገባው ገብቶ ፈራጅ ለመሆን የሚቃጣው ነው።

3. አቶ ፈለቀ፣"በራስ መተማመን ጥሩ ነው። እራስን ሆኖ ለመኖር ያስችላል።የዚህ ችሎታ ባለቤት የሆኑ በርካታ ሰዎችን ተመልክቻለሁ።አብዛኛውን ጊዜ በራሳቸው ሀሳብ ስለሚመሩ በኑሯቸው ስኬታማ ናቸው።ስለዚህ..." አሉ።
   የአቶ ፈለቀን ንግግር ለመጨረስ የሚያስችለው ሀሳብ _____ነው።

   A. በራሳቸው ከማይተማመኑት ብዙ ልዩነት አላየሁባቸውም።
   B. ሰዎች ሁሉ በራስ መተማመን ቢኖራቸው መልካም ነበር።
   C. በራስ መተማመን ሰዎችን ለትእቢተኝነት ያጋልጣልና እንጠንቀቅ።
   D. ህይወታቸው በሰዎች ስለሚመራ ምስቅልቅል ያለ ነው።

4. ከሚከተሉት ሀሳቦች ውስጥ አንዱ አወያይ ነው::

A. ገበሬዎች ገበያ ተኮር ምርቶችን እንዲያመርቱ ለማድረግ የተለያዩ ስልቶች ተቀይሰዋል::
B. ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር ገንዘብ የመላክ አገልግሎት በተለያዩ ባንኮች በስፋት ይሰጣል::
C. አባቴ ከስራ ሲመለስ አትክልት መትከልና መንከባከብ ይወዳል::
D. ሩጫ ከአትሌቲክስ የስፖርት አይነቶች መካከል አንዱ ነው::

5. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መካከል አንዱ አከራካሪ ነው::

A. መስከረም ጠባና የነጎድጓድ ድምፅ ከጆሯችን እየራቀ ሲሄድ ፀሀይዋ ደምቃና ሞቃት ሆና ብቅ አለች::
B. የከባቢ አየር ለውጥ ብቸኛ መንስኤ ያደጉ ሀገሮች ወደ ከባቢ አየር የሚለቁት የተቃጠለ አየር ነው::
C. በከባቢ አየር ለውጥ የተነሳ የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎችን መከላከል የመንግስትም የህብረተሰብም የጋራ ግዴታ ነው::
D. ከየት እንደመጣ የማይታወቅ ደመና ሲጥል ሰማዩ ከብሩህነት ወደ ግራጫነት አየሩ ደግሞ ወደ ቀዝቃዛነት ተለወጠ::

6. ከሚከተሉት አባባሎች መካከል አንዱ ቀስቃሽ ነው::

A. አንድም ሰው በኤችአይቪ እንዳይያዝ፣ እንዳይገለልና እንዳይሞት ሁሉም ኃላፊነቱን ይወጣ
B. ኤችአይቪ በአለም ላይ መኖሩ ከተረጋገጠ ሰላሳ አመትታትን አስቆጠረ
C. ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ እናቶች ተገቢውን ህክምናና ምክር ከተከታተሉ ከቫይረሱ ነጻ የሆነ ልጅ ይወልዳሉ
D. በ2003 ዓ.ም. ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያዊያን የኤችአይቪ የምክርና የምርመራ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል

መመሪያ፦ ከተራ ቁጥር 7 እስከ 11 ድረስ ያለው ጥያቄ ቀጥሎ በቀረበው ምልልስ ላይ የተመሰረተ ነው። ስለሆነም የንግግሩን መንፈስ በመረዳት፣ ለየጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ምረጥ።

ጣይቱ፦ ምን አውቀህ ነው ታዲያ አንቶኔሊን ተክተህ፣ የአገርህ የኢጣሊያ ተወካይ ሆነህ፣ እንደዚህ ያለ ክብር የሚነካ ደብዳቤ ይዘህልን የመጣኸው?

ሳሊምቢኒ፦ እቴጌ በታም ይክርታ እኔ የመሰለው፣ ውቻሌ ውል አስራ ሰባተኛው ክፍል ልክ እንደ ኢታሊያኖ ኳንኳ፣«የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት፣የውጭ ጉዳይ ነገር ሁሉ፣በኢታሊያ በኩል ሊአረጉት እ-ሺ ብሏል» ብሎ ናው።

ጣይቱ፦ ትሰማኛለህ ሳሊምቢኒ?

ሳሊምቢኒ፦ አቤት እቴጌ!

ጣይቱ፦ ለመሆኑ የሀገሬን ታሪክ ታውቀዋለህ?

ሳሊምቢኒ፦ መቼም በመተኑ.....

ጣይቱ፦ ከንግሥተ ሳባ አንስተህ እስከ ትናንቱ አጼ ዮሐንስ ድረስ፣በሀገሩ ክብርና ነጻነት ለድርድር የሚቀመጥ የአበሻ መሪ ሰምተህ ታውቃለህ?

ሳሊምቢኒ፦ አልሰምቶም እቴጌ!

ጣይቱ፦ ታዲያ! የዱሮዎቹን እንኳን ቢረሳ!የትናንቶቹ አጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሐንስ ለእፍኝ አፈራቸው የነበራቸውን ስስት ዘንግቶ፣ ለኢትዮጵያዊ ክብራቸው የከፈሉትን የሕይወት ዋጋ ከሚዛኑ ደፍቶ፣ ዛሬ "እባካችሁ! ሀገሬን በእናንተ ስር አድርጉልኝ!" ብሎ የሚለምን፣ ምኒልክ የእነማን ልጅ ይመስልሃል! ትውልድስ ምን ይለናል! (ንዴታቸውን መቆጣጠር እየተሳናቸው ብድግ ይላሉ።) ትሰማኛለህ ሳሊምቢኒ.....

ሳሊምቢኒ፦ (ሁሉም ይነሳሉ) አቤት እቴጌ!

ጣይቱ፦ (በንዴት እየተንሳፈደዱ) እኔ ሴት ነኝ። ጦርነት አልወድም። ነገር ግን ሀገሬ እንደዚህ ያለ ክብር የሚነካ ዘለፋ ከምትሸከም ጦርነትን እመርጣለሁ!

ጌትነት እንየው፣ እቴጌ ጣይቱ፣34-35

7. ከላይ ከቀረበው ምልልስ ምን መረዳት ይቻላል?

A. ለተፈጠረው የሀሳብ አለመስማማት ምክንያቱ የዘር ልዩነት መሆኑን
B. ለተፈጠረው የሀሳብ አለመስማማት ምክንያቱ የቋንቋ ልዩነት መሆኑን
C. ለተፈጠረው የሀሳብ አለመስማማት ምክንያቱ የሀገር ጉዳይ መሆኑን
D. ለተፈጠረው የሀሳብ አለመስማማት ምክንያቱ አለመከባበር መሆኑን

8. ስለሳሊምቢኒ የአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም ምን ማለት ይቻላል?

A. ሳሊምቢኒ አማርኛ ቋንቋ አጠቃቀሙ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ ታይቶበታል::
B. ሳሊምቢኒ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋው ቢሆንም በሚገባ አዳብሮታል::
C. ሳሊምቢኒ በአማርኛ ቋንቋ ችሎታው የተነሳ ከእቴጌ ጋር መነጋገር አልቻለም::
D. እንደሳሊምቢኒ ያለሰው ሁለተኛ ቋንቋውን አብሮ በመኖር መልመድ አይችልም::

9. የእቴጌ ንግግር ድምፀት ምንድን ነው?

A. ትካዜ
B. ትዝብት
C. ሀዘን
D. ቁጣ

10. ከምልልሱ ስለእቴጌ ምን ማለት ይቻላል?

A. እቴጌ ሀገራቸውን የሚወዱ ቆራጥ ሴት ነበሩ::
B. እቴጌ በሴትነታቸው በሳሊምቢኒ ተንቀው ነበር::
C. እቴጌ ከሰውነታቸው ይልቅ ሴትነታቸው አይሎባቸው ነበር::
D. የእቴጌ የአመራር ብቃት ጉድለት ይታይበት ነበር::

11. በሳሊምቢኒና በእቴጌ መካከል ለተከሰተው አለመግባባት መነሻው ምን ነበር?

A. ሁለቱ ሰዎች በሚጠቀሙበት ቋንቋ እኩል ችሎታ ያልነበራቸው መሆኑ
B. የሳሊምቢኒ አስመሳይነትና ተለማማጭነት
C. የእቴጌ ግንፍልተኛ መሆንና የአመራር ድክመት
D. ሳሊምቢኒ ያመጣው ደብዳቤ ይዘት የኢትዮጵያን ፍላጎት ያሟላ አለመሆኑ

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 12 እስከ 34 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጫ::

12. "ወርቅነሽ <u>በጣም ወፍራም</u> ልጅ አዝላ መጣች::" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት የትኛውን ሀረግ ያመለክታል?

A. ቅጽላዊ ሀረግ
B. ግሳዊ ሀረግ
C. ስማዊ ሀረግ
D. መስተዋድዳዊ ሀረግ

13. "ጎረቤታችን ራሱን እስኪስት ድረስ ጋኗ በጠዋቱ ለምን እንደሚጠጣ ይገርመኛል::" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ከየትኛው የቃል ክፍል ይመደባል?

A. ግስ
B. መስተዋድድ
C. ቅጽል
D. ተውሳከ ግስ

14. "ቆራጥና ጎበዝ የሆኑ ሰዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች የመወጣት ብቃት አላቸው::" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የስም ገላፊ _____ነው::

A. ቆራጥና ጎበዝ የሆኑ
B. ቆራጥና ጎበዝ
C. ቆራጥና ጎበዝ የሆኑ ሰዎች
D. ጎበዝ የሆኑ ሰዎች

15. ተራ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?

A. አርቆ አሳቢ የሆኑ ሰዎች የማመዛዘን ችሎታ አላቸው::
B. ወንዝ ተሻግሮ የመጣ ጠላት ሳይገድል አይመለስም::
C. ታናሽ እህቴ በትላንቱ መርከብ ወደ ውጪ ሀገር ሄደች
D. በሀገሬ ማር የተጣለው ጠጅ ተጠጥቶ አይጠገብም::

16. "በነጋዴዎቹና በሸማቾቹ መካከል የተፈጠረውን ፍጥጫ ማብረድ ካልተቻለ፣ የኑሮ ውድነት በጣም ሊንር ይችላል።" በተሰመረበት ቃል ውስጥ ጠብቆ የሚነበበው ድምጽ የሚገኝበት ሆሄ የትኛው ነው?

A. /ጥ/
B. /ጭ/
C. /ፍ/
D. /ጫ/

17. "ኑሮህ ለአደጋ እንዳይጋለጥ ምን አይነት ጥንቃቄዎችን ታደርጋለህ?" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የትኛውን ይገልጻል?

A. ሁለተኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣ተባእታይ ጾታ
B. አንደኛ መደብ፣ ብዙ ቁጥር፣ተባእታይ ጾታ
C. ሁለተኛ መደብ፣ብዙ ቁጥር፣ተባእታይ ጾታ
D. ሶስተኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣አንስታይ ጾታ

18. "እናቴ ብዙ ደክማ የሰራችው ቤት በአነስተኛ ዋጋ ተሸጠ።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ያለው ግሳዊ ሀረግ _____ ነው።

A. በአነስተኛ ዋጋ
B. እናቴ ብዙ ደክማ
C. በአነስተኛ ዋጋ ተሸጠ
D. የሰራችው ቤት

19. "አቶ ከበደ ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ሀገር ቤት ሄዱ።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ምን ዓይነት ሀረግ ነው?

A. ቅጽላዊ ሀረግ
B. ግሳዊ ሀረግ
C. ስማዊ ሀረግ
D. መስተዋድዳዊ ሀረግ

20. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ትክክል ነው።

A. ንቦች በቋንቋ የሚግባቡ ማህበራዊ እንስሳ መሆናቸው ይታመናል።
B. የቋንቋ ባለቤት የሆነው ብቸኛ ማህበራዊ እንሰሳ ሰው ነው።
C. ወፎች ማለዳ ተነስተው ዝማሬ የሚያሰሙት ቋንቋ ስላላቸው ነው።
D. እንስሳት ቋንቋ ስላላቸው በራሳቸው ቋንቋ ሰላምታ ይለዋወጣሉ።

21. "ሙስና ውስጥ የሚዘፈቁ ሰዎች ለሀገራቸው የማይቆረቆሩ ስግብግቦች ናቸው::" በሚለው አረፍተነገር በተሰመረበት ቃል ውስጥ _____ነፃ ምእላድ ነው::

A. /-ሞች/
B. ስግብግቦ
C. ስግብግብ
D. /-አች/

22. "ከትምህርት ቤታችን መምህራን መካከል ሶስቱ ፈረሶች እንደገዙ ሰማሁ::" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ስንት ጥገኛ ምእላዶች ይዟል?

A. ሶስት
B. አንድ
C. አራት
D. ሁለት

23. በቃላት አደራደር ስርአቱ ትክክለኛነት ተገቢ መልእክት የሚያስተላልፈው የትኛው አረፍተነገር ነው?

A. ሴቶቹ የተቀቡት መዓዛ የሽቶ ያውዳል::
B. ሴቶቹ የተቀቡት የሽቶ መዓዛ ያውዳል::
C. ሴቶቹ የተቀቡት ሽቶ መዓዛው ያውዳል::
D. ሴቶቹ ዮተቀቡት ሽቶ የመዓዛ ያውዳል::

24. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ ውስብስብ ነው::

A. ታታሪ ገበሬ በርካታ የጓሮ አትክልት ለመትከል ይጥራል::
B. ምርጥ ዘር የተጠቀሙ ገበሬዎች የተትረፈረፈ ምርት አገኙ::
C. ቅድመ አያቶቻችን ስራ ወዳድ፣ ታታሪና ጀግና ያደንቁ ነበር::
D. ጎበዝ ተማሪዎች በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ያገኛሉ::

25. በትክክለኛው የቃላት ምርጫ የተገነባው አረፍተነገር የትኛው ነው?

A. የንግድ ምንስቴር ምኒስቴር ዴኤታ ለሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ሽልማት ሰጡ::
B. የንግድ ምንስቴር ምኒስትር ዴኤታ ለሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ሽልማት ሰጡ::
C. የንግድ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ለሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ሽልማት ሰጡ::
D. የንግድ ሚኒስቴር ምኒስትር ዴኤታ ለሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ሽልማት ሰጡ::

26. "የእግር ኳስ አጫዋች ዳኞች <u>ፍትሀዊ</u> መሆን እንዳለባቸው ይነገራል::" በሚለው አረፍተነገር በተሰመረበት ቃል ውስጥ የሚገኘው መድረሻ ምእላድ ምንድነው?

A. /-ኣዊ/
B. / -ሀዊ/
C. /-ትሀዊ/
D. /-ዊ/

27. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የትኛው ቃል ቅጽላዊ ሀረግ ሊያስመሰርት ይችላል?

A. ዘመን
B. ዘመናዊ
C. ሥልጣኔ
D. ሠለጠነ

28. ከሚከተሉት መካከል በመሪነት የተቀመጠው ስም ከምን እንደተሰራ የሚጠቁመውን ስማዊ ሀረግ የያዘው አረፍተነገር የትኛው ነው?

A. የቆዳው ጃኬት ተላልጧል::
B. የአንበሳ ጫማ በውድ ዋጋ ተሸጠ::
C. የቅርጫት ኳስ ይወደዳል::
D. የቦርሳው ዋጋ አይቀመስም::

29. "የንግድ ፈቃዱ በወቅቱ አልታደሰም::" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የግሱ ገላጭ ምን የሚለው ነው?

A. የንግድ
B. ፈቃድ
C. በወቅቱ
D. አልታደሰም

30. ከሚከተሉት ውስጥ ለተውሳከ ግሳዊ ሀረግ የትኛው ምሳሌ ይሆናል?

A. ክፉኛ እየሳለ
B. በጣም ክፉኛ
C. ጠንካራው ተማሪ
D. በጣም ጠንካራ

31. "የአረንጓዴ ልማት ዘመቻ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ፕሮግራም ነው::" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሀረጉ የትኛው ነው?

A. የአረንጓዴ ልማት ዘመቻ ተጠናክሮ መቀጠል
B. የአረንጓዴ ልማት ዘመቻ ተጠናክሮ
C. የአረንጓዴ ልማት
D. የአረንጓዴ ልማት ዘመቻ

32. ከሚከተሉት ውስጥ ለነጻ ምእላድ የትኛው ምሳሌ ይሆናል?

A. ተንከለኛ
B. ሰማእት
C. ስምምነት
D. ስምምነቶች

33. ከሚከተሉት መካከል በተለየ የአጠማመር ስልት የተመሠረተው የትኛው ጥምር ቃል ነው?

A. ትምህርትቤት
B. ሻይቤት
C. ዳቦቤት
D. ቤተመንግሥት

34. "_____አብዛኛውን ጊዜ ስለሰው የሚገልጽ፣ የሚመራመር፣ የሙያ መስክ ነው::" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ለባዶ ቦታው ተገቢ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ጋዜጣዊ
B. ጋዜጣ
C. ጋዜጠኞች
D. ጋዜጠኛነት

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 35 እስከ 47 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ::

35. "ከበደ ጮቅ ነው፤ ሳይታወቅበት ባላጋራዎቹን እንዴት ማሸነፍ እንደሚችል አሳምሮ ያውቃል::" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ፍካሬያዊ ፍቺ ያለው ቃል _____ነው::

A. ጮቅ
B. ማሸነፍ
C. አሳምሮ
D. ባላጋራዎቹን

36. "እጁ በደም የተነከረ ሰው፣ ከህግ ቢያመልጥ እንኳ ከህሊና ወቀሳ ማምለጥ አይችልም::" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተገለጸው ምን አይነት ሰው ነው?

A. አካሉ የደማ
B. ደም የነካው
C. ክፉ የመከረ
D. ወንጀል የሰራ

37. ከሚከተሉት ዘይቤዎች መካከል አንዱ አነጻጻሪ ነው::

A. ሳይሰሩ የሚቀመጡና ዓላማ የሌላቸው ብዙ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ::
B. በእያንዳንዱ ቁርጠኛ ውሳኔ ውስጥ የሽንፈት አደጋ ሊኖር ይችላል::
C. ሰዎች በየእለቱ ለውጥ እንደሚያስመዘግቡ ማሰብ ይጠበቅባቸዋል::
D. በእቅድ የሚመሩ ሰዎች ህይወት እንደ ወርቅ ስታበራ ትታያለች::

38. በተምሳሌታዊ ዘይቤ የተገለጸው የቱ ነው?

A. ጋዜጦቹ ቡድኑ እንደሚሸነፍ በመተንበያቸው አሰልጣኙ ተበሳጩ::
B. ኑሯቸው የጨለማ ጉዞ እንዳይሆን ሰዎች ሁሉ መማር አለባቸው::
C. ጓደኝነትን አርሞና ኮትኩቶ ማለምለም የጓደኞሞች ፋንታ ነው::
D. ውጥረትን የሚቀንሱ ሰዎች ተዝናንቶ የመኖር እድላቸው ሰፊ ነው::

39. "ሳሳ" የሚለው ቃል "ከሳ" የሚል ፍች የሚኖረው በየትኛው አረፍተነገር ውስጥ ነው?

A. አባትየው ለልጁ ሳሳ::
B. በርኖሱ ሳሳ::
C. እንጀራው ሳሳ ይላል::
D. ተድላ ሰውነቱ ሳሳ::

40. "አሰራጨ" የሚለው ቃል "አዛመተ" የሚል ፍቺ የሚኖረው በየትኛው አረፍተነገር ውስጥ ነው?

A. ንጽህናው ያልተጠበቀ ውሃ ለበሽታው መሰራጨት አንዱ ምክንያት ነበር::
B. መመሪያው ከላይ እስከ ታች እየተሰራጨ ነው::
C. ዜናው በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች ተሰራጭቷል::
D. የጋዜጣ በወቅቱ አለመሰራጨት የመረጃ ውሱንነትን ያስከትላል::

41. "ነከረ" የሚለው ቃል በእማሬያዊ ፍቺው የገባው በየትኛው አረፍተነገር ነው?

A. አንድም ቀን በሳል ሀሳብ አቅርቦ አያውቅም፤ የተነከረ ነው::
B. ገመዱን ውሃ ውስጥ ነከረው::
C. እየነከሩ ያወጡት መሆኑ በአነጋገሩ ያስታውቃል::
D. ሰሎሞን ከተነከረ ያልተጠመዘዘ ነው::

42. "ደረቅ" የሚለው ቃል በፍካሬያዊ ፍቺው የገባው በየትኛው አረፍተነገር ውስጥ ነው?

A. ደረቅ በመሆኑ ሰዎቹ ሊያሳምኑት አልሞከሩም::
B. ደረቅ እንጨት በቀላሉ ይሰበራል::
C. ደረቅ ኬክ ከባክቴሪያ ነጻ ነው ተብሎ ይገመታል::
D. የቁርበቱ ደረቅነት በቀላሉ ለመጫን ጠቅሟል::

43. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በሰውኛ ዘይቤ የተጻፈ ነው::

A. መጻህፍት የማያልፍ ምክር የሚለግሱ ጓደኞች ናቸው::
B. ፍርሀት በሁላችንም ዘንድ ያለ የጋራ ችግር ነው::
C. የሱሰኝነት መንስኤ ራስን መጥላት እንደሆነ ይነገራል::
D. ደስተኛ ለመሆን ከፈለጋችሁ የምትወዱትን ነገር ስሩ::

44. "የኔ ስመ ገናናነት <u>ቢከፍቱት ተልባ</u> ነው::" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበትን የሚተካው _____ ነው::

A. የሚጨበጨብለት
B. እርባና ቢስ
C. ቆሌ ቢስ
D. የሚመሰከረለት

45. "በዘንድሮው ዓመት ብዙ መሬት ጠፍ በማደሩ የታሰበውን ያህል ምርት አልተገኘም::" የሚለው አረፍተነገር ምንን ያመለክታል?

A. ብዙ መሬት በጎርፍ መሸርሸሩን
B. ብዙ መሬት አለመታረሱን
C. ብዙ መሬት በውሃ መጥለቅለቁን
D. ብዙ መሬት በማዳበሪያ አለመልማቱን

46. ከዚህ በታች የቀረበው ሀሳብ የተገለጸበት የዘይቤ አይነት ምን ይባላል?
"ልጅቷ ጧቱን ውልቅ ያለች፣ አፍታም ሳትቆይ አመሻሽ ላይ ተመለሰች::"

A. አነጻጸሪ
B. ተለዋጭ
C. ተምሳሌት
D. ምጸት

47. "ሬዲዮው <u>የጀርመን</u> ስሪት ነው:: <u>በጀርመን</u> ሬዲዮ ስለ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ሰፊ ገለጻ ተደረገ::" በሚሉት አረፍተ ነገሮች የተሰመረባቸው ቃላት ከገቡበት ሁኔታ አንፃር በቅደም ተከተል ምንን ያመለክታሉ?

A. የመጀመሪያው ሬዲዮው የተፈበረከበትን ሀገር፣ ሁለተኛው የሬዲዮ ጣቢያውን
B. የመጀመሪያው የሬዲዮ ጣቢያውን፣ ሁለተኛው የተፈበረከበትን ሀገር
C. የመጀመሪያው የሬዲዮ ጣቢያውን፣ ሁለተኛው ሬዲዮው ንብረትነቱ የጀርመኖች መሆኑን
D. የመጀመሪያው ሬዲዮው የተፈበረከበትን ሀገር፣ ሁለተኛው ሬዲዮው ንብረትነቱ የጀርመኖች መሆኑን

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 48 እስከ 57 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተለውን ምንባብ መሠረት ያደረጉ ናቸው:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል በምንባቡ መሠረት ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ::

ዛሬ የማወጋችሁ ስመ ገናና፣ ዝነኛና ታዋቂ ስለሆነው ልጄ ስለ ጥቁር አባይ ነው:: "እ!" ብዬ አምጬ የምወልደው እኔ ነኝ:: ግን የእናት ወግ አሳይቶኝ አያውቅም:: ጥሎኝ ወደ ባእድ ሀገር ይፈተለካል:: ከምስራቅ አፍሪካ ተነስቶ፣ ሰሜን አፍሪካ ሜዴትራኒያን ባህር ያድራል:: ሩቅ ተጓዥ በመሆኑ፣ ብዙዎች ማደሪያ ቢስ ይበሉት እንጂ ምን የመሰለ ማደሪያ አለው::

ልጄ ጥቁር አባይ፣ ከጊሸባይ ተነስቶ፣ ጣና ሃይቅን አቋርጦ፣ ከራሴ ወንዞች ያገኘውን ውሃ ይዞ ወደ ባእድ ሀገር እብስ ይላል:: ከዚህ በተጨማሪ፣ ለብዙ ሺህ አመታት ለፍቼ፣ ደክሜና የሰው ፊት እየገረፈኝ ለልጆቼና ለልጅ ልጆቼ እንዲሆን ያስቀመጥኩትን ጥሪት ጥርግርግ አድርጎ እያግበሰበሰ ባልደፈርም ባይነት ስሜት የጀግና ፉከራ እየፎከረና እየሸለለ፣ ገደል ለገደል እየተገለባበጠ፣ መልከ መልካምነቱን ብቻ እያሳየኝ፣ አይኔ ከእርሱ ጋር ክርትት ሲል ጥሎኝ ጥርግ ይላል:: አጨካከኑን ያየ፣ ዳግም መለስ ብሎ ላያየኝና የልጅ ወጉን ላያሳየኝ ቃለ መሃላ ያለበት ሳይመስለው አይቀርም::

እጅግ የሚገርመው ደግሞ፣ ገና ከቤቱ ወጣ ሲል ጉዞው ሁሉ አደባባይ ለአደባባይ መሆኑ ነው። አመሉን ማሳመሩ ነው መሰለኝ! ከምንጩ ተነስቶ 1400 ኪ.ሜ ያህል ከተጓዘ በኋላ ካርቱም አቅራቢያ ሲደርስ፣ ጉዞውን ኡጋንዳንና ደቡብ ሱዳንን በዋና ከተማዋ በጁባ ላይ አቋርጦ ከደቡባዊ አቅጣጫ ወደ ሰሜን ከሚፈሰው ከነጭ አባይ ጋር ያደርጋል። ከዚህ በኋላ ሁለቱም ጥቁርና ነጭ የሚለውን የግል መጠሪያ ትተው አባይ ይባላሉ። ታዲያ፣ ነጭ አባይ ከጥቁር አባይ ጋር እስከሚገናኝ ድረስ ያለው የውሃ መጠን በቀላሉ የሚገመት ባይሆንም፣ የጥቁር አባይን ያህል የእናቱን ንብረት ጥርግርግ አድርጎ ለማውጣት የሚያስችል አቅም የለውም፤ ቁጥብ ነው።

በልጅ በኩል ብዙ ውሃ ለአባይ እኔ ልገብር እንጂ፣ ከእኔ ይልቅ አባይን ጥሩ አድርገው የተጠቀሙበት ሱዳንና ግብጽ ናቸው። ለበርካታ አመታት ለመስኖ፣ለሀይል ማመንጫ፣ለቱሪስት መስህብነትና ለአሳ ምርት እየተገለገሉበት ነው። በተለይ ግብጻውያንን፣ ጥቁር አባይ ከጥንት ጀምሮ በምግብ እህል ራሳቸውን እንዲችሉ አድርጓቸዋል። ግብጾች ለምን በአባይ ተጠቅመው አደጉ የሚል አንጀት የለኝም። ርህሩህነቴ ይህን እንድል አይፈቅድልኝም። እድገታቸው የእኔም እድገት ነውና። ሆኖም እጅ አመድ አፋሽ መሆኑ ያንገበግበኛል። ልጆቼ፣ በተለያዩ ጊዜያት በተከሰቱ ድርቆች መጠቃታቸውና በአለም ላይ የርሀብና የድህነት ተምሳሌት መሆናቸው በብርቱ ይሰማኛል። "የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው" ማለት ይሄ አይደለም? ገጣሚውስ ቢሆን፣ "...የእጅን ሰጥቶ ጦም አዳሪ፤ ጥጋብ ሰጥቶ ተበዳሪ..." ያለው ምኑን ይመስላችኋል?

አሁን ግን የልጅ ሩቅ አዳሪነቱ ይብቃ ብዬ ተነስቻለሁ! ልጆቼ እስከመቼ የእጃችሁን እየሰጣችሁ በድህነት ትኖራላችሁ? እስከ መቼ የርሃብና የድርቅ ተምሳሌት እየተባላችሁ ትጠራላችሁ? እስከ መቼስ ለዳቦ ስንዴ ትለምናላችሁ? እስከ መቼስ ድህነት ሲነሳ አንገታችሁን ትደፋላችሁ? እንደጀመራችሁት አቅም ያለው በጉልበቱ፣ ሀብት ያለው በገንዘቡ፣ የተማረው ደግሞ በእውቀቱ ተረዳዱና በርትታችሁ ለወንድማችሁ ጎጆ ቀልሱለት። ልጅ ቅርብ እያደሩ መጓዝን ከለመደ፣ እየጠራረገ የሚወስደውን የምድሬን በረከት እዚሁ ስለሚዘረግፍላችሁ፣ ድህነትና ርሃብ ያበቃላቸዋል። እናንተም እንደሌሎች ወንድም ህዝቦች የሲሳዩ ተጋሪ ትሆናላችሁ። ያገራችሁን ሰርዶ ባገራችሁ በሬ ትነቅሉና በምድሬ በረከት ትጠግባላችሁ። እስከዚያው ደህና ሰንብቱልኝ...

48. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ስለ አባይ ትክክል ነው።

A. በስፋት ጥቅም ላይ የዋለው በፈለቀባቸው ሀገሮች ብቻ መሆኑ እሙን ነው።
B. በብዛት ሲያገለግል የቆየው ላልፈለቀባቸው ሀገሮች መሆኑ የተረጋገጠ ነው።
C. ብዙ ውሃ ለሚገብሩለት ሀገሮች ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ ይታወቃል።
D. የፈለቀባቸውንም የሚፈስባቸውንም ሀገሮች እኩል ሲጠቅም ይታያል።

49. በምንባቡ ውስጥ የጥቁር አባይ እናት _____::

A. ስለ ጥቁር አባይ ያላት ሀሳብ ይህ ነው ተብሎ ሊገለፅ አይችልም
B. ስለ ጥቁር አባይ ለልጆቿ በለገሰችው ምክር ተስፋ አድርጋለች
C. በልጇ ሁኔታ በጣም ተስፋ ቆርጣለች
D. በልጇ ድርጊት በጣም ተበሳጭታለች

50. በምንባቡ መጨረሻ ለወንድማችሁ "ጎጆ ቀልሱለት" ምንን ያመለክታል?

A. ጥቁር አባይ የሚጠራርገው አፈር መኖር እንደሌለበት
B. ጥቁር አባይ መጠለያ እንዲሰራለት
C. ጥቁር አባይ ከአገር እንዳይወጣ መገደብ እንዳለበት
D. ጥቁር አባይ መገደብ እንዳለበት

51. "ጥቁር አባይ ባልደፈርም ባይነት ስሜት የጀግና ፉከራ እየፎከረ፣ እያቅራራና እየሸለለ ይፈተለካል::" የሚለው አገላለጽ ጥቁር አባይ _____መሆኑን ይገልጻል::

A. በጣም ብዙ ውሃ ይዞ የሚጓዝ
B. ከፍተኛ ድምጽ እያሰማ የሚሄድ
C. በማን ይነካኛል ስሜት የሚጓዝ
D. ከጀግኖች ሀገር ፈልቆ የሚፈስ

52. ነጭ አባይ ቁጥብ ነው የተባለው ለምንድነው?

A. የሚፈልቅበትን አካባቢ ስለሚታደግ
B. አነስተኛ የውሃ መጠን ስላለው
C. በሜዳማ አካባቢ በፀጥታ ሲጓዝ የሚያስደስት በመሆኑ
D. የጥቁር አባይን ያህል አፈር ጠራርጎ ይዞ ስለማይጓዝ

53. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ትክክል ነው::

A. ለአባይ ብዙ የውሃ መጠን የሚያበረክተው ጥቁር አባይ ነው::
B. ለአባይ ብዙ የውሃ መጠን የሚያበረክተው ነጭ አባይ ነው::
C. ነጭ አባይ ትንሽ ቢሆንም በውሃ መጠኑ ከጥቁር አባይ አያንስም::
D. ለአባይ አነስተኛ የውሃ መጠን የሚያበረክተው ጥቁር አባይ ነው::

54. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የምንባቡን ዋና ሀሳብ ባጭሩ ይገልጻል::

A. ሌሎች ጠግበው እየበሉ ኢትዮያውን በቂ ስንዴ ማምረት ተስኗቸዋል::
B. ጥቁር አባይን በመገደብ የሲሳዩ ተጋሪ መሆን ይቻላል::
C. ጥቁር አባይ ከሀገሩ ወጣ ሲል አመሉን ያሳምራል::
D. በጥቁር አባይ ጥሩ አድርገው የተጠቀሙት ሱዳንና ግብጽ ናቸው::

55. በምንባቡ ውስጥ የጥቁር አባይ እናት ምን አይነት ስሜት ይነበብባታል?

A. የቁጭት
B. የኩራት
C. የምቀኝነት
D. የቅናት

56. ጥቁር አባይ ማረፊያ ቢያገኝ _____::

A. የጥቁር አባይ ስደት ሙሉበሙሉ ያከትማል::
B. ሱዳኖች ድህነትና ረሃብ ይወርሳቸዋል::
C. ድህነትና ረሃብ የኢትዮጵያዊያን መጠሪያነታቸው ያበቃል::
D. የግብጻውያን ሃብታምነት ያበቃለታል::

57. ከዚህ በላይ የቀረበው ምንባብ ለየትኛው የድርሰት አይነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል?

A. ለተራኪ
B. ለሥእላዊ
C. ለአመዛዛኝ
D. ለገላጭ

መመሪያ:- ከጥያቄ 58 እስከ 62 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች በተከታዩ ግጥም ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ለጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ።

የስልጣኔ ምንጭ፣የሰው ዘር መገኛ፣ የታሪክ ከበርቴ
መሆናችን ታውቆ ባለም ከተወራ
እኛ ምንተዳችን «ጭራ ናችሁ» ቢሉን
ከድሆችም ጎራ
ምናባቱ ዛሬ ምናባቱ ነገ ኮርቶ መኖር ካለ
በትላንት አሻራ።
ሙሉነህ መንግስቱ፣ ጉራማይሌ

58. የግጥሙ ድምጸት ምንድን ነው?

A. ቁጭት
B. ሽሙጥ
C. ዘለፋ
D. ጸጸት

59. ግጥሙ ስለኢትዮጵያ የሚገልጸ ነው ቢባል ማስረጃችን ምንድን ነው?

A. ኢትዮጵያ በኩራት የሚኖርባት ሃገር መሆኗ
B. ኢትዮጵያ የድሆች ጭራ መባልን አጥብቆ የሚጠላ ህዝብ ሃገር መሆኗ
C. ኢትዮጵያ ከድህነት ለመውጣት የምትታትር ሃገር መሆኗ
D. ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ፣የስልጣኔ ምንጭና የታሪክ ባለቤት መሆኗ

60. ግጥሙ እንዲጸፍ መነሻ የሆነው ጉዳይ የትኛው ሊሆን ይችላል?

A. የቀደመው ትውልድ ጥረት ለዛሬው ትውልድ በኩራት መኖር አስተዋጽኦ ያደረገ መሆኑ
B. ባለፈው ታሪክ በመሞካሸት ለራስና ለትውልድ የሚበጅ ስራ ለመስራት ያለመነሳት ሁኔታ
C. የትላንት ማንነት ስንቅ ሆኖ ከድህነት ሊያወጣ የሚችል መሆኑ
D. በትላንት ማንነት ዛሬ ተከብሮ መኖር መቻል የሚያስደስት መሆኑ

61. ለግጥሙ ርእስ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

A. ኩራት እራት
B. ማንነት
C. ከእኛ ወዲያ
D. አለባብሰው ቢያርሱ

62. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት?

A. አምስት
B. አራት
C. ስምንት
D. ስድስት

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 63 እስከ 76 ድረስ ያሉትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ የሆነውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጭ/ምረጥ:

63. የራስ አሉላ አባነጋ የህይወት ታሪክ በትክክል ሲጻፍ የትኛው መቅደም ይኖርበታል?

A. የጀግንነት ውሎዎች
B. የትውልድ ስፍራ
C. ወደ ስልጣን የመጡበት ሁኔታ
D. የትምህርት አቀባበል ሁኔታ

64. ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ሪፖርት ባጭሩ አጠቃሎ የሚገልጸው የቱ ነው?

የአግሮ ኢንዱስትሪው አክሲዮን ማህበር በዚህ አመት በ4.6 ሚሊዮን ብር የወተት ከብቶች ግዢ በተጨማሪ፣ ለእንስሳት ተዋፅኦ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ግንባታ የሚሆን ቦታ ከመንግስት በመረከብ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ከመንግስት ባገኘው ቦታ ላይ የአገልግሎት አሰጣጡን ምቹ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል። መብራት አስገብቷል።ሶስት የውሀ ጉድጓዶችን አስቆፍሮ ጥቅም ላይ አውሏል። እንዲሁም በከፍተኛ ወጪ ከዋና ዋና መንገዶች የሚያገናኙ የጠጠር መንገዶችን አሰርቷል።

A. አግሮ ኢንዱስትሪው የማስፋፋት ስራ እየሰራ ነው።
B. አግሮ ኢንዱስትሪው መሰረተ ልማት እያስፋፋ ነው።
C. አግሮ ኢንዱስትሪው ወተት እያመረተ ነው።
D. አግሮ ኢንዱስትሪው ፋብሪካ እየገነባ ነው።

65. "ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገሮች የሚያገናኟት የባበቡር መስመሮች ልትዘረጋ መሆኑ ተገለጸ። መስመሮቹን የሚዘረጋው አንድ ታዋቂ የውጪ ሀገር ኩባንያ ሲሆን፣ ዝርጋታው በአምስት አመት ውስጥ ተጠናቆ ስራ እንደሚጀምር ይጠበቃል።" በሚለው ጽሁፍ ውስጥ _____ ሁለቱን አረፍተ ነገሮች ያያዘ የመሸጋገሪያ ሀረግ ነው።

A. እንደሚጀምር ይጠበቃል
B. መሆኑ ተገለጠ
C. ታዋቂ የውጪ ሀገር ኩባንያ
D. መስመሮቹን የሚዘረጋው

66. የምክንያትና የውጤት ግንኙነት ያለው በየትኛው አረፍተነገር ነው?

A. ባለፈው አመት ወጣቶችን ስራ ፈጣሪ ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና በወጣት ማህበሩ ተሰጥቷል።
B. ባለፈው አመት በወጣት ማህበሩ የተሰጠው ስልጠና ብዙ ስራ አጦችን ስራ ፈጣሪ አድርጓል።
C. የወጣት ማህበሩ ወጣቶችን በአንድ ላይ አሰባስቦ የተለያዩ ስልጠናዎችን ለመስጠት ወሰነ።
D. የወጣት ማህበሩ ስራ አጥነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ በርካታ እቅዶችን ነድፎ አቅርቧል።

67. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ጥሩ የማስታወሻ አያያዝ ችሎታ ያለው ሰው የሚያከናውነው ተግባር ነው።

A. አንብበው የተረዱትን በራስ አባባል በማስታወሻ መጻፍ
B. ያነበቡትን ቃል በቃል ወስዶ ማስታወሻ ላይ መጻፍ
C. ያነበቡትን እንዳለ ሸምድዶ ቃል በቃል በማስታወሻ መጻፍ
D. ያነበቡትን እንዳለ አስፋፍቶ ማስታወሻ ላይ መጻፍ

68. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ፣ አንድ መስሪያ ቤት የተለያዩ ተግባራት እንዲፈጸሙለት ወደ ሌላ መስሪያ ቤት የሚጽፈው ነው።

A. የውስጥ ማስታወሻ
B. የግል ማስታወሻ
C. የስራ ደብዳቤ
D. የሰላምታ ደብዳቤ

69. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የቃለጉባኤ መገለጫ ነው::

A. የስብሰባውን ሂደት በትክክልና በእውነት መግለፀ
B. የስብሰባውን ሂደት እንዳለ መዘገቡ
C. እንደተሰብሳቢዎች ፍላጎት የሚሻሻል መሆኑ
D. እንደተሰብሳቢዎች ፍላጎት የሚጻፍ መሆኑ

70. በማነጻጸር ስልት የቀረበው የቱ አረፍተነገር ነው?

A. ሰዎች በዚህ አለም ላይ ስኬታማና ደስተኛ ሆነው ለመኖር ከፈለጉ ለህይወታቸው ዋጋ የሚሰጡ፣ በሆነ ባልሆነው የማይጨነቁና ራሳቸውን ማዝናናት የሚችሉ መሆን አለባቸው::
B. ጠንካራና የጥሩ ስነምግባር ባለቤት የሆኑ ሰዎች የህይወትን ውጣ ውረድ በቆራጥነት መቋቋም ሲችሉ፣ ልፍስፍሶች ደግሞ በማይረቡ ችግሮች ተደናቅፈው የትም ይወድቃሉ::
C. መሞከር ማለት ችግሮች እስኪፈቱ ድረስ መፍትሄ ማፈላለግ እንደመሆኑ፣ ማንኛውንም ችግር ለማሸነፍ ሳያቋርጡ መፍትሄ መፈለግ ያሻል::
D. ለላከችልኝ ደብዳቤ መልስ ስሰጥ በመካከላችን የተፈጠረው ያለመተማመን ስሜት ያሳዘነኝ መሆኑን መግለጼ ቢያስከፋትም፣ መቀየሜን ልታውቀው ይገባታል::

71. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በትረካ ስልት የቀረበ ነው::

A. አንድነት ሀይል ነው በተባለው መሰረት፣ መሰባሰባችን እጅግ በርካታ ስራዎችን እንድናከወን ጠቅሞናል:: ስለዚህ ሰዎች ሁሉ ውጤታማ እንዲሆኑ በህብረት እንዲሰሩ እንመክራለን::
B. ታዳጊ ወጣት በነበርኩበት ጊዜ አይናፋር ነበርኩኝ:: ከበርካታ ታዛቢዎች ከሚደርሱኝ አስተያየቶች መረዳት እንደቻልኩት፣ አይናፋርነቴ አሁን የበለጠ ተባባሷል::
C. በርካታ ሰዎች የቅንነትን ዋጋ ባልተረዱ ሰዎች ፊት ቅን መሆን፣ የከበረው ቁም ነገር እንዲረገጥ ማድረግ ነው ብለው ያምናሉ::
D. ምርታማነት የትጋት ውጤት ነው:: ንቦች በትጋት መስራት በመቻላቸው፣ በመጠን ትንሽ ሆነው ሳለ እጅግ ጣፋጭ የሆነውን ነገር ማርን ማምረት ችለዋል::

72. ከፍ ብሎ የቀረበው አንቀጽ ኃይለቃል ምን የሚለው ነው?

A. የኋላ የኋላ የሽምድምድ አካል ባለቤት ስለሚያደርግ ለጤናም ጠንቅ ይሆናል::
B. ለተለያዩ ጠቃሚ ነገሮች ይውል የነበረውንም ገንዘብ ስለሚሻማ ኪስን ያራቁታል::
C. በማምረት አቅም ላይ በሚኖረው ተፅእኖ የተነሳ በኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ጥላ ማጥላቱ ሀቅ ነው::
D. ጫት መቃምና ሲጋራ ማጨስ ሊወገዱ የሚገባቸው አጉል ልምዶች ናቸው::

73. የሚከተለው አንቀጽ በየትኛው የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልት ቀርቧል?

ጫት መቃምና ሲጋራ ማጨስ ሊወገዱ የሚገባቸው አጉል ልምዶች ናቸው:: ጫት መቃም ለሥራ ሰዓት መባከን እንደ አንድ ሰበብ ሊቆጠር ይችላል:: ለተለያዩ ጠቃሚ ነገሮች ይውል የነበረውንም ገንዘብ ስለሚሻማ ኪስን ያራቁታል:: የኋላ የኋላም የሽምድምድ አካል ባለቤት ስለሚያደርግ ለጤናም ጠንቅ ይሆናል:: ሲጋራ ማጨስም እንዲሁ የተለያዩ ችግሮች ሰለባ ያደርጋል:: ለመጥፎ ጠረን ያጋልጣል:: በማምረት አቅም ላይ በሚኖረው ተፅእኖ የተነሳም በኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ጥላ ማጥላቱ ሀቅ ነው:: ለምግብ እየሰሰትን ለሲጋራና ለጫት የምናውለው ገንዘብ፣ ኪሳችንን አራቁቶ ለበታችነትና ለውርደት፣ አካላችንን አመንምኖ ለስቃይና ለሞት መዳረጉ እሙን ነው::

A. በትረካ
B. በገለፃ
C. በማነጻጸር
D. በማወዳደር

74. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡት አረፍተነገሮች ተቃንተው ቢፃፉ የአረፍተ ነገሩ ቅደም ተከተል ምን ይሆናል?

1. ለዚህም በሀይለቃሉና እሱን በሚያብራሩት አረፍተነገሮች መካከል ግልጽ የሆነ ዝምድና መኖር አለበት::
2. አንቀጹን ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ሀይል አለው::
3. ሀይለቃል በአጠቃላይ መንደርደሪያ ሀሳብ ሲሆን፣የአንቀጹ አቢይ ጭብጥ በመሆን ያገለግላል::
4. አንድ አንቀጽ በውስጡ ሀይለቃል የሚባል ዋና ክፍል አለው::

A. 4፣3፣2፣1
B. 2፣3፣1፣4
C. 1፣2፣3፣4
D. 3፣2፣4፣1

75. ለራስ የህይወት ታሪክና ለግለሰብ የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ የጋራ <u>ያልሆነው</u> የትኛው ነው?

A. አስተዳደግንና የትምህርት ጊዜ ቆይታን መጻፍ
B. ከማን እንደተወለዱና የትውልድ ቦታ መጻፍ
C. ሕልፈተ ሕይወት መቼና እንዴት እንደሆነ መጻፍ
D. መልካም የስራ ተሞክሮን መጻፍ

76. ዘገባን በተመለከተ ትክክል የሆነው የትኛው አረፍተነገር ነው?

A. መረጃዎቹ ትክክለኛና አሳማኝ ናቸው::
B. የተወሰኑ ሰዎችን ታሳቢ አድርጎ ይቀርባል::
C. በአቀራረቡ ከልቦለድ ጋር ይመሳሰላል::
D. ለጽሁፉ ውበት እንጂ ለይዘቱ አይጨነቅም::

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 77 እስከ 85 ድረስ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ፣ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተስማሚውን መልስ ምረጭ/ምረጥ::

77. የውስጥን አውጥቶ በመናገር መፍትሄ ሊገኝ መቻሉን ለማመልከት የትኛውን አባባል እንጠቀማለን?

A. ዝምታ ወርቅ ነው፣ መናገር መዳብ ነው::
B. ከተናገሩት ምሰው የቀበሩት::
C. ጨርሶ ቢያወሩት ሆድ ባዶ ይቀራል: :
D. ካልተናገሩቱ አይገለፅ ብልሃቱ::

78. "ሲያረጁ አምባር ዋጁ" ለሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የትኛው ይስማማዋል?

A. ሲያጌጡ ይመላለጡ::
B. በእርጅና ይመጣል ጣጣ::
C. ሲያልቅ አያምር::
D. በእስተርጅና ሙሽርና::

LIBRARIES
P. BOX 1176

79. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የስነቃል ዘርፍ ነው::

A. ዘገባ
B. ግጥም
C. ተረት
D. ልቦለድ

80. _____ ሥነጽሁፍ ነው::

A. የህይወት ታሪክ
B. አጭር ልቦለድ
C. የግል ማስታወሻ
D. ለህዝብ የቀረበ ንግግር

81. _____ የረጅም ልቦለድ ባህርይ ነው::

A. በገሀዱ አለም የሌሉ ሰዎችን ፈጥሮ መተረክ
B. በእውነት የተከሰተ ድርጊትን መግለጽ
C. የአለማችንን ሰዎች ግጭት ማሳየት
D. ሰዎችን በፈጠረ ፈጣሪ ተጽፎ መቅረብ

82. አንድን ረጅም ልቦለድ ያነበቡ ሰዎች፣ የልቦለዱን ሂደት የሚገልጹበት ሁኔታ ምንን ያመለክታል?

A. የልቦለዱን ታሪክ
B. የልቦለዱን መዋቅር
C. የልቦለዱን ገጸባህርያት
D. የልቦለዱን መቼት

83. ገጸባህርያት የሚኖሩት _____ ነው::

A. በገሀዱ የሰው ልጆች መኖሪያ
B. በተጻፉበት የልቦለድ አለም ውስጥ
C. የገሀዱ አለም በሚባለው ውስጥ
D. የልቦለዱ አንባቢ ባለበት ዘመን

84. _____ ዘመን በልቦለድ መቼት ስር ሊካተት ይችላል::

A. የልቦለዱ ደራሲ የኖረበት
B. ልቦለዱ ተጽፎ የቀረበበት
C. የልቦለዱ አንባቢ የኖረበት
D. የልቦለዱ ታሪክ የተፈጸመበት

85. የተውኔት ገጸባህርያትን ወክሎ መድረክ ላይ የሚሳተፈው ማን ነው?

A. መራሂተውኔት
B. ጸሀፌተውኔት
C. ተዋናይ
D. የመድረክ መሪ

መመሪያ:- ከተራ ቁጥር 86 እስከ 90 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ስለዚህ ጥያቄዎቹን በጥሞና በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ተገቢውን መልስ ምረጥ/ ምረጭ::

86. "ሰው ሆኖ ሳይሳሳት የሚኖር የለም፤ አልተፈጠረም _____ አይፈጠርምም::" ለባዶ ቦታው ተስማሚ የሚሆነው የትኛው ስርአተነጥብ ነው?

A. ነጠላ ሰረዝ
B. ድርብ ሰረዝ
C. ቅንፍ
D. አራት ነጥብ

87. በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀሙ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. የቀሚሴን ጨርቅ፣ልስላሴ፣ስፌት፣ የአበባ አጣጣል በጣም ወደውታል::
B. የቀሚሴን ጨርቅ ልስላሴ፣ስፌትና የአበባ አጣጣል በጣም ወደውታል::
C. የቀሚሴን፣ጨርቅ ልስላሴ፣ስፌትና የአበባ አጣጣል በጣም ወደውታል::
D. የቀሚሴን፣ ጨርቅ፣ልስላሴ፣ስፌት፣ የአበባ አጣጣል፣በጣም ወደውታል::

88. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ትክክለኛ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም አለው::

A. አስተማሪዬ ስኬታማ፣"ሰዎች ትኩረታቸውን አሰባስበው በተወሰነ ነጥብ ላይ ማድረግ የሚችሉ ናቸው:: ብለው ነገሩኝ"
B. አስተማሪዬ፣" ስኬታማ ሰዎች ትኩረታቸውን አሰባስበው በተወሰነ ነጥብ ላይ ማድረግ የሚችሉ ናቸው::" ብለው ነገሩኝ::
C. "አስተማሪዬ፣ ስኬታማ ሰዎች ትኩረታቸውን አሰባስበው በተወሰነ ነጥብ ላይ ማድረግ የሚችሉ ናቸው::" ብለው ነገሩኝ::"
D. አስተማሪዬ፣ ስኬታማ ሰዎች ትኩረታቸውን አሰባስበው በተወሰነ ነጥብ ላይ ማድረግ የሚችሉ ናቸው:: ብለው ነገሩኝ "

89. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ በስርአተ ነጥብ አጠቃቀሙ ትክክል ነው::

A. ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳዮችን አስቀድሞ መገመት ትንቢት / Prediction / ይባላል::
B. ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳዮችን አስቀድሞ መገመት /ትንቢት Prediction/ ይባላል::
C. ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳዮችን አስቀድሞ /መገመት ትንቢት/ Prediction ይባላል::
D. ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳዮችን አስቀድሞ /መገመት ትንቢት Prediction / ይባላል::

90. ሁለት ነጥብ ከሰረዝ በትክክል ጥቅም ላይ የዋለው በየትኛው አማራጭ ነው?

A. ኢትዮጵያ ብዙ ትልልቅ ወንዞች አሏት፦ ለምሳሌ አዋሽ፣ዋቤ ሸበሌ፣ ጊቤ፣ አባይና ተከዜ ይጠቀሳሉ::
B. ኢትዮጵያ ብዙ ትልልቅ ወንዞች አሏት:: ለምሳሌ፦ አዋሽ፣ዋቤ ሸበሌ፣ ጊቤ፣ አባይና ተከዜ ይጠቀሳሉ::
C. ኢትዮጵያ ብዙ ትልልቅ ወንዞች አሏት:: ለምሳሌ አዋሽ፣ዋቤ ሸበሌ፣ ጊቤ፣ አባይና ተከዜ፦ ይጠቀሳሉ::
D. ኢትዮጵያ፦ ብዙ ትልልቅ ወንዞች አሏት:: ለምሳሌ አዋሽ፣ዋቤ ሸበሌ፣ ጊቤ፣ አባይና ተከዜ ይጠቀሳሉ::

አባሪ 19፡ በጥናቱ የተካተቱ የክፍል ፈተናዎች ናሙና

በጎንደር ከተማ አስተዳደር ት/ጽ/ቤት በሚገኙ የሀገር አቀፍ ፈተና ተፈታኝ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን ያዘጋጅ ዘንድ ታስቦ የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ሞዴል ፈተና ነው። ፈተናው በአጠቃላይ 90 ጥያቄዎችን ይዟል። ጥያቄዎቹም የቋንቋ ትምህርት አላማን መሰረት ያደረጉ ክሂል ነክና የእውቀት ዘርፍ (ስነ-ልሳን፣ ሰዋሰውና ስነ-ፅሁፍን) አካቶ የያዘ ነው። ለእያንዳንዱ ጥያቄም አራት አራት አማራጮች ቀርበዋል። ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ በትክክል መልስ የሚሆነውን ብቻ መርጣችሁ መልስ መስጫው ላይ አጥቁሩ።

የተፈቀደላችሁ ጊዜ 1፡30

አዘጋጆች፡-

1. ተስፋሁን ዓለሙ - ከደብረ-ሰላም ቅ/ማ/ካ/ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት
2. ታደሰ አስረስ - ከዕድገት-ፈለግ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት
3. በለጠ ደማስ - ከፋሲለደስ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ግንቦት 2004 ዓ.ም

መመሪያ 1 ከጥያቄ 1 — 5 ድረስ ያሉ ጥያቄዎች ተከታዩን ግጥም መሰረት አድርገው የቀረቡ ናቸው። ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጥ (ምረጭ)

መሠላል ለመውጣት

አለው ትልቅ ብልሃት

የላዩን ጨብጦ

የታቹን ረግጦ

ወደ ላይ መመልከት

እጆቹን ዘርግቶ

በሃይል መንጠራራት።

ጨብጦ መጎተት የላዩን

ላዩ ታች እንዲሆን

አንድ ባንድ እየረገጡ

መሰላል የወጡ

ብልሆች የማይጣደፉ

ሞልተዋል በየአፋፉ።

ዘርግተው የጨበጡትን መርገጥ

የመውጣት ህግ ነው የማይለወጥ።

ሲወርዱ ግን ያስፈራል

የረገጡን ያስጨብጣል።

1. ግጥሙ ቤት የመታው በስንት ሆሄዎች ነው?
   ሀ/ 17 ለ/ 7 ሐ/ 8 መ/ 15
2. የገጣሚው ድምፀት(ስሜት) ምንድን ነው?
   ሀ/ የቁጭት ለ/ የጭካኔ ሐ/ የትዝብት መ/ የፍርሃት
3. በግጥሙ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ዘይቤ __ ነው?
   ሀ/ ሰውኛ ለ/ አያዎ ሐ/ ተለዋጭ መ/ ተምሳሌት
4. ግጥሙ ስንት አርኬዎች አሉት?
   ሀ/ 4 ለ/ 5 ሐ/ 3 መ/ 2
5. ገጣሚው በግጥሙ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት _____ ነው?
   ሀ/ የመሰላል አወጣጥን ብልሃት ለ/ የኑሮን ውጣ ውረድነት
   ሐ/ ስልጣን ላይ ለመውጣት የሚደረግን ጥበብ መ/የሰውን በራስ የመተማመን እጦት

መመሪያ II ከተራ ቁጥር 6 — 80 ድረስ የተሰጡና ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ (ምረጭ)

6. መንኳኳት፣ ፏፏቴ፣ ጫጫቴ፣ ተንጣጣ ወ.ዘ.ተ የሚሉትን ቃላት ስለ ቋንቋ አጀማመር ሀሳባውያን ከሚሰጡት መላምት የቱን ይገልፃል?
ሀ/ ቋንቋ ባህሪያዊ ነው
ለ/ ቋንቋ ደመነፍሳዊ ነው
ሐ/ ቋንቋ መለኮታዊ ነው
መ/ ቋንቋ በድምፅ ኩረጃ የተገኘ ነው

7. "Post" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ቃል በአማርኛ "ፖስታ" ሆኖ ብናገኘው የአዋዋሱ ብልሃት (ክስተት) ____ ነው።
ሀ/ እሳቤውንም ስያሜውንም እንዳለ መቀበል
ለ/ እሳቤውን ብቻ ወስዶ ሀገራዊ ስያሜ መስጠት
ሐ/ እሳቤውን ወስዶ በስያሜው ላይ የድምፅ ልሳን ለውጥ ማድረግ
መ/ እሳቤውን ወስዶ የግዕዝ ስያሜ መስጠት

8. ከሚከተሉት ውስጥ ውስብስብ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?
ሀ/ ያ ጠይም ልጅ ነገ ወደ ጎጃም ይሄዳል
ለ/ ልማደኛው ወንጀለኛ እስር ቤት ገባ
ሐ/ ከጎጃም የመጡት ገበሬዎች ለፍርድ ቀረቡ
መ/ ያገር ቤት ሰዎች ወደ ከተማ ፈለሱ

9. "ፀጥታና ዝምታ በመዝገበ ቃል ፍቻቸው ተተካኪ ቢሆኑ መጠነኛ ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል ይገመታል። ፀጥታ ሰላም የሰፈነበትን የአዕምሮ እረፍት ያመለክታል። ዝምታ ግን እፎይታን ላያሳይ ይችላል።" ይህ ጅምር አንቀፅ በየትኛው የአንቀፅ ማስፋፊያ ስልት በይበልጥ ሊስፋፋ ይችላል።
ሀ/ በማወዳደርና በማነፃፀር
ለ/ በምክንያትና ውጤት
ሐ/ በምሳሌ
መ/ በትረካ

10. <u>እርሳሴ</u> ጠፋ። በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ በተሰመረበት ቃል መድረሻ ላይ የምትገኘው እስር ምዕላድ ምንን ታመለክታለች?
ሀ/ ባለንብረትነትን ለ/ ተሳቢን ሐ/ ያታን መ/ ረቂቅነትን

11. "አፉን አሟሸ" ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር በፍች የሚስማማው የቱ ነው?
ሀ/ አፉን ፈታ ለ/ ቁርሱን በላ ሐ/ ንግግሩ ተባ መ/ ዝም አለ

12. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በልብ ወለድ ውስጥ አይካተትም?
ሀ/ ምዕራፍ ለ/ ገቢር ሐ/ ጭብጥ መ/ ደራሲ

13. "ጎጆ" የሚለው ቃል በእማሬያዊ ፍቹ የገባው በየትኛው ዐ.ነገር ነው?
ሀ/ የ18 ዓመቱ ወጣት ጎጆ ያዘ።
ለ/ ጎጆ ከያዘ በኋላ ከሱስ ተላቀቀ።
ሐ/ የሳር ጎጆ ከመስራት ቆርቆሮ ቤት መስራት ይመረጣል።
መ/ ወንድሜ የሞቀ ጎጆ አለው።

14. "ዕንቁ" የሚለው ቃል በፍካሬያዊ ፍች የገባው በየትኛው ዐ.ነገር ነው?
ሀ/ የዕንቁ ጥራት መለኪያ አሃድ ካራት ይባላል።
ለ/ ዕንቁ የከበረ ማዕድን ነው።
ሐ/ በአለም ላይ ውስን ሰዎች ብቻ ዕንቁን በማጌጫነት ይጠቀማሉ።
መ/ ዕንቁ የሆነች ልጅ አጋጠመው።

5. "አፍ" የሚለው ቃል በፍካሬያዊ ፍች የገባው በየትኛው ዐ.ነገር ነው?
ሀ/ አፉን ከፍቶ ሳለ ዝንቧ ጥልቅ አለች።
ለ/ እሱ የሚናገረው ምን የሚሉት አፍ ነው።
ሐ/ ብዙ ጊዜ ጠጣር መድሃኒቶች በአፍ ይወሰዳሉ።
መ/ ምላሳችን በአፍ ውስጥ ይገኛል።

6. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ነጠላ ሰረዝ በተገቢ ቦታው **ያልገባው** በየትኛው ዐ.ነገር ነው?
ሀ/ ፈዝ ያስንቃል፣ ያዋርዳልም።
ለ/ በግ፣ ላም፣ ፍየልና በሬ የቀንድ ከብቶች ናቸው
ሐ/ አተር ክክታ፣ ጤፍ ሰልቃ፣ ቂጣ ጋግራና ውሃ ቀድታ ስትጨርስ ትንሽ እረፍት አደረገች
መ/ ገበሬው ታታሪ፣ ደግ፣ ሩህሩህና ቆፍጣና ነው

7. ቅንፍ በትክክለኛ አጠቃቀሙ የገባው በየትኛው ዐ.ነገር ነው?
ሀ/ (ልዩ ልዩ ማዕድናት) እብነ-በረድ፣ ድንጋይ፣ ብረታብረት ለቅርፃቅርፅ አገልግሎት ይውላሉ
ለ/ ልዩ ልዩ ማዕድናት እብነ-በረድ፣ ድንጋይ፣ ብረታ ብረት (ለቅርፃቅርፅ አገልግሎት) ይውላሉ

ሐ/ ልዩ ልዩ ማዕድናት (እብነ-በረድ፣ ድንጋይ፣ ብረታ ብረት) ለቅርፃቅርፅ አገልግሎተ ይውላሉ
መ/ ልዩ ልዩ (ማዕድናት እብነ-በረድ፣ ድንጋይ፣ ብረታ ብረት) ለቅርፃቅርፅ አገልግሎት ይውላሉ

18. ከሚከተሉት ውስጥ ጥምር ግስ የሆነው የቱ ነው?
ሀ/ ሽለ ሙቅ ለ/ ቤተ-መንግስት
ሐ/ ቅስፍ አደረገ መ/ ብረት ድስት

19. የሚከተለው ቃላዊ ግጥም ከየትኛው ወገን ይመደባል?
ካልረባ ሹመት ይሻላል እርሻ
በሰፊ ድግር በሹል ማረሻ
ሀ/ ከስራ ለ/ ከእንጉርጉሮ ሐ/ ከፍቅር መ/ ከክብረ-በዓል

20. የኮምፒውተር አጠቃቀምና የስራ ባህሪያት ሲታሰብ ሁለት ዓይነት የሥራ አፈፃፀም ሊኖር ይችላል። ይህ አረፍተ ነገር ለየትኛው የድርሰት አፃፃፍ ስልት መነሻ ሊሆን ይችላል?
ሀ/ ተራኪ ለ/ ስዕላዊ ሐ/ አመዛዛኝ መ/ ገላጭ

21. <u>የሽማግሌ አታላይ</u> ዘወትር ያጋጥመኛል። የተሰመረበት ሐረግ ___ ነው?
ሀ/ ተውሳከ ግሳዊ ለ/ ቅፅላዊ ሐ/ መስተዋድዳዊ መ/ ስማዊ

22. ከሚከተሉት ተውሳከ ግሶች ውስጥ ነባር ተውሳከ ግስ የሆነው የቱ ነው?
ሀ/ ምንኛ ለ/ ጅልኛ ሐ/ ቶሎ መ/ ክፉኛ

23. ክንዱ ያንበሳ መቼ የሌለ
ለጠላቱ እግር ክፉ አሜኬላ - የዚህ ግጥም ዘይቤ _____ ነው?
ሀ/ ሰውኛ ለ/ ተነፃፀሪ ሐ/ አያዎ መ/ ተለዋጭ

24. ከሚከተሉት ውስጥ ጥምር ቃል የሆነው የቱ ነው?
ሀ/ትንሽ ልጅ ለ/ ቤተሰብ ሐ/ ልዩ ተሰጥኦ መ/ ቶሎ ሄደ

25. "ሽፍታ" የሚለው ቃል ወንበዴ የሚል ፍች የሚኖረው?
ሀ/ "ሽ" ጠብቆ ሲነበብ ለ/ "ፍ" ጠብቆ ሲነበብ
ሐ/ "ፍ" ላልቶ ሲነበብ መ/ "ታ" ላልቶ ሲነበብ

26. ከሚከተሉት ውስጥ ልዩ የሆነው ቃል የቱ ነው?
ሀ/ ናኘ ለ/ ነዛ ሐ/ ዘራ መ/ ናረ

27. "ያ ትልቅ የወርቅ ቀለበት" ይህ ሐረግ ___ ነው?
ሀ/ ስማዊ ለ/ ግሳዊ ሐ/ ቅፅላዊ መ/ ተውሳከ-ግሳዊ

28. "እንደ ቀትር እባብ እየተምዘገዘገ መጣ።" ይህ ዐ.ነገር የቀረበበት ዘይቤ _____ ነው?
ሀ/ ተለዋጭ ለ/ ተነፃፃሪ ሐ/ ሰውኛ መ/ እንቶኔ

29. ከሚከተሉት ውስጥ መስተዋድዳዊ ሐረግ የሆነው የቱ ነው?
ሀ/ እንደተፈተነ ለ/ አሁን ገና ሐ/ ጥቁር ሰው መ/ በፍጥነት ቶሎ

30. ወይዘሮ አለሚቱ <u>ማለፊያ</u> ጠላ ጠመቀች። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች ___ ነው?
ሀ/ መንገድ ለ/ ጥሩ ሐ/ የጎሽ መ/ ቀጭን

31. ካሳ በባንክ ለወንድሙ ገንዘብ ላከለት። በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ ርዕቱ ተሳቢው _____ ነው?
ሀ/ ለወንድሙ ለ/ ገንዘብ ሐ/ ካሳ መ/ በባንክ

32. አንድ ሰው አዲስ ቤት ሰርቶ ሲገባ ጠያቂዎች መልካም ምኞታቸውን ለመግለፅ ወደ ቤት ሲገቡ የሚጠቀሙበት አባባል?
ሀ/ እንኳን ለዚህ አበቃህ ለ/ አምላክ ይማርህ
ሐ/ ቤት ለእንቦሳ መ/ እንቦሳ እሰሩ

33. "ተናገር አንተ ትምህርት ቤት ባለፉት ዘመናት ስንት ብቁ ዜጎች አፈራህ?" ይህ ዐ.ነገር የቀረበበት ዘይቤ _____ ነው?
ሀ/ ምፀት ለ/ አያዎ ሐ/ ሰውኛ መ/ እንቶኔ

34. "አሁን ፈተና እየፈተንኩ ነው።" በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ አብይ ግሳዊ ሐረጉ ምን የሚለው ነው?
ሀ/ ፈተና እየተፈተንኩ ነው ለ/ እየተፈተንኩ ነው
ሐ/ አሁን ፈተና መ/ አሁን ፈተና እየፈተንኩ ነው

35. አንጎራጉራለሁ የደላኝ መስዩ
ሌሊቱ እንዲነጋ ቀኑ እንዲመሽ ብዮ
ከዚህ መንቶ ግጥም ጋር በይዘት የሚዛመደው ተረትና ምሳሌ የቱ ነው?
ሀ/ ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት ለ/ የራሷ ሲያርባት የሰው ታማስላለች
ሐ/ ማሽላ እያረረ ይስቃል መ/ ስራ ያጣ ገንፎ ያላምጣል

36. ችምችም ብለው በቅለው እንደደጋን ከጎበጡት ቅንድቦቹ ራስጌ ባለው ገላጣ ግንባሩ ላይ ሶስት ጨምደድ ያሉ መስመሮች ተጋድመዋል - - ይህ ጅምር ፅሁፍ ለየትኛው የድርሰት አፃፃፍ ስልት ምሳሌ ይሆናል?
ሀ/ ስዕላዊ ለ/ ተራኪ ሐ/ አመዛዛኝ መ/ ገላጭ

37. ከሚከተሉት በዝረው የማይቀርበው የሥነ-ቃል አይነት _____ ነው?
ሀ/ ሀተታ ተፈጥሮ ለ/ ተረት ሐ/ አፈ ታሪክ መ/ ሙሾ

38. ከሚከተሉት ሙያዊ ቃላት ውስጥ በተውኔት ውስጥ **የማያገለግለው** የቱ ነው?
ሀ/ ገቢር ለ/ ትዕይንት ሐ/ መድረክ መ/ ምዕራፍ

39. <u>ቡራ ከረዩ</u> ማለቱን ተ ውና እስቲ ቁጭ ብለን በነገሩ እንወያይ በዐ .ነገሩ የተሰመረበት ፈሊጥ ትርጉም _____ ነው?
ሀ/ ሙግት ለ/ ፉከራ ሐ/ ፈንጠዝያ መ/ ቡረቃ

40. "ላም እሳት ወለደች ልጇ ነበርና ላሰች" ለሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር በፍች የቱ ይስማማዋል?
ሀ/ እጣት ገማ ተብሎ ተቆርጦ አይጣልም። ለ/ እሳት ቢፈጃት ወደ ልጇ ጣለች።
ሐ/ የአባየን እከክ ወደ እማየ ልክክ። መ/ እሳትና ጭድ አንድ ቤት አያድሩም።

41. ከሚከተሉት የቋንቋን ረቂቅነት የሚገልፅ ዐ.ነገር የቱ ነው?
ሀ/ "ጀበና" በሚባለው ቁስና በስያሜው መካከል ተፈጥሯዊ ግንኙነት የለም።
ለ/ የጅኦግራፊ መምህሯ ከምድረ-ገፅ ስለጠፋው ዳይኖሰር ስለተባለ እንስሳ የአካል ክፍል ገለፃ አደረጉ።
ሐ/ ከአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰብ የተወለደ ህፃን እንግሊዝ አገር ውስጥ ቢያድግ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አፉን ይፈታል።
መ/ ማንኛውንም ቋንቋ ተናጋሪው የሚግባባበት በቂ የቃላት መድብልና ስርዓት አለው።

42. ከሚከተሉት ውስጥ በቅፅል የቃል ክፍል የሚመደበው የቱ ነው?
ሀ/ አደገ ለ/ ዕድገት ሐ/ ታዳጊ መ/ አስተዳደግ

43. ከሚከተሉት ውስጥ **ነፃ ምዕላድ** የሆነው የቱ ነው?
ሀ/ ሠልፍ ለ/ ሠልፈኛ ሐ/ ሠልፉ መ/ አሠላለፍ

44. "ሂስ በቅኔ ቤት የተለመደ ነው። የቅኔ ተማሪው ከቅኔ ትምህርት ሌላ በጥበቡ የሚጎለምሰው፣ የኪነት ተውህቦውን የሚያተባው የሚያራቅቀውና የሚያደራጀው በሂስ ጥበብ ነው። የተማሪውን ቅኔ የቀለም ጓደኞቹና መምህሩ ይተቻሉ እሱም እንደዚህ ያደርጋል። ተማሪዎቹ የመምህራቸውን ቅኔ ይተቻሉ። አንዳንዴም ብትንትኑን ያወጡታል። ኩርፊያና ስድብ ዛቻና ቅያሜ የለም።"
የዚህ አንቀፅ ቅርፅ የቱን ይመስላል?
ሀ/ ▽ ለ/ △ ሐ/ ⧖ መ/ ◇

45. በጥያቄ ቁጥር 44 የቀረበው አንቀፅ ጎይለ ቃሉ _____ ነው?
ሀ/ ኩርፊያና ስድብ ዛቻና ቅያሜ የለም። ለ/ ሂስ በቅኔ ቤት የተለመደ ነው።
ሐ/ ተማሪዎቹ የመምህራቸውን ቅኔ ይተቻሉ። መ/ ጎይለ ቃል የለውም።

46. ቃልና ምዕላድን አስመልክቶ ተክክል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ/ ቃልም ምዕላድም ትርጉም አዘል ናቸው።
ለ/ ቃል ራሱን ችሎ ሲቆም ምዕላድ ግን ራሱን ችሎ ላይቆም ይችላል።
ሐ/ ቃልም ሆነ ምዕላድ ከአነሱ ወደ እነሱ ትርጉም አዘል አሃዶች ሊሸነሸኑ ይችላሉ።
መ/ ቃል የይዘት (ቃላዊ) ትርጉም ሲኖረው ምዕላድ ግን ላይኖረው ይችላል።

47. ከሚከተሉት ስለ አንቀፅ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
ሀ/ አንቀፅ ስለ አንድ ሀሳብ ብቻ ያትታል ለ/ የአንቀፅ ግጥምጥምነት ካለ የአንቀፅ አንድነት ይኖራል
ሐ/ በአንቀፅ ውስጥ ሊኖርም ላይኖርም የሚችል የአንቀፅ ባህርይ አፅንኦት ነው
መ/ሁሉም መልስ ናቸው

48. ከሚከተሉት ቃላት በውስጡ ጥገኛ ምዕላድ ያልያዘው የቱ ነው?
ሀ/ ብርቱካን ለ/ መምህራን ሐ/ ምሁራን መ/ ካህናት

49. መስስ እለዋለሁ ነገር አላበዛም፣
እንጀራ ነው እንጅ ሰውን ሰው አይገዛም፤
በዚህ ቃላዊ ግጥም የገጣሚው ስሜት ምንድን ነው?
ሀ/ ጭንቀት ለ/ ናፍቆት ሐ/ ብሶት መ/ ትዝብት

50. ፀደይ ልትመጣ ነው ደገሰች አበባ
ቁንን ተሰናድታ አቀረበች ኮልባ
አደይም ጀመረች ቀይ ቀለም ትቀባ
በለስ ከተፍ አለች ሰውነቷን ታጥባ
በዚህ ግጥም ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው ዘይቤ _____ ነው?
ሀ/ አያዎ ለ/ ሠውኛ ሐ/ ተለዋጭ መ/ እንቶኔ

51. እህቴ ጎረቤቶቿን ምሳ <u>ጋበዘች</u>። በተሰመረበት ቃል ውስጥ የሚገኘው የእስር ምዕላድ አይነት __ ነው?
ሀ/ ቃል ለዋጭ ለ/ መስራች ሐ/ የእርባታ መ/ ሀ ና ለ

52. <u>ጨካኝ</u> ተማሪ <u>ክራኝ</u> ይጎዳል። የተሰመረባቸው ቃላት እንደ ቅደም ተከተላቸው የቃል ክፍላቸው _ ነው?
ሀ/ ስምና ቅፅል ለ/ ቅፅልና ስም ሐ/ ቅፅልና ተውሳከ ግስ መ/ ተውሳከ ግስና ቅፅል

53. ከሚከተሉት ውስጥ አያዎ ዘይቤ ጥቅም ላይ የዋለበት ዐ.ነገር የቱ ነው?
ሀ/ ንግግሯ ሬት ነው። ለ/ እያደር እንደዋርካ ሰፋ።
ሐ/ እንኳን ሰው ሳር ቅጠሉም ብሶቱን እያሰማ ነው። መ/ እየኖሩ አለመኖር የተለመደ ሆኗል።

54. ከሚከተሉት ውስጠ ግንድ ጥገኛ ምዕላድ የያዘው የቱ ነው?
ሀ/ ፈላለጠ ለ/ እየፈለጠ ሐ/ ሲፈልጥ መ/ ፈለጠች

55. "በዛብህ የስለት ልጅነቱን ጠብቆ ታቦቶቹን በድንግልና እያገለገለና እናት 'አባቱን እየጦረ የመኖረ ፍላጎት ሲኖረው በሌላ በኩል ደግሞ እነሱን ጥሎ የስለት ልጅነቱን እርግፍ አድርጎ ትቶ ከትውልድ መንደሩ ርቆ ሌሎች እንደሚኖሩት ትዳር ይዞ ንብረት አፍርቶ የመኖር ፍላጎት ይታየዋል።"
ይህ አገላለፅ በየትኛው የግጭት አይነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል?
ሀ/ ሰው ከሰው ጋር ለ/ ሰው ከህሊናው (ከራሱ) ጋር
ሐ/ ሰው ከተፈጥሮ ጋር መ/ ሰው ከማህበረሰቡ ጋር

56. አጭር ልብ-ወለድ ከረጅም ልብ-ወለድ የሚለይበትን ባህርይ የሚገልፀው የቱ ነው?
ሀ/ መቼቱ ሰፊ ስለሆነ በርካታ ገፀ-ባህርያትን ያስተናግዳል ሐ/ ድርብ ውጤት አለው
ለ/ መቼቱ ጠባብ ስለሆነ ጥድፊያ ይታይበታል መ/ ሰፊ ታሪክን ይዞ ከልደት እስከ ሞት ያትታል

57. ከሚከተሉት ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ- ነጥብ በተገቢው ቦታ የተጠቀመው ዐ.ነገር የቱ ነው?
ሀ/ "ህፃኑ ምን? አለኝ መሰለህ። ጡቱን አለኝ ብላ" ፈገግ ለማለት ሞከረች።
ለ/ ህፃኑ "ምን አለኝ? መሰለህ 'ጡቱን አለኝ' ብላ ፈገግ ለማለት ሞከረች።"

ሐ/ "ህፃኑ 'ምን አለኝ' መሰለህ? ጡቱን አለኝ" ብላ ፈገግ ለማለት ሞከረች።
መ/ "ህፃኑ ምን አለኝ መሰለህ? 'ጡቱን' አለኝ።" ብላ ፈገግ ለማለት ሞከረች።

58. ከሚከተሉት ውስጥ መስራች ምዕላድ የያዘው የቱ ነው?
ሀ/ ሰውነት ለ/ ቤታችን ሐ/ ጉልበቴ መ/ ልሳናት

59. ከሚከተሉት ድርሰት ለመፃፍ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው። በቅደም ተከተል ሲቀመጡ የቱን ይመስላሉ?
1. ርዕሰ መወሰን 2. ረቂቅ ማዘጋጀት 3. ርዕስ መምረጥ 4. አስተዋፅኦ (ቢጋር) ማዘጋጀት
ሀ/ 1፣ 3፣ 4፣ 2 ለ/ 3፣ 1፣ 4፣ 2 ሐ/ 3፣ 1፣ 2፣ 4 መ/ 4፣ 3፣ 2፣ 1

60. ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል ድርሰት ለመፃፍ የሚያስችለው የቱ ነው?
ሀ/ የሀይል ምንጭ እጥረት በአለማችን ሐ/ የሀይል ምንጭ አጠቃቀም
ለ/ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መ/ የከተማችን የኤሌክትሪክ አገልግሎት መቋረጥ አበይት ምክንያቶች

61. የሚረዳለት ሰው የለም _____ እሱም ከእነሱም በከፋ ጭንቀት ውስጥ ነው ያለው። ሁለቱን ዐ.ነገሮች ለማጣመር የሚያገለግለው አያያዥ የቱ ነው?
ሀ/ እንጅ ለ/ ስለዚህ ሐ/ በዚህም ሳቢያ መ/ ደግሞም

62. ከሚከተሉት ስለተውኔት ትክክል **ያልሆነው** የቱ ነው?
ሀ/ ተውኔት አንድ የተመረጠ ማህበረሰብን ገፅታ ተመልካቹን በምናብ ያስቃኛል
ለ/ ተውኔት መድረኩ በመብራት የደመቀ አዳራሹ በጨለማ የተዋጠ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል
ሐ/ ተውኔት ስለ ሰውን ልጅ አኗኗር ሁኔታ ጠንከር ያለ ሂስ ይሰጣል
መ/ ተውኔት የሰውን ልጅ ድርጊት መድረክ ላይ ያሳያል

63. "ህፃናት "ቫይታሚን ኤ" የሚባለውን ጠቃሚ ንጥረ ነገር ያላቸውን ምግቦች በተመጣጠነ ደረጃ ካልተመገቡ ጤናቸው ይታወካል። በዚህ ንጥረ ነገር ጉድለት በአለማችን ላይ በርካታ ህፃናት በየአመቱ ለዳፍንትና ለአይነ-ስውርነት በሽታ እንደሚዳረጉ ጥናቶች ያሳያሉ።"
ይህ ጅምር አንቀፅ በየትኛው ማስፋፊያ ስልት ሊስፋፋ ይችላል?
ሀ/ በትረካ ለ/ በምደባ ሀ/ በምሳሌ መ/ በምክንያትና ውጤት

64. "አዳኙ ውሻው አስከትሎ ወደ ጫካ ሄደ።"
በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ ያለው ሰዋሰዋዊ ስህተት ምንድን ነው?
ሀ/ የተሳቢ አመልካች ምዕላድ በተገቢ ቦታ ላይ አለመገኘት
ለ/ የባለቤትና ተሳቢ በተገቢ ቦታ አለመገኘት
ሐ/ የባለቤቱ ከማሰሪያ አንቀፅ ጋር በቁጥር አለመስማማት
መ/ የባለቤቱ ከግሱ ጋር በፆታ አለመስማማት

65. ግለ-ታሪክ በስንተኛ መደብ ይቀርባል?
ሀ/ በሶስተኛ መደብ ለ/ በሁለተኛ መደብ ተባዕታይ ፆታ ብቻ
ሐ/ በሁለተኛ መደብ ብቻ መ/ በአንደኛ መደብ

66. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል **ያልሆነው** አበባዝ የተከተለው የቱ ነው?
ሀ/ ሊቃውንት ለ/ አዕዋፍ ሐ/ መምህሮች መ/ ካህናቶች

67. በመስሪያ ቤት ደብዳቤ ላይ መፃፍ ከሚገባው የአፃፅፍ ቅደም ተከተል በትክክል የተቀመጠው ከሚከተሉት አማራጮች በየትኛው ነው?
ሀ/ የሥራ ድርሻ ሙሉ ስም ፊርማ
ለ/ ፊርማ ሙሉ ስም የስራ ድርሻ
ሐ/ ሙሉ ስም ፊርማ የስራ ድርሻ
መ/ ፊርማ የስራ ድርሻ ሙሉ ስም

68. ወይዘሮ አልማዝ የጣለችው ጠጅ ስለደረቀባት _____ ::
ዐ.ነገሩን በትክክል የሚያሟላው ፊሊጥ የቱ ነው?
ሀ/ ማር ጨመረች ለ/ ማር በጠበጠች ሐ/ ማር አላሰች መ/ ማር ዘለለች

69. "ቅትርት፣ እርፍ፣ ማነቂያ፣ ወገል" እነዚህ ቋሶች በየተረኛው ጥቅል መጠሪያ ይከተታሉ?
ሀ/ የሽመና መሳሪያዎች ለ/ የጦር መሳሪያዎች
ሐ/ የህንፃ መሳሪያዎች መ/ የእርሻ መሳሪያዎች

70. ከሚከተሉት ውስጥ ሰዋሰዋዊ ስህተት የሌለበት ዐ/ነገር የቱ ነው?
ሀ/ የአባቴ ፍቅር የሌላቸው ትውልድ ነው። ለ/ አባቴ የተከላት የማንጎ ችግኝ ትልቅ ዋርካ አክሏል።
ሐ/ ጎበዙን ተማሪውን ጠሩት። መ/ ሟች የበላሽውን ቁርስ የሰራሁት በጥድፊያ ነበር።

71. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ቃለ-ጉባኤ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ/ ቃለ-ጉባኤ በታሪክ መረጃነት ያገለግላል።
ለ/ ቃለ-ጉባኤ አከራካሪ ሀሳቦችንና የመፍትሄ ሀሳቦችን ይይዛል።
ሐ/ ቃለ-ጉባኤ የተጨመቀ፣ የተመጠነና በቅደም ተከተል የተቀናበረ ነው።
መ/ ቃለ-ጉባኤ በቃል ሊቀርብ ይችላል።

72. ማን ይናገር የነበረ _____። ይህን ምሳሌያዊ ንግግር የሚያሟላው የቱ ነው?
ሀ/ ማን ያርዳ የቀበረ ለ/ ማን ይብላ የተራበ
ሐ/ ማን ያስተምር ያነበበ መ/ ማን ያልቅስ ያዘነ

73. ከሚከተሉት አንዱ ተራ ዐ.ነገር ነው?
ሀ/ ስለደከመኝ እረፍት አደረኩ። ለ/ ስለማፍር ሰው ቀና ብየ አላይም።
ሐ/ አይነ ሙሉ ሰው ደስ ይለኛል። መ/ የቤቱ ባለቤት በሩን ከፍታ ገባች።

74. "ሄደ" ብሎ "ሂደት" ቢል የቃል ክፍሉ ከ _____ ወደ _____ የተቀየረ ነው?
ሀ/ ከቅፅል ወደ ስም ለ/ ከግስ ወደ ቅፅል ሐ/ ከግስ ወደ ስም መ/ ከስም ወደ ግስ

75.

ዘሪሁን አስፋው
የሥነ-ፅሁፍ መሰረታውያን
ሥነ-ፁሁፍ
02 04

ይህ ናሙና የማውጫ ካርድ በ _____ የተዘጋጀ ነው?
ሀ/ በደራሲ ስም ለ/ በመፅሐፍ ርዕስ ሐ/ በዕውቀት ዘርፍ መ/ በይዘት

76. "አበራ ለጊዜው የሚኖርበት ሰፈር በየበአላቱ ቀን የበግ ገበያ ሆኖ ይውላል።የሚኖረው በመስፍን ሀረር መንገድ ከሸላው በላይ ነው።" ይህ አገላለፅ ከልብ-ወለድ አላባውያን የትኛውን ያመለክታል?
ሀ/ መቼትን ለ/ ጭብጥን ሐ/ ግጭትን መ/ ትልምን

77. ባለሪውና በሰራተኛው መካከል ስምምነት ከጠፋ ቆይታል፤ስለዚህ ሁለቱም _____ ሆነዋል። ክፍት ቦታውን የሚያሟላው ፈሊጥ የቱ ነው?
ሀ/ ሰምና ወርቅ ለ/ ብትርና ጀንፎ ሐ/ ሆድና ጀርባ መ/ ሰምና ፈትል

78. አንድ የሳንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተማሪ ያገኘውን አዲስ የማስተማሪያ ዘዴ ለሥነ-ትምህርት ክፍል ይፋ ሊያደርግ የሚችልበት የዘገባ አይነት የቱ ነው?
ሀ/ ሂደታዊ ለ/ የምርምር ሐ/ የንባብ መ/ የጉዞ

79. በልብ ወለድ ውስጥ ወደ ፊት ስለሚከሰት ነገር ፍንጭ የሚሰጥ የልብ ወለድ አቀራረብ ዘዴ _____ ይባላል?
ሀ/ ንግር ለ/ ምልልስ ሐ/ ምልሰት መ/ ገለፃ

80. ከሚከተሉት አንዱ የግል አስተያየት ነው?
ሀ/ ቋንቋ በመልመድ እንጅ በመወለድ አይገኝም።
ለ/ በአፍሪካ ቀንድ ከሚገኙ ነገሮች ኬንያ አንዷ ናት።
ሐ/ኤድስ እስከ አሁን ድረስ ፈዋሽ መድሀኒት ያልተገኘለት በሽታ ነው።
መ/ የእንግሊዝን ፕሪሚየር ሊግ የእግር ኳስ ጨዋታ መመልከት የስራ ፈትነት ምልክት ነው።

መመሪያ III ከተራ ቁጥር 81 — 90 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተሰውን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ናቸው። ለያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ (ምረጭ)

ትዳር በሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎቶች ተርታ ባይመደብም የወደፊት የህይወት አቅጣጫን ከመምራት አንፃር ሲታይ ግን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ጥረህ ግረህ የምታገኘውን የወር ገቢ በአግባቡ ለመጠቀምና በዕቅድ ለመምራት ትዳር ወሳኝነት አለው። ልጅ ወልዶ ለመሳምና አሳድጎ ለቁም ነገር ለማብቃት፣ ከህሳብ ነፃ ለመሆንና ደስተኝነትን ለማትረፍ ቤት ንብረት ለማፍራት ከዝሙት ለመራቅና በዚህ ሳቢያ ከሚተላለፉ የጤና ጠንቆች ለመዳን መድሃኒቱ ትዳር መስርተው አንድ ለአንድ ፀንተው መገኘት ብቻ ነው።

ወንደላጤነት የብቸኝነት እስር ቤት እንጅ ኑሮ አይባልም። ሁልጊዜ ብስጩ ያደርጋል። ገንዘብን አላግባብ ከማባከንና ያለ ዕቅድ ከመምራት በተጨማሪ በህይወት ላይ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ቀላል አይደለም። ወንደላጤ ከህሳብ ነፃ ለመሆን የሚወስደው አማራጭ መጠጥ ነው። ከጠጡም መስከርና ሳያስቡትም በዝሙት መልክስክስ ይከተል ይሆናል። ከኢኮኖሚያዊ ክስረት እስከ ሞት ለሚያደርሱ ነገሮች ለመጋለጥ፡ዕድሉ ሰፊ ነው ወንደላጤ። ባለትዳር ግን ከነዚህ ሁሉ ነገሮች የሚርቅበት አማራጭ አለው።

አንዳንድ የዋሆች ትዳር መመስረት ማለት በገዛ እጅ እስር ቤት እንደመግባት ነው ይላሉ። ይህ ቁንፅል አስተያየት ነው። ለዚህ ሀሳባቸው ሊያቀርቡት የሚችሉትን ማሳመኛ ነጥብ የለም በመሰረቱ ትዳር መመስረትና ቤተሰብን ማፍራት ትልቅ ሀላፊነትን የመሸከም ምልክት ነው። አንድን ማህበረሰብ የመምራት ያህል የሚቆጠር እንጅ እስር ቤት ውስጥ እንዳለን አይነት የሚያዋርድ አይደለም። የህይወትን ምንነት ካጣጣሙና ትልልቅ ሀላፊነቶችንም ከተቀበሉ ሰዎች ጎራም የሚያሰልፍ ነው።

ምንጭ፡- (የሻው ተሰማ፣ **ልሳን ብዕር** ገፅ 278)

81. በፀሐፊው እምነት
ሀ/ ትዳር ለሰው ልጅ ጠቃሚ ነው።
ለ/ ወንደላጤነት ከባለትዳርነት የተሻለ ነው።
ሐ/ ትዳር እስር ቤት ነው።
መ/ ትዳር በህይወት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።
82. ሁልጊዜ ብስጩ ያደርጋል የተባለው ምንድን ነው?
ሀ/ ትዳር ለ/ ወንደ ላጤነት ሐ/አንድ ላንድ ፀንቶ መኖር መ/ ሁሉም
83. በአንቀፅ ሶስት ላይ "ቁንፅል" የሚለው ቃል አገባባዊ ትርጉም _____ ነው?
ሀ/ ጠቃሚ ለ/ አደናጋሪ ሐ/ ጎደሎ መ/ ሙሉ
84. ምንባቡ በየትኛው የድርሰት አፃፃፍ ስልት የቀረበ ነው?
ሀ/ ገላጭ ለ/ አመዛዛኝ ሐ/ ስዕላዊ መ/ ተራኪ
85. ሁለተኛው አንቀፅ ስለ ምን ያትታል?
ሀ/ ስለ ትዳር አስፈላጊነት ለ/ የወደፊት የህይወት አቅጣጫን ስለመምራት
ሐ/ ስለወንደላጤነት አስፈላጊነት መ/ ስለወንደላጤነት አስከፊነት
86. ከሚከተሉት ውስጥ በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነው የቱ ነው?
ሀ/ ትዳር በሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎቶች ተርታ ይመደባል።
ለ/ ትዳር የወደፊት የህይወት አቅጫጫን ይመራል።
ሐ/ ትዳር በገዛ እጅ እስር ቤት እንደመግባት ይቆጠራል።
መ/ ከጤና ጠንቆች ለመዳን ትዳር ያለው ፋይዳ ያን ያህል ነው።
87. ለዚህ ምንባብ ርዕስ መሆን የሚችለው የቱ ነው?
ሀ/ ትዳርና ጣጣው ለ/ የላጤ ህይወት
ሐ/ የትዳር አስፈላጊነት መ/ ትዳር እና እስር ቤት
88. ላጤዎች ከሃሳብ ነፃ ለመሆን የሚወስዱት የመጀመሪያ አማራጭ _____ ነው?
ሀ/ መጠጥ መጠጣት ለ/ ሲጋራ ማጨስ
ሐ/ ጫት መቃም መ/ ሁሉም መልስ ናቸው
89. ትልቅ ሀላፊነትን የመሸከም ምልክት ምንድን ነው?
ሀ/ ማህበረሰብን መምራት ለ/ ትዳር መመስረት
ሐ/ ቤተሰብ ማፍራት መ/ ለ ና ሐ መልስ ናቸው
90. ትዳር መመስረትን እንደ እስር ቤት የሚቆጥሩት እነማን ናቸው?
ሀ/ ሁሉም ባለትዳሮች ለ/ አንዳንድ ብልህ ሰዎች
ሐ/ አንዳንድ የዋህ ሰዎች መ/ ሁሉም ወንደላጤዎች

የተፈቀደ ጊዜ- 90 ደቂቃ

<u>መመሪያ አንድ፡-</u> ከተራ ቁጥር 1-10 ያሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ <u>እውነት</u> ፣ስህተት ከሆኑ <u>ሀሰት</u> በማለት በመልስ መስጫው ላይ አመልክቱ፡፡

1. አንድን ተውኔት በመድረክ ላይ የሚያቀርቡ ሰዎች ተደራሲያን ይባላሉ፡፡
2. በተውኔት ውስጥ የምናገኛቸው ባለታሪኮች ገጸባህርያት በመባል ይታወቃሉ፡፡
3. በስራ ደብዳቤ ላይ የሚፃፈው ቀን ደብዳቤው ለሚመለከተው አካል የደረሰበትን ቀን ያመለክታል፡፡
4. ‘ጭውውት የችግር መፍቻ የሚሆን ሀሳብ የሚገኝበት የሀሳብ ልውውጥ በመሆኑ ቀልዶችን ማከል ተገቢ አይደለም፡፡
5. በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ጠባቂ ድምፃች በአብዛኛው የሚገኙት በቃል መጨረሻ ላይ ነው፡፡
6. “ወደ” የሚለው ቃል የቃል ክፍለ መስተዋድድ ሲሆን “ገና” የሚለው ቃል ክፍል ደግሞ ተውሳከ ግስ ነው፡፡
7. ተራ አረፍተ ነገሮች አጫጭር አረፍተ ነገሮች ሲሆኑ ፣ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ደግሞ ረጃጅም አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡
8. ንግግር ሲደረግ የአድማጮችን ሁኔታ መከታታል ተገቢ ነው ፡፡
9. ምርጥ ንግግር ለማድረግ ከይዘቱ ይልቅ ቅርጽ ላይ ማተኮር ይገባል፡፡
10. ቅኔ በጽሁፍ ብቻ ሳይሆን በቃልም ሊቀርብ ይችላል፡፡

<u>መመሪያ ሁለት፡-</u> ከተራ ቁጥር 11 -15 ላሉት ጥያቄዎች “ሀ” ክፍል ስር ለተዘርዘሩ፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፣ከ”ለ” ክፍል ስር ከተዘረዘሩት በትርጉም የሚስማማቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

<u>ሀ</u>	<u>ለ</u>
11.ሲሮጡ የታጠቁት ፣ሲሮጡ ይፈታል፡፡	ሀ/አስነዋሪ ባህርያትን ይገልጻል
12. ሰርቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ ፡፡	ለ/የመጠንቀቅ አስፈላጊነትን ይመክራል
13. አንድ አይነድ አንድ አይፈርድ	ሐ/ ጀግንነትን ያመለክታል
14.ከአሀያ የዋለች ጊደር ---ተምራ መጣች፡፡	መ/ የችኮላን ጎጂነት ያመለክታል፣
15.ከአንበሳ መንጋጋ ማን ያወጣል ስጋ	ሠ/ የመተባበርን አስፈላጊነት ያስተምራል፡

መመሪያ ሦስት፡- ከጥያቄ 16-25 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ አመልክቱ፡፡

ምንባብ

ሂለን ኪለር በተወለደች በአስራ ሦስት ወሯ ማየትም፣ መስማትም ተስኗታል፡፡ እስከዚያ ድርስ ጤናማ የነበረችው ሂለን ኪለር ከአስራ ሦስት ወሯ ጀምሮ በድጋፍ ህይወቷን መምራት ጀመረች፡፡ ቤተሰቦቿ አጋዥ መምህር ቀጥረውላት ቀሪ ሕይወቷን አሳልፋለች፡፡

የመጀመሪያዋ መምህሯ አኒ ሱሊቫን ለሃምሳ ዓመታት መርታታለች፡፡ ሂለን እየተመራች በዳሰሳ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን ጨርሳለች፡፡ አስራ ሦስት መጻህፍትም አዘጋጅታለች፡፡ ዓለምን ዞራ ከታላልቅ ሰዎችና መሪዎች ጋር ተገናኝታለች፡፡ "ጥበብን ስጡን፣አሰልጥኑን እንጂ አትለምኑብን ፡፡ እንደማንኛውም ሰው እኛም አእምሮአችን ባለው ችሎታ ራሳችንንና አገራችንን ማገልገል እንችላለን ፡፡ስኬታማም መሆን እንችላለን፡፡" ብላለች፡፡

ይህንን ዓላማ ለአለም ለማስተላለፍ ወደ ተለያዩ ሀገሮች ሄዳለች ፡፡በዳሰሳ ፣በዓይነ ህሊናዊ ያየችውን ዓለም ቀይራ በሰማንያ ስምንት ዓመቷ ከማለፏ በፊት ለሁለተኛ ጊዜ የተረከቧት ፖሊ የተባሉት ረዳቷ ደግሞ ለሰላሳ ስምንት ዓመት አብረዋት ቆይተዋል፡፡

አንዴ ለተመሳሳይ ስራ ወደ ሌላ ቦታ ሄዳ ስትመለስ ቤቷ ተቃጥሎ አገኘችው ፡፡ዓለም መልካም ነገሮችን የምትመለከትባቸው ዓይኖች አሏትና የሂለን ኪለርን ቤት እጅግ ባማረ ሁኔታ ከብዙ ሀገሮች በመጣ ጥበብ ተሰራላት ፡፡

ሂለን ኪለር በወጣትነት ጊዜዋ ይጠበቅባት የነበረውን ልምምድ የምታከናውነው ሳትሰለች ነበር፡፡ ሂለን እንደሷ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን ለመርዳት ታላቅ ሀሳብ ነበራት፡፡ ሂለን በታላቅ ጥረትና በማይሰለች ትግል ከምትገኝበት የጨለማና የብቸኝነት ዓለም ለወጡት ጥረት አድርጋለች፡፡ከሰዎችና ከመጻህፍት እንዲሁም ጠቃሚ ከሆኑ የእለት ተእለት ተግባሮች ጋር በጥብቅ ተሳስራ ነበር፡፡ ዓላማዋም ትልቅ ቦታ እንደሚያደርሳት ይሰማት ነበር ፡፡

ሂለን ለእድሜ እኩዮቿ ከሚደረገው የተለየ እንክብካቤ እንዲደረግላት አትፈልግም፡፡ መምህሯ የምታበርታታት ደስ አሰኝታለሁ ፣ሞራሷን ልገነባ እችላለሁ ብላ በማሰብ አልነበረም፡፡ ተገቢውን ሙገሳ የምትቸራት በሰራዋ ነበዝ ስለነበረች ነው፡፡ ባለታሪኳ የዓለም ስምንትተኛዋ ድነቅ ፍጡር ተብላ ዓለምን ቀይረው ካለፉ ሰዎች አንዷ ድንቅ ሰው ለመሆን በቅታለች፡፡

ማንም ሰው አእምሮ እስከለው ድርስ ደህ አይደለም፡፡ እንደ እሷ አባባል ዓለም ሁለት ዓይነት ሰዎች አሏት፡፡ ችግር የሚያሸንፋቸውና ችግር የማያሸንፋቸው ትለናለት፡፡ የሂለን ኪሰር መልእክትም ዓለም ችግርን በሚያሸንፉ ሰዎች ትቀየራለች ነው፡፡

ከዶ/ር ወሮታው በዛብህ፣ <u>በኢንተርኘሪነርሺኘ መበልፀግ፣</u> 2003 ዓ.ም ፣ገጽ 91-93 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ

16. የሄለን ኪለር የትምህርት ደረጃ እስከ ምን ድረስ ነበር ?
ሀ. ማንበብና መጻፍ ብቻ ለ. 1ኛ ደረጃመጨረስ ብቻ
ሐ. 2ኛደረጃ ማጠናቀቅ ብቻ መ. ዩኒቨርሲቲ ጨርሳለች
17. የሄለን ኪለር ዋና ዓላማ ምን ነበር ?
ሀ. አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሰው አእምሮአቸው ባለው ችሎታ ራሳቸውንና ሀገራቸውን ማገልገል እንዳሚችሉ ማሳየት ነው።።
ለ. አካል ጉዳተኞች ከተማሩና ከሰለጠኑ መሰራት የሚችሉ መሆናቸውን ማሳየት ነው።።
ሐ. አካል ጉዳተኞች ከተማሩና ከሰለጠኑ ስኬታማ መሆን እንደሚችሉ ለአለም ማሳየት ነው።።
መ. ሁሉም መልስ ናቸው።።
18. ሄለን ኪለር ትምህርቷን ትክታተል የነበረው እንዴት ነበር ?
ሀ. በማዳመጥ ለ.በማንበብ ሐ. በማስላት መ. በመሞከር
19. ሄለን ኪለርን ውጤታማ እንድትሆን ያስችላት ምን ነበር ?
ሀ. ከሰዎች ጋር አብራ መስራቷ ለ. መጻህፍትን በመውደዷ /በማፍቀሯ
ሐ. የእለት ተዕለት ተግባራቷን በሚገባ መወጣቷ መ. ሁሉም መልስ ናቸው።።
20. በሄለን ኪለር እምነት አለምን ሊቀይሩ የሚችሉ ሰዎች እንዴት ያሉ ናቸው?
ሀ. አካል ጉዳተኞች ለ. ለችግር የማይበገሩ ሰዎች
ሐ. የሀገር መሪዎች መ. በጉልበታቸው አዳሪዎች
21. ሄለን ኪለር በአለም ላይ ካሉ ድንቅ ፍጡር ሰዎች በስንተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች ?

ሀ. 1ኛ ለ. 3ኛ ሐ. 8ኛ መ. 50ኛ

22. ሄለን ኪለር ከታላላቅ ሰዎችና መሪዎች ጋር ስትገናኝ" ጥበብን ስጡን"ማለቷ ምን ለማለት ነው?
ሀ. አስተምሩን ፣አሰልጥኑን ማለቷ ነው ።። ለ. በኑራአችን ደጉሙን ማለቷ ነው።።,
ሐ. የፈጠራ ባለቤት አድርጉን ማለቷ ነው።። መ. እውቅና ስጡን ማለቷ ነው።።
23. በሄለን ኪለር እምነት አካል ጉዳተኝነት ምንድ ነው ?
ሀ. ተረጂነት ነው ለ. ከሰው ማነስ ነው ሐ. ከስኬታማነት አያግድም
መ. ከሰው በላይ ያደርጋል።።
24. ሄለን ኪለር በዚህች ምድር ላይ ለመቆየት የቻለችው ለምን ያህል ዓመታት ነበር?
ሀ. 13 ወር ለ. 38 ዓመት ሐ. 50 ዓመት መ. 88 ዓመት
25. ለምንባቡ ተስማሚ የሆነው ርዕስ የቱ ነው ?
ሀ. አሳዛኟ እመቤት ለ. የጽናት አብነት
ሐ. አካል ጉዳተኛነት መ. መልካም አይናማነት

መመሪያ አራት፡- ከተራ ቁጥር 26-30 ላሉት ጥያቄዎች በ"ሀ" ክፍል ስ- ር ለተዘረዘሩት የሀረግ ዓይነቶች፣ ክፍል ሰር ከተዘረዘሩት የሚስማማቸውን በመምረጥ አዛምዱ ።

ሀ	ለ
26. ሰማዊ ሀረግ	ሀ/ ከወንድሙ ጋር
27. ቅጽላዊ ሀረግ	ለ/ ቁመቱ ምንኛ
28. መስተዋድዳዊ ሀረግ	ሐ/ የገብስ ጠላ
29. ተውሳክ ግሳዊ ሀረግ	መ/ በመኪና አደጋ ሞተ
30. ግሳዊ ሀረግ	ሠ/ እንደ አህቱ የዋህ

መመሪያ አምስት ፡- ከተራ ቁጥር 31-55 ላሉት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመምርጥ አመልክቱ፡፡

31. በመድረክ ላይ የሚቀርብ የገሀድ ዓለም ነፀብራቅ የሆነ የፈጠራ ስራ --------- ነው፡፡
ሀ. ልቦለድ ለ. ተውኔት ሐ. ተረት መ. ሁሉም

32. በተውኔት ውስጥ የድርጊቶችን ምክንያትና ውጤት የሚያሳይ የተውኔት አላባ ------ ነው፡፡
ሀ. ታሪክ ለ. መቼት ሐ. ትልም መ. ግጭት

33. "ቀኑ ቅዳሜ ፣ ሰዓቱ ረፋድ ላይ ነው፡፡ የክረምቱ ዝናብ ያዝ ለቀቅ እያደረገ የደብረ ብርሀን ከተማ ነዋሪን ግራ ቢያጋባም ወቅቱ የአመት በዓል ዋዜማ በመሆኑ ወደ ገቢያ ለመሄድ --- "ይህ አጭር ጽሀፍ ከተውኔት አላባውያን የቱን ያመለክታል?
ሀ. ታሪክን ለ. ትልምን ሐ. ግጭትን መ. ጭብጥን

34. "በናትህ" በሚለው ቃል ውስጥ ጥገኛ ምዕላዱ ---- ነው
ሀ. በ- ለ. እናት ሐ. -ህ መ. ሀ እና ሐ

35. "ለሰው ሞት አነሰው"አለች ቀበሮ፡፡የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የተገለጸበት የዘይቤ ዓይነት-ነው፡፡
ሀ. ተለዋጭ ዘይቤ ለ. ሰውኛ ዘይቤ ሐ. ምፀት ዘይቤ መ. አያዎ ዘይቤ

36. "ይህን ሳደርግ አይቶኝ ቢሆን ኖሮ እንደ መብረቅ ይጮህብኝ ነበር" የሚለው አነጋገር የተገለጸበት የዘይቤ አይነት ------ ነው፡፡
ሀ. አነፃፃሪ ዘይቤ ለ. ተለዋጭ ዘይቤ ሐ. ሰውኛ ዘይቤ መ.ተምሳሌት ዘይቤ

37. "ሀሳቤን በውስጤ ደብቄ ከርሜአለሁ " በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤቱ --- ነው ፡፡
ሀ. ሀሳቤን ለ.በውስጤ ሐ. ከርሜአለሁ መ. እኔ

38."አያ ቦጋለ መብራቱ መልከ መልካም ነው፤ ------ ምንም ሀብት የለውም"ክፍት ቦታውን የሚያሟላው ------- ነው፡፡
ሀ. ወይም ለ. እና ሐ. ነገር ግን መ.በመሆኑም

39."እመት ውድነሽ መስተዋቱን ትኩር ብለው ተመለከቱት ፡፡"በዚህ ከረፍት ነገር ውስጥ ተሳቢውን አመልካቹ ቃል የቱ ነው?
ሀ. አመት ውድነሽ ለ.መስተዋቱን ሐ. ትኩር ብለው መ. ተመለከቱት

40. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ጠብቆና ላልቶ ሲነባብ የተለያየ ፍች የማይሰጠው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ረጋ ለ. ቀና ሐ. ከዳኝ መ. ደባ

41.ልጁ ከት/ቤት ሲመለስ ክፈኛ ወደቀ፡፡ ከስሩ የተሰመረበት ቃል ከየትኛው የቃል ክፍል ይመደባል?

ሀ. ስም ለ. ቅጽል ሐ. ተወሳክ ግስ መ. ግስ

42.ንግግርን አዳምጦ ማስታወሻ ለመያዝ ማድረግ ያለብን ---- ነው፡፡

ሀ. ሀሳብን ማሰባሰብ ለ. የተነገረውን ሁሉ መጻፍ

ሐ. የተባለውን አጋኖ ወይም እንኳሶ መጻፍ መ. መልስ የለም

43.ከሚከተሉት ውስጥ በሁለት ቡድኖች መካከል፣ዳኞች ባሉበት የሚከናወን ተግባር የትኛው ነው?

ሀ. ጭውውት ለ. ክርክር ሐ. ምልልስ መ.ንግግር

44.ውስብስብ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አበበ ምሳውን በላ፡፡ ለ. አልማዝ ጫማና ቦርሳ ገዛች፡፡

ሐ. አበበ እየበላ ያወራል፡፡ መ. ኃይሉ ዓለሙን በዱላ መታው፡፡

45.“ፊሪዎች ከመሞታቸው በፊት ብዙ ጊዜ ይሞታሉ ፡፡”በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሀረጉ የቱ ነው?

ሀ. ፊሪዎች ለ. ከመሞታቸው በፊት

ሐ. ፊሪዎች ከመምታቸው በፊት መ. ብዙ ጊዜ ይሞታሉ፡፡

46.ስነ ቃሎችን ማስባሰብ ምን ጥቅም ያስገኛል?

ሀ. ሀሳብን በማጠናከር ለጭውውት ይጠቅማል፡፡

ለ. የማህበረሰብን ባህላዊ ጉዳዩች ለመረዳት ይጠቅማል፡፡

ሐ. የህብረተሰብን ባህል፣ ወግና ስርዓት ለማጥናት አመች ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

47.ከንግግር አዛጋጀት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. የንግግር ርዕስ መምረጥና መወሰን ለ. አድማጮችን በሚያረካ መንገድ ማቅረብ

ሐ. መረጃ ማሰባሰብና አስተዋጽኦ መንደፍ መ. ልምምድ ማድረግ

48.ባለንብረትነትን አመልካች ምዕላድ የተጨመረበት ቃል የቱ ነው?

ሀ. መጽሐፋችሁ ለ. ብልህነት ሐ. ገበሬዎች መ. ሄዳችሁ

49.“ዘሪሁን ከገበያ አዲስ ሱሪ ገዛ ፡፡ የዚህ አረፍተ ነገር ተሳቢ የቱ ነው?

ሀ. ገበያ ለ. ዘሪሁን ሐ. ሱሪ መ. አዲስ

50.”በትምህርት ቤቱ ውስጥ የተሸለመው ተማሪ በጣም ደስታ ተሰማው ፡፡”የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት የቱ ነው ፡፡

ሀ.ትምህርት ቤት ለ. የተሸለመው ሐ. ደስታ መ. ተማሪ

51.አስቴር ልብሷን በሳሙና አጠበች፡፡ ከስሩ የተሰመረበት ቃል -- ነው፡፡

ሀ. ባለቤት ለ. ተሳቢ ሐ. ዘርፍ መ. ማሰሪያ አንቀጽ

52. በአረፍተ ነገር ውስጥ በማሰሪያ አንቀጽነት የሚያገለግል ቃል ------ ይባላል ::
ሀ. ስም ለ. ቅጽል ሐ.ግስ መ. ተውሳክ ግስ
53. ተዘማጅነት ያላቸውን አረፍተ ነገሮች ለማያያዝ የሚያገለግል የስርዓት ነጥብ አይነት የቱ ነው?
ሀ. ነጠላ ሰርዝ ለ. ድርብ ሰርዝ ሐ. ትዕምርት ጥቅስ መ.አራት ነጥብ
54. በጽሁፍ ውስጥ የገባ የሌላ ሰው ሀሳብን ለመለየት ያገለግላል::
ሀ. ቅንፍ ለ.ትዕምርተ ጥቅስ ሐ. ነጠላ ሰረዝ መ.ድርብ ሰረዝ
55. ስለ ቅኔ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው ?
ሀ. ቅኔ በግጥም ብቻ ይቀርባል:: ለ. የቅኔ መልእክት መሸፈኛ ሰም ይባላል::
ሐ. በቅኔ ውስጥ መንታ ፍች የያዘው ቃል ወይም ሀረግ ሀብረ-ቃል ይባላል::
መ. ቅኔ በቃል ወይም በፅሁፍ ሊቀርብ ይችላል::
<u>መመሪያ ስድስት</u> ፡- ከተራ ቁጥር 56-60 ላሉት ቅኔዎች ከተሰጡት አመራጮች መካከል የቅኔውን ምስጢራዊ ትርጉም /ወርቁን /የሚያሳየውን በመምረጥ አመልክቱ ::
56. ጌታዬ ያንተን ቤት መላው ሲዘርፈው ፣
እኔም ላም አመጣሁ ወርሬ እንደሰው ::
ሀ. እኔም ላም ዘርፌ አመጣሁ :: ለ. እኔም ለማማት ፣ለወሬ መጣሁ::
ሐ. እኔም በአንተ ቤት ዝርፊያ ተሳትፌአለሁ :: መ. ቤትህን ብዙ ሰው ዘረፈው
57. ነጋዴ ነህ አሉ እኔስ አልነግድም፣
ወረቱ ካለቀ ሰው አይወዳድም::
ሀ. ፍቅሩ ከቀዘቀዘ ሰው አይፈላለግም:: ለ. ገንዘቡ ካለቀ ሰው አይወዳድም::
ሐ. ነጋዴ ሳልሆን ሰዎች ነጋዴ ይሉኛል:: መ. መነገጃ ገንዘብ የለኝም::
58. እቴ የናቴ ልጅ እራሴን መታኝ፣
ካሳዬን አልተውም እበላላሁኝ ::
ሀ.የእናቴን ልጅ ለእኔ አላዘነችልኝም:: ለ. ካሳ መቀበሌን አልተውም::
ሐ.የእናቴን ልጅ ከስሼ አስቀጣለሁ :: መ. ካሳዬ ከተባለው ፍቅርኛዬ አልነጠልም::
59. ለርሻ ሄጄ ነበር ካባት ከናቴ አገር፣
ተመልሼ መጣሁ አጥቼ አንድም ዘር::
ሀ.ዘመዶቼ በሙሉ ሞተዋል:: ለ. የተመረጠ ዘር አላገኘሁም::
ሐ. ዘር ስለሌለኝ እርሻ ተውኩ:: መ.ለዘር የሚሆን እህል አጣሁ::
60. ሁለጊዜ በስጋት በዱር ከመኖር፣
ቆቅስ ብትመረቅ ይሻላት ነበር::
ሀ. ቆቅ በዱር መኖር አልተመቻትም :: ለ. ቆቅ ታርዳ ብትበላ ጥሩ ነበር::
ሐ. ቆቅ ስጉ የዱር እንሰሳ ነች:: መ. ቆቅ ለማዳ ብትሆን ጥሩ ነበር ::